# ብርቅርቅታ

ከዳንኤላ ስቲል

ትርጉም በዓቢይ ደምሴ

© መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
All Rights Reserved

የመጀመሪያ ዕትም - 1983
ሶስተኛ ዕትም - 1999

ዋና አከፋፋይ

ዓይናለም መጻህፍት መደብር
አድራሻ:- ከብሔራዊ ቴአትር ጀርባ
ስልክ 011 550 58 44/45
ሞባይል 091 162 49 10

የኮምፒውተር ለቀማና ገፅ ቅንብር
ትዕግስት ንብረቱ
ስልክ 091-113 02 90



<u>መታሰቢያነቱ</u>

ለራሔል ዓቢይ
እና
ለታናናሽ እህቶቿ
- ለኤልሳቤጥ
- ለቤተልሔም
- ለኢየሩሳሌም ይሁንልኝ

## መግቢያ

እንደሚታወቀው ተርጓሚ እጅግ ብዙ ከሆኑ የፈጠራ ሥራዎች መካከል አማርጦ ጥሩ የመሰለውን ለአንባቢ የማስተዋወቅ ዕድል አለው:: የተርጓሚ ጭንቀቱ የትኛውን ሥራ ልምረጥ ብሎ ከመዋተቱ እንጂ፣ ከተለያዩ ከያኒያን አእምሮ የፈለቁትን ስራዎች ወደ ፈለገው ቋንቋ ለመመለስ ችሎታው እስከፈቀደለት ድረስ ምርጫው ወሰን የለውም::

ስለዚህም ነው እኔም ቀደም ሲል 'ጃኩሊን' ና 'ሳልሳዊቷ ልጃገረድ' የተባሉትን የእግሊዛዊቷን የአጋታ ክሪስቲን ልቦለዶች እንደተረጐምሁኝ ሁሉ ወደ ሩቅ ምስራቅ ተሻግሬ የዘለዓለማዊውን ቻይናዊ ደራሲ የሉህ ሱንን 'ትዝታን በፀፀት' ወደ አማርኛ ለመመለስ የሞከርኩት::

ይህ የአሁኑ አራተኛ የትርጉም ሥራዬ ደግሞ ወደ አውሮፖና አሜሪካ አህጉሮች የሚወስደን ነው:: ዕውቋ ደራሲ ዳኒኤላ ስቲል 'ከላይደስኮፕ' በሚል ርዕስ የፃፈችውን ልቦለድ 'ብርቅርቅታ' የሚል ስያሜ በመስጠት ወደ አማርኛ ተርጉሜዋለሁ:: አተረጓጐሜም ቃል በቃል ሳይሆን የተዛምዶ ትርጉም ነው:: እንዲህም ያደረግሁት ያለምክንያት አይደለም::

የዚህ የፈጠራ ሥራ ዋነኛ ጭብጥና ሥነ ፅሑፋዊ ለዛ እንደተጠበቀ እንዲሆን አስፈላጊውን ጥረት ሳደርግ፤ በሌላ በኩል ግን ፅሑፉ ከሚተረጐምለት ሕብረተሰብ ባህል፣ ወግና ሥነልቦናዊ ግንዛቤ ጋር ፍፁም የማይጣጣሙ ወይም እንግዳ ይሆናሉ የምላቸውን አንዳንድ አመለካከቶች አስወግጃለሁ:: በተረፈ ግን ደራሲዋ የጠቀመቻቸው ታሪካዊ፣ ጂኦግራፊያዊም ሆነ ሌሎችም ተጨባጭ ገፅታዎች ፈር እንዳይለቁ በቂ ጥንቃቄ አድርጌአለሁ:: ስለሆነም፤ አንዳንድ ገለፃዎችና ምልልሶች የፅሑፉን ይዘት እንዳያጉድፉና ለፍሰቱ መጠበቅ ሲባል ቢዘለሉ ሆነ ተብሎ ለመደረጉ አንባቢያን ከወዲሁ እንዲያጤኑልኝ አሳስባለሁ:: ለማጠቃለል ይህ የትርጉም ሥራ 'አማርኛ አማርኛ' ብሎ እንዲነበብ ጥረት ከማድረግም ባሻገር እንዲያዝናናና እንዲያስተምር በጥንቃቄ የተደከመበት መሆኑን በተጨማሪ እገልፃለሁ::

ተርጓሚው



### *ሕይወት!*

ስልምልምታ ... ዝልፍልፍታ ... ጭልምልምታ ...
ፍልቅልቅታ ... ውልብልብታ ... ብርቅርቅታ ...
እውነትም ሕይወት ...

እንደማለዳ ፀሐይ - ብርሃን ስትፈነጥቅ
እንደባህር አልማዝ - ስትፍለቀለቅ
እንደሳት ላንቃ - አብረቅርቃ
ከቀትር ፀሐይ - በርታ ደምቃ
ስትጀምር ማለት - ድንግዝግዝ
መባባት አይቀር - መተከዝ

### *ሕይወት ...*

ፀፀት ትዝታን - ደርድራ
ምኞትን ከህልም አዋቅራ
በብቸኝነት - ስታማቅቅ
ቀን ከሌት አትል - ስታስጨንቅ

### *ግን ሕይወት ...*

ብርቅርቅታ ናትና ታበራለች - ቀን ጠብቃ
እንደጨለመች አትቀርም እንዳኮረፈች ተደብቃ
ውሎ ቢያድርም ታበራለች በሕብረ ቀለም አሸብርቃ፣

### *ሕይወት ..*

ድቅስቅስታ ... ዝውርውርታ ... ጥብርብርታ ...
ጥንጥን በረቅ ... ብልጭልጭታ ... ብርቅርቅታ ...

# ክፍል 1

## ሶላንጅ

«እንደማኅተም በልብህ፣
እንደማኅተም በክንድህ አኑረኝ
ፍቅር እንደ ሞት የበረታች ናትና፣
ቅንዓትም እንደ ሲኦል የጨከነች ናትና።»





## ምዕራፍ አንድ

ከሚወርደው ዶፍ ክብደት የተነሳ ቀኑ የቀን ጨለማ ሆኗል፡፡ በኔፕልስ ከተማ ዙሪያ ባሉት ተራሮች ላይም እያፏጨ የሚያልፈው ነፋስ የጆሮ ታምቡር ይበሳል፡፡ ውሽንፍሩም የዓይን ቆብ አያስገልጥም፡፡ ምክር የለበሰውን የዝናብ ካፖርት ክሳድ ከጆሮው በላይ ድረስ ጎትቶ ብርድ ያቆረፈዳቸው እጆቹን ወደ ጠመንጃው ቃታ መለሰ፡፡ ያቺም የቆምባት የቀበሮ ጉድጓድ መለስተኛ ኩሬ ሆናለች፡፡ ሳም ምክር የሃያ አንድ ዓመት ወጣት አሜሪካዊ ሲሆን ወደ አውሮፓም ለመምጣት ምክንያት የሆነው ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ነበረ፡፡

ምክር ለመጀመሪያ ጊዜ በጦር ሜዳ ላይ የዋለው በሰሜን አፍሪካ ነው፡፡ በዚያም ለነበረው የአሜሪካ ጦር የሜዲትራንያንን ባህር አቋርጦ ከዋናው የጣልያን ግዛት ለመድረስ ዓመት ከመንፈቅ ፈጅቶበታል፡፡ ጦሩም አሁን መሽጉ የነበረው ከኔፕልስ ከተማ በስተ ሰሜን ምስራቅ ነበር፡፡ ሳም ምክር የሰሜን አፍሪካ ትዝታ በታወሰው ቁጥር ያንገሸግሸዋል፡፡ ሐሩሩ ያሳብዳል፡፡ ሙቀቱ ዕርቃን ያስኬዳል፡፡ የበርሃው ነፋስ የሚያንገዋልለው የአሸዋ ሞገድ ግማሽ ዕውር የደርጋል፡፡ ቀኑን ሙሉ ዓይን እንደለበለበ እንዳስለቀሰ ነበር የሚውለው፡፡ የዛሬ የኔፕልስ ከተማ አካባቢ ዶፍና ውሽንፍር ግን ከዚያ የባሰ የሚሸነቁጥ ሆነበት፡፡ በምሽጉ ዙሪያ ያለማቋረጥ እያፏጨ የሚያልፈው ነፋስ ደም ስር ይጠዘጥዛል፣ አጥንት ሰርስሮ ይገባል፡፡ የምክር ከንፈሮች በድን ሆነዋል፡፡ ጣቶቹም ደንዝዘዋል፡፡ ሉስ ቢያቅበጠብጠውም ቆርጦ ያስቀመጣትን ቁራጭ ሲጋራ ከከንፈሩ ለማድረስ ክብሪት ጭሮ ለማቀጣጠል አልቻለም፡፡ ያን ጊዜም ነበረ የረገመውን ሰሜን አፍሪካን ማረኝ ወደ ማለቱ የተቃረበው፡፡

ሳም ምክር በጄኔራል ክላርክ በሚመራው ክፍለ ጦር ውስጥ የ45ኛው እግረኛ ሻለቃ ባልደረባ ነበር፡፡ ክፍለ ጦሩ የሲሲሊን ደሴት በሐምሌ ወር በድል አድራጊነት ከያዘ በኋላ ከኔፕልስ ለመድረስ አራት ወራት ፈጅቶበታል፡፡ አሁን ደግሞ ወደ ሮም ከተማ በመግፋት ላይ ነበር፡፡ ሆኖም ባላንጣው የጀርመን ጦር በቀላሉ የሚበገር ኃይል አልነበረም፡፡

ስለዚህ ለእያንዳንዷ ጋት መሬት አይከፍሉ መሥዋዕት መክፈል ነበረበት:: ለሮም የሚደረገው ጦርነት እጅግ አዝጋሚ፣ ሲበዛ የሚዘገንን ነበር:: የሁለቱም ተፋላሚዎች ደም እንደውሃ ፈሶበታል:: በኔፕልስ አካባቢ ሸለቆና ተራሮች፣ ጋራና ሸንተረሮች ላይ በአልፍ የሚቆጠሩ ወጣቶች ረግፈውበታል::

ምክር የደነዘዙ ጣቶቹን አፉ ውስጥ ከቶ ከሆዱ በሚወጣው ሞቃት አየር ነፍስ ሊዘራላቸው ሞከረ:: ከዚያም እጁን ወደ ኪሱ በመክተት ቁራጯን ሲጋራ አውጥቶ ከከንፈሩ ሰካት:: የነበረው የመጨረሻው የክብሪት እንጨት ግን ውሃ ገብቶት ቶሎ አልጫልርህ በማለቱ እስከዚያ ከከንፈሩ ላይ ያደረጋት ቁራጭ ሲጋራ በዝናቡ በስብሳ ፍርክስክስ አለች:: ያን ጊዜም በንዴት "ሺት" ብሎ የክብሪት ቤቱን ከቅል ጥሙ ድረስ ካጠለቀው ኩሬ ውስጥ ወረወረው::

ጃፓን የአሜሪካ ይዞታ የነበረችውን የፐርል ወደብ በአውሮፕላን በደበደበች ጊዜና አሜሪካም በጃፓን፣ በጀርመንና በጣሊያን ላይ ጦርነት ባወጀችበት ወቅት ምክር የዝነኛው የሐርቫርድ ዩኒቨርስቲ ተማሪ ነበር:: ምክርም የሚታየው ሁሉ እንደ ቀድሞዎቹ የሐርቫርድ ምሩቃን እርሱም ትምህርቱን ጨርሶ ወፍራም ደምወዝ የሚያስገኝ ሥራ ሲያማርጥ፣ የገጠርና የከተማ መኖሪያ ቤት ሲኖረው፣ ትዳርም መስርቶ የልጆች አባት ሲሆን ነበር:: ወላጆቹ በአስራ አምስት ዓመት እድሜው በአደጋ ስለሞቱበት በሐርቫርድ ዩኒቨርስቲ ትምህርቱን ለመከታተል ለሦስት ዓመታት ያህል በትርፍ ሰዓቱ በትያትር ቤት ውስጥ በተላላኪነት ጉርሻ እየተሰጠው ሰርቷል:: ታላቅ እህቱ የነበረችው ኢሊንም ከራሷ ተርፏት ለርሱ የምትረዳው ሴት አልነበረችም:: በወታደርነት በመመልመሉም ሲሰናበታት በሔደ ጊዜ ቡና ቤት ውስጥ ተቀጥራ ስትሰራ ነበር ያገኛት:: ኢሊን በታናሽ ወንድሟ ወደ ጦር ሜዳ መላክ ቅንጣት ያህል ሐዘኔታ አልተሰማትም:: እንደ እህት ከአንገቱ ተጠምጥማ አልቅሳ ልትሸኘው ቀርቶ በደህና ተመለስ የሚለውን የተለመደ የበጎ ምኞት መግለጫ እንኳን ነፍጋዋለች:: ሴት አዳሪዋ ኢሊን ምክርን የምትጠላበት ምክንያት ነበራት:: ምክር ከሕፃንነቱ ጀምሮ ብሩህ አእምሮ የነበረው ልጅ ነበር:: በትምህርቱ የሦስት ዓመት ታላቁ የነበረችውን ኢሊንን ቀድሟት በመሔዱ በወላጆቿ የተጠላች፣ የአካባቢውም መዘባበቻ ሆና ነበረ:: በዚያም ላይ ደግሞ ምክር መልከ መልካም ተግባቢ ልጅ ሲሆን፣ እንደ ፀጉሯ መቅላት ደመ ፍሉ የነበረችው ኢሊን ግን ቀጭንና ያለ ዕድሜዋ የበሰለች፣ ተንኮለኛና ምላሰኛ ልጅ ነበረች:: አሥራ ሦስት ዓመት እንደሞላትም ከአንድ ጎረምሳ





ጋር ኮበለለች:: ከዚያን ወዲህ ብዙ ወንዶች አቀያይራለች:: ምክርም ሊሰናበታት በሄደ ጊዜ በስድስት ዓመት ታናሿ የሚሆን የአስራ ስምንት ዓመት ጎረምሳ ቅምጥ ነበረች:: ጎረምሳው ስራ አልነበረውም:: ኢሊን ከቡና ቤት በሚከፈላት አነስተኛ ደመወዝና ሲቀናትም ከሌላ ወንድ ጋር በመውጣት በምታገኘው ገንዘብ ነበር የሚተዳደሩት:: ሆኖም ኢሊንም ሆነች ያ ጎረምሳዋ የሚያድሩት ከሞቀ ቤት ነው:: የምግብና የመጠጥ ችግር አልነበረባቸውም:: በልብስ አልታረዙም:: ምክር ግን በሐርቫርድ ዩኒቨርሲቲ የመጨረሻ ዓመት ተማሪ ነበር:: በወታደርነትም ተመልምሎ መጀመሪያ ወደ ሰሜን አፍሪካ ተላከ:: ዓመት ከመንፈቅ በሰሜን አፍሪካ በረሃ ሲዋጋ ቆየ:: ከዚያም እረፍት ሳያገኝ ወደ ሲስላ ብሎም ወደ ኔፕልስ መጣ:: አሁን ደግሞ ወደ ሮም አቅጣጫ በሚወስደው የጦር ሜዳ ላይ ይገኛል:: ታዲያ ምክር እንደልቡ የሚያጨሰው ሲጋራ እንኳን አላገኘም:: ምናልባት ዕድለኛም ከሆነ ሮም ይደርስ ይሆናል:: ሮምን መያዝ ማለት ደግሞ የጦርነት ማብቂያ ነው ማለት አልነበርም:: ስለሆነም ከሮምስ በኋላ የሚጠብቀው ምን ዕድል ነበረ?

ምክር በሐሳብ ማዕበል ውስጥ ጭልጥ ብሎ ሰጥሞአል:: ዶፉ ግን አሁንም ጠመንጃ በያዙት እጆቹ ላይ እንደወረደ ነው:: ውሸንፍሩም እንደልብ ግራና ቀኝ ሊያሳየው አልቻለም::

"እንካ ይቺን አጢሳት" ሲል አጐኑ የነበረው ሌላው ወታደር አርዘር ፖተርሰን የያዛትን ቁራጭ ሲጋራ ለምክር ሲሰጠው እጁን ዘረጋ:: ምክር በፍጥነት ተቀበለና ከከንፈሩ አድርሶ በማከታተል ሁለት ጊዜ ጢሱን ማግ ማግ ከማድረጉ እሳቱ እጣቱ ጋር ደርሶ ፈጀው:: ቁራጯን ወደ አፉ ቶሎ መልሶ ቢስብም ስስ የከንፈር ቆዳዎቹ በመቃጠላቸው እንትፍ አለና ሲጋራዋን ከውሃው ውስጥ ጥሎ ራሱን በትዝብት ነቀነቀ::

"የማያልፍ ነገር የለም ሳም፣ ያሁኑም ችግር ያልፍ ይሆናል" አለው ፓተርሰን የምክርን መተከዝ ተመልክቶ:: ፓተርሰን በወታደርነት ሲመለመል የሕግ ትምህርቱን ጨርሶ በጥብቅና ሙያ ላይ የተሰማራ የሐያ ሰባት ዓመት ጉልማሳ ነበረ:: ወላጅ አባቱም በህፃንነቱ ስለሞተ ፓተርሰን ያደገው በእናት እጅ ተሞላቆ ነበረ:: አሁን ላየው ግን ሽማግሌ ነበር የሚመስለው:: ሳም ምክር የሐርቫርድ ዮኒቨርስቲን እንዲተው በተገደደበት ወቅት አካባቢ ፓተርሰንም በኒዮርክ ከተማ ከነበረው የጥብቅና ሥራው ላይ ተመለመለ:: እንደ ሳም ምክርም አርዘር ፓተርሰን በሰሜን አፍሪካ በረሃዎች ተዋግቷል:: እንደ ምክርም በሲሲሊ ደሴት ተራሮችና

ሽለቆዎች ውስጥ በኔፕልስ ጋራና ሸንተረሮች ላይ ረጅም የሥቃይ ወራት አሳልፏል:: በድሎት ላደገው ፓተርሰን ደግሞ ይህ ሁሉ ሊቋቋመው ከሚችለው በላይ ቢሆንበትም የአጋጣሚ ጉዳይ ሆነና ሳም ወከርን የመሰለ ፅኑ ጓደኛ አጋጠመው:: ምከር እንደ ፓተርሰን ረጅም ባይሆንም መካከለኛ ቁመትና ደልዳላ ሰውነት ያለው ወጣት ነበረ:: ሳም ምከር ግን ሳቂታና ተጫዋች፣ በዕድሜው ወጣትና በተፈጥሮውም ደፋር፣ ተግባቢና ቀራጥም ነበር::

ምከር የራሽን መያዣ ሻንጣውን ከፈተና አንድ የታሸገ ቆርቆሮ አውጥቶ በሳንጃው ከከፈተ በኋላ "ውድ ጓደኛዬ ፓተርሰን! ፈቃድህ ሆኖ ይህንን የገና ስጦታ ብትቀበለኝ?" አለና ጉንበስ በማለት አበረከተለት::

"በጣም አመሰግናለሁ:: ሆኖም በውስጡ ያለው የተርኪ ስጋና መረቅ ነው ወይንስ የአደንጓሬ ሾርባ?" አለው ፓተርሰን እየተቀበለ::

"ስትቀምሰው ትለየዋለህ፣ ግን እንዳትጨርሰው" አለና ምከር ሁለቱም ጥቂት ተሳሳቁ:: ከዚያም በሰላሙ ወቅት ስላሳለፏቸው የገና በዓሎች አንሥተው ሲጫወቱ ቆዩ:: ድግሱ ከተበላ ከተጠጣ በኋላ የሚጠብቃቸው የሞቀ አልጋ በሓሳባቸው ታወሳቸው:: በተለይ ፓተርሰን በእንደዚህ ያለ ዓመት በዓል ቀን ቀርቶ በሌላውም ጊዜ ቢሆን ብቻውን መተኛት የሚወድ ሰው አልነበረም:: ለፓተርሰን ዓይነ ህሊና ሽክ ብለው ይለብሱ የነበሩት የኒዮርክ የቢሮ ሰራተኛ ልጃገረዶች ታዩት፣ ስለነርሱም ብዙ ብዙ አወራ:: በመጨረሻም "ተወኝ እባክህ ጠግቤአለሁ አሁን ነው የበላሁት" አለ::

"ቅመሰው እንጂ! ይህን የመሰለ ጣፋጭ ምግብ በጣሊያን አገር ውስጥ እናገኛለን ብዬ አልገመትኩም ነበር" እያለ ምከር በማውራት ላይ እንዳለ በአጠገባቸው የሚያልፈው ፃአለቃ ሰምቶ ኖሮ

"ስለምንድነው የምታወራው ምከር?" አለና ባለበት ቆሞ ሁለቱንም ተራ በተራ ሲያያቸው ቆየ:: ሳም ምከር ታዛዥና ደፋር ወታደር ነበረ:: የሌሎቹን ጓደኞቹን ህይወት ለማዳን ከአንድም ሁለት ጊዜ ራሱን ለአደጋ አጋልጧል:: በመሆኑም ፃአለቃው በይፋ ባያሳየውም ይወደው ነበር:: ከማፍቀሩም የተነሳ ለምከር ደህንነት አጥብቆ ያስባል:: ፓተርሰን ግን የምከር ተቃራኒ ነበረ:: ወኔ የለሽ ነው:: በዕውቀት ግን የሚስተካከለው አልነበረም:: "እና ምግቡ አልተስማማችሁም ማለት ነው?"





"ተስማምቶናል ፃአለቃዬ" አለና ምከር የቆርቆሮውን ምግብ ወደርሱ እያቀረበ "እንዲያውም እዚህ የሚሰጠን ምግብ ተወዳዳሪ አይገኝለትም:: እስቲ እርስዎም ይቅመሱት" አለው::

ፃአለቃውም እንደመናደድ ብሎ "ወደዚህ የመጣችሁት ለግብዣ ተጠርታችሁ አይደለም" አለ ምከር ያስጠጋለትን የቆርቆሮ ምግብ በእጁ እየገፋ::

ምከርም "አ! ይቅርታ... የጥሪውን መልዕክት በትክክል ባለማጤኔ ነው" አለና ሳቀ:: ፃ አለቃውም የመጣበትን ሳቅ አፍኖ በጉናቸው አለፈ:: ስለ ማዕረጉም ሆነ ስለ ቁጡነቱ እንደ ፓተርሰን ያሉት ወታደሮች ይፈሩት እንደሆነ እንጂ ምከር ግን ደፍሮ ይቃለደው ነበረ:: አለቃውም ቢሆን ይህን የምከርን ቦርቧራነት አይጠላውም:: አልፏቸው ከሔደም በኋላ አንገቱን ዘወር በማድረግ "በነገው ዕለት ልንንቀሳቀስ ነው:: ማለቴ... ይህን የጋለ ማህበራዊ ግንኙነታችሁን ለማቋረጥ ፈቃደኛ ብትሆኑ" ብሏቸው ጥሏቸው ሔደ::

ፓተርሰን ወደ ፃአለቃው እያየ ድምፁን ዝቅ በማድረግ "ምን እንደሚሻለኝ አላውቅም:: ይህ ሰውዬ ጠምዶ ነው የያዘኝ" አለ::

"አይምሰልህ ፓተርሰን፤ ሰውየው ጨዋታ ወዳድ ሰው ነው" አለ ምከር ልማደኛ እጁን ወደ ኪሱ እየሰደደ:: ምናልባት ሌላ የተረሳች ቁራጭ ሲጋራ ባገኝ ሲል ነበር:: ግን ምንም አላገኘም:: ፓተርሰን ግን ከየት እንዳገኘው አይታወቅም አንድ ሙሉ ሲጋራ አወጣና እያይዞ ለምከር ሰጠው::

"ያምላክ ያለህ! ከየት አገኘህ እባክህ?" ሲል ምከር ጠየቀው::

"ያ ዛሬ ከጣልከው ጀርመን ኪስ ውስጥ አንተ ሬሳውን አልፈህ ወደፊት ስትሮጥ እኔ ኪሱን እበረብር ነበረ:: እና ይቺን አንድ ሲጋራ ብቻ አገኘሁ" አለው ፓተርሰን::

ምከርና ፓተርሰን ሲጋራዋን እየተቀባበሉ ካጨሱ በኋላ ከጉድጓድ ወጥተው ጐን ለጐን ተኙ:: ሲነጋጋም ዝናቡ አባርቶ ስለነበረ ጦሩ መንቀሳቀስ ጀመረ:: የሚቀጥለውን ምሽት ያሳለፉት ከአንድ ከፈራረሰ ከእህል ማከማቻ አዳራሽ ውስጥ ነበር:: ከሁለት ቀናት ጉዞም በኋላ ከአፍ እስከ ገደፉ ሞልቶ ይጋሽብ ከነበረው ከቮልቱርኖ ወንዝ ደረሱ:: ያንን ወንዝ በቀላሉ ማቋረጥ አልተቻለም:: ከክፍለ ጦሩም እባላት አስራ ሁለት የሚያህሉ ሰዎች

በወንዙ እየተወሰዱ ህይወታቸውን አጥተዋል:: ፓተርሰንንም ቢሆን ለጥቂት ያዳነው ምከር ነበረ:: ከዚያም በፊት ቢሆን ፓተርሰንን ከሞት አደጋ አስጥሎታል:: ከላዩ ቆሞ በሳንጃ ሆዱን ሊዘረግፈው የነበረውን የጀርመን ወታደር ምከር በጥይት መትቶ ጥሎለታል:: ስለዚህም ፓተርሰንና ምከር እንደ ታላቅና ታናሽ ወንድም ነበረ የሚተያዩት::

የአሜሪካ ጦር በአንዳንድ አቅጣጫ ወደፊት ቢገፋም በዚያኑ መጠን አልፎ አልፎም ሽንፈት ደርሶበታል:: በኔቱኖና አንዚዎ የመሽገውን የጀርመን ጦር መሥመር ለመስበር ተደጋግሞ ተሞክሮ ባለመሳካቱ የነበረው አማራጭ በተራራማዋ በካሲኖ መንደር በኩል ማጥቃት ብቻ ሆነ:: ለዚህም ተግባር የተመረጠው እነምከር የነበሩበት ክፍለ ጦር ነበር:: ጦርነቱም ገና ከመጀመሩ ፓተርሰን ቆሰለ:: በግንባር ይዋጋ የነበረው ምከር የጓደኛውን ክጉት መለየት እንዳጤነ ወደ ኋላው ተመለሰ:: የፓተርሰን ደረት በደም ተጨመላልቆ ዓይኖቹም ተከድነው አየ:: ምከርም የሞተ መስሎት ከደረቱ ላይ ተደፍቶ የልብ ትርታውን ሲያዳምጥ ትንፋሹ እንዳለ አረጋገጠ:: ከዚያም ተሸክሞት በደጀን ወደ ነበረው የሕክምና ቡድን ካደረሰው በኋላ ወደ ጦር ግንባሩ ተመለሰ::

የካሲኖን መንደር ለመያዝ ብዙ ሳምንታት የፈጀ ውጊያ ተካሄዷል:: መንደሯም እንዳልነበረች ሆናለች:: በመጨረሻውም ቀን ፍልሚያው በመንደሯ ላይ ያላቋረጠ የመድፍ ውርጂብኝ ስለ ዘነበባት፣ ለሰዓታት ጥቅጥቅ ያለ ጨለማ አላብሷት ለዓይን ተሰውራ ነበር:: የመንደሯ እምብርት የነበረው ግዙፉ የካሲኖ ገዳም የዐመድ ክምር መሆኑ የታየውም ጭሱ እየገፈፈ ሲሄድ ነው:: ከካሲኖ ጦርነት በኋላ የጀርመኖች ቅስም ተሰበረ:: አልፎ አልፎ ከነበሩት መለስተኛ ግጭቶች በስተቀር ከእንግዲህ ወደ ሮም የሚወስደው ጐዳና ክፍት ሆነ::

በኔፕልስና በሮም መካከል በተካሄዱት ጦርነቶች እልፍ አዕላፍ ወታደሮች ከሁለቱም ወገን ተሰውተዋል:: በካሲኖ ጦርነት ላይ የሞቱት ብቻ ከሃምሳ ሺህ በላይ ነበሩ:: ፓተርሰን የቆሰለው ክክንዱ ላይ ስለነበረ እነምከር ሮም ከመግባታቸው በፊት ከጦሩ ጋር ተደባለቀ:: ሳያቋርጥ በሚዘንበው ዶፍ ውስጥ እንደ ህፃን በአንብርክኩ እየተንፏቀቀ የተዋጋው የአሜሪካ ጦር ከሰባት ወራት በኋላ ከሮም ከተማ ገባ:: በቬኒስ አደባባይ ላይ በተደረገውም ወታደራዊ ሰልፍ ምከርና ፓተርሰን ጐን ለጐን ተሰልፈው ነበረ:: የከተማውም ህዝብ በነቂስ ወጥቶ ስድል አድራጊው ጦር ያለውን የጋለ ፍቅር በጭብጨባና በዝማሬ ገለፀ:: ጦሩ የሚያልፍባቸው ጐዳናዎችም





በአበባ ተሸፍነው ነበረ:: ዘፈኑና ጭፈራው፣ ሳቅና ፈንጠዝያው በሮም ከተማ ውስጥ ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም:: ያንን የመሰለ አቀባበል ያልጠበቀው ምከር ልዩ ደስታ ተሰማው:: ከደስታውም ብዛት የተነሳ እንባው በጉንጮቹ ላይ ፈሰሰ::

በሮም ውስጥ ለሶስት ሳምንታት ያህል ቆዩ:: በተለይም ምሽቶቹ የሳቅ፣ የጫዋታ፣ የዘፈን፣ የፍቅር ምሽቶች ነበሩ:: ፓተርሰን ሮምን ከጦርነቱ በፊት ጐብኝቶ ስለነበረ፣ ምከርን እያዞረ አንድ በአንድ አሳይቶታል:: ቀን ቀን ታሪካዊ ቦታዎችን፣ ማታ ማታ በከተማው ውስጥ አሉ የሚባሉትን የምሽት ክበቦች ሲያስሱ ከረሙ:: በሰሜን አፍሪካ በረሃ እንዳልተደበደቡና ለወራት በቀበሮ ጉድጓድ ውስጥ ያልከረሙትን ያህል አሁን በሮማ ሆቴሎች ውስጥ ተምነሸነሹ:: የጦርነቱ ጠባሳ ከከተማዋ ላይ ሙሉ በሙሉ ተገፏል ለማለት ባይቻልም የሮም ኮረዳዎች የከተማዋን የምሽት ህይወት እንደ ቀድሞው ነፍስ ዘሩበት:: የምከር ወሲባዊ ፍላጐት ቁጥብ ቢሆንም ፓተርሰን ግን እንደ ኒውዮርኩ ሲዝናና ከረመ::

እንደነገ ከሮም ሊንቀሳቀሱ ሲሉ ማምሻውን የጉዟቸው አቅጣጫ ታወቀ:: ብዙዎቹም ፈርተውት እንደነበረ ሳይሆን ከፓሪስ በስተደቡብ ምስራቅ ከሰፈረው ከጄኔራል ብራድሊ ጦር ጋር እንዲደባለቁ መታዘዛቸው ተሰማ:: የፓሪስን ከተማ ከጀርመን ይዞታ ስር ነፃ ለማውጣት ዘመቻው ቀጠለ:: በነሐሴም ወር ማብቂያ ላይ ፓሪስ በቃል ኪዳን መንግስታት ጦር ኃይሎች ነፃ ወጣች:: የፓሪስ ከተማ ህዝብ ግን እንደ ሮም ከተማ ነዋሪዎች ነፃ አውጪውን የጦር ኃይል በጭፈራና በጭብጨባ አልተቀበለውም:: ከብረት በጠነከረው የጀርመኖች ክንድ ለአራት ዓመታት ያህል ሲቀጠቀጥ የቆየው የፓሪስ ነዋሪ ሕዝብ ወኔው ተኮላሽቶ ሐሞቱም ፈሶ ነበረ:: ጀርመኖችም በእርግጥ ተሸንፈው እጃቸውን በሰላም ይሰጣሉ የሚል ግምትም በነዋሪው ሕዝብ ዘንድ አልታለመም:: ፓሪስን ለመከላከል ጀርመኖች ያደረጉት ዝግጅት ከፍተኛ ነበረ:: በመሆኑም ለሕዝብም የሚታየው ከተማዋ ከዛሬ ነገ ከሰማይ በአውሮፕላን፣ ከምድር በመድፍና በአዳፍኔ ስትደበደብ፣ ውብና ታሪካዊ ሕንፃዎቿ ተደርምሰው ሰፋፊ ጐዳናዎቿ ታርሰው ፓሪስ በእሳት ስትጋይ፣ ልጆቿም የእሳት ራት ሆነው ሲቀሩ ነበረ:: ግን እንደተፈራው ሳይሆን ቀረና ፓሪስ በሰላም ተያዘች:: ሕዝቡም ውሎ ባደረ መጠን የመኖር ተስፋው እየለመለመ ሔደ::

ፓሪስ በተያዘች በአራተኛው ቀን የቃል ኪዳን መንግስታት ጦር ታላቅ ወታደራዊ ሰልፍ አሳየ:: እንደ በፊቱ ሳይሆን በዚያን ቀን የከተማው

ሕዝብ ከየቤቱ ወጣ:: የፓሪስን አውራ ጐዳናዎች አጣበባቸው:: ስልፉኛውም የሚያልፍባቸውን መንገዶች ልዩ መዓዛ ባላቸው አበባዎች ሸፈናቸው:: የሕዝቡ ሆታና ጭብጨባም የከተማዋን አየር ሰንጠቀው:: ምከር በወታደራዊ ስልፍ ላይ ሆኖ በዚያን ቀን ስሁስተኛ ጊዜ አለቀሰ:: ስዚያም ስአበቃው አምላኩ በሆዱ ምስጋና አቀረበ:: የከተሞች ንግስት የምትባለው ፓሪስ ነፃ ከወጣች ከእንግዲህ የተቀረው ጦርነት ስምከር ያን ያህልም ትርጉም የሚስጠው አልነበረም:: የታየው ነገር ቢኖር ጦርነቱ በቅርብ ቀናት ውስጥ ተፈፅሞ እርሱም ወደ አሜሪካ ሲመለስና የሐርቫርድ ዮኒቨርሲቲ ትምህርቱን ሲያጠናቅቅ፣ ከዚያም እንደርሱው የሐርቫርድ ምሩቅ የሆነችውን አንዷን ልጃገረድ አግብቶ የሞቀ ትዳር ሲመሰርት ነበረ::

ከስዓት በኋላ የዕረፍት ጊዜያቸው ስለነበረ፣ፓተርሰንና ምከር በኖትረዳም ካቴድራል የሚካሄደውን የቅዳሴ ሥነ ሥርዓት ሲከታተሉ ቆዩ:: ከዚያም በዱአርኰል ጐዳና የሚገኙትን ሱቆች እያዩ ቀስ ብለው ቁልቁል ወረዱ:: ከመንገዱም ጫፍ ላይ ከነበረች አንዲት ትንሽ መናፈሻ ቤት ጐራ ብለው ቡና አዘዙ:: እንደ ማንኛውም ጊዜ ሁሉ አሁንም የቀረበላቸው ስኳር የሌለው መራራ ቡና ነበረ:: የቤቱ ባለቤት የነበረችው ሴት ወይዘሮ ግን ስመስተንግዷቸው ሳህን ሙሉ ጣፋጭ ብስኩቶች አቀረበችላቸው:: ብስኩታቸውንም እየበሉ ወደ ሀገራቸው ስለሚመለሱበት ጊዜ መቃረብና ስለወደፊቱ ዕድላቸውም ብዙ ተወያዩ:: ስመሔድም ሲነሱ የቡናውን ዋጋ ስመክፈል ሞክረው ነበረ:: ግን ሴትየዋ አልቀበልም አለች:: ፓተርሰን በመጠኑም ፈረንሳይኛ ይናገር ስለነበረ ምስጋናውን ገለፀላት:: ምከር ግን ተጠግቶ ጉንጯን ሳማት:: እርሷም ደስ ብሏት ሳቀች:: የምግብ እጥረት በነበረበት በዚያን ወቅት የሴትየዋ ልግስና ቀላል አልነበረም::

ልክ ከበራፉ እንደ ወጡም ምከር ብራቅ እንደመታው ሰው ባለበት ድርቅ ብሎ ቀረ:: ዓይኖቹም በአጠገባቸው ባለፈችው ልጃገረድ ላይ እንደተተከሉ ነበሩ:: የምከርን መሰዋወጥ ያልተገነዘበው ፓተርሰን እንሒድ እንጂ ሲል በክንዱ ጐሽም አደረገው:: ምከር ግን ከቆመበት አልተንቀሳቀሰም:: በመንፈሱም የተሰረፀበት አንድ ስሜት በመኖሩ በዓይኖች ልጅቱን ተከተላት:: ጉንጉን የተሰራው ወርቃማ ፀጉሯ በብራኳዎቿ መካከል አልፎ ወርዷል:: የለበሰችው ሰማያዊ እጅጌ ጉርድ ቀሚስ ያረጀ ቢሆንም ሸንቃጣ ቅርጿን ውጦ አላስቀረውም:: ልጅቱም በዙሪያዋ ላለው ነገር ሁሉ ደንታ ስላልነበራት የምትራመደው በተቃና አንገት አጣጣል





የፊት ለፊቷን እያየች እንጂ ዓይኖቿ ግራና ቀኙን አይቀላውጡም:: የፓሪስ ነፃ መወጣት አለመውጣት የፓሪስ መንገዶች በጀርመኖችም ሆነ በቃል ኪዳን መንግስታት ወታደሮች መያዝ ለርሷ ልዩነት ያለው አትመስልም:: የምከር ዓይኖቹ ሰበር እያሉ ወደ ዳሌዋና ባቶቿ ተመለከቱ:: ከዚያም በአፉ የሞላውን ምራቁን ገርገጭ አድርጐ ዋጠና ልጅቱን ሲከተላት እግሮቹን አንቀሳቀሰ::

"ወዴት ልትሔድ ነው ሳም? ምን ነካህ?" አለና ፖተርሰን ከኋላው ደርሶ ክንዱን ይዞ ሊያስቆመው ሞከረ::

ምከር ግን ክንዱን አስለቅቆ ልጅቱን ተከተላት:: አሁንም ዓይኖቹ ከበስተኋላዋ በሚያየው ወርቃማ ፀጉርና ሸንቅጥ ቅርጿ ላይ እንደ ተተከሉ ናቸው:: ግራ የተጋባው ፓተርሰንም በተራው ጓደኛውን ተከተለ:: ከእግረኞች ማቋረጫው ጋ ስትደርስ ቆም አለችና በግራና በቀኝ የሚበሩትን መኪናዎች አሳልፋ አቋረጠች:: በስፄን ወንዝ ላይ የነበረውን ድልድይ ከተሻገረች በኋላም ወደ ሞንትቤል አውራ ጐዳና ታጥፋ በዘያው ባረማመዷ መንገዷን ቀጠለች ::

"ምን ነካህ ምከር! አበድክ እንዴ! ወዴት ነው የምትሄደው?" አለው ከጐኑ ጐኑ ይራመድ የነበረው ፓተርሰን::

ምከር ቆሞ ፓተርሰንን እየት አደረገውና ቶሎ ሲል ከዓይኖቹ እንዳትሰወርበት ስሰፈራ ወደ ልጅቷ ተመለሰ:: ለፓተርሰንም መልስ ሳይሰጠው የእርምጃውን ፍጥነት ጨመረ:: ፓተርሰንም ልጅቱን ያያት በዚያን ጊዜ ነበረ:: እንደ አጋጣሚ ገልመጥ ብላ ስለነበረ መልኳን ለማጤን ዕድል አገኘ:: ውበቷ ዓለማዊ አይመስልም ነበረ:: ቁንጅናዋንም ልዩና ፍፁም የሚያደርገው ደግሞ አንድ የተለየ ፀጋ ነበራት:: አረንጓዴዎቹ ትላልቅ ዓይኖቿ የብርሃን ጨረር የሚወረውሩ ይመስሉ ነበሩ:: ለሰኮንድ ፍንካችም ቢሆን እነኛ ዓይኖች በምከር ላይ ማረፋቸውን ፓተርሰን ተመልክቷል:: "ክብርህን ጠብቅ!" የሚል ማስጠንቀቂያ የሚያስተላልፉ ነበሩ::

ምከር ፈረንሳይኛ ለመናገር ባለመቻሉ ለመጀመሪያ ጊዜ ራሱን የረገመው በዚያን ቀን ነው:: የልጅቱም ግልምጫ እንደ እሳት የሚለበልብ ነበረ:: ያም ሆኖ ልጅቱን የመከታተል ስሜቱ ይበልጥ ጠነከረ:: ወደ ፊት ለፊቱም እያየ "ይቺን የመለሰች ልጅ አይተህ ታውቃለህ?" አለው ፓተርሰንን:: መልስም ሳይጠብቅ "በዓለም ውስጥ ተወዳዳሪ

የማይገኝላት ውብ ናት" ሲል ምክር በተጨማሪ ተናገረ:: በእርግጥም ያቺ ልጅ እንደ ሌሎቹ የፓሪስ ልጃገረዶች ፖሪስን ነፃ ባወጡት የቃል ኪዳን መንግስታት ወታደሮች ላይ ከመንገድ ዳር ቆማ አበባ የምትበትን ዓይነት አልነበረችም:: እንደ ሌሎቹም ከወታደሮቹ አንገት ተጠምጥማ ደስታዋን የምትገልፅ ልጅ አይደለችም:: ሁለመናዋ ፀዳል የሚያንፀባርቅ፣ ቀንበጥ ገላ ያላትና ቁጡ የምትማርክ ልጅ ነበረች:: በጀርመን አገዛዝ ሥር ያሳለፈቻቸው እነኛ አራት የግፍ ዓመታት እንኳን እንደ ሌሎቹ ቅስሟን አልሰበሩትም:: እንደ ሌሎችም አንገቷን አላስደፏትም:: በመሆኑም በማንም ሆነ በማን የምትደፈር ዓይነት ልጅ አልነበረችም::

"እንዳልከው በጣም ቆንጆ ናት:: ግን አስተያየቷ ስላላማረኝ ብንመለስ ይሻል ይመስልሀል" ሲል ፓተርሰን አለሳልሶ ተናገረ:: "እንመለስ!" አለና ምክር ጮኸበት "ይልቁንስ በምታውቀው ቋንቋ የሆነ ነገር አናግራት"

"እኔስ አላበድኩም ጌታዬ! ይልቁኑ በጤና ወደ መጣንበት ብንመለስ ይሻላል" ሲል ፓተርሰን ልጅቱ ከአንድ ሱቅ ገባች:: ምክርም ከበራፉ አጠገብ ሄደና ቆመ::

"ኧረ ተው እንሒድ ምክር:: ምንም ጥቅም ላናገኝ ለምን ጊዜያችንን በከንቱ እናባክናለን?" ሲል ፓተርሰን ተለማመጠው::

ምክር ግን ለምን ቡና አንጋብዛትም?" የሚል መልስ ነበረ የሰጠው:: ልጅቱ በወረቀት የተጠቀለለ ዳቦ ይዛ ወጣች:: ዘወር ስትልም እነ ምክርን አየቻቸው:: እርሷን እንደሚከታተሏት ይበልጥ ተጠራጠረች:: ሆኖም ዝም አለችና መንገዷን ቀጠለች:: እነ ምክርም ተከታተሏት:: ከሌላም ሱቅ ስትደርስ አሁንም ገባች:: ምክርም ከበራፉ አጠገብ እንደ በፊቱ ቆመ:: ፓተርሰንም እንሒድ እያለ እንደ ጨቀጨቀው ነበረ::

ለሁለተኛ ጊዜ ከሱቅ ስትወጣ ያንኑ የቀድሞውን ጥቅል ዳቦ ብቻ ነበር የያዘችው:: ስለነምክር ክትትል እርግጠኛ ለመሆን ስትል ብቻ ነበረ ወደ ሱቅ የገባችው:: ቀጥታ ምክር ወደ ቆመበትም በንዴት ተንደርድራ በፈረንሳይኛ አንድ ነገር ተናገረችውና ሄደች::

ምንድነው ያለችው? ስደበችኝ እንዴ?" ሲል ምክር ፓተርሰንን ጠየቀው:: ፓተርሰን ልጅቱ ያለችውን መልሶ ለመናገር ዕፍረት ስለተሰማው ዝም አለ:: ምክር ደግሞ ስላነጋገረችው ብቻ የልብ ልብ ተሰማውና ፈጠን ፈጠን እያለ ተከተላት:: ፓተርሰን ከምክር ጋር ከተዋወቁባት ዕለት ጀምሮ





እንደዛን ቀን ቂላ ቂልና ሐሳበ ግትር ሆኖበት አያውቅም:: ስለ ሴቶችም ቢሆን ሁለቱም ከልምዳቸው አኳያ የተጫወቷቸው ብዙ ነገሮች ነበሩ:: ፓተርሰንም በዓይኑ እንዳየው ምክር ለሴት በቀላሉ የሚሸነፍ ወጣት አልነበረም:: በሮም ከተማ ባሳለፉቸው ቀናት ውስጥ ፓተርሰን ከአንዷ ሴት ወደ ሌላዋ ሲል ምክር ግን ቁጥብ ሆኖ ነበረ የከረመው:: ዛሬስ ምክር በዚች ልጅ ላይ ሙዝዝ ያለው ለምንድን ይሆን ሲል ፓተርሰን ተገረመ:: ምናልባት ቢፈራና ክትትሉንም ቢያቋርጥ ሲል ልጅቱ የተናገረችውን ሊተረጉምለት መረጠ::

"ስማ ምክር! የልጅቱ አመለካከት እንዳየኸው ነው:: እንድንከተላት ፈፅሞ አትፈልግም:: ከእንግዲህ ደግሞ ብንከተላት ቀጥታ ከጦር አዛዦችን ድረስ ሄዳ ክስ እንደምታቀርብብን ነው የዛተችው:: የቀልዷንም እንዳልሆነ ከሁኔታዋ ሳትረዳው የቀረህ አይመስለኝም" አለው ፓተርሰን::

"ለምን እኛም ጄነራሎች ነን አትላትም:: ደግሞም አሁን በተናገርከው እኔ ምክር የምፈራና ወደኋላ የምመለስ አይደለሁም:: ተከታትዬ መድረሻዋን ማወቅ አለብኝ" አለና ምክር መራመዱን ቀጠለ:: አጠገቧም ደርሶ እጇን ያዝ ለማድረግ ሲል በኃይል ተሽከርክራ ዞራ "ከአጠገቤ ሒድ ነው የምልህ! ባለጌ!" ብላ በእንግሊዘኛ ስድባው መንገዷን ቀጠለች:: እንደ ንዴቷ ከሆነ ምክርን ከአሁን አሁን በጥፊ አላሰችው ሲል ፖተርሰን ፈርቶ ነበረ:: ሆኖም አላደረገችውም:: ምክር ግን እንደዚያ ብትሰድበውም ከአጠገቧ ለመለየት አልፈለገም:: በዚያን ጊዜ ልጅቱ ቆም አለችና፤"አትከተለኝ ማለት ምን ማለት እንደሆን አይገባህም? ደደብ ነህ?" አለችው አሁንም በእንግሊዘኛ::

"ደደብስ አይደለሁም:: ብቻ አንቺን ለማነጋገር በመፈለጌ ነው:: እኔ ሳም ምክር እባላለሁ:: ጓደኛዬ ደግሞ አርዘር ፖተርሰን ይባላል:: እባክሽን ያንቺንም ስም ንገሪኝ?" ሲል ልብ የሚሰልብ ፈገግታ አሳያት:: የልጅቱ ፊት በንዴት መቀያየሩን ምክር ተመልክቷል:: በአነጋገሩም ስሜቷን እንደ ጉዳው ገብቶታል:: ምክንያቱንም ስለሚያውቀው አንጀቱ ተላውሶበት የሚያደርገው ጠፋው::

"በከንቱ አትልፋ" አለችና በእጇ ጭምር አስናብታው ልትሄድ ስትል ምክር ከፊቷ ቀደማትና ተጋረጠባት:: "ምን አለበት ብንተዋወቅ" ሲል ደገመና በመለማመጥ ጠየቃት::

"አይቻልም አልኩህ!" አለችው ጮክ ብላ::

“መቻል አሰበት” አላት አሁንም ዎከር::

“ሜርድ! ቧላ! ሴ ኮምፕሪ?” አለችው በፈረንሳይኛ::

“ሜርድ?” አለና ዎከር ወደ ጓደኛው ወደ ፓተርሰን ዞር በማለት “ምን ማለቷ ነው እባክህ?” ሲል ጠየቀው::

“ምናምንቴ ነህ ነው የምትልህ” አለው ፓተርሰን ነገሩን ቀለል በማድረግ:: ዎከርም እንደ በፊቱ ዓይነት ፈገግታውን እያሳያት “ወይኔ ፈረንሳይኛ አውቄ ቢሆን ኖሮ? ስለ ክርስቶስ ፓተርሰን እባክሽ አብረን ቡና እንኳን እንጠጣ በልልኝ” አለው በቀላሉ የምትሸነፍ ልጅ መስሎት::

ፓተርሰን በሚያውቃት መጠነኛ ፈረንሳይኛ የዎከርን ጥያቄ አቀረበላት::

“ለምን?” ስትል ልጅቱ ጠየቀች::

“ጓደኛዬ ሊጋብዝሽ ስለፈለገ ነው” አላት ፓተርሰን አሁንም በፈረንሳይኛ::

“ጓደኛህ ሩህሩህ ሰውዬ ይመስላል:: ስለሆነም መጋበዝ የሚፈልጉ ብዙ ሴቶች በፓሪስ ውስጥ ስለሚገኙ እነርሱን መፈለጉ ይቀለዋል” አለችና ከፊቷ በቆመው ዎከር ጉን አልፋ ሄደች:: በመኖደጿም ፈጠን ብላ ትራመድ እንጂ አሁንም አንገቷን ለበር ሳታደርግ እንደ በፊቱ ኰራ ብላ ነበረ የምትሔደው:: ዎከርም ጫማዎቿን ያየው በዚያን ጊዜ ነው:: ጫማዋም እንደ ሰማያዊ ቀሚሷ ወደ ማለቁ የተቃረበ ነበረ::

“ምንድን ነው ያለችህ?” አለና ዎከር ፓተርሰንን ጠየቀው::

“ያለችው እንኳን ሙሉ ለሙሉ አልገባኝም:: ግን ከእኛ ጋር ለመታየት እንደማትፈልግና ጊዜያችንንም በከንቱ እንዳናባክን ምክሯን ለገሳን ነው የሔደችው” አለ ፓተርሰን ትንሽ ውሸት አክል አደረገበትና::

በዚያንም ወቅት ልጅቱ ወደ ግራንድ ዲግሪ ጉዳና ታጥፋ ጥቂት ከሔደች በኋላ ከአንድ በር አጠገብ ስትደርስ ቆመች:: በቀኝ እጇ ይዛው የነበረውን የዳቦ ጥቅል ከግራ ብብቷ ሥር አደረገችና እንደ ቀሚሷና ጫማዋ ያረጀውን የሳንቲም መያዣ ቦርሳዋን ከፈተች:: ቁልፍም ካወጣች በኋላ በፊት ለፊቷ የነበረውን በር ከፍታ ከገባች በኋላ በሀይል ዘጋችውና





ከበስተውስጥ ቆለፈችው:: ዎከር ድልን እንደ ተቀዳጀ ዓይነት በፊቱ ላይ የደስታ ስሜት ተነበበ:: እንደ መሳቅም ከጀል አደረገው:: “ምን ተገኘና ነው ደስታው?” ሲል ፓተርሰን በፌዝ ጠየቀው::

“አድራሻዋን ማወቃችንም አንድ ነገር ነው:: አይመስልህም እንዴ?” አለው ዎከር የምሩን::

“እና አድራሻዋን አወቅክና ምን ለመሆን ነው?” አለው ፓተርሰን ዎከርን ያስወትሮው በመታዘብ::

“ተመልሳ እስከምትወጣ እጠብቃታለሁ::”

“ባትወጣስ?” አለው ፓተርሰን::

“መውጣቷ የማይቀር ነው:: ጥርጥርም የለውም” ሲል ዎከር መለሰለት::

“አንድ ሰዓት፣ ሶስት ሰዓት፣ አምስት ሰዓት.... ልትቆይ ትችላለች::”

“የቆየችውን ያህል ትቆይ:: እኔ ግን እጠብቃታለሁ::”

“እና እዚሁ ቆመህ ልትውል ነዋ? አብደሃል ማለት ነው?” አለው አሁንም ፓተርሰን:: የልጅቱን ቆንጅና ፓተርሰንም ቢሆን አምኖበታል:: ሆኖም ፓሪስ ውስጥ ሌሎች ቆነጃጅት ነበሩ:: ስለዚህ ፓተርሰን በፓሪስ ውስጥ የሚቆይባቸውን ጥቂት ቀናት ያሰምክንያት ለማባከን አልፈለገም:: ቆንጆ ፍለጋ መሔድ ነበረበት:: “ይቅርታ ዎከር እኔ ከዚህ ግርግዳ ተደግፌ ቆሜ ለመዋል አልፈልግም:: እናም መሔዴ ነው” አለው::

“ሒድ ፓተርሰን ቅድም፤ ቡና ከጠጣንበት መናፈሻ ሥፍራ እንገናኛለን” አለው ዎከር::

“አንተ ግን እዚሁ ልትቆይ ነው?”

“ልክ ነህ:: እዚሁ መቆየቴ ነው” አለና ሲጋራ እያይዘ ከግርግዳው ተደገፈ:: ፓተርሰንም ለጥቂት ጊዜ ራሱን በትዝብት አወዛወዘና ምንም ሳይናገረው ከጉኑ ሔዶ ቆመ:: ዝም ዝም ተባባሉም፣ ደቂቃዎች መብረር ጀመሩ:: ከአንድ ሰዓት ያህልም በኋላ በራፉ ተከፍቶ ልጅቱ ብቅ አለች:: ወዲያውኑም እነ ዎከርን ስላየቻቸው ወደ ውስጥ ፈጥና ገባች:: ግን ብዙም ሳትቆይ ሐሳቧን ለውጣ ነበርና ተመልሳ ወጣች:: የተጉነጉነውን

ፀጉሯን አሁን ለቃው ነበረ። ከበፊቱም ይልቅ ውበቷ ጨምሯል። በእጆቿም ጥቂት መፃህፍት ይዛለች። እንደተኰሳተረችም በአጠገባቸው ልታልፍ ስትል ምክር ቀስ ብሎ እጇን ነካ አደረገው። ዘወር ብላ በአነኛ አረንጓዴ ዓይኖቿ አየት አደረገችው። የዚያን ጊዜው አመለካከቷ ብቻውን ለፊ መልዕክት የሚያስተላልፍ ነበረ። ያሳለፈችው መራራ ኑሮ በአነኛ ዓይኖቿ ውስጥ ተመዝግቦ የሚነበብ ይመስላል። ከዚያም ሌላ ደግሞ የምክር ፍላጐት ምን እንደሆነ ማወቋንና እርሱም እሺ እንደማትለው አፍ አውጥታ ብትነግረው እንኳን ተስፋ የማይቆርጥ ችኮ ሰው መሆኑን መረዳቷን ከዚያ ከአስተያየቷ ለመገንዘብ ይቻል ነበረ።

ጥላቸው ከመሔዷ በፊት ምክር እየተቻኮለ "እባክሽ ፈቃድሽ ይሁንና ምግብ እንኳን ልጋብዝሽ?" ሲል ለመናት። ፓተርሰን እስከሚተ ረጉምላት ድረስ ጊዜም የሚወስድ መስሎት በእጆቹ የመመገብ ምልክት አሳያት። የተናገራት ዓይን ዓይኖቿን በርህራሔ እያየ ነበረ። ሊጐዳት ወይንም ሊያባልጋት አለመፈለጉንም በአስተያየቱ ሊያረጋግጥላት ሞከረ። ምክር የፈለገው ለጥቂት ደቂቃዎች ከፊት ለፊቱ ተቀምጣ ሊያያት ብቻ ነበረ። ለሁለተኛ ጊዜ ደፍሮ እንኳን እጇን እንደማይነካው በሆዱ ወስኖአል። "እሺ በይኛ?" አላት እንደ ህፃን ልጅ ዓይኖቹን እያቁለጨለጨ።

"አልችልም" አለችው ዓይኖቿን ለበር ሳታደርግ። ምክር በመቀየም ምትክ ፈገግ አለና፣ "እባክሽን የኔ ወይዘሪት፣ ሁለተኛ አላስቸግርሽም። ለዛሬ ብቻ ግብዣዬን ተቀበይልኝ" አላት አሁንም በዓይኖቹ ጭምር እየተለማመጠ።

"አልችልም አልኩህ! አልችልም!" አለች ለስለስ ባለ አነጋገር።

"ለምን?" አለ ምክር ተስፋ ባለመቁረጥ።

"ለምን? ለምን?" አለች አሁንም ረጋ ብላ። "ለመጋበዝ ስለማልፈልግ ብቻ ነው" አለች በፈረንሳይኛ።

ምክር ያለችው ስላልገባው ወደ ፓተርሰን ዞር አለ። ፓተርሰንም "ለመጋበዝ ስለማልፈልግ ነው ትልሃለች" አለው።

የምክር ፊት ቀጭም እንደለማት አለና "ግን ለምን? እይው እኔና ፓተርሰን ጨዋ ሰዎች ነን። እኔ የፈለኩት ምግብ እንድጋብዝሽ ብቻ ነው። አምስት ደቂቃ ... እባክሽ?" አላት ሊያለቅስ እንደ ተቃረበ ሰው የዓይን ቆቦቹን ገርበብ አድርጎ።





ዝም ብላ ስታየው ቆየችና ራሷን አወዛወዘች። "ማንም ሰው ጋብዞኝ አያውቅም። ከአንድም አሜሪካዊ ሆነ ጀርመናዊ ጋር ሆቴል ቤት ሄጄ አላውቅም" አለችው። እንደዚህ ተናግራው ብትሄድ ኖሮ የምክር ዓይኖች ያቀረሩትን ዕንባ በዘረገፉትም ነበር። ግን አሁንም ቆማ ታየው ስለነበረ ዕንባውን እንደምንም እየታገለ "ለሜን አፍሪካ ... ጣሊያን ... አሁን ደግሞ ፈረንሳይ። ቀን ጦርነት ... ማታ ጦርነት ..." እያለ ሲንገላቱ መኖራቸውን በውጊያ ምልከቶች ካሳያት በኋላ "እባክሽ ቡና ብቻ ልግዛልሽ ... አምስት ደቂቃ ... እሺ?" አላት።

ያን ጊዜም በርህራሄ አመለካከት አየችው። ምክር እሺ የምትለው መስሎት ፊቱ ፈካ እንደ ማለት አለ። ልጅቱ ግን አሁንም ራሷን አወዛወዘችና "ስለማልችል አዝናለሁ" ብላ ጥላው ፈጠን ፈጠን እያለች ተራምዳ ሄደች። አሁን ግን ምክር አልተከተላትም። ቢከተላትም ዋጋ እንደማይኖረው ያውቃል። ያገኘው አንድ ተስፋ ጭላንጭል ብቻ ነበር። በአነጋገረችው ወቅት ወደ ጣቶቿ አየት አድርጎ ቀለበት አለማድረጓን ልብ ብሏል። አላገባችም ነበር ማለት ነው። ደግሞ ለዚህ በይበልጥ የሚመሰክረው ሰጋ ፊቷ ነበረ። በዚህ ለመፅናናት በቅቷል። ስለዚህ አሁንም ግርግዳውን እንደተደገፈ እስክትመለስ ሊጠብቃት ፈለገ።

"እንሂድ እንጂ ምክር! ከእንግዲህ ምን ታደርጋለህ? ቁርጥ ያለ መልስ ሰጥታህ ነው የሄደችው!" አለና ፓተርሰን መራመድ ጀመረ። "የተናገረችውን ሰምቻለሁ ግን ሃሳቧን ልትቀይር ትችላለች" አለ ምክር ተስፋ ባለመቁረጥ።

ፓተርሰን ቆም አለና፤ "አዎን! ሃሳቧን ልትቀይር ትችል ይሆናል። እንደ ቅድሙም በሰላም አታናግረን ይሆን ይሆናል። እንጋብዝሽ ስንል ብዙ ጊዜ ለምነናት እምቢ ብላለች። ከእንግዲህ ወዲያ ብናስቸግራት ምናልባት አባቷንና ጐረምሶች ወንድሞቿን ጠርታ ጥርሳችንን ልታስረግፈው ትችላለች። ባለውለታ አድርገው የሚቆጥሩ የፈረንሳይ ቆነጃጅት እያሉ በአንዲት ሴት የተነሳ የምንደበደብበት ምክንያት አይታየኝም" አለው እምርሮ።

ምክር ከቆመበት ነቅነቅ ሳይል፤"ፓተርሰን ከተዋወቅንበት ጊዜ ጀምሮ ለሴት በቀላሉ የማልንበረከክ ሰው መሆኔን ታውቃለህ። ይቺ ልጅ ግን ልዩ ሆነችብኝ። እንደዚች ልጅ ያለች አንድም ሴት አይቼ አላውቅም" ሲል ከልቡ ተናገረ።

"እሺ፤ እንዳልከው ልዩ ፍጥረት ናት ልበልልህ። ሆኖም ያለ ፍላጐቷ አስገድደህ ምን ልታደርግ ነው ምክር? ከዕድሜህ በላይ አመዛዛኝ ሰው ትመስለኝ ነበር። ግን ዛሬ ምን እንደነካህ አላውቅም። እኔ ግን ልሄድ መሆኑን እንድታወቀው" አለና ፓተርሰን ጥሎት ሊሄድ ሲል ምክር ሃሳቡን ቀየረና ተከተለው። በየሄዱበትና በየደረሱበት ሁሉ ለምክር የምትታየው ያቺ ልጅ ብቻ ናት። ከፊቱ ድቅን ትልበታለች። ከአረንጓዴ ዓይኖቿ ውስጥ ያነበበው የሀዘን አመለካከቷ ልቡን አስጨንቆታል። የአለባበሷም መጐሳቆል ሆድ ሆዱን በልቶታል። እሺ የማለቷ ነገር አጠራጣሪ ሆነበት እንጂ፤ ያቺን ልጅ ለማስደሰት የተጠየቀውን መስዋዕት ለመክፈል ፈቃደኛ ነበር።

እራት ከበሉ በኋላ ፓተርሰን ከሶስት ልጃገረዶች ጋር በመዳራት ላይ እንዳለ ምክር ጣለውና ተሾልኮ ወጣ። ከዚያም በዱአርኮል ጐዳና አድርጐ በሰዬን ወንዝ ላይ ወደ ተሰራው ድልድይ አመራ። ድልድዩንም ተሻግሮ ወደ ሞንትቤል አውራ ጎዳና ታጠፈ። ብዙ ከተጓዘ በኋላ ከግራንድ ዲግሪ መንገድ ደረሰ። ወደ ልጅቱም ቤት አቅጣጫ አሳብሮ ሄደ። ከበራፍም ቆመና ጥቂት ሲያስብ ቆየ። ከዚያም ከፊት ለፊቱ ወደ ነበረው ቡና ቤት ገባና ከልጅቱ በር ትይዩ የነበረ ወንበር መርጦ ተቀምጦ ቡና አዘዘ። ያንንም መራራ ቡና መጠጣት ጀመረ። ዓይኖቹ ግን በዚያች ልጅ ቤት በር ላይ እንደተሰኩ ነበር።

በሩ ከአሁን አሁን ተከፍቶ ልጅቱ ትወጣለች ብሎ ሲጠብቅ ሲጠብቅ ቆየ። በሩ ግን፤ አንዴም አልተከፈተም። ምክርም ከተቀመጠበት አልተንቀሳቀሰም። በመጨረሻ ላይ ልጅቱ ቀን ከሄደችበት አቅጣጫ ስትመለስ አየ። በእጇም መፃህፍ እንደያዘች ነበረች። ደረጃዎቹን ወጥታ ከበራፍ እንደደረሰች የሳንቲም መያዣዋን በርሻ ከፍታ ቁልፍ ትፈልግ ጀመር። በዚያን ጊዜም ምክር ጥቂት ሳንቲሞች አውጥቶ ከጠረጴዛው ላይ ካኖረ በኋላ እየተቻኮለ ወጣ። ሮጠናም መንገዱን አቋረጠ። ልጅቱም የሩጫ ኮቴ በመስማቷ ተደናግጣ ዞወር አለች። ከምክርም ጋር ዓይን ለዓይን ተጋጩ። ወደኋላዋ ለማፈግፈግ እንደ መከጀል ብላ ነበር። ሆኖም፤ መፍራት እንደማይኖርባት ደግሞ ወዲያውኑ ተሰማትና ባለችበት በልበ ሙሉነት ቆመች። ዛሬ ነጻ በወጣችው ፓሪስ ሳይሆን በጀርመን ይዞታ ስር በነበረችበትም ወቅት ቢሆን ያች ልጅ የፍርሃት መንፈስ አሳይታ አታውቅም። እና አሁንም ምክርን ባየችው ጊዜ አመለካከቷ የመደንገጥ ሳይሆን የመሰልቸት ነበረ።





ለምክር አድራጎቱ ሁሉ የህጻን መስሎ ተሰማው። ልጅቱንም በማስቸገሩ ተፀፀተ። ሆኖም፤ አንድ ጊዜ አድርጎታልና ከእንግዲህ ወደኋላ መመለስ አልቻለም። ድፍረትም በመጨመር፤ "ወይዘሪት እንደምን አምሽተሻል?" ሲል ሰላምታ ሰጣት።

እናት ህጻን ልጇ ሲባልግ ስታየው እራሷን በማወዛወዝ እንደምትገስጸው ሁሉ ያችም ልጅ በትዝብት እራሷን አወዛወዘችና፤ "ፑርኳ ቩመ ፐርሴዩቬ?" አለችው ። ምክር ምን ማለቷ እንደሆነ አያውቅም። ዝም ብሎ ብቻ ያያታል። አስተርጓሚውም ፓተርሰን ከጎኑ አልነበረለትም። የተናገረችው እንዳልገባው ተረዳችና እርሷም በመጠኑም ቢሆን በምታውቀው እንግሊዘኛ፤ "ለምንድ ነው እንደዚህ የምታደርገው? ለምን ትከታተለኛለህ?" ስትል ጠየቀችው።

"ሳነጋግርሽ በመፈለጌ ብቻ ነው" አለ ምክር ድምጹን ልስልስ አድርጎ። ከእጅጌ ጉርድ ሰማያዊ ቀሚሷ ውስጥ የወጡትን ክንዶቿን ሊነካቸውም ፈለገ። ሹራብ ስላልደረበች እንደሚበርዳት ያውቃል። ክንዶቿን በእጆቹ ባሻቸውና ባሞቃቸው ደስታው ነበረ።

ወደ መንገዱ ግራና ቀኝ በእጆቿ እያመለከተች "በፓሪስ ውስጥ ብዙ ልጃገረዶች አሉ። ከአሜሪካኖች... ከጀርመኖች ጋር ለመዳራት የሚፈልጉ፤ ሞልተዋል" አለችው።

"አንቺስ? ከፈረንሳዊ ጋር ካልሆነ በስተቀር አትነጋገሪም ማለት ነው?" አላት ምክር እየተከዘ።

እርሷ ግን ፈገግ አለችና፤ "ፈረንሳዊ... ጀርመን... አሜሪካን ሁሉም ያው ናቸው። ማንንም ለማነጋገር አልፈልግም" አለችው። እንግዳ ባይሆን ኖሮ በጀርመኖች ይዞታ ወቅት ፈረንሳዮች በፈረንሳዮች ላይ የፈጸሙትን የክህደት ስራ ሁሉ በገለጸችለት በወደደችም ነበረ።

"ሌላ የምለምንሽ ምንም ነገር አይኖርም። ሁለተኛም ካላነጋገርሽኝ ብዬ አላስቸግርሽም። ለእኔ መጽናኛ እንዲሆን አንድ ነገር ብቻ እንድትነግሪኝ እማፀንሻለሁ። የኔ ስም ሳም ምክር ነው። የአንቺን ስም ደግሞ እባክሽ ንገሪኝ?" አላት ምክር ዓይን ዓይኖቿን እያየ።

ዝም ብላ ለረጅም ጊዜ ስታስብ ቆየች። ስሟን መናገር አልፈለገችም። ሆኖም ምክር ዳግመኛ እንደማያስቸግራት ቃል ገብቷል።

በተጨማሪም ከፓሪስ በቅርብ ቀናት ውስጥ ሊሔድ ይችላል:: ስለዚህ ስሜን ብቻ በመንገር የምትገላገል ከሆነ ብነግረውስ? ቀላል ነው» ስትል ትከሻዋን ሰበቅ አደረገችና፤ "ሶንላጅ በርትራንድ" አለችው:: ምክር እንድት ጨብጠው እጁን ዘረጋ:: የእርሷ እጅ ግን አልተነቃነቀም::

"ሒዳ፤ ስሜን ነግሬሃለሁ:: ከእንግዲህ ምን ቀረህ?" አለችው በቀላሉ የተገላገለችው መሰሏት::

"አንድ ቡና ብቻ ልጋብዝሽ:: እባክሽ ወይዘሪት እሺ በይኝ:: ከዚያ በኋላ እግሬ ወደዚህ አካባቢ አይደርስም" አላት ምክር ሲቃ እየተናነቀው፡ በርሱ ግምት የምትናደድና የምትሰድበው ነበረ የመሰለው:: እርሷ ግን፤ ለግብገቦው በማወላወል አንገቷን እወዛወዘችና ለመጀመሪያ ጊዜ አቀርቅራ ቆየች:: ቀናም ብላ በግራ እጇ ይዛው ወደ ነበረው መፅሐፍ እያመለከተችው "ዤ ስዊ ትሬ ፋቲግ" አለችው ወደ ፈረንሳይኛዋ ተመልሳ:: በእርግጥም ስለ መድከሟ ከፊቷ ላይ ይነበብ ነበረ::

"ከትምህርት ቤት እያመሸሽ ነው የምትመጪው ማለት ነው? ሲል ምክር ቶሎ አለና ጠየቃት::

"አይደለም ማታ ማታ ከቤቱ ድረስ እየሄድኩ የማስተምረው ልጅ አለ" አለችው::

"እና ቡናውን ተጋበዢልኝ" አለ ምክር ዓይኑ ከርተት እያለ::

"ደክሞኛል እያልኩህ፤"

"እባክሽን ወይዘሪት? አምስት ደቂቃ ብቻ ..."

"ዳ አኮርድ ... እሺ ... ግን አምስት ደቂቃ ብቻ" አለች:: ምክር ለጥቂት ጊዜ ያህል ልቡ ጉሮሮው ውስጥ የተሻጠች መሰለው:: ከደስታውም የተነሳ ለማይና ምድሩ ዞረበት:: ልጅቱ የያዘችውን መፅሐፍ እንዴት እንደተቀበላትና እጇንም ይዞ መንገዱን እንዴት እንዳሻገራት አያውቀውም: ከቡናው ቤት ገብተው ወንበር ይዘው እንደተቀመጡ፤ ባለቤቱ ወደነርሰ መጣና ሰላምታ ሰጣቸው:: ልጅቱንም ያውቃት ነበርና "እንደምን አመሸሽ ወይዘሪት ሶላንጅ?" ሲል ስሟን በመጥራት አነጋገራት::

"ሶላንጅ ... ሶላንጅ ... ሶላንጅ" የልጅቱ ስም በምክር ጭንቅላት ውስጥ እንደ ደወል እንቃጨለበት:: በህልም ዓለም ውስጥ እንዳልነበረም





በዚያን ጊዜ ተረዳ:: ልጅቱ የነገረችው እውነተኛ ስሟን ነበረ:: በዐፀደ ነፍስም ከፊት ለፊቱ ከነበረው ወንበር ላይ አሁን ተቀምጣለች::

ያዘዘችው ሻይ ብቻ ነበረ:: ምክር ግን ምግብ ካልቀረበ ብሎ ሙዝዝ አለ:: ሶላንጅ ተሸነፈችለትና ምግብ ታዘዘ:: ምክር በዚያን አጋጣሚ ነበረ የሶላንጅን ቅጥነት ልብ ብሎ ያየው:: የችግር ጊዜ ማሳለፏን ታወለውና አንጀቱ አለቀለላት:: የደረቷ አጥንቶች መታየት ጀምረው ነበረ:: ሶላንጅ ከእንግዲህ አልተግደረደረችም:: የቀረበላትንም ምግብ በልታ ጨረሰች:: ለማወራረጃ ወይን እንዲመጣላት ምክር አዞ ነበረ:: እርሷ ግን ከሻይ ሌላ እንደማትጠጣ ነገረችው:: ውስጥ ውስጡን ስታብላላ የቆየችውን ጥያቄ ያቀረበችለትም የመጣላትን ትኩስ ሻይ በመጠጣት ላይ እንዳለች ነበረ:: "ለምንድን ነው ልትጋብዘኝ የፈለግከው?" ስትልም ጠየቀችው::

ምክር የሚናገረው ጠፋበት:: ለምን ቀኑን ሙሉ ሲከተላት እንደዋለና እንድታነጋግረው እንደ ፈለገ፤ በተለይም ደግሞ ለምን ምግብ ሊጋብዛት እንደፈለገ ያውቀዋል:: ገና ዓይኖቹ በርሷ ላይ እንዳረፉ ነበረ ምክር የለየለት:: አሁን ግን ምክንያቱን አውጥቶ ለመናገር አቃተው::

"ምክንያቱን እንዲህ ነው ብዬ ለመናገር ይቸግረኛል" አለና ዓይን ዓይኗን ማየቱን መረጠ:: ሶላንጅ ግን በሰጣት መልስ ግራ ለመጋባቷ በግልፅ ይታወቅ ነበረ:: በመሆኑም ምክር ማብራሪያ ለመስጠት ተገደደ:: በቅድሚያ የቀኝ እጁን በልቡ ላይ አደረገ:: ቀጠለናም ዓይኖቹን ነካክቶ፤ "አንቺን ከማየቴ ልቆጣጠረው የማልችለው ስሜት አደረብኝ" አላት::

ባምክር ንግግር ሶላንጅ አልተደሰተችም:: በአባባሱም ዕፍረት ተሰምቷት በቡና ቤቱ ውስጥ የነበሩትን ሌሎች ሰዎች ተገላምጣ ተመለከተች:: አብዛኛዎቹ የአሜሪካ ወታደሮች ናቸው:: በጉናቸውም የፈረንሳይ ሴቶች ነበሩ::

"አይደለም! አይደለም! እንደዛ ማለቴ አይደለም" አላት ምክር እንደሌሎቹ ለብልግና ያልፈለጋት መሆኑን በመግለፅ::

"ታዲያ ለምንድን ነው?" አለችው ሶላንጅ::

"የእኔ የተለየ ነው:: ከልብ የመነጨ ስሜት ነው" አላት::

"ከልብ? ከልብ ብሎ ነገር የለም" አለችው::

"ለምን? አለ እንጂ" አላት ደገመና።

"ሰውን ማመን አይቻልም" አለች ሶላንጅ።

«በዚህ የወጣትነት ዕድሜ ሰውን ሁሉ ለመጠራጠር ከበቃሽ እንድ የደረሰብሽ አስከፊ ነገር አለ ማለት ነው። ምናልባት ከምታፈቅሪያቸው ሰዎች ውስጥ ጀርመኖች ገድለውብሽ ይሆን?" ሲል ጠየቃት። ሶላንጅ ከንፈሯን ነከሰችና ራሷን በኃይል አወዛወዘች። ሆኖም ጥቂት ቆይታ መናገር ጀመረች። ዓይኖቿም እንባ እያቀረሩ፣ «አባቴን ... ወንድሜን ... ጀርመኖች ገደሏቸው። እናቴን ደግሞ የሕክምና እርዳታ የሚያደርግላት አጥታ በብርድ በሽታ ሞተች» አለችው።

"በጣም አዝናለሁ" አለና ምክር በጠረጴዛው ላይ ዘርግታው የነበረውን እጇን ለማፅናናት ሲል ያዝ አደረገው። የርሱም ዓይኖች ቢሆኑ እንባ አግተው ነበረ።

ወንድሜ የአስራ ስድስት ዓመት ልጅ ነበረ። የርሱን ደም ለመበቀል እችል ነበረ። ሆኖም እናቴን ማስታመም ስለነበረብኝ..." አለችና በሌላው እጇ መሐረብ አውጥታ እንባዋን ጠረገች። የምክር ልብ እብሯት አለቀሰ። የሚሆንላትንም አጣው። ከደረቱ ባስጠጋትና እንደ ህፃን ልጅ ፀጉሯን እያሻሸ ባባበላት ደስታው ነበረ። ግን ሶላንጅን ሊደፍራት ከቶ አልቻለም። እስኪያልፍላት ድረስ ዝም ማለቱን መረጠ።

ሶላንጅ አንድም ዘመድ አዝማድ አልነበራትም። ሁሉም ዘመዶቿ በውስጥ አርበኝነት ሲያገለግሉ ነው በጀርመኖች እየታደኑ የተገደሉት። ጠቋሚዎቹ ደግሞ ፈረንሳዮች ነበሩ። ተጫዋችና ተግባቢ የነበረችው ሶላንጅ ከሰው ለመራቅና ብቸኛ ለመሆን የፈለገችው በፈረንሳዮች ላይ ካደረባት ጥላቻ የተነሳ ነበረ። በዛሬው ቀን ግን በማታውቀው ወጣት ለመጋበዝ ፈቃደኛ መሆኗ ራሷንም ጭምር አስገረማት። እጁንም በእጇ ላይ ሲያደርግ ዝም ብላዋለች። ልታስቀይመውም አልፈለገችም። ሶላንጅ እንባዋን ጠራርጋ ወደ መቀዝቀዙ የተቃረበውን ሻይ ረጋ ብላ አነሳችና ጠጣች። ምክርም የዕድሜዋን ለጋነት ልብ ብሎ አጥንቶ ነበረና፣

«ለመሆኑ ዕድሜሽ ስንት ይሆናል ሶላንጅ?" ሲል ጠየቃት።

«ዲዝ ነፍ» አለችው በፈረንሳይኛ።





"ዲዝ ነፍ? ዲዝ ነፍ በእንግሊዘኛ ስንት ማለት ነው?" አላት

"ናይንቲ" አለችው።

"የአምላክ ያለህ! ናይንቲ! ከሃያም አልፈሽ ዘጠና?" አላት በመገረም። ሶላንጅ ስህተቷ ገባትና ለመጀመሪያ ጊዜ ሳቀች።

"ናይንቲን ማለትሽ ይመስለኛል?" አላት ምክርም እየሳቀ።

"እዎን!" አለችው አሁንም እየሳቀች።

"ታዲያ የአስራ ዘጠኝ ዓመት ኮረዳ የዘጠና ዓመት አሮጊት ነኝ ትይኛለሽ?" አለና ምክር ሁለቱም ተሳሳቁ። ሐዘን የተፈራረቀበት የሶላንጅ ፊት አሁን ፈካ። ምክርም ይበልጥ ወጣት ሆና ታየችው። ከልቡም ውስጥ ጠልቃ ገባች።

"አንተስ ስንት ዓመትህ ነው?" አለችው ሶላንጅ።

"ሐያ ሁለት" አላት። የእሁኑ ጭውውታቸው የተለመደ የጐረምሳና የኮረዳ ውይይት ነበረ። ሁለቱም በወጣትነት ዕድሜያቸው የመከራ ጊዜን አሳልፈዋል። ብቸኛዋ ሶላንጅ በፓሪስ ውስጥ፣ እርሱ ደግሞ በሰሜን አፍሪካ በርሃና አሁን ደግሞ በአውሮፓ ውስጥ።

"ተማሪ ነበርክ?" አለችው አሁንም ሶላንጅ።

በአዎንታ ራሱን ጉንበስ አደረገና፣ "ቦስተን በሚገኝ ሐርቫርድ በሚባል ቦታ እማር ነበር" አላት። በሐርቫርድ ዝና ስለሚኰራበትም ነበረ የዩኒቨርስቲውን መጠሪያ ያነሳላት። እንደ ገመተውም ሶላንጅም ስለዩኒቨርስቲው ስምታ ኖሮ "አ! አርቫርድ?" አለች እንደ ፈረንሳዮች አጠራር።

"ስለ ሐርቫርድ ሰምተሽ ኖሯላ?" አላት ምክር።

"ያለጥርጥር! ልክ እንደኛ ሶርቦን ዝነኛ ዮኒቨርስቲ ነው" አለችው። ምክር በአነጋገሯ ደስ አለውና ከልብ የመነጨ ፈገግታ አሳያት።

እርሷም አፀፋውን መለሰችለት። የምግቡ ሳህኖችና የሻይ ብርጭቆዎቹ ከተነሱ ቢቆይም ሶላንጅ ምክርን ትታው ለመሔድ እስከዚህም አልተጣደፈችም ነበረ።

“ነገ ልንገናኝ እንችላለን ሶላንጅ?” ሲል እሺ እንድትለው በዓይኖቹ ጭምር እየተለማመጠ ጠየቃት:: ጠረጴዛው ላይ ወደ ነበሩት መፅሐፎች እያመለከተች ራሷን አወዛወዘች:: “አንቺን በሚመችሽ ሰዓት:: እባክሽ ሶላንጅ? እይው ፓሪስ ውስጥ ብንቆይ በጣት ለሚቆጠሩ ቀናት ይሆናል::

ስለዚህ አትጨክኝብኝ? እባክሽን ነገ ላግኝሽ?” አላት ምከር እጇን አሁንም እንደያዘ:: ጦሩ ወደ ጀርመን አቅጣጫ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ ከሶላንጅ እንዴት ጨክኖ እንደሚለይ ከአሁኑ ሲያስበው አንጀቱ ተላወሰበት:: ከዚያን በፊት ፍቅር ምን ማለት እንደሆነ አያውቅም:: ማስጨነቅ ማስጠበቡን! ማስተከዝ ማስለቀሱ ከዚያ በፊት ደርሶበት አላየውም:: የዚያኑም ያህል ደግሞ ፍቅር ሕይወትን ለዛ የሚያላብስ የሚያድስ፣ የሚያስደስት፣ የሚያስፈነድቅ ነበረ:: እነኚህ ስሜቶች ሁሉ ምከር ሶላንጅን ካያት ደቂቃ ጀምሮ ጐሽሽመውታል:: ከሁሉም በላይ ደግሞ ፍቅር መተሳሰብንም የሚያጐለብት ኃይል ነበረ:: የሶላንጅ መጐሳቆል ምከርን ሲበዛ አሳስቦታል:: የሰውነቷን መክሳት ልብ ብሎ አይቶታል:: ልብስና ጫማዋም እንደነገሩ ነበረ:: የሶላንጅ በራስ የመተማመን ስሜት ላለመንካት ምከር መጠንቀቅ ነበረበት:: ስለ ልብስና ጫማዋ ጉዳይ ጊዜ ያደርሰዋል:: ሆኖም፤ ፓሪስን ከመልቀቁ በፊት ለሶላንጅ አንድ ነገር ማድረግ ነበረበት:: የተጠመደባቸውን እነኛን አረንጓዴ ዓይኖቿን ለማየት ብቻ ሳይሆን ሶላንጅን በየቀኑ ቢያንስ አንድ ጊዜ እያገኘ ደህና ምግብ መጋበዝ ነበረበት::

ዳግመኛ ካልተገናኘን ሲል ምከር እንደ ልማዱ ሙዝዝ አለባት:: እርሷም በረጅሙ ተነፈሰች:: ማንነቷን ደህና አድርጋ ብታውቀውም ከምከር ጋር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በማግስቱ ለመገናኘት እሺ አለችው:: ፓሪስ በጀርመን ይዞታ ሥር በቆየችባቸው ዓመታት ውስጥ ከአንድም የጀርመን ወታደር ጋር ተነጋግራ አታውቅም:: ፓሪስ በአሁኑ ጊዜ ነፃ ስለወጣች ደግሞ ሶላንጅ እንደ ሌሎቹ ልጃገረዶች ከአሜሪካ ወታደሮች ጋር የመታየት ፍላጐት ጨርሶ የላትም:: ከፊቷ ተቀምጦ ይለማመጣት የነበረውን ወታደር ግን ትክ ብላ አየችው:: በመልኩም ሆነ በፀባዩ የሚጠላ ልጅ ዓይነት አልነበረም::

“አመሰግናለሁ” አለና ምከር ከመቀመጫው ተነሳ:: እንዳመጣ ጣቸው መፃህፍቱን በግራ እጁ እርሷን ደግሞ በቀኝ እጁ ይዞ መንገዱን አቋረጡ፥ ደረጃውንም ወጥተው ከበራፉ ሲደርሱ ቆም አሉ:: ሶላንጅ ስለ ግብዣው አመስገነችውና ደህና እደር ስትል እጁን ጨብጣው ገባች:: ከበስተውስጥም በራፉን ቆለፈች::





ምከር በዚያን ምሽት በፓሪስ ጐዳናዎች ላይ ብቻውን በሚንዝበት ወቅት በሕይወቱ ላይ አዲስ ምዕራፍ መከፈቱን አውቆታል:: ከእንግዲህም የዱሮው ግዴለሽና ደፋሩ ምከር ለመሆን አይችልም:: በጥቂት ሰዓታት ውስጥ አስተሳሰቡ ተለወጧል:: ያቺ ልጅ ... ያቺ ልዩ ፍጥረት ... ያቺ ባለአረንጓዴ ዓይን ልጅ ያጋጠመችው ያለምክንያት አለመሆኑም ገብቶታል:: ከአሁኑም እንደ ግማሽ አካሉ ያህል ቆጠራት::

## ምዕራፍ ሁለት

“የት ነው ትናንትና ማታ ያመሸኸው?” አለው ፓተርሰን ቁርስ በመብላት ላይ እንዳሉ:: ፓተርሰንም ቢሆን ብቻውን አላመሸም ነበረ:: ብዙም ጠጥቶ ስለነበረ የዞረው ድምር አለቀቀውም ነበረና አልፎ አልፎ ያዛጋል:: በዚያ ላይ ደግሞ ሌሊቱን ያሳለፈው ከአንዷ ኮረዳ ጋር በመሆኑ ተደካክሞ ነበረ:: ምክር ስላመሸበት ቦታ ሊነግረው እንኳን አልፈለገም:: ይታዘበኛል ሲልም ሕስቧል:: ሆኖም ፓተርሰን፤“የት ነው ያመሸኸው?” ሲል በድጋሚ ጠየቀው::

“ከሶላንጅ ጋር በአንድ ቡና ቤት ውስጥ ነው” አለው ምክር ውሉ ቢያድርም ተሸፋፍኖ የማይቀር ነገር መሆኑ ተሰምቶት::

“ማን ናት እርሷ? እኔን ብቻዬን ጥለኸኝ አንተ ሌላ ሴት ፍለጋ ሄደህ ኖሯል?” አለው ፓተርሰን በትዝብት ራሱን እየነቀነቀ::

ምክር ፓተርሰንን ሙሉ ለሙሉ እያየው “ከሌላ ሴት ጋር ያመሸሁ መስሎህ ይሆናል:: ግን እኔ ያመሸሁት ከዚያች ከልጅ ጋር ነው:: ያቺ ትናንትና እመንገድ ላይ ካገኘናት ልጅ ጋር” አለው::

“ከዚያች ባለ አረንጓዴ ዓይኖችና ፀጉረ ወርቃማ ከሆነችው ልጅ ጋር?” አለ ፓተርሰን የሰማውን ባለማመን::

“አዎን ከርሷ ጋር ነው” አለው ምክር ደገመና::

“ለምን ትዋሻለህ ምክር? ይልቅስ በእውነት የት እንዳመሸህ ብትነግረኝ?” አለው ፓተርሰን አሁንም::

“ከርሷ ጋር ነው አልኩህ፤ ከርሷ ጋር ነው” ሲል ምክር ሊያሳምነው ሞከረ::

“እና የዚያች ልጅ ስም ሶላንጅ መሆኑንም ለማወቅ በቃህ?” አለው ፓተርሰን ሳቅ እየቃጣው::





“ሶላንጅ በርትራንድ!” አለ ምክር ኮስተር ብሎ::

“እውነት ያቺ ልጅ እሺ ብላህ አብራችሁ አመሻችሁ?” አለ ፓተርሰን የቀድሞው ጥርጣሬው በመጠኑ እየቀነሰ::

“እመነኝ አልኩህ እመነኝ!” አለው ምክር መልሶ::

ፓተርሰን በጠረጴዛው ላይ አንገቱን አስገገና፤ “ለመሆኑ የትና እንዴት ልታገኛት ቻልክ?” አለው የማታውን የምክር ገድል ለመስማት እየቋመጠ::

“ወደ መኖሪያ ቤቷ ልትገባ ስትል ከበሯ ፊት ለፊት ካለው ቡና ቤት ተቀምጬ በመጠባበቅ፣ ከቤቱ ድረስ እየሄደች ከምታስተምረው ልጅ ቤት ስትመለስ አገኘኋት::”

“ስታስተምር ማምሸቷን በምን አወቅህ? ልጂቱ የምትናገረው ፈረንሳይኛ ብቻ ነው:: ለዚያውም የተራቀቀ ፈረንሳይኛ” አለው ፓተርሰን በመገረም::

“ሳይበዛም እንግሊዘኛ ትችላለች:: ዕድሜዋንም ስጠይቃት ዘጠና ነው አለችኝ:: ያም ሆኖ ተግባብተን ነበረ ያመሸነው” አለና ምክር ፈገግ አለ:: ፓተርሰን እያመነው መሔድ ጀመረ:: ወዲያውኑም ደግሞ ተቆጨ:: እንደ ምክር ዓላማ ፅኑ ሰው ቢሆን ኖሮ በሚያውቀው ፈረንሳይኛ አግባብቶ ልጂቱን የራሱ ሊያደርጋት በቻለ እንደነበረ ተሰማው:: ምክር የሰው መውደድ አለው:: በሕይወትም ውስጥ በሚያጋጥመው ፋከከር ሁሉ አሸናፊ የሚሆኑት እንደ ምክር ያሉት ናቸው::

“እና ትክክለኛ ዕድሜዋ ስንት ነበረ?” አለ ፓተርሰን ስለ ሶላንጅ በበለጠ የማወቅ ፍላቱ እየጨመረ::

“አስራ ዘጠኝ ነው:: 'ናይንቲን' በማለት ምትክ 'ናይንቲ' ስላለችኝ ነው ብዙም እንግሊዘኛ አትችልም ያልኩህ” ነለው ምክር::

“እኮ የአስራ ዘጠኝ ዓመት ልጃገረድ ይገፔ ከቡና ቤት አመሸሁ ነው የምትለኝ? አባቷ ቢያይ ኖሮ ያርድህ ነበረ” አለው ፓተርሰን::

“አባቷንም፣ ወንድሟንም ጀርመኖች ገድለውባታል:: እናቷም ሞተዋል:: የምትኖረው ብቻዋን ነው” አለ ምክር::

የፓተርሰን ጥርጣሬ ፍፁም ተወገደ:: በእርግጥም ከልጂቱ ጋር ማምሸቱን አመነ "ዳግመኛስ የምትገናኙ ይመስልሃል?" አለው ፓተርሰን::

ምክር ፈገግ ብሎ "ጥርጣሬ አለው? ዳግመኛ መገናኘት ብቻ እንዳይመስልህ:: ጦርነቱ እንዳለቀ እንደምንጋባ እመነኝ" አለው::

ፓተርሰን አፉን ከፍቶ ምክርን ቕዝም ብሎ ያየው ጀመረ: ምክርን አብዷል ሲል አሰበና ወዲያውኑ ደግሞ ምክር አንድን ነገር ለማድረግ ከወሰነ ወደ ኋላ የማይል መሆኑ ታወሰው::

ሶላንጅና ምክር ለሁለተኛ ጊዜ በማግስቱ ተገናኝተው ራት ጋበዛት:: በዚያንም ቀን ሶላንጅ ስለ ፓሪስ ብዙ ነገር አጫወተችው:: በጀርመኖች ቁጥጥር ሥር በነበረችው ፓሪስ ለመኖር እጅግ መሰኛ መሆን ያስፈልግ ነበረ:: በተለይም ፈረንሳዮች እርስ በእርስ በመካካድ ጓደኛ ጓደኛውን አያሳለፈ የሚሰጥበት ወቅት ስለነበረ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግን ይጠይቅ ነበረ:: እንደ ሶላንጅ ላለች ልጃገረድ ደግሞ በሰላም መኖር ያስቸግራል:: ጀርመኖች የወረሩትን የፈረንሳይን ግዛት ብቻ ሳይሆን ሕዝብንም እንዳሻቸው ለማድረግ መብት ያላቸው ይመስላቸው ነበረ:: እንኳንስ ባል ያላገቡት ሴቶች ቀርቶ ባለትዳሮችንም የሚያባልጉበት ጊዜ ነበረ:: ሶላንጅ አባትና ወንድሟ ተገድለውባታል:: እናቷም ህመምተኛ ናቸው:: መድኃኒትም ሆነ ምግብ ለማግኘት ጥበበኛ መሆን ነበረባት:: ክብርናዋን ላለማስደፈር ስትል ከቤት በምትወጣባቸው ቀናት እንኳን እንደ አሮጊት ለብሳና በሻርፕ ተሸፋፍና ነበረ:: እናቷ ከሞቱ በኋላም ለሁለት ዓመት ያህል ብቻዋን መኖር ነበረባት:: በተለይም የታናሽ ወንድሟን መገደል ስታስታውሰው እጅግ አድርጉ ያንገሸግሻታል:: ስለ አገሯም ሆነ ስለህዝቡ ያላት ግምት እጅግ ዝቅተኛ ነበረ:: የምትሄድበትም ብታገኝ ሀገሩን ለቃ ለመሄድ ቅር አይላትም ነበረ::

በመመገብ ላይ እንዳለ "ወደ አሜሪካ አንድ ቀን ብትመጪ ደስታውን አልችለውም ነበረ" አላት ምክር መንገድ ለመጥረግ እየሞከረ::

"በጣም ሩቅ ነው:: አሜሪካ በጣም ሩቅ ነው" አለችው ከምግቧ ላይ ቀና ብላ::

"ያን ያህል ሩቅ አይደለም" አላት ምክር::

"ሩቅ እንኳን ሩቅ ነው:: ግን አንተ ጦርነቱ እንዳለቀ ትምህርትህን እንደምትቀጥል እርግጠኛ ነኝ" አለችው





"ሊሆንም ላይሆንም ይችላል" አላት ራሱን እያወዛወዘ:: ለብዙም ጊዜ ሲመኘው የነበረውን ፍላጎቱን ለሶላንጅ ሊያካፍላት ፈለገ:: "ቲያትር ተዋናይ ለመሆንም ዕቅድ አለኝ" ሲል የግል ምስጢሩ አድርጐ የያዘውን ምኞት ገለፀላት::

ሶላንጅ መመገቡን ትታ በመገረም ስታየው ቆየችና "በአርቫርድ ዮኒቨርስቲ የምትከታተለው ትምህርት ምን ነበረ?" ስትል ጠየቀችው::

"ሥነ ጽሑፍ" አላት

"እንደዚያስ ከሆነ ጥሩ:: የተዋጣለት ተዋናይ እንደሚወጣህ እርግጠኛ ነኝ" አለችና ፈገግ አለችለት:: በዚያን ጊዜ እቅፍ አድርጐ ከደረቱ ቢያስጠጋት፣ እንቡጥ ፅጌረዳ የመሰሉትን ከንፈሮቿን ቢስም ፈቃዱ ነበረ:: ሶላንጅን ግን እንደምትሰበር ዕቃ ሳሳላት:: እንደዚያም ማድረግ ክብሯን መቀነስ መስሎ ተሰማው:: ለፈገግታዋ ፈገግታ ብቻ መለሰና ፍራፍሬ እንዲመጣላት አዘዘ:: የገቡበት ሆቴል በምግብ ዝግጅቱ የታወቀ ነበረ:: ሶላንጅም በምክር ቸርነት ብትገረምም የቀረበላትን ምግብ ደህና አድርጋ በላች:: ምክርንም አላፈረችውም ነበረ:: ለብዙ ጊዜ እንደሚተዋወቅ ጓደኛ ነበረ የቆጠረችው:: በሁለት ቀናት እውቂያ የዚያን ያህል ይግባባሉ ብሎ ማሰቡ ያስቸግራል::

ውሎ ሲያድር መቀራረባቸው እየጠነከረ ሔደ:: ራት ከበሉ በኋላ እጅ ለእጅ ይያያዙና በሰዬን ወንዝ አጠገብ ይንሸራሸራሉ:: ሲደክማቸው ከአንዱ ቡና ቤት ገብተው እረፍ ይላሉ:: ከዚያም እጅ ለእጅ እንደተያያዙ እቤቷ ድረስ ይሸኛታል:: ከበራፉም ሲደርሱ ቆም ይሉና የጀመሩትን ጨዋታ ይጨርሳሉ:: እጅ ለእጅ ይጨባበጡና ይለያያሉ:: ከደቂቃ በፊት በሎራት ደረቱን ነፍቶ የነበረው ምክርም አንገቱን አቀርቅሮ በፓሪስ መንገዶች ላይ ብቻውን ይመለሳል:: ሶላንጅ በዚያን ጊዜ ምን ታስብ ይሆን?

ምክርና ፓተርሰን አብረው ማምሸት ካቆሙ ቀናት አልፈዋል:: የሚገናኙት ቁርስ ላይ ብቻ ነበረ:: በዚያን ቀን ጠዋት ፓተርሰን ያወራለት ዜና ከመርዶ አይሻልም ነበረ:: እነ ምክር ወታደራዊ ሰልፍ ባሳዩበት ዕለት በጄነራል ፓተን የሚመራው ጦር የሙየዝን ወንዝ ተሻግሮ ወደ ቤልጂግ መሐል ሀገር በመገሥገሥ ላይ ነበረ:: በነሐሴም ወር መጨረሻ ላይ እንግሊዞች ብራሰልስንና አንትወርፕን ይዘዋል::

“እኛም ከሁለት ቀናት በኋላ እንደምንቀሳቀስ ሰምቻለሁ” አለ ፓተርሰን ፊቱ ጠቆር እንደ ማለት ብሎ:: ምክር ሲጠጣ ወደ ክንፈሩ አድርሶት የነበረውን ቡና መልሶ አስቀመጠ:: ፓተርሰን የተናገረው ልክ እንደነበረ ታውቆታል:: ግን ከሶላንጅ እንዴት አድርጎ ይለያት ይሆን? በዚያን ዕለት ምሽት ሶላንጅን ከበራፏ ድረስ ሸኝቷት አልተመለሰም:: ወደ ቤቱ ውስጥ ተከትሏት ገባ:: ራሱንጁ ከትከሻዋ ላይ አድርጎ አለቀሰ:: ሶላንጅም ነገሩን በደመ ነፍሷ አውቃው ነበረና ከደረቷ አስጠግታ አቀፈችው:: በምክር ጥቁር ፀጉር ላይ እንባዋ እየተንከባለለ ወረደ:: እንዳቀፈችውም ወደ መኝታ ቤቷ ገቡ:: ጐን ለጐን እንደተቀመጡም ሶላንጅ የመጀመሪያ ፍቅረኛዋን ከንፈሮች ሳመቻቸው:: ምክርም እጀ ጉርድ የነበረውን ሰማያዊ ቀሚሷን አወለቀላትና ተኙ:: ሶላንጅ ለምክር ክብረ ንፅህናዋን በፍቅር ሰጠችው:: ከዚያም ከደረቱ ላይ ተኝታ እንባ አነባች:: ምክርም እንባዎቿ የሚንቆረቆሩበትን ጉንጮቿን ሳማቸው:: የምክርና የሶላንጅ ፍቅር ጊዜ በማይፍቀው ማኅተም ታተመ::

“ካየሁህ ቀን ጀምሮ ልቤ እንደተንጠለጠለልህ እንደነበረ ታውቃለህ ሳም?” አለችው ሶላንጅ:: ትንፋሿ ቁርጥ እስከሚል ድረስ ሳማትና፣ “ህይወቴ ነሽ ሶላንጅ” አላት::

በየትኛው እንጀት ጨክኖ ከሶላንጅ እንደሚለይ አያውቀውም:: ሶላንጅም በሆዷ ትወቀው እንጂ፣ ስለ መለያየታቸው እንዲነሳባት አትፈልግም:: ከድቅድቅ ጨለማ ከጠቆረ ሕይወት አውጥቶ ነፍስ የዘራባት ምክር ነበረ:: ከእንግዲህ ምን ለኝታ አላት? ከመኝታዋ ስትነሳ የሚታያት ከምክር ጋር የሚገናኙበት ሰዓት ነበረ:: እጅ ለእጅ ተያይዘው በስዬን ወንዝ ዳር የሚንሸራሸሩበት ሰዓት የምክር ንግግሩ፣ ቀልዱ፣ ደግነቱ፣ ሩህሩህነቱ... ሶላንጅ አይለምዱ ልምድ ለመደች:: ከምክር ተለይታ ምን ይውጣት ይሆን? የዱሮው ብቸኝነቷ በተሻላትም ነበረ:: በገዛ እጇ መድኃኒት የማይገኝለት ፍቅር የሚሉት በሽታ ገዛች:: በህይወት እያሉ ለፍቅረኞች መለያየት ደግሞ ከሞትም የባሰ መራራ ነበረ:: ለሶላንጅ ሰቆቃ እንዳችም አፅናኚ ኃይል አይገኝለትም::

በመጨረሻውም ምሽት ከደረቱ ላይ ተኝታ ያለማቋረጥ ትንሰቀሰቅ የነበረችውን ሶላንጅን ምክር ሊያፅናናት ሞከረ:: “የጀርመን ጦር ዙሪያውን ተከቧል:: ከእንግዲህ በርሊንን ለመያዝ ግፋ ቢል ሶስት ወር ቢፈጅ ነው:: ከሶስት ወራት በኋላ አብረን እንሆናለን ማለት ነው:: የገናን በዓል ብቻሽን አትውይም” ሲል ከወርቅ የጠራ ፀጉሯን እያሻሸ ነገራት:: ዓይኖቿን፣





ጉንጮቿን፣ ከንፈሯን፣ አፍንጫዋን፣ ግንባሯን ሁሉ ተራ በተራ እየሳመ እንደ ህፃን ልጅ አባበላት::

“ሶላንጅ የኔ ፍቅር ... ላንቺ ያለኝን ፍቅር ቃላት ሊገልፁት አይችሉም:: ልቤ የአንቺ ብቻ መሆኑን እምልልሻለሁ” አላት:: እንደ ሶላንጅ ያለች ልጅ የትም አላየም:: በፓሪስ ውስጥ በጣሊያን፣ በሐርሻርድ አላጋጠመውም:: የመጀመሪያ ፍቅሩም ሶላንጅ ነበረች:: “ጦርነቱ እንዳለቀ ወዲያውኑ ነው የምንጋባው” አላት ምክር ከደረቱ ላይ ቀና አድርጎ ዓይን ዓይኗን እያየ:: አሁንም እንባዋ አያቋርጥ እንጂ መልስ አልሰጠችውም::

“እሺ በይኝ እንጂ ሶላንጅ?” ሲል መልሶ ጠየቃት:: መልስ ልትሰጠው አሁንም አልፈለገችም ነበረ:: “እንጋባለን ስትይ ቃል ግቢልኝ?” ሲል ደጋግሞ ለመናት::

በዚያን ወቅት ያደረባትን ፍርሃት ለመገለፅ ተቸግራ ነበር:: “ሳም” አለችና ጉንጭና ጉንጩን በሁለት እጆቿ ይዛ ትኩር ብላ አየችው:: “ሳም ጦርነቱ አስከፊ ነው:: ለብዙ ነገሮች መለዋወጥ ምክንያት ሊሆን ይችላል:: ሳም... ” ሳያስጨርሳት ከከንፈሩ አስጠግቶ ትንፋሽ እስኪያጥራት ሳማት:: የሶላንጅ አነጋገሯ፣ የስም አጠራሯ፣ ትንፍሿ፣ ፀጉሯ፣ ዓይኗ ... ሁሉም ሁሉም የምክርን ልብ እንደ ሰም አቀለጡት:: የርሱም በመሆኗ ራሱን በቁሙ ከመንግስተ ሰማይ እንደገባ ሰው አድርጐ ቆጠረ::

“ግን እኮ ሳም ጦርነቱ ካለቀ ፓሪስን ትረሳና ወደ እርሻርድ ትመለስ ይሆናል” አለችው ሶላንጅ:: አባባሏ ፓሪስን ሳይሆን እኔን ትረሳኛ ለህ ማለቷ ነበረ:: ነገሩ ለምክርም ገብቶታል::

“የፓሪስ ሕንፃዎች ውበት ሊረሳኝ ይችላል:: ግን የአንቺ ዓይኖች፣ የአንቺ ፀጉር፣ የአንቺ ገላ አይረሳኝም:: ሶላንጅን አልረሳም:: ስለ ተጠራጠርሽኝም” አለና ምክር ከጉያው አስገብቶ ጭምቅ አድርጎ አቀፋት:: እኛደዚያንም ጊዜ እንዴም አልጨከነባትም:: አድራጐቱ ሁሉ የእልህ ነበረ:: የሁለቱም ስሜት እኩል ሲረካ ምክር በጀርባው ተኛና ጐትቶ ደረቱ ላይ አደረጋት:: “አሁንስ ፍፁም እንደምወድሽ አልገባሽም? ሶላንጅ ባልወድሽ ኖሮ ያን ያህል አስቸግርሽ ነበረ? እንደሌሎቹ ወታደሮች በፓሪስ ውስጥ ከሌሎች ሴቶች ጋር መጫወት ያቅተኝ ነበረ? ምን ያህል እንደማፈቅርሽ እንዴት ትጠረጥሪኛለሽ? ስታይኝስ ቃለ አባይና ባለጌ እመስልሻለሁ:: ይልቁንስ ከአሁኑ ራስሽን አዘጋጂ:: ጦርነቱ እንዳለቀ ወደ ሀገሬ ብቻዬን

እንደማልሄድ እወቂ። ካንቺ ጋር ነው ሶላንጅ፤ አብረን ነው የምንሄደው እሺ?" አላት።

ራሷን ዘንበል በማድረግ የእሺታ ምልክት አሳየችው። ሶላንጅ ምክርን መጠራጠር ብቻ ሳይሆን በሆዷ የፈራችው ሌላ ነገር ነበረ። ያ ጦርነት የምትወዳቸውን ሁሉ አሳጥቷታል። ምክርስ ከሚቀረው ጦርነት በደህና ይመለስ ይሆን? አሁን አለኝ የምትለው ምክር ብቻ ነበረ። ጦርነት ጨካኝ ነው። ሶላንጅ በጣም ነው የፈራችው። ያለመጠንም ከመፍራቷ የተነሳ ምክርን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ፍፁም የራሷ ልታደርገው ፈለገች። ለፍቅሯ ገደብ አልነበረውም። ይሉኝታም የሚባለውን ነገር ረሳችው። እንቅልፍ የሚባል ነገር በዓይናቸው ዘወር ሳይል አነጉ።

በመንቀሳቀሻው ዕለት ምክርን ባቡር ጣቢያ ድረስ በመሄድ ልትሸኘው ፈልጋ ነበረ። ምክር ግን አለማስፈለጉን ነገራት። በአደባባይ ሲያለቅስ ለመታየት አልፈለገም። ሶላንጅም ፍርሃቱ ገብቷታል። ከአልጋው ውስጥ ወጥቶ ሱሪውን ለበሰ። ሸሚዙንም በማጥለቅ ላይ እንዳለ ሶላንጅ ከተኛበት እርቃኑን የነበረውን ሸንቃጣ ሸንጡን አየች። ሸሚዙን ጉተተችና መልሳ አስተኛችው። የሱሪውንም ቁልፎች በጣቶቿ ፈታቻቸው። ምክርን አንቅ አድርጋ አቅፋው ተኛች። የመሰነባበቻ ፍቅራቸውን ተለዋወጡ። ምክር በሩፉን ከፍቶ ሲወጣ ሶላንጅ እንዳታይ ፊቷን ተሸፍና ነበረ። ምክርም ቢሆን ዞር ብሎ ለማየት ፈራ። ያን ጊዜ ተመልሶ የሶላንጅን ሁኔታ ቢያየው ኖሮ ምናልባትም ከሰራዊቱ ሊከዳ ይችል ነበረ።

ምክር በደረሰበት ጦር ሜዳ ሁሉ ከቀድሞው በበለጠ ወኔ ተዋጋ። የርሱ ግምት ጦርነቱ ቶሎ ይፈፀምና ከገና በዓል በፊት ወደ ሶላንጅ እመለሳለሁ የሚል ነበረ። ግን በመስከረም ወር ማለቂያ ላይ ሁኔታው ሁሉ እንደተጠበቀው ሳይሆን ቀረ። ለገናም ወደ ሶላንጅ የመመለሱ ጉዳይ የቀን ህልም ሆነ። ጀርመኖች እንደተወራው በቀላሉ የሚሸነፉ አልነበሩም። ከምንጊዜውም በበለጠ ቆራጥነት ነበር የሚዋጉት። በጥቅምት ወር ማብቂያ ላይ አሜሪካኖች መጠነኛ ድል ተቀዳጁ። ግን ያም ሆኖ የክረምቱ ወራት በመግባቱ እንደልብ ወደፊት መግፋት አልቻሉም። በረዶና ጭቃው አሳሳውስ አላቸው። ልክ ከአንድ ዓመት በፊት በኔፐልስ ተራራዎች አካባቢ ይወርድ እንደነበረው ዓይነት ዶፍ ነበረ አሁንም የሚጥለው። ከጥቅምት እስከ ህዳር ባለው ጊዜ ውስጥ የአሜሪካን ጦር ጉልህ እንቅስቃሴ ለማድረግ ተሳነው። ጀርመኖችም አዳዲስ የታንክ ብርጌዶች በማከታተል ወደ ጦር ግንባሩ ይልኩ ስለነበረ የጦርነቱ ጊዜ እንደሚራዘም ግልፅ ሆነ።





በህዳር ወር አጋማሽ ላይ ትልቁ የበልግ ጦርነት ተጀመረ። በቃል ኪዳን መንግስታት የጦር ኃይሎች ላይ ለአንድ ሳምንት ያለማቋረጥ የመድፍ ጥይት ዘነበባቸው። እንዳውም እንኳንስ ጀርመኖች ሊሸነፉ የድል ሚዛኑ ወደነርሱ አዘንብሎ ነበረ። ሆኖም የቃልኪዳኑ መንግስትታት የአየር ኃይል የበላይነት ስለነበረው የጀርመኖችን ቅስም ሊሰብረው ቻለ። የጀርመን ታንኮችና መድፎች ማጓራታቸውን አቁመው ሰማዩም ሊጠራ የቻለው ከሰባት ቀናት በኋላ ነበረ።

በገና በዓል ዋዜማ ምሽት ምክርና ፓተርሰን በበረዶ ከተሸፈነች የቀበሮ ጉድጓድ ውስጥ ተቀምጠው ለዕለቱ የተሰጣቸውን ራሽን በመብላት ላይ ነበሩ። የምክር ዓይኖች ተስፋ የመቁረጥ ምልክት ይነበብባቸዋል። በተጣበቁት ጉንጮቹ ላይ ያደገው ጺሙም ሽማግሌ አስመስሎታል።

"ከአምናውና ከዘንድሮው ምግብ የቱ ይሻላል?" አለ ፓተርሰን ምክርን ለማዝናናት ሲል።

"የአምናው" አለው ምክር።

"ተው የዘንድሮው ይሻላል" ሲል ፓተርሰን በማሾፍ ተናገረ።

"ለእኔስ የአምናው" አለ ምክር።

"የአምናውን የመረጥክበት ምክንያት ይገባኛል። ያን ጊዜ ሐሳብና ጭንቀት የለብህም ነበረ። አሁን ግን እንዳው እህሉም ጭምር ስላስጠላህ ነው" አለው ፓተርሰን።

"እኔ ወንዱ ይህን ያህል የተጨነቅሁ ሶላንጅስ ምን ውጧት ይሆን?" አለ ምክር እየተከዘ።

"ያው አንተኑ እያሰላሰለች ማልቀስ ነዋ! እርሷን በመሰለች ልጅ መወደድ ትልቅ ዕድል ነው" ሲል ፓተርሰን መሰሰለት።

"ለምን ቸኮላታ አልሰጥህም?" አለና ምክር ከኪሱ ውስጥ የደረቀ ብስኩት አውጥቶ እጁን ዘረጋለት።

"ባታስጐመጀኝ ምን አለበት?" ብሎ ፓተርሰን ራሱን በምሬት አወዛወዘ። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን በዚያን ወቅት እነ ፓተርሰን ለምግብ የሚጓጉበት ጊዜ አልነበረም። ከላይ በረዶው ይወርድባቸዋል። ዙሪያቸውን የጀርመን ጥይት ያፏጭባቸዋል። ፓተርሰን ቀድሞውኑም ቢሆን ለነፍሱ

ይሳሳላታል:: ምክርም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መጠንቀቅ አምጥቷል:: ሕይወቱን ለሶላንጅ ለማቆየት ሲል መፍራት ጀምሯል::

የአሜሪካው ጦር የቦንን ከተማ ለመያዝ የቻለው በየካቲት ወር አጋማሽ ላይ ነበረ:: ብዛታቸው ሶስት መቶ ሃያ አምስት ሺህ የሆነ የጀርመን ወታደሮች ተማረኩ:: በመጋቢት አስራ ስምንት ቀንም ከምስራቅ ወደ ምዕራብ እየገፋ የመጣው የሶቭየት ጦርና ከምዓራብ ወደ ምስራቅ በመገስገስ ላይ የሚገኘው የአሜሪካ ጦር በቶርጋው መንደር ተገናኙ:: በርሊንም ሚያዝያ አንድ ቀን ተያዘች:: በስሜን አፍሪካ በርሃ፣ በጣሊያን ተራሮች፣ በፈረንሳይ ሸለቆዎችና በጀርመን ሜዳዎች ላይ የተካሄደው የነምክር የጦርነት ገድል በርሊን ላይ አበቃ:: ምክርና ፓተርሰንም እንደ ወንድማማች ተቃቅፈው አለቀሱ:: ከጐናቸው ብዙዎቹ ጓደኞቻቸው ወድቀዋል:: ፓተርሰን አይወደኝም የሚለው አለቃ እንኳን ያቺን የደስታ ዕለት ለማየት ዕድል አላገኘም ነበረ::





# ምዕራፍ ሶስት

ለምክር የተሰጠው የሶስት ቀናት ፈቃድ ብቻ ነበር:: ከዚያ በኋላ ግን በቀጥታ ወደ ሀገሩ እንደሚመለስ ተነግሮታል:: እርሱም በቀጥታ ወደ ፓሪስ ሄደ:: ሶላንጅም ከበፊቱ ይልቅ የከሳች ብትመስልም እንደ ነበረች አገኛት:: በእነኛ በሶስት ቀናት ውስጥ እንደ ሁለቱ ፍቅረኞች ደስተኛ ሰው አልነበረም:: ስለዚህም እነኚህ ቀናት ለነሶላንጅ ፈጠኑባቸው:: በመጨረሻም ምክር ወደ በርሊን የሚመለስበት ዕለት ደረሰ::

ሶላንጅ ባቡር ጣቢያ ድረስ ሄዳ ሸኘችው:: ምክር አሁን ልበ ሙሉ ነበረ:: ከእንግዲህ ከሶላንጅ የሚለየው ኃይል አይኖርም:: እሞታለሁ የሚለውም ስጋት ቀርቷል:: ስለዚህ ሶላንጅ ባቡር ጣቢያ ድረስ መጥታ ብትሸኘውም እንደማያለቅስ ታውቆት ነበረ:: እርሷ ግን ራሷን በምክር ትከሻ ላይ አድርጋ ለረጅም ጊዜ ስትንሰቀሰቅ ቆየች:: ባቡሩም መንቀሳቀስ ሲጀምር ነበረ ምክርን የለቀቀችው::

ምክር ለሶላንጅ ቀለበት አድርጐላታል:: ከዚያም በኋላ ነው መቀያየሪያ የሚሆኑ ልብስና ጫማ የገዛላት:: ለአራት ወራት ያህልም ሊረዳት የሚችል መጠነኛ ገንዘብ አስገድዶ ሊሰጣት በቅቷል:: ፓሪስ ውስጥ ሊጋቡ ይችሉ ነበረ:: ግን ምክር ቀደም ሲል ወደ አሜሪካ ሔዶ ለመኖሪያቸው የሚሆን ቤት እንዲያዘጋጅ ተስማሙ:: በተጨማሪም ከወታደርነቱ ስለሚሰናበት ለመተዳደሪያቸው ሥራ ማግኘት ነበረበት:: ከዚያም ጥቂት ገንዘብ አጠራቅሞ ሊልክላትና እርሷ በቱሪስት ስም ወደ አሜሪካ እንድትመጣ ተነጋግረው ጨርሰው ነበረ::

ሶላንጅ ባቡሩ ለዓይን እስኪሰወር ድረስ በቀኝ እጇ የያዘችውን ነጭ መሐረብ በማውለብለብ ላይ ነበረች:: ባቡሩም እኩለ ሌሊት ላይ ከበርሊን ደረሰ:: ምክርም በቀጥታ ወደ ጦር ሰፈሩ ሄደ:: ፓተርሰን ከመኝታ ክፍላቸው ውስጥ አልነበረም:: ፓተርሰን የበርሊንን ልጃገረዶች ሲያማርጥ ነበረ ውሎውና አዳሩ:: ምክርም ከአልጋው ላይ ጋደም አለና እርሱና ሶላንጅ ስለሚመሰርቱት ትዳር ሲያስብ ቆየ:: በዚያው እንቅልፍ ወሰደው:: ፓተርሰን የበርሊን ኑሮ ጥሞት ነበረና ለሁለት ሳምንታት

የመቆየት ዕድል ተሰጠው። ከምከርም ጋር በኒዮርክ ከተማ ስመገናኘት ተቀጣጥሪው ምከር በማግስቱ ወደ አሜሪካ በረረ። ከፎርት ዲክስ የጦር ሰፈር ደርሶ ከሠራዊት አባልነቱም እንደተሰናበተ ወደ ኒውዮርክ ሄደ። ከፔን የባቡር ጣቢያ ወርዶ በኒውዮርክ ጐዳናዎች ላይ ሲጓዝ ልክ በጨረቃ ላይ ያረፈ ነበረ የመሰለው። ለሶስት ዓመታት በበረሃ ሲቆላ፣ በዝናብና በበረዶ ሲወገር፣ በጭቃ ሲጨማለቅ ነበረ የከረመው። የኒውዮርክ ከተማም ሆነች ነዋሪዎቿ ያጦርነት ሥጋት ሲያልፍም አልነካቸውም። የሕዝቡ እንቅስቃሴ፣ የመኪናው ትርምስ ከቀድሞውም ብሶበት ነበረ። ምከር መኝታ የተከራየው ከትንሽ ሆቴል ውስጥ ቢሆንም፣ የኒውዮርክን ኑሮ እስከሚላመደው ድረስ ጊዜ እንደሚፈጅበት አውቋል። ከጉኑም ሶላንጅም ሆነች ፓተርሰን ባለመኖራቸው ብቸኝነት አጥቅቶት ነበረ። ሆኖም ሥራ መፈለግ፣ ማፈላለግ ነበረበት።

ከወታደርነት ሲሰናበት የተሰጠው መቶ ሃምሳ አራት ብር ብቻ ነበር። ከዚሁ ላይ ለመኝታና ለምግቡ እየከፈለ ብዙ ቀን ስመቆየት አይችልም። ወጪውን መቀነስ ነበረበት። እንደተቃጠሩት ፓተርሰን ከሁለት ሳምንት በኋላ መጣ። ይህም ለምከር ታላቅ እፎይታ ነበረ። ከፓተርሰን ጋር በመኖር ለመኝታ የሚያወጣውን ገንዘብ አዳነ። እንደ አጋጣሚ በአንድ ሆቴል ውስጥ በአስተናባሪነት ሥራ አገኘ። ስለ ወደፊት ዕድሉ አንስቶ ለሶላንጅ ያጫወታት ነገር ነበረ። እርሷም ቢሆን "የተዋጣላት ተዋናይ እንደሚወጣህ እርግጠኛ ነኝ" እንዳለችው አልተረሳውም። ቀን ቀን ሲሰራ እየዋለ ማታ ማታ የተዋናይነትን ሙያ ለመቅሰም በአቅራቢያው ከነበረው የኪነጥበባት ትምህርት ቤት ተመዘገበ። ቁመናውና የተፈጥሮ ተሰጥኦውም ታክለበትና በሐምሌ ወር ላይ በአንድ ተውኔት ውስጥ ተካፋይ የመሆን ዕድል አጋጠመው። ደስታውንም ለመግለፅ ለሶላንጅ ደብዳቤ ፃፈላት።

በመስከረም ወር ላይ የራሱን ቤት ለመከራየት በቃ። ለሶላንጅም ገንዘብ ልኮላት ነበረና በመስከረም ሃያ ስድስት ቀን ዴ ግራስ በሚባለው መርከብ ከኒውዮርክ ወደብ ደረሰች። ቀኑ ጥርት ያለና የደስ ደስ ያለው ነው። በወደቡም አካባቢ መጠነኛ ነፋስ ይነፍሳል። እንደ ሶላንጅና ምከር ከልብ ለሚፋቀሩ ወጣቶች ከዚያን ቀን የተሻለ መገናኛ ዕለት ሊኖር አይችልም ነበረ። ከመርከቡም ከመውረዷ በፊት አይታው ነበረና ደረጃዎቹን ቶሎ ቶሎ ተራምዳ ወርዳ እየበረረች ከደረቱ ተለጠፈች። እርሱም በጠንካራ ክንዶቹ እቅፍ እንዳደረጋት ለብዙ ጊዜ





ተቃቅፈው ቆዩ። በቀኝ እጁ ከአገጯ ቀና አደረጋት። ከዓይኖቿም የደስታ እንባዎች ይንከባለሉ ነበረ።

"ሶላንጅ ምን ያህል አፈቅርሽ መሰለሽ? አንቺንስ በማግኘቴ አምላክ እንደኔ የወደደው ሰው ይኖር?" አለና እርሱም የደስታ እንባ አነባ። እንደ ተቃቀፉም ከወደቡ ወጡ። ወደ አዲሱ መኖሪያ ቤታቸውም በታክሲ ሄዱ። ከበራፉም እንደ ደረሱ ምከር ከንፈሯን ሳማትና ሳታስበው አንከብክቦ አቅፏት ወደ ውስጥ ገቡ። ከዚያም ለተከታታይ ቀናት ከሥራ ቀርቶ አብሯት ቤት መዋሉን መረጠ። የሁለቱም ፍቅር ከግምት በላይ ነበረ። ቁርስ በልተው መተኛት ነው። ምሳ በልተው ያው ነው። ከራትም በኋላ እንደዚያው።

ገና ሲቃረብ ነበረ፣ ምከርን ስለወደፊት ዕድሉ አጥብቆ እንዲያስብበት ሶላንጅ ልትገፋፋው የጀመረችው። ለምከር ግን፣ ከአንድ ነገር በስተቀር ሁሉም ሕልም መስሎት ነበረ የሚታየው። በርሱ ህይወት ውስጥ ቦታ የነበራት ሶላንጅ ብቻ ነበረች። በመሆኑም ለሶላንጅ ሲል ብቻ መሥራት ነበረበት። መሥራት ብቻ ሳይሆን ዝነኛና ሀብታም ሊሆን ቆርጧል። ለሶላንጅ ሲል ማናቸውንም መሥዋዕትነት ለመክፈል ቆርጧል። በልጅነት ዕድሜዋ ሐዘን የተፈራረቀባት ሶላንጅ አሁን ፍፁም ደስተኛ መሆን አለባት። ምከር የተያያዘውን የተዋናይነቱን ሙያ ማጠናከር ነበረበት። ከሶላንጅ መለየት ቢሆንበትም ማታ ማታ የጀመረውን ትምህርት ቀጠለ። በመምህራኑም ዘንድ አድናቆትን አግኝቶ ነበረ። ከብሮድዌይ ትያትር ቤቶች ሥራ አስኪያጆች ጋር ያስተዋወቁትና በአንዳንድ ተውኔቶች ውስጥ የመካፈል ዕድል እንዲያገኝ የረዱትም መምህራኑ ነበሩ።

እንደ ዱሮው ባይሆንም ከፓተርሰን ጋር አልፎ አልፎ ይገናኙ ነበረ። ፓተርሰን የሕግ አገልገሎት ድርጅት አቋቁሟል። ማርጆሪ የምትባልም ልጅ አጭቶ ነበረ። ማርጆሪ ደግሞ በሶላንጅ ውበት ትቀና ነበረና አትወዳትም ነበረ። በሶላንጅ ሳቢያ ባሏንም ምከርን ስለጠላችው ፓተርሰንና ምከር አዘውትረው እንዲገናኙ አትፈልግም። ፓተርሰንና ማርጆሪ በተጋቡም ጊዜ ለሰርጋቸው ከፍተኛ ድግስ ተደግሶ ነበር። በግብዣውም ላይ ከሰባት መቶ በላይ እንግዶች ተጠርተዋል። ለምከርና ለሶላንጅ ግን ጥሪ አልተደረገላቸውም ነበረ። ምክንያቷም ማርጆሪ መሆኗን ስለሚያውቁ ለደካማው ፓተርሰን አዘኑለት እንጂ አልተቀየሙትም።

ምከር በተዋናይነቱ ለዓመት ከመንፈቅ ያህል ሲለማመድ ቆየ:: ሶላንጅም ከተማውን እያወቀችው በሔደች ቁጥር ከምከር ጐን አትለይም ነበረ:: የህሉቱ መፋቀር መንፈሳዊ ቅናት ያሳደረበት ሥራ አስኪያጅ ነበረ በሚቀጥለው ተውኔት ውስጥ ለምከር ዋነኛውን ገቢር የሰጠው:: ምከርም ሌት ተቀን በመለማመዱ ትያትሩ ተደናቂነትን አተረፈ:: ለአራት ወራት ተከሉም በተከታታይ ሲታይ ቆየ:: ትያትሩን ለማየት ከቦስተን ከተማ ሕዝብ ጥያቄ በመቅረቡም ምከርና ሶላንጅ ወደዚያ ሄዱ:: ለስድስት ዓመታት ያህል ዓይኗን ያላየው እህቱ ኢሊን ትዝ ያለችውም ያን ጊዜ ነበረ::

ኢሊንን ሊያገኛት የቻለው ቀድሞ ከምትሰራበት ቡና ቤት ሔዶ በማጠያየቅ ነበረ:: መርከበኛ የነበረም ባል አግብታ ከከተማው ወጣ ካለ መንደር ውስጥ እንደምትኖር ሰማ:: ኢሊን ከዱሮውም ይልቅ አሁን ከስታ ነበረ:: እነምከርም በደረሱበት ጊዜ መጠጥ በማብዛቷም ሊሆን ይችላል አነጋገሯ ሁሉ ልክ አልነበረም:: ባሏም የርሷው ቢጤ ሰካራም ነበረ:: ከሶላንጅም ጋር ካስተዋወቃቸው በኋላ ብዙም ሳይቆይ ወደ አረፉበት ሆቴል ተመለሱ:: ሶላንጅም ኢሊንን በመታዘቧ የምከር እህት ናት ብላ ለማመን ከቶም አልቻለችም ነበረ:: ምከር መልከ መልካምና ደልዳላ ቁመና ያለው ነው:: ኢሊን ግን በጣም ቀጭን ነበረች:: የርሷ ፀጉር ቀይ ነው:: የምከር ግን ጥቁር ነው:: በመልካም አነጋገርም ጭራሽ አይመሳሰሉም ነበረ:: ምከር ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መጠጥ መጠጣት ቢጀምርም እንደ ኢሊን ሱሰኛ አልነበረም:: ስለዚህ ሶላንጅ ልትረሳት፣ ስለርሷም ዳግመኛ ለምከር እንደማታነሳበት ወሰነች::

ከቦስተን ወደ ኒውዮርክ ተመልሰው ብዙም ሳይቆዩ ምከርን ታላቅ ዕድል ጠበቀው:: «ዋይልደርነስ» በሚለው ታላቅ ተውኔት ውስጥ ለምከር ዋነኛውን ክፍል ተሰጠው:: ብዙም ገቢ የሚያስገኝ መሆኑ ስለሚታወቅ፣ ምከርን በመወከል የተፈራረመለት ፓተርሰን ነበረ:: ዕለቱንም ሻምፓኝ በመክፈት አከበሩት:: በዚያንም ዕለት ምሽት ነበረ ምከር ሌላም የምስራች የሰማው:: ሶላንጅ መፀነሷን ስትነግረው ከመጠን በላይ ተደሰተ:: ከእንግዲህ ምከር ሀብትም፣ ዝናም አግኝቷል:: የርሱንና የሶላንጅን ደስታ ፍፁም ለማድረግ ደግሞ ልጅ ሊያገኙ ነው:: የምከር ምኞት ሊሟላለት ነው ማለት ነው::





ምከር ከቀድሞውም ይልቅ የተዋጣለት ተዋናይ መሆኑን በአዲሱ ተውኔት አስመሰከረ:: ስለ ተውኔቱም ሆነ ስለ መሪ ተዋንያኑ ምከር ጋዜጦች ሰፋ አድርገው በየዓምዳቸው በመፃፍ አድናቆታቸውን ገለፁ:: በተውኔቱም ውስጥ የምከር ፍቅረኛ ሆና የሰራችው ባርባራ ጆርጅ ከምከር ያላነሰ ሙገሳ አገኘች::

## ምዕራፍ አራት

የ'ዋይልደርነስ' ተውኔት ለብዙ ወራት በተከታታይ ሲታይ ከረመ:: የምክርም ስምና ዝና በመላው አሜሪካ ተናኝቶ ነበረ:: በመዝጊያውም ዕለት ሶላንጅና ፓተርሰን በትያትር ቤቱ ተገኝተው ነበረ:: ተውኔቱም ወደ መጋመሱ ሲቃረብ ሶላንጅን ምጥ አፋፍሞ ያዛት:: ወደ ሐኪም ቤትም የወሰዳት ፓተርሰን ነበረ:: በማግሥቱ ጠዋት ላይ ሴት ልጅ ተገላገለች:: የተወለደችው እራስ እንደ አባቷ ጥቁር ፀጉር ነበራት:: የእናቷንም አረንጓዴ ዓይኖች ወርሳለች:: በጣምም የምታምር ልጅ ነበረች:: ከፓተርሰንም የቀረበ ወዳጅ ስላልነበራቸው የክርስትና አባቷ እንዲሆን ተሰመነ:: ማርጆሪም፣ ባታፈቅራቸውም የፓተርሰን ባለቤት በመሆኗ ብቻ ለእራሷ የክርስትና እናት ሆነቻት:: በዚያንም ዕለት ፓተርሰን ለክርስትና ልጁ ሂላሪ የሚል ስም አወጣላት::

እነምክር መኖሪያ ቤታቸውን የቀየሩት ቀደም ሲል ነበረ:: ሰፊ ቤት እንደሚያስፈልጋቸው ግልፅ ነው:: የምክር እንግዶች ቁጥር እየጨመረ በመሔዱ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ብዙ የተውኔት አዘጋጆች ከቤቱ በመመላለስ ከነርሱ ጋር አብሮ እንዲሰራ ጥያቄ አቅርበውለታል:: በመጨረሻ ላይ አንዱን ደስ ያለውን መምረጥ ነበረበት:: ልምምዱም ጊዜ የሚፈጅና ከባድ ቢሆንም ምክር ለሶላንጅና ለሂላሪ ፍቅሩን የሚገልፅባቸው ሰዓታት ቆጥቦ ነበረ::

ሂላሪ በዘጠኝ ወሯ እንደልቧ እየዳኸች ቤቱን ስታዳርስ ነበረ የምትውለው:: በተለይ ለአባቷ የነበራት ፍቅር ለየት ያለ ነበረ:: ከመታጠቢያ ቤት ገብቶ ፂሙን ሲላጭ ትመጣና ከእግሩ ትጠመጠ ማለች:: ከፅህፈት ጠረጴዛው ተቀምጦም በመሥራት ላይ ከሆነ 'ባ፣ባ፣ባ' እያለች እስቲያቅፋት ድረስ ዙሪያውን ትዞራለች:: ምክር ልጅ ከማፍቀሩ የተነሳ ሌላም ልጅ እንዲወለድለት ጓጉቶ ነበረ:: ሆኖም ሶላንጅ ጥቂት መቆየቱን ፈለገች:: ሂላሪን በእንክብካቤ ማሳደጉን መረጠች:: የባልና የሚስቱም ፍቅር እየተጠናከረ ሔደ:: የሶላንጅም ውበት ከቀድሞው ይልቅ አሁን እያበበ መጣ:: ጋዜጦችና መፅሔቶች ፎቶግራፏን እያወጡ ስለ





ቁንጅናዋ ማወደስ ጀምረው ነበረ:: ቅርጿም ሆነ መልኳ ለፊልም ተዋናይነት ወይንም ለሞዴልነት የተሰጠ በመሆኑ ይህንኑ በማስመልከት አንዳንድ ድርጅቶች አነጋግረዋት ነበረ:: እርሷ ግን ጥሩ የቤት እመቤት ሆና ባሏንና ልጇን በማፍቀር መወሰኑን መረጠች::

ሶላንጅ ሁለተኛ ልጇን የፀነሰችው ሂላሪ አራት ዓመት ከሞላት በኋላ ነበረ:: ምጥም በያዛት ጊዜ አሁንም ወደ ሆስፒታል የወሰዳት ፓተርሰን ነው:: ሶላንጅ ሴት ልጅ ደገመች:: እራሷም ልክ እንደናቷ ወርቃማ ፀጉርና አረንጓዴ ዓይኖች ያሏት ነበረች:: ፓተርሰን የምስራቹን ለምክር ሊያበስረው ፈልጎ ልምምድ ወደ ሚያደርግበት ትያትር ቤት ስልክ ቢደውልም ሊያገኘው አልቻለም:: በማጠያየቅ እንደተረዳውም ምክር ልምምዱን ጨርሶ አብራው በመሪ ተዋንያንነት ከምትሰራው ሴት ጋር ተያይዘው መሄዳቸውን አወቀ:: ወደ መኖሪያ ቤቱም እንዳልተመለሰ አረጋግጧል:: የምክር ጠባይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መለዋወጡን ፓተርሰን በሚገባ ተረድቶታል::

ምክር ወደ ሆስፒታል የመጣው በማግስቱ ረፋዱ ላይ ነበረ:: በዚህም ሶላንጅ ቅሬታ ገብቷታል:: ሌሊቱን ሁሉ ከአሁን አሁን ይመጣል ስትል ስትጠብቀው ነው ያደረችው:: እንደ ደረሰም እግረ መንገዱን ገዝቶላት የነበረውን የአልማዝ ቀለበትና የወርቅ አምባር ሰጣት:: የሶላንጅ አረንጓዴ ዓይኖች እንደ ወትሮው ደስታን አላንፀባረቁም:: የት ነው ያደርከው? የሚል የጥርጣሬ ጥያቄ የሚነበብባቸው ይመስሉ ነበረ::

ሶላንጅን ወደ ሆስፒታል እንዳመጣት ሁሉ ወደ ቤትም መልሶ የወሰዳት ፓተርሰን ነበረ:: ምክር ግን በልምምዱ ከባድነት እያመካኘ እንደ ወትሮው ወደ ቤት ሰዓት ጠብቆ መምጣት ትቷል:: ቢመጣም እንኳን መሰወጡን ሶላንጅ አይታለች:: ከልብሱም ላይ ጠረኑ የርሷ ያልሆነ ሽቶ ሸቷታል:: ሆኖም ሁሉንም በትዕግስት ልታሳልፈው ፈለገች:: በምክር ላይ ካደረባት ቅናትና ጥርጣሬ ይልቅ ለርሱ ያላት ፍቅር ያመዝን ነበረ:: ስለዚህ ልቦናው እስኪመለስለት በሰላም ልትተወው ወሰነች::

እራሷም ልጅ ክርስትና በተነሳችበት ዕለት ምክር በሉል ያጌጠ የአንገት ድሪ ስጦታ አበረከተላት:: ከፍተኛ ገንዘብ ያወጣበት መሆኑን ሶላንጅ ታውቃለች:: ሰበደሉ ማካካሻ መሆኑን ሶላንጅ ተስምቷታል:: በተለይም ለእራሷ የክርስትና አባት ለሆነው ለቅርብ ወዳጃቸው ለፓተርሰን ደግሞ የስጦታው መልዕክት በይበልጥ ግልፅ ሆኖለታል:: የእራሷን ልጅ

የክርስትና ዕለት በፍቅር በደስታ አከብረውት ዋሉ:: ፓተርሰንም ለአዲሷ የክርስትና ልጁ አሌክሳንድራ የሚል ስም አወጣላት::

ምክር በርግጥም የተፀፀተ መስሎ ነበረ:: ለጥቂት ቀናትም ለቤተሰቡ የነበረውን ፍቅርና አክብሮት ሲገልፅ ከረመ:: መሥራት ስለነበረበት ደግሞ ወደ ትያትር ቤቶች መሔድ ነበረበት:: አዲስም ተውኔት በመዘጋጀት ላይ ስለነበረ ምክር ውሎ ባደረ ቁጥር የተለመደ ሰዓት ማሳለፉን አመጣ:: ቆየትም ሲል እስከናካቴው ማደር ጀመረ:: ሶላንጅን ሊያፅናና የሚችል አንድ ሰው ብቻ ነበረ:: ፓተርሰን በሶላንጅና በምክር መካከል ገብታ ስለምታምሳቸው አዲሷ ወጣት ኮረዳ አንድ በአንድ ደርሶበታል:: ለሶላንጅ ግን ሊነግራት አልፈለገም::

አንድ ቀን ፓተርሰንን ምሳ ጋበዘችውና በመመገብ ላይ እንዳሉ "የናንተስ ጋብቻ እንዴት ነው? ልጅስ የማትወልዱበት ምክንያት ለምንድነው?" ስትል ጠየቀችው::

የፓተርሰን ሚስት ማርጆሪ ልጅ መውለድ የምትፈልግ ሴት አልነበረችም:: ፓተርሰንም ሲበዛ - ሲበዛ እንደምትንቀው ያውቅ ስለነበረ "ሴትን ልጅ ካልወሰድሽልኝ ብሎ ማስገደድ አይቻልም:: ተገዳ እንኳን ብትወልድ ደግሞ ደህና እናት አይወጣትም:: ትርፉ የሚወለደውን ህፃን ማሰቃየት ነው:: ዕድለኛ ብሆን ኖሮ እንዳንቺ ያለች የተባረከች ሚስት ባጋጠመኝ ነበረ" አላት:: እንደ እውነቱ የሶላንጅ ሁለቱ ህፃናት ልጆች መልአክ ይመስሉ ነበረ:: የሂላሪ መልክና ፀጉር የአባቷን ይመስላል:: ዓይኖቿ ደግሞ እንደ እናቷ ዓይኖች ትልልቅና አረንጓዴ ነበሩ:: እራሷ አሌክሳንድራ ግን በምንም በምንም ቁርጥ እናቷን ነበረ የምትመስለው:: ፓተርሰን ሶላንጅን አየት ሲያደርጋት ከፊቷ ላይ የትካዜ ምልክት አነበበ:: ስለምክርና ስለ አዲሲቷ ተዋናይ ፍቅረኛው ድፍን የኒውዮርክ ነዋሪ የማያውቀው ነው:: ስለዚህም ሶላንጅም የማታውቅበት ምክንያት እንዳልነበረ ፓተርሰን ተሰማውና "ምን ሆነሻል ሶላንጅ? ለምን ትካዜ ይገባሻል?" ሲል ሊያፅናናት ሞከረ::

"የእኔና የምክር ጋብቻ እንደ ዱሮው ጤናማ ይመስልሃል?" አለችው ዓይኖቿ እንባ እያቀረሩ::

"ካላበደ በስተቀር ምክር በጤናው እንደዚህ ይሆናል ብዬ አልገምትም:: ዕድሜው ገና ሰላሳ አንድ ዓመት ነው:: ግን በዓለም ውስጥ ዝነኛ ሰው ለመሆን በቅቷል:: በጣምም ሀብታም ሆኗል:: ይህ ሁሉ





ተጨማምሮ ይሆን የሚሰራውን ያሳጣው? አንቺን የመሰለች ሴት ለማግኘት ማንም ቢሆን ቀኝ እጁን በሰጠ" አለ ፓተርሰን ዓይን ዓይኗን እያየ::

"እጅ ለእኔ ምን ያደርግልኛል ፓተርሰን?" አለችና ዓይኖቿን አባበለች:: ቀና ብላም ፈገግ አለችና፣ "እኔ እጅ አልፈልግም የምፈልገው ልብ ነው:: የምክርን ልብ ብቻ:: ጥፋት ሰርቶ በመጣ ቁጥር ለመደለያ ጌጣ ጌጥ ገዝቶልኝ ይመጣል:: በሳጥን የሚሞላ ዕንቁና አልማዝ አለኝ:: ግን ያ ሁሉ ለእኔ ምኔም አይደለም:: ድሃ ሆኜ ምክር የግሌ ቢሆንልኝ እመርጣለሁ" አለች ሶላንጅ::

"ይገባኛል" አለና ፓተርሰን በተራው ሲተክዝ ቆየ:: ፓተርሰን ለምክር ሙሉ ነገረ ፈጅ ከሆነ ውሎ አድሯል:: በመሆኑም ስለምክር ሀብት ይዞታ ያውቃል:: ሶላንጅ ስለ አልማዝና ዕንቁ ስታወራ ትዝ ያለው ነገር ነበረ:: ለርሷ ብቻ አልነበረም ምክር አልማዝና ዕንቁ የሚገዛው:: በየጊዜው የሚቀያይራቸውን ፍቅረኞቹን ዋጋቸው በናረ ጌጣ ጌጦች ያስጌጥም ነበረ:: ለምክር ገንዘብ መጫወቻው ሆኗል:: ሰሆነ ላልሆነም መርጨት፣ መርጨት ነበረ ሥራው:: በየቀኑ የሚቀያይራቸው ልብሶች በእንግሊዝ ሀገር የተሰሩ ሱፎች ነበሩ:: ከህፃናቱ አሻንጉሊት ጀምሮ የሐር ቀሚሶቻቸውም ሆኑ የሶላንጅ ካፖርቶች ጭምር የሚመጡላቸው ከፓሪስ እየተገዙ ነው:: ፓተርሰን ምክርን ገንዘብ እንዲቆጥብ ደጋግሞ መክሮታል:: የምክር ገንዘብ ግን በገባበት መጠን መውጫ ቀዳዳ ይፈልጋል::

"ምን ማድረግ እንደሚሻለኝ አላውቅም:: አምርሬ ልናገረው እቆርጥና ወዲያውኑ ደግሞ ሆዴ ይዋልልብኛል:: ምክር ተመልሶ የእኔ መሆኑ ላይቀር አላስቀይመው ስል አስባለሁ:: እስካሁንም መመለሱ አልቀረም" አለችና የፓተርሰንን ዓይኖች እያየች ፈገግ አለች::

ፓተርሰንም በአድናቆት ሲመለከታት ቆየና "እንደ አሜሪካዊ ሴቶች ሳይሆን ሚዛናዊ አመለካከት ያለሽ ልጅ ነሽ:: ይህን ጊዜ የአሜሪካ ሴቶች ቢሆኑ ኑሮ ስንት ጉድ ባፈሉ ነበረ:: ባላቸውን በምስጢር የሚከታተል ሰው ይቀጥራሉ:: ሰውየው መረጃ ያሰባስባል:: ባልየውም በህግ ይከሰስና ከፍተኛ ካሳ እንዲከፍ ይደረጋል" አለ ፓተርሰን::

"ካሳ አልክ ፓተርሰን? የእኔ ፍላጐት መቼ ካሳ ሆነና:: የምፈልገው የምወደው ባሌን ብቻ ነው" አለችና እንደ ልማዷ ፈገግ አለች:: ቀጥላም "ሁሉም ነገር እንደሚያልፍ፣ እንደሚበርድለትም አውቃለሁ::

ተዋናይ በመሆኑ በቀላሉ ለብልግና ሊገፋፋ እንደሚችል ይታወቀኛል፡፡ የሥራው ባህርይ ከተለያዩ ቆንጆ ሴቶች ጋር ስለሚያገናኘው ጥፋተኛ ነው ስል መቶ በመቶ አልፈርድበትም» አለች ሶላንጅ፡፡

"እንዳልሽውም ለምክር ጥፋት መንስኤ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ በመሆኑም መቶ በመቶ ላትፈርጅበት ትችያለሽ፡፡ ግን ከምክንያቶቹ ውስጥ አንደኛዋ እራስሽ መሆንሽን ታውቂያለሽ?" አላት ፓተርሰን፡፡

"ለምን?" አለችው ሶላንጅ በመገረም፡፡

"እንደ ጣኦት ታመልኪዋለሽ" እላት ፓተርሰን፡፡

"ማምለክ ነው? ሲበዛ ስለምወደው ህይወቴን ጭምር እሰዋለታለሁ" አለች ሶላንጅ ከልቧ፡፡

"እንግዲህ መበርታት ይኖርብሻል፣ ወደ አንቺ መመለሱ የማይቀር ነው፡፡ አሁን የሚያደርገው ሁሉ ለርሱ ጨዋታ መስሎ ነው የሚታየው፡፡ ይህንንም አውቀሽ መፅናናቱ ላይ ነው ቁምነገሩ" አለ ፓተርሰን፡፡

ጥሩ ምክር ነበረ በመጨረሻ ላይ ፓተርሰን የሰጣት፡፡ እርሱም እንዳለው ታገሰች፡፡ ባሏም ከስድስት ወራት በኋላ ወደርሷ 'ማሪኝ' ብሎ ተመለሰ፡፡ በዚያ ተውኔት ውስጥ ከምክር ጋር ተካፋይ የነበረችው ልጅ ሚስቱን እንዲፈታና እንዲያገባት ትነዘንዘው ነበረ፡፡ ምክር ግን ለጊዜው ሶላንጅን በሌላ ሴት ቢቀይራትም ልቡን እንድ ጊዜ ፓሪስ ጎዳና ላይ ላያት ባለወርቃማ ፀጉርና ባለ አረንጓዴ ዓይኖች ለግላጋ ወጣት ሰጥቶት ስለነበረ እንደማይቻል ነገራት፡፡ ያቺም ተዋናይ ራሷን ለመግደል ሞከራ ነበረ፡፡ ይህም ለርሷና ለምክር መቆራረጫቸው ሆነ፡፡

ምክር 'ማሪኝ' ብሎ ወደ ሶላንጅ ከተመለሰ በኋላ ቤተሰቡን ይዞ ለዕረፍት ወደ አውሮፓ ሔደ፡፡

ምክር ቀደም ሲል ባደረገው ዝግጅት መሰረት ወደ ተከራየው ሆቴል አመሩ፡፡ ምክር ወደ ሶላንጅ ሔደና አንገቷን አቅፎ ራሱን ከትከሻዋ ላይ አደረገና አለቀሰ፡፡ ሶላንጅም በተራዋ ከደረቷ አስጠግታ አቀፈችውና የደስታ እንባ አነባች፡፡ እየተንከባለለ የሚወርደው እምባዋም የምክርን ጥቁር ፀጉር እራሰው፡፡ እንዳቀፈችውም ወደ መኝታ ቤት ገቡ፡፡





ሶላንጅ ከዘጠኝ ዓመታት በፊት ክብረንፅህናዋን በፍቅር ለምክር እንደሰጠችው ዛሬም ምክር ቀሚሷን አወለቀላት፡፡ እንደ ዱሮአቸውም ተኙ፡፡ የዱሮውም ትዝታ በአዲስ ኃይል ታደሰ፡፡ ለመሆኑ ማን አሰቦት ነበረ ኩሩዋ ሶላንጅ እንድ የአሜሪካ ተራ ወታደር ትወዳለች ብሎ? ማንስ ገምቶ ነበረ ያች ብቸኛዋ ሶላንጅ በዝነኛ ተዋንያኑ በምክር ሚስትነቷ የመላ አሜሪካ ሴቶች መቀናኛ ትሆናለች ብሎ? ከቶ ማንስ ነበረ የተጠራጠረ እንደ መልአክ የሚያማምሩት የነሂላሪና አሌክሳንድራ እናት ለመሆን ትበቃለች ብሎ? ማንም አልነበረም፡፡

ከሶላንጅም የቀድሞ ቤት ፊት ለፊት ወደ ነበረው ቡና ቤት ሔዱ፡፡ መንገዱንም ያቋረጡት እጅ ለእጅ እንደ ተያያዙ ነው፡፡ እንደገቡም ቀጥታ የሔዱት ወደ ቡና ቤቱ ባለቤት ነበረ፡፡ "ደህና ነዎት ሙሴ ዡልያን" ስትል ሶላንጅ ሰላምታ ለጥታው ፈገግ አለች፡፡ ባለቤቱ እንጼ እርሷን እንጼ ምክርን ሲያይ ቆየና ራሱን ይዞ "ሶላንጅ! ማድሟዜል ሶላንጅ!" አለና ጮኸ፡፡ ከዚያም እቅፍ አደረገና ግንቧሯን ከሳማት በኋላ ምክርን ፈገግታ አሳይቶ ጨበጠው፤ ቶሎ አለናም ያልተያዘ ጠረጴዛ በዓይኑ ፈልጐ ወደዚያ ሁለቱንም አቅፎ ወሰዳቸው፡፡ ከባለቤቱም ጋር ብዙ ሲጨዋወቱ ቆዩና በፓሪስ ለሰስት ቀናት ያህል ስለሚቆዩ ዳግመኛ እንደሚገናኙ ነግረውት ወጡ፡፡ ከዚያም ታክሲ ይዘው ልጆቻቸው ወደ አረፉበት ሆቴል አመሩ፡፡

ከልጆቻቸውም ጋር የራት ሰዓት እስከሚደርስ አመሹ፡፡ ሕፃናቱም መተኛታቸውን እንዳረጋገጡ ሞግዚቷን አደራ ብለው እነርሱም ራት ለመብላት ሔዱ፡፡ በምክርና ሶላንጅ ጐን ያለፈ የፓሪስ ነዋሪ ገልመጥ ብሎ በአድናቆት ደግሞ ሳያያቸው እያልፍም፡፡ በገቡበትም ሆቴል ውስጥ የነበረው ማንኛውም ሰው እትኩሮቱ በሁለቱ ላይ ነበረ፡፡ በመልካቸው፣ በቁመናቸው፣ በአለባበሳቸው የሚያስቀኑ ባልና ሚስት ነበሩ፡፡

ራት ከተበላ በኋላ ምክርና ሶላንጅ በሰዬን ወንዝ አጠገብ እንደ ዱሮአቸው እጅ ለእጅ ተያይዘው ሲንሸራሸሩ አመሹ፡፡ ሲደክማቸውም ከአንድ ቡና ቤት አረፍ ብለው ቡና ጠጡ፡፡ እጅ ለእጅ እንደ ተያያዙም ወደ መኝታ ክፍላቸው ተመለሱ፡፡ እንደ አሜሪካዊ ምክርና ሶላንጅ ሳይሆን ሁለቱም እንደ ፓሪሉ ምክርና ሶላንጅ ሲፋቀሩ አደሩ፡፡ ፍቅራቸው ታደሰ፡፡ በአዲስ ማህተምም ታተመ፡፡

በማግስቱ፤ ህፃናት ልጆቻቸውን ይዘው ፓሪስን ሲጐበኙ ዋሉ፡፡ ሂላሪ በዚያን ጊዜ ዕድሜዋ እራት ዓመት ቢሆንም እንደ ዕድሜዋ ጨቅላነት

ዋዛ ልጅ አልነበረችም። በዚያን ዕድሜዋ ከእናቷ የተማረችውን ፈረንሳይኛ ና የአባቷ ቋንቋ የሆነውን እንግሊዘኛ መናገር ትችል ነበረ። አሌክሳንድራ ግን ገና አንድ ዓመት ያልሞላት አራስ ነበረች። ሂላሪ በአንድ እጇ ያባቷን በሌላው እጇ የእናቷን እጅ ይዛ ከሥር ከሥራቸው ድክ ድክ ስትል አሌክሳንድራ ደግሞ በሞግዚት እቅፍ ነበረች። የፓሪስን ዝነኛ ሱቆች አንድ በአንድ አዩአቸው። ሶላንጅ አልፈልግም ብትልም ከጊቨንኪ፣ ከቻነልና ከዱዋር የልብስ ሱቆች በደርዘን የሚቆጠሩ የተለያዩ ዘመናዊ ልብሶች ራሱ እየመረጠ ገዛላት። ለህፃናት ልጆቹም እንደዚሁ። ከካርቲየር የጌጣ ጌጥ ሱቅ ሲደርሱም በውበቱ ዓይኑን የማረከውን አንድ በዕንቁና በሉል ያጌጠ የእጅ አንባር ካልገዛሁልሽ አለ። ያን ጊዜ ግን አሻፈረኝ ስትል ሱቁን ጥላ እስከ መውጣት ደርሳ ነበረ። እርሱ ግን ገዛና እንዳትነቃበት ከኋላ ኪሱ ደበቀው።

በዚያን ምሽት ዎከርና ሶላንጅ ለልጆቻቸው መኝታ በያዙበት በሪትዝ ሆቴል ራት በሉ። በማግስቱ ፓሪስን በለቀቁበት ምሽት ደግሞ በማክሲምና በቱር ደ አርጃ ሆቴሎች አመሹ። ወደ ኒውዮርክም ለመብረር እኩለ ሌሊት ላይ በአውሮፕላን ተሳፈሩ። አውሮፕላኑም ከመሬት አኮብኩቦ እንደ ተነሳ ነበረ ዎከር ደብቆት የነበረውን አምባር ከኪሱ አውጥቶ ሳታስበው ከሶላንጅ እጅ ውስጥ ያጠለቀው። ያደረገውን ስታይ ሳቀችና «ሞዛዛው ዎከር» ብላ ከንፈሩን ሳመችው። እርሱም ከደረቱ እቅፍ አደረጋት። እፎይም ሲል በረጅሙ ተነፈሰ። ምናልባት ሶላንጅ ፓሪስ ከደረሰች በኋላ ትከዳኛለች የሚል ሥጋት ገብቶት ስንብቶ ይሆን? ሶላንጅ አሁንም ካለ ዎከር ሌላ ህይወት የሌላት ሴት ነበረች።

ኒውዮርክ መመለሳቸውን ሰምቶ 'እንኳን ደህና መጣችሁ' ሊላቸው የመጣው እንግዳ ሁሉ በሶላንጅ ውበት መታደስ ያልተገረመ አልነበረም። ተመልሳ የአስራ ዘጠኝ ዓመቷን ሶላንጅ ነበረ የመሰለችው። ከእንግዶቹ አንዷ ዝነኛዋ የፊልም ተዋናይ ማርሲን ምንሮው 'ምነው እንቺን ባደረገኝ?' ስትል አፍ አውጥታ አድናቆቷን ገልፃላታለች። ለምንስ የፊልም ተዋናይ እንደማትሆንም ጠይቃት ነበረ። ሶላንጅ ግን «በአንድ ቤት ውስጥ ሁለት ኮከቦች ካሉ ሲዞሩ ሲጋጩ ስለሚችሉ አንድ ብቻ ይበቃል» ስትል እየሳቀች መልሳላት ነበረ። በአመላለሷም የነበሩት እንግዶች ሁሉ አድናቆታቸውን በጭብጨባ ገልፀዋል። ዎከርም እንደዚያን ቀን በሶላንጅ የአእምሮ ብስለት ኮርቶባት አያውቅም።





ብዙም ሳይቆይ ዎከር በአንድ ተውኔት ውስጥ እንዲካፈል ጥያቄ ቀርቦለት ነበረ። ዎከር ግን አልተቀበለውም። በዎከር አቋም ያልተገረመ ሰው አልነበረም። ከጥቂት ቀናት በኋላ ከሆሊውድ በፊልም ተዋናይነት እንዲሰራ ሌላ ጥያቄ ቀረበለት። እሺ ከማለቱ በፊት የፊልሙን ይዘት መረመረ። ዎከርም የሚጫወተው ሚና ከሴት ተዋናይ ጋር የማያቀራርብ መሆኑን እንዳረጋገጠም ጥያቄውን ተቀበለ። ቤተሰቡንም ይዞ ወደ ሆሊውድ ሔደ። በቢቨርሊ ሂልስ ሆቴል ግቢ ውስጥ ከተሰሩት የግል መኖሪያ ቤቶች አንዱን ተከራይቶ ቤተሰቡን ከዚያ አሳረፈ። ለአንድ ዓመት ያህልም በዚያ ቆዩ።

ዎከር ከፊልም ተዋናይነት ይልቅ ከተመልካች ጋር በቀጥታ ለሚያገናኘው ለትያትር ተዋናይነት ምርጫ ነበረው። ዓመሉንም ቢሆን አሻሽሏል። የሆሊውድ ቆነጃጅት በልዩ ልዩ ዘዴ ሊያጠምዱት ሞከረው አልተሳካላቸውም። ዎከር ለሶላንጅ ታማኝ ባል ሆኗል። ከእንግዲህ ወደ ኒውዮርክ መመለሱንና እንደ ቀድሞው በትያትር ተዋናይነቱ መቀጠሉን ሶላንጅም ብትሆን ደግፋው ነበረ።

ወደ ኒውዮርክ እንደተመለሰም ብዙ የትያትር ቤቶች በሚያዘጋጁት ተውኔት ውስጥ እንዲካፈል ጠየቁት። የቀረቡለትንም ጥያቄዎች አንስቶ ከሶላንጅና ከፓተርሰን ጋር ተመካከሩ። የሶስቱም ምርጫ ተመሳሳይ ሆነ። ዎከርም ፓተርሰንን ይዞ ከመረጡት ትያትር ቤት ሥራ አስኪያጅ ጋር ውለታ ተፈራረሙ። ለዎከርም በቅድሚያ የአንድ ሚሊዮን ብር ክፍያ ተደረገለት።

ዎከር ከልቡ ቆርጦ መለማመድ ጀመረ። ተውኔቱ ደግሞ የፍቅር ስለነበረ አቻው ከነበረችው መሪ ሴት ተዋናይ ጋር ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ፍቅረኛዋ መስሎ መቅረብ ነበረበት። ያቅፋታል፣ ታቅፈዋለች፤ ይሰማታል፤ ትስመዋለች፤ ይተኛል፤ ትተኛለች። ልምምዱ ለስድስት ወራት ያለማቋረጥ ቀጠለ። አብራው የምትሰራው ልጅ በዎከር ፍቅር የተነደፈችው በመጀመሪያው ቀን ከሳማት በኋላ ነበረ። ከዚያም ዎከርን የምታቅፈው የምትስመው እንደ ተዋናይ ሳይሆን እንደ ፍቅረኛ ሆነ። የዎከር ልብ ተገዘገዘ... ተገዘገዘና መጨረሻ ላይ ተሸነፈ። መሸነፋም የአደባባይ ምስጢር ሆነ። እንደ በፊቱ ሁሉ ሶላንጅን በልዩ ልዩ ስጦታዎች ሊያባብላት ሞከረ። ለልጆቹም የማይገዛው ነገር አልነበረም።

አንድ ቀን ለሶላንጅ “ጐሲፕ” የተባለው መፅሔት በፖስታ ቤት በኩል ደረሳት፣ የላከላት ግን ማን እንደሆነ ገና ሽፋኑን ከማየቷ ገብቷታል:: የምከርና የአዲሱ ፍቅረኛው ፎቶግራፍ በጉልህ ተቀርፆበታል:: በሥሩም “ለምን አይጋቡም?” የሚል ርዕስ በትልልቅ ፊደላት ተፅፎበታል:: ሊጋቡ የማይችሉበትን ምክንያት የሚዘረዝረው ፅሑፍ የሚገኝበትን ገፅ የሚያመለክት ቁጥርም ሰፍሯል:: 'ለጁን አይጋቡም' ስትል ሶላንጅ መልሳ መላልሳ አሰበች:: ሌላ ርዕስ ቢሆን ኖሮ ሶላንጅ ሳታነበውም ትችል ነበረ:: መፅሔቱንም ቀዳዳ ከቅርጫት ውስጥ በወረወረችው:: ግን ይህ ርዕስ ሕሊናዋን ጨምድዶ ያዘው:: መፅሄቱን ታስቀምጥና መልሳ ታነሳዋለች:: ለወትሮው ምከር ሌላ ሴት ቢያፈቅርም ተመልሶ የርሷ እንደሚሆን እርግጠኛ ነበረች::

መፅሔቱን ሳታነበው ሶስት ቀናት አለፉ:: ግን ያ ከአእምሮዋ የተቆራኘው ርዕስ የመንፈስ እረፍት ነሳት:: በአራተኛው ቀን የመፅሔቱን ገፆች ገለጠች:: ማንበብም ጀመረች:: ምከር አዲሲቷን ፍቅረኛውን ቢያገባ ሊገጥሙት የሚችሉት ችግሮች ደረጃ በደረጃ ተዘርዝረዋል:: እንደ ማንኛ ውም ትዳር ሁሉ ባል ሚስቱን ፈትቶ ሌላ ለማግባት ቢፈልግ የሚገጥ መውን ዓይነት ችግሮች ነበረ:: የሞራል ካሳ፣ የንብረት ክፍፍል፣ ልጅ የማሳደግ ኃላፊነትና....ወዘተ ነበሩ:: የዚህ ሁሉ መፃፍ ሶላንጅን ቅንጣት ያህል አልደነቃትም:: ስለዚህም ማንበቧን ቀጠለች:: በፅሑፉ መደምደሚያ ላይ የሰፈረው ጥያቄ ግን የሚከነክን ነበረ:: “ታዲያ ይህ ሁሉ ቀላል ሆኖ ሳለ ለምንድነው ምከር ሶላንጅን ፈትቶ አዲሲቷን ፍቅረኛውን የማያገባው?” ይላል:: ለጥያቄውም የመፅሔቱ የዝግጅት ክፍል የመሰለውን መልስ አስፍሯል:: “በመተተኛዋ የዱእርኮል ጎዳና ቅሬ በመተብተቡ ነው” በሚሉት ቃላት ፅሑፉ ተደምድሟል::

እርግጥ ሶላንጅና ምከር ለመጀመሪያ ጊዜ የተገናኙት በፓሪሱ የዱእርኮል ጎዳና ላይ ነው:: በቅድሚያም ምከር አያት እንጂ እርሷ አላየችውም:: ሊያናግራትም ሞከረ እንጂ አላናገረችውም:: ከቤቷ በራፍ ልታባርረው ሞከረች እንጂ እንዲገባ አልጋበዘችውም:: ሶላንጅ እንደ ሌሎቹ የፓሪስ ልጃገረዶች የአሜሪካን ወታደሮች ለማጥመድ ከቤቷ አምራና ተኳኩላ አልወጣችም:: እንደ ሌሎቹም ፈገግታ አሳይታ፣ ዳሌዋን እውረግ ርጋና ሽንጧን ሰብቃ በፍቅር የማጥመድ ፍላጐት አልነበራትም:: እና መተተኛ መባል አልነበረባትም:: ደግሞ ቅሬም አልነበረችም:: ቅሬ የሴት ወሮበላ፣ መሸተኛ፣ ባለጌና ጋለሞታ ማለት ነው:: አንደኛውም ቅፅል ለሶላንጅ አይስማማም:: በመፅሔቱ ላይ የወጣው ፅሑፍ ምንጭ የምከር





አዲሷ ፍቅረኛ መሆኗን ሶላንጅ ገብቷታል:: መፅሔቱም እንዲደርሳት ያደረገችው እርሷው ራሷ ስለመሆኗ ሶላንጅ አልተጠራጠረችም:: ዓላማዋም ሶላንጅ በመሰደቧ ተናዳ ባሏን ለመፍታት ሕጋዊ ጥያቄ እንድታቀርብ ለመገፋፋት ነበረ::

አንድ ቀን ከምከር ጋር ቁርስ በመብላት ላይ እንዳሉ ሶላንጅ መፅሔቱን አሳየችውና፤ “ለምን ታሰድበኛለህ?” አለችው:: ምከርም ቢሆን ያንን መፅሔት አላየውም ነበረ:: ከአፉ ያደረሰውን ሹካ መልሶ ከሳህኑ ላይ አስቀመጠና ማንበብ ጀመረ:: እንብቦም እንደጨረሰ ከመቀመጫው ተነሳና ከሶላንጅ እግር ስር ሑዶ ተንበረከከ:: 'ማሪኝም' አለና ከጭኖቿ ላይ ተደፋ፤ ፀጉሩንም ስታሻሽው ቆየችና ከተንበረከከበት ደግፋ እያስነሳችው:-

“አዲስ ተውኔት፣ አዲስ ሴት... ዋ ምከር!” አለችና የሌባ ጣቷን አወዛወዘችበት:: ከትላልቅ አረንጓዴ ዓይኖቿ የሚስረቀረቀው ብርሃን የምከርን ልብ እንደ ጦር ወጋው:: ከዚያች ደቂቃ ጀምሮ ያቺን ተዋናይ ፍቅረኛውን ላለማየት ቆረጠ::

የምከርና የሶላንጅ ኑሮ ጤናማ አየር ሰፈነበት:: ሶላንጅም ለሦስተኛ ጊዜ ፀነሰች:: በዜናው እንደ ሂላሪና አሌክሳንድራ የተደሰተ አልነበረም:: ሶላንጅ ምጥ የተያዘችው ምከር ለሥራ ወደ ካሊፎርኒያ በሔደበት ጊዜ ነበረ:: እንደ ልማዱም ከሐኪም ቤት ያደረሳት ያው ፓተርሰን ነው:: ምከርን በስልክ ለማግኘትና በደህና ሴት ልጅ የተገላገለች መሆኗን ለመንገር ሁለት ቀን ሙሉ ፈጅቶበታል:: የሶላንጅም የተለመደ ጥርጣሬ መታደስ የጀመረው በዚያን ጊዜ ነበረ:: ምከር ዜናውን ቢሰማም ተቻኩሎ አልመጣም:: አራሷ ክርስትና የተነሳችውም እርሱ በሌለበት ነበረ:: እንደ ፊተኞቹ ሁለቱ ሁሉ በቅርቡ ለተወለደችው እራስ ፓተርሰን የክርስትና አባት ማርጆሪ የክርስትና እናት ሆኗት::

ምከር ወደ ኒውዮርክ የተመለሰው ሶላንጅ በወለደች በሦስተኛው ወር ነው:: በዚያን ወቅት ስለ ምከር አዲስ ግንኙነቶች መፅሔቶች ና ጋዜጦች ብዙ ፅፈዋል:: የሚነፍሰውም ወሬ ሶላለጅን እጅግ አድርጎ አስቆጥቷታል:: ምከር እንደ በፊቱ በአንዲት ሴት ሳይቆጠብ የሆሊውድን ቆነጃጅት ተራ በተራ ማዳረስ ይዞ ነበረ:: በተለይም ደግሞ በየዕለቱ መጠጥ አብዝቶ በመውሰዱ ሳይሰክር የማያድርበት ቀን እንደሌለም ሶላንጅ ሰምታለች:: ደሚ እንደፈላ ነበር የምከርን መመለስ ስትጠባበቅ የሰነበተችው::

"መሳቂያ መሳለቂያ አደረግከኝ:: ስለምወድህ ብዙ ታግሼህ ነበረ:: በመደጋገም በላዬ ላይ በደል ፈፀምክ:: ከእንግዲህ ብንለያይ ይሻላል" አለችው ሶላንጅ ጩክና::

"ማነው ብትፋቺ ይሻላል ብሎ የመከረሽ? ፓተርሰን ነው?" እለና ከርሱው ብሶ ጨኸባት:: ❖

"በእኛ መሐል ፓተርስንን የሚያገባው ነገር የለም:: መፅሔት የማላነብ ጋዜጣ የማልመለከት መሰለህ? ከኒውዮርክ እስከ ካሊፎርኒያ ድረስ ስለ አንተ የተፃፈውን አይቻለሁ:: ከዓመት ዓመት፣ ከወር ወር በእያንዳንዱ ተውኔት በእያንዳንዱ ሲኒማ ውስጥ ከአዲስ ኮረዳ ጋር፣ ከአዲስ ሴት ጋር እንደተዳራህ ነህ:: መንዘላዘሉንም በጣም ነው ያበዛኸው:: ይህም እኔን ከመናቅህ የተነሳ ነው:: እኔ ደግሞ የሚወደኝና ለክብሬም የሚቆረቆርልኝ ባል እፈልጋለሁ" አለችው ሶላንጅ ረጋ ብላ::

"ክብር? የምን ክብር አለሽና ነው? ከፓተርሰን ጋር ምን ስትሰሩ እንደምትውሉ የማላውቅ መሰለሽ?" አለና አሁንም ጮኸባት::

"ከማን ጋር ልወያይ ታዲያ? ችግሬንስ ለማን ላካፍለው? ፓተርሰን ብቻ ነው ሳዝን የሚያፅናናኝ" አለችው ሶላንጅ::

"ማፅናናት ብቻ ሳይሆን የሚያስደስትሽም ጭምር እንጂ! በተጨማሪ አንድ ነገር ላስጠነቅቅሽ እፈልጋለሁ" አለ ምከር ከመቀመጫው እየተነሳ:: "ከፓተርስን ጋር ዳግመኛ እንድትገናኚ አልፈልግም! የመፋታትንም ወሬ ሁለተኛ እንድታነሺብኝ አልፈልግም" ብሎ በሩን በኃይል ዘጋና ወጣ:: በዛው ወደ ካሊፎርኒያ ሔደ::

ሶላንጅ ከበፊቱም ይልቅ ንዴቷ አሁን ጨምሮ ነበረ:: ምከር ካሊፎርኒያ የበረረው ካንዲት የኒውዮርክ ልጃገረድ ጋር መሆኑን ስምታለች:: ለጥልም አቆብቁባ ትጠብቀዋለች:: እርሱ ግን ለስድስት ወራት ያህል በካሊፎርኒያ ቆየ:: ምከር ወደ ኒውዮርክ በተመለሰበት ምሽት ሶላንጅን ከቤት አላገኛትም:: ፓተርሰን ራት ጋብዟት ስለነበረ ቆይታ ነበረ የመጣችው:: ምከር እርሷን በመጠባበቅ ላይ እንዳለ የከፈተውን ሙሉ ጠርሙስ ውስኪ ከቂጡ አድርሶታል:: ሶላንጅ ከመድረሷ ከምከር ጋር መነታረክ ጀመሩ:: የአባቷ ጭቅጭቅ አላስተኛ ያላት ሂላሪ ከመኝታ ክፍሏ ወጥታ ከሳሎኑ በር ሥር ተለጥፋ የሚለዋወጡትን ኃይለ ቃል ትሰማ ነበረ:: የዘጠኝ ዓመት ልጅ ብትሆንም በዚያን ምሽት የተፈፀመውን እያንዳንዱን ነገር





ታስታውሰዋለች:: የእምቡላንስና የፖሊስ መኪናዎች ድምፅ በግቢያቸው ውስጥ ማስተጋባቱን... እናቷን በቃሬዛ ይዘዋት መውጣታቸውን ... ፖሊሶች ያሰቅስ የነበረውን አባቷን እጅበው መውሰዳቸውን ... ሁሉንም ታስታው ሰዋለች::

የነሂላሪ ሞግዚት ለፓተርሰን ስልክ ደውላለት መጥቶ ነበረ:: የሰማውንም ለማመን ከቶ ተሳነው:: በቅዠት ዓለም ውስጥ ያለ መሰሉ ተሰማው:: በምከርና በሶላንጅ መካከል ቅሬታ መፈጠሩን ያውቀዋል:: ግን ከዚህ የሚያደርስ ነው ሲል ጥርጣሬም አላደረበትም ነበረ:: ሶላንጅ ምከርን እንደምታፈቅረው እርሱም ከልቡ እንደሚወዳት ፓተርሰን በቅርብ የሚያውቀው ነው:: ለዚህም ክርሱ የተሻለ አንዳችም ምስክር ሊገኝ አይችልም:: የሁለቱን ፍቅር፣ ለመውደድ ያልታደለው ፓተርሰን ብቻ ሳይሆን አገር ቀንቶበታል:: የሶላንጅ ፍቅር በምከር ጥፋት መጠን እየቀነሰ የሚሔድ ሳይሆን ይቅርታ ለማድረግ ብቃት የነበረው ነበረ:: የምከርም ፍቅር በፓሪስ ደ.እርኰል ጎዳና ላይ ያያትን ሶላንጅ ተከታትሎ የራሱ እስከማድረግ ፅናት የነበረው ነበረ:: የሁለቱ ፍቅር የራሱ የሆነ ልዩ ውበት የነበረው ፍቅር ነበረ:: ... ፈረንሳይቷ ልጃገረድ ሶላንጅ ክብረ ንፅህናዋን ያቆየችው ለሐርቫርዱ ተማሪ ለምከር ነበረ:: የምከር ዓይኖች ለሶላንጅ ትዝታ እንዳላነቡ፣ ልቡ እንዳላለቀሰላት፣ አንጀቱ እንዳልተላወሰላት ዛሬ ምን ተፈጠረ? እስክዚያስ የሚያስጨክነው ምን ጉዳይ ተገኘ? ...

ፓተርሰን ከሳሎን ውስጥ ሳይነቃነቅ ጉህ ቀደደ:: እንደፈራውም አልቀረ በሩ ተንኳኳና ሶላንጅ ከተወሰደችበት ሐኪም ቤት የተላከው ሰው መርዶ ይዞ መጣ:: ወረቀቱን የተቀበሉት የፓተርሰን እጆች ተንቀጠቀጡ:: ዓይኖቹም ብዥ አሉበት:: ሕይወት ሕልም ናት ማለት ነው... ስለዚህ ሶላንጅም ሕልም ነበረች ማለት ይቻላል... እንደ ሕልምም ሶላንጅ ዳግመኛ አትታይም ... ሶላንጅ አለፈች... ምከር ሶላንጅን አንቆ ገደላት!!

# ምዕራፍ አምስት

ፓተርሰን ምክርን ለማነጋገር የተፈቀደለት ከሰዓት በኋላ ላይ ሲሆን እስከዚያን ድረስ ምክር በምርመራ ላይ ነበረ:: ምርመራው ግን ያን ያህል ሰዓት የሚፈጅ አልነበረም:: ምክር ከማልቀስ ብዛት በጐረነነ ድምፁ ሁሉንም ነገር ነግሯቸዋል:: ጉሮሮውን ያፈነው ሲቃ እንደ ልብ ባያናግረውም እንዳችም ነገር ሳያስቀር ተናዟል:: ለክሮ እንደነበረ ትዝ ይለዋል:: ቤቱን ጥላለት እንደምትሔድም ዝታበታለች:: ሌላም የተናገረችው ነገር ነበረ:: ምክር ባይጠጣ ኖሮ ነገሮችን ለማገናዘብ በበቃም ነበር:: ያደረገውንም ጨክኖ ባላደረገ ነበረ:: ለዚያ በመጠጥ ለደነዘዘ አእምሮ ግን የተናገረችው ነገሮች ሁሉ እውነት መስለው ታዩት:: ሕሊናውንም አስተው እንደ አውሬ አስጨከኑት::

ምክር የታሰረበትን ክፍል ቁልፍ የያዘው ፖሊስ ፓተርሰንን አስገባውና በሩን ከውጪ ቆለፈ:: ራሱን በሁለት እጆቹ ይዞ አቀርቅሮ ሲያለቅስ የነበረው ምክር ቀና አለና ተመለከተ:: ፓተርሰንን ለማየት ባለመፈለጉም ተመልሶ አቀረቀረ:: ፓተርሰን ግን ምክር ተቀምጦባት ወደ ነበረችው አልጋ ጠጋ አለና ከጐኑ አረፍ አለ:: እጁንም በምክር ትከሻ ላይ በፍቅር አሳረፈና "ሳም..." ሲል ምክርን በማቆላመጥ ጠራው:: ፓተርሰንም እንደ ምክር ሲያለቅስ ውሎ ኖሮ ድምፁ ሻክሮ ነበረ:: ምክር ወደ ጐን አየት አደረገው:: የፓተርሰንንም ዓይኖች መቅላት እንዳጤነ ካቀረቀረበት ቀና አለ::

"ሳም ..." አለው አሁንም ፓተርሰን በቁልምጫ::

"ገደልኳት አይደለም? ... ገደልኳት:: እውነት ሞተች ፓተርሰን?" ሲል ምክር እንባው በጉንጮቹ ላይ እየወረደ ጠየቀው::

"አዎን ሞታለች ሳም:: ከእንግዲህ ከሞት ልትመለሳት አትችልም:: ይልቅስ ለምን እንደዚያ ለማድረግ እንዳበቃህ ንገረኝ:: ምን ስትል ተናገረችህ? ምንስ ብላ ሰደበችህ? በቅድሚያስ እሷ መታችህ?" አለው ፓተርሰን:: እንደ ታናሽ ወንድሙ ለሚያየው ለምክር በሀገሪቱ ውስጥ ካሉት እውቅ ጠበ





ቆች አንዱ እንዲከራከርለት ለመግዛት ፓተርሰን ወስኗል:: በመሆኑም ጠበቃውን ከማነጋገሩ በፊት የግጭቱን መንስኤ ማጣራት ነበረበት::

ምክር በሐሳብ ባህር ውስጥ ጭልጥ ብሎ ሰጠመ:: ቆይቶም ቀና አለና፤ "ከስድብም አልፋ አስፈራራችኝ... ተናዳም ነበረና ሌላም ነገር ተናገ ረችኝ" አለው::

ፓተርሰን የተጠራጠረው ነገር ነበረና "ለምንድን ይመስልሃል የተናደደችው?" ሲል ጠየቀው::

ምክር አቀርቅሮ መሬት መሬቱን አየ:: የማታውንም የሶላንጅን ንዴት አስታወሰ:: አንጀቷ በግኖ ነበረና እርር ትክን ብላ ነበር የተናገ ረችው:: እንደዚያ መናገሯ ደግሞ ሲያንሳት ነው:: ከእንተም ጋር አብሬ አልኖርም ስትል ዝታበት ነበር:: ሶላንጅ ለዘለቄታው ተለይታው ሕይወት እንደማይኖረው ምክር ያውቀው ነበረ:: ከልቡ የሚያፈቅረው እርሷን ብቻ መሆኑም ቆርጠላት ጥላኝ ትሄዳለች ሲል ፈራ:: ሌላም ነገር ስለ ተናገረችው ሕሊናውን ሳተ:: ቀና አለና ተስፋ በቆረጡ ዓይኖቹ ፓተርሰንን አየ:: "አሁንም ሌላ ሴት መያዜን አውቃ ነበረ ... እኔ ደግሞ ለጊዜ ማሳለፊያ ስል ያደረኩት ነበረ... ለዚህ ያደርሰናል ብዬ አልጠረጠርኩም" አለ ምክር::

"መጠርጠር ነበረብህ ሳም! ሶላንጅ ብዙ ጊዜ ታግላሀለች" አለው ፓተርሰን:: ምክር ራሱን ብቻ እወዛወዘ እንጂ ለመናገር አልፈለገም::

"እና መፋታት አሰብን ስትል ነው ያስፈራራችህ?" አለና ፓተርሰን ጠየቀው::

ምክር በአሉታ እጐነበሰና አሁንም በሐሳብ እንደ ተዋጠ ቆየ:: ያ የተናገረችው ሌላ ነገር እሁን ግልፅ መሆን ነበረበት:: ሶላንጅንም ለመግደል ያበቃው በዚያ ነገር የተነሳ ነበረ:: ስካር ነው:: በዚያ ላይ ደግሞ እንደዚያ ስትናገረው እውነት መስሎት ራሱን መቆጣጠር አቅቶታል:: ያ የነገረችው ነገር መፍረጥረጥና ሐቁንም ማወቅ ነበረበት:: ስለዚህ ፓተርሰን ሊጠይቀው ወሰነ:: ቀና አለናም "ከእኔ ተፋታ ከእንተ ጋር ለመጋባት ወስናችሁ ነበረ?" ሲል ጥያቄ አቅርቦለት ትኩር ብሎ ያየው ጀመረ::

ፓተርሰን ግን በሐዘኔታ አመለካከት እያየው "መልሱ ምን ይመስልሃል?" በማለት መልሶ ጠየቀው::

"እንዴት ለማወቅ እችላለሁ? በጣም እንደምትቀራረቡ አውቃ

ለሁ ... ብዙም ጊዜ ስትገባበዙ ነበረ" አለው ምከር::

"ስለመገባበዛችን አንስታ አጫውታህ አታወቅም?"

"ብዙ ጊዜ ነው ያነሳችብኝ::"

"እንደዚያ ማድረግ ታዲያ አንቱኝም ለማስቀናት መስሎ አልታየህም ነበረ? ሶላንጅን በቅናት አሳርረሃታል:: ስለዚህ ምናልባት እርሱንም ባስቀናው ሁለተኛ ከሌላ ሴት አይሄድም፣ ባሌ የኔ ብቻ ይሆናል የሚል ግምት ኖሯት ይሆናል እንደዚያ ያለችህ" አለው ፓተርሰን::

አሁን አእምሮው በትክክል ስለሚያስብ ማመዛዘን ይችላልና ምከር በፓተርሰን ማብራሪያ አመነበት:: ግን በትናንትናው ምሽት ንትርክ መካከል "አንተን ፈትቼ ፓተርሰንን ላገባ ነው" የሚለውም የሶላንጅ አነጋገር ለሰከረው ምከር እውነት መስሎት ነበረ:: እንደ እብድም ስላደረገው ሶላንጅን አንቆ ገደላት... ሶላንጅን፤ የሕፃናት ልጆቹን የነሂላሪን፣ የነ አሌክሳንድራ፣ የነሚጋንን... እናት ሶላንጅን:: ቀምበጧ ሶላንጅ፣ ለግላጋዋ ሶላንጅ፣ ባለወርቃማ ፀጉሯ፣ ባለትላልቅ አረንጓዴ ዓይኖቿ ሶላንጅ ከፊቱ ድቅን አለች:: የመጀመሪያና የመጨረሻ ፍቅሩ የሆነችውን ሶላንጅ ያ እንደዚያ ይብረከረክላት የነበረው ምከር ጨክኖ አንቆ ገደላት:: ዕንባው እንደ ውሃ ፈሰሰ:: የተቀመጠበት አልጋ እስኪንቀጠቀጥ ድረስ ተንሰቅስቆ አለቀሰ:: ፓተርሰንም እጁን ከትከሻው ላይ አድርጎ አብሮት አነባ:: ሊያፅናናውም ሞከረ::

"ልጆቼስ? የልጆቼስ ነገር እንዴት ሊሆን ነው?" አለ ምከር በለቅሶው መካከል ትዝ አሉትና:: ልጆቹ ለአባትና ለእናታቸው የነበራቸውን ፍቅር ያውቀዋል:: በተለይ ሶላንጅ አንድም ቀን ከልጆቿ ተለይታ አታውቅም ነበረ:: ከምከር ያገኘቻቸውም ልጆች በመሆናቸው ከማንኛውም እናት ይበልጥ ነበረ የምትንከባከባቸው:: እነኛ በእናት ሞግዚትነት ያደጉ ሕፃናት እንዴትስ ሊሆኑ ይሆን?

"የሚከራከርልህ ጠበቃ በሀገሪቱ ውስጥ ዕውቅ መሆን አለበት:: ስለዚህም ከፍተኛ ገንዘብ ሊጠይቀን ይችላል:: ለልጆቹም የቤት ኪራይ፣ የልብስ፣ የትምህርት ቤት፣ የሌላ ሌላም ወጪ ይኖራል" አለው ፓተርሰን::

"ሌላ ጠበቃ አልፈልግም:: አንተ ትከራከርልኛለህ" አለ ምከር:: ፓተርሰን አእምሮው ውስጥ ስሜቶች ተጋጩ:: ምከር የሚወደው ጓደኛው ነው:: በጦር ሜዳ ላይ ከአንዴም ሁለቴ ሕይወቱን አትርፎለታል::





ከሰሜን አፍሪካ እስከ በርሊን ድረስ አልተለያዩም:: ሆኖም ሶላንጅን የመሰለች ሚስቱን ገድሏል:: ግፍ የዋለባት እርሱ ሆኖ ሳለ ይባስ ብሎ ሕይወቷን አጥፍቷል:: ስለዚህ የፓተርሰን አቋም ወላወለ:: "እኔ የንግድ ሕግ ምሩቅ እንጂ በወንጀል ህጎች ችሎታ የለኝም::" አለ::

"የፈለገው ይሁን ሌላ ጠበቃ በማፈላለግ ጊዜህን እንዳታባክን" አለ ምከር::

"እባክህ ምከር፤ ከእስር ቤት ለመውጣት ከፈለግህ በሙያው የሰለጠነና ልምድ ያለው ሰው ላፈላልግልህ" አለ ፓተርሰን::

"የምሬን እኮ ነው ፓተርሰን፤ ሌላ ጠበቃ ፈጽሞ አልፈልግም" አለው ምከር::

"ጥሩ ለማንኛውም ህጻናቱ ብቻቸውን እንዳይሆኑ የቅርብ ዘመድ ካለህ ብትነግረኝና ለጊዜው አብሯቸው እንዲኖር ባደርግ" አለ ፓተርሰን::

ምከር ጥቂት አሰብ አደረገና ራሱን በአሉታ አወዛወዘ:: ፓተርሰን ብቻ ነበረ ለሶላንጅም ሆነ ለምከር የቅርብ እውቂያቸው:: እርግጥ በኒውዮርክ በኖሩባቸው ዘመናት ምከር በቲያትር ዓለም ውስጥ ካሉ በሺህ ከሚቆጠሩ ሰዎች ጋር ይተዋወቃል:: ብዙም ጓደኞች ሊኖሩት ይችላሉ:: ሶላንጅ ግን አንድም የቅርብ ጓደኛ አልነበራትም:: ለእርሷ ሕይወቷ ልጆቿና ባሏ ብቻ ነበሩ::

ፓተርሰንና ምከር በጦር ሜዳ ላይ ባሳለፏቸው ሦስት ዓመታት ውስጥ ስለ ብዙ ጉዳዮች አንስተው ተወያይተዋል:: ምከር ወላጆቹ በመኪና አደጋ መሞታቸውን እንዳጫወተው ፓተርሰን ያስታውሳል:: ጊዜው ስለ ረዘመ ከጥርጣሬ ላይ ቢወድቅም፣ እህት እንዳለችውም የነገረው ይመስለዋል:: "የቅርብ ዘመድ እንዳለህ ብትነግረኝ?" አለ ፓተርሰን ደገመና::

"የረባ ዘመድ የለኝም:: እርግጥ ቦስቶን ከተማ ውስጥ እህቴ አለች:: ግን እርሷ ደግሞ ለህፃናቱ አለኝታ ልትሆን ቀርቶ ለራሷም የማትሆን ሴት ናት:: ስለዚህ እሷን መጥራቱ ዋጋ አይኖረውም" አለ ምከር::

"ለጥቂት ቀናት ብንሞክራት?"

"ልፋት ነው ትርፉ ፓተርሰን:: የምትረባ ሴት አይደለችም:: እኔም ሁኔታዋን ገምቼ ነው ያላቀረብኳት:: ባይገርምህ ለመጨረሻ ጊዜ ያየኋት ሂላሪ ከመወለዷ በፊት ነው:: ስለዚህ እርሷን እርሳት" አለ ምከር::

ፓተርሰን ግን የምከርን እህት ለመርሳት አልፈለገም:: ምናልባት ህፃናቱን ስታያቸው ልትራራ ትችላለች:: ለብቸኛዎቹም ሕፃናት በዚያን ወቅት የአባታቸውን እህት ማግኘት ሊያፅናናቸው እንደሚችል ተሰምቶታል:: "ለማንኛውም ስሟን ብትነግረኝ? የሚሆነው አይታወቅም" አለው ፓተርሰን::

"ኢሊን፣ ኢሊን ምከር ትባላለች:: ባሏም መርከበኛ የነበረ ጆንስ የሚባል ሰው ነው:: የሚኖሩትም በቦስቶን ከተማ ነው:: ሴትየዋን ግን እንደማትወዳት እመነኝ:: መጥፎ ሴት ናት" አለና ምከር ከአልጋው ተነስቶ ወደ መስኮቱ ሔደ:: በመስኮቱም ውስጥ ወደ ውጪ ሲመለከት ቆየ:: እንባው ተለል እያለ በጉንጮቹ ላይ ፈሰሰ:: በእጆቹም እንባውን ጠራረገና ወደ ፓተርሰን ዞወር ብሎ "እባክህን ልጆቼን እንዳያቸው አስፈቅድልኝ?" አለው:: ሚስቱ፣ ህፃናት ልጆቹ በዓይኑ ላይ ሄዱበት ሂላሪ፣ አሌክሳንድራ፣ ሚጋን:: ያለ ወላጅ እናት ያስቀራቸው ልጆቹ ዕድል ታሰበው:: ሶላንጅን ከመሰለች እናት ነጥሏቸዋል:: ሶላንጅ ሁልጊዜ ለልጆቿ እንደ ተንሰፈሰፈች ነበረች:: ከጭኗ፣ ከደረቷ፣ ከጉያዋ እንዲርቁባት አትፈልግም ነበረ:: ስማ፣ ልሳ አትጠግባቸውም:: ለስሙ ሞግዚት ብትኖርም፤ የምታጥባቸው፣ ፀጉራቸውን የምታበጥር፣ የምታለብሳቸው፣ የምትመግባቸው እርሷ ነበረች:: ማታ ማታም እንቅልፍ እስከሚወስዳቸው ድረስ ፀጉራቸውን ስታሻሽ፣ ተረት ስታወራላቸው ነበረ የምታመሸው:: እንኳንስ ሌላ ሰው ራሱ ምከርም ቢሆን ለእነኛ ህፃናት የሶላንጅ ምትክ ሊሆን አይችልም ነበረ::

ፓተርሰን ለጥቂት ጊዜ ዝም ብሎ ሲያየው ቆየና፣ "በዚህ እስር ቤት ውስጥ እንዳለህ ህፃናቱ ቢያዩህ ለነርሰ ጥሩ ይመስልሃል?" አለው::

"ጥሩ እንዳልሆነ አውቃለሁ:: ብቻ አንድ ነገር ታስቦኝ ነው ... ለማስረዳት የምፈልገው ነገር ስላለኝ ነው:: ቢያንስ ሂላሪን እንኳን ብታመጣልኝ የምነግራት ነገር ይኖረኛል" አለ ምከር::

"ለዚህ በኋላ ያደርስሃል:: የእኔ የአሁኑ ጭንቀት ከዚህ እስር ቤት እንዴት በአስቸኳይ እንደምትወጣ ነው" አለው ፓተርሰን:: ምከር ያልተጠበቀ ፈገግታ አሳየውና፣ "እና የምታስፈታኝ ይመስልሃል?" ሲል ጠየቀው::





"ከእኔ የተሻለ ጠበቃ እንፈልግ ብልህ እንቢ አልከኝ እንጂ የመፈታት ዕድል ይኖርህ ነበረ" አለው ፓተርሰን::

"ከፓተርሰን የተሻለ ጠበቃ አይኖርም" አለና ምከር መለሰ::

"ቀላል ክርክር የሚጠብቀን እንዳይመስልህ ሳም:: አድራጎትህን በማመን ለፖሊስ ቃልህን ሰጥተሀል:: ወንጀለኛነትህ የተረጋገጠ ነው ማለት ነው:: ለክርክር የሚኖረን አንድ የመነመነ ዕድል ብቻ ይሆናል:: ያንንም ዕድል ከመናገሬ በፊት ይቅርታ እንድታደርግልኝ በቅድሚያ እጠይቅሀለሁ:: ያ ዕድል በዕብደት ማመካኘት ብቻ ነው:: ዕብድ ሰው በሆነ ባልሆነው ሊቀና ይችላል:: አንተም በሚስትህ ላይ ያልሆነ ቅናት ስላደረብህ ገደልካት" አለው ፓተርሰን:: ቃላቱ ከአፉ ከወጡ በኋላ ፓተርሰን የታወሰው ነገር ነበር:: 'የምከር ዕድሜ ገና ሰላሳ አምስት ነው:: ዝነኛ መሆን ከጀመረ አስር ዓመታት አልፈዋል:: ገንዘብ እንደልቡ በማግኘቱ የፈለገውን ሁሉ አድርጓል:: ከመጠን በላይ ይጠጣል ... ያመነዝራል ... ምናልባትም እራሱን መቆጣጠር ያቃተው በእርግጥም የአእምሮ ጉድለት ስላደረሰበት ይሆን?' ሲል አሰበ::

ፓተርሰን ወደ ቢሮው በሚመለስበት ሰዓት ሁሉ ሲያስላስለው የነበረው ይህንኑ የምከርን ሙሉ በሙሉ ጤነኛ መሆንና አለመሆንን ነበረ:: ዝና... ገንዘብ... ሴት... መጠጥ... የእነኝህ ድምር ውጤት ዕብደት ይሆን ይሆን? ካልሆነ ሶላንጅን፣ የልጆቹን እናት፣ እንደዚያ የምትወደውን ሚስቱን እንዴት ሊገድላት ይጨክናል? ምከር ሶላንጅን በመግደሉ በሆዱ ጠልቶታል:: ግን ደግሞ ያለው ጓደኛ እርሱ ብቻ ነው:: በመሆኑም ስለ ምከር ዕብደት ፍርድ ቤቱን በማሳመን ሊያስፈታው ቆርጧል:: እስከዛ ድረስ ግን ለህፃናቱም ቢሆን ፓተርሰን የሚቀርባቸው ሰው አይኖርም:: ምናልባት ያቺ አክስታቸው ሆዷ ከራራ ምከር እስከሚፈታ ህፃናቱን ተንከባክባ ትይዛቸው ይሆናል:: ስለዚህ ፓተርሰን የርሷን ስምና አድራሻ መርሳት የለበትም ነበረ:: ለጊዜው ግን ሊያነጋግራት አልፈለገም::

ቀጥሎም ፓተርሰን ያደረገው ነገር ቢኖር ስለ ምከር ገንዘብና ንብረት ጥናት ማካሄድን ነበረ:: የምከርን የባንክ ደብተሮችና ሌሎችም ሰነዶች በጥንቃቄ መረመረ:: ያገኘው ውጤት ግን ከጠበቀው በታች ነበረ:: የምከር ገንዘብ እንደ አገባቡ መጠን ወዲያውኑ ይወጣል:: በየጊዜው ለሚቀያይራቸው ልጃገረዶች ስፍር ቁጥር የሌለው ስጦታ ያበረክታል:: እንዳውም ገቢው አልበቃ ብሎት በታሳቢ የሚከፈል ገንዘብ ተበድሮም እንደነበረ ፓተርሰን ደርሶበታል:: በባንክ ያለውን ተቀማጭ ከዕዳው ጋር

ሲያመዛዝነው የሚተርፈው ገንዘብ በጣም አናሳ ነበረ:: ምከር እስከሚፈታ ወራት ሲያልፉ ይችላሉ:: የተረፈው ገንዘብ ደግሞ ለሞግዚት፣ ለሰራተኛ ደመወዝ ተከፍሎለት፣ ለህፃናቱ ምግብና ልብስ ሆኖ ለዚያን ያህል ጊዜ የሚቆይ አልነበረም:: ምከር የገንዘብ ፀር ነበረ:: ታዲያ ሶላንጅም ብትሆን ከብኩንነት እንዲታቀብ ብዙ ጥራለች:: ምከር ግን ገንዘብ ከማጠራቀም መቸርን ይመርጥ ነበር:: ስለዚህም ፓተርሰን ከፊት ለፊቱ የነበሩትን ሰነዶች አመሳክሮ ሲጨርስ የተገኘው ገንዘብ መጠን ከአስር ሺህ ብር አይበልጥም ነበረ:: ፓተርሰን ምከርን ቁጥብ እንዲሆን በጥብቅ ሊመክረው በተገባ እንደነበረ የተሰማው በዚያን ወቅት ነበረ:: ምከር ልጆቹን ለድርብርብ ችግር አጋልጧቸዋል ማለት ነው:: አስር ሺህ ብር ህፃናቱ ለሚኖሩበት ቤት የስድስት ወር ኪራይ እንኳን አይበቃም ነበረ::

ፓተርሰን ልጆቹን ወደርሱ ቤት ለመወሰድ በመፈለጉ ባለቤቱን ማርጆሪን አማከራት:: እርሷ ደግሞ ቀድሞውንም ቢሆን እነምከርን ስለማትወዳቸው ልጆቹ አብረዋት በአንድ ጣሪያ ስር እንዲኖሩ አልፈለገችም:: ፓተርሰን በማስተዛዘን ደጋግሞ ለምኗት ነበረ:: እርሷ ግን ይብሱኑ ከነፍሰ ገዳይ ልጆች ጋር አብሬ አልኖርም ስትል ከነጭራሹ ተስፋውን አስቆረ ጠችው::

ለሚቀጥሉት ሁለት ቀናት አንድ ጊዜ ከምከር ጋር፣ አንድ ጊዜ ደግሞ ከህፃናቱ ጋር ሲል ዋተተ:: በዚያም ላይ የሶላንጅን የቀብር ሥነ ሥርዓት ለማስፈፀም ዝግጅት ማድረግ ነበረበት::

ምከር በታሰረ በሶስተኛው ቀን የሶላንጅ የቀብር ሥነ ሥርዓት ተፈፀመ::

አስከሬኑ ለሁለት ቀናት በክብር አርፎ በሺህ በሚቆጠሩ ሰዎች ስንብት ተደረገለት:: በሦስተኛውም ቀን የፍትሐት ፀሎት ሲካሄድ አረፈደ: ትልቁንም ካቴድራል ባጣበቡት ሰዎች ብዛት ፓተርሰን መገረሙ አልቀረም: አብዛኛዎቹም ለምከር የነበራቸውን አክብሮት ለመግለፅ ብቻ ሳይሆ ሶላንጅንም ይወዷት ነበረ:: ስለ ሶላንጅ እያነሱ የማያወሩት የለም::

"ተወዳዳሪ የማይገኝላት ውብ ነበረች... ባሏን ከመጠን በላ ታፈቅረው ነበረ... የፊልም ተዋናይ መሆን ነበረባት... ለሞዴልነት ብ ጊዜ ተለምና እንቢ አለች... አቤት ልጆቿን ስትወድ! ... እውነተኛ የፈረንሳይ ቆንጆ ነበረች... እንደዚያ ስትወደው እንዴት ጨክኖ ገደላት . ይህን ጊዜ ምከር ምን ያስብ ይሆን ... ትሑትና ሰው አፍቃሪ ነበረች.





ክብረ ንፅህናዋን በጀርመኖች እንኳን ያላስደፈረች ጉበዝ ነበረች ... ልጆቿን ምን ይውጣቸው ይሆን?..." ሰው ሚሰጠው አስተያየት ማብቂያ አልነበረውም::

አስከሬኑ ካረፈበት ሳጥን ፊት ለፊት ከነበረው አግዳሚ ወንበር ላይ ፓተርሰን፣ ሂላሪና አሌክሳንድራ ተቀምጠዋል:: ቀጥላም ሚጋንን የታቀፈችው ሞግዚት ነበረች:: ሳጥኑ ከመከደኑ በፊት ሂላሪ ከተቀመጠችበት ተነስታ እናቷን ለመጨረሻ ጊዜ ለመሰናበት ሄደች:: ሶላንጅንም ትኩር ብላ ስታያት ቆየች:: ጎንበስ አለችና ግንባሯን ሳመቻት:: ከዚያም የተከደኑ ዓይኖቿን ሳመቻቸው:: በመጨረሻም ከንፈሯን ስማ ቀና አለች:: በካቴድራሉም ውስጥ ወደ ነበሩት በሺ የሚቆጠሩ ሰዎች አየች:: በዚያች በህፃን ልቧ ከተራራ የከበደ ሀዘን ተሸክማለች:: ግን ሂላሪ አላለቀሰችም:: ሂላሪ የሶላንጅ ልጅ ናትና እንደ ገደል ውሃ ካልፈሰስኩ የሚላትን ዕንባ እንደ አዋቂ አምቃ ያዘችው:: ካልፈነዳሁ ብሎ ጉሮሮዋን የሚተናነቃትንም ሲቃ ውጣ ወደ መቀመጫዋ ተመለሰች:: አሌክሳንድራም ለምን እናቷ ከሳጥን ውስጥ እንደተኛች ጠየቀቻት:: ሂላሪም ስለሞተች ነው ስትል መለሰችላት:: አሌክሳንድራ ግን ሞት ምን ማለት እንደሆነ አታውቅም:: ትዝም ያላት እናቷ ማታ ማታ ከምታጫውታቸው ተረቶች አንዱ ነበረ:: ሶላንጅ፣ በተረቱ ውስጥ እንዳለችው 'ስኖው ኋይት' ተኝታለች:: ስኖው ኋይት ከሽለብታዋ የምትነሳው ፍቅረኛዋ መጥቶ ሲስማት ነው:: "ለምንድነው የእኛስ አባት መጥቶ እናታችንን የማይስማትና እንድትነሳ የማያደርግልን?" ስትል ሂላሪን ጠየቀቻት::

"አክሲ የእኛ እናት እንደ ስኖው ኋይት አይደለም የተኛችው:: አባታችንም መጥቶ ቢስማት አትነሳም" አለቻት ሂላሪ:: በዚያን ጊዜ የፍትሐት ፀሎቱ መዝጊያ የሆነው የድንግል ማርያም ምስጋና ዜማ በመሰማት ላይ ነበረ:: "ለምን?" አለቻት አሁንም አሌክሳንድራ::

"ስለሞተች ነው አክሲ" አለችና የእህቷን እጅ ጭብጥ አድርጋ ያዘችው:: የእናታቸውን አስከሬን የያዘው ሳጥን በአጠገባቸው እያለፈ ስለነበረ የሂላሪ ፊት በድንጋጤ ነጣ:: ቆም አለችና እጇን ከሳጥኑ ላይ በነበረው የአበባ ጉንጉን ላይ አሳረፈች:: ሁለት ነጫጭ ፅጌረዳዎችም መዛ አወጣች:: አንዱን ለራሷ አስቀርታ ሌላውን ፅጌረዳ ለአሌክሳንድራ ሰጠቻት:: አሌክሳንድራ በዚያን ጊዜ ማልቀስ ጀመረች:: ለምንድነው እናቴ እንዳትነሳ ሳጥኑን ከድነው የሚወስዷት ስትል ትንሰቀሰቅ ጀመረ:: ሞት የሚሉት ቃል ትርጉም አይግባት እንጂ ሞት መለያየት መሆኑን ያወቀችው

ይመስላል:: ሌላው ቀርቶ በሞግዚት እቅፍ የነበረችው ሚጋን እንኳን በዚያን ወቅት ከእናቷ መለየቷን ያወቀች ይመስል ከእህቷ ጋር አብራ አልቅሳለች::

ያን በመሰለ የደስ ደስ በነበረው ቀን ሶላንጅ ትቀበራለች ለማለት ላሰበው ይከብድ ነበረ:: ባለፀጉረ ወርቃማዋ ሶላንጅ፣ ባለ ብሩህ አረንጓዴ ዓይኖቿ ሶላንጅ፣ ውቧና ለገላጋዋ ሶላንጅ፣ ያ ቀን ከባሏና ከልጆቿ ጋር የምትስቅበት፣ የምትጫወትበት እንጂ የምትቀበርበት አልነበረም:: ስምን ያ ቀን የደስ ደስ እንደ ነበረው ለመገመት ያስቸግራል::

ፓተርሰን ህፃናቱን ከቤት ካደረሳቸው በኋላ ወደ መቃብር ቦታው ተመለሰ:: የቀብሩም ሥነ ሥርዓት በትክክል መፈፀሙን ካረጋገጠ በኋላ ምከርን ለመጠየቅ ሔደ:: ሂላሪና አሌክሳንድራ ከሬሳ ሳጥኑ ላይ የወሰዱትን ዓይነት ነጭ ፅጌረዳ ለምከርም አምጥቶለት ነበረ::

ዛሬ ፓተርሰን ለምከር ለየት ያለ ፍጥረት መስሎ ነበረ የታየው:: ቁመቱ ረዝሟል፣ ሰውነቱ ቀጥኗል፣ ፊቱ ገርጥቷል:: በዚያ ላይ ደግሞ ከነጭ ሸሚዙ በስተቀር ሌላው ልብሱ ጥቁር ነበረ:: በግራ እጁ የያዘውም ባርኔጣው ጥቁር ነው:: ጫማውም እንደዚሁ ልክ የሞት መላክተኛ መስሎ ነበረ የታየው:: በተዘዋዋሪም መንገድ ፓተርሰን የሞት መላክተኛ ነው ለማለት ይቻላል:: ምከር ሶላንጅን ለመግደል የበቃው በርሱ የተነሳ ነበር:: ምከር ቀና ብሎ ሲያየው መላ ሰውነቱ በሆነ ስሜት ተንዘፈዘፈ::

"ከሶላንጅ የሬሳ ሳጥን ላይ ነው ያመጣሁልህ" አለና ፓተርሰን ነጩን ፅጌረዳ ሊሰጠው እጁን ዘረጋ:: ምከር ረጋ ብሎ ተቀበለውና ፈገግ አለ:: "ልጆቹ ደህና ናቸው?" አለናም ጠየቀው::

"ደህና ናቸው:: ሂላሪ እያለች ምን ይሆናሉ ብለህ ነው:: ልክ እንደ እናታቸው ሆና ነው የምትንከባከባቸው:: ትንሿ ሶላንጅ ሆናለች" አለ ፓተርሰን::

ምከር ከአልጋው ላይ አረፍ አለና በረጅሙ ተነፈሰ:: በእጁ የያዘውንም ፅጌረዳ ወደ ከንፈሩ አስጠጋው:: ለሶላንጅ ያለው ፍቅር ከእንግዲህ ትርጉም አልነበረውም:: ህይወቱም ንቡ እንደ ከዳው ቀፎ ወና ሆኗል:: ሲስመው የነበረውን ፅጌረዳ ወደ አፍንጫው አስጠጋው:: የሳበውም አየር የፅጌረዳ መዓዛ አልነበረም:: በጦር ሜዳ ላይ ቀባሪ አጥቶ እንደሸተተ አስከሬን ሆነበት:: ሶላንጅን ቢያስብ፣ ቢያሰላስላት ከሄደችበት አትመለስም::





ከእንግዲህ አያያትም:: ልጆቹም እንደ ሶላንጅ ሲርቁት፣ ሲሸሹት፣ ሲሰወሩት ታየው:: አዎን! አንድ ቀን ሶላንጅን የመሰለች እናት እንዳሳጣቸው ሲያውቁ እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ ይቅር እንደማይሉት ተሰማው:: የርሱ ህይወት መኖር አለመኖር ከእንግዲህ ከንቱ፣ የከንቱም ከንቱ እንደሆነ ያውቀዋል:: ፓተርሰን በምከር አእምሮ ውስጥ የሚመላለሰውን ሐሳብ ቁጥርጥር፣ ኩምትርትር ከሚለው ፊቱ ላይ አንብቦ ለልጆቹ ሲል ተስፋ መቁረጥ እንደሌለበት አበክሮ አስገንዝቦት ነበር::

ምከር ግን "ከእንግዲህ ምን ላድርግላቸው?" ሲል በምሬት ተናገረ:

"ዕዳ አለብህ:: በህይወት ቆይተህ ህፃናቱን ማሳደግ ግዴታ አለብህ" አለው ፓተርሰን ለዘብ ባለ ሁኔታ::

"ዕዳ የሚከፈለው ተቀባይ ሲኖር አይደለም? የእኔን የአውሬውን፣ የሰው በላውን እርዳታ ልጆቹ እሺ ብለው እንደማይቀበሉት አውቃለሁ" ሲል ምከር መለሰለት::

"የሚሆነውን ወደፊት እናያለን:: ለጊዜው ግን፣ ስለ ልጆቹ ወቅታዊ ችግር ብንነጋገር:: እንደምታውቀው አሁን ያላቸው ገንዘብ ከወጪው አንፃር ሲታይ እጅግ አነስተኛ ነው:: ስለዚህ እንደኔ የሶላንጅ ጌጣ ጌጦች ተሸጠው መጠባበቂያ ገንዘብ እንዲኖራቸው ቢደረግ ጥሩ ይመስለኛል" አለው ፓተርሰን::

"ልጆቹን የሚረዳ እስከመሰለህ ማናቸውንም ነገር ማድረግ ኃላፊነቱ ያንተ ይሆናል:: ጌጣ ጌጦቹ ያሉበት ዕቃ የተቀመጠው ከባንክ በተከራየነው ሳጥን ነው:: ቁልፉንም ከሶላንጅ መኝታ ትራስጌ አጠገብ ካለው ከመሳቢያ ውስጥ ታገኘዋለህ" አለው::

"ጥሩ፣ በዚህ ሰሞን ውስጥ ሽጬ ውጤቱን አሳውቅሃለሁ" ብሎት ፓተርሰን ተሰናብቶት ወጣ::

ፓተርሰን ከእንቅልፉ አልነቃም ነበረ! ስልኩ ሲጮህ:: ከጐኑ ተኝታ የነበረችው ማርጆሪ ተንጠራርታ የስልኩን መናገሪያ አንስታ "ሃሎ" አለች:: የተፈለገው ፓተርሰን ነበረ:: የተደወለውም ምከር ከታሰረበት ፖሊስ ጣቢያ ነበረ:: ፓተርሰን በምከርና በልጆቹ የተነሳ ጊዜውን እንበለ ከንቱ እያጠፋ ነው ለትል ማርጆሪ ሆድ ሆዷን ሲበላት ሰንብቷል:: አሁን ደግሞ በእንቅልፍ ላይ እያለ ከፖሊስ ጣቢያ ስልክ ተደወለ:: ስልኩን ልትዘጋው አሰበችና ሐሳቧን ወዲያውኑ በመቀየር "ለምን ነበር የተፈለገው?" ስትል

ጠየቀች:: መልሱን ከሰማች በኋላ እየተቻኮለች ፓተርሰንን ቀስቅሳ መናገሪያውን ሰጠችው::

"ምን?" አለና ፓተርሰን በስልኩ ውስጥ ጮኸ:: ቀጠለናም "መቼ?" ሲል ጠየቀ:: የፓተርሰን ልብ መምታት አቁሞ ነበረ:: በዚያው በተኛበት ፍሰስ ብሎ ሊቀር ምንም ያህል አልቀረውም:: ነፍስ ሲዘራም የስልኩን መናገሪያ ከትራሱ ላይ ወድቆ አገኘው፧ አነሳውናም "ሃሎ" አለ:: ስልኩ አልተዘጋም ነበረና "ሃሎ" የሚል መልሲ አገኘ:: "ሰውን ማሰር ብቻ እንጂ ጠባቂ አታቀመሙ ማለት ነው?" አለ ፓተርሰን እንዳበደ ሰው:: ስልኩን ከደወለው ክፍል የሚሰጠውን መልስ ሲያዳምጥ ቆየና "ጥሩ ብዘገይ ልብሴን እስከምለብስ ድረስ ብቻ ነው፤ አሁኑኑ እመጣለሁ" አለና ስልኩን ዘጋ::

ፓተርሰን በመኪና ውስጥ ሆኖ ስለ ጓደኛው ስለ ምከር አሰበ:: ምከር እንደዚያ ያደርጋል ሲል ፈርቶ ነበረ:: የፈራውም ውሉ ሳያድር ደረሰ:: እነ ሂላሪ እናትም አባትም አጡ:: እነኛ ህፃናት የሙት ልጆች ሆኑ:: ደፋሩ፣ ቆራጡ... ሩህሩሁ... ቸሩ ምከር ሶላንጅን ሊደርስባት ተከተላት:: በዱአርኩል ጎዳና ላይ ያያትን ልጅ እቤቷ ድረስ ተከትሎ የራሱ ያደረጋት ምከር ዛሬም የተሰየችውን ሶላንጅን በሞት ጎዳና ላይ ሊደርስባት የራሱ ሊያደርጋት ተከተላት:: ሶላንጅን አንቆ እንደ ገደላት ለሶላንጅ ታንቆ ሞተላት:: ፓተርሰን አቀማጥላ ላሳደገችው እናቱ እንኳን እንደዚያ አላለቀሰም::





# ክፍል 2

## ሂላሪ

"ስለምን ከማህፀን አወጣኸኝ? ዓይን ሳያየኝ ምነው በሞትሁ::"

ጠየቀች፡፡ መልሱን ከሰማች በኋላ እየተቻኮለች ፓተርሰንን ቀስቅሳ መናገሪያውን ሰጠችው፡፡

"ምን?" አለና ፓተርሰን በስልኩ ውስጥ ጮኸ፡፡ ቀጠለናም "መቼ?" ሲል ጠየቀ፡፡ የፓተርሰን ልብ መምታት አቁሞ ነበረ፡፡ በዚያው በተኛበት ፍስስ ብሎ ሊቀር ምንም ያህል አልቀረውም፡፡ ነፍስ ሲዘራም የስልኩን መናገሪያ ከትራሱ ላይ ወድቆ አገኘው፡፡ አነሳውናም "ሃሎ" አለ፡፡ ስልኩ አልተዘጋም ነበረና "ሃሎ" የሚል መልዕ አገኘ፡፡ "ሰውን ማስር ብቻ እንጂ ጠባቂ አታቆመሙ ማለት ነው?" አለ ፓተርሰን እንዳበደ ሰው፡፡ ስልኩን ከደወለው ክፍል የሚሰጠውን መልስ ሲያዳምጥ ቆየና "ጥሩ ብዘገይ ልብሴን እስከምሰብስ ድረስ ብቻ ነው፤ አሁኑኑ እመጣለሁ" አለና ስልኩን ዘጋ፡፡

ፓተርሰን በመኪና ውስጥ ሆኖ ስለ ጓደኛው ስለ ምከር አሰበ፡፡ ምከር እንደዚያ ያደርጋል ሲል ፈርቶ ነበረ፡፡ የፈራውም ውሎ ሳያድር ደረሰ፡፡ እነ ሂላሪ እናትም አባትም አጡ፡፡ እነኛ ህፃናት የሙት ልጆች ሆኑ፡፡ ደፋሩ፣ ቆራጡ... ሩህሩሁ... ቸሩ ምከር ሶላንጅን ሊደርስባት ተከተላት፡፡ በዱአርኮል ጎዳና ላይ ያያትን ልጅ እቤቷ ድረስ ተከትሎ የራሱ ያደረጋት ምከር ዛሬም የተሰየችውን ሶላንጅን በሞት ጎዳና ላይ ሊደርስባት የራሱ ሊያደርጋት ተከተላት፡፡ ሶላንጅን አንቆ እንደ ገደላት ሰሶላንጅ ታንቆ ሞተላት፡፡ ፓተርሰን አቀማጥላ ላሳደገችው እናቱ እንኳን እንደዚያ አላለቀሰም፡፡





# ክፍል 2

## ሂላሪ

"ስለምን ከማህፀን አወጣኸኝ? ዓይን ሳያየኝ ምነው በሞትሁ፡፡"

# ምዕራፍ ፳ስድስት

ማርጆሪ ከሥራ መመለሷ ነበረ። ከመኪና አወራረዷ ከበር አከፋፈትና አዘጋጓ ብግን ብላ መናደዷ ይታወቃል። በፓተርሰንም ላይ አፍጣ "በስልክ እንደ ነገርከኝ አደርጋለሁ የምትል ከሆነ እኔን ፈተህ ነው!" ስትል ዛተችበት።

"ምከር እኮ እንደ ወንድሜ ነበረ። ደግሞም ከአንዴም ሁለቴም ከሞት እንዳዳነኝ ነግሬሻለሁ። ስለዚህ የርሱ ውለታ አለብኝ" አላት ፓተርሰን።

"የፈለገው ቢሆን እነኛ ልጆች ያቺን በር አልፈው አይገቧትም" አለች በጣቷ ወደ በሩ እያመለከተች።

"እባክሽ ማርጆሪ! እናትና አባታቸውን አጡ። ብቻቸውን ደግሞ ለመኖር አይችሉም። ለሞግዚት ደመወዝ፣ ለመኖሪያ ቤት ኪራይ ለመክፈል አይችሉም። ያላቸው ገንዘብ ለትምህርት ቤት ክፍያና ለልብስ ጫማቸው ቢበቃቸው ነው። ሰፊ ቤት አለን። ሰራተኛም አለችን። በምግብና መጠለያ ብቻ ብንረዳቸው?" ሲል ለመናት።

"ለዚያውም ሦስት ህፃናት!" አለችና ማርጆሪ በማፌዝ ሳቀች።

"የሚያስቸግሩ ልጆች አደሉም።"

"ማስቸገር አለማስቸገር አይደለም። እኔ ልጅ ሲባል አልወድም። እንደዚያ ቢሆን ኖሮ እስከ ዛሬ እኔስ አልወልድም ነበረ? ስለዚህ ቁርጥ ያለ አቋሜን ነው የምገልፅልህ። አይቻልም!" አለች ድምጿን ከፍ አድርጋ።

"እኔ የከርስትና አባታቸው አንቺ ደግሞ የከርስትና እናታቸው ነሽ። በዚያም ቢሆን እኮ ኃላፊነት አለብን" አላት ፓተርሰን ማሸነፊያ ነጥብ ያገኘ መስሎት።





አንዳንዴ የዋህ ነህ ልበል ፓተርሰን?"አለችና ሳቀችበት። "ወልዳ እናት ለመሆን የማትፈልግ ሴት በስመ ክርስትና ያነሳችውን ልጅ የማሳደግ አምሮት ይኖራታል ብለህ ትገምታለህ?" ብላ በንቀት አመለካከት አየችው።

ፓተርሰን በማግስቱም ማርጆሪን ሊለማመጣት ሞክሮ ነበረ። እርሷ ግን ሚስት ባሏን ደፍራ የማትናገራቸውን የስድብ ቃላት አወረደችበት። በመጨረሻም ላይ "የአባታቸውን ነፍሰ ገዳይነትና ሌላ ሌላ አድራጐቱን ተወውና የእነኚህ ህፃናት እናት እፍ ያለች ሽርሙጣ እንደነበረች በ'ጐሲፕ' መፅሔት ላይ የተፃፈውን አላነበብክም? ከዚያች ከፈረንሳዊ ቅሬና ከምከር ከተወለዱ ህፃናት ጋር አብሬ ለመኖር ለህይወቴ እሳሳላታለሁ። የነፍሰ ገዳይ ልጅ ነፍሰ ገዳይ ነው" ስትል ደመደመች።

ከማርጆሪ ጋር ከእንግዲህ መከራከሩ ውሃ ከድንጋይ ላይ እንደማፍሰስ መሆኑ ግልፅ ሆነለት። ትርፉም ነገርን በማለዘብ ምትክ መሸካከርን ብሎም ፍቺን ሊያስከትል ስለሚችል ዳግመኛ ለማርጆሪ ላያነሳባት ወሰነ። ከማርጆሪ ለመፋታት የሚፈራው ጉዳይ ነበረ። የማርጆሪ አባት የታወቁ የፖለቲካ ሰው ብቻ ሳይሆኑ እጅግም ሀብታም ነበሩ። ስለዚህ ማርጆሪን እንደእመቤቱ አክብሮ መኖር ነበረበት።

ለህፃናቱ ከፓተርሰን የሚቀርባቸው አንድም ሰው አልነበረም። በክርስትና አባትነቱ ብቻ ሳይሆን ምከርንና ሶላንጅንም ይወዳቸው ነበረ። በዚያም ሳቢያ እነኛ ህፃናት የሥጋ ዘመዶቹ መስለው ነበረ የሚታዩት። ውሎ ባደረ ቁጥር የህፃናቱ ሰውነት እየመነመነ ፊታቸው እየጠወለገ መሄዱንም ፓተርሰን ተገንዝቧል። በመሆኑም ህፃናቱን በጉዲፈቻ ሊወስዷቸው የሚችሉ ሰዎችን ለማፈላለግ አስቦ ነበረ። ግን እንዲህም በማሰቡ ራሱን ወቀሰ። እነኛን ህፃናት በጉዲፈቻ ሰጥቶ ማለያየት ከአረመኔነት የባሰም ጭካኔ ሆኖ ተሰማው። የፓተርሰንን ጭንቀት እጅግ ያባባሰው ደግሞ የህፃናቱ ሞግዚት የነበረችው ሴትና የቤት ሰራተኛዋ ተመካክረው ስራቸውን መልቀቅ ነበረ። ህፃናቱም የተላመዷቸው ሁለቱ ሴቶች ናቸው። ሦስቱ ህፃናት ያንን ትልቅ መኖሪያ ቤትና ግቢ ብቻቸውን ታቅፈው ለመኖር አይችሉም። በመሆኑም ፓተርሰን ሌላ መፍትሔ መፈለግ ነበረበት።

የምከርን እህት ኢሊንን ለመፈለግ ወሰነ። እርግጥ ምከር ስለ እህቱ ከንቱነት አጫውቶታል። ቢሆንም 'ትንሽ ስጋ እንደ መርፌ ትወጋ' ነውና ሴትየዋ ህፃናቱን ስታይ ልትራራላቸው ትችል ይሆናል። ደግሞም የምከር የእናት የአባቱ ልጅ እስከሆነች ድረስ ሙሉ በሙሉ ከወንድሟ

ጋር ተመሳሳይ ባህርይ ባይኖራትም እስከዛም ጨካኝ ላትሆን ትችላለች ሲል ፓተርሰን አሰበ፡፡ ዋናው ችግር ኢሊን አሁንም በቦስቶን ከተማ መኖር አለመኖሯ ነው፡፡ ምክር እንደ ነገረው ከሆነ ለመጨረሻ ጊዜ የተያየት ሂላሪ ከመወለዷ በፊት ማለትም ከዘጠኝ ዓመት በፊት ነበረ ማለት ነው፡፡

ፓተርሰን በማግስቱ ልዩ ፀሐፊውን ወደ ቦስቶን እንድትሄድና ስለ ኢሊን በቦስቶን መኖር አለመኖር አጣርታ እንድትመጣ አደረገ፡፡

ኢሊን በቦስቶን ከተማ ቻርልስተን ታዋን በሚባል አካባቢ ጆንስ ከሚባል ባሏ ጋር እንደምትኖር ታወቀ፡፡ ቤቷም ከበስተደቡብ በኩል ካለው የመርከበኞች መንደር ከባህር አጠገብ ነበረ፡፡ ፓተርሰን ስልክ ደውሎ አነጋገራት፡፡ ከማታወቀው ፓተርሰን ጋር መነጋገሩ በቅድሚያ ግር ብሏት ነበረ፡፡ ቀስ በቀስ ግን ነገሩ እየገባት ሄደች፡፡ እርሷም ብትሆን ከጋዜጣ ላይ ያነበበችው አንዳንድ ዜና ነበረ፡፡ ስለ ወንድሟ ሚስቱን መግደል በኋላም የራሱን ህይወት ስለማጥፋቱ እንደምታውቅ ለፓተርሰን ገልፃለታለች፡፡ እንደ አነጋገሯ ከሆነ በወንድሟ ሞት ያዘነችና የተፀፀተች አትመስልም ነበረ፡፡ እንዳውም የጠየቀችው ነገር ቢኖር ምክር በባንክ ስለተወው የገንዘብ መጠን ነበረ፡፡

“ብዙም አይደለም ሚስስ ጆንስ የደወልኩልሽም በዚህ የተነሳ ነው” ሲል ፓተርሰን ወደ ፍሬ ነገሩ አመራ፡፡ “እንደምታወቂው ምክርና ሶላንጅ ሦስት ህፃናት ልጆች አፍለው ነው የሞቱት፡፡ ለጊዜውም እንኳን ቢሆን ህፃናቱን ከባይተዋርነት ለማዳን ከዘመድ ጋር እንዲቀመጡ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ አንቺንም ለማነጋገር የፈለግኩት ህፃናቱን ለዘለቄታውም ሆነ ለተወሰነ ጊዜ ልታሳድጊያቸው ፈቃደኛ መሆን አለመሆንሽን ለመጠየቅ ነበረ” አላት ፓተርሰን፡፡

መልስ ሳትሰጠው ብዙ ቆየች፡፡ ከዚያም በሰለለ ድምፅ እየተቻኮለች “ትቀልዳለህ ልበል? እኔ የራሴ የሆነ አንድም ልጅ የለኝም፡፡ እና የምክርን ሦስት ህፃናት የማሳድገው ምን ቁርጥ ቢያደርገኝ ነው?” አለችው፡፡

“አክስታቸው በመሆንሽ ነዋ! ለህፃናቱስ ከአንቺ የቀረበ ዘመድ ከየት ሊገኝ ነው? የበጋውን ወራት ብቻ ከአንቺ ጋር እንዲቆዩ ነው የማስቸግርሽ፡፡ እስከዚያ ሌላ መፍትሔ ለማግኘት እችላለሁ፡፡ ስለዚህ እባክሽ ልጆቹ ካንቺ ጋር እንዲቆዩ ፈቃድሽ ቢሆን?” ሲል ፓተርሰን ተለማመጣት፡፡





“ገንዘብ ከሰጠኸኝ እሺ!” አለችው፡፡

ፓተርሰን አሰብ አደረገና፤ “ለልጆቹ የሚያስፈልገውን ውጪ ለመሸፈን የሚችል ልሰጥሽ እችላለሁ” አላት፡፡

“እንደዚያ ብቻ ማለቴ አይደለም፡፡ ሌላስ ተጨማሪ?” አለች፡፡

“ገባኝ! ገባኝ!” አለና ፓተርሰን ዝም አለ፡፡ ምክር እህቱን ለምን ይጠላት እንደነበረ አሁን በግልፅ ታወቀው፡፡ “ይቅርታ አድርጊልኝና ለአንቺ ልሰጥሽ የምችለው ሦስት ሺህ ብር ብቻ ይሆናል፡፡ ለእያንዳንዱ ልጅ አንዳንድ ሺህ ብር ማለት ነው”

“ለሞግዚትነቴስ? ቢያንስ ሁለት ሺህ ብር ልትከፍለኝ ይገባል!”

አሁንም ፓተርሰን ጥቂት አሰበና አማራጭ እንደሌለው በማጤኑ “እሺ” አላት፡፡

“ለምን ያህል ጊዜ?” ስትል ኢሊን በመጠራጠር ጠየቀችው፡፡

“ለሦስት የበጋ ወራት ብቻ” አላት ፓተርሰን፡፡

“ከሦስት ወር አንድ ቀን አላፊ ከእኔ ጋር እንደማይቆዩ እንድታውቀው፡፡ ቤቴም የመኖሪያ ቤት እንጂ የሙታን ልጆች መጠለያ ቤት አለመሆኑ እንዲገባህ፡፡ ለዚያውም ደግሞ ባሌ ቢስማማ ነው” አለች፡፡ ባሏ ግን እንኳን ሶስት ሺህ ብር ያህል አግኝቶ ለሶስት መቶውም እንደማይግደረደር ታውቀዋለች፡፡ ማስፈራራቷ ከፓተርሰን ተጨማሪ ገንዘብ ለማግኘት ከወዲሁ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ነበረ፡፡

“መቼም በቂ የመኝታ ክፍሎች አሉሽ ብዬ እገምታለሁ፡፡”

“አንድ ባዶ ክፍል አለኝ፡፡ ከፍ ከፍ ያሉት ሁለቱ ህፃናት አብረው በአንድ አልጋ ይተኛሉ፡፡ ለሌላዋ ደግሞ ዘዴ ይፈለጋል” አለችው፡፡

“ለትንሿ ያራስ ልጅ አልጋ ያስፈልጋታል፡፡ ገና የአንድ ዓመት ህፃን ናት” አለ ፓተርሰን፡፡ ስለ ሌላም ጉዳይ ሊጠይቃት ፈልጐ ነበረ፡፡ ለምሳሌ በሞግዚትነት ልምድ እንዳላትና እንደሌላት ግን ፓተርሰን ሌላ አማራጭ ስለሌለው ሳይጠይቃት ተወው፡፡ ህፃናቱ የሚያማምሩ ስለነበሩ ስታያቸው እንደምትወዳቸው ተማምኖ ነበረ፡፡

ፓተርሰን ህፃናቱን ከአክስታቸው ጋር ባገናኘበት ዕለት ያየው ሁሉ እንደጠበቀው አልነበረም:: የበጋውን ወራት ከአክስታቸው ጋር እንደሚያሳልፉ ለሂላሪ ቀደም ሲል ነግሯታል:: የህፃናቱንም ልብስና ጫማ አንድም ሳይቀር በመልክ በመልኩ እንድታዘጋጅም ገልፆላታል:: ህፃናቱ እንደ ለቀቁ የመኖሪያ ቤቱን ቁልፍ ለባለቤቱ እንደሚመልስና የተቀረውንም ቁሳቁስ ለመሸጥ ማቀዱን ግን ለማንጸ አልተናገረም::

ሂላሪ ስለ ቦስቶኑ ጉዞ በነገራት ወቅት ፓተርሰንን ያየችው በመጠራጠር ነበረ:: እንዲህ ነው ብላ ለመናገር አትችልም እንጂ ፓተርሰን ወደ ቦስቶን የሚወስዳቸው ለተለየ ዓላማ መሆኑን አውቃዋለች:: በተለይም እናቷ ከሞተች ወዲህ የክርስትና አባቷ ለሆነው ፓተርሰን የነበራት የልጅነት ፍቅር ከስሟል:: «ለምንድ ነው ወደ ቦስቶን የምትወስደን?» ስትልም ጠይቃው ነበረ::

«ሞቃቱን የበጋ ወራት በኒውዮርክ ከማሳለፍ ቀዝቀዝ በሚለው በቦስቶን ብታሳልፉት ይሻላል ብዬ ነው:: ደግሞም የምትቆዩት ከአክስታችሁ ጋር በመሆኑ ብቸኝነት አይሰማችሁም» አላት ፓተርሰን::

«ግን ወደ ኒውዮርክ እንመለሳለን:: አይደለም እንዴ?» አለችው አመለካከቷን ሳትቀይር::

«ምን ጥርጥር አለው!» አላት ፓተርሰን:: እቅዱን ያወቀችበት መስሎት በመዋሸቱ ውስጥ ውስጡን ኃፍረት ተሰማው:: ሂላሪም የፊቱን መለዋወጥ አይታዋለች::

“ታዲያ የምንቆየው ለሦስት ወራት ብቻ ከሆነ ለምንድነው ያለ የሌለ ልብሳችንንና አሻንጉሊቶቻችንን ይዘን የምንሔደው?» አለችው ሂላሪ::

«የሚያስፈልጋችሁ ስለ መስለኝ ብቻ ነው:: ሂላሪ በአንቺ ዕድሜ ይህን ያህል ተጠራጣሪ መሆን የለብሽም:: ከአባትሽ እህት ጋር መቆየቱ ብዙ ጥቅም ይኖረዋል» አላት::

ሂላሪ ራሷን አወዛወዘችና አቀርቅራ ማሰብ ጀመረች:: ለቦስቶን ጉዞ መዘጋጀቱን ተዘጋጅታለች:: የለበሰችው ቀሚስ እናቷ ለመጨረሻ ጊዜ የገዛችላትን ነው:: ቀሚሱ ሙሉ በሙሉ ቢጫ ሆኖ ክሳዱ ብቻ በነጭ ሐር የተዘመዘመ ነበረ:: እንደ አባቷ ጥቁር የነበረውን ፀጉሯን ከሁለት ከፍላ ጐንጉናዋለች:: የሚያበሩት ትላልቅ አረንጓዴ ዓይኖቿ ግን ቅሬታ ይነበብባቸው ነበረ:: ከፓተርሰን አነጋገር የተረዳችው ነገር ነበራት:: እንገቷን





እንዳቀረቀረች ቢሆንም ጨረፍ እያደረገች ታየው ነበረ:: ፓተርሰንም ቢሆን ሂላሪን መፍራት ከጀመረ ውሎ አድሯል:: የሶላንጅ አስከሬን በክብር ባረፈባቸው ሦስት ቀናት ውስጥ ወደ እናቷ እንዳይጠጋ ተከላክላዋለች:: የአሁኑ አመለካከቷ ደግሞ አጥንት ሰርስሮ የሚገባ ነበረ:: ሂላሪ ያለ ዕድሜዋ ብዙ የምታውቅ፣ አውቃም ለምታደርገው ሁሉ የምትጠነቀቅ ልጅ ነበረች:: እህቶቿንም ከማፍቀሯ የተነሳ አንድም ሰው አጠገባቸው አታስደርስም ነበረ:: እንደ እናቷ እንደ ሶላንጅ ፀጉራቸውን የምታጥባቸው፣ የምታበጥርላቸው፣ የምትመግባቸው፣ የምታስተኛቸው ሂላሪ ነበረች:: ሶላንጅ ብትሞትም ሂላሪ ተተክታለች::

“ለምንድን ነው አክስታችንን ቀደም ሲል ያልተዋወቅናት? ከአባታችን ጋር አይዋደዱም ነበረ ማለት ነው?» አለችና ሂላሪ ካቀረቀረችበት ቀና ብላ ጠየቀችው:: የሂላሪ ጥያቄ በዘዴ ተቀነባብሮ የቀረበ ነበረ:: እንደ እናቷም ፈጣን የማሰብ ችሎታ እንዳላት በቀላሉም የማትበገር ልጅ ስለመሆኗ ፓተርሰን አውቆታል:: ምን ብሎ እንደሚመልስላትም እስከ ሚያሰላስል የሂላሪ አረንጓዴ ዓይኖች ይከታተሉት እንደነበረም ይሰማዋል::

“በጣም እንደማይቀራረቡ አውቃለሁ:: ያም ማለት አክስታችሁ መጥፎ ሴት ናት ማለት አይደለም ሂላሪ» አለና ፈገግ ብሎ መለሰላት::

ሂላሪ ለጊዜው ሌላ ጥያቄ ልታቀርብለት አልፈለገችም:: ከፓተርሰን ያልተጠበቀ ፈገግታ የተረዳችው ነገር ቢኖርም፤ አይታ እስከምትፈርድ መቆየቱን መረጠች:: ከቦስቶን ከተማ ከቻርለስተን አካባቢ ደርሰው ከመኪና እንደ ወረደችም የተጠራጠረችውን አየች::

ከጠባቡ መንገድ አጠገብ አንዲት መለስተኛ ቤት ትታያለች:: የቤቷም መስኮቶች የፀሐይ መከላከያዎች የተሰባበሩ ነበሩ:: የግርግዳው ቀለም ከዕድሜ ብዛት የፈዘዘ ከመሆኑም በላይ አልፎ አልፎ ተፍቋል:: ግቢውም በአረም የተሸፈነ ነበረ:: ሂላሪ የአሌክሳንድራን እጅ እንደ ያዘች ወደ በራፉ የሚያደርሱትን ሁለት የተሸራረፉ ደረጃዎች ወጣችና ቆመች:: ሚጋንን አቅፎ የነበረው ፓተርሰንም ከኋላዋ ደረሰና የመጥሪያ ደውሉን ተጫነ:: ደጋግሞ ቢጫን በሩ ባለመከፈቱ፣ መጥሪያው በመበላሸቱ መሆኑን አወቀና በሩን አንኳኳ:: ፓተርሰን ወደ ሂላሪ አየት አደረገ:: እርሷም ታየው ነበረ:: አስተያየቷም 'ለምን ወደዚህ ወደ ተጎሳቆለ ቤት አመጣኸኝ?' የሚል ዓይነት ነበረ:: የሂላሪ ዓይኖች በጥላቻና በንዴት እንደተሞሉ ስለታወቀው ዳግመኛ ሊያያት አልደፈረም::

«ማን ነው?» የሚል ሻካራ የሴት ድምፅ ተሰማና በሩ ተከፈተ:: የከፈተችላቸው ሴት ቀይ ፀጉር እንደ ተመሰቃቀለ ነው:: ከመኝታዋም ገና መነሳቷ ሊሆን ይችላል:: የመጣችውም በፒጃማዋ ነበረ:: ከበራፉም ቆመው የነበሩትን እነ ፓተርሰንን ከላይ እስከ ታች እየችና «ምን ነበር?» ስትል ጠየቀች::

«ከኒውዮርክ ነበረ የመጣነው» አላት ፓተርሰን::

«አ! እናንተ ናችሁ ለካ?» አለችና ሳትወድ በግድ ፈገግ አለች:: ከዎከር ጋር የምትመሳሰልበት አንዳችም ነገር አልነበረም::

«ሚስስ ጆንሰን ነሽ?» አለ ፓተርሰን እየተጠራጠረ::

«አዎን ነኝ ግቡ!» አለችና ወደ ውስጥ ይዛቸው ዘለቀች:: ፓተርሰን ከበፊቱም ይልቅ ታላቅ ሀፍረት የተሰማው የቤቱን ቁሳቁስ ባየበት ጊዜ ነበረ:: የትልቁ ሶፋ እግር ሰባራ በመሆኑ ያዘመመ ነበረ:: ሌሎቹም ሦስት አነስተኛ ሶፋዎች ሽፋናቸው ተቀዶ ስፖንጁ አፍጥጦ ይታያል:: የምግብ ቤት ጠረጴዛውም ካያያዝ ጉድለት ተፋፍቋል:: ከበስተጥግ በኩል ካለች አንድ አነስተኛ የፎርማይካ ጠረጴዛ ላይ የተከፈተ ቴሌቪዥን ይታያል:: የሚተላለፈውም ፕሮግራም ቀጥታ ከእግር ኳስ ሜዳ ነበረ:: ድምፁ ያለመጠን በመከፈቱ ጩኸቱ ጆሮ ይሰነጥቅ ነበረ:: ከቤቱ የውጭ እይታ ይልቅ የውስጡ ይብስ ነበረና እነ ሂላሪ ባሉበት ድርቅ ብለው ቆሙ::

«ቢራ ላምጣልህ?» አለችው ፓተርሰንን እንግዶቹን ህፃናት ከምንም ሳትጥፋቸው:: ያቺን ሴት የዎከር እህት ትሆናለች ብሎ ማንም ለመጠርጠር አይችልም::

ዎከር ቁመናው ያማረ መልከ መልካም ሰው ነበረ:: ለአለባበሱም እንከን አይወጣለትም:: አነጋገሩም የተቆጠበ ነበረ:: የሰው መውደድም ያሰው ነው:: እህት የምትባለው ግን የዎከር ተቃራኒ ነበረች:: ዎከርን የምትበልጠው በሦስት ዓመት ቢሆንም ለማንም የሃምሳ ዓመት ሴት ነበር የምትመስለው:: ቀዩ ፀጉሯ ከመሳሳቱም ሚዶ ነክቶት የሚያውቅ አይመስልም:: የዓይኖቿ ቆዳ መሸብሸብ ለካራምነቷን የሚያጋልጥ ነበረ:: እንደ ዎከር የዓይን ብሌኖቿ ሰማያዊ ቢሆኑም ህይወት እይነበብባቸውም ነበረ:: ቢራ ከማብዛቷም የተነሳ ቦርጯ የተዘረገፈ ቢሆንም እግሮቿ ግን ሰላላ ነበሩ:: የፒጃማዋም መቆሸሽ አሳፋሪ ነበረ:: እነኛ ህፃናት ይችን የመሰለች ሴት ሲያዩ ዛሬ ለመጀመሪያ ጊዜ ሆነባቸው::





"ይቺ ሂላሪ ትባላለች" አለና ፓተርሰን አክስቷን እንድትጨብጣት በዓይኑ ጠቀስ አደረጋት:: ሂላሪ ግን ከቆመችበት አልተንቀሳቀሰችም:: "ይቺኛዋ ደግሞ አሌክሳንድራ" ሲል ቤቱን አፍኖት የነበረው የቢራና የሲጋራ ጢስ በአፍንጫው ግጥም አለ:: የጀመረውን ማስተዋወቅ መጨረስ ነበረበትና፤ "የመጨረሻዋ ሚጋን" ትባላለች አለና ጨረሰ:: ሂላሪና አሌክሳንድራ ይበልጥ ተጠጋግተው ቆሙ:: ኢሊንን ለማየት የደፈረችው የሚሆነውን የማታውቀው እራሷ ሚጋን ብቻ ነበረች::

"ተከተሉኝ" አለችና የመኝታ ከፍላቸውን ልታሳያቸው ቀደመች :: ክፍሏ መስኮት የሌላት የእስረኞች ክፍል ትመስል ነበረ:: አንድ ያልተነጠፈ አልጋ ከአንድ ወገን አለ:: ከላዩም ላይ ያረጀ የተጠቀለለ ፍራሽ ነበር:: በወዲያ በኩል ደግሞ አንድ ያራስ ልጅ አልጋ አለ:: ያረጁ ዕቃዎች ከሚጣሉበት አካባቢ አግኝታው እንደሆነ እንጂ፤ እንደዚያ ያለ አልጋ በየትኛውም ሱቅ አይሸጥም ነበረ:: አንዲትም አምፑል ከኮርኒሱ ላይ ተንጠልጥላለች::

"በኋላ እናነጥፈዋለን" አለችና ኢሊን ፓተርሰን ወደነበረበት ክፍል ተመለሰች:: ወደ ሂላሪም አየት አደረገችና፤ "እስቲ ወደ ጓሮ ዙሪና የታጠበው አንሶላ መድረቅ አለመድረቁን እዩ" አለቻት:: ሂላሪ ግን ንቅንቅም ሳትል አፍጥጣ አየቻት:: ኢሊን እንደ ማፈር አለችና ወደ ፓተርሰን ዘወር በማለት "ዓይኖቿ ቁርጥ የእናቷን ይመስላሉ" አለች:: ፓተርሰንም "ሶላንጅን ታውቂያት ነበረ ማለት ነው?" ሲል በመገረም ጠየቃት:: ሶላንጅ ዎከር እህት እንዳለው አንድም ቀን አንስታበት አታውቅም ነበረ::

"አንድ ጊዜ ብቻ ተገናኝተናል:: ዎከር የተካፈለበት ተውኔት በቦስቶን ውስጥ ይታይ ስለነበረ አብራው መምጣቷን አስታውሳለሁ" አለችው::

ሶላንጅ ስለ ኢሊን አንስታ ለምን እንዳላጫወተችው የገባው አሁን ነበረ:: እንደ ዎከርም ሁሉ ሶላንጅ ጠልታት ነበር ማለት ነው:: ሶላንጅ ከጠላቻት ሴት ጋር ደግሞ ህፃናት ልጆቿን ትቶ መሄድ ጨነቀው:: ግን ከማን ጋር ያስቀምጣቸው? ለማንኛውም ሌላ ደህና ቤተሰብ እስኪያገኝላቸው ወይንም ማርጆሪ ጥቂት ለዘብ ብትል እንደሚወስዳቸው አሰበና ለጊዜው ትቷቸው ለመሄድ ቆረጠ::

ሂላሪ ለመኝታ ወደ ተሰጣቸው ከፍል አይታ ራሷን ነቀነቀች:: ከቁምሳጥን... አቅም እንኳን አልነበረውም:: ለልብሳቸው ማስቀመጫ

ወንበር፣ ጠረጴዛ፣ ኮመዲኖ የለም:: አንድ መለስተኛ የአዋቂ አልጋና እግሩ የተሰበረ የአራስ አልጋ!

"ገንዘቡንስ አምጥተሃል?" ስትል ሀፍረቷን የሸጠችው ኢሊን ፓተርሰንን ጠየቀችው:: እርሱ ግን ገንዘብ መስጠቱን ህፃናቱ እንዲያውቁበት አልፈለገም ነበረና ሰውነቱ ሽምቅቅ አለ፤ ሳይወድም ከኪሱ የታሸገ ፖስታ አውጥቶ ሰጣትና "ከህፃናቱ ምግብ ወጪ ጭምር ነው" አላት አፉ እየተጉ ላደፈ::

ልትታገስም ባለመቻሏም ፖስታውን እልጆቹ ፊት ቀዳ ገንዘቡን አውጥታ መቁጠር ጀመረች:: በፖስታው ውስጥ የነበረው ሁሉም ባለመቶ ብር ኖት ነበረ:: ቆጥራም እንደ ጨረሰች ወደ ህፃናቱ አየት አድርጋ ፈገግ አለች:: ለሚቀጥሉት ሶስት ወራት ህፃናቱን መኮሮኒና ሩዝ ብታበላቸው ሊተርፋት የሚችለው ገንዘብ ቀላል እንደማይሆን አውቃለች:: ሆኖም አሁንም ለማስመሰል ስትል፤ "ምናልባት ያልታሰበ ችግር ቢያጋጥም ስልክ ደውዬ አሳስብሃለሁ" አለችው ፓተርሰንን::

"እረ እኔም ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ልጆቹን ለማየት መመለሴ አይቀርም:: መቼም እናንተን ማስቸገር ቢሆንም አንዱን ቀን እመጣለሁ" አለና ከተቀመጠበት ተነሳ::

ፓተርሰን በዚያን ቤት ውስጥ ዓይኑ እያየና የሴትየዋን ሁኔታ እየተመለከተ ጨክኖ ጥሏቸው የሚሄድ አልመሰላትም ነበረ ለሂላሪ:: በአረንጓዴ ዓይኖቿም ፍጥጥ ብላ ትመለከተው እንደ ነበረ ያጤነው ፓተርሰን፤ "ምንም ሐሳብ እይግባሽ:: ከጥቂት ቀናት በኋላ መጥቼ ላያችሁ እሞክራለሁ:: ችግር ቢኖር ደግሞ ደውይልኝ" አላት:: ሂላሪ ቁርጡን አወቀችው:: በመናገር ምትክ አንገቷን ዘንበል አደረገች:: አውጥታ አትናገረው እንጂ በፓተርሰን ላይ ጥላቻዋ ጠነከረ:: 'ፓተርሰን ሌላው በደሉ አነሰና ለምን አሁን ደግሞ ካደግንበት አካባቢ አፈናቅሎ ይህን ወደ መሰለ አካባቢ አመጣን' ስትል በሆዷ ረግማዋለች:: ሂላሪ አቅም ቢኖራት በገደለችውም ደስታዋ ነበረ:: ልታደርገው አትችልምና በምትኩ ታለቅስ ወደነበረችው አሌክሳንድራ ሄዳ ታባብላት ጀመረ::

"አይዞሽ አክሲ ምንም የሚያስለቅስ ነገር የለም:: የመጣነው ለሽርሽር ነው:: የምንቆየው ለጥቂት ቀናት ብቻ ነው:: እስከዚያም ከባህሩ አጠገብ እየሔድን ስንጫወት እንውላለን" እለቻት::





ኢሊን ትጠጣ የነበረውን ቢራ አስቀምጣ "ወይ ውልፍች! ደግሞ የምን ወደ ባህሩ ዳር እየሄዱ ጨዋታ! እግራችሁን ሰብስባችሁ መኖር አለባችሁ" አለችና ተቆጣች:: ከፓተርሰን ላይ አምስት ሺህ ብር ተቀብላለች:: ከዚያም በተረፈ ሂላሪ ጥሩ የቤት ሰራተኛ ሊወጣት ይችላል:: እህቶቿን ካጣጠበችና ከመገበች በኋላ ቤት በማፅዳት፣ ምግብ በማብሰልና በሌላ ሌላም ልትረዳት እንደምትችል ስታስበው ውስጥ ውስጡን ፈንጥዛለች:: ጥቂት ችግር ብትፈጥር ገና በእግሯ ድኩል ድኩል የምትለው ሚጋን ናት:: እርሷን ለመጠበቅ ደግሞ የአሌክሳንድራ ተግባር ይሆናል:: ይህን ሁሉ እያሰበች ሌላ ቢራ ከፈተችና ሲጋራዋን አያይዛ ከቴሌቪዥን ፊት ለፊት ተዝናንታ ተቀመጠች:: ልጆቹም ከፊቷ ዘወር እንዲሉ በመፈለግ "አንሶላውን አስገብተሽ አልጋውን አታነጥፊም?" አለቻት ሂላሪን በቁጣ ጭምር::

አንሶላዎቹ የተቀደዱ ቢሆኑም ንፅህናቸው ደህና ነበረ:: ሂላሪ ጨቅላዋ ሚጋንን በእንቅልፍ ልቧ ተንከባላ እንዳትወድቅ በመፍራት እንካሳዋን የአራስ አልጋ ከበስተግድግዳው በኩል አድርጋ አነጠፈች:: ከዚያም የነርሱን አልጋ አንጥፋ ከጨረሰች በኋላ፤ አሌክሳንድራና ሚጋንን ወደ መታጠቢያ ቤት ወስዳ ገላቸውን አጠበቻቸው:: የሚጠጡትም ውሃ ከሰጠቻቸው በኋላ ወደ መኝታ ክፍላቸው ተመልሰው ተቀመጡ::

"ይሄ ቤት ደስ አይልም" አለች አሌክሳንድራ ድምጿን ዝቅ አድርጋ:: ሲጋራ ካፏ የማይለየውንና ደጋግማ ቢራ የከፈተችውን ኢሊንን እንዳትሰማት ፈርታ ነበረ:: ቀጠልም አደረገችና፤ "እውነት ይቺ ሴት የእኛ አባት እህት ናት?" ስትል ሂላሪን ጠየቀቻት::

"አዎን" አለቻት ሂላሪም በማንሾካሾክ:: ለልብሳቸው እንኳን መስቀያ የተሰጣቸው ነገር አልነበረም:: በክፍሉ ውስጥ መቀመጫ ወንበር የለም:: እና እንደዚያ ግዴለሽ የሆነችውን ሴት አክስት ትሆናለች ብሎ መገመቱ ለአሌክሳንድራ ጭንቅላት ከብዶባታል:: ኢሊን ወደነሂላሪ መኝታ ክፍል የመጣችው አስራ አንድ ሰዓት ሊሆን ሲል ነው:: የልጆቹ አልጋ በደንብ ተነጥፏል:: ሚጋን እንቅልፍ ቢወስዳትም አሌክሳንድራና ሂላሪ አልጋቸው ላይ ጉን ለጉን ተቀምጠው ነበረ::

"እየለመዳችሁ ነው:: አይደለም እንዴ?" አለች ኢሊን በራፉ አጠገብ እንደቆመች::

ሂላሪ ከተቀመጠችበት ብድግ አለችና "መልመድስ እየለመድን ነው:: ግን ጠዋት በበላነው ቁርስ እስከ አሁን በመቆየታችን ርቦናል:: ስለዚህ ምግብ እንዳለ ቢሰጠን" አለች በአረንጓዴ ዓይኖቿ ጭምር እያስተዛዘነች:: ስለ ልጆቹ መብላት አለመብላት ለኢሊን ተዝ አላላትም ነበረ:: በቤቱ ውስጥ ምንም ምግብ አልነበረም:: ኢሊን ማቀዝቀዣውን ከፈት አደረገችው:: ግን በውስጡ ከቢራ በስተቀር ሌላ ምንም የለም:: ኢሊንም ባሏም ጃክ እቤት በመመገብ ምትክ ሆቴል ማዘውተሩን ይመርጡ ነበረ:: መኖሪያ ቤታቸውን የሚጠቀሙበት ለመጠጥ ብቻ ይመስላል::

"ለካ አልበላችሁም ኖሯል:: በነገራችን ላይ አንቺ የትኛዋ መሆንሽ ነው?" አለቻት ኢሊን::

"ሂላሪ" ስትል መለሰችላት:: ሂላሪ አመለካከቷ በልቧ ያመቀችውን ጥልቅ ጥላቻ እንዳያንፀባርቅባት ተጠንቅቃ ነበረ:: ዕድሜዋ ገና ዘጠኝ ዓመት ቢሆንም በእናት አባቷ ሞትና ባሁኑ ዕድል ፋንታቸው ከአዋቂም የበለጠ ሐዘንና መከራ ደርሶባታል::

"ወደ ግሮሰሪ ሔደሽ አንድ ሁለት ቆርቆሮ ቶኖ ብትገዥስ?" አለቻት ሂላሪ::

"ቶኖ?" ስትል ሂላሪ መልሳ ተናገረች:: ምናልባትም ቶኖ የሚባል የምግብ ስም ስትሰማ የመጀመሪያ ቀኗ ሊሆን ይችላል:: ኢሊንም ብትሆን የሂላሪ አጠያየቅ ህሊናዋን ሸንቆጥ እንዳደረገው ከፊቷ ላይ ይታወቃል:: እነ ሂላሪ በቅምጥል ያደጉ ህፃናት ናቸው:: ከእናታቸውም ሞት በኋላ የቤት ሰራተኛዋ ምግብ ታዘጋጅላቸው እንጂ ከዚያ በፊት ግን ሶላንጅ ራሷ ነበረች:: ከትኩስ ምግብም በስተቀር በቆርቆሮ የታሸገ ምግብ ቀምሰው አያወቁም::

ኢሊን ወደ መኝታ ክፍሏ ገብታ ተመለሰችና ለሂላሪ አንድ የአምስት ብር ኖት ከሰጠቻት በኋላ፤ "በስተግራ የሚወስደውን መንገድ ይዘሽ ከመታጠፊው ጋ ስትደርሺ ግሮሰሪውን ታገኛለሽ:: ለእኔም ቢራ እንድትገዥልኝ" አለቻት::

ሂላሪ ወደ ግሮሰሪው ስትሄድ እህቶቿን ይዛ ነበረ:: እዚያ ቤት ውስጥ ብቻቸውን ትታቸው ትሄዳለች ማለት የማይታሰብ ነው:: እንደ አካባቢው መኖሪያ ቤቶች ሁሉ ግሮሰሪውም ያረጀ፣ ውስጡም ንፅህና የሚጎድለው ነበረ:: ሂላሪ በቅድሚያ እንደ ተነገራት የጠየቀችው ሁለት





ቆርቆሮ ቶኖ ሲሆን ከዚያም ዳቦ፣ ማርመላታና ቅቤ፣ እንደዚሁም ግማሽ ደርዘን ዕንቁላሎች፣ ጠርሙስ ወተትና የታሸገ የአራስ ልጅ ምግብ ገዛች:: በተጨማሪም የታዘዘችውን ቢራ አስመጥታ ከፌስታል ውስጥ ከታ ወደ ቤት ተመለሰች:: በመንገድም ላይ ለእህቶቿ ስለምታበላቸው ራትና በማግስቱም ስለምትሰጣቸው ቁርስ ስታስብ ከቤት ደረሰች::

ከበራፉም ኢሊን ትጠብቃት ኖሮ "ቢራዬስ?" ስትል ጠየቀቻት::

"ከፌስታሉ ውስጥ ነው" አለቻት ሂላሪ::

"በይ ቶሎ አምጪልኝ" አለችና አምባረቀችባት:: አሌክሳንድራ በኢሊን ያልታሰበ ጩኸት ክው አለችና ይዛው የነበረውን የትንሿን ሚጋንን እጅ ጭብጥ አደረገችው:: ማንም ሰው ቢሆን በእርሷም ሆነ በእህቶቿ ጮኸባቸውና ተቆጥቷቸው አያውቅም ነበረ::

ሂላሪ ቶሎ ብላ ቢራውን ከፌስታሉ ውስጥ አውጥታ እንደሰጠቻት ኢሊን "ያስመለሽውስ ገንዘብ?" ስትል ሁለተኛውን ጥያቄዋን አቀረበችላት:: ሂላሪም የያዘችውን ጥቂት ሳንቲሞች ሰጠቻት:: ኢሊን ስታያት ቆየችና፤ "ይሄ ብቻ ነው እንዳትይኝ?" አለቻት ከላይ እታች እየገላመጠቻት:: ሂላሪ ግራ ተጋብታ ዝም በማለቷ ኢሊን ሳንቲሞቹን ወርውራ ከፊቷ ላይ ከመታቻት በኋላ፤ "የተቀረውን ገንዘብ ምን አደረግሺው? የትም ነው በትነሽው የመጣሽው?" ስትል አፈጠጠችባት:: ሁኔታዋን ላየው ሰው ፓተርሰን ከጥቂት ሰዓታት በፊት የሰጣትን በፖስታ የታሸገ ብር የረሳችው ትመስል ነበረ::

"ለራታችን የሚሆን ምግብ ገዛሁበት:: ለቁርሳችንም የሚሆን እንቁላል" አለቻት ሂላሪ::

"እኔ ግዢ ያልኩሽን ብቻ እንጂ አንቺ እንደመሰለሽ መግዛት የለብሽም! ለወደፊቱም ከእኔ ትእዛዝ ውጪ አንድ ነገር እንዳታደርጊ አስጠንቅቅሻለሁ! ገባሽ!" ስትል አሁንም ኢሊን ጮኸችባት::

ሂላሪ በኢሊን አነጋገር በጣም ደንግጣ ነበረ:: ለእህቶቿ ራት በምታዘጋጅበት ጊዜ ሁሉ እጆቿ እንደተንቀጠቀጡ ነበረ:: ሂላሪ እህቶቿን ራታቸውን በደንብ ካበላቻቸውና የሚጠጡትም ወተት ከሰጠቻቸው በኋላ እቃዎቹን ለማጣጠብ ወደ ወደ ምግብ ማዘጋጃው ክፍል ሄደች:: መርከበኛ የነበረውም የኢሊን ባል ጆንስ የመጣው በዚያን ጊዜ ነበረ:: ሂላሪም ገና እንዳየችው ሰውየውን ከኢሊንም ይበልጥ ፈራችው፤ ጆንስ እጅግ ግዙፍ

ሰው ነበረ:: በዚያም ላይ የለበሰው ቱታ ስለነበረ የደረቱን ስፋትና የጡንቻውን ፈርጣማነት አጉልቶታል:: ሞቅ ብሎት ነበርና ገና ከበራፉ ከመድረሱ በኢሊን ላይ ይጮህባት ጀመረ:: ሲመታትም ሲል ከጠረጴዛው ላይ የነበረውን ፖስታ አንሥታ እያሳየችው ፈገግ አለች:: ፖስታውን ከእጇ ላይ መነጨቀና ከውስጡ ያለውን ገንዘብ አውጥቶ ቆጠረው:: ሶስት ሺህ ብር! ከመጠን በላይ በመደሰቱ ሊስቄ ቀየና ኢሊንን ከሶፋው ላይ አቅፎ እንስቶ ይስማት ጀመረ:: «የእኔ ኢሊን! የእኔ ቆንጆ! የእኔ ጎበዝ» ሲል አቆላመጣት:: ፓተርሰን ከሰጣት ገንዘብ ውስጥ ሁለቱን ሺህ ብር ቀንሳ መደበቋን ቢያውቅ ኖሮ ግን እንደዚያ እንዳቀፋት እንደ እንቁላል በሰባበራትም ነበረ::

ሂላሪ ዕቃውን ማጠቧን ትታ ሁኔታቸውን ታጠና ነበረ:: ጆንስ አውሬ መስሎ ታያት:: በተለይ ዓይኖቹ ቁርጥ የዓሳማ ዓይን ነበረ የሚመስሉት:: ሂላሪ መፍራት ብቻ ሳይሆን ለዓይኗም ስለቀፈፋት በጣም አድርጋ ነበረ የጠላችው::

ጆንስ ኢሊንን ከሶፋው ላይ መልሶ እያስቀመጣት «ለምን ያህል ጊዜ ነው ከእኛ ጋር የሚቆዩት?» ሲል ጠየቃት::

«ያመጣቸው ሰው ሌላ መጠለያ እስከሚያገኝላቸው ድረስ፤ ለጥቂት ሳምንታት ብቻ ነው እዚህ የሚቆዩት» አለችው ኢሊን::

ሂላሪ እንደጠረጠረችውም ወደ ዱሮው ቤታቸው አይመለሱም ማለት ነው:: ፓተርሰን ቢደብቃትም ሂላሪ ግን ከኒውዮርክ ቤታቸው በደህና እንዳላወጣቸው ታውቃት ነበረ::

«ሌሊቱን ስንደንስ ማሳለፍ አሰብን» አላት ጆንስ::

«ህፃናቱን ብቻቸውን ትተናቸው?» አለች ኢሊን::

«ትልቋ እህታቸው አለች:: ምን እንዳይሆኑ ነው? የዘጠኝ ዓመት ልጅ ህፃናትን መጠበቅ ቀርቶ እንደኔ ዓይነቱንም ማስተናገድ ትችላለች» አለና ሳቀ:: ኢሊንም ሳቀች:: ሂላሪ ግን በፍርሃት ሰውነቷ ይንቀጠቀጥ ጀመረ::

ኢሊን ከተቀመጠችበት ተነስታ አቀፈችውና «የማይበርድልህ መርከበኛ! ... ብለህ ብለህ የዘጠኝ ዓመት ህፃን ...» ስትል ጆንስ ጉንበስ





ብሎ ከንፈሯን በኃይል ሳማት:: እጁንም ከፒጃማዋ ውስጥ አስገብቶ ጭኖቿን እያሻሸ፤ «በስንት ዓመትሽ ነው አንቺ የጀመርሽው!» አላት::

«በአስራ ሦስት» አለችውና ሳቀች

«ውሸታም» አለና እርሱም ሳቀ::

«አስራ ሁለት» አለችው::

«አስራ አንድ» አለና ጭምቅ አድርጎ አቀፋት::

«እሺ ይሁንልህ» አለችና ተራዋን ሳመችው:: ከዚያም ከእቅፉ ወጥታ ቢራ ልታመጣ ልትሄድ ስትል ሂላሪን አይታት ኖሮ «አንቺ ሾካካ! ከዚህ ተለጥፈሽ ለካስ የምንነጋገረውን ሁሉ ስታዳምጪ ኖሯል?» አለች ልትመታት እየቀረበቻት::

ሂላሪ ወደኋላዋ እያፈገፈገች «አይደለም! አይደለም! የተመገብንባቸውን ዕቃዎች ሳጥብ ነበረ:: የዛሬን ይቅር በይኝ!» አለቻት::

«በይ አሁን ወደ ክፍልሽ ሂጂ!» ብላ ጮኸችባትና ቢራውን አውጥታ የማቀዝቀዣውን በር በኃይል ዘጋችው:: ከዚያም «እነኚህ ገሬዎች!» እያለች በማጉተምተም ወደ ጆንስ ሔደች::

ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ሲሆን ኢሊንና ጆንስ ተያይዘው ወጡ:: እነ አሌክሳንድራና ሚጋንም እንቅልፍ ወስዷቸው ነበረ:: ሂላሪ ግን በጀርባዋ ጋደም እንዳለች የምታስበው ሌላ ነገር ነበረ:: እናቷ ታወሰቻትና እንባዋ ሳይታወቃት ተለል እያለ ጆሮዎቿን አጥቦ ወረደ:: እናታቸው በህይወት ብትኖር ኖሮ ልጆቿን በዚያን ዓይነት ቤት ያውም ኢሊንና ጆንስን ከመሰሉ አረመኔዎች ጋር ለደቂቃ እንኳን እንዲቆዩ ባላደረገችም ነበረ:: ለልጆቿ ሌላ ቤት በፈለገችላቸውም ነበረ:: ለአምስት ዓመቷ አሌክሳንድራም ሆነ ለታናሿ ለሚጋን ከእንግዲህ እንደ እናት ያለቻቸው ሂላሪ ብቻ ነች:: ስለዚህ ሂላሪ ለእህቶቿ አንድ ነገር ማድረግ ነበረባት:: ለእህቶቿ ሌላ ቤት መፈለግ አለባት:: ይህንን ለማድረግ ደግሞ ገንዘብ እንደሚያስፈልግ ታውቀዋለች:: ገንዘብ ልታገኝ የምትችልበትንም ዘዴ ማሰብ ነበረባት:: ከእንግዲህ ለእህቶቿ ያለቻቸው አለኝታ እሷ ብቻ ናት:: እነርሱም ቢሆኑ እሷኑ እንደ እናት የሙጥኝ ብለው ነው:: ህፃናቱ አንዳች ነገር እንዳይሆኑ መጠንቀቅ ነበረባት:: ኢሊንና ጆንስ ካሉበት አካባቢ መራቅ አለባቸው:: ለዚህም ያለው አማራጭ ወይንም አረም በተዋጠው ሜዳ ላይ ማጫወት

አለበሊዚያም ከመኝታ ክፍላቸው እንዳይወጡ ማድረግ ነበረ:: በተረፈ ግን በምግብ እንዳይጉዱ ከራሷም ፋንታ እየቀነሰች ልትመግባቸው፣ በየዕለቱ ገላቸውን ልታጥባቸውና በንፅህና ልትይዛቸው አቀደች:: ይህንንም በማሰላሰል ላይ እንዳለች እንቅልፍ ወሰዳት:: ጠዋትም ላይ የቀሰቀሳት በሸንት ጨርቋ መቀዝቀዝ ሚጋን ያሰማችው ለቅሶ ነበረ::

ሚጋን ዓመለ ደርባባ ልጅ ነበረች:: ፀጉሯም እንደ እናቷ ወርቃማ ሲሆን ትላልቅ ሰማያዊ ዓይኖቿ ግን የአባቷን ነበረ የሚመስሉት:: የሂላሪ ፀጉር ደግሞ የአባቷን ሲመስል ዓይኖቿ ቁርጥ የእናቷን ነበሩ:: ፍፁም ሶላንጅን ትመስል የነበረችው አሌክሳንድራ ብቻ ናት:: ፀጉሯ ወርቃማ ነው:: ዓይኖቿም ትላልቅና አረንጓዴ ነበሩ:: ሌላው ቀርቶ ፈገግታዋና አሳሳቋ ለየት ያለ ሆኖ ለሂላሪ የእናትም የእህትም ፍቅር ያስታውሳት ስለነበረ፤ ባየቻት ቁጥር ልቧን ጭንቅ ይለው ነበረ::

ኢሊንና ጆንስ ከመነሳታቸው በፊት ለእህቶቿ ቁርስ አዘጋጅታ ከመገበቻቸውና ፀጉራቸውን አበጥራ አንድ ዓይነት ቀሚስ ካለበሰቻቸው በኋላ ለጨዋታ ወደ ውጪ አወጣቻቸው:: እርሷ ግን ዛሬም የለበሰችው ያንኑ እናቷ በመጨረሻ ጊዜ የገዛችላትን ቀሚስ ሲሆን ያንን ቀሚስ በለበሰች ቁጥር እናቷ አብራት ያለች እየመሰላት ትፅናና ነበረ::

ኢሊን ከመኝታዋ የተነሳችው ከአኩለ ቀን በኋላ ነው:: ዓይኖቿን እያሻሸችና እያዛጋች በራፉን ከፈተችና እየተሯሯጡ በሚጫወቱት በነሂላሪ ላይ "እናንተ መናጢዎች! ከዛሬው መንደርተኛውን ጤና መንሳት ጀመራችሁ!" ስትል ጮኸችባቸው:: በእህቶቿ እግር ስር ድክ ድክ የምትለው ሚጋን እንኳን በኢሊን ጩኸት ፈርታ ባለችበት ቆማ ነበረ:: "ገፊዎች!" አለችና ኢሊን ወደ ውስጥ ገብታ በሩን በኃይል ዘጋችው:: ከዚያም ቢራ ይዛ ቴሌቪዥኗን ከተፈተች:: እንደማያልፍ የለምና እነ ሂላሪ ከኢሊ ጋር ለአንድ ሳምንት ያህል ቆዩ:: የኢሊን ባል ጆንስ ወደ ስራ የሚሄደው በሌሊት ስለነበረ የሚመጣውም አምሽቶ በመሆኑ ሁለቱ ህፃናት አይተውት እርሱም አይቷቸው አያውቅም:: ሂላሪ ግን በጥዋት ተነስታ ለእህቶቿ ቁርስ በምታዘጋጅበት ሰዓት አንድ ጊዜ ስላገኛት፤ ቂጧን እንደ ቀልድ መታ አድርጎ "ያደግሽ ዕለት አገር ታፋጂያለሽ!" ሲል ተናግሯት ነበረ:: ሂላሪም ያንን ቀን ምን ጊዜውም አትረሳውም::

ፓተርሰን በሁለተኛው ሳምንት ስልክ ደውሎ ነበረ:: ሂላሪም ያነጋገረችው በኢሊን ፊት ስለነበረ ስለ ሁኔታቸው እንደልብ ለመናገር አልቻለችም:: አሌክሳንድራ ሌሊት ሌሊት መቃዠት ጀምራለች:: ሚጋንም





ባልታሰበ ሰዓት ማልቀስ አምጥታለች:: ክፍላቸው አፍንፍን ያለችና መስኮትም የሌላት በመሆኑ ሙቀቱ አያድርስ ነበር:: በምግብም በኩል እየተጎዱ ነው:: ሂላሪ ለእህቶቿ ብትርገበገብም ምን እንደምታ ደርግላቸው ግራ ገብቷታል:: የዘጠኝ ዓመቷ ሂላሪ ያለ ዕድሜዋ ዛሬ እናትም ሞግዚትም ነበረች:: ለፓተርሰን ስለችግራቸው አንስታ አንድም ነገር አልተናገረችም:: "ደህና ነን" ብላ ብትመልስለትም በሆዷ እየረገመችው ነበር::

"ከጥቂት ቀናት በኋላ እደውልልላችኋለሁ" አለና ፓተርሰን ስልኩን ዘጋ:: ሂላሪ ለፓተርሰን የስልክ ጥሪ ጉጉት አላደረባትም:: እሱም ቢሆን ቃሉን አክብሮ አልደወለላቸውም ነበረ:: በዚያ ሁኔታ እንዳሉ ከሦስት የበጋ ወራት ውስጥ ሁለቱ አለቁ:: ሦስተኛውንም ወር ተያያዙት:: ፓተርሰንም ልጆቹን የት እንደሚያደርሳቸው መላ ጠፍቶት መጨነቅ ጀመረ::

# ምዕራፍ ሰባት

ሦስተኛው ወር ወደ መገባደዱ ሊደርስ ነበር ፓተርሰን ቀደም ሲል ዘግንኖት የነበረውን አንድ የመፍትሄ ሐሳብ በአእምሮው ለማመላለስ የተደገደደው:: ሦስቱን ህፃናት በአንድነት ወስዶ የሚያሳድጋቸው ቤተሰብ ባይገኝም ሁለቱን በጉዲፈቻ ለመቀበል ፈቃደኛ የሆኑ ሁለት የተለያዩ ሰዎች አግኝቶላቸው ነበር:: ግን እነኛን ህፃናት ማለያየቱ ከባድ ኃጢአት ሆኖ ተሰማው:: በሌላ በኩል ደግሞ ለዚህ ሁሉ ጥፋት መንስኤው እናታቸውን የገደለው አባታቸው እንጂ እርሱ ባለመሆኑ ለመፅናናት በቅቷል:: ስለዚህ ሦስቱንም በአንድነት ለማዳን ባይችልም በመለያየት የተሻለ ህይወት እንዲያገኙ ለማድረግ ወሰነ::

ለአንዲቷ ህፃን በጉዲፈቻ አባት ለመሆን ፈቃደኛነቱን የገለፀለት ጆርጅ ጉርሐም የተባለ የቅርብ ጓደኛው ነበር:: ከፓተርሰን ጋር የህግ አገልግሎት ድርጅት አቋቁመው አብረው ለረጅም ጊዜ ሰርተዋል:: የጎርሐም እድሜ ለጡረታ ቢቃረብም ያገባት ልጅ ግን በዕድሜዋ ከእርሱ በአርባ ዓመታት የምታንስ ማርጋሬት ዌሊንግተን የምትባል ውብና የቫሰር ዮንቨርሲቲ ምሩቅ ነበረች:: ጎርሐም በሞት ከተለየችው ቀድሞ ሚስቱ ልጅ አልወለደም:: በመሆኑም ከማርጋሬት ልጅ ሊያገኝ ይችላል ብሎ ለመገመት ያዳግታል:: የሃያ ዓመቷ ማርጋሬት እኩያዋን ወጣት ታገባለች ሲሉ ቤተሰቦቿ ጓጉተው ነበር:: እርሷ ግን አዛውንቱን ጎርሐምን መረጠች::

ለምን እንደዚያ እንዳደረገች ምክንያቱን የሚያውቅ አልነበረም:: የሚገርመው ሁለቱም ይፋቀራሉ:: ህይወታቸውን የተሟላ ለማድረግ ግን አንድ የሚጐድላቸው ነገር ነበር:: እንደ ባልና ሚስት ልጅ የላቸውም:: ፓተርሰን ለጉርሐም ስለነ ሂላሪ ካንዴም ሁለቴ እያነሳ አጫውቶታል:: ጎርሐም የሰማውን ለሚስቱ ለማርጋሬት ነግሯት ኖሮ ይመካከሩና ከሶስቱ ህፃናት መካከል አሌክሳንድራን በጉዲፈቻ ልጃቸው ሊያደርጓት ይወስናሉ:: ጎርሐም ይህንኑ ሐሳብ ለፓተርሰን ይገልፅለታል::

ውሎም ሳያድር ዴቪድ የተባለ ሌላ የህግ ባለሙያ ፓተርሰንን ለማነጋገር ይመጣል:: የርሱም ፍላጐት እንደ ጎርሐም ሁሉ ከሦስቱ





ህፃናት አንደኛዋን የጉዲፈቻ ልጅ ለማድረግ ነበረ:: ዴቪድ ገና የሰላሳ አራት ዓመት ጎልማሳ ሲሆን፤ ባለቤቱም ሬቤካ የሰላሳ ዓመት ሴት ነበረች:: ከተጋቡ አስር ዓመት ቢያልፋቸውም ልጅ አልነበራቸውም:: ስለ ሬቤካ መካንነት ደግሞ ብዙ ሐኪሞች አረጋግጠዋል:: ለሚዋደዱት ባልና ሚስት ግን ልጅ ማጣት ምክንያት ሆኖ ሊያለያያቸው አልበቃም ነበረ:: ለልጅ ይጓጉ ነበርና በወሬ ወሬ ስለነ ሂላሪ ይሰማሉ:: ፍላጐታቸው እንኳን ሦስቱንም ህፃናት ሳይለያዩ ለማሳደግ ነበር:: ግን ባልና ሚስት ሁለቱም ጠበቆኞች በመሆናቸው ሶስት ህፃናት በእንክብካቤ ለማሳደግ በቂ የሚያ ጊዜ አይኖራቸውም:: በሁለቱም በኩል እስከዚያ የደረጁ አልነበሩም:: ስለዚህ አንደኛዋን ህፃን ብቻ እንደ ልጃቸው አድርገው ለማሳደግ መረጡ:: ምርጫቸውም ምንም በማታውቀው በአራሷ በሚጋን ላይ አረፈ::

የአሌክሳንድራ የጉዲፈቻ አባት ለመሆን የፈለገው ጎርሐም ሐብታም ስለሆነ በጥሩ ሁኔታ ሊያሳድጋት እንደሚችል ፓተርሰን በቅርብ የሚያውቀው ነገር ነው:: ዴቪድና ሬቤካም፣ እንደ ጎርሐም ባለ ብዙ ንብረት ባይሆኑም በስራቸው ላይ ሐቀኞችና ታታሪዎች ነበሩ:: በመሆኑም ሚጋንም መልካም አስተዳደግ እንደምታገኝ ተማምኗል:: ከእንግዲህ የቀረችው ሂላሪ ብቻ ነች :: ስለ እርሷ ደግሞ ሌላ መፍትሄ መሻት ነበረበት:: ስለ ሂላሪ ጉዳይ ለሚስቱ ሊያነሳባት ወሰነ:: ማርጆሪ ግን ከቀድሞ አቋሟ ንቅንቅ ባለማለቷ የሚያደርገው ጠፋው:: ያለውም አማራጭ አንድ ብቻ ሆነ:: ፓተርሰን የዎከርን ማናቸውንም ዕዳ ከፍሎ በእጁ አስር ሺህ ብር ይገኝ ነበር:: ስለዚህ ያንን አስር ሺህ ብር ለኢሊን ለመስጠትና ሂላሪ ከርሷ ጋር እንድትኖር ለማድረግ ወሰነ::

የአሌክሳንድራና የሚጋን የጉዲፈቻ ልጅነት በፍርድ ቤት ከፀደቀ በኋላ ፓተርሰን ለኢሊን ስልክ ደወለላት፤ ስለ እቅዱም አንስቶ አጫወታት:: ኢሊንም አስር ሺ ብር እስካገኘች ድረስ ሂላሪን ላልተወሰነ ጊዜ አብራት እንድትኖር ለማድረግ ፈቃደኝነቷን ገለፀችለት:: ለኢሊን የታያት አስር ሺህ ብር ብቻ አልነበረም:: ሂላሪን እንደገረድ ልታሰራት እንደምትችል ታይቷት ነበር:: ስለዚህም ለደስታዋ ወሰን አልነበረውም:: ከነአሌክሳንድራና ሚጋን መገላገሉ ሌላው እፎይታ ነበረ:: ሂላሪ ስራ ይዛ ዘንጋ ስትል ሚጋን ዱክ ዱክ ትልና ቴሌቪዥኑን ስትጎረጉር ኢሊን ብዙ ጊዜ እየደረሰችባት ቆንጥጣታለች:: አሌክሳንድራም ከሳሎን ገብታ መፅሔት ስታገላብጥ አግኝታት ፊቷ እስከሚቃጠል በጥፊ አልሳታለች:: ሂላሪ ግን ሲበዛ ስለምትፈራት እንዳሻት ትታዘዛት ነበር:: እና «እናንት ገፊዎች» እያለች በየዕለቱ ከምትለድባቸው ሦስት ህፃናት ውስጥ እርባና የሌላቸውን ሁለቱን

መገላገል ለዓመስ ቁጡዋ ኢሊን ደስታዋ ነበር። ከፓተርሰንም ጋር ስላደረገችው አዲስ ድርድር ለባሏ ለጆንስ ማስታወቅ ነበረባት። የስምምነቱንም ገንዘብ ከአስር ወደ ሁለት ሺህ ብር ዝቅ አድርጋ ነገረችው።

"ለምን ሦስት ሺህ እንኳን ሳይሆን?" አላት ጆንስ እራሱን እያወዛወዘ።

"መቼስ የወንድሜ ልጅ መሆኗ ቀረ? በዚያ ላይ ደግሞ ያዘዝኳትን ሁሉ ትሰራልኛለች" አለች ኢሊን ዓይኖቿን በማቁለጭለጭ።

"ከመለለሽ ይሁን" አለ ጆንስ ለመጠጫው ከኪሱ የሚገባው ብር እየታየው።

"አንተስ አይመስለህም እንዴ?" አለችው የተቆረቆረችለት መስላ።

"ይመስለኛል እንጂ! ብቻ ረብሻና ሌላ ችግር እንዳትፈጥር" አለ ጆንስ።

"በጥፊ ማላስ ነዋ!" አለችው ኢሊን።

"እዎን" ብሎ በመሳቅ ስምምነቱን ገለፀ። በዚያን ምሽት ኢሊን የመታጠቢያ ቤቱን በር ዘግታ ከአልባሌ ቦታ ደብቃው የነበረውን የተጠቀለለ ስቶኪንግ ፈለገችና አገኘችው። ቋጠሮውንም ፈታችና ባለ መቶ ብር ኖቶች አወጣች። ደጋግማ ቆጠረችና ፈገግ አለች። ፓተርሰን ከሰጣት ከመጀመሪያው ክፍያ ሁለት ሺህ ብር ከባሏ ደብቃ ልታስቀር ችላለች። አሁንም ከሚከፍላት አስር ሺህ ብር ውስጥ ስምንቱን ሺህ ከጨመረችበት፣ ብትወደውም ዱላው ያስመረራትን ባሏን ጥላው ብትሔድ ከችግር ላይ እንደማትወድቅ ተለማት። ከመስላት ሂላሪን ይዛት ልትሄድ ትችላለች። ይህም እንደምታበረክተው አገልግሎት ታይቶ የሚወሰን ይሆናል። የማትጠቅማት ከመሰላት ግን ለምን ብላ ታስከትላታለች? እደረሰችበት ብትደርስ ኢሊን ምን ተዳዋ?

ፓተርሰን ወደ ቦስቶን የተመለሰው ከሶስት ወራት በኋላ ነበር። አብራውም አንድ ሞግዚት ነበረች። ሂላሪን ሲያያት በጣም ቀጥናለች። አሌክሳንድራና ሚጋንም ገርጥተው ነበር። ሙሉ ጤነኛ ስለመሆናቸውም ፓተርሰን ስጋት ገብቶት ነበረ። ሂላሪን ለብቻዋ ለማነጋገር ወደ ውጪ ይዟት ወጣ። ስለኑሯቸውም እንድትነግረው ጠየቃት። እሷ ግን ምንም





ልትመልስለት አልፈለገችም። ለዚያ ለሲኦል ኑሮ የዳረጋቸው እርሱ በመሆኑ ከመቼውም አሁን ጠልታው ነበረ። ላለፉት ሦስት ወራት ሂላሪ ስቃይዋን አይታለች። የኢሊንን እጅ ጠብቃ በምትወረውርላቸው ጥቂት ገንዘብ አብቃቅታ እህቶቿን መመገብ ነበረባት። የምታጥባቸው፣ የምታለብሳቸው፣ የምታበላቸው፣ የምታስተኛቸው እርሷ ነበረች። እነ ኢሊን እንዳይመቷቸው ነፍስና ስጋዋ እንደተቦጨቀ ከርማለች። እናታቸውን እያስታወሱ ሲያለቅሱ ከደረቷ አቅፋ የምታባብላቸው፣ ፀጉራቸውን እያሻሸች የምታፅናናቸው ሂላሪ ብቻ ናት። የሂላሪ የፊት ቆዳ የህፃን ልጅ ቢመስልም መንፈሷ ቆስሎ ነበር። ያም ሆኖ ለእህቶቿ ከዚያም የበለጠ መስዋእት ለመሆን ዕቅድ ነበራት። ዕድሜዋ አንድ ጊዜ አስራ ስምንት ዓመት ከሞላት ያገኘችውን ስራ ይዛ እህቶቿን ለማሳደግ ነበረ የሂላሪ ምኞት። ያም ቀን እንደሚደርስ ሂላሪ እርግጠኛ ነበረች።

ዛሬ ግን ፓተርሰን በህልሟም በውኗም ያላሰበችውን ነገር ሊያረዳት መጥቷል። እንደዚያ የምትንሰፈሰፍላቸውን እህቶቿን ለመውሰድ ነው አመጣጡ። አብረዋት አይኖሩም ማለት ነው። ዳግመኛም ልታያቸው የምትችለው ምናልባት አሳዳጊዎቻቸው ፈቃደኛ ቢሆኑ ነው። በዚህ ላይ ደግሞ ዴቪድና ሬቤካ አቋማቸውን ግልፅ አድርገዋል። ሚጋን ስለቤተሰቦቿ ምንም ነገር እንድታውቅ አይፈልጉም። ስለወላጆቿም የምታስታውሰው ነገር ስለማይኖር አዲስ ህይወት፣ አዲስ ስብእና እንዲኖራት ነው ፍላጐታቸው።

"ሂላሪ..." አለና ፓተርሰን የሚናገረው ጠፍቶት አፉ ተለጉሞ ቆየ።

"ምነው አጎቴ ፓተርሰን ዝም አልክ? ምን የደረሰ ነገር አለ?" አለችው ሂላሪ። ዳግመኛ ወደ ቀድሞው የኒውዮርክ ቤታቸው መልሶ እንደማይወስዳቸው ታውቃለች። ምናልባት ሦስቱ የበጋ ወራት በማለቃቸው ሌላ ቤት ፈልጐ ሊወስደን ይሆናል ስትል ሂላሪ አሰበችና "ልትነግረኝ ፈልገህ የፈራኸው ነገር አለ። አይዞህ በዕድሜዬ ልጅ ብሆንም ነገሮችን ለማመዛዘን እችላለሁ" አለች ስታበረታታው።

ፓተርሰን ማርጆሪን ምርር ብሎ የተራገመበት ጊዜ ቢኖር ያኔ ነበር። ከእህቶቿ ብትለይም ቢያንስ እንኳን ወደ ኒውዮርክ ይዟት በተመለሰም ነበር። የሂላሪ ዕድሜዋም አስር ዓመት በመድረሱ አንድም ሰው በጉዲፈቻ ልጅነት ሊወስዳት የፈለገ አልነበረም። የአስር ዓመት ልጅ ብዙ ነገር

ያውቃል:: ብዙ ነገር ያስታውሳል:: የእውነተኛ ወላጆቹን ፍቅር ስለሚያስላስልም የጉዲፈቻ ልጅነት አይፈልግም ነበረ::

"የምነግርሽ ... እንደው አንድ ነገር ነበር" አለና አሁንም ዝም አለ:: የሂላሪ መንፈስ በዚያን ጊዜ ተረበሸ:: ሰውነቷም ይንቀጠቀጥ ጀመረ::

ፓተርሰን እንደታወቃት ተሰማውና "እህቶችሽ... እህቶችሽ ለጥቂት ጊዜ ይለዩሽ ይሆናል" አላትና አረፈ::

"እነማን? ሚጋንና አክሲ" አለችና ስማቸውን ጠራች:: እንደዚያም መጠየቋ በመደንገጧ እንጂ ከሁለቱ በስተቀር ሌላ እህት እንደሌላት አጥታው አይደለም:: "ለምን ለምንድንነው የሚለዩኝ?" አለችው::

"ምክንያቱም ... "አለና ፓተርሰን እራሱን በሁለት እጆቹ ይዞ አቀርቅሮ ቆየ:: ሊነግራት ስለሚገባም "ምክንያቱም ሶስታችሁ በአንድነት ለመኖር ስለማትችሉ ነው:: አክስታችሁ ሁለቱን ልጆች ካልወሰድክልኝ ብላ በስልክ ጨቀጨቀችኝ:: ስለዚህ ለጊዜው ወደ ኒውዮርክ እወስዳቸውና ሊያስጠጋቸው ከፈለገ አንድ ሰው ቤት እንዲቆዩ አደርገቸዋለሁ" አለና ዋሸ:: የሂላሪ እንባ በጉንጮቿ ላይ ተለል እያለ ሲፈስ አየ:: ሊያባብላትም "እባክሽ ሂላሪ አታልቅሽ ... ያልሞከርኩት ነገር አልነበረም... እመኚኝ" አለና እጁን በትከሻዋ ላይ ለማሳረፍ ሲሞክር ሸሸችውና እህቶቿ ያኔውኑ የተለዩዋት ይመስል ወደ ቤት ውስጥ መሮጥ ጀመረች::

"ከእህቶቼ ማንም ሊለየኝ አይችልም!" እያለች ትጮህ ነበረ:: አልጋ ላይ ተቀምጠው ይጫወቱ የነበሩትም ሚጋንና አክሲን በሁለት እጆቿ እቅፉ ተንሰቅስቃ አለቀሰች፤ የት እንደምታደርሳቸው እምን ውስጥ እንደምታስገባቸው ጨነቃት:: እንቅ እድርጋ እንዳቀፈቻቸውም ማልቀሷን ቀጠለች:: አትውጣቸው ነገር የማይሞከር ነው:: ጭንቀቷን፣ ፍርሐቷን፣ ስቆቃዋን ለማን ታካፍለው? ልጆቹን በቁማቸው ሲለያይዋቸው አባቷ ባየ ኖሮ፤ ሶላንጅ ይህን ጊዜ በህይወት በኖረች ኖሮ... ሂላሪ ምንም ደጋፊ አይዞሽ ባይ የላትም:: በዚህ ዓለም ውስጥ ያሏት አክሲና ሚጋን ናቸው:: ተቆርቋሪ የላቸውምና ፓተርሰን በውድም ሆነ በግድ እህቶቿን እንደሚወስዳቸው ታውቃለች::

"ምን ሆነሻል ሂሊ?" አለቻት አሌክሳንድራ ቀና ብላ ዓይን ዓይኗን እያየች:: ሚጋንንም ሂላሪ ከደረቷ ጥርንቅ አድርጋ አቅፋት ስለነበረ ማልቀስ ጀመረች:: ሂላሪ ግን የሚጠገብ መስሏት የሚጋንን ጉንጮች እያገላበጠች ሳመች::





"ስለምወዳችሁ ነው ... እንደምወዳችሁ ታውቂያለሽ ... ከልቤ ነው የማፈቅራችሁ:: አክሲ አሁን የምነግርሽን እንዳትረሺ:: ምንጊዜም እንደምወዳችሁ እንድታውቂ"

"እሺ" አለች አሌክሳንድራ ቅር እያላት:: አሌክሳንድራ የአምስት ዓመት ልጅ ብትሆንም ከዛሬው የሂላሪ ሁኔታ የተጠራጠረችው ነገር ነበራት:: የሂላሪ ለቅሶ ያለ ምክንያት አለመሆኑም ተሰምቷት "ሂሊ የምታለቅሺው ለምንድነው? አንቺም ልትሄጂብን ነው እንዴ? እንደ አባታችንና እናታችን በሳጥን ውስጥ አድርገው ሊወስዱሽ ነው?" አለቻት::

ሂላሪ አሁንም እያለቀሰች ብትሆንም እራሷን አወዛወዘችና "እንደዚያ አይደለም አክሲ አይዞሽ እንደዛ ይሆናል ብለሽ አትፍሪ:: እይው አጐታችን ፓተርሰን አንቺንና ሚጋንን ለጥቂት ቀናት ያህል ወደ ኒውዮርክ ዘመዶቻችንን እንድታዩ ሊወስዳችሁ ነው" አለቻት:: አሌክሳንድራም ብትሆን ከርሷ ለመለየት እንደማትፈልግ ታውቀው ነበርና ልታደፋፍራት እንደሚገባ ሂላሪ ተሰምቷታል:: ትንሿ ሚጋን ግን ምናልባት ከእህቶቿ በመለየቷ ለጥቂት ቀናት ታለቃቅስ እንደሆነ ነው እንጂ፤ እንደ አክሲ ነገር ለይታ አታውቅም:: ሂላሪ እህቶቿን ምንጊዜም አትረሳቸውም:: የዕድሜ ልክ ትዝታዋ ይሆናሉ፤ በግዴታም ከእቅፎቿ ወጥተው የተወሰዱትን እህቶቿን አንድ ቀን ታገኛቸው ይሆናል:: ፓተርሰንና ከኒውዮርክ ያመጣት ሞግዚት ከበራፉ ላይ ቆመው እንዳየችም መቼም ይሁን መች እህቶቿን ፈልጋ ለማግኘት በሆዷ ማለች::

"ልንሄድ ነው ሂላሪ" አለ ፓተርሰን::

ሂላሪ ዓይኖቿ በእንባ እንደተሸፈኑ ከአንገቷ ጐንበስ አለች:: አሌክሳንድራ ግን "አልፈልግም! አልሄድም! ከሂሊ አልለይም!" እያለች የእህቷን እጅ እንቅ አድርጋ ይዛ እሪ ትል ጀመረ::

ሂላሪ የአሌክሳንድራን እንባ እየጠረገች "አክሲ እኔ ትልቅ ነኝ:: እና ምንም ልሆን አልችልም:: አንቺ ግን ለሚጋን ስትይ መሔድ አለብሽ:: ሚጋንን ብቻዋን የወሰዷት እንደሆነ ማን እህት ይሆናታል? ስለዚህ አክሲ ሚጋንን ለመጠበቅ ስትያ ሂጂ" አለችና ጉንጮቿን ሳመቻት:: አሌክሳንድራ ከሂሊ ለመለየት አልፈለገችም:: አልሄድም ብላ ለመቅረት እንዳትሞክር ደግሞ ፓተርሰን ምንም የማታውቀውን ሚጋንን ከአልጋው ላይ አንስቶ ለሞግዚቷ ሰጥቷታል:: ሂላሪም ሚጋንን ለመጠበቅ ለእኔ ስትይ ሒጂ

ብላታለች:: ሂላሪ ጨክና ሒጂ ካለቻት መሔድ አለባት ማለት ነው:: ያም ሆኖ አሌክሳንድራ ማልቀሷን አላቋረጠችም ነበረ::

ይህ ሁሉ ሲሆን ኢሊን በአካባቢው ዝር አላለችም:: የመታጠቢያ ቤቱን በር ዘግታ ፓተርሰን የሰጣትን የአስር ሺህ ብር ኖቶች ደጋግማ በመቁጠር ላይ ነበረች:: ገንዘቡ ከእጇ ቁንደገባና እየቆጠረችው እንደሆነም ብታይም እውነት አልመሰላትም ነበረ:: የደበቀችውን ስቶኪንግ አወጣችና በቀድሞው ሁለት ሺህ ብር ላይ ስምንት ሺህ ብር ጨመረችበት:: የባለ መቶውን ብር ኖቶች ክምር አየችና ሳቅ አለች:: ሳም አደረገችና ከስቶኪንጉ ውስጥ አስገባችው:: የተጣጠፈውን ስቶኪንግ ከደረቷ ላይ አድርጋ ስታስብ ቆየች::

አሌክሳንድራና ሚጋን ወደ መኪናው ውስጥ ሲገቡ ሂላሪ ብቻዋን ነበረች:: የተቀመጡትም ከሞግዚቷ ጋር ከኋላው ወንበር ነበረ:: ሚጋን ያን ጊዜ ነገር አመጣች:: እህቷን ከውጪ ቆማ በማየቷ እጆቿን ወደርሷ እየዘረጋች ምርር ብላ ታለቅስ ጀመረ:: አሌክሳንድራም እንባዋ እየተዝረከረከ "ሂሊ! ሂሊ!" ስትል ጮኸች:: ፓተርሰንም እንባው እየተናነቀው ከመኪናው ውስጥ ቶሎ ገባና ሞተሩን አስነሳ:: ማርሽ በማስገባትም ላይ እንዳለ "በቅርቡ መጥቼ አይሻለሁ" አላትና መኪናውን አንቀሳቀሰ:: ሂላሪ ግን ልትሰማው አልፈለገችም:: እህቶቿን ነጥቆ የሞት ሞት ገድሏታል:: እጆቿን ወደሚላቅሉት ህፃናት እያውለበለበች "የምወድሽ አክሲ ... የምወድሽ ሚጋን ... ደህና ሁኑ! ... ደህና ሁኑ!" አለችና በጉልበቷ ተንበርክካ ዓይኖቿን በእጆቿ ሸፈነች:: እምባዋም በጣትና ጣቶቿ መካከል ጀረር እያለ ወረደ::

እንደዛ ባለ ሁኔታ ለምን ያህል ጊዜ እንደቆየች አታውቀውም:: ብቻ አንድ እጅ ከኋላዋ ፀጉሯን ጐትቶ ከተንበረከከችበት እንዳስነሳት ነው የምታስታውሰው:: "የምን ማልቀስ ነው? ደግሞስ በአካባቢው ለሚተላለፈው ሰው እንደዚህ ሆነሽ ሲያይሽ እኛ የበደልንሽ አይመስለውም? በይ ቶሎ ወደ ቤት ግቢ!" አለቻት ኢሊን::

ሂላሪ ከመኝታ ክፍሏ ገብታ በሩን ዘጋችና አልጋው ላይ ድፍት አለች:: የአሌክሳንድርያና የሚጋን ጠረን ሸተታት:: እንደ ነጋ አሌክሳንድራንና ሚጋንን ገላቸውን አጥባቸዋለች:: ከዚያም ያለባበሰቻቸው ከአልጋው ላይ አስቀምጣቸው ነበረ:: ሚጋኝን የቀባቻት ፖውደር ሽታ፣ የአሌክሳንድራን ወርቃማ ፀጉር ያሸችበት የሻምፖ ጠረን በክፍሉ ውስጥ





እንዳለ ነው:: ለሂላሪ የእህቶቿ ትዝታ ከአሁኑ የማትችለው ነገር ሆነባት:: ትንሽም ልቧ ልትፅናና አልቻለችም::

አልጋው ላይ በግንባሯ እንደተደፋችም ለሰዓታት አለቀሰች:: በመጨረሻም ላይ እዛው ባለችበት እንቅልፍ ወሰዳት:: ሰውነቷም ዝሎ ነበርና ጭልጥ ባለ እንቅልፍ ውስጥ እንዳለች አንድ ነገር ታያት:: እህቶቿን ይዞባት የሄደውን መኪና ታገኘውና ልትደርስበት ትሮጣለች... ትሮጣለች...ትሮጣለች...ግን አትደርስበትም:: መኪናው ግን አሁንም ይታያታል፤ ትከተለዋለችም:: በመጨረሻ ላይም ትደርስበታለች:: እህቶቿ ግን ከወስጡ የሉም:: ያን ግዜም ረጅም የሳቅ ድምፅ ይሰማታል:: የስካሯሟ የኢሊን የማይቋርጥ የሳቅ ድምፅ... ጆንስ ከሶፋው ላይ አስተኝቶ ይኮረኩራት ነበረ::

## ምዕራፍ ስምንት

እህትማማቾቹን ጨክኖ ያለያየው፣ ስጋን ከስጋ ያቆራረጠው ፓተርስን ሂላሪን በስልክ አግኝቶ ሊያነጋግራት ብዙ ጊዜ ሞክሮ ነበረ:: ሂላሪ ግን ከእርሱ ጋር ለመነጋገር እንዴም ፈቃደኛ ሆና ወደ መናገሪያው አልቀረበችም:: ውሎም ባደረ መጠን ፓተርስን ስልክ መደወሉንም እስከናካቴው ተወው:: ስለ አሌክሳንድራና ስለ ሚጋን ሁኔታ ግን በቅርብ ይከታተል ነበረ:: ሁለቱም ህፃናት በእንክብካቤ በመያዛቸው እንደ ድሮው የደስ ደስ ያላቸው ልጆች ሆነዋል:: የአሌክሳንድራ የጉዲፈቻ አባትና እናት የሆኑት ጎርሐምና ማርጋሬት ሐብታሞች በመሆናቸውም እንደ ብርቅ ለሚያይዋት አዲሷ ልጃቸው የግል መምህር ቀጥረውላት ነበረ:: ዴቪድና ሬቤካም ሚጋንን ከነፍሳቸው አስበልጠው ይወዷት ነበረ::

የገና በዓል ሊዳረስ ሲል ሂላሪን ለማየት ወደ ቦስቶን ሄዶ ነበረ:: ፓተርሰን ከመኪናው ወርዶ ወደ ቤት ሲገባ በመስኮት ያየችው ሂላሪ በጓሮ በር ወጥታ ግቢውን ለቃ ሄደች:: ወደ ቤት የተመለሰችውም የፓተርስን መኪና የቆመችበትን ስፍራ ከለቀቀች በኋላ ነበረ:: ፓተርስን ሂላሪ ሆን ብላ እንደተደበቀችው ያውቃል:: ቢያገኛትም ኖሮ ልታነጋግረው ፈቃደኛ እንደማትሆን ግልፅ ነበር:: የእርስ ፍላጐት በዓይኑ ዓይቷት ስለሁኔታዋ ለመረዳት ነበረ:: ግን በመደበቋ ሳያያት ተመልሶ ሄደ::

ስለ ሂላሪ ምንም ሳያውቅና ሳይሰማ ዓመት ያህል አለፈ:: በመሀሉም የአሌክሳንድራ የጉዲፈቻ አባት የነበረው ሚስተር ጎርሐም በልብ ድካም በሽታ ሳይታሰብ ሞቶ ነበረ:: ወደ ዓመቱም መጨረሻ ላይ ዴቪድና ሬቢካ የተሻለ ስራ ስላላገኙ ከኒውዮርክ ለቀው ወደ ካሊፎርኒያ ሚጋንን ይዘዋት ሄዱ:: የጐርሐምን ባለቤት ማርጋሬትን ለመጨረሻ ጊዜ ያያት በባሏ የቀብር ሥነ ሥርዓት ላይ ነበረ:: የስራ ውጥረት ስለነበረበትም ሂላሪን ያስታወሳት የሚቀጥለው የገና በዓል በደረሰበት ወቅት ነው::

መኪናውን ወደ ኢሊን ቤት ከሚወስደው መንገድ መጠምዘዣ ላይ አቆሞ ሂላሪን ሳታስበው ደረሰባት:: ፊቷንም ሲያየው ደነገጠ:: መገርጣት ብቻ ሳይሆን ከፊቷ ላይ የሚነበበው ሌላ መልዕክት ነበረ::





የጥላቻና ተስፋ የመቁረጥ ሁኔታ ታየውና ስጋትም ገባው:: ምከር ህይወቱን ባጠፋበት ዕለት የነበረው ዓይነት አመለካከት ነበረ በሂላሪም ገፅታ ላይ የሚነበበው:: ሊያነጋግራት፣ ሊያፅናናት ብዙ ሞከረ:: ግን አንዳችም መልስ አልሰጠችውም:: በመጨረሻም ላይ ተሰናብቷቸው ሊወጣ አንድ የተስፋ ጭላንጭል ታየው:: ያ እንደዚያ ይቀፍ የነበረው ቤት የውስጥ ይዞታ ፍፁም ተቀይሯል:: የቤቱን ንፅህና፣ የዕቃዎቹ አቀማመጥ እንከን የማይወጣለት ነበረ:: የኢሊንም አለባበስ ለመጀመሪያ ጊዜ እንዳየው ሳይሆን፣ የፀዳ ነበረ:: ኢሊን ራሷን መጠበቅ ጀምራለች ማለት ነው ሲል አሰበ:: እንደዛ ሳይሆን በቤቱ ውስጥ ለተደረገው ለውጥ ምክንያቷ ሂላሪ ነበረች::

ልብስ የምታጥበው፣ ቤት የምትወለውለው፣ ምግብ የምታዘጋጀውና በግቢው ውስጥ የነበረውን አረም የምታርመው፣ የአበባውን ቦታ የምትኮተኩተው ሂላሪ ብትሆንም፣ በትምህርቷም አትሰንፍም ነበር:: የሚያነጋግራት አንድም ጓደኛ የላትም:: እንዲኖራትም አትፈልግም:: የኔ የምትለው ቤት ቢኖራት ኖሮ ግን ሂላሪ ብቸኛ ባልሆነች ነበረ:: መምህራን የሚሰጧትን የቤት ስራ እስከ አኩለ ሌሊት ድረስ ስትሰራ ታመሻለች:: የፈተና ውጤቷም ከፍተኛ ነበረ::

ኢሊን ማናቸውንም የቤት ኃላፊነት ለሂላሪ ለጥታለች:: ቢራ መጠጣቷንም እንደቀጠለች ቢሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሰውነቷ እየመነመነ መሄድ ጀምሯል:: በተለያዩ ሐኪሞችም ተመርምራለች:: ግን የተሰጣት መድሃኒት ሁሉ አንዳችም ፋይዳ አልሰራላትም:: ምናልባት አየር ብትቀይር የሚሻላት መስሏት ለባሏ ለጆንስ አጫውታዋለች:: እርሱም ወደ ሞቃቱ ወደ ፍሎሪዳ ግዛት ይዟት ለመሄድ ወሰነ:: ሂላሪ ተከትላቸው ከመሄድ በስተቀር ሌላ አማራጭ አልነበራትም:: ዕድሜዋ አስራ ስምንት እስከሚሞላት ድረስ፣ ቢበድሏት፣ ቢያንገላቷት፣ ጥርሷን ነክሳ መቆየት ነበረባት:: ከዚያ በኋላ ግን እህቶቿን መፈለግ ትጀምራለች:: እንደምታገኛቸውም እርግጠኛ ነበረች:: አክሲን አግኝታ እንደ ህፃንነቷ ወርቃማ ፀጉሯን ስታበጥርላት ይታያታል:: ሚጋንን እንደአራስነቷ ከአንገቷ ለጥፋ አቅፋት በህፃን ትንፋሿ ጉንጯን ስታሞቀው ይሰማታል:: እና አንድ ቀን... አንድ ቀን... እህቶቿን እንደምታገኛቸው እርግጠኛ ነበረች::

ኢሊን ህመሟ እየፀናባት በመሄዱ ምግብ ከለከላት:: እንደ ልቧም መንቀሳቀስ እያቃታት በመሄዱ ጆንስ በፍሎሪዳ ግዛት ውስጥ ጃክሰንቪል ወደምትባል ከተማ ወሰዳት:: የገናንም በዓል ያሳለፈችው በአልጋ ላይ ነበረ:: ኢሊን ወደ ሞት እየተቃረበች ለመሆኑ ግልፅ ቢሆንም ባሏ ጆንስ

እስከዚህም ጭንቀት አልገባውም:: የሚመጣው አምሽቶና በስካር ጢንቢራው ዞሮ ነው:: የሚተኛውም ለብቻው ስለነበረ ባሻው ሰዓት ገብቶ ባሻው ሰዓት ይወጣ ነበረ:: ኢሊን ሆስፒታል እንድትገባ ጐረቤቶቿ ቢጨቀጭቋትም አልፈለገችም:: ባሏንም ሲያማክሩት ለሆስፒታል የሚከፈል ገንዘብ የለንም ሲል መልሶላቸዋል:: ስለዚህ ኢሊንን የማስታመሙ ኃላፊነት በሂላሪ ላይ ተጣለ:: ሂላሪም ከኢሊን መኝታ ክፍል ከወለሉ ላይ እያነጠፈች ነበረ የምትተኛው:: ኢሊን እንደዚህ በአልጋ ቁራኛ ተይዛ እንኳን ለሂላሪ አታዝንላትም ነበረ:: ከትምህርት ቤት እንደተመለሰች አንድም ሳታርፍ ይህን ስሪ፣ ይህን እንዲህ አድርጊ እንዳለቻት ነበረ የምታመሸው:: ከእንቅልፏም ቀስቅሳ የሽንት ስሀን አምጭልኝ፣ ብርድልብስ ደርቢልኝ፣ ትራስ አንተራሺኝ ... የማትላት፣ የማታዛት ነገር አልነበረም::

ወደ ፍሎሪዳ በሄዱ በዓመት በመንፈቁ ኢሊን አረፈች:: በዚያን ጊዜ ሂላሪ አስራ ሁለት ዓመት ሆኗት ነበረ:: ኢሊን በሞተችበት ዕለት ልሳኗን ዘግቷት ነበር:: አይኗቿንም ከገጿ በማትሰየው ሂላሪ ዓይኖች ላይ እንደሰካቻቸው ነበረች:: ለመናገር የምትፈልገው ነገር እንዳለ ሂላሪ ገብቷታል:: ያም ሆኖ ሂላሪ ከኢሊን አንደበት በጐ ቃላት ይወጣሉ ብላ አልገመተችም:: ያው ስድብና እርግማን ብቻ ነው:: ኢሊን አንዲትም ቃል ሳትተነፍስ ሞተች::

ከዚያን ቀን ጀምሮ ሂላሪ በመጠኑም ቢሆን ሻል ያለ ኑሮ ለመኖር ቻለች:: መላ ትኩረቷም በትምህርቷ ላይ ሆነ:: በርግጥ ሌላ ችግር ነበረባት:: ጆንስ ማታ ማታ የሚመጣው እንደ ልማዱ ሰክሮ ነው:: ደግሞም ሴቶች እየቀያየረ መምጣት ጀምሮ ነበረ:: ኢሊን በሞተች በማግስቱም አንድ የሰጣት ማስጠንቀቂያ አለ:: በዚያ ቤት ለመቆየት እስከፈለገች፣ ጆንስ ወዳጆቹን ይዞ በሚመጣበት ወቅት ከመኝታ ቤቷ ውጪ ልውስ ማለት የለባትም:: በተጨማሪም ሌላ የሰጣት ትዕዛዝ ነበረ:: ከኢሊን ልብሶች ውስጥ ለራሷ የሚሆነውን መርጣ አስቀርታ የተቀ ረውን በመሰላት ዘዴ እንድታስወግድ ነግሯታል:: የኢሊን ቀሚሶችና ሱሪዎች ለሂላሪ አይሆኗትም:: ከሹራቦቿ ውስጥ ግን አንዳንዶቹን ለራሷ አስቀርታ የተቀረውን በሙሉ ቤተክርስቲያን ወስዳ ለችግረኞች እንዲታደል ሰጠች:: ቀጥላም የኢሊን ሙታንታዎች አማረጠች:: እያጠበች ልትለብሳቸው እንደምትችልም ገመተች:: የኢሊን እግሮች ቀጭን ስለነበሩ ስቶኪንጎቿን ሂላሪ እንዳሉ ልታደርጋቸው ትችል ነበረ:: ስለዚህም ሁሉንም ሰብስባ ወደ መኝታ ክፍሏ ወሰደች:: በመልክ በመልኩም በምታስቀምጥበት ሰዓት አንደኛው የተጣጠፈ ስቶኪንግ እጇ ላይ ከበደባት ዘቀዘቀችና ስታራግፈውም





ከፊቷ አንድ ጥቅል ዱብ አለ:: ያየችውን ማመን ተስኗት ለብዙ ጊዜ ፈዛ ቆየች:: ነፍሷ መለስ ሲልላትም ያንን ጥቅል አነሳችው:: ወደ ዓይኖቿም አስጠጋችው:: የባለ መቶ ብር ኖቶች ጥቅል ነበር:: ለጥቂት ጊዜ ስታስብ ቆየች:: ጆንስ ስለዚያ ገንዘብ መኖር አለማወቁን እርግጠኛ ሆነች:: ኢሊንን ሐኪም ቤት ለማስገባት ገንዘብ የለንም ሲል የተናገረውን አስታወሰች፣ ያኔም የልብልብ ተሰማትና ኖቶቹን መቁጠር ጀመረች:: አንድ መቶ ባለ መቶ ብር ኖቶች የያዘ ነበረ:: በአእምሮዋም የገንዘቡን መጠን አሰላች:: አስር ሺህ ብር! በዚያው በስቶኪንግ መልሳ ጠቀለለችና ከልብሶቿ መካከል ሽጐጠችው:: ሌሊቱንም ስለ ሚጋንና አሌክሳንድራ ስታስብ አደረች::

የሚቀጥለውን አንድ ዓመት ሂላሪ በሰላም አሳለፈች:: በትምህርቷም የሚስተካከላት አልነበረም:: በርሷ እድሜ አካባቢ ያሉትን ተማሪዎች በአንድ የክፍል ደረጃ በመቅደም በአስራ ሶስት ዓመት ዕድሜዋ አስረኛ ክፍል ደርሳለች:: የጆንስም ዓመል መቀያየር የጀመረው ያኔ ነው፤ ለወትሮ ጆንስ ከጐኑ ሴት እስካለች ከፊቱ ቢራ እስከተደረደረ ሂላሪን አያስታውሳትም ነበረ:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በሰበብ ባስባቡ ሊጨቀጭቃት ጀምሯል:: ምግብ የማዘጋጀት ችሎታ የለሽም ይላታል:: ግን ከቤት ተመግቦ አያውቅም ነበረ:: የሂላሪ ቀሚሶች ረጃጅም በመሆናቸውም ለምን እንደወቅቱ ፋሽን አጭር ቀሚስ አትሰብሽም ሲልም ይነዘንዛታል::

አንድ ቀን አፍ አውጥቶ "ጎረምሶች እንዲያሽኮረምሙሽ አትፈልጊም ማለት ነው?" ሲል ጠይቋት ነበረ::

እርሷም "አልፈልግም! ጎረምሳ የሚባል ነገር ያስጠላኛል" ስትል መለሰችለት::

"ለምን ሂሊ! ለምን?" ሲል ስሟን አቆላምጦ ጠየቃት::

"ሳያቸው ደስ ስለማይሉኝ ነው" አለችው ዓይኖቿን ሰበር አድርጋ::

"እንደኔስ ዓይነቱ ሰው! ለምሳሌ እኔ ደስ አልልሽም ማለት ነው?" አላት ቢራውን ወደ አፉ እያስጠጋ:: ጆንስ በዚያን ጊዜ ዕድሜው አርባ አምስት ዓመት ነበረ::

ሂላሪ የመሰላትን መልስ መስጠት እንደማትችል ታውቀዋለች:: ስለዚህ ዝም እንዳለች ወደ ምግብ ማዘጋጃው ክፍል ገባች:: በስሱ የቆረጠችውን ሥጋ በመጥበስ ላይ እንዳለች ጆንስ ሌላ ቢራ ክፍቶ በእጁ

እንደያዘ ወደ ምግብ ማዘጋጃው ክፍል መጥቶ ከበሩ ላይ ቆመና ለጥቂት ጊዜ ዝም ብሎ ሲያያት ቆየ:: ሂላሪም አስተያየቱ አላማራትም ነበረ::

"ለእራት ምንድነው ያለሽ?" አላት ዓይኖቹን ከላይዋ ላይ ሳይነቅል::

"የስጋ ጥብስ" አለችው ሂላሪ::

"በጣም ጥሩ" አለና ወደ እግሮቿ አየት አደረገ:: የባቶቿ ቅርፅ የተዋጣለት ነበረ:: ከፍ አለናም እንዝርት የመሰለውን ሽንጧንና ፍርጥም ያሉትን ጡቶቿን ተመለከተ:: ከዚያም ጉን ጉኑ ከወገቧ የደረሰውን ጥቁር ፀጉሯን አየ:: የመልኳንም ቅርፅ ረጋ ብሎ አጠና:: እንከን የማይወጣላት ውብ ልጅ ነበረች:: የሐዘንና የጭንቀት ጊዜ በማሳለፏ ግን ዕድሜዋ የገፋ ይመስል ነበረ::

ጆንስ ወደ ውስጥ ገብቶ ከቂጧ ላይ መታ አድርጐ ከኋላዋ ታኳት አለፈና ምግቡን አዘጋጅታ እስክትጨርስ አጠገቧ ቆመ:: ሂላሪ ያን ጊዜ ፈራች:: እጆቿ ይንቀጠቀጡ፣ ልቧም ትር ትር ይል ጀመረ:: ሳታስበውም ጆንስ አሁንም በጀርባዋ ታኳት ወደ ሳሎን ተመለሰ:: ብዙም ሳይቆይ የውጪው በር ተከፍቶ ሲዘጋ ተሰማት:: ያም ለሂላሪ ታላቅ እፎይታ ነበረ:: ሂላሪ የተዘጋጀውን ምግብ ቅምስ ሳታደርገው በሳህን ላይ እንዳለ ከማቀዝቀዣው ውስጥ አኑራ መኝታ ክፍሏ ሄደች:: ከገባችም በኋላ መብራቱን አጥፍታ ተኛች:: ከባድ ዝናብ በመጣል ላይ ስለነበረ ወዲያውኑ እንቅልፍ ወሰዳት::

ጆንስ እኩለ ሌሊት ላይ በስካር እየተንገዳገደ ተመለሰ:: ሲያደርገው ያሰበው ነገር እንዳለ ቢታወሰውም ምን እንደነበረ ዘንግቶታል:: ወደ መኝታ ክፍሉ ሊገባ ሲል ግን አንድ ነገር ታየው:: የምግብ ማዘጋጃው ክፍል በር አልተዘጋም ነበረ:: ከጥቂት ሰዓታት በፊት በዚያች ክፍል ውስጥ ከሂላሪ ጋር ጉን ለጉን ቆሞ እንደነበረ አሁን ታወሰው:: ቀጥታም ወደርሷ መኝታ ቤት ሄዶ የበሩን እጀታ አዞረና ከፈተው:: ወደ ውስጥም ገባ:: ሂላሪ በውስጥ ልብሷ ጋደም እንዳለች ነበረ እንቅልፍ የወሰዳት:: የበሩንም መከፈት አልሰማችም::

የሲጋራው ጢስ ሳንባውን አፍኖት ኖሮ ጆንስ አንድ ጊዜ የሳል ድምፅ አሰማ:: ሂላሪ በእንቅልፍ ልቧ ገልበጥ አለችና በጐኗ ተኛች:: ውስጥ ልብሷ ወደ ላይ በመሰብሰቡ የአንደኛው እግሯ ጭን ይታያል:: የዳሌዋም ቅርፅ የሚያስጐመጅ ነበረ:: ጆንስ የሱሪውን ቁልፎች ቀስ ብሎ





ፈታና ከወለሉ ላይ ሲወድቅ በጫማው ተራ በተራ እየረገጠ አሾልኮ አወጣው:: በዝናብ የበሰበሱትን ኮትና ሸሚዙን ድምፅ ሳያሰማ አውልቆ ከወለሉ ላይ አኖረ:: በሙታንቲ ብቻ እንደቆመ የሂላሪን ቅርፅ እንደገና ያጠና ጀመረ:: የደሙ ግለት እየጨመረ ሄደ፣ ሰውነቱም ነዘረ:: ሂላሪን መመኘት ከጀመረ ዓመታት ቢያልፉም በዛሬው ቀን ግን የርሱ ልትሆን ነው:: ምናልባትም ከእንግዲህ ጆንስ ከሂላሪ በስተቀር ሌላ ሴት ላይፈልግ ይችላል:: መግቢያም ስለሌላት ጥላው አትሔድም:: እንደፈለገው የምትታዘዝለት ልጅ ትሆናለች::

ከጐኗ ጋደም አለና በረጅሙ ተነፈሰ:: በሲጋራና በመጠጥ የተበከለው ትንፋሹ ሂላሪን አጠናት:: አንድ ዓይኗን ገለጥ አደረገችና ስታይ አጠገቧ የተኛ ሰው አለ:: ከአልጋውም ላይ ተፈናጥራ ተነሳች:: ጆንስ ፈጣን ነበረና የውስጥ ልብሷን ጨምድዶ ያዘው:: ለማስለቀቅ ስትታገልም እንዳለ ተቀደደና እርቃኗን ቀረች:: ምን እንደምታደርግ ግራ ገባት:: ሮጣ እንዳትወጣ ጨነቃት:: እጆቿን በጭንና በጭኗ መካከል ሸፍና ቆመች::

"ለምን ትሸፍኚዋለሽ ሂሊ? መታየት ያለበት ነገር ነው:: እምን! ከአሁን በፊት ልምድ ስለሌለሽ ልታፍሪ ትችያለሽ:: ስለዚህ ከአንሶላው ውስጥ ግቢና ተኚ" አላት:: ሂላሪ ከቆመችበት ባለመነቃነቋ ጆንስ ሊይዛት እጁን ሰደድ ሲያደርግ አመለጠችና ወጣች:: እየሮጠችም ወደ ምግብ ማዘጋጃው ክፍል ገባች:: ጆንስም ከአልጋው ላይ ተነስቶ እየተግተረተረ ተከተላት:: የጓሮውን በር ከፍታ እወጣለሁ ስትልም ዘለለና ያዛት:: ሂላሪም እንደነብር በጥፍሮቿ ፊቱን፣ እጁን፣ ሆዱን ቧጨረችው:: ሆኖም ከጆንስ ጠንካራ ክንዶች ለማምለጥ አልቻለችም:: እየጐተተም ወደ መኝታ ክፍሉ ሊወስዳት ሲል ዓይኗ አንድ ብልጭ በሚል ነገር ላይ አረፈ:: ከመቅፀበትም አነሳችውና ከጐኗ ልጥፍ አድርጋ ያዘችው:: ከዚያ በኋላ ግን ጆንስን ብዙም ሳትታገለው ወደ መኝታ ክፍሏ ሄደችለት:: በሰላም የማይተዋት ከሆነ ልትገድለው ቆርጣ ነበረ::

"እንደ አሁኑ ጥሩ ልጅ መሆን አለብሽ:: ሂሊ ለምንጊዜም አብረን እንኖራለን:: ገባሽ አይደል!" አለና ከአልጋው አጋድሟት ከበላይዋ ሊተኛ ሲል አንድ ሹልና ስል ብረት ሆዱን ጠቅ ሲያደርገው ተሰማውና ለማየት ጐንበስ አለ:: ሂላሪ ለራት ያዘጋጀችውን ሥጋ የቆረጠችበት ቢላዋ ነበረ::

"ከእንግዲህ ጫፌን ብትነካኝ ሆድህን እንደምዘረግፈው እንድታውቀው" አለች:: የምትናገረው የምሯን ለመሆኑ ጆንስም ቢሆን

ተረድቶታል:: ወደ ኋላው ጥቂት አፈገፈገና ቆሞ ያያት ጀመረ:: ሂላሪ "ክዚህ ክፍል ውስጥ በሰላም ብትወጣ ይሻልሀል" አለችው ቢላዋውን በሆዱ አቅጣጫ እንደያዘች እየተጠጋችው::

"እሺ ... እሺ ..." እያለ እየተቻኮለ የኋሊት ሲያፈገፍግ ክወለሉ ላይ አስቀምጦት የነበረው ልብስ አደናቀፈውና በጀርባው ተዘረጋ:: እግሮቹም ወደ ሰማይ ሲነጥሩ የሂላሪን እጅ መቶተውት ኖሮ ቢላዋው ከእጇ ላይ ተስፈንጥሮ ክአልጋው ሥር ወደቀ:: ሂላሪም ቢለዋውን ለመፈለግ ባጐነበሰችበት ወቅት ጆንስ ዘሎ ተነሳና አላይዋ ላይ ተከመረባት:: ባለ በሌለም ጉልበቱ ፀጉሯን ጨምድዶ ጭንቅላቷን ከግድግዳው ጋር እያላተመ ደም በደም እስክትሆን ደበደባት:: ሰውነቷ መዛሉን እንዳየም አወሰሉ ላይ ጥሏት ወጣ:: የዚያን ቀኑ ቅጣት ብቻውን ለሂላሪ ትምህርት እንደሚሆናትና ለወደፊቱም ፍፁም ታዛዥ እንደሚያደርጋት ተሰምቶት ወደ መኝታ ክፍሉ ገባ:: መድረሻ ቢሷ ሂላሪ ከእንግዲህ የርሱ ናት፤ በዚህ ፍፁም በመደሰቱና በመዝናናቱ ገና ጋደም ከማለቱ ኸው ያለ እንቅልፍ ወሰደው::

ሂላሪ ከወደቀችበት እየተንገዳገደች ተነሳች:: ጆንስ ተመልሶ ይመጣል የሚል ፍርሃት ስለገባትም ዋናውን በር ክፍታ እርቃነ ስጋዋን ወጣች:: መርገጥ ያቃታቸውን እግሮቿን እየጐተተች ከቅርብ ካገኘችው ቤት በር ደረሰች:: ያን ጊዜም አዞራትና ወደቀች:: ነፍሷን እንደሳተችም ለብዙ ጊዜ ቆየች:: በላይዋ ላይ ዝናብ ይወርዳል:: ካፍንጫዋና ከራሷም ደም ይፈሳል:: በዚህም ሁኔታ ላይ እንዳለች መጀመሪያ ያየቻት በጠዋት ተነስታ የነበረችው የቤቱ እመቤት ሚስስ አርቸር ነበረች::

ሚስስ አርቸር የከፈተችውን በር መልሳ ዘጋችና "የእግዜር ያለህ! የእግዜር ያለህ!" እያለች ባሏ ተኝቶ ወደነበረበት ክፍል እየጮኸች ሮጠች:: "ተነስ! ተነስ! ከበራፋችን ላይ የሞተች ሴት አለች:: እርቃነ ስጋዋን ናት" ስትልም ነገረችው:: ባሏም በሌሊት ልብሱ ተክትሏት ወጣ:: ወደ ሂላሪም ጎንበስ ብሎ ተመለከተ:: ከጭንቅላቷ ላይ ከነበረው ቁስል አሁንም ደም እንደፈሰሰ ነበረ::

"ኢየሱሱ ክርስቶስ!" አለ ሚስተር አርቸር እራሱን በሁለት እጆቹ እንደያዘ "ይቺ እኮ በቅርቡ አክስቷ የሞተችባት፤ የጎረቤቶቻችን ልጅ ናት" ብሎ ወደነጆንስ ቤት ዞር አለና ተመለከተ:: ሚስስ አርቸር ግን በዚያን ጊዜ ስልክ በመደወል ላይ ነበረች:: ብዙም ሳይቆይ የፖሊስና የአምቡላንስ መኪናዎች መጡ:: የሚስስ አርቸር ግምት ሂላሪ ድብደባ ብቻ ሳይሆን እርቃኗን ወድቃ በመገኘቷ ብልግናም ተፈፅሞባታል የሚል ነው:: ሆኖም





ሐኪሞች ባደረጉት ምርመራ ሂላሪ ክሶስትና አራት ቦታዎች ብትቆስልም ክብረ ንፅህናዋ ግን አልተደፈረም ነበረ:: እንደፈሰሳትም ደም ብዛት ሁኔታዋ ለስጋት እንደማይሰጥም ሐኪሞች አረጋግጠዋል:: ሚስተር አርቸርና ባለቤቱ ወደ ቤታቸው የተመለሱት የሂላሪ ቁስሎች ተሰፍተው ሌላ ሌላም አስፈላጊ ሕክምና ተደርጐላት እንቅልፍ ካሸለባት በኋላ ነበረ::

"ማን ይሆን በልጅቱ ላይ እንደዚያ ያለ ጭካኔ የፈፀመው?" ስትል ሚስስ አርቸር ባሏን በመንገድ ላይ እንዳለ ጠየቀችው:: ለጊዜው አንድም ሰው የሚጠረጠር አልነበረም:: ሂላሪም ብትሆን ለመናገር ፈቃደኛ አልነበረችም:: ብትናገር እንደሚገድላት ታውቀው ነበረ:: በፖሊሶችም በኩል ለጆንስ ተደጋጋሚ ጥያቄዎች ቀርበውለት ሁለት ቀናት ሙሉ ከካደ በኋላ በሶስተኛው ቀን ጥፋቱን አመነ:: ከዚያም መርማሪው ፖሊስ ሂላሪን አነጋገራት::

"ተመልሼ የምገባበት የለኝም:: እንደሚገድለኝም አውቀዋለሁ" ስትል እያለቀሰች ተናገረች::

"ወደዚያ ቤት ተመለሺ ብሎ የሚያስገድድሽ ሰው አይኖርም:: ለጊዜው ከመጠለያ ቤት እንድትቆይ ለማድረግ ይቻላል" አላት ፖሊሱ::

"መጠለያ ቤት!" አለች ሂላሪ በፍርሐት ዓይኖቿ ፍጥጥ እንዳለ::

"አዎን! የሚሰበስባቸው ወላጅ የሌላቸው ልጆች ሊቆዩባቸው የሚችሉባቸው ሥፍራዎች ናቸው"

"ድርጅት ነው ማለት ነው!"

"ድርጅት እንኳን አይደለም:: አንዳንድ ቤተሰቦች እንቺን የመሳሰሉትን ልጆች ለማሳደግ በፍርድ ቤት ውክልና ይሰጣቸዋል:: ከዚያም እስከ አምስትና ስድስት እየሆናችሁ በአንድ ቤት ውስጥ ልትኖሩ ትችላላችሁ:: ይህን ካልፈለግሽ ደግሞ ዕድሜአቸው ለአቅመ ሔዋን ያልደረሰ የልጃገረድ አጥፊዎች ከሚጠበቁበት የጠባይ ማረሚያ ተቋም ውስጥ ልናስገባሽ እንችላለን::"

"እንደዚያስ ከሆነ ምርጫዬ የመጀመሪያው ነው" አለች ሂላሪ እንደርሷ ያሉ አምስትና ስድስት ልጃገረዶች ባሉበት ቤት ውስጥ ወንድ ሊደፍራት እንደማይችል ተሰምቷታል:: ዕድሜዋም አስራ ስምንት እስከሚሞላ ድረስ ጨክና የሚቀሯትን ዓመታት ማሳለፍ ነበረባት:: ከሁለት

ቀናት በኋላ ለሂላሪ መጠለያ ለመስጠት ፈቃደኛ የሆነ ቤተሰብ ተገኘላት:: ሂላሪም ልቧ የተለቀለው ለደበቀችው አስር ሽህ ብር ስለነበረ ልብሶቿን ለመውሰድ ወደ ቀድሞው ቤቷ መመለስ ነበረባት:: ጆንስን በመፍራቷ ግን ሚስስ አርቸርን ለምናት አብረው ሔዱ:: የምትፈልጋቸውንም ልብሶቿን በአንድ ሻንጣ ውስጥ አድርጋ ወጣች:: እንዳለ ያለው ጆንስ በዚያች በሻንጣ ውስጥ አስር ሺህ ብር መያዟን ቢያውቅ ኖሮ አንቆ በገደላትም ነበረ::

ሂላሪን ከአዲሱ ቤቷ ያደረሰቻት የከተማው አስተዳደር የማኅበራዊ አገልግሎት ዘርፍ ሰራተኛ ነበረች:: ቤቱ ከጃክሰንቪል ከተማ ዳር ላይ የተ ሰራ ቤት ነበረ:: ከመኪናም እንደወረዱ ሂላሪ አንድ ነገር ትዝ አላትና መልኳ ልውጥውጥ አለ:: ከፊት ለፊቷ የምታየው ቤትና የቦስተኑ የነኢሊን ቤት ተመሳሳይ ነበረ:: ግድግዳው የተቀራረፈ፣ ጣሪያው ያረጀ፣ የመስኮቶቹ ፀሐይ መከላከያዎች የተለባበሩ ቤት ነበረ:: ወደዚያ ቤት መግባት ቢቀፋትም ተመልሳ የምትሔድበት አማራጭ ስለሌላት የማኅበራዊ ጉዳይ ሠራተኛ ዋን ተከተለች:: በሩም እንደተንኳኳ አንዲት መካከለኛ ሴት ከፈተችላቸው:: ሞቅ ባለ ፈገግታ ተቀበለቻቸው:: የቤቱም የውስጥ ቁሳቁሶች ያረጁ መሆና ቸውን ሂላሪ አየች:: ከዚያ ሌላ ግን ስድስት ያህል ወንድ ልጆች ጎን ለጎን ተቀምጠው በመመገብ ላይ ነበሩ::

የሴትየዋ ስም ሉዊዝ ይባል ነበረ:: እርሷም ሂላሪን መኝታ ክፍሏን ልታሳይ ወሰደቻት:: በክፍሉም ውስጥ ሦስት ልጃገረዶች በመንገደኛ አልጋዎቻቸው ላይ ተቀምጠው በሣህን በሣህን የተሰጣቸውን ምግብ እየበሉ ነበረ:: ሉዊዝ እንደገባችም ከመቀመጫቸው ብድግ ብለው በአክብሮት ተቀበሏት:: እርሷም ሂላሪን አስተዋውቃት ተመለሰች:: ለሂላሪም ምሳ መጥቶላት እንደነገሩ በመመገብ ላይ እንዳለች ነበረ ልጃገረዶቹ ሂላሪን ሊያነጋግሯት የጀመሩት::

በቅድሚያም ማይዳ የተባለችው ጥቁር ልጃገረድ «ሂላሪ የሚባል ስም ገና ዛሬ መስማቴ ነው:: ትርጉሙ ምን ማለት ይሆን?» ስትል ጠየቀቻት:: ማይዳ ረጅምና ቀጭን ልጃገረድ ነበረች:: በዚያም ቤት ውስጥ መኖር ከጀመረች ዘጠኝ ወራት አልፏታል::

"ትክክለኛ ትርጉምን ባላውቀውም ሂላሪየስ ከሚለው ቃል የወጣ ይመስለኛል" ስትል ሂላሪ መለሰች::

"ሂላሪየስ? ሂላሪየስ ለሚደነቅ፣ ለሚያስደስት፣ ለሚያስቅ ነገር የሚሰጥ ስም ነው:: እና እዚህ ቤት ውስጥ ለመኖር የዳረጉሽ ወላጆችሽ





ይህንን የመሰለ ስም ስላወጡልሽ በጣም ተሳስተዋል" አለቻት ማይዳ:: የማይዳ አገላለጽ ትክክል ነበረ:: ሂላሪም ሌላ መልስ አልነበራትም::

"ከየትኛው ግዛት ነው የመጣሽው?" ስትል ሌላዋ ልጃገረድ ጠየቀቻት::

"ከኒውዮርክ ... በስቶን... በፍሎሪዳም ውስጥ ሁለት ዓመት ኖሬያለሁ::"

"ግን ወደዚህ መጠለያ ለምን ለመምጣት በቃሽ? አባትና እናትሽ እስር ቤት ገብተውብሽ ነው?" አለችና ማይዳ የአውራ ጣቷን ጥፍር በጥርሷ ትነክስ ጀመረ:: የእርሷ ወላጆች ታስረውባት ነበረ:: እናቷ በሴተኛ አዳሪነትና በስርቆት፣ አባቷ ደግሞ በድብደባ ወንጀል::

"ወላጆቼ በመሞታቸው ነው" አለች ሂላሪ

"ወንድሞችና እህቶችስ አሉሽ?"

ሂላሪ እህቶች አሉኝ ለማለት ቃትቷት ነበረ:: ግን አለኝ ብትል ባትል በዚያን ወቅት ምንስ ትርጉም ሊኖረው? ስለዚህ ዝም እንዳለች እራሷን አወዛወዘች:: ማይዳ ለሂላሪ ሳታዝንላት አልቀረችም:: ስለዚህም ነው "አይዞሽ! ሁሉንም ነገር እየለመድሽው ትሄጃለሽ:: ሉዊዝ ግን አረመኔ እንዷ ሰው እንዳትመስልሽ" አለቻት:: ሂላሪ ገና ከመኪና እንደወረደች ችግር ሊገጥማት እንደሚችል ታውቋታል:: ግን ምን ታድርግ? ወዴትስ ትግባ?

"ለመሆኑ ምን ምን ስራ ነው የምታሰራችሁ?" ስትል ሂላሪ ጠየቀቻት::

"ማረፍ የሚባል ነገር የለም:: የተገኘውን ስራ ነው የምታሰራን:: ልብስና ቤት ማጠብ፣ ህፃናት ልጆቿን መጠበቅ፣ የአትክልት መደብ መቆፈር፣ አረም ማረም... ሁሉንም እንደባሪያ ነው የምታሰራን:: ዋናው ነገር የምንተኛበት አልጋና ምግብ ትሰጠናለች::"

"እንግዲያውስ ከዚህ የጠባይ ማረሚያ ተቋም ይሻል ነበራ?" አለች ሂላሪ እንደመፀፀት ብላ::

"ጠባይ ማረሚያ? እርሱስ ባፍንጫዬ ይውጣ! መለስተኛ እስር ቤት ማለት አይደለም እንዴ? እንደልብሽ መግባት መውጣት አትችይም:: ህጋዊ ኃላፊነት ወስዶ የሚያስጠጋሽ ዘመድ ካላገኘሽ ወይንም ዕድሜሽ አስራ ስምንት ሞልቶ ለአቅመ ሄዋን ካልደረስሽ ከግቢው ውጪ ንቅንቅ ማለት አትችይም:: ስለዚህ ለሉዊዝ ባሪያ መሆኑን እመርጣለሁ:: ደግሞም እናቴ በሚቀጥለው ወር ስለምትፈልገኝ ወደ ቤታችን ትወስደኛለች::" አለች ማይዳ:: ሂላሪ በዚህን ሰዓት ሌላ ትዝታ መጣባት:: ከዚያ ቤት የሚኖሩት ልጆች ሁሉ እንደማይዳ ከወላጆቻቸው ጋር የመገናኘት ዕድል ሊኖራቸው ይችላል:: የርሷ አባት ግን እናቷን ገድሎ የራሱንም ህይወት አጥፍቷል:: 'ምነው ለእንደዚህ ዓይነት ህይወት ከሚዳርገኝ በዚያን ምሽት ከእናቴ ጋር በገደለኝ ኖሮ' ስትል ተመኘች:: ማይዳ በሂላሪ ሁኔታ ሳትገረም አልቀረችም:: ሂላሪ በአቋቋሟ፣ በመልኳ፣ በአነጋገሯ ሁሉ በዚያን ዓይነት መጠለያ ቤት ውስጥ ከሚኖሩት ልጃገረዶች ለየት ያለች ነበረች:: ስለዚህ ማይዳ "አንቺስ በዚህ ቤት ውስጥ እስከመቼ የምትቆይ ይመስልሻል? የቅርብ ዘመዶችስ የሉሽም?" ስትል ጠየቀቻት:: ሂላሪ የለኝም ስትል ራሷን በማወዛወዝ ላይ እንዳለች የማህበራዊ ጉዳይ ሰራተኛዋ ገባች::

"ከአሁኑ ሞቅ ያለ ወሬ ይዛችኋልና" አለችና ፈገግ አለች::

"አዎ! ከሂላሪ ጋር እየተጫወትን ነበረ" አለቻት ማይዳ::

"ጉሽ ማይዳ በደንብ አለማምጃት" አለቻትና ተመልሳ ወጣች:: ወዲያውኑም የደወል ድምፅ ተሰማ:: ልጆቹ ስራ የሚጀምሩበት ሰዓት ደርሶ ነበር::

ለዚያን ዕለት ለሂላሪ ተሰጥቷት የነበረው የቤት ውስጥ ስራ ነበረ:: ለልጆቹ የሚሆን እራት የምታዘጋጀውን ሉዊዝን ስታግዛት አመሸች:: ራት ከተበላም በኋላ ዕቃዎቹን አጣጥባ ጨረሰችና ወደ መኝታ ክፍሏ ሄደች:: የተቀሩት ልጃገረዶች በስራ ተዳክመው ነበርና ጋደም ጋደም ብለው ነበረ:: ሂላሪም ከአልጋዋ ላይ ወጣችና በጀርባዋ ተንጋላ አዲሱ ኑሮዋንና ከጆንስ ጋር ያሳለፈችውን ጊዜ ማገናዘብ ጀመረች:: የአሁኑን እጥፍ በእጥፍ የሚሻል ሆኖ አገኘችው::

ከምሽቱ አንድ ሰዓት ተኩል ላይ ሉዊዝ ወደ መኝታ ቤታቸው መጥታ መብራቱን ካጠፋች በኋላ በሩን ከወጪ ቆልፋ ሄደች:: የመኝታ ቤት በር ሲቆለፍ የማትወደው ሂላሪ ድምጿን ዝቅ በማድረግ "ማይዳ! ማይዳ" ስትል ተጣራች::





"አቤት!" አለቻት ማይዳ::

"ለምንድነው በራፉን ከውጪ የምትቆልፈው?" አለቻት ሂላሪ::

"ከወንዶቹ ልጆች ጋር የምንገናኝ እየመሰላት ነው ትቀናለች መሰለኝ" ብላ ሌላዋ ከሂላሪ አጠገብ ተኝታ የነበረችው ልጃገረድ መለሰችላትና ሁለቱም ተሳሳቁ::

"ወደ መፀዳጃ ቤት መሄድ ቢያስፈልገንስ?" አለች ሂላሪ አሁንም::

"ለሽንት ከሆነ ቀላል ነው አልጋሽ ላይ መልቀቅ ነው" ስትል ሦስተኛዋ ልጃገረድ ቀለደችባት::

"በማግስቱ ግን አንሶላሽን እራስሽ ነሽ የምታጥቢያት" አለችና የመጀመሪያዋ ልጃገረድ አከለችበት፣ አሁንም ተሳሳቁ::

"የእሳት ቃጠሎ ቢነሳስ ማይዳ?!" አለችና ሂላሪ ሌላ ጥያቄ አነሳች::

"መጠበስ ነዋ ሂላሪ! እንደ ድንች መለብለብ! አይዞሽ ግፋ ቢል ነጭ ቆዳሽ እንደኔ ጣዝማ ቢመስል ነው" አለችና ማይዳ አሳቀቻት::

የመጠለያው ሁኔታ እንደዛን ዕለቱ የሚዘልቅበት ከሆነ ሂላሪ የሚቀጥሉትን አምስት ዓመታት በቀላሉ ልታሳልፍቸው እንደምትችል እርግጠኛ ሆነች:: ከዛ በኋላ ግን ከሻንጣዋ ውስጥ የደበቀችውን ብር አውጥታ እህቶቿን መፈለግ ነበረባት::

ማይዳ በዚያ መጠለያ ውስጥ እስካለች ድረስ ሂላሪ ፍፁም ደስተኛ ነበረች:: ቀደም ሲል ማይዳ እንደነገረቻት ከጠዋት እስከማታ እንደለሩ ቢውሉም ቢያንስ የሚበሉት ምግብና መጠለያ ነበራቸው:: ሉዊዝም ብትሆን ለልጃገረዶቹ የምታደርግላቸው ጥንቃቄ እንደቀጠለ ነበር:: ወንዶቹ እንዳያስቸግሯቸው ማታ ማታ በሩን ከውጪ መቆለፏን አትረሳውም:: በምግብም ጊዜ እንኳን ለየብቻ ነበረ የሚመገቡት::

ማይዳ ከመጠለያው በሄደች በአስራ አምስተኛው ቀን ሌላዋንም ልጃገረድ ወላጆቿ መጥተው ወሰዷት:: የርሷም እናትና አባት ዕፅ በመሸጥ ወንጀል ተይዘው የታሰሩባት ነበሩ:: የተቀሩትም ሁለት ልጃገረዶች ሲሆኑ በዚያ መጠለያ ብዙ አልቆዩም:: በሰባተኛው ወር ላይ ሂላሪ ብቻ ቀረች:: በዚያን ጊዜ ከወንዶቹም ልጆች ሶስቱ በወላጆቻቸው ተወስደው ነበረ::

ሂላሪ ብቻዋን ማደር ከጀመረችበት ቀን አንስቶ ሉዊዝ እንደ በፊቱ የመኝታ ቤቱን ከውጪ መቆለፏን ትታዋለች:: ምናልባትም ወንዶች ልጆች ሦስት እስከሆኑ ድረስ ሊተፋፈሩ ስለሚችሉ አንዷን ልጃገረድ ምንም ሊያደርጓት አይችሉም የሚል ግምት ኖሯት ሊሆን ይችላል:: ልጆቹ ግን በልባቸው ሂላሪን ቢከጅሏትም ከስታራዋን ሉዊዝን ያለመጠን ይፈሯት ነበረ:: በነማይዳም ምትክ ወደ መጠለያው ይመጣሉ የተባሉት ልጃገረዶች ባለመድረሳቸው ሂላሪ ቅራ በዝቶባት ሰነበተች:: ሉዊዝም የማህበራዊ ጉዳይ ሰራተኛዋን ከአንድም ሁለት ጊዜ ወደ ቢሮዋ ሂዳ አነጋግራታለች:: እነኛም ወንዶች ሂላሪን ሊደፍሯት የበቁት በዚያን አጋጣሚ ነበረ::

ሉዊዝ በምሳ ሰዓቱም ባለመመለሷ ለልጆቹ ምግብ ያቀረበች ላቸው ሂላሪ ነበረች:: እንደተለመደው እርሷ ምሳዋን በስህን አድርጋ ወደ መኝታ ክፍሏ አመራች:: እነኛም ወንዶች በዚያን ጊዜ ተጠቃቀሱና በዓይናቸው ይከተሏት ጀመረ:: መግባቷንም እንዳዩ ከመኻላቸው ትልቁ የነበረው ጆርጅ ተነሳና ወደ ሂላሪ ክፍል ሄዶ ከበራፍ ላይ ቆመ:: እራስ ምታት እንዳመመውም አስመስሎ ሂላሪን ስፕሪን ካላት እንድትሰጠው ጠየቃት:: እርሷም በእጇ የያዘችውን ሰህን አስቀመጠችና ሻንጣዋን ከአልጋው ስር ለመሳብ ጐንበስ አለች:: ያን ጊዜም ጆርጅ ኮቴ ሳያሰማ ገብቶ ከኋላዋ ጥርቅም አድርጐ ያዛት:: የተቀሩትም ሁለት ወንዶች ልጆች ወዲያው ደረሱና ተጋግዘው ሂላሪን ከአልጋው ላይ ጣሏት:: ከደረቷም ቀና እንዳትል አንደኛው ልጅ ከአልጋው ጋር አጣበቃት:: ሌላው ልጅ ደግሞ የሚንፈራገጡ እግሮቿን ጥርቅም አደርጐ ያዛቸው:: ጆርጅ በራፉን ከውስጥ ዘጋና የሱሪውን መዝጊያ እየተቻኮለ ከፈተ:: ከዚያም የሂላሪን ቀሚስና ውስጥ ልብስ ወደ ላይ ብሎ ሙታንታዋን ተረተረው:: ከጭንና ጭኖቿ መሀል ገባ:: ሂላሪ ምንም ያህል እራሷን ለማስለቀቅ ትፍጨርጨር እንጂ ከአንግዲህ ክብረ ንፅህናዋን ላለማስደፈር የነበራት ዕድል የመነመነ ነበረ:: ጆርጅ ዕድሜው አስራ ስድስት ዓመት ቢሆንም አካላቱ ከአዋቂ የሚያንስ አልነበረም:: እግርና እግሮቿም ተወጥረው ስለተያዙለት ሂላሪን በቀላሉ ደፈራት:: ደም በደም ቢያደርግም ስሜቱ እስኪረካለት አልለቀቃትም ነበረ:: ጆርጅ ከላይዋ ተነሳና እግሮቿን ይዞ ለነበረው ልጅ ተራ ለቀቀለት:: ቀጠለናም ሦስተኛው ልጅ ተተካ:: የሂላሪ እንባ ጉንጭና ጉንጬ ላይ ይፈስ ነበር:: ጆርጅ በድጋሚ ተገናኛት:: ከዚያም... ከዚያም ሲል ሦስቱም እንዳሻቸው ተፈራረቁባት:: ከዚያ በኋላ ሂላሪ ህሊናዋን መሳቷን እንዳዩ ለቀቋት::





ሉዊዝ ወደ ቤት የተመለሰችው ምሽት ላይ ነበረ:: ከሂላሪም መኝታ ክፍል ገብታ የሆነውን ሁሉ አየች:: ሂላሪም በዚያን ጊዜ ነፍስ ዘርታ ስለነበረ ሉዊዝ ደጋግፋ ወስዳ ገላዋን አጠበቻት፤ መኝታዋን አንጥፋ አስተኛቻት::

ሂላሪ ከአልጋዋ ውስጥ የወጣችው በሦስተኛው ቀን ነበረ:: መሄጃ በማጣቷ እነኛ ልጆች ባሉበት ቤት ውስጥ መቆየቱ የግድ ሆነባት:: ሉዊዝም ብትሆን በስራ ስለሚያግዟት እነኛን ወንዶች ልጆች ከመጠለያው ልታባርራቸው ቀርቶ ወቀሳም አልሰነዘረችባቸውም ነበረ:: በዚህም የልብ ልብ ተሰማቸው:: በዚያንም ቀን ምሽት ሂላሪ የመኝታ ክፍሏን በር ከውስጥ ከቆለፈች በኋላ ተኛች:: ደክሟት ስለነበረ ወዲያውኑ እንቅልፍ ወስዷት ነበረ:: ልጆቹ ግን የመስኮቱን እጀታ ቀደም ሲል አላልተውት ኖሮ እኩለ ሌሊት ሲሆን ድምፅ ሳያሰሙ መስኮቱን ከፈቱና እየተንጠላጠሉ ገቡ:: ጆርጅ ከጀርባዋ ቀስ ብሎ ተኛና እንዳትጮህ አፏን አፈናት:: በመጀመሪያው ቀን እንዳደረጉትም እንዳትፍጨረጨር እግርና እጇን ወጥረው ያዟት:: ከዛም ከተፈራረቁባት በኋላ በገቡበት መስኮት ተመልሰው ወጡ::

ሂላሪ በማግስቱ ጠዋት ላይ ሻንጣዋን ይዛ ወደ ማህበራዊ ጉዳይ ሰራተኛ ቢሮ ሄደች:: የደረሰባትን ግፍ ሂላሪ አውጥታ ባትናገረውም ከፊቷ ላይ ይነበብ ነበረ:: ዳግመኛም በማናቸውም መጠለያ ቤት ውስጥ ቢሆን ለመኖር እንደማትፈልግ ሂላሪ በመግለጿ የማህበራዊ ጉዳይ ሰራተኛ ዋ ለጊዜውም ቢሆን ተቸግራ ነበረ:: በመጨረሻ ላይ ግን ከከተማው ወጣ ብሎ በተሰራው የልጃገረዶች ጠባይ ማረሚያ ተቋም ውስጥ ቦታ አገኘ ችላት::

በተቋሙም ውስጥ ለሂላሪ የግል መኝታ ክፍል ተሰጣት:: ከሌሎችም ልጃገረዶች ጋር ተገናኝታ ለመጫወት አትፈልግም ነበረ:: አቋርጣም የነበረውን ትምህርት ለመከታተል አሁን ዕድል በማግኘቷ በርትታ ታጠና ጀመረ:: ያገኘችውንም መፅሐፍ ማንበብ ትወድ ነበረ:: ያላትም ዓላማ አንድ ነገር ብቻ ነው:: ዕድሜዋ ለአቅመ ሄዋን ሲደርስ ከዚያ ተቋም ውስጥ ወጥታ እህቶቿን መፈለግ ነበረባት:: በእርሷ ላይ የደረሰው ግፍ በእህቶቿም ላይ እንዳይፈፀም ትምህርቷን ጠንክራ በመከታተል ስራ መያዝና እህቶቿን ማሰባሰብ ኃላፊነቷ መሆኑ ጠልቆ ይሰማታል:: በመሆኑም ለትምህርቷ አንድም ቀን ቦዝና አታውቅም:: የብቸኝነት ጠባይዋም አንድ ጊዜ በመታወቁ ማንም ሊቀርባት አልደፈረም

ነበረ፡፡ የምትመኘውንም የሰላም ኑሮ በማግኘቷ እንደ አጥንት ደርቆ የነበረው ሰውነቷ ቀስ በቀስ እያማረበት ሄደ፡፡

ቀናት ወደ ወር፣ ወራትም ወደ ዓመታት እየተሸጋገሩ በአስራ ሰባት ዓመት ዕድሜዋ ሂላሪ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን አጠናቀቀች፡፡ ፈተናውንም በከፍተኛ ማዕረግ በማለፏ የነፃ የኮሌጅ ትምህርት የመከታተል ዕድል ተሰጥቷት ነበረ፡፡ ሂላሪ ግን ይህን ዕድል በማግኘቷ አልተደሰተችበትም፡፡ ምንጊዜም ከፊቷ ድቅን ይሉባት የነበሩት ሚጋንና አሌክሳንድራ ነበሩ፡፡ ኮሌጅ ገብታ ትምህርቷን እስከምትጨርስ ድረስ የእህቶቿን ነገር ቸል ልትለው አልፈለገችም፡፡ እነኛን ያለ እናትና አባት የቀሩ ህፃናት፣ እነኛ ከአንድ እህታቸው በግድ ተነጥለው የተወሰዱ ህፃናት ትዝታ ምን ጊዜም እንደእግር እሳት ያንገበግባት ነበረ፡፡ ስምንት የመራራ፣ የመከራ ዓመታት አሳልፋለች፡፡ አቅመ ሄዋን ለመድረስ የሚቀራት ደግሞ አንድ ዓመት ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ ከቢሮዋ ድረስ አስጠርታ የነፃ ትምህርት ዕድል ማግኘቷን ወደ ነገረቻት የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር በሀዘኔታ እያየች ትምህርት የመቀጠል ፍላጐት እንደሌላት ራሷን በማወዛወዝ ገለፀች፡፡

"ለምን! ምናልባት ሌላ ምርጫ ይኖርሽ ይሆን?" ስትል ርዕሰ መምህሯ ጠየቀቻት፡፡ "ነበረኝ፡፡ ግን ዕድሜዬ አስራ ስምንት ባለመሙላቱ ብቻ ነው የተቸገርኩት" አለች ሂላሪ አንገቷን ሰበር አድርጋ፡፡

"በግምት ወደ ሌላ ከተማ ለመሄድ የምትፈልጊ ይመስለኛል" አለቻት ርዕሰ መምህሯ፡፡

"አዎን፡፡ ግን እንደልቤ እንዳልንቀሳቀስ መሰናክል የሆነብኝ የዕድሜዬ ጉዳይ ነው" አለች ሂላሪ እንባዋ እየመጣባት፡፡

"የት ለመሄድ ነበር የምትፈልጊው?"

"ወደ ኒውዮርክ ነበረ" ስትል ሂላሪ መለሰችላት፡፡

"ኒውዮርክ በጣም ትልቅ ከተማ ነው፡፡ ከዚያ ዘመዶች አሉሽ?" ሂላሪ ራሷን በአሉታ አወዛወዘች፤ ዘመድ ቢኖራትማ ኖሮ እንዴት አራት ዓመታት የሚያህል ጊዜ በጃክሰንቪል ከተማ በሚገኝ ጠባይ ማረሚያ ውስጥ ትቆይ ነበረ! ወደ ኒውዮርክ ለመሄድ የፈለገችው ግን ዕድል ቀንቷት ትንንሽ እህቶቿን ለመፈለግ ነው፡፡ መተማመኛውም በሻንጣዋም ውስጥ የነበረው አስር ሺህ ብር ነበረ፡፡





"በእርግጥ ለመሄድ ከፈለግሽ ከሚመለከታቸው ባለስልጣኖች ጋር ተነጋግሬ በጥቂት ቀናት ውስጥ መታወቂያ ላስወጣልሽ እችላለሁ" አለቻት ርዕሰ መምህሯ፡፡

ሂላሪ በዚህ ባልተጠበቀ ዕድል የተሰማት ደስታ ከእስከ አልነበረውም፡፡ ርዕሰ መምህሯን አመስግና ከተሰናበተቻት በኋላ ክፍሏ ሄደች፡፡ ከአልጋዋ ላይ ጋደም ብላ ጣሪያ ጣሪያውን እያየች ፈገግ አለች፡፡ የስምንቱ የስቃይ፣ የውርደት፣ የብቸኝነት ዓመታት ማብቂያ መድረሱ ተሰምቷት ለመጀመሪያ ጊዜ ልቧ በደስታ ዘለለ፡፡ የእህቶቿንም ዕድሜ በአእምሮዋ አሰላች፡፡ ትንሿ ሚጋን በዚያን ጊዜ ዘጠኝ ዓመት አሌክሳንድራ ደግሞ አስራ ሶስት ዓመት ይሆናቸዋል፡፡ ሂላሪ ስራ ፈልጋ እስከምትይዝ ድረስም ቢሆን ከሻንጣዋ ውስጥ በደበቀችው አስር ሺህ ብር እህቶቿን በወጉ ተንከባክባ ለማስተዳደር እንደምትችል ታውቃለች፡፡ እህቶቿን ማግኘ ት ከባድ ነገር መስሎ አልታያትም፡፡ ኒውዮርክ እንደ ደረሰች ቀጥታ ፓተርሰን ጋ ትሄዳለች፡፡ ከርሱም አድራሻቸውን ጠይቃ እህቶቿን በአንድ ጣሪያ ስር ማሰባሰብ ቀላል ነው፡፡ ከአንድ ሳምንት በኋላ ሂላሪ ወደ ኒውዮርክ በሚወስደው አውቶብስ ተሳፈረች፡፡ ከፊቷም ላይ የብሩህ ተስፋ ነፀብራቅ ይነበብ ነበረ፡፡ የጃክሰንቪልን ከተማ ትታ በመሄዷም የሚሰማት ቅሬታ፣ ትዝታ፣ ከቶ አልነበረም፡፡ የምትለየው ዘመድና ጓደኛ አልነበራትም፡፡ አረንጓዴዎቹ ዓይኖቿ ህልማዊ አመለካከት የሚያዩ ይመስሉ ነበረ፡፡ ያለፉትም ስምንት የቅዠት ዓመታት ከአእምሮዋ ተፍቀው በአዲስ ተስፋ ታደሱ፡፡

## ምዕራፍ ዘጠኝ

ክጃክሰንቪል ከተማ የተነሳው አውቶብስ በሁለተኛው ቀን ኒውዮርክ ደረሰ፡፡ ሂላሪም ከስምንት ዓመታት በኋላ የኒውዮርክን አውራ ጎዳናዎች በእግሯ ለመርገጥ በቃች፡፡ ፓተርሰን ወደ ቦስቶን ከተማ የወሰዳት አባቷ ህይወቱን በገዛ እጁ ባጠፋ በሦስተኛው ሳምንት ነበረ፡፡ ያሰ መጠንም ብቸኝነት ስለተሰማት ከራስ ፀጉሯ እስከ እግር ጥፍሯ ዘገነናት፡፡ በዓይነ ህሊናዋም ላይ የእህቶቿ የሚጋንና አሌክሳንድራ፣ የእናቷ የሶላንጅና የአባቷ የዎከር ትዝታ ተራ በተራ እየቀረበ ዓይኖቿ እንባ አቋቱ፡፡ ልትቆጣጠረውም ባለመቻሏ እንደ ክረምት ምንጭ ያሰማቋረጥ ፈሰሰ፡፡ ከአውቶብስም መናኻሪያ የወጣችው ከሌሎች ተሳፋሪዎች እጅግ ዘግይታ በመጨረሻ ላይ ነበረ፡፡

የጃክሰንቪል ከተማ ጠባይ ማረሚያ አስተዳደር ሂላሪን ባዶ እጇን አላሰናበታትም፡፡ ሰጊዜውም ቢሆን የሚረዳት አምስት መቶ ብር ተሰጥቷታል፡፡ በዚያ ላይ ደግሞ ያ አስር ሺህ ብር ነበራት፡፡ ሂላሪ ከአንዲት አነስተኛ ሆቴል ሄዳ ገለልተኛ የሆነ መኝታ ክፍል መርጣ ከተከራየች በኋላ ከአቅራቢያ በሚገኘው ባንክ ገንዘቧን አስቀመጠች፡፡ ሰዚያንም ቀን ራቷን በያዘችው ሆቴል ውስጥ ተመገበች፡፡ ከእንግዲህ ግን ሂላሪ ገንዘብ መቆጠብ ነበረባትና በሳንዱዊችና በሐምበርገር ለመኖር ወሰነች፡፡ በቀላሉ ስራ ለማግኘት እንደማትችል ታውቃለች፡፡ ብታገኝም ምናልባት ከዝቅተኛ ደረጃ መጀመር ይኖርባታል፡፡ ከዚያም ራሷን በማታ ትምህርት የማሻሻል ዕድል ብቻ ይጠብቃታል፡፡ በመሆኑም እህቶቿን ያለ ችግር ለማስተማር ከዚያችው ደቂቃ ጀምሮ ሂላሪ ሰገንዘብ አወጣጧ ጥንቁቅ መሆን ነበረባት፡፡ ፓተርሰንንም ከማነጋገሯ በፊት ልታሟላው የሚገባት አንዳንድ ነገር መኖሩን በቅድሚያ አሰባበታለች፡፡

እህቶቿን ለማየት እንደነበራት ጉጉት ቢሆን ኖሮ ሂላሪ ከአውቶብስ እንደወረደች በቀጥታ የፓተርሰንን አድራሻ አጠያይቃ ባነጋገረችውም ነበረ፡፡ ግን ከነፍሰ ገዳይ የባሰ አውሬ አድርጋ ከምትቆጥረው ፓተርሰን ፊት በዚያ ሁኔታዋ ለመቆም አልፈለገችም፡፡ የአካል ቁመናዋ የሚያሳጣት





ባይሆንም አሰባበሷ ግን እንደነገሩ ነበረ፡፡ ሰለዚህም ኒውዮርክ በደረሰች በማግስቱ ጥሩ ጥሩ ቀሚሶችና ጫማዎች፣ አብረውትም የሚሄዱ ሌሎች ነገሮችን ስትገዛ ዋለች፡፡ ሂላሪ ወደ ትንሿ መኝታ ክፍሏ ተመልሳ የገዛቻቸውን ልብሶች እያፈራረቀች ሞከረቻቸው፡፡ በቁም ሳጥኑ መስታወት ውስጥ የምትታየው ልጅ ስምንት የመከራ ዓመታትን ያሳለፈች ልጃገረድ አትመስልም ነበረ፡፡ ሂላሪ ውብና ለግላጋ ኮረዳ እንደ ወጣት ሰራሷም ተሰማት፡፡

ፓተርሰንን ከማየቷ በፊት ሌላም አንድ ነገር መፈፀም ነበረባት፡፡ ሰገንዘብ ስትል ባይሆንም ለነ ልቦናዊ እርካታ እንዲሰማት ብቻ ስራ አፈላለገች፡፡ በየጋዜጣውም የሚወጡትን ማስታወቂያዎች አንድ በአንድ አነበበች፡፡ በሁለትና በሦስት ድርጅቶች ለቃለ መጠይቅ ፈተና ቀርባ ነበረ ግን በዕድሜዋ አናሳነትና በፀሐፊነት ሙያ ባለመሰልጠኗ የስራ ዕድል ተነፈጋት፡፡ ለብልግና ሲሆን ግን ሊዳሯት የሞከሩ ነበሩ፡፡

"ዕድሜሽ ስንት ነው?" አላት ራሰ በራውና ሆዱ የገፋው የአንድ ንግድ ድርጅት የአስተዳደር ክፍል ኃላፊ፡፡

"አስራ ዘጠኝ" አለች ሂላሪ ትንሽ ውሸት አክላበት፡፡

"አስራ ዘጠኝ የሚሞላሽ አይመስለኝም፡፡ እስቲ ለማንኛውም ቁሚና ልይሽ" አላት በግራ እጁ በያዘው መሐረብ ፊቱ ላይ ችፍፍ ያለውን ላብ እየጠረገና ከመቀመጫው እየተነሳ፡፡ ሂላሪ እንደታዘዘችው ተነስታ ቆመች፡፡ ቦርጫሙ ራሰ በራ ሰውዬ ወደርሷ ተጠጋና አገጯን ይዞ ፊቷን ቀና በማድረግ ዕድሜ በዓይን ይነበብ ይመስል፣ አረንጓዴ ዓይኖቿን ትክ ብሎ ሲያያቸው ቆየ፡፡ ከዚያም ቀስ ብሎ ወደ ደረቷ ወረደና ጡቶቿን አሻሻቸው አዝማሚያው ቢገባትም ሂላሪ ነኝ እንዳለችው ዕድሜ ለማስመሰል ስትል ዝም አለችው፡፡ ዝቅ አለና ዳሌዋን ጥብቅ አድርጎ ይዞ ሊስማት ሲል በቃሪያ ጥፊ ዓይኑ ላይ ግጥም አደረገችበት፡፡ ክው ብሎ ደንግጦ ነበረና ሂላሪ ከአቅፉ አምልጣ ከክፍሉ እየተቻኮለች ወጣች፡፡ በመንገድም ላይ እንዳለች ደጋግማ የምታሰላስለው አንድ ነገር ነበረ፡፡ 'ለምንድን ነው ወንዶች ሊያባልጉኝ የሚፈልጉት? የአክስቴ ባል ጆንስ... እነኛ ወንዶች ልጆች... አሁን ደግሞ ይሄ ሰው ... በዚህ ሁኔታ ከቀጠለ ስራ ማግኘቴንም እንጃ' ስትል አሰበችና ትካዜ ገባት፡፡

ተስፋ እንደቆረጠች ሳይሆን፣ ሂላሪ ከአንድ የሰራተኛ ማሰልጠኛ ድርጅት ውስጥ በአስተናባሪነት የመቀጠር ዕድል አጋጠማት፡፡ ሂላሪ ቆንጆ

ብቻ ሳትሆን፣ በአስተሳሰቧ በሳል፣ በአለባበሷም ጥንቁቅ በመሆኗ ዕድሜዋ እንዳለችው አስራ ዘጠኝ ባይመስልም በሳምንት ዘጠና አምስት ብር እየተከፈላት ለመስራት ተቀጠረች:: በማግስቱም ስራ እንድትጀምር ተነግሯት ስለነበረ እስካሁን ያዘገየችውን ተቀዳሚ ተግባር በዚያን ዕለት ከሰዓት በኋላ ላይ ለመፈፀም ወሰነች::

ፓተርሰንን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለማነጋገር በፖርክ አውራ ጎዳና ላይ ወደ ሚገኘው ቢሮው ታክሲ ተከራይታ ሄደች:: በመስታወትና በክሮም ከተዋበው ረጅም ህንፃ ደርሳ ከታክሲው ስትወርድ ሆዷን ባር ባር አለው:: ወደ ህንፃውም ለመግባት አመነታች:: በህፃንነት ዕድሜዋ አይሰቃዩ ስቃይ ቢደርስባትም፣ እህቶቿን አንድ ቀን አገኛቸዋለሁ የሚለው ጉጉቷ ነበረ የመንፈስ ፅናት ሰጥቷት በትዕግስት ያሳለፈችው:: ያም ቀን ዛሬ ደረሰ:: ከፓተርሰን የእህቶቿን አድራሻ ጠይቃ ታገኛለች:: ከዚያም በሳምንቱ መጨረሻ ላይ አሉበት ድረስ በመሄድ ታመጣቸዋለች:: ስታገኛቸውም ምን እንደሚሰማት ከወዲሁ ታያትና መላ ሰውነቷ ተንዘፈዘፈ::

የተሸከሟት እግሮቿ ሊከዷት ቢቃረቡም እንደምንም ከህንፃው ውስጥ ገብታ ወደ ሊፍቱ አመራች:: እንደ ጥይት የሚወረወረው ሊፍ ትም ሳታውቀው ከሰላሳ ስምንተኛ ፎቅ ደርሶ ቆመ:: ሂላሪ እንደዚያ ያለ ህንፃ አይታ አታውቅም:: እርግጥ አባቷና እናቷ ለሽርሽር ወደ አውሮፓ ወስደዋቸው በነበረበት ወቅት በሮምና በፓሪስ ከተማ አንዳንድ የሚያስደንቁ ህንፃዎች አይታ እንደነበረ ታስታውሳለች:: በተለይ የሮማውን ኮሎሰየም፣ የፓሪሉን የኢፊል ታወር አትረሳቸውም:: ፓሪስ ውስጥ በከረሙባቸው ቀናት ያደሩበት የሪትዝ ሆቴል፣ እናቷ ሰላንጅ እጇን ይዛት በትላልቅ ሱቆች ውስጥ ያደረጉት ጉብኝት አይዘነጋትም:: ከሁሉም ከሁሉም ደግሞ አባቷ እናቷን በገደለበት ምሽት እርሱ ምን ብሎ እንደተናገረና እርሷም ምን ብላ እንደመለሰችለትና በንዴትም ዘሎ አንገቷን እንዳነቀው ከህሊናዋ የማይፋቅ ነው::

የሊፍቱ በር ተከፍቶ ሂላሪ ወረደችና ወደ ፓተርሰን ቢሮ የሚያመለክተውን ቀስት ተከትላ በኮሪደሩ ላይ ሄደች:: ከእንግዳ ማረፊያ ክፍል እንደገባችም አንዲት ከርሷ በዕድሜ ብዙ የማትበልጥ ልጅ ተቀበለቻት:: ሂላሪም በማግስቱ የሚጠብቃት የአስተናባሪነት ስራ ከዚህ የተለየ አልነበረም:: ሂላሪ ራሷን ከልጅቱ ጋር በሐሳቧ አወዳደረች:: ከዚያች ከልጅ በአለባበስም ሆነ በመልክ እጅግ እንደምትሻልም ተሰማት::





እንደ አዋቂም ኮስተር ብላ ተጠጋቻትና "ሚስተር ፓተርሰንን ለማነጋገር እፈልግ ነበረ" አለቻት::

"እርሳቸውን ለማነጋገር ቀጠሮ ሰጥተውሽ ይሆን?" ስትል ልጅቱ ሳቅ አለችና መለሰችላት:: ሂላሪ ግን ከቀድሞ ሁኔታዋ አልተለወጠችም ነበረ:: በዙሪያ የምታያቸው እጅግ ዘመናዊ የቢሮ ዕቃዎች፣ ሶፋዎች፣ እንደረግረግ ትሙክ ትሙክ የሚለው ዳር ከዳር የተንጣለለው ምንጣፍ ተደማምረው ክፍሉን ግርማ ቢያላብሱትም የሂላሪን በራስ የመተማመን ስሜት አላወኩትም፤ ስለዚህም ፍፁም ተዝናንታና እራሷን ተቆጣጥራ "ቀጠሮ መያዝ የሚያስፈልግ አይመስለኝም ደግሞም አሁኑኑ ነው ላናግረው የምፈልገው" ብላ ሂላሪ ስትመልስላት ልጅቱ ሚስተር ፓተርሰንን ዘርጥጣ አንተ በማለቷ ግራ እንደመጋባት ብሏት "ስምሽን ብትነግሪኝ?" አለች ለመፃፍ የማስታወሻ ደብተሯን እያዘጋጀች::

"ሂላሪ ዎከር" አለቻት ሂላሪ::

"ሂላሪ ዎከር ነው ያልሽኝ?" ስትል ልጅቱ ስሟን በድጋሚ ጠራችና ሳትፅፍ ቀና በማለት "እንደነገርኩሽ በቅድሚያ ቀጠሮ መያዝ ይኖርብሻል" አለቻት::

"ሂላሪ ዎከር ልታነጋግርህ ትፈልጋለች ብለሽ ንገሪው:: ከዚያም ለምን ቀጠሮ መያዝ እንዳላስፈለገኝ ታውቂዋለሽ"

"አልችልም የኔ እመቤት፤ ታስቀጪኛለሽ" አለች ልጅቱ::

"አይቆጣሽም" አለቻት ሂላሪ

"ለምን?" አለችና ከላይ ታች በመገረም ታያት ጀመረ::

"የክርስትና አባቴ ነው" አለችና ሂላሪ ፤ የተናገረቻቸው ቃላት በልጅቱ ላይ ሊያሳድሩ የሚችሉትን ለውጥ በዓይኖቿ ተከታተለች::

ልጅቱም "ነው እንዴ?" አለችና  የቢሮው ውስጥ መነጋገሪያውን መሳሪያ ቁልፎች ቁጥር እየተቻከለች ተጫነች:: ብዙም ሳይቆይ መልስ በማግኘቷ "የሚስተር ፓተርሰን ልዩ ፀሐፊ እየጠበቀችሽ ስለሆነ ከሚቀጥለው ክፍል ውስጥ ብትገቢ" ስትል ከመቀመጫዋ ተነስታ ወደ አንድ የተዘጋ በር አሳየቻት:: ሂላሪም አመስግናት ወደ ተነገራት ክፍል አመራች:: ዳር እስከዳር በቀይ ምንጣፍ አጊጦ የነበረው ክፍል ከመለስተኛ አዳራሽ አያንስም:: ዙሪያውንም በቆዳ በተደጎሱ የህግ መፃህፍት የተጨናነቁ ባለ መስታወት

መደርደሪያዎች ተገጥግጠዋል:: መሐል ላይ ከሚታየው ትልቅ ጠረጴዛ በስተኋላ አንዲት ጠና ያለች ሴት የሂላሪን መግባት ቆማ ትጠባበቅ ነበረ:: ፈገግታም እያሳየቻት ወደርሷ ቀርባ የእጅ ሰላምታ ከሰጠቻት በኋላ ወደ ሚስተር ፓተርሰን ቢሮ ይዛት ሄደች::

አዎን! ሂላሪ ፓተርሰንን ከስምንት ዓመታት በኋላ ልታየው ነው:: ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ዛሬ ታነጋግረዋለች:: እርሱ ነው ያለ ፍላጐቷ ከነ ኢሊን ጋር እንድትኖር ያደረጋት። ለኢሊን ባል ለጆንስ ጭካኔም አሳልፎ የዳረጋት ፓተርሰን ነበረ:: ወላጆች ያልነበራቸው ልጆች በሚኖሩበት መጠለያ ቤትም ለመኖር ያበቃት ዋናው ምክንያት ያው ፓተርሰን ነበረ:: በእነኛ ወንዶች ልጆች ክብረ ንፅህናዋ እንዲደፈር ኢሰብዓዊ አድራጐት እንዲፈፀምባት፣ በጃክሰንቪል ጠባይ ማረሚያ ለመግባትም ምክንያቱ አሁንም ፓተርሰን ነው:: በተለይም እባቷ እናቷን በገደለበት ምሽት ለጥሉ መንስኤ የነበረው ይኸው ፓተርሰን መሆኑን ተደብቃ ከነበረችበት ከበራፉ ስር ሆና አዳምጣለች:: ከሚጋንና ከአሌክሳንድራም ጋር የለያት ፓተርሰን ነው:: በዚያን ቀን ከመንገድ ዳር ተንበርክካ የእህቶቿን ስም እየጠራች ያለቀሰችው ለቅሶ ታወሳትና በዓይኖቿ ጢም ያለውን እንባዋን ታግላ ዋጠችው::

ልዩ ፀሐፊዋ በሩን ስታንኳኳ “ይግቡ!” የሚል ድምፅ ተሰማ:: ሂላሪ ያንን ድምፅ በደንብ ታስታውሰዋለች:: ፀሐፊዋ በሩን ከፍታ ካስገባቻት በኋላ ዘጋችውና ተመልሳ ሄደች:: ሂላሪና ፓተርሰን ከስምንት ዓመታት በኋላ ተያዩ:: ከመስታወትና ከአልሙኒየም ከተሰራ ጊዜ እመጣሽ ጠረጴዛ ኋላ ተቀምጧል:: ክጀርባውም በነበረው ሰፊ መስኮት የኒውዮርክ ከተማ ወሰል ብላ ትታያለች:: የፓተርሰን ዕድሜ በሃምሳው አካባቢ ቢሆንም ላየው ሰው ሽማግሌ ነበረ የሚመስለው:: ከመርገፍ የዳነው ፀጉሩ ሸብቷል:: የዓይኑ ቆዳዎች ተሸብሽበው ጉንጮቹ ተጣብቀዋል:: ሂላሪም ሰላምታ ሊሰጣት ሲነሳ፣ የረጅም ቁመናውን አከሳስ እያየች ከመቃብር ያመለጠ አስከሬን መስሎ ታያት::

እርሷ ግን ገና የምታድግ ለግላጋ ወጣት ናት:: ከአባቷ ከወረሰችው ጥቁር ፀጉሯ በስተቀር ቁርጥ እናቷን ሶላንጅን ነበረ የምትመስለው:: ልክ ከሃያ አንድ ዓመታት በፊት በፓሪስ ደአርኩል ጎዳና ላይ ፓተርሰንና ምክር እንዳገኟት ሶላንጅ የሂላሪም አቋምና አመለካከት ተመሳሳይ ነበረ:: ፓተርሰን ተጠግቶ እጇን ሰመጨበጥ ፈለገና ሐሳቡን ቀየረ:: አስተያየቷ ከበረዶ የቀዘቀዘ ስለነበረ ወደፊት ለመሄድ ፈራ:: ምን ያህል እንደምትጠላውና እጁን በላይዋ ለማሳረፍ ቢምክር ልትገድለው እንደማትመለስ ታወቀውና





ባለበት መቆምን መረጠ:: በተሰባበረም አነጋገር “ሂላሪ፤ ደህና ነሽ?” የሚሉትን ቃላት ብቻ ደፍሮ ተናገረ::

ስለ ሂላሪ ደህንነት መጠየቂያው ጊዜ አሁን አይደለም:: ፓተርሰን ቃላቱ ከአፉ ካመለጡት በኋላ ተቆጨ:: ሂላሪም ብትሆን እንደዚያ ብሎ ስለጠየቃት ይበልጥ ጠላችው:: ልፍስፍስና ወኔ ቢስ ሰው መሆኑን ለማንበብ የቻለችው በዚያን ጊዜ ነበረ:: ከእርሱ ጋር በሰላምታ ልውውጥ የምታጠፋው ጊዜ፣ ያለፈ ትዝታ አንስታ የምትጫወትበት ትዕግስት አይኖራትም:: የመጣችው ለአንድ ነገር ብቻ ነው:: ስምንት ዓመታት በሙሉ በልቧ እንደፅላት ቀርፃ ላቆየችው አንድ ነገር ብቻ ስትል ነው ፓተርሰንን ለማነጋገር የምትፈልገው::

“እህቶቼ የት እንዳሉ እንድትነግረኝ ነው የምፈልገው?” ዓይኖቿን ከዓይኖቹ ላይ ተክላ:: ሂላሪ ለጥያቄዋ መልስ እስከሚሰጣት የፊቱን መለዋወጥ በቀላሉ አጤነችው:: ፍርሐትና ጭንቀት ይፈራረቁባታል:: ልክ ከበፊቱም ይልቅ አሁን ፃዕረ ሞት መስሎ ቢታያትም ትንፋሿን ሰብስባ ምን እንደሚል ጠበቀችው::

ፓተርሰን ዛሬ ሂላሪን ሊያታልላት አይችልም:: ዛሬ የዘጠኝ ዓመት ህፃን ሳትሆን ለአቅመ ሄዋን የደረሰች ልጃገረድ ነበረች:: ከስምንት ዓመታት በፊት አታሎ እህቶቿን ወሰደባት:: ዛሬ ግን እህቶቿን ለመፈለግ መጥታለች:: ስለዚህም የት የት እንዳደረሳቸው መናገር ነበረበት:: “ሂላሪ... እባክሽ ብት ቀመጪ... ለመወያየት ያመቻናል..." በስተጥግ ወደነበረው ሶፋ እያመለከተ::

“ካንተ ጋር ለመቀመጥ አልፈልግም ... ካንተ ጋር ለመወያየትም አልፈልግም... ባንተ የተነሳ ወላጆቼን አጣሁኝ:: ላንድ ቤተሰብ መፍረስ ምክንያት ከሆንክ ሰው ጋር ለመነጋገር አልሻም:: የመጣሁት የእህቶቼን አድራሻ እንድትነግረኝ ብቻ ነው:: ከዚያም እሄዳለሁ::” አለችው አመለካከቷን ሳትቀይር:: ፓተርሰን የሚናገር የሚያደርገው ጠፋው:: ሂላሪ የተናገረችው በሙሉ ትክክል መሆኑን በሚገባ ያውቀዋል:: ግን ሂላሪ ለሶላንጅ ሞት እርሱ ምክንያት መሆኑን በምን ልታውቅ ቻለች ሲል አእምሮው ተበጠበጠ:: ሂላሪ ወላጆቿን አጥታለች... እህቶቿን ተነጥቃለች... ስምንት የስቃይ ዘመናት አሳልፋለች... ያ ሁሉ ሆኖ እንደ ሶላንጅ የማትበገረው ሂላሪ ከፊት ለፊቱ ቆማ መልስ እየጠበቀች ነው:: መልስ መስጠት ደግሞ ግዴታው እንደሆነ ያውቀዋል:: ሂላሪ ደግሞ የሚያግኛት ልጅ አልነበረችም::

ትላልቅ አረንጓዴ ዓይኖቿ ልብ የሚያስላስለውን፣ አእምሮ የሚያመላልሰውን ጠልቀው የማየት ችሎታ ያላቸው ይመስሉ ነበረ::

"እኔ የተጨነኩት ሳንቺ ነው እንጂ እህቶችሽንስ የሰጠኋቸው ለደህና ቤተሰቦች ነበረ::" አላት ፓተርሰን::

"እንዲህ አድርጐም መጨነቅ የለ! ስለተጨነክልኝ ነዋ የእነ ኢሊን፣ የነጆንስ መጫወቻ ያደረከኝ? በጃክሰንቪል ከተማ በየመጠለያው ቤትና በጠባይ ማረሚያ ተቋም እንድሰቃይ የተውከኝ? የዛሬውን ሃዘኔታህን 'የአዞ እንባ' ከማፍሰስ ሰይቼ አላየውም:: ስለዚህ ልሰማ በማልፈልገው ወሬ ጊዜ አታባክንና ይልቁኑ አሌክሳንድራና ሚጋን የት እንደሚገኙ ንገረኝኝ ብሄድ?" አለች አፈር ድሜ በሚደባልቅ አስተያየት እያየችው::

"አድራሻቸውን አላውቅም" አላትና እርፍ አለ::

"ምን? አድራሻቸውን አላውቅም? ማወቅ አለብህ ሚስተር ፓተርሰን! ትሰማኛለህ! ማወቅ አለብህ! ከእቅፌ ውስጥ ነጥቀህ የወሰድካቸውን እህቶቼን ለማንና የት እንደሰጠሀቸው ማወቅ ይኖርብሃል!" ብላ አምባረቀችበት:: ሂላሪን እንደረሳት እህቶቿንም ይረሳቸዋል የሚል ግምት አልነበራትም:: ስለዚህም አሁንም ተስፋ ባለመቁረጥ ዝም ብላ ታየው ጀመረ:: ፍርሐት... ፀፀት... በደለኛነት... የመሳሰሉት ስሜቶች ይመላለሳሉ::

መቆምም ስላልቻለ ካጠገቡ ካገኘው መቀመጫ ላይ አረፍ አለና በረጅሙ ተነፈሰ:: በግንባሩ ላይ ችፍፍ ያለውን ላቡን መሐረብ አውጥቶ ከጠረገ በኋላ፤ ሂላሪን ቀና ብሎ እያየ አሌክሳንድራን ጐርሐም ለሚባለው ጠበቃ ነበረ የሰጠኋት:: ማርጋሬት የምትባልም ወጣትና ቆንጆ ሚስት ነበረችው:: "አሌክሳንድራን እንደነፍሳቸው ይወዷት ስለነበረ በሄዱበት ሁሉ ከስራቸው አይለዩዋትም ነበረ:: ወደ አውሮፓ ለሽርሽር ሄደው እንደተመለሱ፤ ጐርሐም ዕድሜው ገፍቶ ነበርና በልብ ድካም በሽታ ሞተ:: ማርጋሬት በባሏ ሞት እጅግ ከማዘኗ የተነሳ በአሜሪካ ላለመኖር ቆርጣ ወደ ፈረንሳይ አገር እንደ ሄደች አውቃለሁ:: አሌክሳንድራም አብራት ነበረች... ከፓሪስም ደብዳቤ እንደፃፈችልኝ አስታውሳለሁ... ለመጨረሻም ጊዜ የፃፈችልኝ ከስድስት ዓመታት በፊት ነው ... ከዚያን ወዲህ ግን የት እንደደረሰች አላውቅም... ሌላ ባል ታግባ ወይም ወደ ሌላ አገር ትሂድ የማውቀው ነገር የለኝም" አለ ፓተርሰን ቁርጥ ቁርጥ በሚል ትንፋሽ::





የሂላሪ ዕንባ በጉንጭና ጉንጯ ላይ እየተንከባለለ የቆመችበትን ምንጣፍ አራሰው:: 'አክሲ ... አክሲ ... የአምስት ዓመቷ አክሲ ... ሂሊ እያለች ታቆላምጣት የነበረችው አክሲ ... አክሲ ባለ ወርቃማ ፀጉሯ ... አክሲ ባለአረንጓዴ ዓይኖቿ፤ ድምጿ... አሳሳቋ... እናቷን ሶላንጅን ታስታውሳት የነበረችው አክሲ ... አክሲ ... አክሲ ... አክሲ ...' የሂላሪ ልብ የተጨነቀ አመታቱን ጨመረ... ጮኽ የማይወጡት ሲቃ ጉሮሮዋን አፈነው:: አክሲ ሳቂታዋ... አክሲ ተጫዋቿ... አክሲ የትንሿ የሚጋን ሞግዚት... "ሚጋንስ?" አለች ሂላሪ ጉዴን ልወቀውና ልረፈው በትል::

የፓተርሰን ፊት ሐፍረት ብቻ ሳይሆን የሞት ጥላ ያንገበበት ይመስል ነበረ:: እርሱም ቢሆን ቁርጡን ነግሮ ቶሎ ሊገላገላት በመፈለጉ "ሚጋንን የሰጠኋት ደግሞ ዴቪድና ሬቤካ ለሚባሉ ባልና ሚስቶች ነበረ... ሁለቱም ጠበቃዎች ናቸው... የተሻለ የስራ ዕድል ስላገኙ ወደ ካሊፎርኒያ የሄዱት በዚያኑ ዓመት ነበረ:: እነርሱ ግን ከኔ ጋር ምንም ግንኙነት እንዲኖራቸውና ሚጋንም ስላለፈው የቤተሰቧ ታሪክ አንድም ነገር እንድ ታወቅ አልፈለጉም... ስለዚህ ወደ ካሊፎርኒያ መሄዳቸውን ብቻ ነው የማውቀው" አለና አቆመ::

ሂላሪ አሁን አላለቀሰችም:: ነፀብራቅ የሚወረውሩ በሚመስሉ አረንጓዴ ዓይኖቿ ፓተርሰንን ቁልቁል ስታየው ቆየችና "ሁለት ሰዎች ገደልክ... ሦስት እህትማማቾች ደግሞ አለያየህ... ለአምስት ሰዎች ጥፋት ምክንያት ነህ ማለት ነው:: ለምን? ለምን የእኛ ቤተሰብ ፀር ሆንክ? ወላጆቼስ የበደሉህ ነገር ነበርን? እኛስ ህፃናቶቹ ምን አደረግንህ? እኔን ለስንት ዓይነት ስቃይ እንደዳረከኝ ታውቀዋለህ? ያን ሁሉ ታግሼ ለዛሬዋ ቀን ለመድረስ የበቃሁት በእህቶቼ ትዝታ በመፅናናት ነበረ:: አግኝቼ እንደ እናት ሆኜ አሳድጋቸዋለሁ ስል እጓጓ ነበረ:: አንተ ግን እህቶቼን በታተንካቸው! ይባስም ብለህ የት እንዳሉም እንኳን አታውቅም! ለዚህ ሁሉ ስራህ እግዚአብሔር ይፍረድብህ! ለኔ ግን ያንተን ዓይን ዳግመኛ አያሳየኝ! እኔ ሂላሪ ተራ ሰው ሆኜ የምቀር እንዳይመስልህ:: አንድ ቀን ትልቅ ሰው እሆናለሁ:: እህቶቼንም እፈልጋቸዋለሁ:: ትሰማኛለህ! አንድ ቀን አገኛቸው ይሆናል" ብላ በሩን ከፍታ እንደ ጥላ ከፊቱ ተሰወረች::

ፓተርሰን ለመጀመሪያ ጊዜ አለቀሰ:: ጭብጥ ብሎም እንደተቀመጠ የጓደኛው የምክርና የሶላንጅ ትዝታ ታወሰው:: የሚፋቀሩ፣ ደስተኞች ባልና ሚስት ነበሩ:: የሚወዷቸውን ህፃናት ልጆቻቸውን አፍስሰው ለመሞት ምክንያት የሆነው ፓተርሰን ነበረ:: ፓተርሰን በዚያ ቤት ላይ ግፍ ውሏል::

በደሉንም የሚያስተሰርይለት ምንም ኃይል እንደማይኖር ተሰማው:: 'ሁሰቱ የሂላሪ እህቶች ይሄን ጊዜ ወዴት ደርሰው ይሆን?' ሲል አሰበ::

መልስ የሚገኝለት ጥያቄ አልነበረም:: ሂላሪ ከፓተርሰን ቢሮ እንደወጣች በቀጥታ የሄደችው በፖርክ አውራ ጎዳና ላይ ወደሚገኘው ቤተ መፃህፍት ነበረ:: የኒውዮርክን ከተማ ስልክ ማውጫ ዘርግታ በመና በገ ፊደላት የሚጀምሩትን ስም ዝርዝሮች አንድ በአንድ ተመለከተች:: ማርጋሬትና ጉርሐም የሚሉ አምዕትክሞች ብቻ አገኘች:: እያንዳንዱንም ቤት ደውላ አሌክሳንድራ የምትባል የጉዲፈቻ ልጅ ስለመኖር አለመኖሯ ጠየቀች:: አሌክሳንድራ የምትባል ልጅ በአንደኛውም ቤት የለችም:: ቀጠለችና በካሊፎርኒያ ያሉትን ጠበቆች ስም ዝርዝር የያዘውን ጥራዝ አውጥታ ዴቪድና ሬቤካ የሚሉትን ስሞች ፈለገች፤ ስምቹ ከነጭራሹ አልተመዘገቡም:: እነ ዴቪድ ከካሊፎርኒያ ከለቀቁ ቆይተዋል ማለት ነው:: ፍፁም እምነት የነበራት በፓተርሰን ነበረ:: የሚታያትም በሳምንቱ መጨረሻ ላይ እህቶቿን አግኝታ እንደ ህፃንነታቸው አንዷን በቀኝ፣ አንዷን በግራ እጇ ስታቅፋቸው ነበረ:: በቃ እንግዲህ የነ አሌክሳንድራ ነገር... አለቀለት... የትንሿ የሚጋን ነገር... ሂላሪ ከቤተመፃህፍቱ ጀምራ ሆቴሏ እስከምትደርስ ድረስ መንገድ ለመንገድ እንዳለቀሰች ነበረች:: እህቶቿንም እንደ እናቷ ዳግመኛ እንደማታገኛቸው ተሰማት:: በእናቷም የሬሳ ሳጥን ላይ ከነበረው የአበባ ጉንጉን እንደወሰደቻቸው ሁለት ነጫጭ ፅጌረዳዎች እህቶቿም እየጠወለጉ ሲከስሙ፣ ብሎም ወደ አፈርነት ተለውጠው ኢምንት ሲሆኑ ለአይነ ህሊናዋ ታያት::





# ክፍል 3

# አሌክሳንድራ

"የማያልፍ ነገር የለም ምሽትም በማለዳ ይተካልና!!"

## ምዕራፍ ፲ አስር

ከፎሽ አውራ ጎዳና ገንጠል ብሎ በሚወስደው መንገድ ላይ በግምብ አጥር የታጠረ አንድ ውብ ህንጻ አለ። ወደ ውስጥም ሲገቡ በግራና በቀኝ ዓይን የሚስቡ የጥድ ተክሎች የተሰያየ ቅርጽ ያላቸው የአበባ መደቦች ይታያሉ። ቤቱ ከጥንታዊ የፈረንሳይ መሳፍንት ቤተሰቦች አንዱ የነበረው የባሮን ሄነሪ ነው። ባሮኑ በዘሩ ይኩራራ እንጂ እስከዚህም ሀብታም የሚባል ሰው አልነበረም። ያንንም የመሰለ መኖሪያ ቤት ሰማግኘት የበቃው የኮምት ደ.ቦርን ልጅ የነበረችውን አሌክሳንድራን በማግባቱ ነበረ። በጋብቻውም ሳቢያ ካገኘው ሌላ ሌላ ስጦታ ጎን በሪቪዬራ የባሕር ዳርቻ በየዓመቱ የበጋውን ወራት የሚያሳልፍበት እራሱን የቻለ ቪላ ነበረው።

ሄነሪና አሌክሳንድራ ከተጋቡ አስራ አራት ዓመት አልፏቸዋል። ሜሪና አክሲል የተባሉ ሁለት ሴት ልጆች ሰመውሰድም በቅተው ነበረ። በኑሮአቸውም ፍጹም ደስተኞች ነበሩ። ከሀብት ሀብት፣ ከልጅ ልጅ በሁሉም የታደሉ፣ የሚፋቀሩ ባልና ሚስት ነበሩ። ሄነሪ አሌክሳንድራን በሐያ ዓመት ቢበልጣትም ገና እንዳየችው ወደደችው። ያን ጊዜ እርሷ ገና የአስራ ዘጠኝ ዓመት ልጃገረድ ነበረች። አባቷ ኮምት ደ.ቦርን ጋብቻቸውን ሰሁለት ዓመት እንዲዘገይ አድርገው ነበረ። ምናልባትም በዚህን ወቅት አሌክሳንድራ ግን መልከ ቀናውንና ቁመናው የሚያምረውን ሄነሪን ያፈቀረችው ከልቧ ኖሮ እርሷ በሐያ አንድ አመቷ፣ እርሱ በአርባ አምስት ዓመቱ ተጋቡ።

ኮምት ደ.ቦርን ለአሌክሳንድራ ሁለተኛ የጉዲፈቻ አባቷ ነበሩ። ያም ሆኖ አሌክሳንድራ ከወላጅ አባት አስበልጣ ነበረ የምትወዳቸው። የመጀመሪያው የጉዲፈቻ አባቷ አሜሪካዊ ጉርሐም ከሞተ በኋላ ከእናቷ ከማርጋሬት ጋር ወደ ፈረንሳይ መጡ። በዚያን ጊዜ ዕድሜዋ ስድስት ዓመት ነበረ። በፓሪስ ከተማ ውስጥ ለስድስት ወር ያህል እንደተቀመጡ ማርጋሬትና ኮምት ደ.ቦርን ይገናኛሉ። ሁለቱም የትዳር ጓደኞቻቸው በሞት ተለይተውባቸው ስለነበረ ከጥቂት ጊዜ ትውውቅ በኋላ ይጋባሉ።





ኮምት ደ.ቦርን ሌላ ልጅ ስላልነበራቸው አሌክሳንድራን በጉዲፈቻ ሕጋዊ ልጃቸውና ብቸኛ ወራሻቸው ያደርጓታል። እርሳቸውም ቢሆኑ ከመጠን በላይ ይወዷት ስለነበረ አንቀባረው ነበረ ያሳደጓት። አሌክሳንድራም ሁለተኛ የጉዲፈቻ አባት መሆናቸውን ከርሳቸውና ከማርጋሬት በስተቀር ሚስጥሩን የሚያውቀው ሌላ ሰው አልነበረም።

አንድ ነገር ሳይጓደልባት በምቾትና በድሎት ያደገችው አሌክሳንድራ በአስራ ዘጠኝ ዓመት ዕድሜዋ ሄነሪን ለማግባት በመፈለጓ ያልተገረመ ሰው አልነበረም። በተለይም ደግሞ ኮምት ደ.ቦርን በዚህ በልጃቸው ውሳኔ ቅሬታ ገብቷቸዋል። እንደርሳቸው ምኞት ቢሆን ኖሮ አሌክሳንድራ በዕድሜ ከሚቀራረባት ወንድ ጋር በተጋባች ነበረ። የሄነሪንና የርሷንም ጋብቻ ሰሁለት ዓመት እንዲዘገይ ያደረጉት ያስምክንያት አልነበረም። ግን ያም ሆነና አሌክሳንድራ በሀሳቧ በመፅናቷ በመጨረሻ ላይ ሄነሪን እንድታገባ ተፈቀደላት። ሄነሪም እርሷን በማግኘቱ ዕድለኛ ሆነ። እንደርሱ እርሷም የመሳፍንት ዘር ነበረች። ከአባቷም ኮምት ደ.ቦርን እጅግ ሀብታም ነበሩ። በስርጋቸው ዕለት ከሺህ የሚበልጡ እንግዶች ተጋብዘዋል። ከዚያም የጫጉላ ጊዜያቸውን ያሳለፉት የአትላንቲክ ውቅያኖስን አቋርጠው በሀይቲ ደሴት ነበረ። ልክ በዓመቱም አሌክሳንድራ ሴት ልጅ ወለደች። አባቷም ኮምት ደ.ቦርን የልጅ ልጅ ባዩ በሁለተኛው ዓመት ዓረፉ።

ከኮምት ደ.ቦርን ሞት በኋላ አሌክሳንድራ ለባሏ ትሳሳለትና ታስብለት ጀመረች። እርሱም የሚለያት እየመሰላት ሲበዛ ትንሰፈሰፍለት ነበረ። አድርጊ ያላትን ሁሉ ከመፈፀምም ወደ ኋላ አትልም ነበረ። የፖለቲካ ሰው ለመሆን ዕቅድ ስለነበረውም በየምሽቱ እንግዶች አንደጋበዘ ነው። አሌክሳንድራም ጥሩ አስተናጋጅ ሆና መቅረብ ነበረባት። እርሷም አንዴም ቅር ብሏት አያውቅም። እናቷ ማርጋሬት ግን ልጇን የጨቆነባት እየመሰላት አትወደውም ነበረ። አንድ ቀን ማርጋሬትና አሌክሳንድራ ሻይ በመጠጣት ላይ እንዳሉ የሄነሪ ነገር ተነሳና ማርጋሬት ቅሬታዋን ሳትደብቅ ገለፀችላት።

“አይ እማማ!” አለችና አሌክሳንድራ ልታግባባት ጀመረች። “እይው ሄነሪ ዝና ይወዳል። ይህ ደግሞ ተፈጥሮው ነው። ስለዚህ ባሌ የሚፈልገውን ዝና እስኪቀዳጅ በሆነው ዘዴ ሁሉ ልረዳው ይገባል። አንቺ ግን እኔ የተጨቆንኩ መስሎሽ እንደምትቆረቆሪልኝ ይሰማኛል። ሆኖም የማደርገው ሁሉ ባሌን እስካስደሰተው እኔም ደስተኛ መሆኔን እወቂልኝ” አለቻት

አሌክሳንድራ:: ማርጋሬት ግን በአሌክሳንድራ መልስ አልረካችም:: በሐሳቧም በሞተው ባሏ ደ.ቦርን፣ በልጇ ባል ሄነሪ መካከል ያለውን ልዩነት አውጠነጠነች:: የርሷ ባል ጨዋታ ወዳድ፣ ቤተሰቡን አፍቃሪና ትሁት ሰው ነበረ:: በዘርና በሀብት ከሄነሪ ወላጆች ቢበልጥም ኩራት የሚሉት ነገር አያውቅም:: ሄነሪ ግን ቁንንና ሰው ሰው የማይመስለው ጉረኛ ነበረ:: በዚያ ላይ ደግሞ ጨዋታው ለዛ ቢሶና ደረቅ ነበረ:: ማርጋሬት ሁለቱን ሰዎች በአእምሮዋ ታመዛዝናቸው እንጂ ከአፏ አውጥታ ለልጇ ለመናገር አልፈለገችም:: አሌክሳንድራ ሄነሪን ለማስደሰት የምትፈልግውን ያህል ማርጋሬት አሌክሳንድራ እንድትደሰት ትሻለች::

ዝና የጠማው የሄነሪ ፍላጎት ግን ከቀን ቀን እየጨመረ ይሄድ ነበረ:: ዕለት በዕለት በሚያደርገው ግብዣ ላይ ሚስቱ ከማንኛውም የፓሪስ ሴት ተቆንጅታና አጊጣ እንድትገኝለት ይፈልጋል:: በዘሯም፣ በሁብቷም መኩሪያው ስለነበረች ምን ጊዜም ከጐኑ እንድትለይ አይፈልግም:: እናቷን ለመጠየቅ ከመሄዷ በፊት እንኳን እርሱን ማስፈቀድ ነበረባት:: ግን ሄነሪ የማያውቀው አንድ ሚስጥር ደግሞ፤ማርጋሬትና ኮምት ደ.ቦርን ከተወያዩበት በኋላ ከሄነሪ እንደተሰወረ እንዲኖር ወስነዋል:: በዘሩ የሚኩራው ሄነሪ ሚስቱ አሌክሳንድራ ከኮምት ደ.ቦርን አብራክ የተወለደች እንጂ የጉዲፈቻ ልጅ መሆኗን አያውቅም:: ይህንንም አሌክሳንድራም ብትሆን በጊዜ እርዝመት እረስታዋለች:: የሚገርመው ግን አሌክሳንድራም ብትሆን የማታውቀው አንድ የተለየ ሌላ ሚስጥር ነበረ:: የአሌክሳንድራ የመጀመሪያው የጉዲፈቻ አባቷ ጉርሐም በሞተ ጊዜ የአምስት ዓመት ልጅ ነበረች:: ከዚያ በፊት ሌላ ቤተሰብ እንደነበራትና ወላጆቿም በአሳዛኝ ሁኔታ መሞታቸውን ፈፅሞ አታስታውሰውም:: ያንን ሚስጥር የምታውቀው የጉርሐም ባለቤት የነበረችውና አሌክሳንድራም ወላጅ እናቷ አድርጋ የምትቆጥራት ማርጋሬት ብቻ ነች:: ማርጋሬትም አሌክሳንድራን እንደ ብቸኛ ልጇ ነው የምታያት::

አሌክሳንድራ ታላቋ ልጇን ማሪን በወለደችበት ወቅት ለማርጋሬት ደስታ ለከት አልነበረውም:: አያት ለመሆን በመብቃቷም ኮርታባት ነበር:: በዓመቷም ወንድ ልጅ ስትደግም ደስታዋ ከመጠን አለፈ:: ሆኖም ልጅየው ከተወለደ ከጥቂት ቀናት በኋላ በመሞቱ የተደሰተችውን ያህል በሀዘን ተጨበጠች:: ከአምስት ዓመት በኋላ አሌክሳንድራ አክሲልን በሀኪሞች እርዳታ ተገላገለች:: ከዚያ በኋላ ግን ብትፀንስ ለህይወቷ እንደሚያሰጋት ተነገራት:: አሌክሳንድራ በሁለት ሴት ልጆቿ ረካታለች:: ሄነሪ ደግሞ ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፍ





የመጣውን የቤተሰቡን የማዕረግ ስም ወራሽ ወንድ ልጅ ስላላተረፈችለት ትዝ ባለው ቁጥር አሌክሳንድራን ጨክኖ ባይረግማትም ይቀየማት ነበረ:: ይህንን ቅሬታውን አሌክሳንድራም ብትሆን ታውቀዋለች::

ወንድ ልጅ ባለማግኘቱም መቀየሙ ያነሰው ይመስል፤ ለሄነሪ ሌላ ራስ ምታት የሆነበት ነገር ነበረ:: ልጇን በየጊዜው ለመጐብኘት የምትመጣውን አማቱን ማርጋሬትን አይወዳትም ነበረ:: ስለ እርሷም ብዙ አቃቂሮችን ማውጣት ይወዳል:: ረጃጅሞቹን አሜሪካዊ ባቶቿን እንደ ምሳሌ ይጠቅስና ወንዳ ወንድ ናት ይላል፤ ስትስቅ እንደ ጭዋ ሳይሆን እንደ ባለጌ ታስካካለች ይላል:: ፈረንሳይኛ ስትናገር አንዳንዶቹን ቃላት ሰበርበር ታደርጋቸው ነበርና እንደ ጥፍር ሲጢጥታ ለጆሮው ይቀፈዋል:: ለልጅ ልጆቿ የምታመጣላቸው ስጦታዎች ሁሉ አንዱም ደስ አይለውም:: ወደ ኒውዮርክ ሄዳ በተመለሰች ቁጥር እየገዛች የምታመጣላቸውን ልብሶች አይወዳቸውም:: ልጆቹም እነኛን ልብሶች እንዲለብሱ አይፈቀድላቸውም:: ክብራቸውን ብሎም የርሱንም ክብር የሚያስነኩ ይመስለዋል:: አሌክሳንድራም በእናቷ ባለመውጣቷ እግዚአብሔርን ያመሰግናል:: አሌክሳንድራ እንደ እናቷ ለፍላፊ አይደለችም:: በቅርፅም ሆነ በመልኳ እንዲሁም በባህሪዋ ከእናቷ የተለየች ናት:: ዓይነተኛ ለፈረንሳዊው መስፍን የምትስማማ ሚስት ነበረች:: ውበቷ ብቻ ሳይሆን የሚደነቀው አሌክሳንድራ ብልህ፣ ደግ፣ ታዛዥና ረጋ ያለች ልጅ ነበረች:: ማርጋሬት ግን... ሽማግሌው ኮምት ደ.ቦርን ምኗን አይቶ ይሆን ያገባት?

የሄነሪን ወደ ቤት መመለስ አሌክሳንድራ አላወቀችም ነበረ:: ከፅህፈት ጠረጴዛዋ ላይ አቀርቅራ በመፃፍ ላይ እንዳለች ቁልቁል አያትና ፈገግ አለ:: እንዲች ያለች የተባረከች ሚስት በማግኘቴ ዕድለኛ ነኝ አለ በሆዱ:: አሌክሳንድራ ከእናቷ ጋር የአባቷን ሀብት ተካፍላ ነበርና ሄነሪን የገንዘብ ችግር አይገጥመውም:: በአሌክሳንድራ የቤት አያያዝ ችሎታ ቤቱ ገነት ነበረ የመሰለው:: የመጋረጃ አመራረጧ፣ የሶፋ የጠረጴዛና የወንበር አቀማመጧ፣ የግርግዳ አጋጌጧ ... የምንጣፍ ቀለም፣ ሙዚቃው፣ ምግቡ፣ ምድረ ግቢው ... አሌክሳንድራ ክትልቅ ተወልዳ በትልቅ ቤት ለማደጓ ምስክር ነበሩ:: 'አሌክሳንድራ ደ.ቦርን ደ.ሞሪኒ! አንቺን ባላገኝ ኖሮ ህይወቴ እንዴት በጨለመ' ሲል አሰበ::

ሄነሪ ጎንበስ ብሎ ሚስቱን ከግንባሯ ላይ ከሳማት በኋላ "በማለም ላይ ያለሽ ትመስያለሽ" ሲል በለሆሳስ ድምፅ ተናገረ:: ሄነሪ ጮኾ መናገር አይወድም ነበረ:: ደግሞም የሚጮህበት ምክንያት አይኖርም:: ትሁት

ታዛዥ አፍቃሪ ሚስት አለችው:: ዕድሜው ገፍቶ አሁን ሃምሳ ዘጠኝ ዓመት ቢሆነውም ቁመናውና መልኩ ግን ከአሌክሳንድራ ጋር ከተዋወቁበት ጊዜ አልተቀየረም:: አሌክሳንድራም በዚያን ጊዜ የሰላሳ አምስት ዓመት ቆንጆ ነበረች:: ትላልቅም አረንጓዴ ዓይኖቿና ወርቃማው ፀጉሯ የተለየ ውበት ያላብሷት ነበረ::

"ለእራት እንግዶች መጋበዜን ነግሬሻለሁ:: እና ዝግጅቱ እንዴት ነው?" አላት ሄነሪ እርግጠኛ ሸመሆን ሲል::

"እንደተለመደው ስለሚሆን አታስብ" አለችው አሌክሳንድራ::

"ነገ ደግሞ አዲሱን የመከላከያ ሚኒስቴርና የቅርብ ጓደኞቹን ስለምጋብዝ ሁሉም ነገር የተሟላ እንዲሆን" አላት:: ሄነሪ የአንድ ባንክ ሥራ አስኪያጅ ቢሆንም በዚያ በቃኝ ብሎ የሚኖር ሰው አልነበረም:: ለራሱም ሆነ ለአሌክሳንድራ ክብር ሲል ወደ ፖለቲካው ዓለም ለመግባት ምኞት ካደረበት ውሎ አድሯል:: ለዚህም ነበረ ከትላልቅ ባለስልጣኖች ጋር የሚቀራረበው::

"አልነገርኩህም እንጂ ነገ በምሳ ሰዓት ከእናቴ ጋር ለመገናኘት ተቀጣጥረናል:: ቢሆንም ለሰራተኞች መመሪያ ለጥቻቸው ስለምሄድ ችግር አይኖርም" ብላ ቀና አለችና አየችው:: ፊቱ ከመቅፅበት ሲለዋወጥ ይታያል:: ከአሜሪካዊ እናቷ ጋር አሌክሳንድራ አዘውትራ እንድትገናኝ አይፈልግም ነበረ::

በዚያን ጊዜ ማሪና አክሴል እየተሯሯጡ ገቡ:: ገና ከትምህርት ቤት ተለቀው መመለሳቸው ነበረ:: ሁለቱም ተራ በተራ ከአሌክሳንድራ አንገት ላይ ተጠምጥመው ጉንጮቿን ከሳሙ በኋላ ለአባታቸው በአክብሮት እጅ ነስተውት ቆሙ:: እርሱም እንደ ህፃን ሲያቀብጣቸው አይፈልግም:: በመጠኑም ቢሆን የምትዳፈረው ትንሿ አክሴል ነበረች::

"አክሴል ትምህርትሽን በደንብ እየተከታተልሽ ነው?" አላት አባቷ ቁልቁል እያያት:: የማሪ ሰውነት ሽምቅቅ ሲል አሌክሳንድራ አይታለች:: ማሪ ዕድሜዋ አስራ ሁለት ቢሆንም አስተሳሰቧ እንደ አዋቂ ነበረ:: በተለይም ረጅም ጥቁር ፀጉሯን፣ ትላልቅ አረንጓዴ ዓይኖቿንና ሽንቃጣ ቅርጿን ባየቻቸው ቁጥር የአሌክሳንድራን ልብ እንደመርፌ ጠቅ የሚያደ ርገው አንዳች ነገር ነበረ:: አሌክሳንድራ ምክንያቱን ለይታ ለመናገር ያቅታት እንጂ ማሪን የምትመስል ሌላ ልጃገረድ በዓይኗ ላይ ውልብ ብላ ትጠፋባታለች:: ነገሩንም ወዲያው ትረሳዋለች:: ትንሿ አክሴል ግን





በፀጉሯም፣ በመልኳም፣ በአነጋገሯም ቁርጥ እናቷን ነበረች:: ከፊት ለፊት የቆመውን አባቷን አንጋጣ እያየች "ዛሬ እኮ አልተማርኩም:: እክፍል ውስጥ በመረበሼ አስተማሪዋ አስወጥታኝ ነው የዋልኩት" አለችና ሳቀች:: ማሪ ግን አክሴል የሰራችውን ታውቅ ነበረና ስለ ትንሽ እህቷ እፍረት ተሰምቷት አቀረቀረች::

"ምን አድርገሽ ነው የረበሽው?" አለ ሄነሪ ኮስተር ብሎ አክሴልን እያያት::

"አስተማሪዋ ብላክ ቦርድ ላይ ስትፅፍ እኔ መስቲካ አኘክ ነበረ:: በኋላም እነፋዋለሁ ስል ፈነዳ"

"አስተማሪዋ ደነገጠችና ከክፍል አስወጣችሽ ማለት ነው?"

"መደንገጥ ነው? ቸኩ እጇ ላይ ተሰበረ" አለችና የልጅነቷን ሳቀች::

"ዳግመኛ እንዳይደገም! አንቺ በእናትሽም በአባትሽም የመሳፍንት ዘር ሆነሽ ሳለ የዱርዬ ባህርይ ማሳየት የለብሽም" አለና ማስጠንቀቂያ ሰጣት:: ለማሪ ግን ምንም ዓይነት ጥያቄ አላቀረበላትም:: ማሪ ትጉህ፣ ብልህና አስተዋይ ልጅ በመሆኗ ይኮራባታል:: አሌክሳንድራም ብትሆን ለማሪ አንጀቷ የሚላወሰበት በዚህ ልዩ ተሰጥዎ የተነሳ ይሁን ወይንም በሌላ ምክንያት ግለፅ አልሆን እያላት ከትንሿ ልጇ ትልቋን አስበልጣ በመውደዷ ትገረም ነበረ::

በማግስቱ በምሳ ሰዓት ላይ አሌክሳንድራ እናቷን ለመጠየቅ ከፓሪስ ከተማ ውጪ ወደሚገኘው የገጠር መኖሪያ ቤት ሄደች:: ያ ቤት አሌክሳንድራ ያደገችበት ቤት ነበረ:: ስለዚህም ባየችው ቁጥር የአባቷን የኮምት ደ.ቦርን ትዝታ ይቀሰቅስባታል:: የሴትሮይን መኪናዋን በር የከፈተላት ሹፌሩ ሳይሆን ነባርና ያሳደጋት የምድረ ግቢው ኃላፊ ነበረ:: አሌክሳንድራ ለቤት ሰራተኞች ተራ በተራ ሰላምታ ከሰጠች በኋላ የእናቷ ክፍል ወደሚገኝበት ወደ አንደኛው ፎቅ ወጣች:: ከእናቷም ጋር ተገናኝተው ተቃቅፈው ከተሳ ሳሙ በኋላ ማርጋሬት አሌክሳንድራን ራቅ አድርጋ በመያዝ ልብሷን ስታይ ቆየችና "ማነው የሞተው?" ስትል ጠየቀቻት::

አሌክሳንድራ እንደመደንገጥ ብላ "ምነው እማማ ለምንድነው እንዲህ ብለሽ የጠየቅሺኝ?" አለቻት::

"አለባበስሽ! አለባበስሽ ነዋ ይህን ለማለት ያበቃኝ" አለቻት ማርጋሬት::

“ምን ወጣው አለባበሴ? ሄነሪ ነው መርጦ የገዛልኝ:: ያውም ከዱዋር የልብስ መደብር” አለች አሌክሳንድራ ፈገግ እያለች::

“ይህን የሐዘንተኛ ልብስ የመሰለ? እንዲህ አድርጉም ምርጫ የለም!” አለች እናትየዋ በትዝብት ራሷን እየነቀነቀች:: የማርጋሬት ምርጫ ብሩህ ቀለም ላላቸው ልብሶች ነው:: አሌክሳንድራ የለበሰችው ግን ወደ ጥቁር የሚወስደው ቀሚስና የቆዳ ኮት ነበረ::

“ሄነሪ እስከወደደው ድረስ ለእኔም ያምረኛል” አለቻትና ሳቀች:: አሌክሳንድራ ከባሏና ከልጆቿ ጋር በፈረንሳይኛ ብትናገርም አሁን ከእናቷ ጋር የምትጫወተው በእንግሊዘኛ ነበረ::

“ይህንንስ ማቃጠል ነበረ” አለችና ማርጋሬት ትንሽ ከተሳሳቁ በኋላ የአሌክሳንድራን ትከሻ ይዛ ወደ ምግብ ጠረጴዛው አመሩ:: ማዕድ ቀርቦ ከተመገቡ በኋላ የሚጠጡት ወይን ጠጅ መጣላቸው:: እየጠጡም እንዳሉ ማርጋሬት አሌክሳንድራን በፍቅር ዓይን ስታያት ቆየችና “ፀጉርሽን ጥቁር ቀለም እንዳትነክሪው ብዬ ስንት ጊዜ ነው የመከርኩሽ አሌክሳንድራ?” አለቻት::

“ምን ላድርግ እማማ? ሄነሪ እኮ ነው ጥቁር ቀለም ተቀቢው የሚለኝ:: ወርቃማ ፀጉር በቀላሉ ዓይን ይማርካል ይላል:: ስለዚህ የሴት ወይዘሮ ፀጉር ጥቁር መሆን አለበት የሚል እምነት አለው”

“አይ ሄነሪ! ...ምስኪን ሰው! ከዚህ ሁሉ ለምን ጥቁር ሰው ለራሽ ፀጉር ገዝቶልሽ አያርፍም? የአሁኑ ፀጉርሽ ቀለሙ እየለቀቀ በሄደ ቁጥር ወርቃማነቱ መታየቱ አይቀር! እኔ አንቺን ብሆን ኖሮ እግዚአብሔር የፈጠረልኝን ፀጉር አለውጥም ስል እምቢ ባልኩት ነበረ”

“እስቲ እንዳለው ይሁንለት እማዬ! በዚህ የሚደሰት ከሆነ በበኩሌ ግድ የለኝም” አለችና አሌክሳንድራ የወይን ጠጅ የያዘውን ብርጭቆ ወደ ከንፈሯ አስጠጋች:: ማርጋሬት አሌክሳንድራን ባገኘቻት ቁጥር ሄነሪን በነገር ነካ ነካ ሳታደርግባት አልፋ አታውቅም:: ሄነሪም ቢሆን ለማርጋሬት ያለው ጥላቻ የባሰ ነበረ:: ዕድል ሲያጋጥመው ብጥልጥሏን ያወጣዋል:: አሌክሳንድራ በዘዴ ልታቀራርባቸው ብዙ ብትሞክርም ባለመቻሏ ተሰፋ ቆርጣ ከተወችው ረጅም ጊዜ ሆኗል::

“እንዳንቺ እርሱም ጥሩ ሰው በሆነ!” አለችና ማርጋሬት ከሩቢ ወደ ተሰራው የጆሮ ጉትቻዋ እያመለከተች “ይህንንስ ወደድሽው? ገና ዛሬ ነው ያደረኩት” አለች::





“መውደድ ነው? እንዴት መሰለሽ ያማረብሽ! መቼም ይህን ጊዜ ዋጋው ...”

“ከመቶ ሺህ ትንሽ ነው የሚቀንሰው”

“ፍራንክ ነው ብር?”

“ትቀልጃለሽ? ብር! የአሜሪካ ብር!”

“አይ ያንቺ ነገር! ይህን ጊዜ አንድ ዕቅድ ቢኖርሽ ነው የገዛሺው” በሚቀጥለው ሳምንት ወደ አሜሪካ ሳልሄድ አልቀርም:: ክረምቱ ከመግባቱ በፊት ደርሼ የምመጣበት ጉዳይ አለኝ:: ከዚያም ወደ ሮምና ሳን ሬሞ የዱሮ ጓደኞቼን ለመጠየቅ እሄዳለሁ”

“ለምን ስትመለሺ እኛ ጋር ለጥቂት ሳምንታት አትቆይም?”

“ለአንቺ ደስ ቢልሽ ሄነሪን እንደሚከፋው አውቃለሁ”

“ለልጆቹ አሻንጉሊትና ሌላ ስጦታ እስካላመጣሽላቸው ቅር የሚለው አይመስለኝም” አለቻትና አሌክሳንድራ ሁለቱም እንባቸው እስከሚፈስ ተሳሳቁ:: ማርጋሬት ለትንሿ ለአክሴል ሲጫኑት የፊሽካ ድምፅ የሚያሰማ የላስቲክ አሻንጉሊት ገና የአራት ዓመት ልጅ እንዳለች አምጥታላት ነበረ:: አክሴል ጨዋታ ይመስላትና ላስቲኩን አባቷ ከሚቀመጥበት ሶፋ ኩሽን ስር ትደብቀዋለች:: በዚያን ቀን ሄነሪ ወደ ቤት የመጣው ከሚያከብረው አንድ ትልቅ እንግዳ ጋር ነበረ:: እንግዳውን እንዲቀመጥ ጋብዞ እርሱም አረፍ ሲል ሲል ከኩሽኑ ስር ያልተጠበቀ ድምፅ በመስማቱ ዘሎ ይነሳል:: ሌላም ነገር መስሎት ሳቡ እስከሚንቀረቀር ደንግጦ ነበረ:: አሜሪካዊቷን ማርጋሬት ረገማት:: ጨዋ ልጆቼን የምታባልጋቸው እርሷ ናት ሲልም ጥላቻው እየጨመረ ሄደ::

“ታዲያ ከኛ ጋር ለጥቂት ጊዜ እንደምትቆይ ፈቃደኛ መሆንሽን ለሄነሪ ልንገረው?” አለች አሌክሳንድራ::

“ለርሱ መንገር አይኖርብሽም:: ከጉዞዬ እንደተመለስኩ ሳይታሰብ አንዱን ቀን እመጣለሁ”

“እንደምትመጪ እኔ ሳልሆን ሄነሪ ቢያውቀው ጥሩ ነው:: አንቺ እንደምትገምቺውም እኮ ክፉ ሰው አይደለም”

“ክፉ ላይሆን ይችላል:: ግን ሲበዛ ጉረኛ ነው:: በአንቺ በሚስቱ ላይ ሳይቀር ሲንቀባረር ሳየው ደሜ ነው የሚፈላው”

"አይ እማማ! አብሮት የተፈጠረውን ባህሪ ምን ያድርገው ብለሽ ነው:: ቢሆንም እኔ ከልቤ አፈቅረዋለሁ:: ከርሱም የሚስተካከል አንድም ሰው የለኝም..." እየተባባሉ ሲያወሩ እንደ ልማዱ ሳይታወቃቸው ሰዓቱ በሮ ኖሮ አስር ሰዓት ተኩል ሆኗል:: አሌክሳንድራ ወደ ቤቷ ለመመለስ እየተቻኮለች ተነሳች::

"ዛሬም እንግዳ ይኖራችኋል ማለት ነው?" አለቻት ማርጋሬት አሌክሳንድራን በሐዘኔታ እያየች::

"አዎን! ዛሬም ነገም!" አለች አሌክሳንድራ::

"እኔ አንቺን ብሆን ኖሮ በግብዣው ላይ ከሰውነቴ የተጣበቀ ጂንስ ሱሪና እጅጌ ጉርድ ሸሚዝ ለብሼ በመውጣት የሚሆነውን አይ ነበረ" አለችና በተንኮል አመለካከት አሌክሳንድራን እያየች ሳቀች::

"አንቺ አታደርጊም አይባልም:: እማዬ! እኔ እኮ ለምን እንዳንቺ ደፋር መሆን እንደማልችል አይገባኝም?" አለች አሌክሳንድራ::

"ሄነሪን የመሰለ ባል አግብተሽ በየት? ለርሱ የምትገባው ልክ ልታስገባው የምትችል ሴት እንጂ እንደ አንቺ ንፁህና የዋህ አይደለችም:: ለማንኛውም ጥናቱን ይስጥሽ" አለቻት ማርጋሬት:: በዚያን ጊዜ ከቤት ወጥተው የአሌክሳንድራ ሲትሮይን መኪና ከቆመችበት ደርሰው ነበረ:: የምድረ ግቢውም አስተዳዳሪ የኋላ ጋቢናውን ከፍቶ አሌክሳንድራን ለማስገባት እየተጠባበቀ ነበረ:: አሌክሳንድራ ሁል ጊዜ እናቷን ለመጠየቅ ለትመጣ የምትደሰተውን ያህል ስትሰያት ታዝን ነበረ:: የምትወደው ባሏ ሄነሪና ልጆቿ ማሪና አክሴል ባይኖሩ ኖሮ አሌክሳንድራ ከፎሽ አውራ ጎዳና ገንጠል ብሎ በሚወስደው መንገድ ላይ ይገኝ ወደ ነበረው ህንፃ ተመልሳ ባልሄደች ነበረ::





# ምዕራፍ አስራ አንድ

ሂላሪ ፓተርሰንን ስለእህቶቿ ጠይቃው የሚያውቀው ምንም ነገር እንደሌለ ነግሯት ስታለቅስ ብትውልም በማግስቱ ወደ አዲሱ መስሪያ ቤቷ ሄዳ ነበረ:: ከመቼውም ጊዜ ይልቅ አሁን ሂላሪ ከቁርጥ ውሳኔ ላይ ደርሳለች:: ጋዜጠኛ መሆን አለባት:: ያውም ዕውቅ ጋዜጠኛ! ሙያውም በሚያቀዳጃት ዕድል በመጠቀም የአባቷንና የእናቷን የህይወት ታሪክ የሚያውቋቸውን ሰዎችና ስለነርሱም በየጊዜው በመፅሔቶችና ጋዜጦች ላይ ከተፃፉ አስተያየቶች በማሰባሰብ አንድ መፅሐፍ ለማዘጋጀት አቅዳለች:: እስከአሁን የነበራት ተስፋ እህቶቿን አገኛለሁ የሚለው ጉጉት ነበረ:: ከእንግዲህ የአሌክሳንድራና የሚጋን ነገር አከተመለት:: ሂላሪ በህይወት ለመቆየት ሌላ ነገር ማለም ነበረባት:: ስለዚህም የወላጆቿን ታሪክ ለማሰባሰብ በማቀዷ ከስሞ የነበረው ተስፋዋ ለመለመ::

የእህቶቿ ነገር ሙሉ በሙሉ ከልቧ ባለመውጣቱ አልፎ አልፎ እንደቁስል ቢጠዘጥዛትም በስራዋ ላይ ታታሪ ነበረች:: ማታ ማታም የኮሌጅ ትምህርት መከታተል ጀመረች:: ሂላሪ እንደሌሎቹ የኒውዮርክ ልጃገረዶች ሳቂታ፣ ቀልቃላ አልነበረችም:: ከትላልቅ አረንጓዴ ዓይኖቿ የሚንፀባረቀው መልዕክት በዚያ በወጣትነት ዕድሜዋ የስቃይ ህይወት ያሳለፈች ለመሆኑ በግልፅ ይነበባል:: ሂላሪ በአነጋገሯ፣ በአረማመዷ ረጋ ያለች ልጅ ነበረች:: በአለባበሷም ጥንቁቅ ትሁን እንጂ እንደዘመኑ ልጃገረዶች ጭኖቿን የሚያሳዩ ቀሚሶች አንድም ቀን ለብሳ አታውቅም:: በአስተናባሪነት ሥራዋ እንግዶችን በትህትና ትቀበላለች:: በቅንነትም ታስተናግዳለች:: በአጭር ጊዜ ውስጥም በሁሉም ዘንድ ተወዳጅ ለመሆን በቃች ነበረ::

ከአንድ ዓመት በኋላ ወደነበራት ዋና ምኞት መንገድ ጠራጊ ዕድል አጋጠማት:: በአንድ ዜና አገልግሎት ድርጅት ውስጥ ክፍት የሥራ መደብ እንዳለ በጋዜጣ ላይ አየች:: ለርሷ የሥራ ልምድና የትምህርት ደረጃ ተመጣጣኝ የሆነ የሥራ መደብ ነበረ:: ደመወዙም አሁን ከሚከፈላት እጥፍ ይሆናል:: የቃለ መጠይቅ ፈተና አቅርባላት የነበረችው ሴት በሂላሪ ጠቅላላ ሁኔታ በመደሰቷ ቅድሚያ የመቀጠር

ዕድል እንድታገኝ አደረገቻት:: ከዚያ በኋላ ለሂላሪ ሁሉም ነገር እየቀለላት ሄደ:: ቀን ቀን በስራዋ ላይ ከምታገኘው ልምድ በተጨማሪ ማታ ማታ የኮሌጅ ትምህርቷን በትጋት ትከታተላለች:: ሙያዋን ለማዳበር ይረዳሉ የምትላቸውንም መፃህፍት ያለመሰልቸት ታነብ ነበረ:: የሥራ አፈፃፀሟ ከፍተኛ በመሆኑም በሁለት ዓመት ጊዜ የዜና ፕሮግራም ረዳት አዘጋጅ ለመሆን በቃች:: ደመወዟም የዚያኑ ያህል አድጐላት ነበረ:: ከሰባት ዓመት በኋላም ወደ ዋና አዘጋጅነት ደረጃ ተሸጋገረች:: ያን ጊዜ ሂላሪ የማስተሬት ዲግሪዋን አግኝታ ነበረ:: በሃያ አምስት ዓመት ዕድሜዋ ዋና አዘጋጅ ለመሆን የበቃችው ሂላሪ ለወደፊቱ ብሩህ ተስፋ እንደሚጠብቃት ግልፅ ነበረ:: በአነጋገሯ ቁጥብ፣ በሥራዋ ግን ቀልጣፋ በመሆኗ የበላይ ሹማምንቱ ሲወዷት በሌሎቹም ሰራተኞች ዘንድ ለመከበር በቅታለች:: ትርፍ ሰዓቷን ጭምር ለስራዋ መሥዋዕት በማድረጓ ለምሽት ዜናዎች ዋና አዘጋጅነት ማዕረግ ደርሳለች:: በሹመቷም ደስ ደስ ሳቢያ ነበረ የዜና አገልግሎት ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ ለራት የጋበዛት:: ብቸኛዋ ሂላሪ ጥቂት ስታመነታ ቆየች:: ግን ሥራ አስኪያጁ አፍ አውጥቶ ጠይቋታልና እምቢ ማለቱ መዘዝ ሊያስከትል እንደሚችል ተሰምቷት እሺ ለማለት ተገደደች::

ለመጀመሪያ ጊዜ ወንድ ለግብዣ ይዟት ሲወጣ ነው:: በብራስልስ ሆቴል ውስጥ ራት ከበሉ በኋላ ሻምፓኝ ቀረበላቸው:: በቅድሚያ ስለ ስራቸው ብዙ ሲወያዩ ቆዩ:: ድርጅቱንም ለማጠናከር ምን ምን መደረግ እንዳለበት የየበኩላቸውን አስተያየትም ተለዋወጡ:: በመጨረሻም ላይ ነበረ ሥራ አስኪያጁ አዳም ኬን ሂላሪን ስለወደፊት ዕቅዷ የጠየቃት::

"ዋና ስራ አስኪያጅ መሆን ቢያቅተኝ ቢያንስ ምክትል ሥራ አስኪያጅ የምሆንበት ቀን ይመጣል" ስትል ምኞቷን ሳትደብቅ ነገረችው:: ኬን በሂላሪ ግልፅነትና ልበ ሙሉነት ሳይደሰት ባይቀርም "ግን ለምን በኃላፊነት ደረጃ ለመስራት ትፈልጊያለሽ?" ሲል ጠየቃት:: የሚያምሩ የነበሩት የኬን ቡናማ ዓይኖች ለሂላሪ የነበራቸው አመለካከት የፍቅር ነበረ:: ሂላሪ ቆንጆ፣ ወጣትና ኮስታራ ልጅ ናት:: እንደ ዕድሜዋ ከሆነም አፍላ የመቃበጫ ጊዜዋ ነበረ:: እርሷ ግን ብቸኛ ናት:: በህሊናዋ የማይፋቅ አሳዛኝ ነገር እንደ ደረሰባት አዳም ኬን በቀላሉ ለመረዳት ችሏል:: ከንግግሯ ደግሞ ዓለማዊ ምኞት እንዳለት ተገንዝቧል:: ሁለት ህፃናት ልጆች የወለደችለትንና በቅርቡ የፈታት ሚስቱን አስታወሰና "ሴቶች የቤት እመቤት ሆነው ልጆች እየወለዱ ከማሳደግና በሰላም ከመኖር ይልቅ የቢሮን ሥራን መረጡ:: ጊዜው ለወጣቸው ልበል?" ሲል ሂላሪን እያየ ተናገረ::





የኬን አነጋገር ሂላሪንም በቀጥታ የሚመለከት ነበረ:: ፈገግ አለችና በአእምሮዋ ነገር ስታመላልስ ቆየች:: ስለወደፊት ዓላማዋ ጠይቋት ለኬን የሰጠችው መልስ ግልፅ ያለ ነበረ:: በመሆኑም እስከዚያ ድረስ በልቧ የምታስበውን እፍረጥርጣ በመናገሯ አልተፀፀተችም:: ከፊት ለፊቷ ተቀምጦ ያጫውታት የነበረው ኬን ጥሩ ሰው መሆኑን ታውቅ ነበረና ልትደብቀው አልፈለገችም:: ሂላሪም ከሐሳቧ ተመለሰችና "ለአንዳንዶቻችን ከጋብቻ ይልቅ ቢሮው ሳይሻለን አይቀርም" አለችው:: አእምሮዋን ለአስራ ሰባት ዓመታት ሲበጠብጠው ከቆየው ስቃይ ሂላሪ አሁንም ሙሉ ለሙሉ አልተላቀቀችም:: ህሊናዋ ከማሰብ፣ ከመጨነቅ እፎይታ የሚያገኘው በሥራ ስትጠመድ ብቻ ነው:: ይህንን ችግሯን ደግሞ ለአንድም ሰው ቢሆን አላካፈለችም:: ሂላሪ ብቸኛ ነበረች::

ኬን ሂላሪን ዝም ብሎ ሲያያት ቆየ:: በሆዱ አዘነላትም:: በሰላሳ ስምንት ዓመት ዕድሜው ውስጥ ብዙ ነገሮች አይቷል:: ማፍቀርና መፈቀርም ምን ማለት እንደሆነ ያውቃል:: ልቡ ተሰቅሎላት የነበረችውን ልጃገረድ ያገባው በሃያ ሶስት ዓመቱ ነው::

"ትዳር ይዘሽ ልጅ የመውለድ ዕቅድ የለሽማ?" አላት ኬን::

ሂላሪ ራሷን በአሉታ አወዛወዘች:: የምሯንም "ባልም ልጅም አልፈልግም" ስትል መለሰችለት:: እንደዚያ ለማለት ሂላሪ የግሏ ምክንያት ነበራት:: ከምታፈቅራት እናቷ ከሶላንጅ፣ ከምትወደው አባቷ ከምክር፣ እንጀቷ ከሚንሰፈሰፍላቸው እህቶቿ ከአክሲና ከሚጋን ለዘለዓለም ተቆራርጣለች:: ከእንግዲህ ግን ዳግመኛ አፍቅራ፣ ከምታፈቅረው ለመለየት አትፈልግም:: እርሷም ልጅ ወልዳ እንደ ሁለቱ ትንንሽ እህቶቿና እንደርሷ እንዲሰቃዩ አትሻም:: ብቸኝነቷን መርጣለች:: ያለጥርጥር የሚያዋጣትም የአሁኑ ኑሮዋ እንደሆነ ታውቀዋለች:: ኬንን አየት አደረገችው:: እንደ ዓይኖቹ ፀጉሩም ቡናማ ነበረ:: ቁመናውና መልኩም ማራኪ ነው:: ሂላሪ ያለልማዷ አንድ ነገር አሰበች:: 'ኬን ከደረቱ አስጠግቶ ቢያቅፈኝ ምን ይሰማኝ ይሆን?' ስትል ለራሷ ጥያቄ አቀረበች:: እንደዚያ ያሳሰባት ሳይታወቃት ያንን ሻምፓኝ ደጋግማ ይሆን? ወይንስ ...

"ለእኔ በዓለም ውስጥ እንደልጆቼ ደስታ የሚሰጠኝ ምንም ነገር የለም:: ስለዚህ ልጅን በተመለከተ የተሳሳተ አስተያየት እንዳይኖርሽ" አላት ኬን:: አልልልሽ ብሏት ነው እንጂ ለዚህማ እርሷስ አክሲና ሚጋንን የመሳሰሉ 'ልጆች' እንዴ አልነበሯትም:: እንደ እናት የሚያይዋትን እነኛን ህፃናት በጉልበት ነጠቋት:: እና ይህንን ምስጢሯን ለአንድም ሰው ቢሆን

ሳስመናገር ቆርጣለች:: ኬን ሳቀረበላት ምክር አስተያየቷን ሰመስጠት ብቻ ስትል ግን "ልጅ ካልወለዱ በስተቀር ህይወት ምሉዕነት አይኖራትም የሚል አስተሳሰብ ለምን አንዳንድ ሰዎች ይኖራቸዋል?" አለችው::

"ላነሳሽው ጥያቄ ምናልባት በአሁኑ ዕደሜሽ መልስ ላትሰጪበት ትችይ ይሆናል:: ግን ሂላሪ ከአስር ከአስራ አምስት ዓመት በኋላ ምን ማለት እንደሆነ ይገባሻል:: ያን ጊዜም አጅብቀሽ ታዝኚያለሽ:: ልጅ መውለድ በልጅነት ነው" አለና ዓይን ዓይኖቿን እያየ "ለምን ባል አታገቢም?" ሲል በድጋሚ ጠየቃት::

"ገና ሃያ አምስት ዓመቴ ነው:: ለትዳር መቸኮል የለብኝም" አለችው ሳቅ ብላ:.

"እኔ በስንት ዓመት ዕድሜዬ እንዳገባሁ ታውቂያለሽ? በሃያ ሶስት ዓመቴ ነው ያገባሁት:: ሚስቴ ደግሞ አስራ ዘጠኝ ዓመቷ ነበረ:: ያን ጊዜ በጣም እንፋቀር ነበረ:: ማለትም ከአስራ አምስት ዓመት በፊት:: ከዚያን ወዲህ ግን ብዙ ነገሮች ተለዋወጡ:: እኛ በተጋባንበት ዘመን አንቺ ህፃን ነበርሽ" አለና ቀጠል በማድረግ "ያኔ ኒውዮርክ ውስጥ ነበርሽ ወይንስ ሌላ ከተማ?" ሲል ጠየቃት::

ሂላሪ የዓይን ቅንድቦቿን ከደን አድርጋ ጊዜውን አሰላች:: ከዛሬ አስራ አምስት ዓመት በፊት... አዎን! በቦስቶን ከተማ ከአክስቷ ከኢሊንና ከጆንስ ጋር ነበረች:: አክሲንና ሚጋንን ፓተርሰን ወለዷቸው ሌት ተቀን እንዳስታወሰቻቸውና ዕንባዋን እንዳፈሰሰችው የምትውልበት ጊዜ ነበረ:: አሁንም በዓይኗ ግጥም ያለውን ዕንባዋን ዋጠችና ገርበብ ያሉ ዓይኖቿን ከተፈች:: ኬን በሰውነቷ መለዋወጥ እንዳይነቃባት ፈገግ አለችና "አ! በዚያን ጊዜ በቦስቶን ከተማ ከአክስቴ ጋር ነበረ የምኖረው አለችው::

"ወላጆችሽስ?" አላት ኬን::

"ወላጆቼ እንኳን... እነርሱስ የዘጠኝ ዓመት ልጅ እንዳለሁ ነበር የሞቱት"

"በአንድ ጊዜ ነው የሞቱት?"

በአዎንታ ራሷን ጉንበስ አደረገች:: ሂላሪ ሥለ ስራ ጉዳይ እንድትወያይ እንጂ ስለቤተሰቦቿ ትዝታ ለማውራት አልፈለ ገችም::

ኬን ግን "በአደጋ ነው?" ሲል ጠየቃት:: ሂላሪ አሁንም ራሷን





ጉንበስ አደረገችና ሙሉውን ብርጭቆ ሻምፓኝ በአንድ ትንፋሽ ጨለጠችው::

"አንቺን ብቻ ነበር የወለዱት?" አላት አሁንም ኬን ሂላሪ ዓይኖቿን እንዳያያቸው ሰበር አደረገችና "አዎን" አለችው::

"በጣም የሚያሳዝን ነው" አለና ኬን አቀረቀረ:: ሂላሪ ግን ኬንም ሆነ ሌላ ማንም ሰው እንዲያዝንላት አትፈልገም:: ስለዚህ ኬንን ከስፈነበት ትካዜ ለማውጣት ሞቅ ያለ ፈገግታ አሳየችውና "ሥራዬን በጣም የምወደው ለዚህ ነው:: ዘመድ አዝማዴ ሥራዬ ብቻ ነው" አለችው::

ኬን ሳይታወቀው እጇን ጨበጥ አደረገና "ዛሬ ለራት አብረን በመውጣታችን የተሰማኝ ደስታ ከፍ ያለ ነው:: ላነጋግርሽም ከፈለኩኝ ብዙ ጊዜ ሆኖኝ ነበረ:: ለሥራሽ ባለሽ ፍቅር ድርጅታችን ይኮራብሻል" አላት::

"ሰባት ዓመት ለቆየሁበት ድርጅት ከአሁኑም የበለጠ አስተዋፅኦ ለማድረግ ብችል ምን ያህል ደስ ባለኝ" አለች ሂላሪ:: እዚህ ላይ ሂላሪ እውነት አላት:: ማን ነበረ ሂላሪ በአንድ ዝነኛ ዜና አገልግሎት ድርጅት ውስጥ ለኃላፊነት ልትደርስ ትበቃለች ብሎ የገመተ? ወደ ቦስቶን የወሰዳት ፓተርሰን... ኢሊን... ጆንስ... የመጠለያ ቤቷ ሉዊዝ... የጃክሰንቪል ከተማ ጠባይ ማረሚያ ተቋም መምህራን ...

"በዚሁ ድርጅት ውስጥ ትቆያለሽ ስል እገምታለሁ::"

"እኔም እገምታለሁ ሌላ ስራ ምን ያደርግልኛል?"

"አይ! በዚህ ሙያ ላይ የተሰማሩ ሰዎች ብዙ ጊዜ የተሻለ ዕድል እያገኙ ሲለቁ በማየቴ ነው"

ሂላሪ ራሷን ስታወዛውዝ ቆየችና "እኔ ግን የትም አልሄድም:: ልቤ የሚመኘው በዚሁ ድርጅት ውስጥ ማደግ ነው" አለችው::

"ለምን?" አላት ኬን ለሥልጣን መጓጓቷ እየገረመው:: ኬን ራሱ ባለስልጣን ነው:: ሥራውን እጅግ አክባሪ ነው:: ግን በአገልግሎቱ ለማዕረግ በቃ እንጂ የሥልጣን ጉጉት አልነበረውም:: ስለዚህም በወጣቷና በውቧ ሂላሪ የሥልጣን ጥም ግራ ሳይጋባ አልቀረም::

"ምክንያቱም ለእኔ ሥልጣን ማግኘት በጣም ስለሚያስፈልገኝ ነው:: ከዚያ በኋላ ብቻ ነው በራሴ ለመተማመን የምችለው:: እንደልቤም እንቅልፍ የሚወስደኝ"

"ስለወደፊቱ እርግጠኛ ሆነሽ መናገር አትችይም:: ከሥራ መባረር ሊኖር ይችላል::"

ሂላሪ ፈገግ አለችና "እንደማልባረር እርግጠኛ ነኝ" አለችው::

እንደሂላሪ ልበ ሙሉ የሆነች ሴት ኬንን አጋጥሞት አያውቅም፤ በቆራጥነቷም አደነቃት:: አፓርትማዋ በር ድረስ ሸኘቷት ነበረ:: ወደ ውስጥ እንዲዘልቅ ትጋብዘኛለች የሚል ተስፋ ነበረው:: ሂላሪ ግን እጁን ጨብጣው ገባች:: እቤቱ እስኪደርስ ድረስ ልቡ እንደተሰቀለላት ነበረ:: ብትታዘብም ተታዘበው እንጂ ስልክ ደውሎ ማነጋገር ነበረበት:: ደወለላትም::

"ይቅርታ አድርጊልኝ ሂላሪ አብረሽኝ ስላሳለፍሽው ምሽት ላመስግንሽ ነው የደወልኩት:: ከእንቅልፍሽም ቀስቅሼሽ ከሆነ ወድጄ አይደለም" አላት ኬን በሚርገበገብ ድምፅ:: በውበቷ ለመጠመዱ ጥርጥር የለውም::

ሂላሪ ሳቅ አለችና "እኔም ላመስግንህ ይገባል:: ግን ሚስተር ኬን፤ አንድ ነገር ልንገርህ:: እንደ አሁኑ በስራ ላይ እንዳለሁ እንዳትደውል ልልኝ:: በሌላ ሰው የተነሳ ከስራዬ ለመባረር አልፈልግም" አለችው ደስ በሚል ድምጿ::

"ገባኝ! ገባኝ" እርሱም ሳቅ ካለ በኋላ "ከሰኞው አንዱን ቀን ምሳ እንድጋብዝሽ ብትፈቅጅልኝ?" አላት::

"ስራ ካልበዛብኝ እሺ" አለችው::

"ነገ ብጋብዝሽ?"

እንደገና ሳቅ አለችና "ጥድፊያው ለምንድን ነው? እኔ እንደሆን ከዚያ ድርጅት እንደማለቅ ነግሬሀለሁ" አለችው::

"ጥድፊያውማ ትዕግስት ሊኖረኝ ባለመቻሉ ነው:: ስለዚህ አንድም ቀን ሕይወት ነውና ልክ ስድስት ሰዓት ከሩብ ላይ ቢሮሽ ድረስ እመጣለሁ እሺ?" የኬን አነጋገር እንደጎረምሳ ነበረ:: ሂላሪም ልቧን እየተጠራጠረችው ነበረ:: አንድ የነካት ነገር እንዳለ በግልጽ ይሰማታል:: ወደኒዮርክ ከመጣችበት ጊዜ ጀምሮ እንደዛ ያለ ስሜት ሲሰማት ያን ቀን የመጀመሪያዋ ጊዜ ነው:: ኬን ዓመለ ጥሩ ብቻ ሳይሆን ያማረ ቁመና ነበረው:: ለሁለት





ለሦስት ቀን ብቻ ግብዣውን ለመቀበል ወሰነች:: ዝም ብላው በመቆየቷ "እሺ?" ሲል ኬን ዳግመኛ ጠየቃት::

"እሺ" አለችው::

በማግስቱ ከቢሮዋ ስትገባ አንድ ቀይ ጽጌረዳ ከጠረጴዛዋ ላይ ተቀምጦ ነበረ:: በዚያንም ቀን ምሳቸውን በአካባቢው ይገኝ በነበረ ሆቴል ቢመገቡም ሂላሪ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ከሩብ ድረስ ወደ ቢሮዋ አልተመለሰችም ነበረ::

ራሷን ዞር በማድረግ ረጅም ጥቁር ጸጉሯን ትከሻዋ ላይ ወርወር አድርጋ ከተቀመጠችበት እየተነሳች "በጣም የሚያሳዝን ነው:: እድገት ባገኘሁኝ በማግስቱ የስራ ሰዓት ማሳለፍ ጀመርኩኝ:: ባንተ የተነሳ ከስራ ሳልባረር አልቀርም ስል ሰጋሁ" አለች ሂላሪ::

"በሆነማ ያን ጊዜ ላግባሽ ብልሽ እሺ ትይኝ ይሆናል:: ከዛም ከከተማው ውጪ ሰፊ ቤት እንከራያለን:: አሥር ልጆችም ትወልጂልኛለሽ"

"አይበለው!" አለችና ዝም አለች:: ኬን ሁኔታዋን አጠና:: ሂላሪ ዙሪያዋን በግንብ የታጠረች ፅጌረዳ መስላ ታየችው:: ከፅጌረዳዋ ለመድረስ ግንቡን መውጣት አለበት:: ለዛውስ ሂላሪ ትፍቅድለት ይሆን? ደጋግሞ መሞከር ነበረበት::

ኬን ለምሳ ወይም ለእራት እንውጣ ባላት ቁጥር እምቢ ልትለው አልቻለችም:: ፍርሐት ቢሰማትም ከኬን ጋር መጫወቱን ትወደው ነበረ:: ባየችውም ቁጥር ሌላ ማንም ወንድ አሳድሮባት የማያውቀው ስሜት ሰውነቷን ይወረዋል:: በዚያ ላይ ደግሞ አለቃዋ መሆኑ ይሰማታል::

አንድ ቀን ራት በልተው ከአዲሱ አፓርታማዋ ድረስ ሊሸኛት በመንዝ ላይ እንዳሉ "መቼ ነው ሂላሪ እኔና አንቺ ልብ ለልብ የምንቀራረበው?" ሲል ጠየቃት:: በከንዶቹ ሲያቅፋት፣ ከደረቱ ላይ ለያስተኛት፣ እነኛን ትላልቅ አረንጓዴ ዓይኖቿን ሲስማቸው፣ ረጅም ጥቁር ፀጉሯን የምታጥብበትን ሎሽን ከአፍንጫው አስጠግቶ ሲያሸተው ከተመኘ ሳምንታት አልፈዋል::

"ከዚያ በላይ ምን እንቀራረብ?" አለችው ሂላሪ አንገቷን ሰበር አድርጋ::

"እንዳቅፍሽ፣ እንድስምሽ የምትፈቅጂልኝ ማለቴ ነው::

"ይህማ ጥሩ አይሆንም:: በአንድ ድርጅት ውስጥ እየሰራን ሌላ ግንኙነት ሊኖረን አይገባም:: በዚያ ላይ ደግሞ አለቃዬ መሆንህን ሁለታችንም መዘንጋት የለብንም" አለችው::

ኬን በዚያ ጊዜ ፈገግ አለና "ከእንግዲህ የእኔ አልቅና ለሁለት ሳምንት ብቻ ነው የሚቆየው:: ኒውጀርሲ ውስጥ የትልቅ ኩባንያ ስራ አስኪያጅ እንድሆን በዛሬው ቀን ቴሌግራም ደርሶኛል" አላት::

"የምትደለትበት ስራ ይመስልሀል?" ስትል ጠየቀችው:: ሂላሪ ለኬን ደህንነት ከአሁኑ ማሰብ ጀምራ ነበረ::

"ደመወዙ በጣም ከፍተኛ ነው:: ስራውንም እወደዋለሁ ስል እገምታለሁ:: ቅር የሚለኝ ነገር ቢኖር ካንቺ መለየቱ ነው:: ማለቴ ጥሩ መኖሪያ ቤት እስከማገኝና አንቺን እስከምወስድሽ"

ሂላሪ የስራዋ ጉዳይ አይሆንላትም:: በተለይም ደግሞ በዚያ ሙያ ላይ የተሰማራችው ለአንድ ቁርጠኛ ዓላማ ነበረ:: ስለዚህ ወደ ኒውጀርሲ ለመሄድ ፍቃደኛ መሆን አለመሆኗን ሳትገልፅ ዝም ማለቱን መረጠች::

"እውነቴን እኮ ነው:: እንደ ግማሽ አካሌ ነው የምቆጥርሽ" አላትና ፈገግ አለ:: ዕድሜው ሰላሳ ስምንት ነው ቢባልም ከሰላሳ ዓመት የሚበልጠው አይመስልም ነበረ::

"ኬን! በቅድሚያ ማንነቴን እንኳን አታውቀውም:: አየህ እኔ ...ላፋም ኡዝ የቢር..." የመጨረሻዎቹ ቃላት ሳታውቀው ነበር ያመለጧት::

"አሁን ያልሽው ምንድነው?"

"ፈረንሳይኛ ነው" አለች ሂላሪ:: ከእናቷ የወረሰችውን ቋንቋ ላለመርሳት የፈረንሳይኛ መፅሐፍ በብዛት ታነብ ነበረ:: "ባለ አረንጓዴ ዓይኖቿ ሴት" ማለት ነው ስትል ተረጎመችለት::

"ፈረንሳይኛ እንዴት ለማወቅ ቻልሽ?" ሂላሪ በአነጋገሯ ቁጥብ ሆነችበት እንጂ ኬን ስለ እርሷ ማናቸውንም ነገር ለማወቅ ይፈልጋል::

"ከብዙ ዓመታት በፊት እነጋገርበት ነበረ ... ትንሽ ልጅ ሆኜ:: እንዳይረሳኝም የፈረንሳይኛ መፃህፍት አነባለሁ::"

"ወላጆችሽ ፈረንሳይኛ ተናጋሪ ነበሩ?" እውነቱን የነገረችው እንደሆነ በነገር ነገር ታሪኳን ሊያውጣጣት ነው:: እርሷ ደግሞ ሚስጥሯን ለመደበቅ ትፈልጋለች::





"አልነበሩም:: ከህፃንነቴ ጀምሮ ቋንቋውን ስለተማርኩት ነው"

ያመናት ይመስላል፤ ሌላ ጥያቄ አላቀረበላትም ነበረ:: ከአፓርታማዋ እንደደረሱ ባትጋብዘውም ተከትሏት ገባ:: ጐን ለጐን ከሶፋ ላይ ተቀምጠው ለስላሳ ሙዚቃ እያዳመጡ ወይን ሲጠጡ ቆዩ:: ሳይታወቃቸውም እኩለ ሌሊት አልፎ ነበረ:: ኬን ሰዓቱን አየና ከተቀመጠበት በትካዜ ተነሳ:: ሂላሪንም ቁልቁል እየተመለከተ ፈገግ አለና ሲፈራ ሲቸር "እባክሽን የሌላ አታስመስይብኛና ሌሊቱን አብረን ብናሳልፍስ ሂላሪ?" ሲል ጠየቃት እንደማይሆን ለመግለፅ ራሷን አወዛወዘች::

"ለምን? ሌላ የምታፈቅሪው ሰው ይኖር ይሆን?"

አሁንም ራሷን አወዛወዘችና "ከወንድ ጋር ፍቅር ይዞኝ አያውቅም ደግሞም ወንድ ከነካኝ... ረጅም ጊዜ ... ብዙ ዓመታት..."

"ምነው? የተለየ ችግር አለብሽ?"

"ብዙ ችግሮች... ለመግለፅ የሚከብዱ ችግሮች..."

"እስቲ አንዳንዶቹን አንኳን ንገሪኝ?"

ሂላሪ አቀረቀረች:: ስላሳለፈችው ሕይወት ለማንም ላለመናገር ቆርጣለች:: ያንን ሕይወቷን ማንም ሊያውቀው አይገባም:: ዛሬ ሂላሪ የተለየች ሴት ናት:: ባለ ስራ ናት፣ የተከበረች ናት:: ያለፈው ትዝታዋ ነልፎ አልፎ ሰላም ቢነሳትም ለሌላ ሰው የሚነገር አልነበረም:: "አዝናለሁ ኬን ምንም ነገር ልነግርህ አልችልም" አለችው ቀና ብላ::

"ለምን?" አለና ጎንበስ ብሎ ሁለቱንም እጆቿን ያዛቸው:: ከዚያም ከፊቷ በርከክ ብሎ ዓይን ዓይኖቿን እያየ "የማትነግሪኝ ስለማታምኚኝ ነው?" ሲል ጠየቃት::

"ስለማላምንህ አይደለም" አለችና ከተንበረከከበት እንዲነሳ እርሷም ቆመች:: ዓይኖቿ እንባ በመቋጠራቸው እራሷን በራሷ ወቀሰች:: ፊቷን ዞር በማድረግ "ባንተ ላይ እምነት አጥቼ ሳይሆን ያለፈውን ላስታውሰው ስለማልሻ ነው" አለችው::

ኬን እጆቹን ትከሻዋ ላይ አድርጎ አስጠጋትና "ሂላሪ፤ ይህን በልብሽ ውስጥ አፍነሽ የያዝሽውን ጭንቀት አውጥተሽ ካልተናገርሽውና መፍትሔም ካልተፈለገለት ውስጥ ውስጡን ይጎዳሻል:: ጎበዝና ቆራጥ ልጅ መሆንሽን በስራሽ ላይ አይቼዋለሁ:: ስለዚህ ያለብሽን ችግር መናገሩ የሚከ

ብድሽ አይመስለኝም:: በዚህ የተነሳ ያንቺም የኔም ደስታ ሊጨልም አይገባውም:: ሕይወታችንም መበላሸት የለበትም»

“አይ ሕይወት! ሕይወት የጦር ሜዳ ናት!»

“ይህማ ሰራስ ተስፋ ቢስ ሆኖ ሌላውንም ተስፋ ማስቆረጥ ነው:: እንደኔ ደስተኛ ሕይወት ለመኖር ቋማንችልበት ምክንያት የለም» አላት ከልቡ:: ኬን ጨዋና የዋህ ሰው ነበረ:: በህይወቱም ያዘነበት ጊዜ ቢኖር ያለ ውድ በግዴታ ከሚስቱ ጋር በተለያየበት ወቅት ነው:: ከዚያ በተረፈ ሌላ ስቃይ ደርሶበት አያውቅም:: ዕድለኛም በመሆኑ ሂላሪ ቀንታበታለች:: «ጣዕም ያለው ሕይወት... እንደማር የጣፈጠ ኑሮ ለመኖር እንችላለን”

“ምናልባት አንተ ትችል ይሆናል:: ለኔ ግን አይመስለኝም:: ምን ዓይነት ሕይወት እንዳሳለፍኩ የማውቀው እኔ ነኝ”

“እንግዲውስ ያንን ያለፈውን ሁሉ ብትረሺው ምናለበት? ከዛሬ ከዚች ደቂቃ ጀምሮ አዲስ ሕይወት ለመኖር እባክሽን ሞክሪ” አላት ዓይን ዓይኗን እያየ::

“ከሆነልኝ እሞክራለሁ” አለችው እርግጠኛ ሳትሆን:: ያንጊዜም ከደረቱ ልጥፍ አደረጋትና ከንፈሮቿን በከንፈሮቹ ዳሰሳቸው:: ቀጠለና ሳማቸው፣ ገመጣቸው፣ ጎረሳቸው:: ልቡን አላስተነፍስ ያለውን የታመቀ ስሜት የሚገላገልበት ወቅት ደረሰ:: ሂላሪን ታቅፎ ከመኝታ ክፍሏ አገባት:: ከአልጋውም ላይ አስተኝቷት ልብሱን በጥድፊያ አወለቀ::

እስቲጨንቃት ቢያቅፋት፣ ትንፋሿ ቁርጥ እስኪል ቢስማት የሂላሪ ሰውነት እንደ በድን የቀዘቀዘ ነበረ:: ዓይኖቿን በኮርኒሱ ላይ ስክታ ሌላ ነገር ታሰላስል ነበረ እንጂ ከጭኖቿ መሀል ገብቶ በትኩሳት ይቃጠል የነበረውን ኬንን ረስታዋለች:: የሚታያት ሁሉ በጃክሰንቪል ከተማ በአንድ መጠለያ ቤት ውስጥ ሶስት ወንዶች ልጆች ያደረጓት ድርጊት ነው:: አሁንም ኬን በማድረግ ላይ ያለው ከልጆቹ ያልተለየ ነገር በመሆኑ ፍርሐት ወሯት ነበረ:: ኬን ስሜቱ ባይረካም ከላይዋ ላይ ወረደና፤ “ምን ሆንሽ ሂላሪ? አትወጂኝም ማለት ነው?” ሲል በመጨነቅ ጠየቃት::

“አዝናለሁ...” የሚለውን ቃል ብቻ በለሆሳስ ተናገረችና ፊቷን አዙራ ተኛች:: ምንጊዜም ከወንድ ጋር ብትተኛ ወሲባዊ ፍላጐቷ እንደማ ይቀሰቀስ ተሰማት:: ዕድሜዋ ሃያ አምስት ደርሷል:: እስከ ዛሬ የነበራት ስሜቷ ከእንግዲህ ወዲያ ሊቀሰቀስ ይችላል የሚል ግምት ከቶ በህሊናዋ አላደረም:: ስለዚህ ከተለያየው በደላቸው ጉን ለዚህም ያበቋትን ሰዎች





አሰበችና በሆዷ ተራገመች:: ፓተርሰን... ኢሲን... ጆንስ ... ህጓን የገሰሱት ልጆች ... ባሰመጠለያ ቤቷን ሉዊዝን... የጃክሰንቪል ጠባይ ማረሚያ ... በመጨረሻም ላይ እናቷን የገደለው አባቷ ... የእነኚህን ሁሉ ትዝታ በልቧ ተሸክማ ሂላሪ አቻዋ እንደሚሆኑ ሌሎች ሴቶች አልጋ ላይ ለመጫወት አልቻለችም::

ዞር ብላ ኬንን አየችውና “ስለማልወድህ እንዳይመስልህ:: ሌላ ችግር ስላለብኝ ነው” አለችው::

“ምን ዓይነት ችግር? ሂላሪ ልትነግሪኝ ይገባል” አለና ከአልጋው ጠርዝ ላይ እጆቹን አጣጥፎ ተቀመጠ:: ሂላሪ ኬንን ልታሳዝነው አልፈለገችም:: ከሚያዝንባት ይልቅ ቢደነግጥም ሀቁን መንገሩን መረጠች:: “በጉልበት ነበር ህጌ የተገሰሰው...” አለችው:: ከተናገረችው ችግሯን ተረድቶ ሌላ ጥያቄ እንደማያነሳባት ተስፋ አድርጋ ነበረ::

“እንዴትና በማ?” አላት::

“ታሪኩ ረጅም ነው” ከየት ጀምራ እንደምትነግረው ግራ ገባት:: እንዴት ወደ መጠለያ ቤት ለመግባት እንደቻለች? ጆንስ ካልደፈርኩሽ ብሎ ነፍሷን እስክትስት እንደ ደበደባት? እነኛ ልጆች እንዴት እንደተጫወቱባት? የምትነግረውን አንዱንም የሚያምናት አልመሰላትም::

“ለመሆኑ መቼ ነው ይህ የተፈፀመው?”

“የአስራ ሶስት ዓመት ልጅ ሆኜ ከዚያ በኋላ ግን ወንድ አጠገቤ ደርሶ አይውቅም:: የመጀመሪያው አንተ ነህ”

“ክርስቶስን ሂላሪ ጥፋተኛ ነሽ! እኔ እንዲህ ያለ ችግር እንዳለብሽ እንዴት ለመጠርጠር እችላለሁ? ስለዚህ ቀደም ስትይ ልትነግሪኝ በተገባ ነበረ”

“እኔም ብሆን ከባድ ችግር መስሎ ስላልታየኝ ነው”

“ትቀልጃለሽ! ከአስራ ሁለት ዓመት በፊት ህግሽ ተገሶ እስከ ዛሬ ድረስ ወንድ አልደረሰብኝም ነው ያልሽኝ:: ለዚህን ያህል ጊዜ ያለ ወሲባዊ ፍላጐት መቆየት ችግር መስሎ ካልተሰማሽ ስህተተኛ ነሽ:: ለመሆኑ የስነ አእምሮ ጠበብቶችስ ምን አሉሽ?” ሲል ጠየቃት:: የኬን ግምት ሂላሪ የስነ አእምሮ ሐኪሞችን እንዳማከረች ነው:: ትንሽም ትልቅም ችግር የደረሰበት የሚሮጠው ወደነኛ ባለሙያዎች ነበረ:: እርሱም ቢሆን ከሚስቱ ጋር እንደተፋታ መፅናኛ ምክር የተለገሰው ከነኚሁ ሰዎች እንደ ነበረ ያስታውሳል::

“ማንንም አላነጋገርኩኝም” አለችና ከተኛችበት ተነስታ የሌሊት ልብሷን ለበሰች:: ኬን ሂላሪን ቅርጿን በማየቱ ፍላጐቱ እንደገና ታደሰበት:: እንደበረዶ የነጡ ባቶቿ፣ ሸንቃጣ ወገቧ፣ ሰፋ ያለ ዳሌዋ፣ ወሲባዊ ስሜቱን እንደእሳት አጫሩት:: ያም ሆኖ ኬን ራሱን ለመቆጣጠር ቻለ::

“ማንንም አላነጋገርኩኝም ስትይ ምን ማለትሽ ነው? ልጆቹ ከደፈሩሽ በኋላ እርዳታ እንዳገኘሽ እርግጠኛ ነኝ:: አይደለም እንዴ ሂላሪ?” ሳቅ አለችና “እርዳታ አላስፈልገኝም ነበረ” አለችው::

“እንደዛ እንደ አሻንጉሊት ተጫውተውብሽ እርዳታ አላስፈለገኝም ነበር እንዴት ትያለሽ?”

“እሺ ብፈልግም እርዳታ የሚያደርግልኝ ሰው ለማግኘት አልችልም ነበረ ብልህስ?”

“በዛን ጊዜ የነበርሽው የሰው ዘር በማይታይበት የስሜኑ ዋልታ እንደሆነ እንጂ የስነ እእምሮ ሐኪሞች በሽበሽ በሆኑበት አሜሪካ ውስጥ እያለሽ የሚረዳኝ አጣሁ ብትይኝ አላምንሽም” አላት ኬን አሰማወቁ እንጂ ሂላሪ በዚያን ጊዜ በሉዊዝ መጠለያ ቤት ነበረች:: በአነጋገሩም ስሜቷ በመነካቱ “እባክህን ኬን! ስለዚህ ማውራቱን ብንተወውና ሌላ ሌላ ነገር ብንጫወት:: ስላሰፈው ህይወቴ ባታነሳብኝ” አሰችው::

“ካልተናገሩ መድኃኒት አይገኝም:: ስለዚህ ሂላሪ እባክሽ አጫውቺኝ?”

“ሁሉንም ነገር ብንረሳውስ?” አለች ሂላሪ፣ ከፊቷ ላይ የሚነበበውን ስቃይ እንዳያይ ዘወር ብላ::

“ሁሉንም ነገር ስትይ የዛሬውንም ምሽት ጭምር ማሰትሽ ነው?” “አይደለም! ስላሰፈው ታሪኬ ባታስታውሰኝ ማሰቴ ነው”

“ሂላሪ ! በስራሽ ላይ ጎበዝ ልጅ መሆንሽን አውቃለሁ:: ስለዚህ ሰዚህ ችግርሽ ደግሞ መፍትሔ ለመሻት የምትፈሪበት ምክንያት አይኖርም”

“ቀናት እያሰፉ በሄዱ መጠን ችግሩም እየቀሰሰ ስለሚሄድልኝ ሌላ መፍትሔ የሚያስፈልገኝ አይመስለኝም”

“መሰለሽ? ይህ ችግር ከተፈጠረ ስንት ዓመታት አልፈዋል? አንቺ እንደነገርሽኝ አስራ ሁለት ዓመታት? እና ውሎ ስላደረ ከችግሩ ተላቀቅሽ? አልተላቀቅሽም! አሁኑኑ ሌላ መፍትሔ እስካልተገኘልሽ አርባም፣ ሃምሳም





ዓመት ቢሞላሽ ከእሁኑ ሂላሪነትሽ አትሰወጪም:: ስለዚህ እባክሽ ሂላሪ የምመክርሽን ተቀበይኝ” አሰና እጇን ስቦ ከጎኑ አስቀመጣት:: ከንፈሯን ሳመና ከአልጋው ላይ አጋድሟት ከበላይዋ ሆነ:: ሂላሪን የሚያደርጋት ጠፋው:: ነፍሷ ብቻ ሳይሆን አካሏም የርሱ መሆን ነበረበት... ሁለመናዋ ... እንዲያፈቅረው እንዲወደው:: ደስ ብሏት አላዩ ላይ እንድትንጠለጠል፣ ትንፋሿ እንዲሞቀው... የልብ ትርታዋ እንዲሰማው ጉጉቱን ልታሟላለት እንደማትችል ለሂላሪ ይታወቃታል:: በፍቅር የምትሰጠው ምንም ነገር የላትም:: ኬን ሊወዳትና ፍቅሩን ሊያካፍላት ይችላል:: እርሷ ግን ፍቅሯን እሚጣ ከሰጠች ቆይታሰች:: ሰእህቶቿ ሰአክሲና ለሚጋን አካፍላቸዋለች:: ከነርሰም ጋር አብሮ ከስሟል:: አሁን የነበራት ፍቅር ግን ለስራዋ ብቻ ነበረ::

ኬን ከላይዋ ላይ ሳይወርድ ቁልቁል እያያት “የታወቀ የስነ አእምሮ ሐኪም ፈልጌ እንድታነጋግሪው አደርጋለሁ” አላት:: ሐኪሙ ቢገኝም በማነጋገር ብቻ መፍትሔ የሚያገኝላት አልመሰላትም:: ምናልባት ናላዋን ኦፐራሲዮን አድርጎ አንጎሏን ከመረመረው ያን ጊዜ ፍንጭ ያገኝ ይሆናል:: በወሬ ሂላሪን አድናለሁ ማለት ግን ዘበት ነበረ:: ስለዚህም “አልፈልግም” አሰችው::

“ሰምን ሂላሪ?”

“ጊዜ ስሰሌሰኝ ነው”

“ዕድሜሽ ገና ሃያ አምስት ዓመት ነው:: እና ይህን የመሰሰውን ችግር ተሸክመሽ የተቀረውን ዕድሜሽን ልትገፊ?”

“የተላመድኩት ስሰሆነ አይከብደኝም”

“ታዲያ ይህንን ከመኖር ትቆጥሪዋለሽ?”

“ጊዜ ስጠኝ ኬን! ጊዜ! ገና ዛሬ ነው አብረን ያደርነው:: ስስዚህ ትንሽ ታገሰኝ” አለች ፈገግ አሰችና::

ኬን ግን አሁንም እንደተጨነቀላት ነበረ:: በሐዘኔታ አመለካከት እያያትም “ያልነገርሽኝ ሌላም ሚስጥር እንዳለ ይታወቀኛል” አላት:: “ያን ያህል ጠቃሚ አይደሰም”

“አይመስለኝም:: የምትኖሪው በሚስጥር ግንብ ዙሪያውን ታጥረሽ ነው::”

“ዱሮ... ከብዙ ዓመታት በፊት ማለትህ ከሆነ ልክ ነህ” “ሰምን?”

"ምክንያቱም በኔ ላይ ጉዳት ለማድረስ የሚፈልጉ አንዳንድ ሰዎች ስለነበሩ ነው"

"አሁንስ?"

"አሁንማ እጠገቤ አላስደርሳቸውም" አለችው:: ከዚህ መልሷ አንድ ነገር ተረዳ:: አፈቅርሀለሁ ብላ ባትነግረውም አጠገቧ ከመድረስም አቅፏት እንዲተኛ ፈቅዳለታለች:: ጎንበስ ብሎ ሳማትና ጭኖቹን ከጭኖቿ መካከል አስገባቸው:: "ሂሊ! ሂሊ! የኔ ፍቅር! አይዞሽ አልጎዳሽም!" ሲል ያባብላት ጀመረ::

አፈቅርሻለሁ ቢላትም መልስ አልሰጠችውም:: እንባ ያቀረሩ ዓይኖቿን ገርበብ አድርጋ ዝም ብላ ታየዋለች:: የኬን ጣቶች፣ ጡቶቿን፣ ሆዷን፣ እምብርቷን፣ ዳሌዋን ረጋ ብለው ከላይ ታች፣ ከታች ላይ ሲያሹ ቆዩና ከጭኖቿ ደረሱ:: ምላሱን ከአፏ ውስጥ ከቶ ከምላሷ ጋር አገናኘው:: ከሥሩ ልቧ ትርትር ሲል፣ ሰውነቷ ስቅጥጥ አለና ሕይወት ዘርቶ ማተኮስ የጀመረው ሰውነቷ ቀስ በቀስ መቀዝቀዝ ጀመረ:: በክንዶቹ መካከል ያቀፈው የሂላሪ ገላ እየበረደ መሔዱን ኬን ቢረዳም አሁን ግን ስሜቱ እስከሚረካ ከላይዋ ላይ አልወረደም ነበረ:: በመጨረሻም ከጉኗ በጀርባው እንደተኛ "ሂሊ! በጣም እዝናለሁ... ይቅርታ አድርጊልኝ" አላት ብቻውን በመደሰቱ እየተፀፀተ::

"ለምንድን ነው የምታዝነው? እኔ ግን በጣም ነው ደስ ያለኝ" አለችውና ራሷን ከደረቱ ላይ አደረገችው:: እናት የልጆቿን ፀጉር እየደባበሰች ልጇን እንደምታስተኛ ኬንም የሂላሪን ረጅም ጥቁር ፀጉር ሲያሻሽላት ብዙ ቆየ:: ከዚያም ሁለቱንም እንቅልፍ ወሰዳቸው::

ኬን ከእንቅልፉ የነቃው ከሂላሪ በፊት ነበረ:: እንዳይቀሰቅሳትም ልብሱን ቀስ ብሎ ለበሰና ወጣ:: በዚያን ቀን ከሂላሪ ጋር ሲገናኙ አልቻሉም፤ ሁለቱም በየፊናቸው ሥራ በዝቶባቸው ነበረ የዋሉት:: ማምሻውንም በስብሰባና በሌላም ፕሮግራም ተጠምደው ነበረ::

በማግስቱ ኬን ስልክ ደወለላት:: የሳምንቱ መጨረሻ በመሆኑ ከእናታቸው ጋር ይኖሩ የነበሩትን ልጆቹን ለማየት ይሄድ ነበረ:: ሂላሪን አብራው እንድትሄድ አጥብቆ ለመናት:: ፈቃደኛም ባለመሆኗ ልጆቹን እሁድ ዕለት ሴንትራል ፓርክ ድረስ አምጥቶ ሊያሳያት ተስማሙ:: ኬን ልጆቹን አይታ እንድትወድለት ይፈልጋል:: ከእናታቸው ላይ ወስዶ ሊያሳድጋቸው ይፈልጋል:: በተጨማሪም ሂላሪ ልጅ እንድትወልድለት





ዕቅድ ነበረው:: ሂላሪ ግን ከህፃናት መሸሽ ካመጣች ዓመታት አልፈዋታል:: የኬንንም ልጆች ለማየት ከወዲሁ ፍርሐት ፍርሐት ብሏት ነበረ::

ሴንትራል ፓርክ እንደ ደረሰች ኬንና ሁለቱን ህፃናት ልጆቹን ለማግኘት ጊዜ አልፈጀባትም:: ከአንድ ዛፍ ስር ተቀምጠው ከሩቁ ታይዋት:: ትንሽየው ልጅ አባቱ ጭኖች ላይ፣ ትልቅየው ደግሞ ከአባቱ ጐን ተቀምጠዋል:: ሂላሪ ባየችው እንጀቷ ተላወሰ:: ልቧም ለአንድ ለረሳችው ነገር ተሰቀለ:: ወደመጣችበት ልትመለስ ነበረ:: ግን ለኬን የገባችለትን ቃል ማፍረስ ከበዳት:: በቀረበችበትም መጠን የልቧ መሰቀል ጨመረ:: በህፃናቱና በኬን መካከል የነበረው ፍቅር ልክ በርሷና በእህቶቿ መካከል እንዳለው ዓይነት ነበረ::

አብራቸው ምሳ ለመብላት አልቻለችም:: በራስምታት አመካኝታ ቶሎ ተለየቻቸው:: ከሴንትራል ፓርክ እያለቀሰች አፓርትማዋ ደረሰች:: ታክሲ ለመከራየት ወይንም አውቶብስ ለመያዝ አልሞከረችም:: መንገድ ለመንገድ እንዳለቀሰች መሄዱን መረጠች::

ቀኑን ሙሉ ከአልጋዋ ሳትወጣ ዋለች:: ዕንባዋም ትራስና አንሶላውን አራሰው:: የማታ ማታ ራሷን አፅናናችው:: ሚጋንም አሌክሳንድራም ለምንጊዜውም የተለይዋት መሆኑን እራሷን አሳመነች:: የት እንዳሉ አይታወቅም:: ስለዚህ ላታገኛቸው ማልቀሷ ትርጉም የለውም ነበረ:: ደግሞም እኮ አሁን ሚጋንና አክሲ እንደ ዱሮው ህፃናት አይደሉም:: ሂላሪ ሃያ አምስት ዓመት ከሞላት፣ አሌክሳንድራ ሃያ አንድ፣ ሚጋን አስራ ሰባት ዓመት ይሆናቸዋል:: ስለዚህ እነ አክሲ የጠፉ ህፃናት አይደሉም:: ትልልቅ ልጃገረዶች ናቸው:: የሂላሪ ለቅሶ እንዳው ነበረ:: ከዛሬ ጀምሮ ልትረሳቸው ቆረጠች::

በዚያን ምሽት ለመገናኘት ቀጠሮ ባይኖራቸውም ኬን ከአፓርትማዋ ድረስ መጥቶ ነበረ:: ከቀኑ የሴንትራል ፓርክ ሁኔታዋ ኬን የተጠራጠረው ነገር ነበረ:: የሂላሪ ኃዘን ከህፃናት ጋር ለማዛመድ ሞክሯል:: በሌላ በኩል ደግሞ ሂላሪ ልጅ ልትወልድ ቀርቶ ለአስራ ሁለት ዓመታት ወንድ እንዳል ደረሰባት ያውቃል:: ወንድምና እህትም እንደሌላት ነግራዋለች:: ሂላሪ ህፃናት ልጆቹን በማየቷ መለዋወጧን ግን በሚገባ አጢኗል:: ለምን? ለምን?

የአፓርታማውን ደወል ሲጫን የከፈተችለት ሂላሪ የቀኗ ሂላሪ አልነበረችም:: ከመታጠቢያ ቤት ገና በመውጣት ላይ ለመሆኗ በአለባበሷ

አውቋል:: ረጅም ጥቁር ፀጉሯ ተለቆ ከትከሻዋ ላይ ወርዷል:: ከፊቷ ላይ የሚነበበው እንደፈራው ትካዜ ሳይሆን ውበትና ሕይወት ነበረ:: እንደገባም ቀድማ ያቀፈችውና የሳመችው ሂላሪ ነበረች:: ኬን ስለ ሂላሪ የነበረውን የቀድሞ ግምት ከመቅፅበት ቀየረና ቀጥታ ወደ መታጠቢያ ቤት ገባ:: አምስት ደቂቃ ባልሞላም ጊዜ ውስጥ ሰውነቱን ተለቃልቆ ወጣ::

ሂላሪ ከመኝታ ቤቷ ውስጥ ሆና ፀጉሯን በማድረቅ ላይ ነበረች:: የኬንን መግባት ዘወር ብላ ተመለከተች:: እርቃኑን ነበረ:: እንደዚያ ያለ ነገር አይታ ባለማወቋ ተደነቀችና ልብ የሚያቀልጥ ፈገግታ አሳየችው:: እርሱም ከተቀመጠችበት እንደህፃን አቅፎ አነሳትና ከአልጋው ላይ ጣላት:: እንደእሳት የሚፋጁት ጭኖቹም ከጭኖቿ ውስጥ ገቡ:: እንዳትነቃነቅም በሰውነቱ አጣብቆ አቀፋት:: ራሱንም ከአንገቷ ስር ሸጉጠው:: ባለ በሌለ ኃይሉም ተገናኛት:: ሂላሪም ፀጉሯን የታጠበችበት ሎሽን ሽታ እንደተመኘው አፍንጫውን አወደው:: ሂላሪ ዛሬ እንዳለፉት ቀናት አልነበረችም:: አቅፋው አልጠግብ ብትል በጥፍሮቿ ወጋችው:: በከንፈሮቿም ስማ አልበቃ ስላላት በጥርሶቿ ነከሰችው:: ሂላሪ በደስታ አለቀሰች:: በህልሟም በውኗም ይኖራል ብላ ካላሰበችው ዓለም ውስጥ ገባች:: የሁለቱም ልብ ትርታ እኩል ከጨመረ በኋላ ሁለቱም በአንድ ጊዜ በረጅሙ ተነፈሱ:: ኬን ከላይዋ ላይ ወርዶ በጀርባው ተኛ::

ሂላሪ ግን ክንዶቿን አንተርሳው ከደቂቃዎች በፊት ምን እንዳ ደረገላት በማሰላሰል ፈገግታ እያሳየችው፤ "አሁንም ትወደኛለህ ኬን?" አለችው:: ኬን ሳይመልስላት እንደገና ከላይዋ ላይ ወጣ:: ሰውነቷም ወዲያውኑ ግሎ በደስታ ማፅበል ተንሳፈፈች:: አሁንም ከደስታዋ ብዛት አለቀሰች:: በመጨረሻም በኃይል አቃሰተች ሰውነቷ ከኬን ሰውነት ጋር ተጣበቀ፣ መላ አካላቷም በኃይል ነዘረና በእፎይታ ተነፈሰች:: ኬን ከላይዋ ላይ አልወረደም ነበረ:: "በድጋሚ ትወደኛለህ ወይ?" ብላ ስትጠይቀው::

"አንቺስ?" አላት ኬን::

"እወድሃለሁ"

"ታገቢኛለሽ?"

"ሥራዬስ?" አለችው::

"ስራሽ የቤት እመቤት መሆን ብቻ ይሆናል"

"ልጅ ማሳደግ?"

"አዎን?"





"አስር ልጆች?" አለችና ሳቀች::

"ምን አስር ብቻ ያየሻቸውን ሁለቱን ህፃናት ጭምር እንጂ?"

"የደርዘኖች እናት ልታደርገኝ ነዋ?"

"ደስ አይልሽም?"

"ደስ ይለኛል" አለችና ራሱን ቁልቁል ስባ ሳመችው::

ኬን ተንጠራራና ከትራስኔ የነበረውን ስልክ ስቦ አንድ ቁጥር ደወለ:: ወደ ኒውጀርሲ ለመብረር መቀመጫ እንዲያዝለት ለማድረግ ነበረ:: ኬን ወደ አዲሱ ሥራው የሚሄድበት ቀን ተቃርቧል:: ሆኖም ከዚያ በፊት ጥሩ መኖሪያ ቤት ማግኘት ነበረበት:: ለርሱና ለሂላሪ 'ለደርዘን ልጆቻቸው' ጭምር የሚሆን ትልቅ መኖሪያ ቤት:: ጠዋት ላይ ልብሱን ለባብሶ ሲወጣም ሂላሪ ከመኝታዋ ወጥታ በመስኮት ታየው ነበረ:: ኬን ግን ከመስኮቱ መቆሟን ቢያውቅ ኖሮ ምናልባት ሳይመለስ አይቀርም ነበረ:: ባለማወቁም ከቀይዋ ፊራሪ መኪናው ውስጥ ገብቶ እየነዳ ሄደ::

ያ ዕለት በምስኪኗ ሂላሪ ሕይወት ላይ ሌላ ጥቁር ነጥብ ጥሎ ያለፈ ዕለት ነበረ:: ዜናውንም በቅድሚያ የሰማችው ሂላሪ ነበረች:: የምሽት ዜናዎች ፕሮግራም በምታዘጋጅበት ወቅት ያልጠረጠረችው መርዶ ደረሳት:: ኬን በመኪና አደጋ ሞተ! ወደ ኒውጀርሲ አውሮፕላን ማረፊያ በሚበርበት ወቅት ነበረ ከተሳቢ መኪና ጋር ተጋጭቶ የሞተው:: ጥፋቱም የኬን እንደነበረ ዜናው ላይ ተገልጧል:: ኬን ቤት ሲያፈላልግ በመዘግየቱ ወደኒውዮርክ የሚመልሰው አውሮፕላን እንዳያመልጠው በመቻኮሉ እንጂ በማግስቱ ለመምጣት በቻለ ነበረ:: ሌሊቱን ያለ ሂላሪ እንዳያሳልፈው ይሆን ችኮላው?

ሂላሪ ከሌላ ካልተጠበቀ አጋጣሚ ላይ ባትወድቅ ኖሮ ለኬን በልቧ እንዳለቀሰችለት በኖረች ነበረ:: ግን ኬን ከሞተ ወዲህ የያዛት ኢንፍሉዌንዛ ከሳምንት ሳምንት እየባሰባት ሄዷል:: ሰውነቷም መንምኗል:: የሚያምራት ነገር እንቅልፍ ብቻ ነው:: ምግብ ደግሞ ለዓይኗ አስጠልቷታል:: ሌላው ቀርቶ ትወደው የነበረው ቡና ሽታ በሩቁ ያጥወለውላታል::

ከስድስት ሳምንታት በኋላ ስልክ ደውላ ከሐኪሟ ጋር ቀጠሮ ያዘች:: የተለያየ የደም ምርመራ እስከሚደረግላትም ድረስ ሐኪሙ የአንቲ ባዮቲክ እንክብሎች ሊያዝላት አስቦ ነበረ:: "አንድ ዓይነት ቫይረስ ሆድሽ

ውስጥ የገባ ይመስለኛል:: ለመሆኑ በቅርቡ ከከተማ ውጪ ለሽርሽር ሄደሽ የማይስማማሽ ምግብ በልተሽ ይሆን?» ሲል ጠየቃት::

ላለመብላቷ ሂላሪ ራሷን ዝግ ብላ በማወዛወዝ አሳየች:: በሽታው ድቅቅ አድርጓት ነበረና ለውነቷን ማላወሱም ከብዷታል:: ከአልጋው ውስጥ ገብታ ቀኑን ሙሉ ስትተኛ ብትውል ፈቃዷ ነው:: የደሙ ምርመራ ውጤት ከሁለት ቀናት በኋላ ታወቀ:: ሂላሪ የህመሟ ምክንያት ተገለፀላት:: ሐኪሙ ደሟ በጥንቃቄ እንዲመረመር ማድረጉ ምናልባት በዘር የተላለፈ ውርዴነት ቢኖርባት ነው ብሎ ነበረ:: ሆኖም ሂላሪ በመፅነሷ እንጂ ሌላ በሽታ እንደሌለባት ተረጋገጠ:: በዚያን ወቅት ምርጫ ስለሌላት እንጂ ሂላሪ ከመፀነስ በደም የተላለፈ ውርዴነት ብቻ ሳይሆን በሽታው በቀጥታ ቢይዛትም ትመርጥ ነበረ::

ከመደንገጧም የተነሳ ቀጥታ ወደ ቤቷ ሄደች:: ከአልጋዋም ላይ ተኝታ በሐሳቧ ነገሮችን ማውጣትና ማውረድ ጀመረች:: ልቧም ዋለለባት:: ግማሽ ጐኗ ፅንሱን አስወርጂ ይላታል:: በሌላ በኩል ደግሞ የአክሲና የትንሿ የሚጋን ትዝታ ከፊቷ ድቅን ይልና፣ ሁለት ህፃናት እንዳላጣች አሁን ደግሞ ሶስተኛውን ህፃን የማጣቷ ጉዳይ ሆዷን ያባባዋል:: የምትወደው የኬን ልጅ በመሆኑ ህፃኑ ቢወለድ ባልከፋትም:: ግን አባት የሌለው ልጅ ማሳደግ ምንኛ ይጨንቃል:: ለህፃኑ ስትል ስራዋንም እስከመተው ልትደርስ ትችላለች:: ለአንድ ሳምንት ያህል በጉዳዩ ስታስብበት ቆየች:: ምግብ አልበላልሽ ስላላት ከብደቷ ቢቀንስም የቀድሞዎቹ ቀሚሶቿ ሆዷ አካባቢ ጠርነቅ እያደረጉ ሊይዟት ጀምረዋል:: ሂላሪ ስው ናትና እንደ ኬን በወጣ ችበት ልትቀር ትችላለች:: ያን ጊዜስ ህፃኑ ምን ይውጠዋል? ማን ያሳድገዋል? እንደርሷ ወላጆቻቸው በሞቱባቸው ልጆች መጠለያ ቤት?... ጠባይ ማረሚያ? ... ሂላሪ ራሷን በሁለት እጆቿ ይዛ «አይሆንም!» «አይደረግም!» ስትል ጮኸች:: አክሲና ሚጋንን እንደረሳቻቸው በማህፀኗ የተሸከመችውን ፅንስ አስወጥታ ልትረሳው ወሰነች::

ሂላሪ በጣም ፈርታ ነበረ:: ሐኪሙም ወደነበረችበት ክፍል እስከሚገባ ከአንዴም ሁለቴም ሐሳቧን በመቀየር ከዚያ ክፍል ውስጥ ለመውጣት አስባ ነበረ:: ሆኖም አስታማሚዋ መጣችና የሚሞላ ፎርም ሰጠቻት:: ሂላሪ በሚንቀጠቀጥ እጇ ፎርሙን ሞልታ ፈርማ መለሰችላት:: ወዲያውኑም ሐኪሙ የቀዶ ጥገና ልብሱን ለብሶ ገባ::

የሂላሪን ድንጋጤ ከሁኔታዋ ተረድቶታል:: ሲያበረታታም «አይዞሽ ቀላል ነገር ነው» አላት:





«ብቻ... መቼም እንቅልፍ የሚያስወስድ መድሐኒት ትሰጠኝ የለም?» አለች ከንፈሮቿ እየተንቀጠቀጡ:: «የሚያስፈልግ አይመስለኝም:: በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ የምትገላገይው ይሆናል» አለና ወደ አንድ የተለየ ክፍል እያመለከተ፤«ከዚያ ገብተሽ ልብስሽን ቀይሪ» አላት::

ሂላሪ ተዘጋጅቶ የሚጠብቃትን ልብስ ቀይራ ወደ ክፍሉ እንደተመለሰች ከአንድ ረጅም ጠረጴዛ ላይ አስተኟት:: አስታማሚዋም የሂላሪን እግሮች ማዶና ማዶ ወጥራ ከጠረጴዛው ጋር በሽራ አሰረቻቸው::

«ምነው? ለምን?» አለች ሂላሪ በጀርባዋ ከተኛችበት ቀና ብላ ወደ እግሮቿ እያየች::

«ራስሽን እንዳትጐጂ ነው»

«እረ እኔ አልሞክረውም እባክሽን እግሮቼን ፍቺኝ»

«እጅሽም መታሰር ይኖርበታል»

«ከዚህ ሁሉ ምናለበት የእንቅልፍ መርፌ ብትወጉኝ»

ሐኪሙና አስታማሚዋ ተያዩ:: በራሱም ምልክት ስላሳያት ወደ መድሃኒት መደርደሪያው ሄዳ ብዙም ሳትቆይ ተመለሰች:: ሂላሪንም በክንዷ ላይ መርፌ ወጋቻት::

«በደቂቃዎች ውስጥ እጨርሳለሁ ስለዚህ ከአንድ አስከ አስር ቁጠሪ» አላት ሐኪሙ:: ከሰውነቷ ውስጥ ብረታማ ነገር መግባቱ ተሰማትና በኃይል ጮኸች:: እነኛ በመጠለያ ውስጥ የነበሩት ልጆች እንኳን ተራ በተራ ሲፈራረቁባት የአሁኑን የህል አላመማትም:: ማደንዘዣውም ሰርቶ ህሊናዋን የሳተችው በዚያን ጊዜ ነበረ:: የሂላሪን ፅንስ ካስወረዱ በኋላ ሐኪሙና አስታማሚዋ ወደ ሌላ ክፍል ሄዱ:: የሚጠብቃቸው ሌላ ባለተራ ነበረ::

ከአንድ ሰዓት በኋላ አስታማሚዋ ተመልሳ ገባች:: ለሂላሪም ውሃ የነካው ፎጣ ሰጠቻት:: ከዚያም አንዳንድ ገለፃዎች አደረገችላት:: ደም መፍሰስ ከጀመራት ቶሎ ተመልሳ መምጣት እንዳለባት አስጠነቀቀቻት::

ሂላሪ ለሶስት ተከተታይ ቀናት ስራ አልሄደችም:: መጨረሻም ላይ ጤናማ መሆኗ እየተሰማት ሄደ:: የፈራችውም አለፈ:: በአድራጎቷ አሁንም ብትፀፀት፤ ከባለ ፀፀት ለመዳን ስትል ሳትወድ አደረገችው እንደነ አክሲና ሚጋን ልትረሳውም ሞከረች:: ለዚህ ደግሞ መፍትሔው በስራ መጠመድ እንደሚሆን ታውቃለች::

ፊቷ ቢወይብና ሙሉ በሙሉ ጤነኛ አለመሆኗ ቢያስታውቅም፤ በአራተኛው ቀን ስራ ጀመረች:: በቢሮዋ እንደስራች ትውላለች፣ ከቤቷም ስትስራ ታመሻለች:: ሂላሪ ቆርጣ የተነሳችበት ግብ ነበራት:: የዚያ የዜና አገልግሎት ድርጅት ስራ አስኪያጅ መሆን አለባት:: ከዚያ በኋላ በተለበለበ መንፈስ የወላጆቿን የሕይወት ታሪክ መፃፍ ትጀምራለች:: ጥናቷም በጋዜጣና በመፅሄቶች ላይ ብቻ በወጡ ፅሑፎች ሳያተኩር ከወላጆቿ የልደት ስፍራ ድረስ በመሄድና ሰዎችን በማነጋገር በምታገኘውም መረጃ የተደገፈ መሆን አለበት:: ለተከታታይ ሶስት ዓመታት ሂላሪ አንድም ቀን እረፍት የሚባል ነገር ሳትጠይቅ ለስራዋ ብቻ ቅድሚያ ሰጠች:: በሁሉም ዘንድ ተደናቂና በአርአያነት የምትጠቀስ ሆነች:: በሃያ ስምንት ዓመቷም ከምሽት ዜና አዘጋጅነቷ ወደ ቀን ዜና ዋና አዘጋጅነት ተዛወረች::

"እንደ መልኳ በስራዋም ሌላ ነገር ናት ይባላል" አሉ ከአዲሶቹ ፀሐፊዎቿ አንደኛዋ ለሌላዋ:: ሂላሪ አልፋቸው ወደ ቢሮዋ በመግባት ላይ ነበረች::

"አያደርስ እንጂ እርሷ ጋር ቀልድ የለም ይላሉ"

"በምኑ?"

"በስራ!"

"አትይኝም?"

"ወሰምዘለም የሚል ሰራተኛ ካጋጠማት ማባረር ብቻ ነው"

"የማታ ዜናዎች አዘጋጅ ሆኖ ያባረረችው ሰው አለ?"

"ከአምስት የሚበልጡ!"

"በይ እመቤቴ ወሬሽን አቁሚልኝ"

ሂላሪ በሰላሳ ሁለት ዓመቷ የዚያ ዝነኛ የዜና አገልግሎት ድርጅት ተጠባባቂ ም/ስራ አስኪያጅነት ደረጃ ደረሰች:: በሰላሳ አምስት ዓመቷ ምክትል ዋና ሥራ አስኪጅ፣ በሰላ ዘጠኝ ዓመቷ ዋና ስራ አስኪያጅ ሆነች:: ዜናውን ጋዜጦች በየዓምዶቻቸው አወጡት:: የኒውስ ዊክና የታይም መፅሄቶች ሂላሪን ቃለ መጠይቅ አቀርበውላት፣ ለለ ድርጅቱ ያላትን አስተያየትና ዕቅድ በሰፊው ዘርዝረው ፃፉ:: የሂላሪ ፎቶግራፍ በያለበት ተዳረሰ:: ሂላሪ ምከር አንድ ቀን ለኬን አጫውታው እንደነበረው ከቁንጮው ደረሰች::





# ምዕራፍ አስራ ሁለት

ሁለት ሰዓት የፈጀ የሕክምና ምርመራ ተደርጎለት ሲወጣ ፊቱ እንደጨፈገገ ነበረ:: የውጪውንም ነፋስ መሳብ አቅቶት ያለከልካል:: ሐኪሙ በነገረው እምብዛም አልተደነቀም:: ሊሆን እንደሚችልም የገመተው ነገር ነው:: ግን አርዘር ፓተርሰን የተደናገጠው በሕይወት የሚቆይበት ጊዜ ከስድስት ወር እንደማይበልጥ ስለተነገረው ነው:: መኪናው እስከቆመበት እንኳን ለመድረስ ሁለት ሶስት ጊዜ ማረፍ ነበረበት:: ሕመሙ በመላ ሰውነቱ ተሰራጭቶ እያሰቃየው ነበረ:: ሳንባውን አፍኖ እያስጓራ ሲያስለው ያየ አንድ መንገደኛ ሊደግፈው ጠጋ ብሎ ነበረ:: ፓተርሰን ግን ትንፋሹ መሰስ ስላለለት ወደ መኪናው እያዘገመ ሄደ:: ከቤቱም እስከሚደርስ ድረስ ሹፌሩን አንድም ቃል አላነጋገረውም::

በጉዞው ላይ ሆኖ የሚያስበው ሐኪሙ የተናገራቸውን ቃላት ነበረ:: ከዚያ በላይ ዕድሜ መመኘት እንደማይኖርበትም ያውቀዋል:: ሰባ ሁለት ዓመት ቀላል ዕድሜ አይደለም:: ደግሞም ያሳለፈው ህይወት የከፋ አልነበረም:: ባይታደልና ልጅ ባይኖረውም እንደ ጓደኞቹ እርሱም ሚስት አግብቶ ነበረ:: ማርጆሪ ከሞተች ሶስት ዓመት ሆኗታል:: ፓተርሰን ስለ ሚስቱ ማርጆሪ ብዙ ሲያስብ ቆየ:: ልጅ ባለመውለዷ እንጂ ልትወልድ ትችል ነበረ:: 'እንዲህ ሲቀር ለሚቀረው ዓለም ለምን ትዝታችንን እንኳን የሚያስታውስ አንድ ልጅ ሳትወልድ ቀረች?' ሲል ራሱን ጠየቀ:: 'ለመኖር ከፍተኛ ትግል ብታደርግም ማርጆሪ ደስተኛ ነበረች ወይ?' አለ በሐሳቡ:: እንዳልነበረች ያውቀዋል:: ሞትም አልቀረላትም::

የእርሱም የመሞቻው ጊዜ ሩቅ አይደለም፤ ፓተርሰን አሁን ከሚሰቃየው ስቃይ ሞቶ ቢያርፍ ይመርጣል:: ስለዚህ ሞትን አልፈራም:: ያሳዘነው ነገር ቢኖር በሕይወቱ ውስጥ አንድ ስሙን የሚያስጠራበት ሥራ ባለመስራቱ ነው:: በሕግ ሙያው ያበረከተው አንዳችም በምሳሌነት የሚጠቀስ ክርክር አልረታም:: ከሌሎቹ ጠበቆች ጋር የነበረው ግንኙነት የጠነከረ አልነበረም:: ከጓደኛ እንኳን የረባ ጓደኛ አልነበረውም:: ምናልባት ትንሽ እንኳን ቢሆን ልታዝንለት የምትችለው ለብዙ ዘመን ልዩ ፀሐፊው ሆና ያገለገለችው ሌት ብቻ ናት::

ከመኖሪያ ቤቱ እንደ ደረሰ ሹፌሩ ደግፎ አወረደው። ከመኝታ ቤቱም አስገብቶ ተመለሰ። ፓተርሰን ከአልጋው ላይ ተቀምጦ ራሱን በሁለት እጆቹ ደግፎ አቀርቅሮ ሲያስብ ቆየ። ያን ጊዜም ሌላ የታወሰው ነገር ኖር ሰንባው ተሰል እያለ ወረደ። አልፎ አልፎም እንደሸምበቆ የቀጠነው ሰውነቱ በሲቃ ይኮመታተር ነበረ። ፓተርሰን ከልቡ ገብቶ ያንገ በግበው አንድ ትዝታ አለ። እውነተኛ ጓደኛዬ የሚለው፣ እንደ ታናሽ ወንድሙም ያየው የነበረው ሰው መልክ ከፊቱ ድቅን ብሎበታል። ምክር ሐቀኛ ጓደኛው ብቻ ሳይሆን ከአንድም ሁለት ጊዜ እንዴት ሕይወቱን እንዳዳነው ለዓይነ ሕሊናው ታየው። እርሱን ለማዳን ያ ጓደኛው እራሱን ለአደጋ ማጋለጥ ነበረበት። ሆኖም ፍቅር መሥዋዕትነትን ትጠይቃለችና ምክር ለራሱ ሳይሳሳ ለጓደኛው ማዳላቱን መረጠ።

እስኪ.ጨልም ድረስ ፓተርሰን ከተቀመጠበት አልተንቀሳቀሰም ነበረ። በሐሳቡም ከብዙ ዓመታት በፊት የተፈፀሙ ድርጊቶችን ተራ በተራ አስላሰለ። ከሰሜን አፍሪካ በረሀ እስከ ጣሊያን ተራሮች ድረስ ከምክር ጋር አልተለያዩም። በሮም ከተማ በተደረገው ወታደራዊ ሰልፍ ላይ ጐን ለጐን ነበሩ። ፓሪስም ውስጥ እንደዚሁ አንድ ቀን በዲ.አርኮል ጎዳና ላይ ምክር ያያት ልጅ ታወሰችው። ባለ ትላልቅ አረንጓዴ ዓይኖች ልጅ... ባለ ወርቃማ ፀጉር ውብ ልጃገረድ... ያቺ ሸንቃጣ ኮስታራ ልጅ... የምክር ፍቅረኛ ሶላንጅ ዛሬ ታወሰችው። ሶላንጅ የነ ሂላሪ፣አክሲና ሚጋን እናት... በፍቅረኛዋ እጅ ሕይወቷ ያለፈው ሶላንጅ... ሶላንጅ... ምክር ... ሶላንጅ። ፓተርሰን ለጓደኛውና እንደ ታናሽ ወንድሙ ያየው ለነበረው ለምክር አለቀሰ። ለፓሪሷ ልጃገረድ ለሶላንጅ አነባ። ያለወላጅ የቀሩት ልጆቻቸው እነ ሂላሪ ታወሱት። እንደ ነፋስ በታትኗቸው የቀረው እህትማማቾችን ዳግመኛ እንዳይገናኙ ያደረገው ራሱ ፓተርሰን ነበረ። እንደዛም በማድረጉ ራሱን ወንጀለኛ አደረገ። ግን የእንግዲሁ ፀፀት ምን ሊፈይድ። እነ ሶላንጅ ከሞቱ ከሰላሳ ዓመት በላይ ሆኖታል።

ፓተርሰን አንድ ሐሳብ ብልጭ አለበትና ካቀረቀረበት ቀና አለ። "ለምን አላደርገውም? ለምን አልሞክርም?" ሲል በዚያ ብቸኛ ቤት ውስጥ ድምፁን ከፍ አድርጐ ተናገረ። "አዎን! ማድረግ አለብኝ!" አለ ደገመና። እህትማማቾቹ በመረሳሳታቸው በአሁኑ ዕድሜያቸው ቢገናኙ ምናልባት እንደጥንቱ ላይፋቀሩ ይችላሉ። ያም ሆኖ ፓተርሰን ከመሞቱ በፊት ያለያየውን ቤተሰብ ለማገናኘት ቆረጠ። የፈሰገውን ድካምና ወጪ ቢጠይቅም ፓተርሰን ሶስቱን እህትማማቾች አግኝቶ ስለ ከፍተኛ በደሉ መናዘዝ ነበረበት። ያን ጊዜም ብቻ ነበረ ንፁህ ሕሊና አግኝቶ ዕለተ ሞቱን በሰላም





ለመጠባበቅ የሚችለው። ትንንሽ እህቶቿን ነጥቆ ሲወስዳቸው ሂላሪ እንዴት እንደለመነችው ሁኔታዋ ሁሉ ከፊቱ ድቅን ይልበት ነበረ።

ሌሊቱን ሙሉ እንቅልፍ በዓይኑ ሳይዞር አደረ። እንዴትስ ሊያገኛ ቸው እንደሚችል በአያሌው አሰበ። የጊዜው ጉዳይ ወሳኝነት ነበረው። ፓተርሰን ልጆቹን ይቅርታ ጠይቆ በተለይ በጋራ የሚያወርሳቸው አንድ ንብረት ነበረው። የጡረታ ዘመኑን ለማሳለፊያ በኰኔክቲክት ግዛት ውስጥ የገዛው አንድ በአስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን የተሰራ እጅግ ውብ ቤት ነበረው። እርግጥ ኒውዮርክ በኖረበት ረጅም ዘመኑ ውስጥ በባንክ ተቀማጭ ገንዘብና በአንዳንድ ፋብሪካዎች አክሲዮኖች የሉትም ማለት አይደለም። ግን እንደዚያ ባለ አንድ ፎቅ ህንፃና ለፊ ምድረ ግቢ ለፓተርሰን ከብደው ባለመታየታቸው ነው። ከእንግዲህ ጡረታ ወጥቶ በዚያ ግቢ ውስጥ ለመንሸራሸር፣ የአበባ መደቦችን ለመኮትኮት፣ የዛፍ ቅርንጫፎችን ለመከ ርከም ዕድል አይኖረውም። መጥለቂያዋ እንደተቃረበ ፀሐይ፣ የርሱም ሕይወት አክትሞ ወደ መቃብር የሚወርድበት ሰዓት ደርሷል። በኤክስሬይ የተደረገለት ምርመራ ሁሉንም ነገር ነግሮታል። የያዘው ካንሰር በሽታ ከሕክምና ቁጥጥር ውጪ ሆኗል። እድናለሁ የሚለው ተስፋ አክትሟል።

እኩለ ሌሊት ላይ የእንቅልፍ ኪኒን ቢወስድም ሸለብም ሳያደርገው ወለል ብሎ ነጋ። በዓይኖቹ ላይ ብልጭ ድርግም እያለ በተለይ እንቅልፍ የነሳው የሂላሪ ሁኔታ ነበረ። እርሷም ትንሽ ብትሆን ትናንሽ እህቶቿን በወሰደበት ዕለት ሁለቱንም እንቅ አድርጋ አቅፋ ላለማስነካት ሞከረች። እንደማትቋቋመውም ቁርጡን ስታውቅ እህቶቿን ለቃ አለቀሰች። መኪና ውም እየበረረ ሲሄድ ከመንገድ ዳር ተንበርክካ ታነባ እንደነበረ ፓተርሰን አይዘነጋውም። ያቺ ሂላሪ ነበረች አሁን በዓይኑ ላይ እየሄደች እንቅልፍ የነሳችው። የምክርና የሶላንጅ ልጅ... ያቺ የነ አሌክሳንድራና የሚጋን እህት ብቸኛዋ ሂላሪ!

# ምዕራፍ አስራ ሦስት

ፓተርሰን እኩስ ቀን ላይ ከእንቅልፉ ተነሳ:: ሌሊቱን ባለመተኛቱ ሰውነቱ እንደዛለ ቢሆንም ወደ ቢሮው ለመሄድ ቆርጧል:: እስከ አስራ አንድ ሰዓት ድረስ ወደ ተለያዩ ቦታዎች ስልክ ሲደውል ቆየ:: የሚፈልገውንም ዓይነት ሰው ስም በመጨረሻ ላይ አገኘ:: የዚያን ዓይነት ሙያ ያለው ሰው ለምን እንዳስፈለገው ግን በስልክ ካነጋገራቸው ውስጥ ለአንደኛውም አልተናገረም::

ፓተርሰንን በጣም የገረመው ነገር ቢኖር ያ የፈሰገውን ሰው ቀጠሮም ሳያበዛ በዚያኑ ቀን ሊያነጋግረው ፈቃደኛነቱን መግለፁ ነው:: ጆን.ቻፕማን በሙያው ላይ ዝናን ያተረፈ ሰው በመሆኑ ፈላጊው ብዙ ነበረ:: ግን እንደ ፓተርሰን ያለ የሕግ ጠበቃ አስቸኳይ እርዳታ ሲጠይቀው ለከባድ ነገር መሆኑ ገብቶት ወዲያውኑ ከቢሮው ድረስ መጥቶ እንዲያነጋግረው ፈቀደ:: ፓተርሰን ምስጋናውን ከገለጠ በኋላ ስልኩን ዘግቶ ባለው ቅስም ከቢሮው እየተቻኮለ ወጣ::

በፓተርሰንና በቻፕማን ቢሮዎች መካከል ያለው ርቀት ያን ያህልም አልነበረም:: ፓተርሰን ከአስተናባሪዋ ክፍል ገባና ስሙን ተግናሮ ተቀመጠ:: ብዙም ሳይቆይ የቻፕማን ልዩ ፀሐፊ ብቅ ብላ ወደ ውስጥ እንዲዘልቅ ጋበዘችው:: ተራ የሚጠብቁ ብዙ ሰዎች ቢኖሩም ለፓተርሰን ቅድሚያ ተሰጥቶት ነበረ::

የቻፕማን ቢሮ እንደ ፓተርሰን ቢሮ በህግ መፃህፍት ከዳር እስከዳር የተሞላ ነበረ:: ፓተርሰን ይህንን በማየቱም ሊሆን ይችላል ለአካባቢው የእንግድነት ስሜት አልታየበትም:: ጥቂትም ቢሆን የተደነቀው በቻፕማን አለባበስ ነበረ:: ቻፕማን ሱፍ አለበሰም:: ከረባትም አላሰረም:: በግራጫ ቢትልስ ሹራብ ላይ የደረበው ቀይ ጃኬት ነበረ:: ያም ሆኖ ከአቋሙና የደስ ደስ ካለው መልኩ የሰውየውን ማንነት ለመገመት ቀላል ነው:: ምሁርና የሥራ ሰው ለመሆኑ ከፊቱ ላይ ይነበባል::





ፓተርሰንን ከበሩ ድረስ ሄዶ በአክብሮት ተቀበለው፤ ወንበርም አመቻችቶ እንዲቀመጥ ጋበዘውና እርሱም አጠገቡ ካለው ወንበር ላይ አረፍ አለ:: ቻፕማንና ፓተርሰን ሁለቱም ረጃጅሞች ቢሆኑም በዕድሜ ግን ብዙ ይራራቁ ነበረ:: ፓተርሰን በትንሹ በሰላሳ ዓመት እንደሚበልጠው ግልፅ ነበረ::

“በጣም ነው የማመሰግነው ...” አለና ፓተርሰን አንድ ሁለት ጊዜ ካሳለው በኋላ “... ዛሬውኑ ጥያቄ አቅርቤልህ ልታነጋግረኝ ፈቃደኛ በመሆንህ በድጋሚ አመሰግናለሁ:: ያስቸገርኩህም ያለ ምክንያት አይደለም:: ጊዜ ሊሰጠው የማይቻል አንድ የምታደርግልኝ ነገር ስላለ ነው:: ከጊዜ ጋር መሻማት አለብኝ” አለና አሁንም ሳለ::

ቻፕማን ፓተርሰን የሚነግረውን በማስታወሻ ላይ ለማስፈር ተዘጋጀ:: የፓተርሰን ጥድፊያም ውስጥ ውስጡን አሳስቦታል:: ምናልባትም ዕድሜው በመግፋቱ ስለውርስ ጉዳይ ያነሳ ይሆናልም ሲል ገምቷል:: የቻፕማን ድርጅት የታወቀው በወንጀል ምርመራ ነው:: በመሆኑም ፓተርሰን በውርስ የተነሳ አንድ ያጋጠመው ችግር ሊኖር እንደሚችልም ተጠራጥሯል:: የፓተርሰን ደጋግሞ መሳልም ለችኮላው ምክንያት መሆኑ ቻፕማን በግምት ደርሶበታል:: ስለዚህ “በቅድሚያ እስቲ ችግሩን ይንገሩኝና በምን መንገድ ልረዳዎት እንደምችል ላስብበት” አለ ቻፕማን:: እንደ መደብ ጀርባው የትምህርት ችሎታውና የሥራ ደረጃው ልኩራራ የማይለው ቻፕማን ለአነጋገሩ ለዛ ነበረው:: የቻፕማን አባት ወንድሞቹ ባለ ፋብሪካዎች ከበርቴዎች ነበሩ:: እንደነርሱም ቻፕማን ተንደላቆ ለመኖር በቻለ ነበረ:: እርሱ ግን አእምሮን በሚያስጨንቅና ለአደጋ በሚያጋልጥ የወንጀል ምርመራ ሥራ ላይ ተሰማራ::

“የግል ጉዳይ ነበረ” አለ ፓተርሰን ካስነጠሰው በኋላ አፍና አፍንጫውን በመሐረብ እየጠራረገ “በግል የተቸገርኩበት ጉዳይ ነበረኝ:: በእኔ ዘንድ የከበረ ስፍራ የምሰጠው ጉዳይ በመሆኑም በምስጢር መያዝ አለበት:: ከአንተ በስተቀር ሌላ ሰው ሊያውቀው አይገባም” አለው... ዓይን ዓይኑን እያየ::

“እኔም ብሆን የሌላ ሰው የግል ምስጢር አንስቼ ከማንም ጋር አልጫወትም:: ስለዚህ ምንም ሳይጠራጠሩ ቢቀጥሉ?”

“ጥሩ ምስጢሩ ድብቅ ይሁን ማለቴ ብቻ ሳይሆን በጉዳዩም ላይ አንተ ራስህ ክትትል እንድታደርግልኝ እፈልጋለሁ:: ከአንተ እኩል ማንም ሊረዳኝ እንደማይችል ከሰዎች ጠይቄ አጣርቻለሁ::”

ወደ ታሪኩ ቶሎ በመግባት እንዲያጫውተው ቻፕማን ቢፈልግም ከዚያ በፊት ግን ፓተርሰን ባነሳው ሐሳብ ላይ አቋሙን መግለፅ ስለሚኖርበት «እንደ ሁኔታው ነው። በእርግጥም ጉይዩ ከባድ እስከሆነና ያለኔም የማይፈፀም መስሎ ከተሰማኝ ራሴ እከታተለዋለሁ» አለው ቻፕማን።

«እንግዲህ በቅድሚያ እንዳጫወትኩህ ከጊዜ ጋር መሻማት ይኖርብናል። ለክትትሉም ከፍተኛ ትኩረት ማድረግ በማስፈለጉ አንተው ራስህ ሁኔታውን እንድትይዘው ላሳስብሁ እወዳለሁ» አስና ፓተርሰን በኃይል አሳለው። ትንፋሹም መለስ ሲልለት «አደራህን ሚስተር ቻፕማን እንደ ምታየው በሕይወት ለመቆየት ያለኝ ዕድል የመነመነ ነው» አለ።

ቻፕማን ፓተርሰንን በሐዘኔታ ሲያየው ቆየ። በጣም ለመጨነቁ ግልፅ ነበረ። ፓተርሰን በሚንቀጠቀጥ እጁ ከቦርሳው ውስጥ አንድ ፋይል አወጣና ሰጠው። እንደ ቻፕማን ግምት ፋይሉ ስለውርስ ጉዳይ የሚያወራ እንጂ ሌላ ሚስጢር ያዘለ አልመሰለውም። ሰዎችም መሞቻቸው በተቃረበ ቁጥር ኑዛዜአቸውን ሲቀያይሩ ብዙ ጊዜ የተመለከተው ጉዳይ ነው።

«እንደ ሐኪሙ ግምት ከሆነ በሕይወት የምቆይባቸው ወራት ቢበዛ ስድስት አለበለዚያ ሦስት ወራት ይሆናሉ። በበኩሌ ሦስቱን ወራት አስተማማኝ አድርጌ መምረጡን እወዳለሁ። እና በእነኚህ ሦስት ወራት ውስጥ ሦስት ወጣት ሴቶችን እንድታገኝልኝ እፈልጋለሁ» ሲለው ቻፕማን ከኃዘኔታ ይልቅ በመገረም ያየው ጀመረ። ልጆቹ ካልሆኑ በስተቀር የሦስት ወጣት ሴቶች መገኘት ለሽማግሌው ፓተርሰን ምን ያደርግለታል ሲልም ለራሱ ጥያቄ አቀረበ።

ፓተርሰን ግን ንግግሩን በመቀጠል «የሦስቱ ሴቶች እናትና አባት የቅርብ ወዳጆቼ ነበሩ። የሞቱትም ከሰላሳ ዓመት በፊት ነው። ወላጆቻቸውን በህፃንነታቸው ካጡት ከእነኚህ ህፃናት መካከል ሁለቱን በጉዲፈቻ ልጅነት ለተለያዩ ቤተሰቦች ስሰጣቸው ሦስተኛዋን ግን ከአክስቷ ጋር እንድትኖር አደረግሁ። ለመጨረሻም ያየኋቸው ትንሺ ልጅ ገና የዓመት አራስ ልጅ እንደሆነች ሲሆን ያን ጊዜ መካከለኛዋ አምስት፣ ትልቋ ዘጠኝ ዓመታቸው ነበረ። እነኛ ልጆች አሁን የት እንዳሉ አላውቅም። የሁለቱን ህፃናት የጉዲፈቻ አባቶች ግን አስታውሳቸዋለሁ። ትልቋም ብትሆን ከሐያ ሁለት ዓመት በፊት ከጃክሰንቪል ከተማ ወደ ኒውዮርክ ተመልሳ በመምጣት አነጋግራኝ ነበረ። ተጨማሪ መረጃዎች ቢያስፈልጉህ ከፋይሉ ውስጥ በየርዕሉ ካስፈርኳቸው አንዳንድ ፅሑፎች ለማግኘት ትችል ይሆናል።





አባታቸውም በጊዜው ዝነኛ ተዋናይ ነበረ» አለና ፓተርሰን በረጅሙ ተነፈሰ።

ቻፕማንም ጣልቃ ገባና «ለመሆኑ ወላጆቻቸው በአንድ ጊዜ በአደጋ ነው የሞቱባቸው?» ሲል ጠየቀው።

«የሁለቱም ሕይወት በአደጋ ማለፉ እርግጥ ነው» አለና ፓተርሰን አንገቱን አቀርቅሮ ሲተክዝ ቆየ። «ለምን እንደሆነ በግልፅ ባይታወቅም አባታቸው እናታቸውን አንቆ ገደላት። የቀብሯም ሥነ ሥርዓት በተፈፀመበት ዕለት ምሽት ደግሞ የራሱን ሕይወት አጠፋ። ከዚያም እነዚያን ህፃናት በአንድ ጣሪያ ሥር አሰባስቤ የማሳደግ ዕቅድ ነበረኝ፤ ሞክሬም ነበረ። ግን... ግን...» አለና ማርጆሪ ሚስቱ ተስፋ እንዳስቆረጠችው ትዝ ብሎት ይተናነቀው የነበረው ዕምባ ዱብ ዱብ አለ። ቻፕማን አሁንም በድብልቅ ስሜት ያየው ጀመረ። በዚያን ዕድሜው አንብቶ ማልቀሱ የፀፀቱን ጥልቀት ቢያሳይም እንደ ህግ ባለሙያነቱ ግን ሰላሳ ዓመታት በላይ የተለያዩ እህትማማቾችን መልሶ ለማገናኘት ማቀዱ ጥቅሙ ከምኑ ላይ እንደሆነ ለቻፕማን ግልፅ አልሆንልህ አለው፤ 'ምናልባትም በህፃናቱ ላይ የፈፀመው በደል ኖሮ ያንን ለማካካስ ሲል ካልሆነ በስተቀር የአሁኑ የፓተርሰን ድካም ከንቱ ነው' ሲልም አሰበ።

«ህፃናቱን ለመለያየት አልፈለኩም ነበረ። ነገር ግን ሦስቱንም በአንድነት ሲያሳድጋቸው ፈቃደኛ የሆነ ቤተሰብ ለማግኘት ባለመቻሌ ነው» ሲል ፓተርሰን ለአድራጎቱ ትክክለኛነት ምክንያት ለመስጠት ሞከረ። የራሱን ደካማነት ግን አውጥቶ ለመናገር አልደፈረም። የሞተችውንም ሚስቱ የማርጆሪን ስም በማያውቃት ሰው ፊት ለማንሳት አልፈለገም። በእጁ ይዞት የነበረውን አንድ የጋዜጣ ቁራጭ ወደ ቻፕማን አቀረበ «ይኸውልህ ይህ ጋዜጣ በቅርቡ የወጣ ነው። በዚሁ ኒውዮርክ ከተማ ውስጥ ባለ አንድ ዕውቅ የዜና ማሰራጫ ድርጅት ውስጥ ሥራ አስኪያጅ ሆና ስለተሾመች ሴት ያወራል። ስሟ ከሶስቱ ህፃናት መካከል ከታላቂቱ ጋር ተመሳሳይ ነው። ሆኖም ያቺ ከሃያ ሁለት ዓመት በፊት ያየኋት ልጅ ከዚህ ታላቅ ሥልጣን ትደርሳለች የሚል ግምት ባይኖረኝም ለማንኛውም በዚያም በኩል ቢሆን ጥናት ብታካሄድ» አለ ፓተርሰን። በታይምስ ጋዜጣ ላይ የወጣውን ዜና ካገኘ ጥቂት ሳምንታት አልፏል፡ ሂላሪ ምከር የሚለው ስም ከፎቶግራፉ ጐን በትላልቅ ፊደሎች ተፅፏል። እንደ ሌሎቹ የጋዜጣ ፎቶግራፎች ሁሉ ይህኛውም ደብዛዛ በመሆኑ ካያት ከሃያ ዓመት በላይ የሆናትን ልጅ መልክ ለመለየት ተቸግሮ ነበረ። ቢሆንም የጋዜጣውን

ቁራጭ ከሰጠው በኋላ “እንግዲህ ቻፕማን አደራህን እነኛን ሶስት ልጆች እንደ ምንም ብለህ እንድትፈልግልኝ” አለው:: ልጆች የተባሉት በፓተርሰን እስተሳሰብ እንጂ ቻፕማን ዕድሜአቸውን በአእምሮው እንዳሰላው ሶስቱም ወደ ሙሉ ሴትነት የተቃረቡ ነበሩ:: ትልቋ ሰላሳ ዘጠኝ፣ መካከለኛዋ ሰላሳ እምስት፣ ትንሿ ደግሞ ሰላሳ አንድ ዓመት ይሆናሉ:: ቻፕማን እንደ ተጠራጠረውም ፓተርሰን ቀጠል በሚያደርግ “የሁለቱ ህፃናት የጉዲፈቻ ወላጆች ኒውዮርክን ከለቀቁ ብዙ ዓመታት አልፏል:: ወዴት እንደሄዱም የማውቀው ነገር የለም... ታገኛቸዋለህ የሚል ተስፋ ግን አለኝ” አለው::

“እሞክራለሁ!” አለ ቻፕማን የጋዜጣውን ቁራጭ ከፋይሉ ውስጥ ከነበሩት ሌሎች ወረቀቶች ጋር እያያዘ:: ከዚያም ቀና አለና “ቢቀናኝና ባገኛቸውስ?” ሲል ለፓተርሰን ጥያቄ አቀረበለት::

“በቅድሚያ ትክክለኛ አድራሻቸውን ካረጋገጥህ በኋላ ለእኔ ታስታውቀኛለህ:: ከዚያም ማንነታቸውን ታስረዳቸውና እኔም የወላጆቻቸው ጓደኛ እንደ ነበርኩና የተለያዩት እህትማማቾች እንዲገናኙ ማቀዴን ትገልፅላቸዋለህ:: ተገናኝተው የሚተዋወቁትም በኮኔክቲከት በሚገኘው በእኔ የገጠር መኖሪያ ቤት ውስጥ ይሆናል:: ቦታውንም መወሰኔ ከእንግዲህ እንደልብ ከሰፍራ ሥፍራ መንቀሳቀስ እንደማልችል ስለማውቀው ነው:: ስለዚህ ሶስቱም እዚያ ቤት ድረስ መምጣት ይኖርባቸዋል::”

“ፈቃደኛ ባይሆኑስ?” ሲል ቻፕማን ያልተጠበቀ ጥያቄ አቀረበ:: ቻፕማን ይህንን ጥያቄ ያነሳው በግል ልምዱ ያካበታቸውን አንዳንድ ሁኔታዎች በማስታወስ ነበረ::

“ልታሳምናቸው ይገባል!” አለ ፓተርሰን::

“በተለይ ትንንሾቹ ሁለቱ እህት ይኑራቸው አይኑራቸው ለማስታወስ አይችሉም ይሆናል:: አዲስ ሕይወት በመምራት ብዙ ዓመታት ካሳለፉ የተለያየ ቤተሰብ ከመሰረቱ በኋላ ኑ ከእህቶቻችሁ ጋር ተገናኙ ቢባል በዚህ ባልተጠበቀ ዜና ከሚደርስባቸው ድንጋጤ ባሻገር በማህበራዊ ኑሯቸው ውስጥ አንዳንድ ቀውስ ሊያስከትልባቸውም ስለሚችል ፈቃደኛ ላይሆኑ ይችላሉ” አለ ቻፕማን:: እርግጥ ፓተርሰን በውርስ ሊተውላቸው የሚችል ንብረት እንደሚኖር ቻፕማን አልተጠረጠረም ነበረ::

“እህትማማቾቹን መልሶ የማገናኘት ኃላፊነት አለብኝ:: በግዴታ እንዳለያየኋቸው ሁሉ በተገኘው ዘዴ ሁሉ በመጠቀም ላሰባስባቸው ይገባል:: ጥፋቱ የእኔ ነው ... ሶስቱንም ለማሳደግ ፈቃደኛ የሚሆን ቤተሰብ መፈለግ ነበረብኝ:: ያለፈው አለፈ:: ያም ሆኖ አሁን ስለ ደህንነታቸው ለማወቅ





እፈልጋለሁ:: የገንዘብ እጥረት እንደሌለባቸውም ማረጋገጥ ይኖርብኛል:: ወላጆቻቸውም ለዋሉልኝ ውለታ ቢያንስ ቢያንስ በከፊል እንኳ ለልጆቻቸው መክፈል አለብኝ::”

ቻፕማን 'ዱሮ ቀረ' ሲል ሊናገረው ፈልጎ ነበረ:: እውነትም አሁን የሰላሳ ዘጠኝ፣ የሰላሳ አምስትና የሰላሳ አንድ ዓመት ዕድሜ ያላቸውን እህትማማቾች ማገናኘት ምን ትርጉም ይኖረዋል? እርስ በርስ ተረሳስተዋል:: እህትም ይኑራቸው አይኑራቸው የሚያውቁት ነገር ላይኖር ይችላል:: ስለዚህ 'የፓተርሰን ጥበብ ከምኑ ላይ ነው?' ሲል ቻፕማን በሐሳቡ ያወጣና ያወርድ ነበረ::

ከቻፕማን ሁኔታ ተስፋ ወደ መቁረጡ የተቃረበው ፓተርሰን “እና ልጆቹን ልትፈልግልኝ ፈቃደኛ ነህን?” ሲል በማባበል ጭምር ጠየቀው::

“እሞክራለሁ” አለ ቻፕማን::

“ፍለጋውን እራስህ እንደምታካሄደው ቃል ትገባልኛለህ?”

በአብዛኛው እኔው ራሴ እፈፅመው ይሆናል:: ሆኖም ቃል ከመግባቴ በፊት በየፋይሉ ውስጥ የሰፈሩትን ፅሑፎች ማንበብ ይኖርብኛል:: በተጨማሪም በተለያዩ ግዛቶች ወኪሎች ስላሉኝ በእነርሱ መጠቀሙም የሚሻልበት ጊዜ ሊኖር ይችላል::

ፓተርሰን በቻፕማን መልስ እረክቷል:: ሆኖም የርሱ ፍርሃት ሌላ ነበረ:: ስለዚህም “ምናልባትም ፋይሉ ውስጥ የምታገኘው መረጃዎች እምብዛም ጠቀሜታ ሊኖራቸው ስለማይችል በእነርሱ ላይ እንድታተኩር ለማለት ነው” አለ::

“ግድ የለም! ችግር እንዳለ ስለሚገባኝ የአመለካከቴን አድማስ ሰፋ አደርገዋለሁ” አለና ከፓተርሰን ጀርባ ከነበረው ግርግዳ ላይ ተሰቅሎ ወደ ነበረው ሰዓት አየት አደረገ:: ቻፕማንን ለማነጋገር ተራ የሚጠብቁ ብዙ ሰዎች መኖራቸው ለፓተርሰን የታወሰው ያንጊዜ ነበረ::

“ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው” አለ ፓተርሰን ከመቀመጫው የግዱን እየተነሳ::

“የተቻለኝን ሁሉ እንደማደርግ ይመኑኝ” አለ ቻፕማን እየደገፈው:: “በተጨማሪም ሴቶቹን ለማግኘት የሚደረገው ክትትል ከፍተኛ ወጪ ሊጠይቅ እንደሚችልም ሊያውቁት ይገባል” ሲል በተጨማሪ አሳሰበው::

"ያለኝን ሐብት ሁሉ ለዚህ ዕቅድ ብቻ ላውለው ነው ፍላጐቴ ግልፅ ሆነልህ ቻፕማን?" አለና የተጨማደደ ፊቱን ፈካ ለማድረግ ሞከረ፡፡

ቻፕማን በመልሱ ፈገግታ እያሳየው መኪናው ድረስ ደግፎ አደረሰው፡፡ ስለጉብኝቱም አመስግኖት በትሕትና ከሸኘው በኋላ ወደ ቢሮው ተመለሰ፡፡ አንገቱን እንዳቀረቀረም ነበረ፡፡ ፓተርሰን ያጫወተው ታሪክ አእምሮውን ጨምድዶት ነበረ፡፡ 'ፓተርሰን ሕፃናቱን በመለያየቱ ሌላም ተጨማሪ በደል በዚያ ቤተሰብ ላይ አድርሶ ይሆን?' የሚለው ጥያቄ ነበረ በተለይ በህሊናው ደጋግሞ የደወለው፡፡

የዕለቱን ሥራ ጨርሶ የሔደው ቀጥታ ወደ መኖሪያ ቤቱ ነው፡፡ ምሽቱን ያሳለፈው ፓተርሰን ባመጣው ፋይል ውስጥ የነበሩትን ፅሑፎች በማንበብ ነበረ፡፡ ምከር ሶላንጅን በገደለበት ወቅት በተለያዩ ጋዜጦች ወጥተው የነበሩትን ዜናዎች አንድ በአንድ አነበባቸው፡፡ ለተፈፀመው ወንጀል መንስኤ ነው ሊባል በግልፅ የሰፈረ እንዳችም ምክንያት የለም፡፡ ቻፕማን ደግሞ በወንጀል ምርመራ ሙያ ላይ ተሰማርቶ ብዙ ሚስጥሮችን ፈልፍሎ ያወጣ ሰው ነበረ፡፡ ስለሆነም አንድ ወንድ ያውም የሚያፈቅራትን ሚስቱን ያለምክንያት እንደማይገድል ያውቀዋል፡፡ ታዲያ ምከር ለምን ሶላንጅን ገደላት? በላይዋ ላይ ሌላ ሴት አፍቅሮ ሊያስወግዳት በመፈለጉ? ወይንስ ራሱ ቅናት አድሮበት ይሆን? ሶላንጅ ምን ጥፋት ሰርታ ይሆን? ፓተርሰን የጠየቀው ሶስቱን የጠፉትን የነሶላንጅን ልጆች እንዲፈልግለት ቢሆንም አእምሮው ላነሳቸው ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ተጨነቀ፡፡ በፋይሉ ውስጥ ያገኛቸው ሌሎችም የጋዜጣ ቁርጥራጮች ስለ ምክር ታላቅ ተዋናይነት ስለ ሶላንጅ ቁንጅና ለባሏና ለልጆቿ ስለነበራት ፍቅር... ይህን ስለመሳሰሉት ያወራሉ፡፡ አልፎ አልፎ ግን መልከ መልካሙ ምክር ከአንዳንድ ሴቶች ጋር የተነሳቸው ፎቶግራፎችና በዚያም ሳቢያ የተፃፉ አንዳንድ ሐተታዎች ነበሩ፡፡ እነኚህም ቢሆኑ ባልን በሚስት ላይ እስከዚያ ሊያስጨክኑ የሚችሉ ምክንያቶች አሳዘሉም፡፡

ቻፕማን ማንበቡን ቀጠለ፡፡ ከፊት ለፊቱ በፓተርሰን የሚንቀጠቀጥ እጅ የተፃፈ አጭር ማስታወሻ ነበረ፡፡ አጠር አጠር በማድረግ ያሰፈረው ማስታወሻ የሚጀምረው አርሱና ምከር በሰሜን አፍሪካ የጦር ሜዳ እንዴት ለመተዋወቅ እንደበቁ በመግለፅ ነው፡፡ ከዚያም በሲሲሊ ደሴት በኔፕልስ ከተማ አካባቢና የሮምን ከተማ ለመያዝ በተደረጉት ጦርነቶች ሳይለያዩ እንደተዋጉና ምከር ከአንድም ሁለት ጊዜ ከሞት እንዳዳነው ፓተርሰን በፅሑፉ ላይ ይዘረዝራል፡፡ በተለይም ፓሪስ ደርሰው በደ.አርኮል ጎዳና ላይ ሶላንጅን ካዩዋት ጊዜ ጀምሮ ያለውን ታሪክ ያሰፈረበት ቋንቋ





ውበት የተለየ ነበረ፡፡ የሶላንጅን ትላልቅ አረንጓዴ ዓይኖች፣ የሶላንጅን ወርቃማ ፀጉር፣ የሶላንጅን ሸንቃጣ ቅርፅ፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ የሶላንጅን መንፈስ ጠንካራነት አጉልቶ ያሳያል፡፡ ያቺን በጀርመን ወታደሮች እንኳን ሳትደፈር የቆየች ልጃገረድ ምከር እንዴት ሊያሸንፋት በመጨረሻም ሊያገባት እንደቻለ ያወራና መደምደሚውን የሶላንጅንና የምከርን ሞት ያደርገዋል፡፡

በሚቀጥለው ምዕራፍ ውስጥ ፓተርሰን ስለ ሶስቱ ህፃናት ልጆቻቸው መተረክ ይጀምራል፡፡ ሂላሪ የተባለችው ትልቋ ልጅ ለአባቷ ታላቅ እህት ለኢሊን ተሰጥታ ነበረ፡፡ ኢሊን ያን ጊዜ ጆንስ የሚባል መርከበኛ አግብታ በቦስቶን ከተማ በቻርልስተን ታወን ቀበሌ ትኖር ነበረ፡፡ ከስምንት ዓመታት በኋላም ሂላሪ የእህቶቿን አድራሻ ለመጠየቅ ከፓተርሰን ቢሮ በመጣችበት ወቅት ከቦስቶን ወደ ጃክሰንቪል ከተማ መሄዳቸውን፣ አሳዳጊ በሌላቸው ልጆች መጠለያ ቤት ውስጥ መቆየቷንና በመጨረሻም በጠባይ ማረሚያ ተቋም መግባቷን እንደነገረችው በማስታወሻው ላይ አስፍሯል፡፡ የእህቶቿንም አድራሻ ሊነግራት ባለመቻሉ ከምሬቷ የተነሳ እንዴት እንደረገመችውና ዳግመኛም ዓይኑን ለማየት እንደማትሻ በጠንካራ ቃላት የተናገረችውን ሁሉ ፅፏል፡፡ ቻፕማን ለጊዜውም ቢሆን ከዚህ ፅሁፍ ከአንድ መደምደሚያ ላይ ለመድረስ ችሎ ነበረ፡፡ በቅድሚያ ሂላሪ ከጠባይ ማረሚያ ተቋም ለመግባት ከበቃች ጠባየ ጥፉ ልጅ መሆን አለባት፡፡ ይህም ማለት ከአደገች በኋላ በቀላሉ ሌላ ወንጀል ፈፅማ እንደኛው እስር ቤት ውስጥ ትገኛለች ማለት ነው፡፡ ስለዚህ በመላው አሜሪካ በሚገኙት ወህኒ ቤቶች ስልክ በመደወል በጥቂት ቀናት ውስጥ ለማጣራት ይቻላል፡፡ የሂላሪን አድራሻ ማግኘቱ ከባድ እንደማይሆንበት ለቻፕማን ተሰማው፡፡

ስለ ሁለተኛዋ ህፃን የተፃፈውን ማንበቡን ቀጠለ፡፡ የአሌክሳንድራ የጉዲፈቻ አባት ጐርሐም የሚባል ጠበቃ ነበረ፡፡ ጐርሐም በዕድሜው የገፋ ሰው ስለነበረ ከጉዲፈቻው ሥነሥርዓት በኋላ ብዙም ሳይቆይ በመሞቱ በዕድሜ ከርሱ በጣም ታንስ የነበረችው ማርጋሬት የምትባል ሚስቱ ህፃኗን ይዛ ወዴት እንደ ደረሰች አይታወቅም፡፡ ምናልባት የማርጋሬትን አድራሻ ለማፈላለግ የሚኖረው ተስፋ አንድ ብቻ ይሆናል፡፡ የጐርሐምን ሐብትና ንብረት በአደራ የሚያስተዳድር ድርጅት ካለ ማርጋሬት ከድርጅቱ ጋር መፃፃፉ ስለማይቀር ከዚያ በማጠያየቅ አድራሻዋን የማግኘት ዕድል ሊገጥመው ይችላል፡፡ የህፃኗ በሕይወት እስከዛሬ መኖር አለመኖር ግን በሁለተኛ ደረጃ የሚነሳ ጥያቄ ይሆናል፡፡

የሁለቱም ታናሽ የሆነች ሚጋን የጉዲፈቻ አባት አድራሻ ግን ደብዛው ጠፍቶ ነበረ:: መጀመሪያውንም ቢሆን የሚጋን የጉዲፈቻ አባት ዴቪድ ለፓተርሰን ግልፅ የሆነ አቋሙን ነግሮት ነበረ:: ሚጋን አራስ ልጅ በመሆኗ ስለ ወላጆቿ ምንም ትዝታ አይኖራትም:: ስለዚህ ዴቪድንም ሆነ ሚስቱን ሬቤካን እንደ እውነተኛ ወላጆቿ ትቆጥራቸዋለች ማለት ነው:: ስለዚህ ከፓተርሰን ጋር ምንም ዓይነቱ ግንኙነት እንዲኖራቸው አይፈልጉም:: የኒውዮርክን ከተማ ወዲያውኑ ለቀው ወደ ካሊፎርኒያ የሄዱትም ለሚጋን ሲሉ ነው የሚል ጥርጣሬ እንዳለበት ፓተርሰን ጠቁሟል:: ሚጋን የጉዲፈቻ ልጅ መሆኗ በማይታወቅበት አካባቢ ብታድግ ይበልጥ ጤናማ የሆነች ህፃን እንደሚወጣት የማይጠረጠር ነው:: ስለዚህ እነ ዴቪድ ወደ ካሊፎርኒያ ግዛት ከሄዱበት ዕለት ጀምሮ ተሰወሩ ለማለት ይቻላል::

ቻፕማን በመጨረሻ ላይ ያነበበው ፓተርሰን ከታይምስ ጋዜጣ ላይ ቆርጦ የያዘውን ዓምድ ነበረ:: በስመ ሞክሼ ካልሆነ በስተቀር የወጣትነት ዕድሜዋን በፀባይ ማረሚያ ተቋም ውስጥ ያሳለፈች ልጅ ከፍተኛ ውድድር ለሚጠይቀው ለአንድ ሀገር አቀፍ የዜና አገልግሎት ድርጅት ሥራ አስኪያጅነት ትበቃለች ብሎ ለመገመት ለቻፕማንም ተስኖታል:: እርግጥ 'ሂላሪ ምክር' የሚለው ስም በጋዜጣው ዓምድ ላይ በትልልቅ ፊደሎች ተፅፏል:: ፎቶግራፍም አብሮ ወጥቷል:: ግን ያቺ የምክርና የሶላንጅ ልጅ ሂላሪ፣ ሥቃይና መከራ የተፈራረቀባት ሂላሪ ለዚያ ደረጃ ትደርሳለች ሲል ፓተርሰንም ቢሆን በህልሙም በውኑም አላመነም:: ፎቶግራፉም እርሱ የሚያውቃት የክርስትና ልጁ የነበረችው የዚያች የሂላሪ አልመስል ብሎታል:: ግን ይቺ ጋዜጣ ላይ የወጣችው ሴት እውነትም የነአክሲና የነሚጋን እህት ሂላሪ ከሆነች በቀላሉ ተገኘች ማለት ነው:: ከምትሰራበት ድርጅት ስልክ በመደወል ያለ ችግር ለማረጋገጥ ይቻላል:: ግን በወንጀል ምርመራ ላይ ከፍተኛ ልምድ ላለው ቻፕማን አልመስል አለው:: የተደበቀን ሚስጥር አነፍንፎ የማወጣት ብቃት ላለው ቻፕማን የታየው የመነመነ ተስፋ ነበረ::

ያም ሆኖ ቻፕማን የፓተርሰንን ጥያቄ በቀላሉ አልወሰደውም:: ያለውድ በግዴታ እንዲለያዩ የተደረጉት እህትማማቾች ታሪክ ከመጠን በላይ አሳዝኖታል:: ምክንያቱን እንዲህ ነው ብሎ ለመናገር ባይችልም በተለይ የሂላሪ ታሪክ አንጀቱን አላውሶታል:: ስለዚህም በቅድሚያ ሂላሪን ለማግኘት ነበረ ዕቅዱ:: ፓተርሰን በቻርልስተን ታወን ከኢሊን ጋር አንድ ትኖር ከተዋት በኋላ ለምን ወደ ጃክሰንቪል እንደ ሄደች ምን እንደ ደረሰባት





የሚታወቅ ነገር የለም:: ከብዙ ዓመታት በኋላም ወደ ኒውዮርክ ተመልሳ ፓተርሰን እህቶቿን የት እንዳደረሳቸው እንዲነግራት ከጠየቀችበት ዕለት ወዲህ ላሉት ዓመታት ምን ውሃ እንደ በላት አይታወቅም:: እርግጥ ከጥቂት ሳምንታት በፊት 'ሂላሪ ምክር' የሚለው ስም በተለያዩ ጋዜጣዎች ላይ ታይቷል:: ግን በአሜሪካ ውስጥ ብዙ ሂላሪ ምክሮች ሊኖሩ ይችላሉ:: እና የጋዜጣዋ ሂላሪ ምክር የፓተርሰኗ ሂላሪ ምክር ትሆናለች ብሎ ለመጠርጠር ለቻፕማን ብሩህ አእምሮ ተስኖት ነበረ::

# ምዕራፍ ፲ስራ አራት

ቻፕማን ከቢሮው የደረሰው ጹጠዋቱ የሥራ መግቢያ ሰዓት በፊት ነበረ። በሳምንቱ መጨረሻ ላይ ወደ ቦስቶን የመሄድ ዕቅድ ስለነበረው በቅድሚያ አንዳንድ ጉዳዮችን ማጠናቀቅ ነበረበት። ከሁሉም በፊት ግን የጋዜጣዋን ሂላሪ ምከርን ለማነጋገር ፈለገ። ለማንኛውም መሞከሩ አይከፋም ነበረ። ስለምን ሩቅ ከመሄድ እዛው አፍንጫው ስር ሊያገኛት ይችል ይሆናል። ሰዓቱን ተመለከተ። ሶስት ሰዓት ከሩብ ገደማ ነው ስልኩን አንስቶ ወደ ማዞሪያ ደወለና የሂላሪ ምክርን ስልክ ቁጥር ጠየቀ። እንዳገኘም ወደ ሂላሪ ቢሮ ደወለ።

"እባክሽ እመቤት ሂላሪ ምከርን ብታገናኚኝ?" ሲል ልዩ ፀሐፊዋን ጠየቀ። ከንፈሩም በመድረቁ በመጠኑም ቢሆን ሳይገረም አልቀረም። የሶስቱ እህትማማቾች ጉዳይ እጅግ እያሳሰበው በመሄድ ላይ ለመሆኑ ግልፅ ነበረ።

"ስምዎን ቢነግሩኝ?" አለች ፀሐፊዋ።

"ጆን ቻፕማን እባላለሁ። የቻፕማን የወንጀል ምርመራ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ ነኝ። ምናልባት እመቤት ሂላሪ ላታውቀኝ ትችላለች። ግን ላናግራት የፈለግኩት ሰጥብቅ ጉዳይ ስለሆነ እባክሽን እንደምንም ብለሽ ብታገናኚኝ?" አለ ቻፕማን።

"ጥቂት ቢጠብቁኝ" አለችው። ከዚያም በኢንተርኮም ሂላሪን አነጋገረቻት። ሂላሪ ጆን ቻፕማን የሚለውን ስም ሰምታ አታውቅም። በተጨማሪም በአራት ሰዓት ላይ ሰጠራችው የአስተዳደር ጉባኤ አንዳንድ ቅድመ ዝግጅት ማጠናቀቅ ነበረባት። እና ሂላሪ ሰአልባሌ ጉዳዮች የምታ ጠፋው ጊዜ አልነበራትም።

"በሌላ ጊዜ ይደውል" ብላ ትዕዛዝ ካስተላለፈች በኋላ ወዲያውኑ ሐሳቧን በመቀየር "ግዴለም እስቲ ላነጋገረው" አለች። ፀሐፊዋ እንዳገናኘቻትም "ሂላሪ ምክር ነኝ። ለምን ነበር የተፈለግኩት?" አለች ረጋ ባለና የደስ ደስ ባለው ድምፅ።





ቻፕማን ከሂላሪ አነጋገር የተረዳው ነገር ነበረ። በጨዋ ቤተሰብ ያደገችና ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ያላት እንጂ በጠባይ ማረሚያ ውስጥ ለዓመታት የቆየች የፓተርሰኗ ሂላሪ ልትሆን ትችላለች የሚለው ጥርጣሬው ከመቅፅበት በነነ። ሆኖም አንድ ጊዜ ጀምሮታልና የጥሪውን ምክንያት መግለፅ ነበረበት።

"ልታነጋግሪኝ ፈቃደኛ በመሆንሽ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው። ጊዜሽን እንዳላባክን ስል ቀጥታ ወደ ፍሬ ነገሩ አመራለሁ። ጆን ቻፕማን እባላለሁ። የቻፕማን የወንጀል ምርመራ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ ነኝ። ሂላሪ ምከር በሚል ስም የምትጠራ ሴት እየፈለግሁ ነበረ። አባቷ ሳም ምከር እናቷም ሶላንጅ ይባላሉ። ከኒውዮርክ ወደ ቦስቶን ተወስዳ ኢሊን ከምትባል አክስቷ ጋር ትኖር ነበረ። ያቺ ሂላሪ ምከር ምናልባት አንቺ እንደሆንሽ ስል ነው ስልክ የደወልኩት እመቤት" አለ። የሂላሪ ፊት ሲለዋወጥ አለማየቱ እንጂ ቻፕማን በዚያን ጊዜ ምን ይል እንደነበረ ለመገመት ያዳግታል። በድንጋጤ ክው ብላ የቀረችው ሂላሪ ከራስ ፀጉሯ እስከ እግር ጥፍሯ ትንቀጠቀጥ ነበረ። ከፊቷ የነበረውን ጠረጴዛ በአንድ እጇ ጨምድዳ ይዛ ደገፍ ብላ ቆየች።

'አይደለሁም' ብላ ነገሩን በአጭሩ ለመቅጨት ፈልጋ ነበረ። ሆኖም በሌላ በኩል ደግሞ የተፈለገችበትን ምክንያት ለማወቅ ጓጓች።መቼም እነኛ ከሰላሳ ዓመታት በፊት የተለይዋት እህቶቿ አስታውሰዋት ሊፈልጓት እንደማይችሉ ግልፅ ነው። አንድ ሰው ብቻ ... ያ ዳግመኛ ልታነጋግረው ቀርቶ ልታየው እንኳን የማትፈልገው... ያ እህቶቿን የነጠቃት ፓተርሰን ብቻ ነው። ስለ ሳም ምከርና ሶላንጅ የሚያውቀው። ፓተርሰን ... ያ ጨካኙ... ያ አረመኔ... ያ እርጉም...

"አንተ ያልካት ሂላሪ ምከር ባልሆንም ስለምን ነበር የፈለግካት?" ስትል በተረጋጋ ድምፅ ጠየቀችው።

"አንድ ሰው በስም ተጠቃሿን እንድፈልግለት አደራ ስላለኝ ነበረ። ስለአንቺም ሹመት በቅርቡ በታይምስ ጋዜጣ ላይ የወጣውን ዜና በማየቱ ምናልባት እርሱ የሚፈልጋት ሂላሪ ምከር ትሆኛለሽ ሲል ጓጉቶ ነበረ። ግን ግምቱ ትክክል አለመሆኑን አሁን ለመረዳት በመቻሌ ጊዜሽን በከንቱ ስላባከንኩብሽ ይቅርታ እጠይቅሻለሁ" አላት። ረጋ ያለው አነጋገሯና የድምፅ አለባበሯ ነበረ ቻፕማንን ለዚህ እምነት ያደረሰው።

"ልረዳህ ባለመቻሌ የሚሰማኝ ሐዘኔታ የጠለቀ ነው፤ ሚስተር ቻፕማን" አለችው፡ ድምጿን አሁንም ረጋ ያለና እንደውሃ የሚፈስ በመሆኑ

ለጥርጣሬ እንኳን ፍንጭ የሚሰጥ አልነበረም::

"ስላደረግሽልኝ ትብብር በጣም አመሰግናለሁ እመቤት"

"ምንም አይደል" ብላ ስልኩን ዘጋችው:: ቻፕማንም የስልኩን መነጋገሪያ ቀስ ብሎ አስቀመጠ:: ተስፋም ቆርጦ ነበረ:: ግን ከርሱ ቢሮ ባሻገር ካለው ሌላ ቢሮ ውስጥ ተቀምጧ ትንቀጠቀጥና ፊቷ ተለዋውጦ የነበረችውን ሂላሪን ባየ ኖሮ ምን ይል ይሆን? ያ የስልክ ጥሪ ለሂላሪ ከመናፍስት ዓለም የተደወለ ነበረ የመሰላት:: ይሆናል ብላ ፍፁም ያልገመተችው ነገር ነው:: ሆኖም ማን እንደሚፈልጋት ያሰጥርጥር አውቃዋለች:: ከመሞቱም በፊት ይቅርታ ሲጠይቃት እንደሆነም ተሰምቷት ነበረ:: ሂላሪ ግን ይቅርታ ልታደርግለት አልፈለገችም:: እንደ ክርስትና አባትነቱ ለርሷም ሆነ ለእህቶቿ የዋለላቸው አንዳችም ውለታ አልነበረም:: ስለዚህ ከነፀፀቱ ወደ መቃብሩ ውስጥ ቢገባ ምርጫዋ ሆነ::

ስብሰባ የጠራችበት አራት ሰዓት ደርሶ ወደ አዳራሹ ስትገባ ሰውነቷ እንደ ተለዋወጠ ነበረ:: የፓተርሰን ጭካኔ በማስታወሷና የእህቶቿም ትዝታ ውልብ እያለባት ስበሰባውን መርታ የጨረሰችው እንደነገሩ ነው:: "ቆፍጣናዋና ጠንቃቃዋ ሂላሪ ዛሬ ምን ነካት?" ሲሉ የስብሰባው አባሎች በሆዳቸው ሳይታዘቧት አልቀሩም::





# ምዕራፍ አስራ አምስት

ቻፕማን ተስፋ በመቁረጥ ዓይኖቹን በጣሪያው ላይ ሰክቶ ለብዙ ጊዜ ሲያስብ ቆየ:: የጋዜጣዋ ሂላሪ ምክር እርሱና ፓተርሰን የሚፈልጓት ሂላሪ ምክር አለመሆኗን አምኗል:: በረጅሙ ተነፈሰና በእጁ ይዞት የነበረውን የጋዜጣ ቁራጭ ከፋይሉ ውስጥ ከቶ ማሰቡን ቀጠለ:: ከዚያም አንድ ሐሳብ ብልጭ አለበት:: ወደ ቦስቶን ከተማ ሄዶ እነ ኢሊን ይኖሩበት ከነበረው ከቻርልስተን መንደር በመነሳት ስለ ሂላሪ ክትትሉን ለመጀመር ወሰነ::

ምናልባት ከተፈለገ የሚገኝበትን አድራሻ ለልዩ ፀሐፊዋ ከተናገረ በኋላ የቦስቶን ጉዞውን ጀመረ:: እንደ ደረሰም ፓተርሰን ከሰጠው ፋይል ውስጥ የኢሊንን ቤት አድራሻ አረጋግጦ ወደ ቻርልስተን መንደር አመራ:: ያ ዕድገት የማይታይበት መንደር አሁንም ከአርባ ዓመታት በፊት የነበረውን ገፅታ እንደያዘ ነው:: ለህፃኗ ሂላሪ ዓይኖች የቀፈፉት የዚያ መንደር ቤቶች በአሁኑ ጊዜ ምን እንደሚመስሉ መገመቱ አያዳግትም:: ግርግዳዎቻቸው ዘመዋል፣ ቀለማቸው ተቅረፍርፏል፣ ደረጃዎቻቸው ተሰባብረዋል:: ስለ ዓይጥ ጉሬነታቸውም ቢሆን የሚያጠያይቅ አልነበረም:: ቀስ ብሎ ይነዳት የነበረውን መኪናውን ከነኢሊን ቤት ፊት ለፊት አቁሞ ወረደ:: በጠባቧም የእግር መንገድ አድርጎ ወደ በራፉ ተቃረበ:: ግቢውን አረም ውጦታል:: በሩም የቆመው በቋፍ ነበረ:: በአንድ ወቅት ሂላሪና እህቶቿ በዚያ ቤት ውስጥ መኖራቸው ታውሶት ተገረመ::

ደረጃውን ረጋ ብሎ ወጣና ሲፈራ ሲቸር በሩን ቀስ ብሎ አንኳኳ:: የኤሌክትሪክ ደውሉ የኮረንቲ ሽቦ ተበጥሶ ከግርግዳው ላይ መንጠልጠሉን ቀደም ሲል አይቶታል:: ከቤቱም ውስጥ ድምፅ ቢሰማውም በሩ የተከፈተለት ብዙ ከቆየ በኋላ ነው:: ጥርሶቿ ወልቀው ያለቁ አንዲት አሮጊት ሴት በሩን ገርበብ አድርጋ በጥርጣሬ እያየችውና ምን እንደሚፈልግ ጠየቀችው::

"ኢሊንና ጆንስ ስለሚባሉ ባልና ሚስቶች አንዳንድ ለማወቅ የምፈልጋቸው ጉዳዮች ነበሩኝ:: ከብዙ ዓመታት በፊት በዚህ ቤት ውስጥ

ይኖሩ ነበረ:: ምናልባት ያውቋቸው ይሆን?" ሲል ድምፁን ከፍ አድርጐ ጠየቃት:: ከሁኔታዋ እንደ ተረዳው የመስማት ችግር እንዳለባት ገምቶ ነበረ::

"ስማቸውን ስላነሳኸው ባልና ሚስት ሲወራ ሰምቼ አላውቅም:: ድንገት ከማዶው ቤት ውስጥ የሚኖረው ቻርሊ ሊረዳህ ይችል ይሆናል:: ከሁለተኛ ዓለም ጦርነት ጀምሮ እዚሁ መንደር ውስጥ ስለመኖሩ ሲወራ ሰምቻለሁ:: ስለዚህ እርሱ ያውቃቸው ይሆናል" አለችው::

ቻፕማን ስለ ትብብሯ አመሰገንና ወደ ቤቱ ውስጥ አየት አደረገ:: ባየውም አዘነ:: እንደውጪው ሁሉ የውስጥ ግርግዳው ቀለም የተሳሳጠ ነበረ:: የቤት ዕቃዎቹም ከአገልግሎት ብዛት የተሰባበሩ ናቸው:: 'የነሂላሪም ጊዜ ቤቱ እንደ አሁኑ ይሆን ይሆን?' ሲል ራሱን ጠየቀ:: ለሂላሪም ሲል 'የለም ያን ጊዜ የተሻለ መሆን ይኖርበታል' ሲል ተመኘ:: ግን እንደማይሻል ማንም የሚገምተው ነው::

"በጣም አመሰግናለሁ" ብሎ ፈገግ አለና በድጋሚ ተሰናበታት:: ከዚያም አሮጊቷ ወደ አሳየችው ቤት መንገዱን አቋርጦ ሄደ:: ቻርሊ ያለችውም ሰው ከበረንዳው ላይ ተቀምጦ ፒፖ ያጨስ ነበረ:: ቻፕማን ገና ደረጃውን በመውጣት ላይ እንዳለ ሽማግሌው ቻርሊ ከተቀመጠበት ተነስቶ በአክብሮት ተቀበለው::

"ባልሳሳት ሚስተር ቻርሊ ይመስሉኛል!" አለ ቻፕማን ፈገግታ እያሳየው::

"አዎን! እኔ ነኝ ቻርሊ የምባለው! ምን ልረዳህ እችላለሁ?" አለው ሽማግሌው ሰውዬ እጁን ለመጨበጥ እየዘረጋ::

"በቅድሚያ ስሜ ጆን ቻፕማን ይባላል" ብሎ ከሽማግሌው ጋር ራሱን ካስተዋወቀ በኋላ ወደነ ኢሊን ቤት እያመለከተ "በዚያ ቤት ውስጥ ከብዙ ዓመታት በፊት ይኖሩ ስለነበሩ ባልና ሚስት የሚያውቅ ሰው ባገኝ አንዳንድ ጥያቄዎች ለማቅረብ እፈልግ ነበረ:: ሴትየዋ ኢሊን ባሏ ደግሞ ጆንስ ይባላሉ:: ድንገት ጌታዬ እነኚህን ሰዎች ያስታውሷቸው ይሆን?" አለ በታላቅ ትህትና::

"በሚገባ አስታውሳቸዋለሁ:: ጆንስና እኔ በመርከበኝነት ተቀጥረን እንሰራ ነበረ:: ታዲያ ባልና ሚስቱ ሁለቱም ሰካራሞች ነበሩ:: በኋላም ሴትየዋ ለሞት የበቃችው በመጠጥ ጦስ ነው እየተባለ ሲወራ ሰምቻለሁ:: ያን ጊዜ እኔ ባለትዳርና የስድስት ህፃናት አባት ነበርኩ..."





"ልጆች ነበሩዎት ማለት ነው?" አለና ቻፕማን አቋረጠው::

"አዎን! አሁን ግን ሁሉም አዋቂዎች ሆነዋል:: ሚስቴ እንኳን ከሞተች ዘንድሮ አስራ አራት ዓመት መሆኑ ነው:: ሁሉም ልጆቼ ሥራ ይዘዋል ..."

"ዕድለኛ ነዎት! ይቅርታ ያድርጉልኝና ስለ ህፃናት ከተነሳ ዘንዳ ከሰላሳ ዓመት በፊት ኢሊን የምታሳድጋቸው ሶስት ህፃናት ነበሩ:: አባባሌን ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ ትልቋ የዘጠኝ ዓመት፣ መካከለኛዋ የአምስት ዓመትና ትንሽቱ ደግሞ የዓመት ልጆች ነበሩ:: ምናልባት ያስታውሷቸው ይሆን?"

"ኢሊን መቼ ወለደችና ነው ልጅ የምታሳድገው? ባልና ሚስቱ ሰመጠጥ ይበሏቸው እንጂ መቼ ለዚህ ዓይነቱ ወግ ማዕረግ በቁና? በየዕለቱ እንደተደባደቡ፣ እኛም ፖሊስ መጥራቱ እንዳለሰቸን ነበረ:: እንዳ ውም ሴቲቱ በመጠጥ ጠንቅ ሞተች ተብሎ ይወራ እንጂ ባሏ ሳይሆን አይቀርም የገደላት የሚል ጥርጣሬ አለኝ..." እነኚህን ለመሰለ ባልና ሚስት ሶስት ህፃናትን እንዲያሳድጉ መስጠት ትልቅ ስህተት መሆኑ ለቻፕማን ተሰማው::

"ህፃናቱ ኢሊን የወለደቻቸው ሳይሆኑ የወንድሟ ልጆች ነበሩ:: እርግጥ ሁለቱ ትንንሾቹ ከርሷ ጋር ብዙም አልቆዩም:: ትልቋ ግን ከኢሊን ጋር ቆይታ ነበረ ..." አለና ቻፕማን የሽማግሌው የቻርሊን መልስ በጉጉት ጠበቀ::

ቻርሊ ጥቂት ሲያስብ ቆየ:: ከዚያም ህፃናቱን ለማስታወስ ከፊቱ ላይ እየተነበበበት "አዎ! አዎን! የወንድሟ ልጆች ስትለኝ አሁን ትዝ አለኝ:: በየጋዜጣው ላይ ወጥቶ ነበረ... አባታቸው እናታቸውን አንቆ የገደላት... እኔ እንኳን ህፃናቱን ብዙ ጊዜ አላየኋቸውም... ግን ሚቹ ባለቤቱ ስለነርሱ እያነሳች አንዳንዴ ታጫውተኝ ነበረ... የሚያማምሩ ልጆች ነበሩ... እዚህ ከመጡ በኋላም በጣም ተጉሳቁለው ነበረ... ባለቤቴ ስለሚያሳዝኗት አልፎ አልፎ ምግብ ትወስድላቸው ነበረ... ግን ያቺ ሰካራም ኢሊንና ያ መናጢ ባሏ ለልጆቹ ፍርፋሪም ያቀምሷቸዋል የሚል ግምት አልነበረንም... ደግነቱ ትንንሾቹን አንድ የተባረከ ሰው መጥቶ ወሰዳቸው ... ኢሊን ግን ሞቃት አየር ወደሚገኝበት ወደ አሪዞና ይሁን ወደ ካሊፎርኒያ ግዛት ከባሏና ከትልቋ ልጅ ጋር መሄዳቸው ይታወሰኛል... በሄደች በስንተኛ ው ዓመት እንደሆነ አሁን ትዝ ባይለኝም፣ ኢሊን በመጠጥ ብዛት መሞቷን ሲያወሩ ሰምቻለሁ:: ባሏና ያቺ ልጅ ግን ከዚያን ምን እንደዋጣቸው

አላውቅም» አለና ሽማግሌው ቻርሊ ንግግሩን አቆመ:: ቻፕማን ስለ ሂላሪ ለማወቅ የፈለገውን ያህል መረጃ ባያገኝም ከአንድ የተደበቀ ምሥጢር ግን ለመድረስ በቅቷል:: ፓተርሰን በዚያን ዕድሜው ለመፀፀት ያበቃውን ምክንያት አሁን ግልፅ ሆነለት:: ያንን ለመሰሉ ባልና ሚስቶች ሶስቱን ህፃናት መስጠቱ ከባድ ጥፋት ነበረ:: ሁለቱን ህፃናት በኋላ መልሶ ቢወስዳቸውም፤ ትልቂቱንም ቢሆን እኛን ከመሰሉ ሰዎች ጋር እንድትኖር ማድረግ አልነበረበትም:: ከመንገድ ማዶ ላይ ባለው በዚያ ቤት ውስጥ ሂላሪ ምን ዓይነት ሕይወት እንዳሳለፈች ለመገመት ቀላል ነው:: ቻፕማን ነገሩን ሲያሰላስለው ሰውነቱን ዝግንን አለው::

«ከርስዎ ሌላ ስለነኢሊን የሚያውቅ ሰው በአካባቢው ይኖር ይሆን?» ሲል ቻፕማን ቻርሊን ጠየቀው::

ቻርሊ እራሱን ጭምር እያወዛወዘ፤«ማንም የለም:: ሁሉም እዚህ መኖር ከጀመሩ ከአስርና አስራ አምስት ዓመት አይበልጣቸውም:: እኔንም ትልቁ ልጄ አብሬው እንድኖር ብዙ ጊዜ ጠይቆኝ ነበረ:: ግን ሚስቴ የሞተችው እዚሁ ቤት ውስጥ ነው:: እኔም እንደ እርሷው እዚሁ ሞቴን እጠብቃለሁ» አለው::

ቻፕማን «ስላደረጉልኝ ከፍተኛ ትብብር አመሰግናለሁ» ብሎ ሊወጣ ሲል የቻርሊ ዓይኖች ሳይታሰብ ብርሃን አንፀባረቁ:: ቻፕማንንም ትኩር ብሎ እያየው፤«ግን ለምንድን ነው ስለ ኢሊን ለማወቅ የፈለግከው? ሐብት አውርሷቸው የሞተ ሰው አለ እንዴ?» ሲል ያልታሰበ ጥያቄ አቀረበለት::

ቻፕማን ፈገግ ብሎ እራሱን እወዛወዘና፤«ነገሩ እንኳን እርስዎ እንደገመቱት አይደለም:: እኔ ግን ለማግኘት የምፈልገው እነኛን ህፃናት ልጆች ነበረ:: አንድ የወላጆቻቸው ጓደኛ የሆነ ሰው በጥብቅ ይፈልጋቸዋል» አለው::

«ከስንትና ስንት ዓመታት በኋላ? ልጆቹ በሕይወት ከኖሩ ይህን ጊዜ ትልልቅ ሴቶች ይሆናሉ:: እንዴትስ ተብሎ ለማግኘት ይቻላል?»

ቻርሊ የተናገረው ትክክል ነበረ:: ቻፕማንም ሐሳቡን በመደገፍ «እንዳሉት ልጆቹን ለማግኘት ቀላል ነገር አይደለም:: ለዚህም ነው እርስዎን የመሳሰሉ ሰዎች በማፈላለግ ለማነጋገር የቆረጥኩት:: በበኩልዎም ያደረጉልኝ ትብብር ቀላል አይደለም:: ስለዚህም ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው» ብሎ ሊሰናበተው እጁን ዘረጋ::





"እንዲቀናህ እመኝልሃለሁ:: ግን የነገሩን አዝማሚያ ሳየው 'ሰዶ ማሳደድ' የሚሉትን ዓይነት ሆነብኝ:: ለእነኛ ህፃናት ማሰብና መጨነቅ ቀድሞ ቀረ:: የአሁኑ ልፋት ግን አይታየኝም» አለው::

ቻፕማን ከመኪናው ገብቶ ቁልቁል በሚወስደው መንገድ ላይ በሚነዳበት ጊዜ ሁሉ የቻርሊን አባባል በህሊናው እያብላላ ነበረ:: በተለይም የሂላሪ ሁኔታ አሳዝኖታል:: ሁለቱ ትናንሽ እህቶቿ ነፍስ ባለማወቃቸው ከዚያም አልፎ በጉዲፈቻ ልጅነት የተሰጡት ለደህና ቤተሰቦች በመሆኑ መልካም አስተዳደግ እንደማይነፈጉ ገምቷል:: ግን ምስኪኗ ሂላሪስ ከነኢሊን ጋር እንዴት ያለ ሕይወት አሳልፋ ይሆን? ፓተርሰን እህቶቿን ቀምቶ ሲወስድባትስ ምን ተሰምቷት ይሆን? ለዘለዓለምስ ከሕሊናዋ የማይፋቅ ቁስል ይሆን ይሆን?

# ምዕራፍ አሥራ ስድስት

ቻፕማን በቻርልስተን ታዉን ቶብኘቱ ተስፋ ቆርጦ ወደ ኒውዮርክ አልተመለሰም:: በሌላ የበረራ መስመር ተሳፍሮ ወደ ጃክሰንቪል ከተማ አቀና:: በአውሮፕላኑም ውስጥ እንዳለ ደግሞ ደጋግሞ የሚያስበው ስለ ሂላሪ ነበረ:: ሂላሪ ከኢሊንና ከጆንስን ጋር የኖረችበትን ቤት በዓይኑ አይቷል:: ስለ ኢሊንም ጠባይ ሽማግሌው ቻርሊ አጫውቶታል:: ያቺ ወላጆቿን ያጣች ህፃን፣ ያቺ እህቶቿን የተነጠቀች ብቸኛ ልጅ ከነጆንስ ጋር ያሳለፈችው የሥቃይ ኑሮ በሐሳብ እየተመላለሰበት ከመጠን በላይ አሳዝኖታል::

ጃክስንቪል እንደደረሰም በቀጥታ ወደ ጠባይ ማረሚያው ተቋም በመሄድ ከአስተዳዳሪዋ ጋር ስለመጣበት ጉዳይ ተወያዩ:: እንደተለመደው አሰራር ከሆነ በጠባይ ማረሚያው ውስጥ ስለቆዩ ወጣቶች ያለፈ ታሪክ ማውራትም ሆነ የግል ማህደራቸውን አውጥቶ ማሳየት የተከለከለ ነበረ:: ሆኖም ቻፕማን ስለ ሂላሪ የሚያደርገው ክትትል ጤናማና በተጨማሪም ብዙ ዓመታት ያለፈው ታሪክ መሆኑን ለማስረዳትና ለማሳመን በመብቃቱ አስተዳዳሪዋ በማግስቱ እንዲመለስ ቀጠሮ ሰጠችው::

ተሰናብቷት ከወጣ በኋላ በከተማው ውስጥ በመሂሂር ደህና ሆቴል ፈልጎ መኝታ ያዘ:: ከዚያ የስልክ ማውጫውን አንስቶ በጆንስ ስም የተመዘገበ የስልክ ቁጥር መኖር አለመኖሩን ተመለከተ:: አምስት ጃክ ጆንስ የሚሉ ስሞች አገኘ:: ተራ በተራም እያንዳንዱን ቁጥር ደወለ:: በጆንስ ስም የሚጠሩት የመጀመሪያዎቹ ሶስት ሰዎች ሁሉም ጥቁር አሜሪካዊያን ነበሩ:: አራተኛው ስልክ ደግሞ የሚመልሰው አልነበረም:: አምስተኛውን ቁጥር የደወለለት ሰው ግን አባቱ ጆንስ ይባል እንደነበረ ከቦስቶን ከተማ ከቻርልስተን ታወን አካባቢ እንደመጣና የእርሱንም እናት ከማግባቱ በፊት ኢሊን የምትባል ሚስት እንደ ነበረችው መስማቱን አጫወተው:: በስልኩ ውስጥ ቻፕማንን የሚያነጋግረው ልጅ ገና የአስራ ስምንት ዓመት ወጣት ሲሆን አባቱም ከሞተ አስር ዓመት ያለፈ መሆኑን እግረ መንገዱን አውግቶታል:: በተጨማሪም ሊያነጋግረው የሚፈልገውም ነገር ቢኖር እቤቱ ድረስ ሊመጣ እንደሚችል ገልጾለታል::





"የአሁኑ ቤታችሁ ድሮም አባትህ ይኖርበት የነበረው ነው ወይንስ አዲስ ቤት ቀይራችኋል?" ሲል ቻፕማን ጠየቀው::

"ያው የዱሮው ቤት ነው" አለ ልጅየው በችኮላ:: ያንን ቤት ለማየት የቻፕማን ጉጉት ጨመረ::

"አድራሻውን ብትነግረኝ?" አለው ቻፕማን:: ልጅየው የቤቱን አካባቢና ቁጥር እንደነገረው አመስግኖ ስልኩን ከዘጋ በኋላ ታክሲ አስቁሞ ገባ:: ወደተነገረው አድራሻ እንደደረሰም ከታክሲው ወርዶ ዙሪያውን ቃኘ:: የሚያያቸው ቤቶች ሁሉ ከቻርልስተን ከተማ ቤቶች የሚሻሉ አልነበሩም:: እርግጥ በዚህ አካባቢ የሚኖሩት ሰዎች በብዛት ጥቁር ናቸው:: ኢሊንና ጆንስ ይኖሩበት ወደነበረውም ግቢ አመራ:: ጉረምሳው ልጅ ከበራፉ ይጠብቀው ስለነበረ ከእናቱ ጋር ሊያስተዋውቀው ወደ ውስጥ ይዞት ገባ:: የቤቱ ሁኔታ የሚያሳዝን ነበረ:: የግርግዳው መላላጥ፣ የዕቃዎቹ ማርጀት፣ የሚተነፍገው ሽታ ለደቂቃም አያስቆምም:: ልጅየው ከጓዳው ውስጥ አንድ የፊት ቆዳዋ የተሸበሸበ፣ ጥርሶቿ የወላለቁ ሴት አምጥቶ አስተዋወቀው:: ከሴትዮዋ መልክ ያሳለፈችውን የሥቃይ ኑሮ ለማንበብ ይቻላል:: ጆንስ ይደበድባት እንደነበረ እርሷም ከብስጭት የተነሳ መጠጥ ታዘወትር እንደነበረ በቀላሉ መገመት አያዳግትም:: ዕድሜዋ ከአርባ ዓመት የማይበልጣት ሴት ብትሆንም በኑሮ በመጉሳቆሏ አሮጊት ነበረ የምትመስለው:: ምንም ነገር ልትረዳው እንደማትችል በመረዳቱ ራሱን በሐዘን አወዛወዘና ወጣ:: ጉረምሳውም የጆንስ ልጅ ተከተለውና ከጉረቤቶቹ አንዳንዶቹን ቢያነጋግር ምናልባት ስለሚፈልገው ነገር ሊረዱት እንደሚችሉ ሐሳብ አቀረበለት:: በተለይም ከነጆንስ ቤት አጠገብ ያለችው ሴት በዚያ አካባቢ ብዙ ዓመታት የኖረች መሆኗን ስለገለፀለት ቻፕማን ወደዚያው ቤት አምርቶ በሩን ቆረቆረ::

"ማ-ን-ነ-ው?" የሚል የሴት ድምፅ ተሰማው::

"ለአካባቢው እንግዳ ነኝ እመቤቴ ስሜን አያውቁትም"

ሴትየዋ በራፉን በከፊል ከፈት አደረገችና "ምን ነበር የፈለግከው? ፖሊስ ነህ ልበል?" አለችው::

"አይደለሁም:: ግን አንድ ከርስዎ የምጠይቀው ትብብር ነበረ" አለና ወደነጆንስ ቤት በጣቱ እያመለከተ "ጊዜው በጣም ረጅም ነው:: ወደ ሰላሳ ዓመት ይጠጋዋል:: እና በዚያ ቤት ውስጥ አንድ ሂላሪ ምከር የምትባል ልጅ ኢሊን ከምትባል አክስቷ ጋር ትኖር ነበረ:: ስለዚያች ልጅ የሚያስታውሱት ነገር ቢኖርና ወዴትስ እንደ ደረሰች የሚያውቁ ከሆነ ቢነግሩኝ?" አላት::

ሴትየዋ ራሷን ስታወዛውዝ ቆየችና ሐዘኔታ በተሞላበት አመለካከት ቻፕማንን እያየችው "ለምንድ ነው የፈለግካት?" አለችው::

"የወላጆቿ የቅርብ ጓደኛ የሆነ ሰው ሊያገኛት ስለሚፈልግ ነው" አለ ቻፕማን::

"ይሄ ድሮ ቀረ! ያቺን አሳዛኝ ፍጥረት የመጠየቂያው ጊዜ አሁን አልነበረም" አለችና ገርበብ ያለውን በር ከፍታ ወጣች:: የሌሊት ልብሷን እንኳን አልቀየረችውም:: ከዚያ ከደረጃው ላይ እንደቆመች "ያ የአክስቷ ባል የነበረ የሰይጣን ቁራጭ እንዳልሆነ ደብድቧት ነፍሷ የዳነው በመከራ ነበረ:: ከዚች አሁን ከቆምኩባት ደረጃ ላይ እርቃኗን ወድቃ ሌሊቱን ዝናብ ሲወርድባት ነበር ያደረው:: ከዚያም እኔና ባለቤቴ አምቡላንስ አስጠርተን ወደ ሆስፒታል ወሰድናት:: ክብረ ንፅህናዋን ካልደፈርኩ ብሎ ነው እሉ እንደዚያ የደበደባት..."

"ክስ ተመስርቶበት ነበረ?" ሲል ቻፕማን መታገስ አቅቶት ጠየቀ:: የሂላሪ ታሪክ ይበልጥ እያሳዘነው ሄደ:: በዚያን ዕድሜዋ ወላጆቿን አጥታ ይህ ሁሉ ስቃይ የደረሰባት ያቺ ትንሽ ልጅ ለዓይነ ህሊናው ታየችው::

"ማን ደፍሮ ሊከሰው?... ሂላሪ ናት ከሳሽዋ? ከዳነች እንኳን ልብሷን ለማውጣት እዚያ ቤት መግባት በመፍራቷ እኔ ነኝ አብሬአት የሄድኩት"

"ከዚያስ ወዴት ደረሰች?"

"አንድ አሳዳጊ የሌላቸው ልጆች መጠለያ ውስጥ መኖር ጀምራ ነበረ:: ከዚያም በሆነ ምክንያት ትለቅና ከጠባይ ማረሚያ ትገባለች:: እኔና ባሌም ከአንዴም ሁለቴም ልንጠይቃት ሄደን ነበረ:: ምን ያደርጋል ያቺን የመሰለች ልጅ በበደል ላይ በደል ደርሶባት ኖሮ ፍፁም ጭምትና ብቸኛ ሆና ነበረ:: ከማንም ጋር ለመነጋገር ፍላጎት አልነበራትም::"

"ስለ ትብብርዎ በጣም አመሰግናለሁ" ብሎ ቻፕማን ተሰናብቷት ተመለሰ:: ወደ ጠባይ ማረሚያ የገባችበት ምክንያት በዚሁ ሳቢያ ይሆን ወይንስ ሌላ ወንጀል በኋላ ላይ ፈፅማ? ሲል ቻፕማን ሐሳብ ገባው::

ሂላሪ ግን ከጠባይ ማረሚያ የገባችው ጥፋተኛ ሆና ተገኝታ አይደለም:: ይህንንም በማግስቱ ጠዋት ላይ ከተሰጠው የግል ማህደሯ ለማጣራት በቅቷል:: እንዳውም ሂላሪ ምስጉን ተማሪ መሆኗን ማህደሯ ይናገራል:: አድራሻው ተመዝግቦ ከነበረው የመጠለያ ቤት ለቃ በጠባይ ማረሚያው በቆየችባቸው ሶስት ዓመታት ውስጥ በትምህርትና በጠባይዋ ተወዳዳሪ የማይገኝላት ልጅ ነበረች:: የአስራ ሁለተኛ ክፍል መልቀቂያ





ፈተና ወስዳ በከፍተኛ ማዕረግ በማለፏ የትምህርት ቤቱ አስተዳደር መጠነኛ ገንዘብ ሰጥቷት ጠባይ ማረሚያውን መልቀቋን ማህደሯ ይገልፃል:: ከዚህ በተረፈ ግን ቻፕማን ሌላ መረጃ ለማግኘት አልቻለም::

ጃክሰንቪል ድረስ ከመጣሁኝ አይቀር ሲል ቀደም ትኖርበት የነበረውን የመጠለያ አድራሻ ማስታወሻው ላይ ፅፎ ከአስተዳዳሪዋ ቢሮ መጣ:: እንደ ሌሎቹ ታዳጊ ከተሞች ሁሉ እዚህም ያረጁ ቤቶች በአዳዲስ ህንፃዎች በመተካት ላይ ስለነበሩ ምናልባት ያ የመጠለያ ቤት እስከ አሁን ፈርሷል የሚል ግምት ቢኖረውም እንደ ፈራው ሳይሆን ከከተማው ዳርቻ ላይ የነበረውን የሉዊዝን ግቢ አገኘው:: ሉዊዝ አሁን በጣም ያረጀች ሴት ሆናለች:: ስለ ሂላሪ አንስቶ ሲጠይቃት ግን ወዲያውኑ ልታስታውሳት ችላ ነበረ:: ሂላሪ መጠለያ ቤቱን ለቃ ወደ ጠባይ ማረሚያ ለመግባት የተገደደችበትን ምክንያት አስረዳችው:: ዝምተኛ፣ ታዥና ስራ ወዳድ ልጅ እንደነበረች ገልፃለት፤ ግን በእነኛ ወንድ ልጆች ምክንያት በዚያ ቤት ውስጥ ለመቆየት አለመቻሏንም አጫወተችው:: ቻፕማን ከምንጊዜውም ይልቅ ለሂላሪ አሁን አዘነላት:: በበደል ላይ በደል እንደተፈፀመባት በዚያ ዕድሜዋ ምን ጊዜም ከአእምሮ የማይፋቅ ስቃይና መከራ እንደ ደረሰባት አሁን በይበልጥ ተሰማው:: በዚህንም ጊዜ ነው የኒውዮርኳን የዜና አገልግሎት ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ ሂላሪ ምክርና ይቺኛዋን ምስኪን ሂላሪ ምክር አንድ ሲያደርጋቸው በመሞከሩ ትልቅ ስህተት መፈፀሙ ጉልቶ የታየው::

ወደ አውሮፕላን ማረፊያ በሚወስደው ታክሲ ውስጥ ተቀምጦ ሁሉ ቻፕማን ስለ ሂላሪ ማሰቡን አላቋረጠም:: በአባቷ እናቷን መግደል የተነሳና በኋላም የራሱን ሕይወት በማጥፋቱ ሳቢያ በዚያች በዘጠኝ ዓመት ትንሽ ልጅ ላይ መድረስ የጀመረው መከራ አንድ በአንድ ይታወሰው ነበረ:: እንደዛም ሆኖ መጨረሻ ላይ እህቶቿን አገኛለሁ ብላ በተስፋ ፓተርሰንን ብታነጋግረው አድራሻቸውን እንደማያውቀው ገለፀላት:: እንግዲህ ይቺን በደረሰችበት ሁሉ መጥፎ ዕድል የሚጠብቃትን ልጅ እንዴት አፈላልጎ ለማግኘት ይቻላል? ተስፋ በመቁረጥ ራሷን ልትገድል ትችላለች... ወይንም ከባድ ወንጀል ፈፅማ ከአንደኛው ወህኒ ቤት ውስጥ ገብታም ሊሆን ይችላል ... ሌላም ሌላም...

አውሮፕላን ውስጥ እንዳለ እንኳን የሂላሪ ነገር አእምሮውን እንደ በወዘውና የውስጥ ስሜቱን እንዳመሰው ነበረ:: የማያባራና ሩህሩህነት የጐደለው ምጣት በጀርባዋ ላይ ያለማቋረጥ የዘነበባት ሂላሪ ... ያለወጋወጋዊ ሥርዓት ክብረ ንፅሕናዋ የተደፈረ ይቺ ትንሽ ልጅ ... እሮሮ ራትና ምላዋ

የሆነባት ይቺ የዘጠኝ ዓመት ጮርቃ... ቻፕማን አገባበት ገብቶ ሲያገኛት ከቁርጥ ውሳኔ ላይ ደረሰ ... እስከዚያው ድረስ ግን ምን ማድረግ እንደሚኖርበት ለራሱ ጥያቄ አቅርቦ ሲያሰላስል እንቅልፍ ሸለብ አደረገው::

ከኒውዮርክ አውሮፕላን ማረፊያ እንደ ወረደ በቀጥታ የሄደው ወደ ቢሮው ነበረ:: ወዲያውኑም ለሚስተር ፓተርሰን ስልክ ደውሎ ስለ ቻርልስተን ታወንና የጃክሰንቪል ጉብኝቱ አንድ ባንድ አጫወተው:: ሂላሪን መናጢ ዕድሏ ከምን እምን ላይ እንደጣላት ፓተርሰን በስማ ቁጥር ፊቱ ሐዘን እየተላበሰ ሄደ:: ለቻፕማን አይታየው እንጂ በዚያን ወቅት ከፓተርሰን ዓይኖች የእንባ እንክብሎች ተከታትለው በመውረድ ላይ ነበሩ::

ቻፕማን ስለ ደረሰበት ሌላም ውሳኔ ለፓተርሰን አወጋው:: ሂላሪን ለማፈላለግ፣ በሰራተኛ መቅጠሪያ ድርጅቶች... በወህኒ ቤቶች... በፖሊስ ጣቢያዎች... በትምህርት ተቋሞችና... ወዘተ ረዳቶቹን ከዚያች ደቂቃ ጀምሮ ያሰማራል:: ያም ሆኖ ግን ቻፕማን ራሱ ሊከታተለው የፈለገ ጉዳይ ነበረ... ሁለተኛዋን ህፃን አሌክሳንድራን ለማግኘት!!!

"የአሌክሳንድራ የጉዲፈቻ አባት የነበረው ሚስተር ጉርሐም ከሞተ ወዲህ ሚስቱ ሀገር ጥላ መሄዷን ነግረውኝ ነበረ መሰለኝ?" አለው ቻፕማን የስልክ ንግግሩን በመቀጠል::

"አዎን! ማርጋሬት ብዙም ሳትቆይ ወደ ውጪ አገር መሔዷን ሰምቻለሁ:: ግን በትክክል ወደየትኛው ሀገር እንደሄደች አላውቅም"

"ምናልባት ስለባሏ ሐብትና ንብረት በማስመልከት የፃፈችው ደብዳቤስ ይኖር ይሆን?"

"በእኔ በኩል የደረሰ ልብ የምለው ነገር የለም:: ድንገት ካለ ከጉርሐም የግል ማህደር ጋር እንደሚያያዝ እርግጠኛ ነኝ"

"እንግዲያውስ አቢሮዎ መምጣት ሳያስፈልገኝ አልቀረም:: እርስዎም እንደነገሩኝና ከሰጡኝም ፋይል ውስጥ እንደተረዳሁት የሁለተኛ ዋ ህፃን የጉዲፈቻ አባት ጆርጅ ጉርሐም አብሮዎት ለብዙ ጊዜ ሰርቷል::

በኒውዮርክ ከተማ ውስጥ ብቻ ሳይሆን ከዚያም ውጪ በስሙ የተመዘገበ ሐብትና ንብረት ሊኖር ይችላል:: ስለዚህም የሚያስረዳ አንዳንድ ሰነድ ከግል ማህደሩ ውስጥ ማግኘት ይቻል ይሆናል:: ወራሹም ስለሆነችው ሚስቱ አድራሻ ምናልባት ከዚሁ ማህደር ውስጥ መረጃ ላናጣ እንችላለን" አለው ቻፕማን::





ፓተርሰን ለሂላሪ ያነባውን እንባ ከጉንጮቹ ላይ እየጠረገ "ጥሩ ሐሳብ ነው:: ግን እኔ እንዴት እስከ ዛሬ አሁን ያጫወተከኝን ሳላስብበት ቀረሁ? ከማርጀትም ጃጅቻለሁ ማለት ነው? እና መቼ ልጠብቅህ?" አለና በኃይል ይስል ጀመረ::

"ነገ በሶስት ሰዓት" አለው ቻፕማን::

"እሺ" ብሎ ፓተርሰን ቢሮ ሔዶ የጆርጅ ጉርሐምን የግል ማህደር አንድ ባንድ ሲመለከት አረፈደ:: በመጨረሻም ላይ የሚፈልገውን መረጃ አገኘ:: ያም ከጉርሐም ሚስት ከማርጋሬት የተፃፈ ደብዳቤ ነበረ:: ደብዳቤው ማርጋሬት በኒውዮርክ ውስጥ ስለሚገኝ የባሏ ቤት ሽያጭ ጉዳይ የፓተርሰንን የህግ አገልግሎት ድርጅት የወከለችበት ነው:: ውክልናውን ያስፈፀመው ከፓተርሰን ረዳቶች አንዱ ኖሮ እርሱ ጋር አልደረሰም ነበረ:: በመሆኑም ነው ፓተርሰን ስለዚያ ከሃያ አራት ዓመታት በፊት ስለተፃፈ ደብዳቤ ምንም አለማወቁ:: አሰበለዚያማ ሂላሪ ስለ እህቶቿ አድራሻ በጠየቀችው ጊዜ ሌላው ቢቀር ስለ ሁለተኛዋ እህቷ ስለ አክሲ ቢያንስ አንድ ነገር በጠቆማት ነበረ::

ያ ደብዳቤ ተፅፎ የነበረው ከፖሪስ ነው:: በዚያን ወቅት ደብዳቤውን ፀሐፊዋ ማርጋሬት ፈረንሳዊውን መስፍን ኮምት ደ.ቦርን አግብታ በቫርኔ አውራ ጎዳና አጠገብ በሚገኘው ትልቅ ህንፃ ውስጥ ነበረ የምትኖረው:: በፖስታው አድራሻ ላይ የተፃፈው ስሟም ኮምት ተስያ ደ.ቦርን ነበረ የሚለው::

ቻፕማን የማርጋሬትን አድራሻ እንዳገኘ ቀጥታ ወደ ፓሪስ ስልክ ደውሎ ከአንድ ከሚያውቀው ሰው ጋር ተገናኘ:: የማርጋሬትን አድራሻ ከነገረው በኋላ በሕይወት ስለመኖር አለመኖሯ አጣርቶ መልሱን እንዲያስታወቀው አደራ አለው:: ከዚያው ከፓተርሰን ቢሮ ሳይወጣም ከፓሪስ መልሱ ደረሰው:: ማርጋሬት አሁንም የምትኖረው በዚያው በጥንቱ ቤቷ ውስጥ ነበረ:: ይህም ዜና ለአሌክሳንድራ መገኘት መቶ በመቶ አስተማማኝ ባይሆንም ብሩህ የተስፋ ጭላንጭል በመቅደዱ ፓተርሰንና ቻፕማን የሰዓት በኋላውን ጊዜ በደስታ አሳለፉት:: የአሌክሳንድራ ዕድል እንደ ሂላሪ የከፋ አይደለም ማለት ነው:: ማርጋሬት አንድ ፈረንሳያዊ መስፍን ለማግባት ከበቃች አሌክሳንድራን ተንከባክባ አሳድጋት ይሆናል የሚል ግምት በሁለቱም ሰዎች ዘንድ ነበረ::

# ምዕራፍ አስራ ሰባት

በነጋታው ቻፕማን ወደ ፓሪስ በረረ:: ፓተርሰንም አጥብቆ ስለ ጐተጐተው በአውሮፕላኑ ውስጥ የተያዘለት ቦታ አንደኛ ማዕረግ ነበረ:: እኩለ ሌሊት ሲሆንም ከፓሪስ ደረሰ:: ከኒውዮርክ ከመነሳቱ በፊት በስልክ መኝታ ወደ አስመዘገበበት የብሪስትል ሆቴል ቀጥታ ሄደ:: እንደ ድካሙ ቢሆን ወዲያውኑ እንቅልፍ በወሰደው ነበረ:: ግን ስለ አሌክሳንድራ እያሰበ ብዙ ተጨነቀ:: "በሕይወት ትኖር ይሆን? ልታነጋግረውስ ፈቃደኛ ትሆን ይሆን?... ማርጋሬትስ በምን ሁኔታ ትቀበለው ይሆን?..." እስከ ሌሊቱ አስራ አንድ ሰዓት ድረስ እንቅልፍ በዓይኑ አልዞረም::

በማግስቱ ግን ከእንቅልፉ የነቃው ከረፈደ አምስት ሰዓት ላይ ነው:: ከአልጋው ውስጥ ተስፈንጥሮ ወርዶ ቡናና ቁርስ መኝታ ክፍሉ ድረስ እንዲመጣለት ካዘዘ በኋላ ሰውነቱን መለቃለቁን ትቶ ወደ ማርጋሬት መኖሪያ ቤት ስልክ ደወለ::

"አሎ!" በስልክ ውስጥ የተሰማው ድምፅ የወንድና የፈረንሳዊ ነበረ::

"ኮምትስ ደ.ቦርን ለማነጋገር አፈልግ ነበረ" አለ ቻፕማን::

"ስለምን ነበረ?" አለው ያ ድምፅ አሁንም በፈረንሳይኛ::

"ስሜ ጆን ቻፕማን ይባላል:: እና እባክዎን እመቤት ማርጋሬትን ቢያገናኙኝ" አለ ቻፕማን በትህትና::

"ቻፖት! ቻፖት!" አለና ያ ድምፅ ለጥቂት ጊዜ ዝም አለ:: ትንሽም ቆይቶ "ሙሴ ቻፖት?" የሚል የሴት ድምፅ ተሰማው::

"ይቅርታ እመቤቴ ጆን ቻፕማን ነው የምባለው:: ከኒውዮርክ ነው የመጣሁት" አላት::

"እ! አሜሪካዊ ነህ! እኔ እኮ የቤት ሰራተኛዬ ሙሴ ቻፖት ሲለኝ ፈረንሳዊ መስለኸኝ ነበረ:: ፈረንሳዮች የአሜሪካኖችን ስም በትክክል





መጥራት ያስቸግራቸዋል::" አለችና ማርጋሬት ሳቀች:: ድምጿም አሳሳቋም ለዛ የተሞላ ነበረ:: ቻፕማን ደግሞ የወደደው በተለይ ግልፅነቷን ነበረ::

"ቀደም ሲል የምንተዋወቅ አይመስለኝም?" ስትል ጠየቀችው

"እርግጥ ነው እመቤቴ አንተዋወቅም:: ወደ ፓሪስ የመጣሁት እርስዎን ለማነጋገር ስል ብቻ ነው:: እና ፈቃደዎ ሆኖ መቼ አግኝቼ ላነጋግርዎት እንደምችል ቢገልፁልኝ?"

"ጉዳዩ ስለምን እንደሆነ በስልክ ልትነግረኝ አትችልም?"

"አዎን እመቤቴ! ከበድ ያለ ነገር ስለሆነ በስልክ መግለፅ ያስቸግረኛል"

"ምናልባት ስለገንዘብ ጉዳይ ከሆነ በቅድሚያ ከጠበቃዬ ጋር መነጋገር ያስፈልግህ ይሆናል"

"ስለገንዘብ አይደለም:: ለየት ስላለና የቀድሞ ባልዎን ስለሚመለከት ጉዳይ ነው:: ዱሮ ወዳጃቸው የነበረው ሰው ነው እንዳናግርዎት የላከኝ"

"የማን ጓደኛ? የኮምት ደ.ቦርን?"

"ይቅርታ! የመጀመሪያው ባልዎ የሚስተር ጐርሐም ማለቴ ነበረ"

"አ! የጐርሐም! ግን እኮ ጐርሐም ከሞተ ሰላሳ ዓመት ሆኖታል:: ረጅም ጊዜ ነው... ሚስተር ቻፕማን"

"ይገባኛል እመቤቴ እኔም የማነጋግርዎት በዚያኑ ዘመን አካባቢ ስለተፈፀመ ጉዳይ ነው::"

"ምነው? ያን ጊዜ የፈፀምነው ስህተት ይኖር ይሆን?"

"በፍፁም! በፍፁም! እኔን የላኩኝ አዛውንት ከመሞታቸው በፊት አንድ ሊያገኙት የሚፈልጉት ሰው አለ:: እና ያንን ሰው በማግኘቱ በኩል እመቤቴ ሊረዱን ይችላሉ:: እርስዎንም ያስቸገርኩት በዚህ የተነሳ ነው:: በስልክ የሚነገር ነገር ስላልሆነም እባክዎን ፈቃድዎ ሆኖ ለጥቂት ደቂቃዎች ተገናኝተን ለመወያየት ብንችል?"

"እ... ሺ!" አለች እያመነታች:: ቻፕማንን ከመገናኘቷ በፊት ስለማንነቱ በቅድሚያ ማጣራት ነበረባት:: አታላይ ሰው ሊሆን ይችላል:: እንዲውም የለየለት ወንጀለኛም የማይሆንበት ምክንያት የለም:: ስለዚህ

ጊዜ ያስፈልጋታል ማለት ነው:: "ድንገት ነገ ልንገናኝ እንችል ይሆናል:: ለማንኛውም የኒውዮርክ አድራሻህን ብትነግረኝ?" አለችው::

ቻፕማን በጥያቄዋ ስለነቃ ፈገግ አለና "የቻፕማን የግል ወንጀል ምርመራ ድርጅት ሃምሳ ስባተኛ ጎዳና ኒውዮርክ" አላት::

"ጥሩ" አለች ማስታወሻ ላይ አድራሻውን እየመዘገበች::

"ታዲያ ነገ በስንት ሰዓት እንገናኝ?"

"በአምስት ሰዓት" አለችው:: የቀጠሮውን ጊዜ አመራረጧ ሆን ብላ ነበረ:: ከቻፕማን ጋር ባደረገችው የስልክ ልውውጥ ከአሁኑ መንፈሷ መረበሽ ጀምሯል:: በአምስት ሰዓት የቀጠረችው ሰዓቱ አጓጉል ስለሆነ ሊቀር ይችላል ወይንም ይረሳዋል በሚል ግምት ነበረ:: ያም ሆኖ ወደ ኒውዮርክ ስልክ ደውላ ስለቻፕማን አጣራች:: ቻፕማን እንደ ጠረጠረችው ሳይሆን ጨዋና የታወቀ ሰው መሆኑን አረጋገጠች:: "ግን ከኒውዮርክ ፓሪስ የሚያስመጣ ምን ከባድ ጉዳይ ቢገጥመው ነው?" ስትል ቀኑን ሙሉ እንዳሰበች ዋለች::

በማግስቱ ቻፕማን የደረሰው ልክ በቀጠሮው ሰዓት ነበረ:: ከበራፍ ሆኖ ይጠባበቀው የነበረው የማርጋሬት ወንድ አሽከር ዝቅ ብሎ እጅ ከነሳው በኋላ በአንደኛው ፎቅ ላይ ወደሚገኘው የእንግዳ መቀበያ ክፍል ወሰደው:: ዙሪያውን ያያቸው መቀመጫዎችና በግርግዳው ላይ የተሰቀሉት ሥዕሎች ለዓይን እጅግ የሚማርኩ ነበሩ:: ባለብዙ ጉጦች ሆኖ ከመሐል ላይ የተንጠለጠለው የኤሌክትሪክ መብራት የፀሐይ ጨረር አርፎበት እንደ ዕንቁ የተለያዩ የብርሃን ጨረሮች ይረጫል:: ከመስኮቱም ፊት ለፊት በልዩ ልዩ አበቦች ያሸበረቀ የተንጣለለ ሜዳ ነበረ:: ባየው ሁሉ በመገረም ላይ እንዳለ ማርጋሬት ደ.ቦርን ገባች::

"ሚስተር ቻፕማን" አለችና እጇን ለሰላምታ ዘረጋችለት:: እንደሚ ተዋወቅ ወዳጅም እጁን ደጋግማ በመጨበጥም ሞቅ ባለ ሁኔታ ተቀበ ለችው:: እንዳነጋገሯ መልክና ቁመናዋም የደስ ደስ ነበረው:: በአለባበሷም ጥንቁቅ ነበረች:: የእንግሊዝ አገር ሥራ ከሆነው ከረጅም ቢጫ ቀሚሷ ጋር የሚስማማ ጫማ አድርጋለች:: ከአልማዝ የተሰራው የጆሮ ጌጧም በቅርቡ የሞተው ሁለተኛ ባሏ ለገና በዓል ያበረከተላት ስጦታ ነበረ:: ለቻፕማን ፈገግታ እያሳየችው ተመቻችቶ እንዲቀመጥ ሰፋ ያለውን ወንበር መርጣ አረፍ እንዲል ጋበዘችው፤ እርሷም ፊት ለፊት ከነበረ ሌላ መቀመጫ ላይ ተቀመጠችና፤ "ይኸውልህ ይህን ክፍል አዘውትሮ





የሚጠቀምበት ባሌ ነበረ:: እርሱ ከሞተ በኋላ ብዙም እንግዳ ስለማይመጣ ወደዚህ ክፍል ብቅ የምለው አልፎ አልፎ ነው:: በእርግጥ ሴቷ ልጄና የልጅ ልጆቼ ሊጠይቁኝ በመጡ ቁጥር ስለሚወዱት ከዚህ ክፍል ውስጥ አይወጡም:: እኔም ለነርሱ ስል እዚህ መዋል ይኖርብኛል::"

'ማንን ይሆን ልጄ ያለችው? አሌክሳንድራን ወይንስ ሌላ የወለደቻት ልጅ ትኖር ይሆን?' ሲል ቻፕማን አሰበ:: ወደ መጣበትም ዋና ምክንያት መቃረቡ ተሰምቶት የልቡ አመታት ጨመረ:: 'ከዚህ ቤት የምወጣው ምን ዓይነት ውጤት ይዤ ይሆን? ተልዕኮዬ ተሳክቶ ወይንስ ተስፋ ቆርጬ?' ፍርሃት የማያውቀው ቻፕማን ዛሬ ፈራ::

"ተጫወት እንጂ" አለችው ማርጋሬት ፈገግታዋ ሳይለወጥ::

"እሺ እመቤቴ! ስለ ክፍሉ ቁንጅና በሀሊናዬ እያደነቅሁ ነበረ" አላት ቶሎ አለና:: እርሷ ግን ሌላ በማሰብ ላይ መሆኑን አውቃበታለች::

"ለመሆኑ እኔን ለማነጋገር ከኒውዮርክ እዚህ ድረስ የላከህ ማነው?" አለች በበኩሏም ታሪኩን ለመስማት ጓጉታ ጭምር::

"ፓተርሰን ... ሚስተር አርዘር ፓተርሰን ይባላሉ"

"ፓተርሰን? ፓተርሰን" ስትል ማርጋሬት ስሙን በመደጋገም ሰውዬውን ለማስታወስ ሞከረች::

"የቀድሞው ባለቤትዎ የሚስተር ጉርሐም ጓደኛ ነበሩ::"

"እና ፍሬ ነገሩ ምን ነበረ?" አለች በቻፕማን ተልዕኮ የነቃች ይመስል ሰውነቷ እየተለዋወጠ::

"አሌክሳንድራ የምትባለዋን ህፃን ለሚስተር ጉርሐም በጉዲፈቻ ልጅነት የሰጧቸው ሚስተር ፓተርሰን ነበሩ::"

ደግነቱ ማርጋሬት መቀመጧ እንጂ ህሊናዋን እንደመሳቷ ቢሆን እወለሉ ላይ ተዘርራ በወደቀች ነበረ:: ለረጅም ጊዜ ፊቷ እንደተለዋወጠ ትንፋሿም ቁርጥ ቁርጥ ማለቱን እንደቀጠለ ቆየ:: ቻፕማን ደፍሮ ሊቀርባት ሊረዳትም አልቻለም:: ነፍሷን እስከምትዘራ በተቀመጠበት መጠበቁን መረጠ:: የማርጋሬት ዓይኖች ቀስ በቀስ ተከፈቱ:: ሰውነቷም ከላይ ታች በኃይል ከነዘረ በኋላ በረጅሙ ተነፈሰች::

"ከዚህ ሁሉ ዘመን በኋላ ፓተርሰን አሌክሳንድራን እንዴት አስታወሳት?" አለች በተሰባበረ ድምፅ::

"በአሁኑ ጊዜ በጣም ታመዋል:: ለምን እንደሆነ በግል ባልረዳውም ከመሞታቸው በፊት ሦስቱን የምክርን ልጆች ለማገናኘት ዕቅድ አላቸው:: የልጆቹ ወላጆች የቅርብ ጓደኞቻቸው ነበሩ:: እርሳቸውም ቢሆኑ ለሦስቱም ህፃናት የክርስትና አባት ነበሩ:: ስለዚህ መሞታቸው ሲቃረብ የተፀፀቱበት ነገር ያለ ይመስለኛል:: በመሆኑም ሦስቱም ደህና መሆናቸውን ለማረጋገጥና በግዴታ እንዳለያዩዋቸው..." አለና ከአፉ ቀጥሎ የሚወጣውን ትክክለኛ ቃል በመምረጥ ላይ እንዳለ ማርጋሬት አቋረጠችው::

"... ብቻ ሲያገናኛቸው ይፈልጋል እንዳትለኝ!" ስትል ማርጋሬት ጮኸች::

"አዎን!" አለ ቻፕማን በሐዘኔታ እየተመለከታት::

"በጣም ዘግይተሀል በለው ሚስተር ቻፕማን! በጣም ዘግይቷል! ልጆቹ እኮ አሁን ሕፃናት አይደሉም!"

"አውቃለሁ እመቤቴ! ለምን ይህን ያህል ዘግይቶ እንዲገናኙ ለማድረግ እንዳሰቡ ለእኔም ቢሆን ግራ ገብቶኛል:: ለዓመታት የረሷቸውን ልጆች በማስታወስ ስለ ደህንነታቸው ዛሬ ተቆርቋሪ ለመሆን በቅተዋል..."

"ስለማን ደህንነት?"

"ስለእህትማማቾቹ እመቤቴ"

ማርጋሬት በንዴት ከተቀመጠችበት ተነስታ በክፍሉ ውስጥ ትንጐራደድ ጀመረ:: "ስለ ልጆቹ ደህንነት አስቦ አይመስለኝም:: አእምሮውን ያስጨነቀው ሌላ ነገር ቢኖር እንጂ:: በቅድሚያ ልጆቹም ቢሆኑ እንኳንስ እርሱን ሊያስታውሱት ቀርቶ እህት እንዳላቸውም አያውቁም:: የተለያዩት በህፃንነታቸው ነው" አለች ንዴቷ ሳይበርድ:: ቻፕማን በደቂቃዎች ውስጥ የተለዋወጠውን ዓይኗን አይቶ አዘነላት:: ልጂ ናት ብላ ካሳደገቻት ከአሌክ ሳንድራ አጠገብ እንደማታደርሰውም ተረዳው:: "እስቲ ስለ እግዚአብሔር አንተው ራስህ ፍረድ ልጆቹ አሁን ትልልቅ ሴቶች ሆነዋል:: ሁሉም የየራሳቸውን የተደላደለ ኑሮ በመምራት ላይ ናቸው:: የረሱትን ነገር አስታውሶ እነርሱን ማግኘት ጥቅሙ ከምኑ ላይ ነው?"

ቻፕማን የሚመልሰው ጠፍቶት ነበረ:: የማርጋሬት ንግግር ትክክል መሆኑን ያውቀዋል:: ሆኖም ፓሪስ ድረስ የመጣው ፓተርሰንን ወክሎ ነው:: ስለዚህ "እህትማማቾቹን መልሶ ማገናኘቱ የሚኖረውን ጥቅም ሲያውቁት የሚችሉት ሚስተር ፓተርሰን ብቻ ናቸው:: የእኔ





ኃላፊነት የሦስቱን ሴቶች አድራሻ እስከ ማግኘትና እህት እንዳላቸውም እንዲያውቁ እስከማድረግ ነው" አለ ቻፕማን ረጋ ብሎ::

"ያምላክ ያለህ!" አለች ከተነሳችበት ወንበር ላይ ተመልሳ እየተቀመጠች:: "በበኩሌ በዚህ ሐሳብ አልስማማም:: ከልጂ አጠገብ እንድትደርስ አልፈቅድልህም! ምናለ ልጆቹን በሰላም እንዲኖሩ ብትተዋቸው:: ለምሳሌ የኔዋ ልጅ ሰላሳ አምስት ዓመት ሆኗታል:: የሌሎቹም በዚያው አካባቢ መሆን ይኖርበታል:: ሁለት የማታውቋቸው እህቶች አሏችሁ ብሎ በአሁኑ ወቅት መንገሩ ምን ያደርግላቸዋል? የረሷቸውንም ወላጆቻቸውን እንዲያስታውሱ ማድረግ ከሐዘንና ከኃፌሬታ ላይ ይጥላቸዋል እንጂ ምን ጠቀሜታ ይኖረዋል? ስለ ወላጆቻቸው አሟሟት ታውቅ የለ ሚስተር ቻፕማን?" አለችው:: ቻፕማን በአዎንታ ጉንበስ አለ:: እርሷም መናገሯን ቀጠለች:: "እኔም አውቀዋለሁ የእኔ ልጅ አሌክሳንድራ ግን አንድም የምታውቀው ነገር የለም:: እኔና ጉርሐም እንደራሳችን ልጅ አድርገን እናፈቅራት ነበረ:: ከጉርሐምም በኋላ ያገባሁት ባሌ ኮምት ደ.ቦርን ደግሞ ከሁላችን ይልቅ አብልጦ ይወደት ነበረ:: የእኛ ልጅ ሆና በእንክብካቤ አደገች:: ከእኔ ሌላ እናት እንዳላት አታውቅም:: የእኔና የኮምት ደ.ቦርን ልጅ በመሆኗ ያገባችው ባል ከፈረንሳይ ነገስታት ዘሮች የሚወለድ ነው:: ባሏን ታፈቅረዋለች:: ቆንጆ ቆንጆ ልጆች ወልዳለታለች:: ታዲያ ይህን የመሰለ ሰላማዊ ኑሮ በመኖር ላይ ለምትገኘው ልጂ ለምን ራስ ምታት ልትሆኑባት ትፈልጋላችሁ?" አለች ምርር ብላ:: ማርጋሬት በዚያን ወቅት የታያት የአሌክሳንድራ ባል የሄነሪ ነገር ነበረ:: አሌክሳንድራ የኮምት ደ.ቦርን ልጅ አለመሆኗን ሲያውቅ... አሌክሳንድራ የጉዲፈቻ ልጅ መሆኗን ሲረዳ ... የአሌክሳንድራ እውነተኛ አባት ሚስቱን የገደለው ሰው መሆኑን ሲደርስበት... የአሌክሳንድራ ሰላም ሲበጠበጥ፣ መልካሙ ትዳሯ ሲፈርስ፣ ህፃናቱ ልጆች ችግር ላይ ሲወድቁ... ያና ሌላ ሌላውም ታያት::

"እመቤቴ የተናገሩት ምሬትዎ ሁሉ ለምን እንደሆነ የገባኝ ይመስለኛል:: ግን ማንኛችንም ብንሆን ልንመልስ የማንችለው አንድ ጥያቄ አለ:: አሌክሳንድራ እህቶች እንዳሏት ካወቀች ልታገኛቸው ፈቃደኛ ትሆናለች ወይንስ አትሆንም? የሚል ጥያቄ ልናነሳ ይገባናል:: ለዚህም ጥያቄ መልስ የምትሰጠው አሌክሳንድራ እንጂ እኛ ልንሆን አንችልም:: ለመሆኑ የጉዲፈቻ ልጅ ስለመሆኗስ የምታወቀው ነገር አለ?" አለ ቻፕማን::

ማርጋሬት ጥቂት እንደ ማመንታት ብላ "ታውቃለችም አታውቅ ምም ለማለት እርግጠኛ ሆኜ መናገር አልችልም:: ከብዙ ዓመታት በፊት

ነግረናት እንደነበረ እስታወሳለሁ:: ግምቴ ግን ፈፅሞ ረስታዋለች የሚል ነው:: ስለዚህ የጉዲፈቻ ልጅ መሆን አለመሆኗ ምንም ጠቀሜታ አይኖረውም:: ከጉዳት በስተቀር የሚያስከትለው አንዳችም ነገር የለውም:: ለእናንተም ቢሆን ሚስተር ቻፕማን! ስለዚህ የመጣው ቢመጣ አንተ ስላነጋገርከኝ ጉዳይ አላነሳባትም» አለችው::

«ይህማ ጥሩ አይመስለኝም እመቤት ማርጋሬት!» አለ በዛ በተለመደ ረጋ ያለ አንደበቱ:: «እርስዎ ፈቃደኛ ባይሆኑ አሌክሳንድራን ፈልጌ ማግኘት አያቅተኝም:: ስለዚህ ከእኔ ይልቅ እርስዎ ማንኛውንም ነገር ቢያጫውቷት የሚሻል ይመስለኛል:: የጉብኝቴንም ምክንያት ከርስዎ አፍ ብትሰማው ይቀላል ብዬ እገምታለሁ» ሲልም ረገጥ አድርጐ ተናገረ::

የማርጋሬት ደብሮን ዓይኖች የንዴት ዕንባ አዘሉ:: «ልታስፈራራኝ እየሞከርክ ይመስለኛል:: በደስተኛ ሕይወቷ ላይ ጥቁር ጠባሳ ጥሎ የሚያልፈውን ዜና እንዳበስራት እያስገደድከኝ ነው» አለችው::

«እህቶቿን ለማየት ካልፈለገች በግድ ካላየሻቸው ብሎ የሚያስ ቸግራት ሰው አይኖርም:: ልገናኛቸው አልፈልግም የማለቱ መብት ግን የርሷ የብቻዋ ነው:: እህቶች እንዳሏት ትወቅ:: ከዚያም የመምረጡን ዕድል ለርሷ እንተወው:: ማን ያውቃል? እርስዎ እንደገመቱት ሳይሆን ምርጫዋ እህቶቿ ሊሆኑ ይችላል»

«አይመስለኝም! ከሰላሳ ረጅም ዓመታት በኋላ ምን ዓይነት ሴቶች እንደሆኑ አታውቅም:: በአስተዳደጓም ሆነ አሁን ባላት የኑሮ ደረጃ ከነርሱ ጋር የምትመሳሰልበት አንድም ነጥብ የለም:: የምታውቀው ከመሳፍንት ወገን መወለዷንና ከነገስታት ዘር መጋባቷን ብቻ ነው:: ስለዚህ ለምን በሰላምና በደስታ እንድትኖር አንተዋትም? እባክህን ለማይጠቅም ነገር አንዘጥዝጣት!» አለችው:: የማርጋሬት አነጋገር እውነት ነበረ:: ቻፕማን ስለ ትንሺቱ ስለ ሚጋን እስከ አሁን የተረዳው ነገር አይኑር እንጂ ሂላሪ ለኢሊን እንደ ገረድ እያገለገለች ነው ያደገችው:: ለዓመታት በመጠለያ ቤትና በጠባይ ማረሚያ ውስጥ ኖራለች:: ከአክስቷ ባል ከጆንስ ክብረንፅህናዋን ብታተርፍም በመጠለያ ቤት ውስጥ በነበሩ ሦስት ወንዶች ልጆች አስደፍራለች:: በዚያን ወቅት ተከታይ እህቷ አሌክሳንድራ ፓሪስ ውስጥ ትምህት ቤት የምትመላለሰው በሲትሮይን መኪና እየተንፈላሰሰች ነበረ:: የሁለቱ እህትማማቾች ዕድል የለማይና የምድርን ያህል የተራራቀ ነበረ:: በመሆኑም ቻፕማን ሂላሪን አሁንም አስታወሰና አንጀቱ እስከሚላወስ አዘነላት::





«እባክዎን የእኔ እመቤት... ሲረዱኝ ቢሞክሩ ምን አለበት? ለአሌክሳንድራ የሚቀርቧት እርስዎ ነዎት... እናም ይህን ከባድ ነገር እኔ ከምነግራት ይልቅ በርስዎ በኩል እንድታውቀው ቢደረግ የተሻለ ይሆናል:: አለበለዚያ ግን እኔው ልነግራት ነው ማለት ነው» አለ ቻፕማን::

«ምን ብለህ ነው የምትነግራት?»

«ሁለት እህቶች እንዳሏትና በተለይም ሂላሪ የምትባለው ታላቅ እህቷ ከዓመታት በፊት ትንንሾቹን ለማግኘት ምን ያህል ጉጉት እንደነበራት»

«የሁለቱንም አድራሻ ደርሰህበታል ማለት ነው?»

ራሱንም ጭምር በማወዛወዝ «ለጊዜው አልደረስኩበትም እንደማገኛ ቸው ግን እርግጠኛ ነኝ» አላት::

«ታዲያ ያን ጊዜ ተመልሰህ መምጣቱ አይሻልም?»

«ምንም ጊዜ ለማባከን አልፈለግም:: እንደነገርኩዎት የሚስተር ፓተርሰን ጤና በጣም እየተዳከመ ነው::»

«ምነው ቀደም ሲል በሞተ ኖሮ! እስቲ ለስንት ሰው ሰላማዊ ኑሮ ጠንቅ ሲሆን ነው?» ብላ ተናገረች:: ለአሌክሳንድራ ስለ ወላጆቿም ሆነ ስለ እህቶቿ አንድም ቀን አንስታ አውርታባት አታውቅም:: ብትነግራት ስነ ልቦናዊ ተፅእኖ እንደሚኖረው ታውቃለች:: ስለዚህ ፎልፏላና ሳቂታዋ አሌክሳንድራ ደስ እንዳላት እንድታድግ ተንከባከበቻት:: አሁን ግን ይህ ከኒውዮርክ የመጣ እንግዳ ሰው መልካሙን ኑሮዋን ሊበጠብጠው ተቃርቧል:: ማርጋሬት ብትገድለው ደስታዋ ነበረ:: እርሱ ግን ሁኔታዋን ተረድቶ አዘነላት:: አሌክሳንድራን እንደ ጥሩ እናት ሆና ነው ያሳደገቻት:: አሌክሳንድራም ሌላ እናት እንዳላት አታውቅም፤ ለርሷ ወላጅ እናቷ ማርጋሬት ናት:: ይህንን ጠንካራ ግንኙነት እንደቀላል ነገር ማፍረስ ስህሲና ይከብዳል::

«አልነግራትም! በፍፁም አይሞከርም!» አለች ንዴት የሚያንፀባርቁ ዓይኖቿን በቻፕማን ላይ ሰክታ::

«እመቤት ማርጋሬት! ጭንቀትዎ ይሰማኛል:: ስለዚህም ማዘኔን ልገልፅልዎት እወዳለሁ::»

«ያልከው እውነት ከሆነ ለምን ለሚስተር ፓተርሰን አላገኘኋትም ስትል አትነግረውም?»

ቻፕማን ራሱን አወዛወዘ:: ለተሰማራበት ሙያ ትልቅ ፍቅር ብቻ ሳይሆን አክብሮትም ነበረው:: ውሸትም የሚናገር ሰው አልነበረም::

ማርጋሬት ፊቱን ስታጠና ቆየች:: ከዚያም "እስቲ ነገሩን እንዳስብበት ጥቂት ጊዜ ስጠኝ:: ለአሌክሳንድራም እንዴትና መቼ ልገልፅላት እንደምችል ዘዴ ልፍጠር:: በተለይ ስለወላጆቿ ስነግራት በጣም ልትደነግጥ ስለምትችል መላ መሻት አለብኝ አለችው::

ቻፕማን በህሊናው አንድ ነገር አስታወሰና ተፅናና:: ማርጋሬት የፈራችውን ያህል አሌክሳንድራ ላትደነግጥ ትችላለች:: አሌክሳንድራ ህፃን ልጅ ወይንም በዕድሜዋ ያልገፋች ልጃገረድ አይደለችም:: ብዙ ነገሮች ለማመዛዘን ስለምትችል የምትሰማውን ያልተጠበቀ ዜና ልትቋቋመው እንደምትችል አምኖበታል::

"በነገው ቀን ምሳ የምንበላው አብረን ነው:: ስለዚህም በዚያን ጊዜ ልነግራት እሞክር ይሆናል:: ሁኔታው አመቺ ከሆነ" አለች ማርጋሬት ራሷን እየተጠራጠረችው::

ቻፕማን ራሱን ዘንበል አደረገና "ያረፍኩት ብሪስትል ሆቴል ነው:: እኔም ብሆን አሌክሳንድራን ላነጋግራት እወዳለሁ:: ማለትም እርስዎ ዜናውን ካበሰሯት በኋላ"

"እርሷስ ልትገናኝህ ያልፈለገች እንደሆነ ሚስተር ቻፕማን? እሺ አትልም የሚል እምነት ነው ያለኝ" ብላ ማርጋሬት ዲ.ቦርን ከመቀመጫዋ ተነሳችና የመጥሪያ ደወሉን ተጫነች:: የቤት ሰራተኛው እንደገባ ቻፕማንን እንዲሸኘው ተናግራ 'ደህና ዋልም' ሳትለው እያለቀሰች ወደ ሌላ ክፍል ውስጥ ገባች::

የእመቤቱን ሁኔታ ያጤነው አሽከር ቻፕማንን በኃይል ከገላመጠው በኋላ ፊት ፊቱ እየሄደ ከምድር ቤቱ ደረሱ:: ከዚያም ቻፕማንን አስወጣና በሩን እስኪጮህ ዘጋው:: ዳግመኛ ቻፕማን ወደዚያ ቤት ቢመለስ የሚያስገባው ሰው እንደማይኖር ግልፅ ነበረ::





# ምዕራፍ አስራ ስምንት

ጌጣ ጌጥ የምትወደዋ ማርጋሬት ዲ.ቦርን፣ ያሸበረቁ ልብሶች የምታዘወትረዋ ሴት ዛሬ ጉትቻም፣ ቀለበትም አላደረገችም:: የለበሰችውም አንድ ወጥ የሆነ ፈዛዛ ሰማያዊ ቀሚስ ነበረ::

አሌክሳንድራ ፎቁን እየሮጠች ከወጣች በኋላ ከእንግዳ መቀበያው ክፍል ውስጥ ትጠብቃት ወደ ነበረችው እናቷ ገባች:: ተንደርድራም ከአንገቷ ላይ ተጠመጠመች:: የመነፋፈቃቸውን ያህል ተቃቅፈው ለረጅም ጊዜ ቆዩ:: ማርጋሬት ልጇን ከእቅፏ ላለመልቀቅ የፈለገች ይመስል እንቅ አድርጋ ነበር የያዘቻት:: ቆይቶ ቆይቶም ተላቀቁና በፍቅር ዓይን ተያዩ:: ያን ጊዜም ነበረ አሌክሳንድራ የእናቷን መልክና አለባበስ መቀያየር ያጤነችው::

"ምን ሆነሻል ዛሬ እማዬ? ሁኔታሽ ሁሉ ተቀያየረብኝ" ስትል ጠየቀቻት:: ማርጋሬት ጉተት አድርጋት አሁንም ከደረቷ አስጠጋቻት:: በመጠኑም ፈገግ ለማለት ሞከረች:: ግን አልሆነላትም:: ሲያለቅሱ ያደሩት ዓይኖቿም ውስጣዊ ስሜቷን በግልፅ ያንፀባርቁ ነበረ::

"ንገሪኝ እንጂ እማዬ? አንድ የደረሰብሽ ነገር መኖር አለበት" አለች አሁንም አሌክሳንድራ::

ማርጋሬት አንገቷን ሰበር አደረገችና፣ "ምንም አልሆንኩኝም አሌክሳንድራ ይልቅስ ነይ ምሳ እንብላ" ብላ ወደ ምግብ ጠረጴዛው አመራች::

አሌክሳንድራ ከኋላ ኋላዋ እየተከተለች "ምንም አልሆንኩኝም ብትይኝም አላምንሽም፤ አንድ የሆንሺው ነገር መኖር አለበት የዱሮዋ እማዬ አይደለሽም:: ፊትሽ ላይ የማነበው ሐዘን ነው:: ሌላው ቀርቶ የዛሬው አለባበስሽም ያልተለመደ ነው፤ እባክሽን እማዬ ምን ሆነሻል? ጨነቀኝ እኮ ንገሪኝ? አለበለዚያ አለቅሳለሁ" አለቻት::

"አታልቅሺ የእኔ ፍቅር! ትናንትና አንድ ዜና ከኒውዮርክ ስለ ደረሰኝ ነው ያዘንኩት እንጂ ለሌላ ነገር አይምሰልሽ" አለች ልታፅናናት በመሞከር::

ከዚያም የቀረበላቸውን ምሳ መመገብ እንደ ጀመሩ ማርጋሬት እንደ ወትሮዋ አንዳንድ የሰማቻቸውን ቀልዶች እያወራች ሁለቱም ይሳሳቁ ጀመረ። በእናቷም መዝናናት አሌክሳንድራ ለጊዜውም ቢሆን ቀልቧ መለስ ቢልም የደበቀቻት ምስጢር እንዳለ ተረድታ ነበረ።

“እማዬ!” አለቻት አሌክሳንድራ ዓይን ዓይኗን እያየች “አንድ ያስጨነቀሽ ነገር ለመኖሩ ምንም አልጠራጠርም። እባክሽን ንገሪኝ?” አለቻት። ፍርሃት የገባት ስለ እናቷ ጤና ነበረ። ባለፈው ሳምንት ሳይ የሕክምና ምርመራ የተደረገላት መሆኑን በስልክ ነግራት ነበረ። ሆኖም ሙሉ ጤነኛ መሆኗን ሐኪሟ የገለፁላት መሆኑን ጭምር ነበረ የገለፀችላት። 'ታዲያ የደበቀችኝ ነገር አለ ማለት ነው? እርሷ የደበቀችኝን እርሱ ይነግረኝ ይሆን?...' ስትል መመገቡን ትታ ማሰቧን ቀጠለች።

“ብይ እንጂ አሌክሳንድራ! ምንድነው የምታስቢው?” አለቻት እናቷ።

“እማዬ እንዴት ብዬ ልብላ? ሁኔታሽ እኮ በጣም ነው የተለዋወጠብኝ።”

“እስከዚህ ተለዋውጥኩብሽ ማለት ነው?” አለችና ማርጋሬት እንባ ያቆረዘዙ ዓይኖቿ እንዳይታዩባት አቀረቀረች። ያንንም በትናንትናው ዕለት ከቤቷ ድረስ መጥቶ ያነጋገራትን ጆን ቻፕማን የሚባል ሰው በሆዷ ተራገመች። እርሷ ባትነግራት እርሱ አድራሻዋን ፈልጎ እንደሚነግራት አስጠንቅቋታል። አሌክሳንድራ እንደዚያ ያለውን ዜና ከሌላ ሰው አንደበት ከምትሰማው ይልቅ እናቴ ከምትላትና ከምትወዳት ማርጋሬት መስማቷ እንደሚሻል ግልፅ ነው። ቡና ቀርቦላቸው እስኪጠጡም ሁለቱም ዝም ተባብለው ነበረ።

አሌክሳንድራ እጇን በጠረጴዛው ላይ አሻግራ የእናቷን እጅ ጭምቅ አድርጋ ያዘችና “አልነገርሽም አልሺኝ አይደል እማዬ?” አለቻት በሚለማመጡ ዓይኖቿ እያየቻት። ማርጋሬት ከእንግዲህ በአቀራረቧ ዘዴኛ መሆን እንጂ ሐቁን ከመናገር ሌላ አማራጭ አልነበራትም።

“ምን መሰለሽ አሌክሳንድራ፤ በትናንትናው ቀን አንድ በሕልሜም በውኔም ይደርሳል ብዬ ያልጠበቅኩት ነገር ተከሰተ” አለችና ታለቅስ ጀመረ። አሌክሳንድራ በድንጋጤ ከመቀመጫዋ ተነስታ የእናቷን አንገት አቀፈችና፤ “ምንድነው የተከሰተው እማዬ?” ብላ እርሷም ማልቀስ ጀመረች።





“እፎይ ...” አለችና ማርጋሬት በረጅሙ ተነፈሰች። ዓይኖቿንም በመሐረብ አደራረቀችና “ታሪኩን ከየት እንደምጀምርልሽ ይቸግረኛል። ረጅም ከመሆኑም በላይ ለማመን ይከብዳል” አለች። አሁንም በመሐረቧ ቀስ ብላ አፍንጫዋን ከጠረገች በኋላ፤ “ነይ ከጐኔ ተቀመጭና እጄን ያዢኝ። ከዚያም እነግርሻለሁ” አለቻት። አሌክሳንድራ ከእናቷ ጐን ተቀምጣ እጇን በማሻሸት ልታደፋፍራት ሞከረች።

“ከብዙ ዓመታት በፊት... ከብዙ ዓመታት በፊት ኮምት ደ.ቦርን ከማግባቴ አስቀድሞ ስለነበረን ኑሮ የምታስታውሺው አለ አሌክሳንድራ?” ስትል ጠየቀቻት።

“ምንም አላስታውስም እማማ” አለች አሌክሳንድራ ለመልስ አለጣጧ ሳትጨነቅ። ምናልባትም ብዙ ብታስብበትና ክብደት ብትሰጠው ኖሮ አንዳንድ ነገሮች ትዝ ባሏትም ነበረ። “ግን ለምንድነው ይህን ጥያቄ ያቀረብሽልኝ? እንዳስታውሰው የምትፈልጊው ነገር አለ ማለት ነው?” ስትል በተራዋ ለእናቷ ጥያቄ አቀረበች።

“ከኮምት ደ.ቦርን በፊት ሌላ ባል እንደነበረኝ አይታወስሽም? እስኪ ጥቂት ለማስታወስ ሞክሪ?”

ጥያቄው ለአሌክሳንድራ ከባድ ነበረ። እንደ እውነተኛ አባቷ የምትቆጥረው ኮምት ደ.ቦርን ነው። ዓይኖቿን ጨፍና ለብዙ ጊዜ ስታስብ ቆየች። በመጨረሻም ላይ ዓይኖቿን ከፍታ እናቷን በመገረም እያየች፤ “አሁን አስታወስኩ... ግን እኮ አሁን አንቺ ባትነግሪኝ አንዳችም ነገር ትዝ አይለኝም ነበረ። አባቴ ነው የምለው ኮምት ደ.ቦርን ብቻ ነው” አለቻት አሌክሳንድራ። እንደተናገረችው ሁሉ አንድም ጊዜ ሌላ አባት አለኝ ብላ ስታወራ ተሰምቶ አይታወቅም። በህፃንነቷ የተፈፀመው ሁሉ ከአእምሮዋ ተፍቋል።

ማርጋሬት ራሷን ዘንበል ቀና አደረገችና፤ “የኮምት ደ.ቦርን የጉዲፈቻ ልጅ ነበርሽ። ከርሱ በፊት ሌላ ባል ነበረኝ” አለቻት።

አሌክሳንድራ አሁንም ሌላ ትዝታ ተቀስቀሰባትና ፈገግ እንደ ማለት አለች። የኮምት ደ.ቦርን የጉዲፈቻ ልጅ የሆነችበት ዕለት ታወሳት። ከአንድ ጠበቃ ጋር ወደ ፍርድ ቤት እንደ ሄዱ... በዚያም አንዳንድ ሥነ ሥርዓቶች መፈፀማቸው... በምሽቱ ላይ በታላቁ የማክሲም ሆቴል ለብዙ እንግዶች ግብዣ እንደተደረገ... ለብሳው የነበረው ከወተት የነጣ ቀሚስ ... በተለይም የእናቷ ደስታ ተራ በተራ በዓይነ ህሊናዋ ታያት።

"ግን እኮ የጉዲፈቻ ልጅ ነኝ የሚል ጥርጣሬ አንዴም ተሰምቶኝ አያውቅም ነበረ" አለችና ሌላ ሐሳብ በአእምሮዋ ውስጥ ብልጭ ብሎ ወዲያውኑ ዕፍረት ስለተሰማት፤ "ነገሩ ሁሉ እንዲህ መሆኑን ባውቅ ኖሮ ሄነሪን ከማግባቴ በፊት ልነግረው በተገባ ነበረ:: ከነገስታት ዘር በመወለዱ ..."

"ታዲያ ይወለዳ! አንቺም ከኳምት ደ.ቦርን አብራክ ባትወጪም እንደ ልጁ አደርጎ ነው ያሳደገሽ:: ይልቁንስ ችግሩ ሌላ ነው" አለችና ማርጋሬት አቀረቀረች:: የተለመደውም እንባዋ ይተናነቃት ጀመረ::

"ሌላ ችግር? ግዴለሽም እማዬ ንገሪኝ? ሕፃን አይደለሁም! ብዙ ነገር ለማመዛዘን እችላለሁ" አለች አሌክሳንድራ የእናቷን እጅ በኃይል ጭብጥ አድርጋ::

"ምን መሰለሽ አሌክሳንድራ? አየሽ ከዚያም በፊት ..."

"እሺ!"

"እና ከዚያም በፊት አባት ነበረሽ"

"እኔ?"

"አዎን! እንግዲህ ጠንክር በይ! ህፃን አይደለሁም ብለሽኛል:: ሐቁን ሌላ ሰው ከሚነግርሽ ይልቅ ከእኔ አንደበት መስማቱ ይቀልሻል ለማስማት ዝግጁ ነሽ አሌክሳንድራ?"

"ፍርሐት ፍርሃት ቢለኝም ንገሪኝና ልረፈው::"

"እኔስ ለመናገር ያልፈራሁ መሰለሽ? የተረሳውን ነገር ሊያስታ ውስሽ ሌላ ሰው አቆብቁቦ በመጠባበቅ ላይ ባይሆን ኖሮ ብሞትም አልነግ ርሽም ነበረ:: ምን ላድርግ? አማራጭ በማጣቴ ነው አሌክሳንድራ"

"እንዳልሽው መስማቴ የማይቀር ነገር ከሆነ አንቺው ብትነግሪኝ ይሻለኛል እማዬ!"

"አይው አሌክሳንድራ! በጣም እንደምወድሽ፣ እንደ ዓይኔ ብሌን እንደምሳሳልሽ ታውቂያለሽ:: በዚህ ዓለም ውስጥ ለእኔ ያለሽኝ አንቺ ብቻ ነሽ:: ለቀናት ስንለያይ እንኳን እንዴት እንዴት እንደምናፍቅሽ ታውቂያለሽ:: ባልና ልጆች ባይኖሩሽ ከእኔ እንድትለይም ባልፈለግሁ ነበረ:: በአጠቃላይ የደስታዬ ምንጭ አንቺ ነሽ::"





"ይህ ሁሉ መሆኑን አውቃለሁ እማዬ!"

"እማዬ ስትይኝ የሚሰማኝ ኩራትና ደስታ ግን አታውቂውም:: ሌላ እማዬ የምትይው የለሽም:: ሆኖም እኔ ወላጅ እማዬሽ አይደለ ሁም::"

"ምን ማለትሽ ነው እባክሽ!"

"አዎን! ወላጅ አባትሽና እናትሽ ገና አምስት ዓመት ሳይሞላሽ ነው የሞቱት:: እኔና የፊተኛው ባሌ ጉርሐም ገና እንዳየንሽ ወደድንሽ ... እንድናሳድግሽ ፓተርሰን የሚባለውን የአባትሽን ጓደኛ ለመንነው ... አንቺንም በጉዲፈቻ ልጃችን አደረግንሽ..." ማርጋሬት እስከ መጨረሻው መናገር አልቻለችም:: ፊቷ በእንባ ታጥቦ ነበረ:: አሌክሳንድራ ግን የሰማችውን ማመን አቅቷት ፈዝዛ ታያታለች:: ምን ማለቷ ነው? የወለደችሽ ሌላ ሴት ናት ልትለኝ ነው? አይደረግም! ሳይታወቃት በማርጋሬት አንገት ላይ ተጠመጠመችና ታለቅስ ጀመረ::

"አንቺ ነሽ የወለድሽኝ! አንቺ ብቻ ነሽ እናቴ..." አለችና ከእቅፏ ወጥታ የምትሰወርባት ይመስል ተጣበቀችባት::

"የእኔን እናትነት ምንም ነገር እንደማይተካው አውቃለሁ፤ እናትሽ ነበርኩ... እናትሽ ነኝ... ወደፊትም ያለሁሽ እኔ ብቻ ነኝ:: ግን አንድ ሌላ ማወቅ ያለብሽ ነገር ስላለ አሌክሳንድራ አዳምጪኝ" አለችና ማርጋሬት ዓይኖቿንና አፍንጫዋን ጠራረገች::

"በግድ ማወቅ አለብኝ?"

"አዎን! እንደዚያማ ባይሆን ኖሮ ለምንስ የተረሳ ነገር አንስቼ ጤናማዋን ልጄን እበጠብጥሽ ነበረ:: ስለዚህ አሌክሳንድራ ትዕግስት ኖሮሽ ታሪኩን አድምጪኝ"

"በይ ይሁና እማዬ! ንገሪኝ" አለቻት::

"ወላጆችሽ የሞቱት የአምስት ዓመት ህፃን ሆነሽ ነው:: እናትሽ በሞተች በሶስተኛው ቀን አባትሽም ሞተ:: የነበራችሁ ዘመድ ከአባትሽ በኩል የሆነች አንድ አክስታችሁ ብቻ ነበረች:: ግን ሴትየዋ ኃላፊነት የሚሰማት ዓይነት ባለመሆኗ ያ ፓተርሰን ያልኩሽ የአባትሽ ጓደኛ ስለ ሁኔታው ለጉርሐም አጫውቶት ነበረ:: እኛም ገና አንቺን እንዳየንሽ ደስ አለሺን:: እንደ ልጃችንም ልናሳድግሽ ወሰድንሽ:: በዓለምም ውስጥ እንደኛ ደስተኛ ሰው አልነበረም:: ሆኖም ባሌ ከስድስት ወራት በኋላ በመሞቱ

ይገፎሽ ወደ ፈረንሳይ ሀገር መጣሁ:: ከዚያ በኋላ የሆነውን ሁሉ የምታውቂው ነው" አለቻት::

አሌክሳንድራ አሁንም ታወጣና ታወርድ የነበረው እንዴት ከማርጋሬት ሌላ የወለደቻት እናት ልትኖር እንደምትችል ነው:: በመጠራጠሯም በቅድሚያ ጥያቄ ያቀረበችው: "እንዳልሺው የወለደችኝ ሌላ ሴት ከሆነች ምን ሆና ነው የሞተችው?" ስትል ነበረ::

ማርጋሬት በዚህ ባልታሰበ ጥያቄ ወገቧ ቁምጥ ሲል ተሰማት ዓይኖቿንም ጨፍና ለጥቂት ጊዜ አቀርቅራ ቆየች:: ምን ብላ ትመልስላት? ለአሌክሳንድራ... ለምትወዳት ለምታፈቅራት ልጇ አንድም ቀን ሐሰት ቃል ተናግራት አታውቅም:: ዛሬስ? ካቀረቀረችበት ቀና ብላ ዓይኖቿን ከፈተች:: ከዚያም ረጋ ብላ ተናገረች::

"አንድ ምሽት በወላጆቻችሁ መካከል የከረረ አለመግባባት ተፈጥሮ ነበረ:: አየሽ እርሱ በአሜሪካ ውስጥ ዕውቅ ተዋናይ ነበረ:: እርሷ ደግሞ በጣም ውብ ሴት ነበረች ..."

"የእኔ ጥያቄ ያ አይደለም እማማ" አለችና አሌክሳንድራ የሆነ ነገር ትዝ ያላት ይመስል ተንሰቅስቃ ታለቅስ ጀመረ:: በእርግጥም የማርጋሬት ጭንቀት ከዓመታት በፊት የተፈፀመ ድርጊት ሊያስታውሳት በቅቷል:: ግን ከማርጋሬት አፍ ልትሰማው በመፈለግ፤ "እናቴ ምን ሆና ነው የሞተችው?" ስትል በድጋሚ ጠየቀቻት::

"አባትሽ ነው የገደላት"

አሌክሳንድራ ከፊት ለፊቷ በነበረው መስኮት ውስጥ ይታይ ከነበረው የአበቦች መደብ ላይ እንባ የሚንቀረቀራቸውን ዓይኖቿን ለክታ በአእምሮዋ ነገር አመላለሰች:: ነጭ ፅጌረዳ!... የሬሳ ሳጥን !... ነጭ ጽጌረዳ! የሬሳ ሳጥን!... "አባቴም 'ሕይወቱን በገዛ እጁ አጠፋ! ራሱን ለቀለ' ብለው ሲያወሩ የሰማሁት ነው አይደል?" አለችና ስቅስቅ እያለች አለቀሰች:: ማርጋሬት ከደረቷ እቅፍ አደረገቻትና አልቅሳ እስኪወጣላት እንደ ህፃን ፀጉሯን ስታሻሽላት ቆየች::

"እንዴት ተረሳኝ?... ለካስ ሁሉም ነገር ተረስቶኝ ኖሯል?... የእናቴ ፀጉር እንደኔ ፀጉር ወርቃማ ነበረ... ይህን ሁሉ ረስቼው ኖሯል" አለችና ከመቀፅበት በወላጆቿ ትዝታ የወየበውን ፊቷን ቀና በማድረግ "ፈረንሳዊ አልነበረችም?" ስትል ማርጋሬትን ጠየቀቻት::





"አዎን ነበረች" አለቻት ማርጋሬት:: በተለይ ስለ እናቷ ወርቃማ ፀጉር ማንሳቷ ማርጋሬትን አስደነቃት:: የአሌክሳንድራም ፀጉር ያው ወርቃማ ነው:: የዘር ነገር ሆኖ የአሌክሳንድራ ትንሿ ልጅ አክሲል ባለ ወርቃማ ፀጉር ናት:: ማርጋሬት አክሴልን ባየቻት ቁጥር የምታስታውሳት የዱሮዋን ህፃኗን አሌክሳንድራን ነበረ::

"ግን አባቴ ለምንድነው ሕይወቱን ያጠፋው? እናቴን ስለገደላት ተፀፅቶ ነው?" አለች አሌክሳንደራ:: ዱሮ ዱሮ የረሳቻቸውን ነገሮች ሁሉ አሁን ለማወቅ ፈለገች::

"ሲገድላት ሕሊናውን ስቶ ነበረ ይባላል:: ንዴቱ እየበረደለት ሲሄድ የፈፀመው ጨካኝ ተግባር ታወሰው:: እናታችሁንም በጣም ይወዳት ስለነበረ፤ እርሷ በተቀበረችበት ዕለት እርሱም ሕይወቱን አጠፋ:: ከዚያም አንቺና..." ብላ ማርጋሬት ዝም አለች:: ለመናገር የከበዳት የታሪኩ ዋና ክፍል ከዚያ የሚቀጥለው ነበረ:: የአሌክሳንድራን እጆች እንቅ አድርጋ ያዘችና እነኛን አለንጋ የሚመስሉ ጣቶቿን ታሻሸቸው ጀመረ:: እንደ እውነቱ ከሆነ አሌክሳንድራና ማርጋሬት በመልክም በቁመናም አይመሳሰሉም ነበረ:: ለዚህም ልዩነታቸው አሌክሳንድራ ዋጋ ሰጥታው አታውቅም:: ዛሬ ግን ለምን እንደሆነ ገባት:: የእውነተኛ እናቷም ወርቃማ ፀጉር ተመላልሶ በዓኖቿ ላይ አለፈ:: መልኳን ግን እንዲህ ነው ለማለት ተዘንግቷታል::

"ሌሎችም ... ሌሎችም ሁለት እህቶች ነበሩሽ" አለች ማርጋሬት ቃላቱን ለመናገር የማማጥ ያህል ተጨንቃ፤ የአሌክሳንድራ ሰውነት በስለት የተወጋ ያህል ተኰመታተረ:: እነኛም ቃላት አእምሮዋ ውስጥ እንደ ገደል ማሚቶ ደግመው ደጋግመው ጮሁባት:: ሁለት እህቶች! ...ሁለት እህቶች!... አዎን ሁለት እህቶች!... ትዝ አላት:: ከመኪና መንገድ ዳር ተንበርክካ ታለቅስ የነበረችው እህቷ! ሂሊ!... ሂላሪ...ሂሊ! "አክሲ እወድሻለሁ... ምን ጊዜም እንደምወድሽ እንዳትረሺ!" የአሌክሳንድራ ፊት በዕንባ ታጠበ:: ጨሂ ጨሂ ሲል ከውስጥ የሚገፋፋትን ስሜት ለመቆጣጠር ጉሮሮዋን አነቀችው:: ከተቀመጠችበትም ተነስታ ወደ መስኮቱ ሄደችና ዓይኖቿን ከውጭ በሚታዩት አበቦች ላይ ለክታ ስታስብ ቆየች:: የሂላሪ ጥቁር ፀጉር ... የትንሿ እህቷ ጠረን ...

"ሶስታችሁንም ወስደን ለማሳደግ ባለመቻላችን አሌክሳንድራ በጣም ነው የማዝነው" ስትል ማርጋሬት ከሐሳቧ ልትመልሳት ብትሞክርም አልቻለችም:: የሚታያት ከእህቶቿ ጋር የተለያየችበት ያ ዕለት ነበረ:: በተለይ ሂላሪ ከመንገድ ዳር ተንበርክካ 'ምን ጊዜም እንደምወድሽ እንድ

ታውቂ ... አክሲ እወድሻለሁ' ስትል የተናገረቻት ... የትንሿ እህቷ የዚያን ዕለት የመረረ ለቅሶ ... ስሟ ማን ነበረ?

በድንገት ዘወር አለችና "የትንሿ እህቴን ስም ታውቂዋለሽ እማማ?" ስትል ማርጋሬት ጠየቀቻት።

"አላውቀውም የማስታውሰው ቿላቅና ታናሽ እህቶች እንዳሉሽ ብቻ ነው" አለች ማርጋሬት።

"እኔስ ብሆን ስሟን እንዴት ለመዘንጋት በቃሁ?" አለች አሌክሳንድራ በፀፀት እራሷን እየታዘበች።

"አይፈረድብሽም አሌክሳንድራ! በዚያ በጨቅላ ዕድሜሽ ብዙ ሐዘን ደርሶብሻል። ስለዚህ መርሳቱ ይሻልሽ ነበር እላለሁ። እናንተ ምንም ያጠፋችሁት ነገር የለም። ስለዚህም አዲስ ኑሮ የመኖር መብት አላችሁ። ስለዚህ ነው እኛም አንቺን ደስ ብሎሽ በእንክብካቤ እንድታድጊ ያደረግነው።"

"አውቃለሁ እማማ! ምንጊዜም ቢሆን ለእኔ እናቴ አንቺ ነሽ። ዛሬ የሰማሁት ታሪክ በምንም ዓይነት ያንቺንና የእኔን እናትና ልጅነት አይቀይረውም።"

"እርግጠኛ ነሽ?" አለቻት ማርጋሬት በመጠራጠሯ ሐፍረት ሳይሰማት።

"እመኚኝ እማዬ!" አለች አሌክሳንድራ።

"እስቲ ከኒውዮርክ ፓሪስ ድረስ በመምጣት ባይበጠብጡን ምናለበት ነበረ? መቼ በመካከላችን ጥርጣሬስ ይፈጠር ነበረ?"

"እነማን ናቸው እነሱ?"

"ቀንደኛው አርዘር ፓተርሰን ይባላል። የአባታችሁ የቅርብ ጓደኛ ነበረ። እርሱ ነው ለእኛ በጉዲፈቻ ልጅነት የሰጠን። ወደ ፓሪስ የመጣው የርሱ ወኪል ነው። አንቺና ሌሎቹም እህቶችሽ በህይወት መኖራችሁን ለማረጋገጥ ይፈልጋል። ከዚያም እንድትገናኙ ለማድረግ ነው ዕቅዱ።"

"የሌሎቹንስ አድራሻ አውቀውታል?"

"እስከአሁን አልደረሱበትም። በማፈላለግ ላይ መሆናቸውን ግን አውቃለሁ። አንቺን እንዳገኘሽ የተቀሩትን ያገኛቸዋል የሚል ግምት ነው ያለኝ።"





አሌክሳንድራ አሁንም ወደ መስኮቱ ዞራ ዓይኖቿን አበቦቹ ላይ ለክታ በሐሳብ ተመሰጠች። የሰማችው ታሪክ ለጆሮ የሚከብድ ነበረ። በአንድ ቀን ውስጥ ለዚያውም ከምሳ በኋላ ባሉት ሰዓታት ብቻ የአሌክሳንድራ የቤተሰብ ታሪኳ ተቀይሯል። ባለ ሁለት እህቶች ለመሆን በቅታለች። ፈረንሳዊና ባለወርቃማ ፀጉር የነበረች እናት እንደነበረቻትም አስታውሳለች። ሚስቱን ገድሎ የራሱንም ሕይወት ያጠፋው አባቷ ትዝ ይላታል። ከአንድም ሁለት የጉዲፈቻ አባቶች እንደነበሯት ዛሬ ተነግሯታል። ዕድሜዋን ሙሉ እናቴ ናት የምትላትን ማርጋሬት ወላጅ እናቷ አለመሆኗን አውቃለች። ይህን ሁሉ ታሪክ ሰምቶ በአንድ ጊዜ ማጣጣሙ ከበዳትና፤ "ወይን ጠጅ ብታስመጪልኝ እማማ?" አለች ዞር አለችና።

"መጠጥስ ላንቺ ብቻ ሳይሆን ለኔም ያስፈልገኛል" አለችና የመጥሪያውን ደወል ተጫነች። ሰራተኛው እንደገባ የሚጠጣ እንዲያ መጣላቸው አዛ ወደ አሌክሳንድራ እያየች፤ "ለመሆኑ ከእህቶችሽ ጋር ለመገናኘት ትፈልጊያለሽ?" ስትል ጠየቀቻት።

"ለምን አልፈልግም? እርግጥ ከተለያየን ከሰላሳ ዓመት በላይ ሆኖናል ተረሳስተናልም። ደግሞም የየግል ኑሮአችንን መስርተናል። ግን ያም ሆኖ እህቶቼን ዛሬውኑ ባገኛቸው ደስታዬ ነው" አለች አሌክሳንድራ።

"ጥያቄውን ያቀረብኩልሽ ለምን መሰለሽ? የባልሽን የሄነሪን ነገር ታውቂዋለሽ በዘሩ በጣም የሚኩራራ ሰው ነው። አንቺንም ያገባሽ የኮምደ.ቦርን ልጅ መስለሽው ነው። ታዲያ እውነተኛውን ታሪክሽን ከሰማ በትዳራችሁ ላይ ችግር እንዳያስከትል ብዬ ነው።"

"ለምን? ከወደደኝ ስለ ቤተሰቤ ታሪክ ምን ያገባዋል? እርግጥ ታሪኩ ሊያስደነግጠው ይችላል። የማይቀር ነው።"

"እንዳይሰማ ብንደብቀውስ?"

"ይሄስ የማይሆን ነው እማማ! የዛሬ ወሬ ሊደበቅ አይችልም፤ ውሎ ይደር እንጂ መሰማቱ አይቀርም። ይልቅስ ያን ጊዜ ነው የበለጠ ሊናደድ የሚችለው። እና እኔ ብነግረው ይሻላል። ይኼንን የመሰለ ሚስጥር ከምወደው ባሌ መደበቅ ማለት አታላይነትም መስሎ ይሰማኛል።"

"እኔ ግን ፈርቻለሁ አሌክሳንድራ!"

"መፍራትሽ ልክ ነው። በኮምት ደ.ቦርን ልጅነቴ ምን ያህል እንደሚኮራብኝ አውቀዋለሁ። አንቺን እንኳን አሜሪካዊ በመሆንሽ እንዴት

እንደሚንቅሽ ራስሽ የምትረጂው ነው:: እውነተኛው አባቴ ኮምት ዴቦርን ሳይሆን አንድ አሜሪካዊ ተዋናይ፤ ለዚያውም ፈረንሳዊት ሚስቱን የገደለ መሆኑን ሲሰማ ምን እንደሚል ይታወቀኛል:: ደግነቱ የልብ ድካም የለበትም እንጂ በድንጋጤ ከአደጋ ላይ ሊወድቅ እንደሚችል ይሰማኛል:: ጋብቻችን እንዲፈርስ ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል:: ልጆቼንም ሊቀማኝ ይችላል ስል እኔም እሰጋለሁ:: ግን ይህ ሁሉ ሆኖ ልነግረው ግዴታ አለብኝ"

ማርጋሬት የቀረበላትን መጠጥ ቶጉነጨችና "አሌክሳንድራ! የሄነሪ ሚስት ስለሆንሽ ፍፁም ታማኝና ታዛዥ ሚስቱ ነሽ ማለት አይደለም:: የምትለብሺውን ልብስ የሚመርጥልሽ እሱ ነው፡ ስለ ፀጉር አሰራርሽ መመሪያ የሚሰጥሽ እሱ ነው:: እንደ ሚስት ሳይሆን እንደ ገረድ ነው የሚያዝሽ:: በዚህም ሁኔታ መኖርን ስለተላመድሽው ለሄነሪ ፍፁም ታማኝ ለመሆን በቅተሻል:: ግን ሚስት ብትሆንም አንዳንድ ጊዜ የግሏ የሆነ ሚስጥር ሊኖራት ይችላል:: ስለዚህ እንደኔ ዛሬ የለማሽውን ታሪክ የግል ሚስጥርሽ አድርጊ ነው የምልሽ!"

"ግን እኮ እማማ እስከመቼ ደብቄው ልቆይ እችላለሁ? ለምሳሌ እህቶቼ ተገኙ እንበል:: የሚኖሩትም በአሜሪካ ይሁን፤ ታዲያ ላያቸው ወደዚያ መሄዴ አይቀርም:: እና በዚያ ጊዜ ለሄነሪ ምን ምክንያት እሰጠዋለሁ?"

"ጥሩ! እንግዲያውስ እንዲህ ይሁን:: እህቶችሽ ለመገኘታቸው መጀመሪያ እርግጠኞች እንሁን:: ከዚያ ማድረግ ስለሚኖርብሽ ዘዴ እንፈልጋለን" አለችና ማርጋሬት በቁራጭ ወረቀት ላይ የጆን ቻፕማንን ስምና አድራሻ ፅፋ እየሰጠቻት፤ "ከኒውዮርክ የመጣው ሰውዬ ሊያነጋግርሽ ይፈልጋል:: የስልክ ቁጥሩንም ስለፃፍኩልሽ ደውለሽ አነጋግሪው" አለቻት::

"ለምን ሊያነጋግረኝ ፈለገ?"

"በህይወት ስለመኖርሽ እርግጠኛ ለመሆን ሲል ይሆናል::"

"እንደዚያስ ከሆነ እደውልለታለሁ" ብላ ቁራጯን ወረቀት ከቦርሳዋ ውስጥ ከተተችና ሰዓቷን ተመለከተች:: ድንጋጤ ተሰማት አስራ አንድ ሰዓት አልፎ ነበረ:: ቶሎ ወደ ባሏና ልጆቿ መመለስ ነበረባት:: ከእናቷ ጋር ምሳ ለመብላት ሄነሪ የፈቀደላት ሁለት ሰዓት ብቻ ነው:: በጣም እንደሚቆጣት ታውቀዋለች::





ማርጋሬት ከምድር ቤቱ በር ድረስ ሸኘቻት:: ልትለያትም ስትል ከደረቷ እቅፍ አድርጋት እንደገና አሰቀለች::

"እማዬ በጣም እንደምወድሽ ታውቂያለሽ! እባክሽን አታልቅሺ!" አለቻት አሌክሳንድራ::

"እሺ አላለቅስም:: ግን እንደ ድሮው የእኔዋ ትንሿ አሌክሳንድራ ዛሬም ትወጂኛለሽ?"

"ይበልጥ እማዬ! በእግዚአብሔር ስም እምልልሻለሁ!" አለችና ተራዋን እናቷን እቅፍ አድርጋ ጉንጮቿን ሳመቻት::

በእነኛ የሰዓት በኋላ ሰዓታት አሌክሳንድራ ደስታና ሐዘን ተፈራር ቀውባታል:: ለእናቷና ለአባቷ አልቅሳላቸዋለች:: ሂሊን... ሂላሪን አስታውሳበታለች:: ከስሯ የማትለያት እንደ እናት የምትንለፈለፍላት ሂላሪ ገላዋን አጥባ፣ ፀጉሯን ታበጥርላት የነበረችው ሂላሪ ታየቻት:: 'አክሲ ምን ጊዜም እንደምወድሽ አትርሺ ...' የሚሉት የእህቷ የመለናበቻ ቃላት ታውሷት:: የአሌክሳንድራ እንባ ዠረር ብሎ ወረደ:: ሐሳቧም ከሂላሪ ስሟን ወደ ረሳችው አራስ እህቷ እንደገናም ተመልሶ ወደ ሂላሪ ከዚያም ወደ ትንሿ እህቷ እንደተመላለሰ በሹፌር የሚነዳው ሲትሮይን መኪናዋ ከቤቷ ደረሰ::

# ምዕራፍ አሥራ ዘጠኝ

አሌክሳንድራ እቤቷ ከገባች በኋላ እንኳን መልኳ እንደተሰዋወጠ ነበረ፡፡ ማርጋሬት የነገረቻትን ሁሉ ማስታወሱ በጣም ነው የከበዳት፡፡ የምትንቀሳቀሰውም በሕልም ዓለም ውስጥ መስላት፡፡ ከብዙ ዓመታት በፊት ታውቃት የነበረችው ባለወርቃማ ፀጉር ሴት... ሂሲ ትላት የነበረችው ልጅ ... አሁን ስሟን ብትዘነጋውም አልጋ ላይ አስተኝታ እየኮረኮረች ታስቃት የነበረችው ትንሽ ልጅ... እንደ ብርቅርቅታ በዓይኖቿ ላይ ብልጭ ድርግም እያሉባት ነበረ፡፡

ትከሻዎቿ ከባድ ሸክም እንደተሸከመ ሰው ጉብጠው፤ ወደ መኝታ ክፍሏ የሚወስደውን ደረጃ በመውጣት ላይ እንዳለች "ለምን ዘገየሽ?" የሚል የወንድ ድምፅ አምባረቀባት፡፡ ለጥቂት ጊዜ ያህል ባለችበት ክው ብላ ከቆየች በኋላ ዘወር ብላ ተመለከተች፡፡ የጫማዋን ኮቴ የሰማው ባሏ ሄነሪ ከጥናት ክፍሉ በር ላይ ቆሞ ነበረ ጥያቄውን ያቀረበላት፡፡

"እማማን የማግዛት አንዳንድ ሥራዎች ስለነበሩ ነው የዘገየሁት፡፡ ገንዘብን በሚመለከቱ አንዳንድ ሰነዶች ስንመረምር ሳይታወቀኝ ጊዜው አለፈ፡፡ ይቅርታ አድርግልኝ ሄነሪ" አለችው፡፡ ራቅ ብሎ በመቆሙ እንጂ ዓይኖቿ አሁንም እንባ እንደቋጠሩ መሆናቸውን በቀላሉ ባየ ነበረ፡፡

"አላምንሽም! ስለዚህ በትክክል የት እንደቆየሽ ንገሪኝ?" አላት ወደ ደረጃው እየመጣ፡፡

"እውነቱን ነው የነገርኩህ ..." አለችው ከዚያ ቀረብ ቢል በማልቀሷ እንዳይነቃባት እየፈራች "ከእናቴ ቤት በስተቀር የትም አልሄድኩም" ስትልም ጨመረችበት፡፡

"የማይመስል ነው! በስድስት ሰዓት የወጣሽ ሴት እስከ አስራ ሁለት ሰዓት እናቴ ቤት ቆየሁ ብትይኝ አላምንም!" አነጋገሩ የንዴት ነበረ፡፡ አሌክሳንድራ መረር ብላ ካልተናገረችው ንዝንዙን እንደሚቀጥል ታወቃት፡፡ ቀኑን እንደዚያ እንዳላሳለፈች አሁን ደግሞ ሌላ ትካዜ ውስጥ ለመግባት አልፈለገችም፡፡





"ብታምንም ባታምንም አንድ ጊዜ እናቴ ቤት ነበርኩ ስል ነግሬሃለሁ፡፡ ስለመዘግየቴ ደግሞ እራሴው ፀፀት ተሰምቶኝ ይቅርታ ጠይቄሃለሁ" አለችው ኮስተርተር ብላ፡፡

ንዴቱ ባይበርድላትም ደረጃውን ለመውጣት ሰንዝሮት የነበረውን እግሩን መልሶ "ዳግመኛ ግን እንዳይደገም! እርሷስ ብትሆን ለምንድነው እንድትዘገይ የምታደርግሽ? የማን ሚስት መሆንሽንና ከባድ ኃላፊነት እንዳለብሽ ሳትረዳው ቀርታ ነው? ዘልዛላ ..." ለሰና ሊናገር የፈለገውን ቃል ውጦ አስቀረው፡፡ ከማርጋሬት ጋር በዕድሜ ስለሚቀራረቡ አሮጊት ብሎ እንደማይሰድባት ግልፅ ነው፡፡ ምናልባትም በአሜሪካዊነቷ በግዴለሽነቷ ሊሰድባት ይችላል፡፡

አሌክሳንድራ መልስ ሳትሰጠው ከንፈሯን ነክሳ አየችው፡፡ እናቷ ያቆየቻት ለቀላል ጉዳይ አልነበረም፡፡ ሁለት የጉዲፈቻ አባቶች እንደነበሯት አስታውቃታለች... ወላጅ አባቷ እናቷን እንደገደላት ነግራታለች... እስከ ጭራሹም ረስታቸው የነበሩትን እህቶቿን አስታውሳታለች፡፡ ይህ እንግዲህ የሚያስድባት ነው? ሄነሪስ እንደሚገምተው ቀላል ነገር ነበረ?

ዝም እንዳለችው ዞረችና ወደ መኝታ ክፍሏ ገባች፡፡ በዚያን ምሽት የራት ግብዣ ስለነበረባቸው ቀደም ሲል መርጣው የነበረውንም ልብስ ቶሎ ቶሎ መቀየር ጀመረች፡፡ ፊቷን ከተጣጠበችና ፀጉሯን ካበጠረች በኋላ ሳሳ አድርጋ የከንፈር ቀለም ተቀባች፡፡ ሃያ ደቂቃዎች ባልፈጀ ጊዜ ውስጥ ከምድር ቤት ወደሚጠብቃት ባሏ ወረደች፡፡ የሚመስሉትም እጅግ አምሽተው ስለሚሆን ከአባታቸው ጋር ቆመው የነበሩትን ሁለት ልጆቿን "ደህና እደሩ" ስትል ግንባራቸውን ሳመች፡፡ በዚያን ጊዜም እንባዋ እንደገና አቀረረ፡፡ እነኛ ረስታቸው የነበረችውን እህቶቿን አስታወሰችና ካገኑበስች በት ቀና ሳትል "እናንተ ሁለታችሁም ዕድለኞች ናችሁ፡፡ ስለዚህ ልትፋቀሩ ይገባል" አለቻቸው፡፡ እንዳለችውም እንደርሷ የሚንሰፈሰፍላቸው እናት እንደ ሄነሪ ያለ ቆፍጣና አባት ነበራቸው፡፡ እርሷም ብትሆን ሲበዛ ዕድለኛ ናት ለማለት ይቻላል፡፡ የማርጋሬትና የኮምት ደ.ቦርን የጉዲፈቻ ልጅ ሆኖ ማደግ የሚቀናበት ነበረ፡፡ ቀና ብላም ሄነሪን አየችውና ምሥጢሯን በመደበቋ ኃፍረት ተሰማት፡፡

"እንደነገርሽኝ ከሆነና እውነትም ችግር ከገጠማት እናትሽ ባለሙያ ከሆኑ ጠበቆች ወይንም የባንክ ባለስልጣኖች ጋር ለምን አትወያይም? አንቺ ገንዘብ ጠቀስ በሆኑ ጉዳዮች ልዩ ችሎታ ያለሽ አይደለሽም" አላት ሄነሪ ወደ ግብዣው ቦታ በመጓዝ ላይ እንዳሉ፡፡

አሌክሳንደራ ወዲያው አልመለሰችለትም:: ፊዝዛም በመስታወት ውስጥ ውጪ ውጪውን ታይ ነበረ:: ቆይታም "ችሎታ ባይኖረኝም እናቴ ችግሯን ልታዋየኝ ፈለገች:: ሳይታወቀንም ሰዓቱ አለፈ" አለች::

በሰጠችው መልስ ስላልረካ ሄነሪ ወደ ጐን አየት አደረጋትና "እንደዚያም ቢሆን እኔን ብታነጋግረኝ ይተሻላት ነበረ:: ቢያንስ ቢያንስ ካንቺ በተሻለ ሁኔታ ልረዳት እንደምችል ታውቃለች" አላት:: እንዲያውም ምን ልናገር ሲል ከአፉ ወጥቶ ካልሆነ በስተቀር ማርጋሬትን እንደማይወዳት ስለምታውቅ ከርሱ እርዳታ የምትጠይቅ ሴት ሆና አይደለም እንደዚያ ማለቱ::

ባቴለስ ሆቴል ደርሰው ሄነሪ እጇን ይዞ ይጠባበቋቸው ወደነበሩት እንግዶች ጠረጴዛ ሲወስዳት አሁንም አሌክሳንድራ ፍዝዝ እንዳለች ነበረች:: የዚያን ትልቅ ሆቴል አዳራሽ የሞሉት የፓሪስ ታላላቅ ሰዎች ናቸው:: ወንዶቹ ሁሉም ጥቁር ሱፍ ለብሰው ከረባት አስረዋል:: አብረዋቸውም የነበሩት ቆነጃጅት በልዩ ልዩ ጌጣ ጌጦች ተውበዋል:: ሄነሪ ለዛሬ እራት ግብዣ የጠራቸው ሰዎችም የመንግስት መስሪያ ቤት ባለስልጣኖች ነበሩ:: በፖለቲካው ዓለም ለመሳተፍ ላለው ዕቅድ የእነኚህ ሰዎች እርዳታ እንደሚያስፈልገው ግልፅ ነበረ:: ውይይታቸው ቁም ነገር አዘል ቢሆንም አሌክሳንድራ ግን በመንፈስ ከነርሱ ጋር አልነበረችም:: ያሳለፈችውን ታሪክ በሐሳቧ ትዳስስና መጨረሻ ላይ ያቺ ከመንገድ ዳር ተንበርክካ ታለቅስ የነበረችው ባለጥቁር ፀጉር ልጅ ትታያታለች...ሂሲ ...ሂሲ ... 'አክሲ ምንጊዜም እንደምወድሽ እንድታውቂ ...'

በዚያን ምሽት አሌክሳንድራ ከአስር ጊዜ በላይ በዓይኖቿ ግጥም የሚለውን እንባዋን ታግላ ውጣዋለች:: ሰዎቹም የሚናገሩትን አንዱንም አልሰማችም:: ለሚያቀርቡላት ጥያቄ እንኳን በትክክል ለመመለስ ባለመቻሏ የባሏ እንጀት እርሮ ነበረ:: አንድም ምሽት እንደዚያ ምሽት ሰልችቷትና ረዝሞባት አያውቅም::

የራት ግብዣው አልቆ ወደ ቤት በመመለስ ላይ እንዳሉ ሄነሪ መኪናቸውን የሚነዳው ሹፌር እንደሚሰማ ቢያውቀውም "በዛሬው ሁኔታሽ አፍሬብሻለሁ:: በጣም ነው ያዘንኩብሽ" አላት በምሬት::

"ይቅርታ አድርግልኝ ሄነሪ ... ዛሬ አእምሮዬ ልክ አይደለም ... ሐሳቤን ማሰባሰብ ተቸግሬ ነበረ ... እኔ ..." አለችና ዝም አለች:: የሚታሰባት የነገው ውሎዋ ነገር ነበረ:: በብሪስተል ሆቴል የሚገኘው ጆን ቻፕማን





የተባለውን ሰው ለማነጋገር ጥድፊያዋ ጥድፊያ አያህልም::

"ጨነኛነት ካልተሰማሽ መምጣት አልነበረብሽም! የዛሬው አድራጐትሽ ምን ያህል ሊጐዳኝ እንደሚችል አታውቂም?" አላት ወደ ጐን ዓይኑን አፍጥጦ እያያት::

"የመጣሁት አንተን ለማስደሰት ብቻ ነው ... ደግሞም ከሰዎቹ ጋር ለመጫወት ሞክሬ ነበር... ግን መንፈሴ ስለተረበሸ..." አለችና ሳይታወቃት ዕንባዋ በጉንጮቿ ላይ እየተንከባለለ ወረደ:: ሄነሪን ፈፅሞ ልታሳዝነው አንድም ቀን ሞክራ አታውቅም:: አትፈልግም::

"የምትደረድሪውን የይቅርታ ጋጋታ አልቀበለውም!" ሲል ጮኸባት:: ልክ ተማሪ ሲያጠፋ መምህሩ ሲቆጣው እንደሚሰማው ዓይነት ስሜት ነበረ አሌክሳንድራ ያደረባት:: "ደግሞም ያቺ እናትሽ ..."

"እናቴን እዚህ ውስጥ የሚያገባት ነገር የለም ሄነሪ!" አለችው በመጠኑም ቢሆን እንደ መናደድ ብላ::

"ለምን አያገባትም? እስከ አስራ ሁለት ሰዓት ድረስ የት ነው የቆየሽው?" ሲል እንደ አዲስ ነገር ጠየቃት::

አሌክሳንድራ ራሷን በትዝብት አወዛወዘችና ውጪ ውጪውን ስታይ ቆይታ በመጨረሻም ላይ ዞር ብላ "ከእናቴ ጋር ነው ስል አንድ ጊዜ ነግሬሃለሁ" አለችው::

"ሌላስ ሰው አልነበረም?" ሲል ጠየቃት::

ሄነሪ ሚስቱን ሲጠረጥራት የመጀመሪያው ጊዜ ነው:: ለዚህም በመብቃቱ አሌክሳንድራ በጣም በማዘኗ "ሌላስ ሰው የለም? ስለ እግዚአብሔር! እንዳው ምን ታደርጋለች የሚል ስጋት ገብቶህ ይሆን?" አለችው:: ባይሆን እርሱ ነበረ ከአንዳንድ ሴቶች ጋር በመታየቱ ይታማ የነበረው:: አሌክሳንድራ ግን ውስጥ ውስጡን በቅናት ብትደብንም ልታነሳበት አልደፈረችም:: ዛሬም እንደዚያው ነበረች:: ቀስ ብላ እጇን በእጁ ላይ አኖረችና እየዳሰሰችው "እባክህ ሄነሪ..." ብላ መናገር ጀመረች::

እርሱ ግን እጇን መንጭቆ "አዋርደሺኛል! አዋርደሺኛል!" ሲል አሁንም ጮኸባት::

“አዝናለሁ ሄነሪ፤ እራሴን በኃይል ስላመመኝ ነው” አለችው። ከዚያ በኋላ አንድም ቃል ሳይለዋወጡ በፎሽ አቨንዩ አጠገብ ወደሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው ደረሱ... ሄነሪም ጋቢናውን ከፍቶ ከወጣ በኋላ ዞር ብሎም ሳይመለከት ወደ ቤት ገባ። ቀጥታ ወደ መኝታው ክፍል ሄዶ በሩን ከውስጥ ቆልፎ ተኛ። አድራጎቱ ግልፅ ነው። ለአሌክሳንድራ ማስጠንቀቂያ ለመስጠት ብቻ ሳይሆን ቅጣትም ጭምር ነበረ። አብራው እንደትተኛ ስላልፈቀደላትም አሌክሳንድራ ማዘኗ አልቀረም። ሆኖም ከዚያን በላይ ምንም ይቅርታ ልትጠይቀው አልፈለገችም።





## ምዕራፍ ሃያ

ጠዋት ላይ ሄነሪ ወደ ቢሮው እንደሄደ አሌክሳንድራ የብረስተልን ሆቴል ስልክ ቁጥር እናቷ ከሰጠቻት ማስታወሻ ላይ ተመለከተችና ደወለች። ስልኩን ላነሳችውም የሆቴሉ ኦፕሬተር ጆን ቻፕማን የተባለውን ሰው እንድታገናኛት ጠይቃ በጉጉት ጠበቀች። እራሷንም በምታስተዋውቀበት ወቅት ፍርሃት ገብቷት ነበረ። አድራጎቷን በሄነሪ ላይ የከህደት ተግባር እንደፈፀመች አድርጋ ቆጠረችው። ምናልባትም በዚያን ጊዜ ምን በማድረግ ላይ እንዳለች ቢያውቅ ወይንም በትናንትናው ዕለት እናቷ የነገረቻትን ታሪክ ቢረዳ ቀጥታ የፍቺ ጥያቄ እንደሚያቀርብ ተሰማት።

“እናትሽን አነጋግረሻቸው ነበረ?” ሲል ቻፕማን ረጋ ባለ የደስ ደስ ባለው ድምፅ ጠየቃት።

“አዎን ... ትናንትና... ሁሉንም ነገር ረስቼው ነበረ” አለች አሌክሳንድራ በስልኩ ውስጥ። በእርግጥም ሌላው ቀርቶ የኮምት ደ.ቦርን የጉዲፈቻ ልጅ መሆኗን እንኳን ከጊዜ በኋላ ዘንግታው ነበረ። ቀስ በቀስ ነው ጉርሐምን... ባለ ጥቁር ፀጉሯን ሂሊን... ያቺን ስካራምና ተደባዳቢ የነበረች አክስቷን ለማስታወስ የበቃችው። በዚህም ደግሞ ጆን ቻፕማን ሊታዘባት አይገባም። ሰላሳ ያህል ዓመታት አልፈው ነበረ።

“ከረጅም ጊዜ በኋላ የረሳሽውን ነገር ማስታወስ ጥሩ እንዳልሆነ ይሰማኛል። ግን አደራ ስለተጣለብኝ ሌላ አማራጭ በማጣቴ ነው” ሲል በቅድሚያ በትህትና አነጋገራት። ቀጥሎም “እና ከተመቸሽ ብንገናኝ በተጨማሪም ወደዚህ እንድመጣ የላከኝ ሰው የሰጠኝ ፋይል እንድታይው እፈልጋለሁ። ስለ እህቶችሽም የምትነግሪኝ ተጨማሪ መረጃዎች ሊኖሩ ይችላሉ። እንደዚሁም በቅድሚያ ልታውቂያቸው የሚገቡ አንዳንድ ነገሮች አሉ” አላት።

"በጣም ጥሩ! እሆቴልህ ድረስ ልመጣ እችላለሁ" አለችና ሰዓቷን አየት አደረገች:: መቼ ልትደርስ እንደምትችልም በአእምሮዋ አሰላች:: ገና ገላዋን መታጠብ አለባት፣ ልብሷን እስከምትቀይር እስከምታጋጊጥ ጊዜ መውሰዱ አይቀርም:: ማታም ላይ እንግዶች ስለሚመጡ አንዳንድ ዝግጅቶች እንዲጠናቀቁ ለሰራተኞች መመሪያ መስጠት ነበረባት "አምስ ሰዓት ላይ ብንገናኝ ምን ይመስልሃል?" ስትል ጠየቀችው::

"ለእኔ ይስማማኛል" አላት:: ምናልባትም ዕድል ከቀናው ከሰዓት በኋላ ላይ ወይንም በምሽት ወደ ኒውዮርክ የሚበረውን አውሮፕላን ለመያዝ ይችላል:: ብዙም ሥራ ተወዝፎ እንደሚጠብቀው ያውቃል:: "ከሆቴሉ እንግዳ መቀበያ ክፍል እጠብቅሻለሁ:: ስለ እኔም ምልክት ልንገርሽ ቁመቴ ስድስት ጫማ ነው፣ ፀጉሬ ወርቃማና ከጉን በኩል ተከፍሎ የተበጠረ ሲሆን፣ ኸርንጉርጉር ጃኬት ከሰማያዊ ሸሚዝ ጋር እለብሳለሁ:: ሱሪዬም ግራጫማ ይሆናል" አላት:: አለባበሱ ለአሌክሳንድራ ዓይነ ህሊና ታያትና ፈገግ አለች:: ከኒውዮርክ ፓሪስ ድረስ እንደ ተላከ የወንጀል ምርመራ ባለሙያ ሳይሆን እንደ ግዴለሽ የኮሌጅ ተማሪ ነበረ::

ስለ ራሷም ምልክት ልትነግረው ስለሚገባ፤ "የእኔም ፀጉር እንዳንተ ወርቃማ ነው:: ቁመቴም አንድ ሜትር ከስልሳ..." አለችና በመሐሉ ሳቅ ብላ "ይቅርታ! በእንግሊዘኛ ምን ነበረ የሚባለው? አዎ! አምስት ጫማ ተኩል ይመስለኛል... ከግራጫ ጉርድ ቀሚስ ጋር ሰማያዊ ሸሚዝ እለብሳለሁ" አለችው:: ያንን አለባበሷን ባሏ ሄነሪ በጣም ነበር የሚወደው።

ከብሪስተልም ሆቴል ስትደርስ ሽክ ያለች ሴት ወይዘሮ ሆና ነበር:: ከጌጣጌጦቿ ከቡልጋሪ ፍራክ የተሰሩትን የወርቅ የጆሮ ጉትቻዎችን መርጣለች:: ከሄርሜስ የተሰራም ሐምራዊ የአንገት ስካርፍ አድርጋለች:: እግሮቿ ከእብነ በረድ ወደ ተሰራው የእንግዳ ማረፊያ ክፍል ገና ከመግባታቸው ቻፕማንን ያለችግር ለየችው:: ከበስተጥግ በኩል ካለ ሶፋ ላይ ተቀምጦ መፅሄት በማገላበጥ ላይ ነበር:: እርሱም ወዲያውኑ ከመቀመጫው ተነስቶ ወደርሷ መጣና ተዋወቃት:: ያሳያትም የፊት ፈገግታ ልብ ክፍል የሚያደርግ ነበረ:: የጥርሶቹ ማማር፣ የዓይኖቹ ማራኪነት ለሌላ ነገር ያልተዘጋጀችውን አሌክሳንድራን ወከክ አደረጋት:: እርሷም በአፀፋው ተመሳሳይ ፈገግታ አሳየችውና እጅ ለእጅ ተጨባበጡ:: ከዚያም ከበስተጥግ በኩል ወዳለው





መቀመጫ ወሰዳት:: በአንዱ እጁ የእጅ ቦርሳ መያዙን አየች:: በዚያም ቦርሳ ውስጥ የእርሷንና የእህቶቿን ምስጢር የያዘው ፋይል እንደሚገኝ ታወቃት:: ጉን ለጉን እንደተቀመጡም አሌክሳንድራ ጥቂት በመዘግየቷ ይቅርታ ጠየቀችው:: "ምንም አይደለም! ይልቅስ የሚጠጣ ነገር ልዘዝልሽ" አላት። "አመሰግናለሁ! ግን አሁን ምንም ነገር አላለኝም" አለችና ትኩር ብላ እያየችው፤ "ሌሎቹንስ እንደ እኔ የምታገኛቸው ይመስልሃል?" ስትል በጉጉት ጠየቀችው::

"ይገኛሉ ስል ተስፋ አለኝ:: እስከ አሁን ስለ ሂላሪ የምናውቀው ከሃያ ዓመታት በፊት አርዘር ፓተርሰንን ማነጋገሯን ነው:: በዚያን ወቅት አንቺንና ትንሿን እህታችሁን የት እንዳደረሷችሁ ልትጠይቃቸው ወደ ኒውዮርክ መጥታ ነበረ:: ስለ እናንተም አድራሻ ምንም የሚያውቁት ነገር እንደሌለ ሲነግሯት በንዴት አብዳ ረግማቸው ትሄዳለች:: ከዚያ በኋላ እንግዲህ በግሏ ልታገኛችሁ ሞክራ ሳይሳካላት ቀርቷል ማለት ነው:: ለወላጆቻችሁም ሞት ሆነ ስለ ጠቅላላ ቤተሰባችሁ መፍረስ ተጠያቂ ያደረገችው ፓተርሰንን እንደነበረ ራሳቸው አጫውተውኛል:: አምርራ ብትጠላቸውም አያስደንቅም:: ያሳለፈችው ሕይወት የሥቃይና የመከራ ነበረና:: ስለ ትንሿ ሚጋን ግን..."

"ማን አልከኝ! ሚጋን? ሚጋን? ..."

"ስሟ ተረስቶሽ ነበር ማለት ነው?"

አሌክሳንድራ መሐረቧን አውጥታ እንባ የቋጠሩ ዓይኖቿን ጠራረገች:: 'ሚጋን... ትንሿ ሚጋን... አልጋ ላይ ተኝታ የምታጫውታት ... የምትኮረኩራት ትንሿ ሚጋን... ባለወርቃማ ፀጉር ... እራሷ ሚጋን' በዓይኗ ላይ ውልብ አለችባት::

"እሺ ስለ ትንሿ ሚጋን ምን ልትነግረኝ ነበረ?» አለችው ቆይታ ቆይታ::

"አይ ስለ እርሷ እንኳን ምንም ያገኘነው ፍንጭ የለም:: ሆኖም ሂላሪ ግን እንዳንቺ ዕድለኛ አልነበረችም" ብሎ የደረሰባትን ሁሉ አጫወ ታት:: አክስቷና የአክስቷ ባል የፈፀሙባትን በደል፣ በመጠለያ ቤት ውስጥ ያየችው መከራ፣ በጠባይ ማረሚያ ቤት ውስጥ ስለአሳለፈቻቸው ዓመታት አጫወታት:: አሌክሳንድራ በዚህ ሁሉ መሐል የእህቷ ስቃይ እየታያት ያለ ሐፍረት ተንሰቅስቃ አለቀሰች::

"ታዲያ ይኸውልሽ ይህን ሁሉ ፈተና ካሳለፈች በኋላ የነበራት ምኞት እናንተን እህቶቿን ለማግኘት ነበረ:: ወደ ኒውዮርክ መጥታ ሚስተር ፓተርሰንን ካነጋገረች በኋላ ግን የት እንደደረሰች አይታወቅም:: ያም ሆኖ በሀገር አቀፍ ደረጃ እርሷን ለማግኘት የተጠናከረ ክትትል እንዲያደርጉ ለሥራ ባልደረቦቼ መመሪያ ሰጥቻለሁ:: ስለዚህ በቅርቡ ከአንድ ውጤት ላይ እንደምንደርሷ አልጠራጠርም:: አንድ ጊዜ አግኝተናታል ስንልም ተስፋ አድርገን ነበረ:: ግን የስሙ ሞክሼ ነገር ሆነና ተሳቀን ቀረን:: ዳግመኛ ግን ያን የመሰለ ስህተት አይፈጠርም አላት:: በስሙ ሞክሼ ያላት የዚያን የዜና አገልግሎት ድርጅት ሥራ አስኪያጅ ነበር::

"ውይ ሂላሪ... ሂሊ... ሂሊ .. ምን ዓይነት መራራ ሕይወት ነው ያሳለፈችው?" አለችና እንባዋን አደራርቃ ቻፕማን የዘረጋላትን ፋይል ተቀበለች::: ከዚያም ማንበብ ጀመረች:: ግን በምታነበው ስሜቷ ስለተነካ መሐረቧን እንዴም ከእጇ አልተለየም ነበረ::

በፓተርሰን ከተፃፈው የወላጆቿ ታሪክ በመካከላቸው ስለነበረው ፅኑ ፍቅር ልትረዳ ችላለች:: ትረካው አሜሪካዊው አባቷ ሳም ምከር ፈረንሳዊቷን እናቷን ሶላንጅን፣ በፓሪሱ ዴ.አርኮል ጎዳና ላይ ካየበት ጊዜ ይጀምራል:: ደረጃ በደረጃም ይቀጥልና ምከር ወደ አሜሪካ ከተመለሰ በኋላ ሶላንጅን ከፓሪስ እንድትመጣ አድርጎ እንዳገባት ያወራል:: ከዚያም ምከር ዝነኛ ተዋናይ እየሆነ መሄዱንና ሶላንጅም ሶስት ልጆች እንደ ወለደችለት ይገልፃል:: በመጨረሻም ላይ ግልፅ ባልሆነ ምክንያት እንዴት እንደገደላትና የራሱንም ህይወት እንዳጠፋ ያትታል:: ያለ አሳዳጊ ስለቀሩትም ህፃናት በመጠኑ ይዳስሳል:: እንደ ምንም ብላ ራሷን በመቆጣጠር "እህቶቼን ለማግኘት በበኩሉ የምረዳህ ነገር ካለ እባክህ ንገረኝ?" ስትል ቻፕማንን ጠየቀችው::

"ለጊዜው ምንም አይኖርም:: ሚስተር ፓተርሰን ሁሉንም ወጪ ስለሚሸፍኑ የገንዘብ እጥረት አይገጥመኝም:: ይልቁኑ እህቶችሽን እንዳገኘኋቸው ወዲያውኑ በስልክ አስታውቅሻለሁ:: ከዚያም ወደ አሜሪካ ትመጪና ሚስተር ፓተርሰን ባዘጋጁላችሁ በኮኔክቲክቱ ቤታቸው ትገናኛላችሁ" አላት::

"ይገርማል እኮ! ለመሆኑ እኚህ ሚስተር ፓተርሰን እንዴት ያሉ ሰው ናቸው? ፈፅሞ እረስቻቸዋለሁ" አለች:: ለነገሩማ የአባቷንም





መልክ ቢሆን ያስታወሰችው በፋይሉ ውስጥ የነበረውን ፎቶግራፉን ካየች በኋላ ነበረ:: ሲበዛ መልከ መልካም በመሆኑ ዝነኛ ተዋናይ ቢወጣው አይበዛበትም ስትልም በሆዷ አሰባለች:: የእናቷም ሁለት ፎቶግራፎች ነበሩ:: አንደኛው በጣም ወጣት ሆና የተነሳችው ነው:: ወርቃማው ፀጉሯ ከትከሻዋ ላይ ተዘናፍሏል:: በተለይም አረንጓዴ ዓይኖቿና የፈገግታዋ ሁኔታ ከትንሿ ከአሌክሳንድራ ልጅ ጋር ቁርጥ አንድ ነው:: ሌላው ፎቶግራፍ ከሶስት ትናንሽ ሴት ልጆች ጋር የተነሳችው ነበረ:: አሌክሳንድራና ሂላሪ ከእናታቸው ግራና ቀኝ ነጫጭ የሐር ቀሚስ ለብሰው ቆመዋል:: ከመሐል የተቀመጠችው እናታቸው አራሷን ሚጋንን ታቅፋለች:: አሌክሳንድራ እንዳቀረቀረች ፎቶ ግራፉን ስታይ ቆየች:: ወደ ደረቷም አስጠግታ ካቀፈችው በኋላ ተራ በተራ የእናቷንና የእህቶቿን ምስል በመደጋገም ሳመች:: እንባዋም እየወረደ ነበረ:: ቻፕማን አንጀቱ እስቲላወስ አዘነላት:: የተለያዩትን እህትማማቾች ለማገናኘት ይበልጥ ስሜቱ ተቀሰቀሰ::

ትኩረቷንም ለማስቀየር ሲል አንስታበት ለነበረው ጥያቄ እንዲህ ሲል መለሰላት:: "ሚስተር ፓተርሰን በአሁኑ ጊዜ በጣም ያረጁና በሕመም የሚሰቃዩ ሰው ናቸው:: የወላጆቻችሁም የቅርብ ጓደኛ በመሆናቸው ከመሞታቸው በፊት እናንተን ለማገናኘት ይፈልጋሉ:: በሕይወት የመቆየት ዕድላቸው የመነመነ ነው::"

"ሌሎቹን ሳታገኛቸው ቢሞቱስ?" አለችው::

"ያለ የሌለ ሀብታቸውን የተናዘዙት ለሶስታችሁ ስለሆነ ቢሞቱም ፍላጋው ይቀጥላል ማለት ነው:: ጉጉታቸው ግን በሕይወት እንዳሉ ስትገናኙ ለማየት ነው::"

"እስከዚህ የሚያስቡልን ከሆነና የወላጆቻችን የቅርብ ወዳጅ ከሆኑ ለምን ዱሮውኑ እንድንለያይ አደረጉ? ለምን ራሳቸው እያሳደጉንም ነበረ?" ያነሳችው ጥያቄ ልክ ነበረ:: እህትማማቾቹን ከሰላሳ ዓመታት በላይ እንዲለያዩ አድርጎ አሁን መሞቻቸው ሲቃረብ ለማገናኘት መጣሩ ከህሊና ወቀሳ የሚያድን አይሆንም::

"ምክንያቱን እርግጠኛ ሆኜ ለመናገር አልችልም:: እንደ ጠረጠርኩት ግን ሚስታቸው እናንተን ለማሳደግ ፈቃደኛ ባለመሆኗ ሳይሆን አይቀርም:: እና በዚያን ጊዜ የፈፀሙት ስህተት አሁን ለፀፀት ዳረጋቸው" አለና ሚስተር ፓተርሰን እንዲጠይቅለት አደራ ያለው

አንድ ነገር ታውሶት "ይቅርታ አርጊልኝና አሌክሳንድራ ለመሆኑ በኑሮሽ ደስተኛ ነሽ? የላኩኝ ሰው ለማወቅ ስለሚፈልጉ ነው ይህን ጥያቄ ደፍሬ ያነሳሁብሽ" አላት።

"በጣም ደስተኛ ነኝ፤ አንድም ቀን ከፍቶኝ አያውቅም። እንደ ኮምት ደ.ቦርን የመሰለ አባት ለዚያውም የጉዲፈቻ አባት የሚገኝ አይመስለኝም። ያደግኩት በከፍተኛ እንክብካቤ ነው። እናቴንም ደግሞ በትናንትናው ዕለት ራስህ ያነጋገርካት ስለሆነ፤ ስለ ጥሩ ሰውነቷ ለመገመት የቻልክ ይመስለኛል። ይልቅስ ብትፈቅድልኝ አንድ ሌላ ጥያቄ ባቀርብልህ?" አለችው። ቻፕማን ቀጥይ ሲል በራሱ ምልክት አሳያት።

"አባቴ እናቴን ለመግደል የበቃበትን ምክንያት በግልፅ የሚያውቅ ሰው ይኖር ይሆን?" አለች ትኩር ብላ እያየችው።

"ያለ አይመስለኝም" አላት ቻፕማን ራሱን ጭምር በማወዛወዝ። "በዚያን ምሽት በመካከላቸው ጭቅጭቅ ተፈጥሮ እንደነበረና አባትሽም በጣም ጠጥቶ ስለነበረ ህሊናውን እንደ ሳተና ጨክኖም ሊገድላት እንደበቃ ነው የተወራው። የሚገርመው ግን አባትሽ ከመጠን በላይ ያፈቅራት እንደነበረ ሚስተር ፓተርሰን አጫውቶኛል። ምናልባትም ከቅናት የተነሳ ሊሆን ይችላል እንደዚያ ያደረገው"

አሌክሳንድራ ራሷን ዘንበል አድርጋ ለጥቂት ጊዜ ስታስብ ቆየች። 'ካፈቀራት በቀላሉ ሊቀናባት ይችላል ... እርሷስ አታፈቅረውም ነበር ማለት ነው?...' ስትልም አሰበችና ቻፕማንን ልትጠይቀው ከአፏ አድርሳ መለሰችው። ቻፕማን ስለ ወላጆቿ የሚያውቀው ነገር በእርግጥ አልነበረም።

"ሚጋንና ሂላሪን በቶሎ ታገኛቸዋለህ የሚል ተስፋ አለኝ" አለች። ከአሁኑ ለእህቶቿ ማሰብ ጀምራ፤ "ይገርምሃል ትልቋ ልጄ ማሪን ልክ ፎቶ ግራፉ ላይ ያለችውን ሂላሪን ነው የምትመስለው። ማሪን ባየኋት ቁጥር ሆድ ሆዴን የሚበላኝ ነገር ነበር። ታዲያ ምን እንደሆነ አላውቀውም ነበረ። ዛሬ ግን ግልፅ ሆነልኝ። ለካስ ሂሊን በመምሰሏ ኖሯል" አለች። ለመግረሙስ የርሷም ወደ እናቷ ትውልድ ሀገር ተመልሳ በፓሪስ ውስጥ ለመኖር መብቃቷም የሚገርም ነው።

ከዚያም ቻፕማን "ለመሆኑ ስለዚህ ጉዳይ ለባልሽ አጫውተሽዋል?" ሲል ከባድ ጥያቄ አቀረበላት።





ራሷን በርጋታ እያወዛወዘች "ሄነሪ በጣም ሊበሳጭ እንዲያውም ሊያብድ ስለሚችል አልነገርኩትም። ጥፋቱ ስንጋባ ስለ እኔ ማወቅ የሚገባውን ሁሉ ቤተሰቦቼ ሳይነግሩት ከመቅረታቸው ላይ ነው። ምናልባትም ማንነቴን አውቆት ቢሆን ኖሮ ላያገባኝ ይችል ነበረ። ስለዚህ እህቶቼ እስከተገኙ ድረስ አልነግረውም" አለች። ሄነሪ ዜናውን ሲሰማ የሚደነግጠው ድንጋጤ በዓይነ ህሊናዋ ታያትና ሰውነቷ ዝግንን አለ።

"እህቶችሽ ሲገኙ?" ሲል ቻፕማን ጠየቃት።

"ያን ጊዜ መንገር ይኖርብኛል" አለችና በመጠኑም ፈገግ አለች። "አሜሪካ ድረስ ያለ አጥጋቢ ምክንያት ልሄድ አልችልም፤ አይመስልህም ሚስተር ቻፕማን?"

"መቼም አንቺ አውቀሽ የደበቅሺው፣ ያታለልሺው ነገር የለም" አለ ጭንቀቷን በመረዳት ሊያበረታታት አስቦ።

"እኔ ባላደርገውም ቤተሰቦቼ ደብቀውታል። ስለዚህም አታለውታል ማለት ነው። የእርሱ እምነት የኮምት ደ.ቦርን ልጅ እንደሆንኩ ነው። ሄነሪም ትውልዱን እስከ ዘጠኝ ቤት ድረስ በመቁጠር በነገስታት ዘርነቱ ይኮራበታል። እና የእኔ እውነተኛ አባት የሚስቱን ሕይወት ያጠፋ ነፍሰ ገዳይ፣ እናቴም በፓሪስ አውራ ጎዳና ላይ ስትዘዋወር የተገኘች ሴት መሆኗን ሲሰማ እንደሚያብድ አልጠራጠርም" አለች። ደግነቱ ከሄነሪ ወንድ ልጅ አለመውለዷ! ወልዳ ቢሆን ኖሮ የሄነሪን ክብርና ማዕረግ ወራሽ የሚሆነው ወንድ ልጅ አያቱ ኮምት ደ.ቦርን ሳይሆን አሜሪካዊ ተዋናይ ነበር ማለት ነው። ሄነሪ ደግሞ ለእንደዚያ ዓይነቱ ልጅ አንድም ነገር በውርስ እንደማይተውለት ግልፅ ነበረ። ቻፕማን የአሌክሳንድራን ጭንቀት በይበልጥ ተረዳላት። ባሏም ቀላል ሰው አለመሆኑን አወቀ።

"ለጊዜው ቢናደድም ውሎ ሲያድር ነገሮችን ማመዛዘኑ አይቀርም። ከተጋባችሁ ብዙ ዓመታት ስላለፉም ትዳሩ እንዲፈርስ የሚፈልግ አይመስለኝም። በዚያ ላይ ደግሞ ያፈቅርሻል የሚል ግምት አለኝ" አላት።

አሌክሳንድራ መልስም ሳትሰጠው መጠነኛ ፈገግታ ብቻ አሳየችው። ሄነሪን እርሷ ታፍቅረው እንጂ ስለርሱ ፍቅር እርግጠኛ ሆና ለመናገር አትችልም። አንድን ውድና የተዋበ ሥዕል ተንከባክበው

እንደሚይዙት ዓይነት ነበረ ሄነሪ ለርሷ ያለው አመለካከት:: ያ ሥዕል ደግሞ ወጡ ሥራ ሳይሆን የተጭበረበረ መሆኑ ሲደረስበት የተራክሰ ይሆናል:: በመሆኑም ሄነሪም የአሌክሳንድራን ወላጆች ምንነት ሲያውቅ ልጆቿን አስቀርቶ ሊያባርራት ይችላል::

ቻፕማን በበኩሉ ምንም ሳይናገር ለረጅም ጊዜ ዝም ብሎ ሲያያት ቆየ:: በጣም ነው ያዘነላት:: ውብና ጨዋ ሴት ወይዘሮ ናት::

ከአረንጓዴማና ትላልቅ ዓይኖቿም የሚወረወረው ብርሃን የልቧን የዋህነት የሚያንፀባርቅ ነበረ:: ታዲያ በሰላም ትኖር የነበረችውን ይህችን የመሰለችውን ሴት ትዳር መበጥበጥ ተገቢ ነውን? የሚስተር ፖተርሰንስ ምኞት ይደገፋልን? በየትኛው ጥፋቷ ነው ከሰላሳ ዓመታት በኋላ አሌክሳንድራ ይህ ሁሉ ሥቃይ የደረሰባት?

"እባክሽን ፈቃድሽ ቢሆንና ምሳ አብረን ብንበላ አሌክሳንድራ በማዕረግ ስምሽም ስላልጠራሁሽ ይቅርታ አርጊልኝ?" አለና ደስ የሚል ፈገግታውን አሳያት::

እርሷም ሳቅ አለችና "ልጥራሽም ብትል በጣም ረጅም ስለሆነ አትችልም" አለችው::

"ምን ያህል ረጅም እንደሆነ ባውቀውስ?"

"ጥሩ! ባሮነስ ሄነሪ ኤድዋርድ አንትዋን ካቬየር ሳንብሩ ሚ ደ.ሞሪኚ ይባላል:: ቆንጆ ስም አይደለም?" አለችው::

"ለመሆኑ ይሄ ሁሉ ስም በመታወቂያ ደብተርሽ ላይ ተፅፏል?" አለና አሳቃት:: ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ለወላጆቿና ለእህቶቿ እንባዋን ያለማቋረጥ ስታፈስ ያረፈደችው አሌክሳንድራ እንደዚያ ስትስቅ ማየቱ ደስ ይል ነበረ::

ሳቁም ታገስ ሲልላት ወደ ቻፕማን አየት አደረገችና "መቼም ሚስተር ቻፕማን! ብልህ ሰው መሆንህን አውቃለሁ አንተ በእኔ እግር ብትሆንና ይህን የመሰለ ጉዳይ ቢያጋጥምህ ትደነግጥ ነበረ?" ስትል ጠየቀችው::

"መደንገጥ አልደነግጥም:: በዚህ አጋጣሚ ግን አንድ ሳልነግርሽ ሳልፈው የማልፈልገው ነገር አለ:: በአንድ ሰው ጥፋት የተነሳ ቤተሰባችሁ በመፈራረሱ የተሰማኝ ሐዘን ጥልቅ ነው:: ከሁሉም ደግሞ በዛሬው





ዕለት ያለፈ ትዝታ ቀስቅሼ በማስለቀሴ ከሐዘንም ሐዘን ተሰምቶኛል:: ለላኩኝ ለሚስተር ፓተርሰን ቃል ባልገባላቸው ኖሮም ምናልባት ሐሳቤን ለመቀየር ሳልገደድ አልቀርም ነበረ:: ሆኖም የጣሉብኝ አደራ ቀላል ባለመሆኑ ከከባድ ሐዘን ላይ ጣልኩሽ:: ግን አንድ መፅናኛ ያገኘሽ ይመስለኛል:: እንደ ተረዳሁት ከሆነ እህቶችሽን ለማየት ከአሁኑ ጉጉት አድሮብሻል" አላት::

ያለማመንታት "አዎን" ስትል መልሳለት "ሂላሪ ትዝ ትለኛ ለች:: በጣምም ትወደኝ እንደነበረ አስታውሳለሁ::ለእኔም ለሚጋንም እንደ እናታችን ነበረች:: ከእኛ በመለየቷ ምንኛ የመረረ ኑሮ እንዳሳለፈች ሲታወሰኝ አዝንላታለሁ:: አሁን ደግሞ በሕይወት ስለ መኖራችን ስትሰማ የምትደነግጠው ድንጋጤ ይታየኛል::"

"ያው እንቺ የደነገጥሽውን ያህል ብትደነግጥ ነው"

"አይመስለኝም፤ ሂሊ ሲበዛ ሩህሩህ ነበረች"

"አንቺም ርህሩህ ነሽ አሌክሳንድራ:: ስለዚህ ቅድም አብረን ምሳ እንብላ ስል ያቀረብኩልሽን ጥያቄ ውድቅ አታደርጊብኝም" አለና ፈገግ አለ:: ካያት ደቂቃ ጀምሮ ይበልጥ እየወደዳት ነበረ የሄደው:: እርግጥ አሌክሳንድራ ቆንጆና ማራኪ ሴት ናት:: ቻፕማን ግን ይህ ነው ብሎ ለመናገር ይሳነው እንጂ የወደዳት ከዚህ በተለየ ምክንያት ነበረ::

አሌክሳንድራ የምሳውን ግብዣ ከመቀበሏ በፊት አንዳንድ ነገሮችን በአእምሮዋ ማውጣትና ማውረድ ነበረባት:: ከዚያም ግብዣው የሚያስከትለው ጉዳት እንደማይኖር አመዛዝና "በጣም ደስ ይለኛል" ስትል መለሰችለት::

"የምትመርጪው ሆቴል ቢኖር? እኔ ለፓሪስ እንግዳ ነኝ" አላት::

"ረዘም ያለ ዕድሜ ያላቸው ሆቴሎች ናቸው ጥሩ ምግብ የሚያዘጋጁት" ብላ ከመቀመጫዋ ተነሳች:: ቻፕማንም ፋይሉን ከእጅ ቦርሳው ውስጥ ከቶ ተከተላት:: እንደ እውነቱ ከሆነ በዚያን ወቅት ከእናቷ ጋርና ከእህቶቿ ጋር የተነሳችውን ፎቶግራፍ እንዲሰጣት ልትጠይቀው ነበረ:: ግን ጥቂት አሰብ አደረገችና ሐሳቧን ቀየረች:: ፎቶግራፉም ሌሎቹን እህቶቿን እንዲያገኝ የሚረዳው መሆኑ ገባት:: ያን

ጊዜም ሌላ አንድ ተጨማሪ ሐሳብ በአእምሮዋ ተመላለሰ:: እንደ ሌሎቹ ህፃናት ሁሉ እርሷም የልጅነት ጊዜ ፎቶግራፏን አይታ ለማወቋ የጉዲፈቻ ልጅ በመሆኗ እንደሆነ ተረድታ "የህፃንነት ጊዜዬን ፎቶግራፍ ባለማየቴ መቼ ጥርጣሬ አድሮብኝ? ለካስ ጉዱ ሌላ ኖሯል!" አለች::

"እንደ ወለዱሽ ያህል ተንከባክበው ስላሳደጉሽ ምን ብለሽ ትጠረጥሪያለሽ:: በነገራችን ላይ የት ነው ታዲያ ምሳ የምንበላው?"

"የእኔ ምርጫ ሪትዝ ሆቴል ነው:: የአዛውንቶች መሰብሰቢያ እዚያ ነው" አለችና ሳቅ ብላ እጁን ይዛው ጐን ለጐን መሄድ ጀመሩ::

"ለምን አዛውንቶችን መረጥሽ?" አለና እርሱም ፈገግ አለ::

"በነርሱ መካከል ስታይ በጣም ቆንጆና ወጣት ስለምመስል ነው" አለች አሁንም እየሳቀች::

"አሁንስ ቢሆን ወጣትና ቆንጆ ነሺና! መልክሽን በመስታወት ውስጥ አይተሽው አታውቂም ማለት ነው?"

"ማየቴማ መች ይቀራል:: የማየው ምስል ግን ወጣትና ቆንጆ ስለማይመስለኝ ነው እንጂ::"

እንዳው ምን ብዬ ላዋራው ለማለት ያህል ካልሆነ በስተቀር አሌክሳንድራ ስለ ውበቷ ታውቀው ነበረ:: ዕድሜዋም ሰላሳ አምስት ይድረስ እንጂ ገና የሃያ ሰባት ዓመት ሴት ነበር የምትመስለው::

"የገረመኝ ደግሞ የአንተም ፀጉር እንደኔ ወርቃማ መሆኑ" አለችና ፈገግ አለችለት:: 'ውብ ብቻ ሳትሆን የደስ ደስ ያላት ሴት... ባሏ ባይጨቁናትና እንደ ልቧ የምትኖር፣ የምስሰብስ የምታጌጥ ቢሆን ኖሮ ይህን ጊዜ ምን ትመስል ይሆን?' ሲል ቻፕማን አሰበ::

በሪትዝ ሆቴል በቀረበላቸው ምሳ ላይ ስለተለያዩ ነገሮች አንስተው ሲጫወቱ ቆዩ:: እርሱ በተለይ ስለ ቦስቶንና ኒውዮርክ ሲያወጋት እርሷ ደግሞ የዕረፍት ጊዜዋን ስለምታሳልፍባቸው ኬፕ ኮድና ሴን ጃን ካፕ ፌራ አጫወተችው:: ልክ ለብዙ ዓመታት እንደ ተዋወቁ ጓደኛ ስለ ህይወት ታሪኩም ዘረዘረላት:: በወንጀል ምርመራ ሙያ ላይ ለመሰማራት የፈለገበትን ምክንያትና ካጋጠሙትም ልምዶች የማይረሱትን አንዳንዶቹን በማንሳት ተረከላት:: እርሷ እንደ ታላቅ





ወንድም እርሱ ደግሞ እንደ ታናሽ እህቱ አያት:: ከሆቴሉም አድርሳው ሲለያዩ ሁለቱም ቅር ቅር እንዳላቸው ነበረ::

"ስለ እህቶቼ ከሆነ ፍንጭ ላይ እንደ ደረስክ እንድትደውልልኝ" አለችው ከመኪናዋ ውስጥ ከመግባቷ በፊት::

"አታስቢ አደውልልሻለሁ፤ በተጨማሪም ምንም ዓይነት ጭንቀት አይግባሽ! ስለ ባልሽም ጉዳይ ቢሆን የምንወያይበት ይሆናል" አለና ከአገጯ ቀና አድርጐ ጉንጯን ሳማት::

አሌክሳንድራ በዚያ በመኪና በተጨናነቀ የፓሪስ አውራ ጎዳና ላይ በምትነዳበት ጊዜ ሁሉ ስለ ቻፕማን ማሰቧ አልቀረም ነበረ:: መልከ መልካም ነው:: ተጫዋች ነው:: ብልህ ነው:: ይህ ሁሉ ሆኖ ግን፤ በውይይታቸው ወቅት ሚስት እንደሌለው አውግቷታል:: የልጃገረድ ሚስቱን ፈትቶ የወንደላጤ ኑሮ ነበረ የሚኖረው:: 'ለምን ሌላ ሚስት አላገባም? መቼም የርሱን ቁመና አይታ የማትማረክ ሴት ትኖራለች ብዬ አልገምትም:: እስከ ዛሬ የምትስማማው ሴት በኒውዮርክ ከተማ ውስጥ ሳትገኝ ቀርታ ነው ወይንስ እርሱ ወንደላጤነቱን መርጦ?' ስትል ለራሷ ጥያቄ አቀረበች::

ወዲያውኑ አእምሮዋ ወደ ሌላ ነጥብ ዘለለ:: አሁን ደግሞ ወደ ፓሪስ ስለመጣበት ምክንያት ማሰላሰል ጀመረች:: ባለፈውና በዛሬው ቀን የሰማችው ታሪክ ለሰላሳ ዓመታት የነበራትን እምነት አፈራርሶታል:: እውነተኛ ማንነቷንም እንድታውቀው አድርጓታል:: ከመኖሪያ ቤቷ ደርሳ የበራፉን ደወል በምትጫንበት ጊዜ ነበረ ሰዓቷን አየት ያደረገችው:: ሳይታወቃት ከቀኑ አስር ሰዓት በመድረሱ እንደ መደንገጥ አለች:: ከአምስት ሰዓታት በላይ ውጪ ቆይታለች ማለት ነው:: ባሏ እራት ለጋበዛቸው እንግዶች በመዘጋጀት ላይ ያለው የምግብ ዓይነት በሰጠችው መመሪያ መሰረት መሰራቱን እየተዟዟረች ተመለከተች:: የመረጠቻቸውም የወይን ጠጅ ዓይነቶችና ሌሎችም መጠጦች በየጠረጴዛው ላይ በትክክል መደርደራቸውን አየች:: የአበባ ማስቀመጫዎች ቦታቸውን መያዛቸውንና ትኩስ በተቆረጡ አበቦች መሞላታቸውን አረጋገጠች::

አስራ ሁለት ሰዓት ሲሆን ሲል ለምሽቱ የምትለብሰውን ልብስና የምታጌጥባቸውን ጌጣ ጌጦች ማማረጥ ጀመረች:: ከዚያም ገላዋን

ታጥባ በመለባበስ ላይ እንዳለች ሄነሪ የመኝታ ክፍሉን በር በኃይል በርግዶ ገባ፡፡

እሌክሳንድራ እንደ መደንገጥ ብትልም "ደህና ዋልክ ፍቅሬ?" ብላ በፈገግታ ሰላምታ ሰጠችው፡፡ ግን ከመቅፅበት ያ ፈገግታ ክስም አለ፡፡ "ምነው? ምን የሆንከው ነገር አለ? ስለ ግብዣው እንደሆነ ሁሉም ነገር መዘጋጀቱን አረጋግጫለሁ" አለችው፡፡

ሄነሪ ፊቱን በንዴት እንደ ጨፈገገ "ብለሽ ብለሽ የድፍን ፓሪስ መሳቂያ ታደርጊኝ? ምን በደልኩሽና ነው እባክሽ?" ሲል ጮኸባት፡፡

"ያምላክ ያለህ! ስለምንድነው የምታወራው ሄነሪ?" ስትል ጠየቀችው፡፡

"የማወራውማ በዛሬው ቀን በሪትዝ ሆቴል ውስጥ ስለ መታየትሽ ነዋ! ምሳም እዛው ስለመብላትሽ! ከማን ጋር እንደነበር ተደርሶብሻል! በአንቺ ቤት ግን ያልታየሽ መስሎሻል!"

የአሌክሳንድራ ፊት በንዴት ተለዋወጠ፡፡ ያለወትሮዋም ኮስተርተር ብላ፤ "በድብቅ የምሰራው ነገር ቢኖር ኖሮ ወደዚያም ሆቴል ባልሄድኩኝም ነበረ፡፡ ብዙ ሕዝብ ባለበት አዳራሽ ውስጥ ምሳ በልቻለሁ፡፡ የጋበዘኝም ከኒውዮርክ የመጣ ሰው ነው፡፡ ለግብዣውም ምክንያት የእናቴን ንብረት በሚመለከት የምንወያይባቸው ነጥቦች በመኖራቸው ነው" አለችው፡፡

"በትናንትናውም ዕለት የነገርሺኝ ይህንኑ ምክንያት ነው፡፡ ግን ዳግመኛ ልታታልይኝ እንደማትችይ እወቂ! ለካስ ትናንት ማታ እንደዚያ የነሆለልሺው ለዚሁ ኖሯል? ከነገ ጀምሮ በዚህ ቤት ውስጥ አትኖሪአትም! እንደነጋ ልጆችሽን ይዘሽ ወደ ካፕ ፌራት!" ሲል አሁንም ጮኸባት፡፡ እንደ ወንጀለኛ በግዞት ሊቀጣት በመወሰኑ እንባዋን ልትቆጣጠረው አልቻለችም ነበረ፡፡

"ሄነሪ! አንተን መቼም ቢሆን ላታልልህ ሞክሬ አላውቅም እባክህን እመነኝ" አለችው ከቆመችበት ሥፍራ ሳትነቃነቅ፡፡ እንደ ወትሮው ደፍራ ልትጠጋው ልታቅፈው አልቻለችም፡፡ ባለጋራ ይመስል ማዶ ለማዶ ቆመው እርሷ በመለማመጥ እርሱ በቁጣ ይነጋገራሉ፡፡





"እስከ ዛሬ ሳምንሽ ቆይቻለሁ፡፡ ከእንግዲህ ግን ያምነኛል ብለሽ አታስቢ!"

"እውነቴን ነው ሄነሪ!"

"በቃ! በቃ! ለዚያችም ለእናትሽ ቢሆን ልክ ልኳን ነው የምነግራት! ለመባለግ ሽፋን የሆነችሽ እርሷ ናት፡፡ ዳግመኛም እግሯ ከቤቴ እንዳይደርስ አደርጋለሁ!"

"እባክህን ሄነሪ! ጨክነህ እንዴት እንዲህ ታደርጋለህ? ቢያንስ ህፃናቱን ለማየት እንኳን ልትፈቅድላት ..."

"ይህማ ድሮ ቀረ! አንቺን ከተለያዩ ወዳጆሽ ጋር ከማቃጠር መቆጠብ ነበረባት!"

"ኧረ እኔ አንድም ወዳጅ የለኝም!" ስትል ጮሃ አለቀሰች፡፡ "እናቴም ብትሆን እስከዚህ ባለጌ..."

"እህ! ባለጌ አይደለችም ልትይ ነው? ለጉዳይ እያለች የምትጠራሽ ለምን ይሆን?" አለና ዓይኑን አፍጥጦ ተጠጋት፡፡ አሌክሳንድራ ተስፋ በመቁረጥ ወደ ኋላዋ አፈግፍጋ ካገኘችው መቀመጫ ላይ ተቀመጠችና ዝም ብላ ዓይን ዓይኑን ታየው ጀመረ፡፡ ንዴቱም እየጨመረ በመሄዱ ከአጠገቧ ደርሶ ከአገጯ ቀና አደረጋትና "እኮ ለምን ጉዳይ እንደምትፈልግሽ ንገሪኝ?" ሲል አምባረቀባት፡፡ ልትነግረው የማትፈልገው የደበቀችው ነገር እንዳለ ከሁኔታዋ ተረድቷል፡፡ እርሷ ያወቀችውን ደግሞ አፍረጥርጣ ብትነግረው ከዚህ የባሰ እንደሚደርስባት ታውቀዋለች፡፡

"ስለ ጉዳዩ አሁን ልገልፅልህ አልችልም፡፡ ግን የወላጆቼን ንብረት የሚመለከት ምስጢር መሆኑን ብቻ ልነግርህ እችላለሁ" አለችው፡፡ ሰውነቷ ይንቀጠቀጥና ፊቷ ዐመድ የተነፋበት መስሎ ነበረ፡፡ ሳታስበው ሄነሪ ውልቅ ብሎ ከክፍሉ ወጣና እንደገና ዘወር ብሎ ተመለከታት፡፡

"በእኔ ላይ ሌላ ወንድ ትሄጃለሽ ብዬ አላምንም ነበረ፡፡ ግን የሆነው ሆነ፡፡ ከእንግዲህ ግን እባልጋለሁ ብትይ ባዶ እጅሽን እንደማባርርሽ እንድታውቂ! ህፃናቱን እንኳን እንዳታያቸው ነው የማደርገው፡፡ ለአሁኑ ግን ወደ ካፕ ፌራት ለመሄድ የምትወስጂውን

ዕቃና ልብስ አዘጋጂ! ጠዋት ዓይኔ እንዳያይሽ!» ብሎ በሩን እላይዋ ላይ በኃይል ዘግቶባት ሄደ:: አሌክሳንድራ ተስፋ በመቁረጥ ስታለቅስ ቆየች:: በኋላም ላይ ነበረ ወደ ግዞት ስፍራዋ ከመሄዷ በፊት ማድረግ የነበረባት አንድ ነገር ትዝ ያላት:: ስልኩን አንስታ ወደ ብሪስተል ሆቴል ደወለች:: ቻፕማንንም እንዳገኘችው የካፕ ፌራትን የስልክ ቁጥሯን ነገረችው:: ስለ እህቶቿ ሊያነጋግራት ከፈለገ የሚቀኘግኛት በአዲሱ አድራሻዋ ነበረ::

«በቅርቡ እንደምደውልልሽ ተሸፋ አለኝ» አላት::

«እኔም እንዳንተው እንደምትደውልልኝ ተስፋ አደርጋለሁ» አለችው:: እንደዚህ ብላ በማሰቧ ግን ኃፍረት ተሰምቷት ነበረ:: ቻፕማን መልከ ቀናና ደግ ሰው ቢሆንም የራሱ የሆነ ሴት የመምረጫ ሚዛን ሊኖረው ይችላል:: በዚያ ላይ ደግሞ አሌክሳንድራ ባለትዳር ናት:: እና እንኳንስ ስለእርሱ በልቧ አሰላስላ ገና ለገናም ከአሁኑ በመጠርጠሯ የደረሰባት ውርጂብኝ የታየ ነው::

«ፍንጭ እንዳገኘሁ ወዲያውኑ ነው የማስታውቅሽ::»

«በጣም አመሰግናለሁ ሚስተር ቻፕማን መልካም ጉዞ እመኝልሃለሁ»

«እኔም ስለ መልካም ምኞትሽ አመሰግንሻለሁ:: በጠዋቱ አውሮፕላን ነው የምሄደው» ብሎ ተሰናበታት::

ቻፕማን በዚያኑ ምሽት ወደ ኒውዮርክ ለመብረር አቅዶ ነበረ:: ግን አውሮፕላኑ ስላመለጠው ለማደር ተገደደ:: በተጨማሪው በውቧ በፓሪስ ከተማ ውስጥ አንድ ምሽት ማሳለፍ የሚጠላ አልነበረም:: ቻፕማን እስከ እኩለ ሌሊት በሪትዝ ሆቴል ውስጥ አሳለፈ:: ለእርሱም ቢሆን ቀን ላይ ከአሌክሳንድራ ጋር ምሳ ሲበሉ ያደረጉት ውይይት ልዩ ትዝታ አሳድሮበት ነበረ::

ሄነሪ በውሳኔው በመፅናቱ ጠዋት ላይ የአሌክሳንድራና የልጆቹ ልብስና ዕቃ በልዩ መኪና ተሳፈረ:: እርሷም ወደ ሲትሮይኑ መኪናዋ በመግባት ላይ እንዳለች ሄነሪ አስቆማትና «አንድ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ልስጥሽ እፈልጋለሁ:: ወደ ካፕ ፌራት ቪላ አንድ ወንድ ቢገባ ወዮልሽ! በየጊዜውም ስልክ ስለምደውል ከቤት እንዳላጣሽ!» አላት:: ለማምለጥ ሞክሮ እንደተያዘ እስረኛ ነበረ የቆጠራት::





ንዴት ውስጥ ውስጡን እያብገነገናት፤ «ወደ ባህሩ ዳርቻ ሄጄ ለመናፈስ እንኳን አልችልም ማለት ነው? ከባርነትም የባሰ ቀንበር ነው የጫንክብኝ!» አለችው::

«በራስሽ ጥፋት! በራስሽ ብልግና!» አለና ደህና ዋይ ሳይላትም ወደ ቤት ገባ:: ወዲያውም አሌክሳንድራንና ልጆቿን የያዘው ሲትሮይንና የቤት ሰራተኞቹንና ዕቃ የጫነው ፔጆ መንቀሳቀስ ጀመሩ:: የፓሪስንም ከተማ እስኪወጡ ድረስ አሌክሳንድራ ታሰላስል የነበረው የአባቷን የሳም ምክርና የእናቷን የሶላንጅን ፍቅር ማብቂያ ነበረ:: በድንገትም «አባባ ለምንድነው የተናደደው?» ስትል ጥያቄ ያቀረበችላት ትንሿ አክሴል ነበረች:: ቀጠልም አድርጋም «ባንቺ ነው የተናደደው አይደለም እንዴ?» አለቻት ዓይን ዓይኗን እያየች::

«በመጠኑ» ብላ አሌክሳንድራ ህፃኗን አክሴልን እቅፍ አድርጋ ወርቃማ ፀጉሯን እያሻሸች መለሰችላት:: ያን ጊዜም ለአሌክሳንድራ እህቷ ሂላሪ ትዝ አለቻት:: ዱሮ... ዱሮ... ዱሮ... ሂላሪም አሌክሳንድራን እንደዚያ ትወዳት ነበረ:: ከእህቶቿ ጋር የምትገናኝበት ቀን መቼ እንደ ሚደርስ ናፈቀች:: ቻፕማን ቢቀናውና ስልክ ከደወለላት ያለ አንዳች ማመንታት ወደ አሜሪካ ለመሄድ ቆርጣለች::

«ለእኔ የአባባ ንዴት እንደ ድሮው አልመሰለኝም:: በጣም ነው ዛሬ የተናደደው:: ያጠፋሺው ጥፋት አለ እንዴ?» አለችና አሁንም ትንሿ አክሴል ጠየቀቻት:: አሌክሳንድራ ለጊዜውም ፈገግ ከማለት በስተቀር መልስ አልሰጠቻትም:: ለጥቂት ሳምንታትም ቢሆን ከሄነሪ ጭቅጭቅ ርቆ በካፕ ፌራ ቪላ ከልጆቿ ጋር በሰላም መክረሙ እንደሚሻል ያን ጊዜ ነው የተሰማት::

«ማጥፋት ሳይሆን በየዋህነት አንድ ነገር በመስራቴ ነው» ስትል አሌክሳንድራ መለሰችላት::

«ያኔ እንደ ገዛሽው ባለ ላባ ባርኔጣ ዓይነት አሁንም ገዝተሽ ነው? አባባ ከንዴቱ የተነሳ በመስኮት እንደ ወረወረው ትዝ ይለኛል» ለአክሴም ያ ባርኔጣ ቆንጆ ስለ መስላት አትረሳውም::

«አዎን ... እንደዚያ በማድረጌ ነው»

«ቆንጆ ነበር?»

«በጣም!» አለችና በትንሿ ልጇ ጥያቄ ሳቀች:: አክሌልም አናት እናቷን እያየች ፈገግ አለች::





## ምዕራፍ ሃያ አንድ

ሂላሪ ተገኘች!!! ቻፕማን ፓሪስ ውስጥ በስነበተባቸው ቀናት የሥራ ባልደረቦቹ በሂላሪ ላይ የሚያደርጉትን ክትትል አጠናክረው ነበረ:: ፓተርሰንን ለመጨረሻ ጊዜ ካነጋገረችበት ወቅት በመነሳት ስለ ሂላሪ አንዳንድ ጥናቶች አካሄዱ:: የመጀመሪያውንም ፍንጭ ያገኙት ትምህርቷን በማታ ለመከታተል ከተመዘገበችበት ኮሌጅ ነበረ:: በዚያንም ወቅት ከምላ ችው የሕይወት ታሪኳ ላይ በአስተናባሪነት ተቀጥራ እንደምትሰራ ለመረዳት በቁ:: ከዚያም የአስተናባሪነቱን ሥራ ለቃ በከተማው ውስጥ በሚገኘው ዝነኛ የዜና አገልግሎት ድርጅት ውስጥ መቀጠሯንና ደረጃ በደረጃ ዕድገት በማግኘቷ ለዋና ሥራ አስኪያጅነት ስልጣን መድረሷን አወቁ:: ቻፕማን ቀድሞውንም ቢሆን በስልክ አነጋግሯት ነበረ:: እርሷ ግን ተፈላጊዋ ሂላሪ ምከር አለመሆኗን ያለማመንታት ነግራዋለች:: በአጭሩ ለመታወቅ አትፈልግም ማለት ነው:: ግን ለምን? ለዚህ ጥያቄ መልስ ለማግኘት ጊዜ ይፈጃል:: እራሱ ሂላሪን ፊት ለፊት ማነጋገር አሰበ:: የሚሻለውም ትንሿን ሚጋንን ካገኛት በኋላ እንደሚሆን አምኖበታል:: እስከዚያ ድረስ ግን ዝም ሊላት ወሰነ::

ሆኖም ቻፕማን ስለ ሂላሪ ባሰበ ወይንም ስለ እርሷ የተጠናቀ ረውን መረጃ ባነበበ ቁጥር እጅግ ያዝንላት ነበረ:: በዓለም ውስጥ ብቸኛ አለመሆኗን፣ የሚወዷት ሰዎች መኖራቸውን፣ ከእንግዲህም ራሷን ማግለል እንደማይኖርባት ሊነግራት ይፈልግና በሌላ በኩል ደግሞ በአሁኑ ወቅት ስላለችበት ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ባለማወቁ ሐሳቡን ይቀይራል:: ማን ያውቃል? ሂላሪ ባለትዳርና የልጆች እናት ልትሆን ትችላለች:: እርሱ እንደፈራውም ሳይሆን ደስተኛ ሴት የማትሆንበት ምክንያት የለም:: የቦስቶኗ ምስኪን ሂላሪ! የጃክሰንቪሏ ጎስቋላ ሂላሪ! ለሥራ አስኪያጅነት ማዕረግ በቃታለች:: ስለዚህ ...

ቻፕማን አግኝቶ እስከሚያነጋግራት ድረስ የሕሊና ዕረፍት አጣ:: የሦስቱ እህትማማቾች ታሪክ ለመግለፅ በሚያስቸግር ሁኔታ እንቅልፍ ነስቶታል:: ይህ ደግሞ ልምድ ላለው ቻፕማን እንግዳ ነገር ሆነበት::

መንፈሱን ጨምድዶ ያዘው:: ለምን? ሲል ራሱን ጠየቀ:: መልስ ግን አላገኘለትም:: ስለዚህ ሌላ ሰው ማማከር ነበረበት:: ለምክሩም ዕውቅ ደራሲ የነበረችውን የቀድሞ ሚስቱን ኤልዋዝን መረጠ:: ስልክ ደውሎላት ለምሳ እንዲገናኙ ለመናት:: ኤልዋዝ ለምትደርሳቸው መፃህፍት ገፀ ባህርያትን መሳል ነበረባት:: በመሆኑም የሦስቱ እህትማማቾች ነገር የርሱን አእምሮ የጨመደደውን ያህል የኢልዊዝም ገፀ ባህርያት በግል ህይወቷ ላይ የሚጫወቱት ሚና መኖር አመኖሩን ሊጠይቃትና ሊረዳ ፈለገ::

ለምሳ የተቀጣጠሩት ደራሲያን ከሚያዘወትሩት ከፎር ሲዝንስ ሆቴል ነበረ:: ጉን ለጉን ተቀምጠው በመመገብ ላይ እንዳሉ ቻፕማን "ለመሆኑ ኤልዋዝ! በየመፃህፎችሽ ውስጥ ከምትፈጥሪያቸው ገፀ ባህሪያት ጋር ፍቅር ይይዝሻል?" ሲል ያልጠበቀችውን ጥያቄ አቀረበላት:: ኤልዋዝ ረጋ ያለች ቆንጆ ሴት ነበረች:: የጥልቅ አስተሳሰቧ ውጤት የሆኑት ልቦለድ መፅሐፎቿ ለብዙ ሽልማት አብቅተዋታል::

"ከገፀ ባህርያቶችሽ ጋር ፍቅር ይይዝሻል ወይ ነው ያልከኝ? ግን ለምን እንዲህ ዓይነት ጥያቄ እቀረብክልኝ? የስነ ፅሑፍ ሰው ለመሆን እያቀድክ ነው ልበል?" አለችና ትክ ብላ ታየው ጀመረ::

ቻፕማን ራሱን አወዛወዘና፤ "አይደለም ኤልዋዝ! አንድ ለየት ያለ ምርመራ እያካሄድሁ ነው:: ታሪኩ ከተፈፀመ ሠላሳ ዓመታት አልፈውታል:: ታሪኩም የሶስት ህፃናት እህትማማቾች ታሪክ ነው:: በቁሜም በሕልሜም እነዚያ ሦስት ሕፃናት ልጆች ይታዩኛል:: አንጀቴም ይላወስላቸዋል:: እርግጥ በአሁኑ ወቅት ትልልቅ ሴቶች ሆነዋል:: ግን እንደ ተለያዩ እንዳይ ቀሩ ነው የእኔ ጥረት:: ከልቤ ነው የወደድኳቸው" አላት::

"ደህና ታሪክ የሚወጣው ይመስለኛል:: ለምን አትፅፈውምና እንዲታተም አናደርገውም?"

"የሥነ ፅሑፍ ዝንባሌ እንደሌለኝ ታውቂያለሽ:: ከዚያም በላይ ደግሞ ቢፃፍ እንኳን ታሪኩ ተዓማኒነት ሊያገኝ የሚችል አይመስለኝም:: እኔን ግራ እያጋባኝ ያለው ምን መሰለሽ ኤልዋዝ? የሕፃናቱን ታሪክ ከወረቀት ላይ እንብቤ ነው ያወቅኩት:: ግን በሕይወቴ ከጐኔ ያሉ እየመሰለኝ የአእምሮ እረፍት አጣሁኝ"

"እኔንም አንዳንዴ የምፈጥራቸው ገፀ ባህርያት እንደዚሁ ያስጨንቁኛል ሆኖም በመጨረሻ ላይ ከአንድ እልባት ትደርሳለህ" አለችው እርግጠኛ ሆና:: "አንድ መፅሐፍ ፅፌ ስጨርስ እነኛን እንደዚያ





የሚያስጨንቁኝ ገፀ ባህርያት ከአእምሮዬ ተነው ይጠፋሉ:: ዳግመኛም የሕሊና ዕረፍት አይነሱኝም:: ቁም ስቅሌን አያሳዩኝም::"

"ልክ ነሽ! እኔም ለማለት የፈለግኩት አሁን አንቺ ያልሺውን ነው" አለ ከከንፈሩ ያደረሰውን የሾርባ ማንኪያ ወደ ሳህኑ እየመለሰ:: በተለይም የቁም ስቅል የሆነችበት ሂላሪ ነበረች:: የቦስቶኑ ሥቃይዋ እየታየው ተሰቃይቶባታል:: በጃክሰንቪል የደረሰባት ግፍ መንፈሱን አቁስሎታል:: ስለ ሂላሪ ማሰቡን ሲያቆም አሌክሳንድራ ትታወሰዋለች:: ሂሊ እያለች የምታቆላምጣት ታላቅ እህቷ ዝነኛ የዜና አገልግሎት ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ የመሆኗን ዜና ቻፕማን ወዲያውኑ ነበረ ያበሰራት:: ለአሌክሳንድራ ደስታ ከእስከ አልነበረውም:: ሜጋንን እስከሚያገኛት ድረስ ግን አሌክሳንድራ በትዕግስት እንድትጠባበቅ ነግሯታል:: ሚስተር ፓተርሰንም በሽታው እየፀናበት በመሄዱ ሜጋን በአስቸኳይ መገኘት ነበረባት:: ስለዚህም ቻፕማን ከምንጊዜውም ይልቅ ረዳቶቹን በየአቅጣጫው አሰማርቶ ክትትሉን አጠናክሮ ነበረ::

"እና እኔም ሦስቱንም እህትማማቾች ካገኘኋቸው በኋላ ልረሳቸው እችል ይሆን?" ሲል ኤልዋዝን በመጠራጠር ጠየቃት::

"እምን! ትረሳቸዋለህ! ስለዚህ በርትተህ ልታገኛቸው ሞክር:: ከዚያ በኋላ እፎይ ትላለህ:: ከባድ ችግር እንደ ገጠመህ ይገባኛል"

"በጣም ከባድ እንጂ! እስከ አሁን ሁለቱን ደርሼባቸዋለሁ:: የሦስተኛዋ ሕፃን ጉዳይ ነው ደብዛው የጠፋው:: ምናልባት ዕድል ቀንቶኝ ካገኘኋት የሦስቱንም ታሪክ በዝርዝር አጫውትሻለሁ:: በአንቺ የሥነ ፅሑፍ ችሎታ ጥሩና ተነባቢ መጽሐፍ ሊወጣው ይችላል::"

"እንዲቀናህ እመኝልሃለሁ:: እኔም ብሆን ከሚቀጥለው ሳምንት ጀምሮ አዲስ መፅሐፍ ለመድረስ ስላቀድሁ መንደርደሪያ የሚሆነኝ አንደ ነገርከኝ ዓይነት ታሪክ ባገኝ አልጠላም" አለችው:: ኤልዋዝ ግልፅና ሥራ ወዳድ ሴት ነበረች:: ከቻፕማን ጋር ለመለያየት የበቁት በአንድ ምክንያት ብቻ ነው:: ለኤልዋዝ ልጆቿ ከአእምሮዋ አፍልቃ የምትፅፋቸው መፃህፍት ናቸው:: ቻፕማን ደግሞ ስሙን የሚያወርሰው አቅፎ የሚያሳድገው ከኤልዋዝ ማህፀን የወጣ ልጅ ይፈልጋል:: ዋናው ጥላቻው ይሄው ነበረ:: ሆኖም ትዳራቸው ቢፈርስም የሚተያዩት እንደ ወንድምና እህት ነበረ::

"ያቺስ ተዋናይ ወዳጅህ ደህና ናት?" አለችው ኤልዋዝ ፈገግ ብላ::

"ምን ደህንነት አለ ብለሽ ነው? ትርዒት ለማሳየት አገር ለአገር ስትዞር ነው የምትከርመው:: በፊት በፊት እንኳን ለጋብቻም ከጅያት ነበረ:: ሳስበው ግን እኔ የአርባ ሁለት ዓመት ሰው እርሷ የሃያ አንድ ዓመት ኮረዳ! ለረጅም ጊዜ ተጣጥመን የምንቆይ አይመስለኝም"

"ከደራሲ ተዋናይ አይሻልም ብለህ ነው?"

"አትቀልጂ! ይብሳል እንጂ ቢያንስ ቢያንስ አንቺን ሥራ ውዬ ወደ ቤቴ ስመለስ አገኝሽ ነበረ:: ይቺን እኮ በተከታታይ ሰቀናት ለሳምንታት አላያትም:: እንዳውም ከአንቺ የምደብቀው ነገር የለምና በስልክ እንኳን መገናኘታችን ተቋርጧል" አላት::

"አንተን ላለማስቀየም እያልኩ እንጂ እኔም ቀድሞውኑ እንደማትሆን ይሰማኝ ነበረ"

"አንቺስ ሌላ ባል የማግባት ዕቅድ የለሽም?"

"የለኝም! ሰምን አንተን ፈታሁና ነው ሌላ ባል የማገባው? ለሁብቱ? ለቁመናው? ለመልኩ? ለማዕረጉ? ከአንተ የሚበልጥብኝም አንድም ሰው አይኖርም:: ያልተግባባነው በልጅ የተነሳ ብቻ ነው:: ልጅ ብወልድ እንደ አሁኑ ነፃ ሆኜ ጊዜዬን ለሥነ ፅሑፍ ላውለው አልችልም:: ይህ አመለካከቴ በሴትነቴ ጤናማ ላይመስልህ ይችላል:: እኔ ግን ሥነ ፅሑፍን በጣም ነው የምወደው:: በምሰራውም ፍፁም ደስታን አገኝበታለሁ" አለችው:: ስለ ደስተኛነቷ ቻፕማን የሚያውቀው ነገር ነው:: ለዚህም ነው በእርቅ ሰምኖ አብራው እንድትኖር ያላደረገው::

"ከሶስቱ እህትማማቾች አንደኛዋን አግኝቻት እንደነበረ የነገርኩሽ አይመስለኝም:: አንቺ ለሥራሽ ታማኝ እንደ ሆንሽ እርሷ ደግሞ ለባሏ ታማኝ ናት:: የምታስጉመጅ በጣም ውብ ናት:: ግን ምን ያደርጋል ..." አለና ቆመ::

"ከዚያች ከተዋናይህ ትሻላለች ማለት ነው?"

"መሻል ብቻ! እንደነገርኩሽ ለባሏ ታማኝ ባትሆን ኖሮ..." አለና አሁንም የጀመረውን በእንጥልጥል ተወው::

"አይዞህ! አንድ ቀን የምትስማማህን ሴት ታገኝ ይሆናል:: ከኛ ብጤዎቹ ግን ራቅ! ጥሩ ሚስቶች አይወጣንም:: በእኔና በዚያች በተዋናይህ





ያየኸው ነው! በል እንግዲህ ሸኘኝ" አለችና በጠረጴዛው ላይ ተንጠራርታ ጉንጩን ሳመችው::

"ግን ትወጂኝ ነበረ?" አለ ከመቀመጫው እየተነሳ::

"ልቤ እስከሚጠፋ!" አለችና ሳቀችበት:: ወገብ ለወገብ እንደተቃቀፉም መኪናዋ ጋር ደረሱ:: በሩን ከፍቶ ካስገባት በኋላ በተራው ጐንበስ ብሎ ጉንጯን ሳመና እርሱም ወደ መኪናው ሄደ::

እቢሮው የጠበቀው ሌላ የምስራች ዜና ቻፕማን በዚያን ፍጥነት ይፈፀማል ብሎ ያልገመተው ነው:: ወደ ሳንፍራንሲስኮ ልኮት የነበረው ረዳቱ የሚጋንን የጉዲፈቻ አባት ዴቪድን ባያገኘውም ሚስቱ ሬቤካ የምትሰራበትን ቦታ ሊደርስበት ችሎ ነበረ::

ቻፕማን በአስቸኳይ ወደ ሳንፍራንሲስኮ ስልክ ደውሎ ከረዳቱ ጋር እንደተገናኘ "የምርህን ነው? በእርግጥ ያገኘሃት ሴት ሬቤካ ናት?" ሲል ጥርጣሬ ገብቶት ጠየቀ:: በተሰጠውም መልስ ከመጠን በላይ ተደሰተ:: በሳንፍራንሲስኮ ከተማ ውስጥ ዴቪድ በሚል ስም የተመዘገበውን ሰው ሁሉ የቻፕማን ረዳቶች አነጋግረዋል:: ግን የሚፈልጉትን ሰው ለማግኘት አዳግቷቸው ነበረ:: ይህም ያለ ምክንያት አልነበረም:: ዴቪድና ሬቤካ ከሃያ ዓመት በፊት ሳንፍራንሲስኮን ለቀው ወደ አትላንታ ይሄዳሉ:: በዚህም በህግ ሙያ ላይ ተሰማርተው ሲሰሩ ይቆያሉ:: ወደ ፍራንሲስኮ የተመለሱት ዴቪድ ግማሽ አካሉን ሽባ ባደረገው በሽታ ከተለከፈ በኋላ ነው:: ሥራም በማቆሙ ስሙ በሳንፍራንሲስኮ ስልክ ማውጫ ላይ አልተመዘገበም:: በምትኩ በጥብቅና ሙያ አሁንም እርዳታ ትሰጥ የነበረችው ሚስቱ የሬቤካ ስም ነበር የተመዘገበው::

ቻፕማን ስረዳቱ ሌላ እርምጃ እንዳይወስድ በጥብቅ ካስጠነቀቀው በኋላ የሬቤካን አድራሻ ጠይቆ ስልኩን ዘጋ:: ወዲያውንም ወደ ሬቤካ ደውሎ ካነጋገራት በኋላ ለጥብቅ ጉዳይ ሊያገኛት እንደሚፈልግ ገልፆ በቀጠሮ ተስያዩ:: በማግስቱም ወደ ሳንፍራንሲስኮ በአውሮፕላን ለመሄድ መቀመጫ አስያዘ:: ከዚያም ለቀናት ሊያረገው እየፈለገ ሳይፈፅመው የቀረውን አንድ ነገር ለማድረግ ቆርጦ ተነሳ::

እስር ሰዓት ሊሆን ሲል መኪናውን አስነስቶ ሂላሪ ወደምትሰራበት ዜና አገልግሎት ድርጅት አመራ:: ያለምክንያት ክህንፃው ለመግባት ስለማይቻልም በልዩ ዘዴ አግኝቶ የነበረውን የፖሊስ

መታወቂያ ካርድ ለተቆጣጣሪዎቹ አሳይቶ አታሎ አለፈ:: አስተናባሪዋንም ሂላሪን በስልክ እንድታገናኘው ጠየቃት:: እርሷም ባለስልጣን መስሏት ደወለችለት:: ስልኩን ያነሳችው የሂላሪ ልዩ ፀሐፊ ነበረች:: ስብሰባም ላይ መሆኗን ነገረችው::

"አስተዳደር ነክ ስብሰባ ነው ወይንስ ሌላ?" አለ ቻፕማን ስለ ድርጅቱ ብዙ የሚያውቅ በሚመስል::

"ከምክትል ዋና ስራ አስኪያጅ ቤከር ጋር ናቸው!"

"አ! ገባኝ! ግን በስንት ሰዓት የሚጨርሱ ይመስልሻል?"

"አስራ ሁለት ሰዓት ላይ የሚሄዱበት ቀጠሮ ስላላቸው ከዚያ በፊት ይጨርሳሉ ብዬ ነው የምገምተው"

"አመሰግናለሁ" አለና ቻፕማን ስልኩን ዘግቶ ወደ ሂላሪ ቢሮ ለመውጣት ወደ ሊፍቱ ሄደ:: ከዚያም ከእንግዶች ማረፊያ ክፍል ፊንጢር ብሎ ተቀመጠና መፅሔት ማገላበጥ ጀመረ::

ሂላሪ ከቢሮዋ የወጣችው ልክ አስራ አንድ ሰዓት ተኩል ነበረ:: ቻፕማንም ማንም ሳይነግረው አውቋታል:: ከጥቁሩ ፀጉሯ በስተቀር በአረንጓዴ ዓይኖቿ በተቀረው መልክና ቁመናዋ ሌላዋ አሌክሳንድራ ነበረች:: ልዩ ፀሐፊዋም በአክብሮት በመጥራት ስትለናበታት ሰምቷል:: ሂላሪ ራሷን ጎንበስ በማድረግ አፀፋውን መልሳላት ግራና ቀኝ ሳታይ ወጣች:: ቻፕማንም ያን ጊዜ ከኋላ ኋላ ተከተላት:: እርሷ ከገባችበት ሊፍት አጠገብ ካለው ሌላ ሊፍት ውስጥ ገባ:: ከህንፃው ወጥታ በሹፌር ወደሚነዳው መኪናዋ ስትሄድ እርሱም ወደ መኪናው ሄደ:: የተጀመረውም ክትትሉ ቀጠለ:: ከመሐል ከተማ ደርሳ ከመኪና ስትወርድ እርሱም ወረደ:: ክትትሉም ከመኪና ወደ እግር ተሸጋገረ:: ከአንድ ሱቅ ውስጥ ገብታ ያኔውኑ በመውጣቷ ከበራፉ ቆሞ ከነበረው ቻፕማን ጋር ሰጥቂት ሊጋጩ ነበረ:: በአረንጓዴ ዓይኖቿ እንደ መገላመጥ ብላ አየችው:: ትላልቅ አረንጓዴ ዓይኖቿ ነፍስን ሰርስረው የሚገቡ ነበሩ:: ለቻፕማንም ግልፅ መልዕክት አስተላለፉለት:: ማንም እንዲቀርባት የምትፈልግ ሴት አልነበ ረችም:: ሁለት ረጃጅም ህንፃዎች አልፋ ከአንድ ቡና ቤት ውስጥ ገባች:: ቻፕማንም ተከትሏት ገባ:: የሂላሪ ቀጠሮ ከአንዲት ወጣት ሴት ጋር ነበረ:: ሂላሪን ብድግ ብላ ከተቀበለቻት በኋላ ሁለቱም ተቀምጠው መነጋገር ጀመሩ:: ስለምን እንደሚያወሩ ለቻፕማን ባይሰማውም ወጣቷ ሴት ከሂላሪ





የምትጠይቀው እርዳታ ለመኖሩ ከሁኔታዋ ያስታውቃል:: በመሐሉም ታለቅስ እንደ ነበረች ቻፕማን አይቷታል::

ህፃን ልጅ ዳግመኛ እንዳያጠፋ ጣትን በመወዝወዝ እንደሚያስጠነቅቁት ሁሉ ሂላሪም ለሴትዮዋ ተመሳሳይ ምልክት አሳይታት አንድ ነገር ተናገረች:: በዚያን ጊዜም ሴትየዋ ከመቀመጫዋ ተነስታ ያለ ይሉኝታ የሂላሪን እጅ እያገላበጠች ሳመችው:: ቻፕማን የራሱን ግምት ወሰደ:: ሴትዮዋ በጥፋት ከሥራ ተባራ አሁን ግን ይቅርታ የተደረገላት መሆን አለባት አለ በሆዱ:: ሂላሪ ከቡና ቤት ውስጥ ስትወጣ እንደ በፊቱ ኮስተርተር ብላ አልነበረም:: ደግነት ስለ ሰራችም ሊሆን ይችላል ፊቷ ላይ ፈገግታ ይታይባት ነበረ:: ወደ መኪናዋ ስትሄድ ቻፕማንም ወደ መኪናው ሄደ:: በሰባ ሁለተኛው አውራ ጎዳና አጠገብ ካለ አንድ መኖሪያ ቤት ፊት ለፊት ሂላሪ ወረደች:: በራፉንም ከፍታ ገባች:: ቤቱ ከቡናማ ድንጋይ የታነፀና ለዓይንም ማራኪ ሲሆን ከሌሎች ፊንጠር ብሎ የተሰራ ነበረ:: የብቸኝነት ኑሮ መምረጧም አንድ ምልክት ነበረ:: በጣም አዘነላት:: የልጅነት ዘመኗ ታሪክም ታወሰውና በሆዱ አሰቀለላት:: ቆየት ብሎ ደግሞ ራሱን በራሱ አፅናና:: ማን ያውቃል? ሲያይዋት ብቸኛና ኮስታራ ሴት ብትመስልም ደስተኛ ልትሆን ትችላለች:: ባል ባይኖራት እንኳን የምታፈቅረውና የሚያፈቅራት ሰው ሊኖር ይችላል አለ በሐሳቡ:: ግን ያለፈው ታሪኳ ትዝ ሲለው የዛሬውኑ የብቸኝነት ሁኔታዋን ሲያስበው ወዲያውኑ አልመሰል አለው:: ወደ ቤቱም ሄዶ ከአልጋው ላይ ጋደም እንዳለ የሚያስበው ስለ ሂላሪ ነበረ:: ወደ አየው መኖሪያ ቤቷ ሄዶ ሊያነጋግራት ዳድቶት ነበረ:: እጇን፣ በወዳጅነት ሊጨብጠው ስለ አሌክሳንድራ ሊያወራት... የሚያፈቅራት ሰው ስለመኖሩ ሊገልፅላት ... ግን ለዚህ ሁሉ ጊዜው ገና ነበረ:: የሚጋን ነገር ቁርጡ መታወቅ አለበት::

# ክፍል 4

# ሚጋንና ከዚያም...

“አፌም እንደገና በሳቅ ተሞላ፣ ከንፈሮቼም እልልታ አሰሙ”





## ምዕራፍ ሃያ ሁለት

ከሳንፍራንሲስኮ አውሮፕላን ማረፊያ የደረሰው ከቀጠሮው ጊዜ ሁለት ሰዓት ቀደም ሲል ነበረ:: ስለዚህ ሬቤካን ለመገናኘት በቂ ጊዜ ነበረው ማለት ነው:: ከአውሮፕላን እንደ ወረደም ወደ ተመዘገበበት ሆቴል ሄዶ ዕረፍት አደረገ:: ከዚያም ወደ ሬቤካ ቤት አመራ:: ቤቱ በአስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን የተሰራ እንደ መሆኑ ከውጪ ሲያዩት ያረጀ ይመስላል:: ወደ ውስጥ ሲገቡ ግን የንፅህናው፣ የቤቱ ዕቃዎቹ ጥራትና የግድግዳዎቹ ጌጦች ለዓይን የሚማርኩ ነበሩ:: ሬቤካም ብትሆን ዕድሜዋ ከስልሳ ይለፍ እንጂ በአለባበሷ፣ በፀጉር አበጣጠሯና በጠቅላላ ሁኔታዋ ሃምሳም ዓመት የሞላት አትመስልም:: ሽበት ጣል ጣል ያለበት ፀጉሯን ጉንጉን ተሰርታዋለች:: ከነጭ ሸሚዝ ጋር ሰማያዊ ጂንስ ሱሪ ለብሳለች:: እንደ ቀዩ የጆሮ ጉትቻዋ ሁሉ ክፀጉሯም ላይ የሰካችው አበባ ቀይ ነበረ:: ላያት የደስ ደስ ያላት ብልህ፣ በወጣትነቷ በጣም ቆንጆ የነበረች ሴት ናት:: ቻፕማንንም ሞቅ ባለ ፈገግታ ከተቀበለችው በኋላ ወደ ግል ቢሮዋ እንዲገባ ጋበዘችው:: የመጣበትን ምክንያት ካለማወቋም ይዞት የነበረውን የእጅ ቦርሳ በእንግዳ መቀበያ ክፍል ውስጥ አስቀምጦ ሲከተላት እንኳን ሌላ ጥርጣሬ አላደረባትም::

“ብቻ ሳይህ ትልቅ ሰው ትመስለኛለህ፣ የእኔን እርዳታ የምትፈልግ ዓይነት አይደለህም::” አለችውና ፈገግ ብላ፤ “ቡና ወይንስ ሻይ ይምጣልህ?” ስትል ጠየቀችው:: ቻፕማን ምንም ለመጠጣት አልፈለገም:: እንደዚያችም ያለችውን መልካም ሴት ሲነግራት በመጣው ዜና እንድትበጠበጥ ፍላጎት አልነበረውም:: ሆኖም ያ ለፓተርሰን የገባው ቃል ኪዳን እንዲናገር አስገደደው::

“የመጣሁት ስለ አንድ ለየት ያለ ጉዳይ ላነጋግርዎት ነበረ:: እርስዎንና ባለቤትዎን በማፈላለግ ላይ ከቆየሁ ብዙ ቀናት አልፈዋል:: ይህም ትልቅ ችግር ፈጥሮብን ነበረ:: ከሰላሳ ዓመታት በፊት በኒውዮርክ ያስመዘገባችሁትን የመጨረሻ አድራሻችሁን ብቻ ነበር ለማግኘት የቻልኩት” አለ ቻፕማን ሰውነቱን እንደ መዘግነን እያለው::

ሬቤካ ግን እንደ ልማዷ ፈገግ አለችና በወንበሩ ላይ ተዝናንታ ተቀመጠች፡፡ በተረጋጋ አነጋገርም "አዎ ከኒውዮርክ ከመጣን ወዲህ በተለያዩ ግዛቶች ውስጥ ተዘዋውረን ሰርተናል፡፡ ወደዚህም የተመለስነው ባሌ በመታመሙ በቅርቡ ነው" አለችው፡፡

"በጣም ታመዋል ማለት ነው?"

"ነበረ! አሁን ግን እየተሻለው ነው፡፡ ሽባ ሆኖ የነበረው እጅና እግሩ አሁን በመጠኑም ቢሆን እየተፍታታለት ነው" አለች፡፡

"ሚጋንስ?" አላት ቻፕማን የልቡ ትርታ እየጨመረ፡፡

"በጣም ደህና ናት፡፡ አሁን ያለችው በኬንታኪ ግዛት ነው፡፡ ግን ሚስተር ቻፕማን ስለ እኔ ቤተሰብ እንዴት ለማወቅ ቻልክ?" አለችው፡፡ እጅግ በመገረሟ ግንባሯን ቋጠር ታድርገው እንጂ ያ ፈገግታዋ ከፊቷ ላይ አልተለየም ነበረ፡፡

"እኔ እንኳን የማውቀው ነገር አልነበረም፡፡ በተዘዋዋሪ መንገድ ግን እንዳውቀው ተደረግሁ፡፡ የሰለጠንኩበት ትምህርት እንደ ርስዎ በሕግ ቢሆንም በወንጀል ምርመራ ሙያ ላይ መሰማራቱን መረጥኩ፡፡ እና በዚያ ሳቢያ ሚስተር አርዘር ፓተርሰን ከሚባሉ ሰው ጋር ለመተዋወቅ ቻልን፡፡ እና እርሳቸው ናቸው ስለርስዎ ቤተሰብ ያጫወቱኝ፡፡ ሚጋንን በጉዲፈቻ ልጅነት የሰጧችሁ ሰው ስለሆኑ እንደሚያስታውሷቸው አልጠራጠርም" አለ ዓይኑን ሰበር አድርጐ እየተመለከታት፡፡

ይህን ስትሰማ ያ ሁሉ ፈገግታ ከፊቷ ላይ ከመቅፅበት ተገፎ "ምን አዲስ የተፈጠረ ነገር አለ? ለምንስ ነው ሚስተር ፓተርሰን ከዚህን ሁሉ ዓመታት በኋላ ሊያስታውሰን የበቃው?" አለች፡፡ ሬቤካን ፍርሐት በጣም ገብቷታል፡፡ ሚጋንን ነጥቆ የሚወስድባት መስሳት ያ ፍራቻዋ ግን አዲስ ሳይሆን ምን ጊዜም ያልተለያት ነበረ፡፡

"በአጭሩ መሞቻቸው በመቃረቡ ነው፡፡ ከዚህ በፊት ግን ሶስቱ እህትማማቾቹ ደህና መሆናቸውን ለማወቅ ይፈልጋሉ፡፡ ሶስቱም ደስተኞች መሆናቸውንና የገንዘብም ችግር እንደሌለባቸው ለማረጋገጥ ይሻሉ፡፡ በሕይወት እንዳሉም ሶስቱን እህትማማቾች ለማገናኘት ምኞት አላቸው፡፡ እህትማማቾቹ እንደተነጣጠሉ እንዲቀሩ አይፈልጉም፡፡"





"ለዚህ ጊዜው ዛሬ ነው? ከሰላሳ ዓመታት በኋላ? ቢገናኙስ ጠቀሜታ ይኖረዋል? ለነርሱስ ቢሆን ምን ልዩነት ያስከትላል?" ስትል በንዴት የጥያቄ ጋጋታ አወረደችበት፡፡

"የእህትማማቾቹ መገናኘት በሕይወታቸው ላይ ልዩነት ይኖረዋል የሚል እምነት ሚስተር ፓተርሰን አላቸው፡፡ የእርስዎ ፍርሐት ደግሞ ይገባኛል፡፡ ስሜትዎም ምን ያህል እንደተጐዳ አውቀዋለሁ፡፡ በዚህም በጣም ነው የማዝነው፡፡"

የሚነግራትን ሁሉ የምትሰማው አትመስልም ነበረ፡፡ ከንፈሯን በንዴት ደጋግማ እየነከሰች፤"ገና ሚጋንን በጉዲፈቻ ልጅነት ከመውሰዳችን በፊት ጀምሮ ነበረ ያስጠነቀቅነው፡፡ ከእርሱም ሆነ ከእህቶቿ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት ሊኖራት እንደማይችል ገልፀንለት ነበረ፡፡ እኛም ወደ ካሊፎርኒያ የመጣንበት ዋነኛው ምክንያት ሚጋንን ከተወለደችበት አካባቢና ማንነቷን ከሚያውቁት ሰዎች ለማሸሽ ነበረ፡፡ እና ሚጋንን ምንም ከማታውቀው ታሪክ በአሁኑ ዕድሜዋ ለማስተዋወቅ መሞከሩ ትክክል አይመስለኝም" አለች፡፡

"ምርጫውን ለርሷብንተወው፡፡ ከፈለገች ከእህቶቿ ጋር ለመገናኘት ትችላለች፡፡ ካልፈለገችም የሚያስገድዳት የለም፡፡ በነገራችን ላይ የምትኖረው በኬንታኪ ግዛት ውስጥ ነው ብለው የነገሩኝ ይመስለኛል?"

"አዎን! በሕፃናት ሕክምና የዶክትሬት ዲግሪዋን ወስዳ አሁን አፓላቺያ በሚባለው መንደር ውስጥ ልምምድ በማድረግ ላይ ናት" አለች ሬቤካ በልጇ ልዩ ችሎታ ኩራት እየተሰማት፡፡

"እዚያ ላገኛት እችላለሁ ማለት ነው?" ሲል ቻፕማን ሲፈራ ሲቸር ጠየቃት፡፡

እንደፈራውም አልቀረ አባባሉ አናዷት ኖሮ ከመቀመጫዋ ብድግ ብላ "አይሞክርም! አታደርገውም!" ስትል ጮኸችበት፡፡ በረድ ሲልላትም ከመቀመጫዋ ተመልሳ አረፍ አለችና በረጅሙ ከተነፈሰች በኋላ "እንዴት ከዚህ ሁሉ ዓመት በኋላ መጥተህ በሰላም የምትኖረውን ልጃችንን ልትበጠብጣት ትፈልጋለህ? ለምንስ ነው ስሐዘን ልታጋልጣት የምትሻው? ለመሆኑ የወላጆቿን አሟሟት እንዴት እንደነበረ ታውቀዋለህ?" ስትል ጠየቀችው፡፡

"እምን እውቀዋለሁ ግን ሚጋንስ?" ሲል ተራውን ጠየቃት።

"ፍፁም አታውቀውም። ስለዚህ አቋሜን ግልፅልፅ አድርጌ ልነግርህ እፈልጋለሁ። በዛሬው ቀን ያቀረብክልኝ ጥያቄ ሊነሳ የሚገባ አይደለም። ሚጋን የጉዲፈቻ ልጅ መሆኗን እንኳን አታውቀውም" ብላ ትኩር ብላ ታየው ጀመረ። ሬቤካም ሆነች ባሏ ዴቪድ የሕግ ባለሙያዎች ብቻ ሳይሆኑ ለሰብአዊ መብቶች ተከራካሪዎች ናቸው የሚል ስም እንዳላቸው ቻፕማን ሰምቷል። ታዲያ እንደዚህ ያሉ የሰውን ዘር አፍቃሪ ፍጡሮች ከሆኑ እንደምን ለሚጋን የጉዲፈቻ ልጅነቷን ሳያስታውቋት ቀሩ የሚል ሐሳብ ተሰምቶታል። ስለምን ቀደም ብለው እውነቱን ነግረዋት ቢሆን ኖሮ የዛሬውን ችግር ባላስከተለ ነበረ።

"ሌሳ ልጅ የላችሁም?" ሲል ቻፕማን በሐዘኔታ ጠየቃት።

"የለንም! እንዲኖረንም አንፈልግም ነበረ። ሚጋንን እንደ ዓይን ብሌናችን ነው የምናያት። ከእራስነቷም ጀምሮ ነው ያሳደግናት። ስለዚህ እርሷም እንደ ወላጆቿ ነው የምትወደን። እኛም ከአደገች በኋላ ስለ እውነተኛው ቤተሰቧ የምንነግርበት ምክንያት አልነበረም።"

"እሁንስ ልትነግሯት ፈቃደኛ አይደላችሁም?" አለ እንባ ያቀረሩ ዓይኖቿን ላለማየት እንደ ማቀርቀር ብሎ። እሺ ትለኛለች የሚል ግምት ከቶም የለውም። ቢሆንም የሚጋንን አድራሻ ነግራዋለች። ካስፈለገ ወደ ኬንታኪ ግዛት ሄዶ እፈላልጐ ሊያገኛት ይችላል። ስለ እህቶቿ ማወቅ መብቷ ነው። ግን ታሪኩን ከርሱ ከማታውቀው አፍ ከምትሰማው ይልቅ በምትወዳቸው አሳዳጊዎቿ በኩል እንድታውቀው ቢደረግ እንደሚሻል ተሰምቶታል።

ሬቤካ መልስ ሳትሰጠው ለረጅም ጊዜ ስታስብ ቆየች። ከዚያም እርግጠኛ ባለመሆን፤"በእሁኑ ሰዓት እነግራታለሁ ወይንም አልነግራትም ከሚል ቁርጥ ካለ መልስ ላይ ለመድረስ ያዳግተኛል። በቅድሚያ ስለ ጉዳዩ ከባሌ ጋር ልወያይበት ይገባል። ከዚያ በፊት ግን የእርሱን የግል ሐኪም ማነጋገር ይኖርብኛል። ምናልባት ሐኪሙ ድንጋጤ ሊያስከትል ልበትና ከሌላ አደጋ ላይ ሊጥለው ይችላል ካለኝ ላላነሳበትም እችላለሁ። ቀደም ሲል እንደ ነገርኩህ ባሌ ሕመምተኛ ነው" አለችው።

"ችግሩ ይገባኛል። ለማንኛውም የምቆየው በማርክ ሆፕኪንስ ሆቴል ስለሆነ ከአንድ ወይንም ከሁለት ቀን በኋላ ስልክ ቢደውሉልኝና ውጤቱን ቢገልፁልኝ?"





"ከአንድ ውሳኔ እንደ ደረስን እደውልልሃለሁ።" አለችና ከመቀመጫዋ ተነሳች። ይህም ለውይይታቸው ማብቂያ ምልክት ነበረ።

"እስከዚያ ለምን ወደ ኒውዮርክ አትመለስም?" አለችው ከፊት ፊቱ ወደ በሩ እየሄደች።

"እዚህ ሆኜ መጠበቁ ይሻላል። ምናልባት ባለቤትዎም ሊያነጋግሩኝ ይፈልጉ ይሆናል"

"ከመሰለህ ጥሩ" አለችና በመለናበት እጁን ጨበጠችው። በዚህን ጊዜ ግን የቀድሞ ፈገግታዋን አላሳየችውም። በሩን ዘግታ ወደ መቀመጫዋ ተመልሳ በግንባሯ ከጠረጴዛው ላይ ድፍት አለች። ራሷንም በሁለት እጆቿ ይዛ ስታለቅስ ቆየች። እንደፈራችው ከሰላሳ ዓመት በኋላ ልጇን ሊወስዱባት ነው። ለሰላሳ ዓመት እንደ ወላጅ እናትና ልጅ የሚተያዩትን ሬቤካንና ሚጋንን በማታውቃቸው እህቶቿ ሳቢያ ሊያራርቋቸው ነው። ለነሬቤካ ውለታ ለዚያ ለፍቅራቸው የሚከፈላቸው ውለታ በዚህ መልክ መሆን አልነበረበትም።

በዚያኑ ዕለት ከሰዓት በኋላ ላይ የዴቪድን ሐኪም አነጋገረችው። እንደ ሐኪሙም አባባል ከሆነ ዴቪድ ያንን አስደንጋጭ ዜና ቢሰማም በጤናው ላይ ጉዳት የማያስከትልበት ነበረ። ያም ሆኖ ሬቤካ ለሁለት ቀናት ያህል ደፍራ ሳትነግረው ቆየች። በሶስተኛው ዕለት ግን ጨክና ነገረችው። ከደረቱ ላይ ተኝታ እንባዋን እያፈሰሰች ከመጀመሪያውም ስትፈራው የነበረው ነገር እንደደረሰ አጫወተችው። ሚጋንን የርሷ ብቻ እንጂ ሌላ ቤተሰብ እንዲኖራት አትፈልግም ነበረ። "ከእንግዲህ ስለ ሁሉም ነገር ለማወቅ ትፈልጋለች። ስለ እውነተኛዎቹ ወላጆቿም ማንነት ለመረዳት መጓጓቷ አይቀርም" ስትል ለባሏ ፍርሃቷን ገለፀችለት።

"ምናለበት? እንነግራታለና" አለ ዴቪድ።

"ስለ እኛ ያላት የፍቅር ስሜት ይቀንሳል ብዬ ነው የምፈራው።"

"ሬቤካ ብዙ ብዙ ነገር ታውቂያለሽ። ታዲያ እንዴት በዚህ ቀላል ጉዳይ ለመጨነቅ በቃሽ? እንደምትወደን ታውቂያለሽ። እንደ እውነቱም ከሆነ ከእራስነቷ ጀምሮ ያሳደግናት እኛ በመሆናችን በማታውቃቸው ወላጆቿ የምትለወጠን አይመስለኝም። ስለሆነም እህቶቿን ብታገኛቸው ምንም የሚያሰጋሽ ነገር ሊኖር አይገባም። ለምሳሌ እኔ በነገው ቀን ሁለት እይቻቸው የማላውቀው እህቶች አሉህ ተብዬ ብነገር ልገናኛቸው እጓጓለሁ።

ስለ እየጓቸው ደግሞ ለአንቺ ወይንም ለሚጋን ያሰኘን ፍቅር ይቀንሰዋል ማለት አይደለም» አላት:: ሬቤካና ዴቪድ በዚሁ ጉዳይ ላይ እየደጋገሙ እስከ እኩለ ሌሊት ሲወያዩ ቆዩ:: ሬቤካ በዴቪድ አስተያየት ሙሉ በሙሉ አልረካችም:: እሁንም ቢሆን ሚጋንን የምታጣት እየመሰላት ፈርታለች:: ዴቪድ ግን ዜናውን ለሚጋን የመንገር ኃላፊነት እንዳለባቸው ፅኑ አቋም ወስዷል::

ተስፋ ወደ መቁረጡ ተቃርቦ ለነበረው ቻፕማን በማግስቱ ሆቴሉ ሬቤካ ስልክ ደወለችለት:: በምሳ ሰዓት እቤት ድረስ እንዲመጣ ጋበዘችው:: ለሚጋንም እንዴት እንደሚነግሯት ለረጅም ጊዜ ተወያዩ:: ችግሩን ለማቃለል ሲል ቻፕማን ሳይወድ በግድ የአሌክሳንድራንና የጉዲፈቻ እናቷን የማርጋሬትን ሁኔታ አንስቶ በዝርዝር አጫወታቸው:: በመጨረሻም ላይ ለሚጋን እንደ አሌክሳንድራ ሁሉ ሬቤካ እንድትነግራት ከእልባት ላይ ደረሱ:: ሚጋን ከሁለት ሳምንታት በኋላ ለዕረፍት ትመጣ ነበረ:: ጥሩም አጋጣሚ የሚሆነው ያ ወቅት በመሆኑ ከዚያ በኋላ ለቻፕማን ስልክ ልትደውልለት ተስማምተው ተለያዩ::

ወደ ኒውዮርክ እንደተመለሰ ሚስተር ፓተርሰንን ማነጋገር ነበረበት:: ሕመሙ እየተባባሰበት በመሄዱ ቢሮ መሄድ ካቆመ ውሎ አድሯል:: ስለ ሚጋን መገኘት በመስማቱ ቢደሰትም ለሁለት ሳምንት ያህል የመጠበቁ ጉዳይ ግን እርሱንም ቻፕማንንም አሳስቧቸዋል:: በመሐሉ ሊሞት እንደሚችል ግልፅ ነው:: ሆኖም ሌላ አማራጭ ባለመኖሩ ያለውን ዕድል በትዕግስት መጠበቁ ብቻ ነበረ::

"ከዚህስ በኋላ ምን ለማድረግ ነው ያቀድከው?" ሲል ቻፕማንን ጠየቀው::

"የሬቤካን መልስ በስልክ እጠብቅና ውጤቱን እንደሰማሁ ለሰሚገና ኙበት ቀን ቀጠሮ እይዛለሁ:: በአሌክሳንድራ በኩል እንዳችም ችግር አይኖርም:: በመለሰኝ ዕለት ብጠራት እንደምትመጣ ገልፃልኛለች:: ሂላሪን ግን እሁን ላነጋግራት አልፈልግም:: የቀጠሮው ዕለት ሲቃረብ ባነጋግራት እንደሚሻል ይሰማኛል::" እለ ቻፕማን:: ትክክል ነበረ:: ሂላሪ እህቶቿን ረስታቸዋለች:: ሌት ተቀን እንዳላሰቀለችላቸው አገኛቸዋለሁ ብላ እንዳልጓ ጓችላቸው፣ ወሽመጧ ቁርጥ ብሎ እሁን የሚታያት የሥራዋ ጉዳይ ብቻ ነበረ:: በዚያ ላይ ደግሞ ፓተርሰንን ዳግመኛ ለመገናኘት እንደማትፈልግ እያጠራጥርም::





ፓተርሰንም በቻፕማን ውጤት በመደሰቱ ተሰናብቶት ሊወጣ ሲል "በጣም ነው የማመሰግንህ:: ሶስቱንም እህትማማቾች ታገኛቸዋለህ የሚል ግምት አልነበረኝም" አለው::

"እኔም አልመሰለኝም ነበረ" ብሎ ቻፕማን ፈገግ አለ:: ሐቁን ለመናገር ክትትሉን ሲጀምር እንኳንስ ሁሉንም ቀርቶ አንደኛዋን እንኳን አገኛለሁ የሚል ተስፋ አልነበረውም:: እሁን ግን ሂላሪን፣ አሌክሳንድራንና ሚጋንን ሶስቱንም አግኝቷቸዋል:: ምናልባትም ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ለሰላሳ ዓመት ያህል የተለያዩ እህትማማቾች ይገናኙ ይሆናል:: ቻፕማንም የተጣለበትን አደራ ተወጣ ማለት ነው:: ይህንንም ሲያስበው እንደ ሸክም ከትከሻው ላይ የወረደለት ያህል ቀለል አለው:: የቀድሞዋ ሚስቱ ኤልዋዝም ምላ በመብላት ላይ እንዳሉ የተናገረችው ትዝ ያለው በዚያን ወቅት ነበረ:: ሶስቱ እህትማማቾች ከተገናኙ በኋላ ነው የቻፕማን አዕምሮ እንደ ዱሮው ከሐሳብና ከጭንቀት ነፃ የሚሆነው::

## ምዕራፍ ሂያ ሶስት

ቃል እንደ ገባችው ሬቤካ ከሁለት ሳምንት ተኩል በኋላ ስልክ ደወለችለት:: ከድምጿም እንደተረዳው ከሆነ ያንን ታሪክ ለሚጋን መንገሩ ምን ያህል እንደ ከበዳት ሊያውቀው ችሏል::

"የፈራሁትን ያህል አልደነገጠችም" አለችው በስልክ ውስጥ የሚሰማው ድምጿ ቁርጥ ቁርጥ እያለ:: "በጣም ነው የኮራሁባት... ምን ጊዜም ለርሷ ከፍተኛ ግምት ነበረኝ... ወደ ኬንታኪ ግዛት እንደ ተመለሰች እራሷ ስልክ ደውላ ታነጋግርሃለች" አለችው::

"አሁን ላነጋግራት አልችልም ማለት ነው?" ሲል ቻፕማን ረጋ ብሎ ጠየቃት::

ሬቤካ የስልኩን መነጋገሪያ በእጇ ሸፍና አጠገቧ ካለ አንድ ሰው ጋር ተነጋገረች:: ከዚያም የሚያውቀው ዓይነት ድምፅ ሰማ:: ያ ድምፅ ከአሌክሳንደራ ድምፅ ቅላፄ ጋር ተመሳሳይ ነበረ:: አሳሳቃቸውም የማይለይ ነው::

"ሚስተር ቻፕማን ነዎት?"

"አዎን ነኝ!"

"ምን ጊዜም ያልጠረጠርኩትን ታሪክ ለማሁኝ" አለችው::

"በጣም አዝናለሁ ሚጋን:: ጤናማውን ኑሮሽን በመበጥበጤ ከልቤ ነው ይቅርታ የምጠይቅሽ"

"ለምን? ምንም ያጠፋት ነገር የለም:: ግን ሊያነጋግሩኝ የፈለጉት ስለምን ነበረ?"

"ከእህቶችሽ ጋር ስለምትገናኝበት ቀን ቀጠሮ ለመያዝ ነበረ"

"የሚመችኝን ቀን ለመናገር በግድ ወደ ሥራ መደቤ መመለስ አለብኝ:: ከዚያም በኋላ ነው ከአለቃዬ ጋር ተነጋግሬ ፈቃድ የማገኝበትን ቀን የማውቀው"





"ቀኑን በስልክ ትገልጪልኛለሽ?"

"ቆይ እስቲ" አለችና ለጥቂት ጊዜ ዝም አለች:: በአእምሮዋ የምታሰላው ነገር ነበረ:: ቀጠል አድርጋም "ከመስከረም አንድ ቀን ጀምሮ የአንድ ሳምንት ዕረፍት ስለሚኖረኝ ለምን በዚያን ጊዜ አናደርገውም?" አለችው::

"ጥሩ! እንግዳው አሌክሳንደራ ከወዲሁ እንድትዘጋጅ መስከረም አንድ ቀንን በጊዜያዊ ቀጠሮነት እንያዘው?"

"እሺ" አለችና ሚጋን አሁንም ጥቂት አሰብ ካደረገች በኋላ

"ከእህቶቼ ጋር ከመገናኘቴ በፊት ስለነርሱ አንዳንድ ነገር ለማወቅ እፈልጋለሁ:: ስለዚህ ማስቸገር ባይሆንብኝ የፊታችን ቅዳሜ ኬንታኪ ድረስ ቢመጡ?"

"በደስታ!" አላት::

"በጣም አመሰግናለሁ" ብላ ተሰናብታው ስልኩን ዘጋች:: የሚጋን ድምፅ ከታላቅ እህቷ ከአሌክሳንድራ ጋር ተመሳሳይ ቢሆንም እንደ አስተዳደጓ አስተሳሰቧም ለየት ያለ ነበረ:: አሌክሳንድራ ገራገርና ፎልፏላ ስትሆን ሚጋን ግን ኮስታራና ፍፁም የስራ ሰው ነበረች:: በሕክምና ሙያዋ ለመርዳት የመረጠችውም ዕድል የጠመመችባቸውን ድሃ ቤተሰቦች ነበረ:: በዚህ ዓይነቱ ሙያ ላይ መሰማራትን አሌክሳንድራ አልማውም አታውቅም:: ተንደላቃ በማደጓም ድህነት የሚባል ነገር ስለመኖሩም የምታውቅም አትመስልም:: ሂላሪም ብትሆን የወጣትነት ጊዜዋን በሥቃይና በመከራ ታሳልፈው እንጂ፣ አሁን ከከፍተኛ ሥልጣን ላይ በመድረሷ ትኩረቷ ሁሉ ከዚያ ደረጃ ላለመውረድ ኑሮዋን በዘዴና በጥንቃቄ መምራት ነበረ:: ከአንድ ማሕፀን የወጡ፣ ከአንድ አባት የተወለዱት እህትማማቾች በአስተዳደጋቸው ልዩነት ሳቢያ ያላቸው ዓለማዊ አመለካከት የተለያየ ለመሆን በቃ:: ይህንንም በማሰላሰል ላይ እንዳለ ነበረ ቻፕማን አሌክሳንድራ ተናግራው የነበረውን አንድ ነገር ትዝ ያለው:: ስለ ሂላሪ ታሪክ አንስቶ ሲያወጋት፣ በእህቷ የደረሰውን ሥቃይ ከራሷ ኑሮ ጋር በማወዳደር 'ሕይወት ብርቅርቅታ ናት:: ትበራለች ትጠፋለች:: በቅድሚያ አባትና እናታችንን አሳጣችን:: ከዚያም እንድንበታተን አደረገች:: እኔ እንደመሳፍንት ልጅ ሳድግ የሂሊ ዕድል ግን የጨለመ ሆነ' ብላው ነበረ::

እውነትም ሕይወት ብልጭልጭታ ብርቅርቅታ፤ አሁን ደግሞ የሕይወት ሌላ ገፅታዋ በሚጋን ተከሰተ:: ሚጋን በሕክምና የዶክትሬት ዲግሪ አላት:: እንደ ሌሎቹ ብጤዎቿ ከተማን ሳትመርጥ በአንድ የገጠር መንደር ውስጥ የሚኖሩ ድሆችን በመርዳት ላይ ነበረች:: የትናንቷ ምስኪኗ ሂላሪ... በዓይኑ ላይ ውልብ ያለች የሥቅቅታ ብልጭልጭታ! ... ዋና ሥራ አስኪያጇ ሂላሪ እንደ ሰሜን ኮከብ የምታበራ ሌላ ብርቅርቅታ... ከነገስታት ዘር ተጋብታ የወለደችው አሌክሳንድራ እንደዚሁ ሌላ የኮከብ ፅርየት ብልጭልጭታ!... ሚጋን ወጣቷ ሐኪም የአጥቢያ ኮከብ ፍልቅልቅታ... ምክር ... ሶላንጅ... ሶላንጅ ... ምክር ... በኒውዮርክ ከተማ አንድ ጊዜ እንደ ፀሐይ ሞቀው እንደ ጨረቃ ደምቀው ያበሩ የነበሩ ሌላ ብልጭልጭታዎች... ሕይወት ምን ጊዜም አፍታዊ በረቅ... ወገግ ፈካ... ቦግ ጭልም... ብልጭልጭታ!... ብርቅርቅታ... ውልብልብታ::

ከሚጋን ጋር ቀጠሮ ይዞ እንደጨረሰ ወዲያውኑ ለሚስተር ፓተርስን ደውሎ ስላገኘው ውጤት አጫወተው:: ቀጠለናም አሌክሳንድራን ለማነጋገር በካፕ ደፌራ ወደሚገኘው ቤቷ አሁንም ስልክ ደወለ::

"አትለኝም?" በጣም ከመደነቋ የተነሳ ጠየቀችው::

"እውነት ሁሉቱንም አገኘኻቸው?" አለች ጉጉቷ እየጨመረ::

"ለመሆኑ ሚጋን የት ነው ያለችው?"

በአሌክሳንድራ ሁኔታ ቻፕማን በመገረሙ ፈገግ አለ:: ሚጋንን ለሰላሳ ዓመት እንደ ተለየቻት ሳይሆን ሳታያት ጥቂት ቀናት እንዳለፈ እህቷ አስመስላ ነበር አጠያየቋ ሁሉ:: "በሕክምና የዶክትሬት ዲግሪዋን አግኝታ በኬንታኪ ግዛት ውስጥ በማገልገል ላይ ትገኛለች" አላት::

"ያምላክ ያለህ! ትንሿ ሚጋን ዶክተር ለመሆን በቃታለች? ይገርማል!" አለችና "ሂላሪስ ደህና ናት?" ስትል ጠየቀችው::

"አዎን ደህና ናት:: በቅርቡ አይቻታለሁ" ሲል መለሰላት::

"እና ለእርሷም መስከረም አንድ ቀን እንደምንገናኝ ነግረሃታላ?" አለችና የሚመልስላትን ለመስማት ልቧ ተሰቅሎ ጠበቀች::

"እስከአሁን አልነገርኳትም:: ቀኑ ሲቃረብ ባነጋግራት ይሻላል የሚል ግምት አለኝ::"





የፈካው ፊቷ ክስም አለና "ሳታገኛት ለሥራ ወይንም ለሌላ ጉዳይ ከከተማ ውጪ ብትሄድስ?" ብላ ቅሬታዋን ባለመሸሸግ ገለፀችለት::

"ሐሳብ አይግባሽ:: ሌላ ቦታ እንደማትሄድ ስለማውቀው ነው:: በዚያ ላይ ደግሞ የትም ብትገባ ከእኔ እንደማትሰወር መዘንጋት የለብሽም" አላትና ሁለቱም ተሳሳቁ:: ከዚያም ጥቂት ተጫዋውተው የስልክ ንግግራቸውን አበቁ::

ስልኩ ከመዘጋቱ ወዲያውኑ አሌክሳንድራ መነጋገሪያውን እንደያዘች ወደ እናቷ ዘንድ ደወለች::

"እማዬ?"

"አዎን ነኝ አክሲ! ደህና ነሽ?"

"ሁለቱንም አገኛቸው እኮ!" አለች ለመናገር እየተቻኮለች "ምኖቹን?" ስትል ማርጋሬት መለሰችላት:: ማርጋሬት ገና ከመኝታዋ ተነስታ የቀረበላትን ቡና በመጠጣት ላይ እንዳለች ነበረ አሌክሳንድራ ስልክ የደወለችላት:: ስለዚህም ነው ምን ዕቃ ጠፍቷት ሌላ ሰው አግኝቶላት ይሆናል ብላ በመገመት አሁንም ምኖቹን? ስትል ደግማ የጠየቀቻት::

"እህቶቼን ነዋ! ሚስተር ቻፕማን አሁን ከኒውዮርክ ደውሎ ነገረኝ ሁለቱንም አግኝቷቸዋል"

የአሌክሳንድራ ደስታ ለከት ባይኖረውም ያ ዜና ማርጋሬትን ሳያስደነግጣት አልቀረም:: እንደርሷ ግምት ቻፕማን እህትማማቾቹን ጨርሶ አያገኛቸውም የሚል ነበረ:: ያ የተመኘችው ተስፋ ግን አሁን ደበዘዘ::

"ጉሽ! በጣም ደስ የሚል ዜና!" አለች ማርጋሬት አሌክሳንድራ እንዳትታዘባት እርሷም የተደሰተች በመምሰል:: "ደህና ስራ ይዘዋል አለሽ?"

"አዎን! አንደኛዋ ሐኪም ናት፤ ትንሺቱ ማለቴ ነው:: ትልቋ ደግሞ ሂላሪ በኒውዮርክ ውስጥ በሚገኝ አንድ የዜና አገልግሎት ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ ናት::"

"የሚያኮሩ እህትማማቾች ወጥተዋቸዋል! አንቺም ብትሆኚ የተጋባሺው ከነገስታት ዘር ነው:: ታሪካችሁ ቢጠናቀር ቆንጆ ፊልም ይወጣዋል"

ክልቧ ላለመናገሯ ለሌክሳንድራ ገብቷታል። ልታፅናናት ይገባ ስለነበረም "እማዬ ምን ማለትሽ ነው? እህቶቼን ስላገኘሁ ለአንቺ ያለኝ ፍቅር ይቀንሳል ማለት አይደለም። አንቺን የምወድሽ በእናትነትሽ ነው። እባክሽ እመኚኝ!"

ማርጋሬት ባመነቻት ደስ ባላት ነበረ። ግን እንደ ሬቤካ ሁሉ እርሷም ልጇን የምታጣት እየመሰላት ፍርሃቷ አልቀረም። "መቼ ልትገናኙ ነው?"

"መስከረም አንድ ቀን። ቻፕማን እንደነገረኝ ከሆነ በኮኔክቲከት ግዛት ውስጥ ባለው በሚስተር ፓተርሰን ቤት ነው ለመጀመሪያ ጊዜ የምንገናኘው።"

"ለሄነሪስ ምን ብለሽ ትነግሪዋለሽ?"

"ስለዚህ እንኳን ጠለቅ ብዬ አላሰብኩበትም። ያም ሆኖ በኒውዮርክ ስለሚገኘው ስለ አንቺ ንብረት ጉዳይ ለመነጋገር ነው የምሄደው ብለው ምን ይመስልሻል?"

"ፈፅሞ አያምንሽም።"

"አውቃለሁ። ግን እውነቱን እንዳልነግረው ደግሞ ፍርሃት ፍርሃት አለኝ። እስቲ ለማንኛውም ጊዜ ስላለኝ የሚያዋጣኝን ምክንያት እፈልጋለሁ" ብላት በዚሁ ተለያዩ። ግን አምስት ደቂቃም ሳይሞላ ማርጋሬት ተራዋን ስልክ ደውላ አሌክሳንድራን አነጋገረቻት።

"እኔም አብሬሽ እሄዳለሁ" አለቻት ማርጋሬት።

አሌክሳንድራ የሰማችውን ማመን አቅቷት "ምናልሽ እማዬ? ... እውነትሽን ነው?"

"እዎን የምሬን ነው" አለቻት። ማርጋሬት የእህትማማቾቹን ግንኙነት በቅርብ ሆና ለመከታተል ብቻ ሳይሆን ለአሌክሳንድራም ሽፋን ልትሰጣት ፈልጋ ነበረ። በተለይም የፈራችው ከአሌክሳንድራ መለየቱን ነው።

"ግን እኮ እማዬ ወደ ሮም እሄዳለሁ ብለሺኝ ነበረ። ለእኔ ስትይ ይህን ያህል መቸገር የለብሽም"

"የሮሙ ጉዞዬ ስመለስ ይደርሳል። ቀድሞውንም ቢሆን ወደዚያ ለመሄድ ያሰብኩት ያቺን ጓደኛዬን ማሪሣን ለመጠየቅና እግረ መንገዴንም





ጥሩ ጥሩ ጫማዎች ለመግዛት ነው። ለዚህ የሚያጣድፈኝ ነገር የለም አንቺን ቅር እስካላለሽ ድረስ አብሬሽ ብሄድ ..."

"ለምን እንደዚህ ትያለሽ እማዬ? ምኑ ነው ቅር የሚለኝ?" አለች እንባዋ በዓይኖቿ ግጥም እያለ። እናቷ ግን ያን ያህል መስጋት አልነበረባትም። "አንቺ አብረሺኝ በመሄድሽ ራሴን ዕድለኛ ነው የማደርገው። ለእኔ ስትይ ካላሰብሽው ችግር ውስጥ እንዳትገቢ ብዬ ነው ..."

"ለምን ትቀልጃለሽ አሌክሳንድራ። ለእኔ ችግር የሚሆንብኝ ከአንቺ መለየቱ እንጂ ከአንቺ ጋር አብሮ መሄዱ አይደለም" ብላ ጥቂት እንደማሰብ ካለች በኋላ ያልተጠበቀ አንድ ነገር በአእምሮዋ ብልጭ አለባትና "እንዳውም አክሴልንና ማሪንም ይዘናቸው እንሄዳለን" አለች ሳቅ ብላ።

አሌክሳንድራ በዚህ በእናቷ አዲስ ሐሳብ በጣም ነው ደስ ያላት። አንድም ጊዜ ተለይተዋት የማያውቁትን ሕፃናት ለጥቂት ቀናትም ቢሆን በሞግዚት እጅ ትታቸው ለመሄድ አልፈለገችም። ጉዱ እንግዲህ የሄነሪ ጉዳይ ነው። እንኳንስ ልጆቹን ቀርቶ ለርሷም ቢሆን የሚፈቅድላት ዓይነት ሰው አልነበረም።

"ግሩም ሐሳብ ነው እማማ። እኔ ኮኔክቲከት ደርሼ እስከምመለስ ድረስ ሶስታችሁ ኒውዮርክ ትጠብቁኛላችሁ። ከዚያም ወደ ፓሪስ ከመመለሳችን በፊት የተወለድኩበትን ከተማ እየተዘዋወርን እንጎበኛለን።"

"በጣም ጥሩ! ከአሁኑ ወደ ኒውዮርክ ደውዬ ሆቴል እንዲያዝልን አደርጋሁ። የአውሮፕላን ቲኬት ከወዲሁ መግዛት ስለሚያስፈልገን ከዚህ የምንነሳበትን ቀን ብትነግሪኝ?"

"መስከረም አንድ የሚውለው ዓርብ ቀን ስለሆነ እኛ እረቡ ዕለት ብንነሳስ?"

"ልክ ነሽ። ለማንኛውም አስር ቀን ያህል እንደምንቆይ አድርጌ ሆቴል እስይዛለሁ። ካልሽስ ከዚያ በፊት ልንመለስ እንችላለን።"

"በጣም አመሰግንሻለሁ፤ በጣም ነው የምወድሽ እማዬ!"

"እኔም በጣም ነው የምወድሽ አክሲ፤ የቱን ያህል እንደምወድሽ ታውቂያለሽ።" ቻፕማን ካነጋገራት ቀን ጀምሮ በሐሳብ ትዋልል የነበረችው ማርጋሬት ዛሬ ተረጋጋች። አሌክሳንድራን እንደማታጣት ዛሬ ተማመነች።

ሄነሪ ኩርፊያና ንዴቱ በርዶለት ከባለቤቱና ከልጆቹ ጋር ጥቂት ቀናት ለማሳለፍ ወደ ካፕ ፌራት ከመጣ ውሎ አድሯል:: አንድ ቀን ከበረንዳው ላይ ተቀምጠው የስዓት በኋላ ሻይ በመጠጣት ላይ እንዳሉ አሌክሳንድራ ያንን ልታናግረው ፈርታ የነበረውን ነገር አነሳችበት::

"በነሐሴ ወር ማብቂያ ላይ እማማ ወደ ኒውዮርክ አብሬአት እንድሄድ ጠይቃኛለች" አለችው:: በተቻለ መጠን ቀላል ነገር አስመስላ ልታቀርበው ሞክራ ነበረ:: ቀና አለና ከፊኛ ገላመጣት፣ ለፓሪሱ አድራጎቷ ይቅርታ ያድርግላት እንጂ አሁንም በታሰበው ቁጥር ውስጥ እንደ በገነ ነበረ::

"ምን ለመሆን?" አላት የጉሪጥ እያያት::

"እይ! ነገሩስ ቀላል ነው:: በኒውዮርክ ውስጥ ስላሳት ንብረት አንዳንድ የምትፈራረመው ውለታ ስላሳት አብሬአት እንደሄድ ጠየቀችኝ:: ከወላጆቿ ስለ ወረሰችው ንብረት ..."

"አይቻልም" አላት ኮስተር ብሎ::

"ልጆቹም እኮ አብረውኝ ይሄዳሉ"

ከት ብሎ ሳቀና "ልጆቹም? የምትገርሚ ሴት ነሽ! ለምንድነው በነሐሴ ውስጥ ወደ ኒውዮርክ መሄድ ያስፈለገሽ?" አላት:: እናቷንና እርሷን በጆርባው ሌላ ተንኮል የሚሸርቡበት ከመሰለው ጊዜው ቆይቷል::

"በነሐሴ መጨረሻ ላይ ነው:: ለልጆቹም ቢሆን ጥሩ ዕድል ነው እላለሁ:: የሴት አያታቸውን አገር አይተው ቢመጡ ክፋት የለውም::"

"በነሐሴ ወር ልትሄጂ አትችይም:: እኔ በምፈቅድልሽ ጊዜ ያውም ልጆቹን ሳትይዢ ልትሄጂ ትችያለሽ" ምርር ያለው አነጋገሩ እንደ ቀዝቃዛ አየር በሰረሰሯ ሲወርድ ይሰማታል:: ባያውቀው ነው እንጂ አሌክሳንድራ ለመሄድ ቆርጣለች:: ልጆቿንም ጭምር ይዛ ከመሄድ ምንም ኃይል አያስቀራትም ነበረ::

"ተሳስተሃል ሄነሪ! የምሄደው በነሐሴ ነው! ከእናቴና ከልጆቼ ጋር ለመሄድ ወስኛለሁ!"

ከተቀመጠበት በንዴት ቱር ብሎ ተነስቶ ቁልቁል እያፈጠጠባት፣ "ትንሽ ያበዛሺው ይመስለኛል! ለመሆኑ ከመቼ ወዲህ ነው አንቺን ብሎ





ወሳኝ? በዚህ ጣሪያ ስር ስለ አንቺም ሆነ ስለ ልጆቹ ውሳኔ ለመስጠት የሚችል አንድ ሰው ብቻ ነው:: ይህን ላስታውስሽ እወዳለሁ" አላት የሌባ ጣቱን በዛቻ እያወዛወዘ::

"ይህን ያህል የሚያናድድህ ነገር ሊሆን አይገባም ሄነሪ! እናቴ እኔንም ልጆቹንም ጋበዘችን:: ግብዣዋን አክብረን መቀበል ደግሞ ይኖርብናል::"

"አትሄዱም ብዬሻለሁ! አትሄጂም!"

"የእናቴን ጥያቄ ውድቅ ላደርገው ስለማልችል እንደምሄድ እወቀው::"

"እናትሽ በሽተኛ አይደለችም:: ብቻዋን ለመሄድ ትችላለች:: ስለ አንቺ መቅረት ግን ራሴ ስልክ ደውዬ እነግራታለሁ::"

"ስማ ሄነሪ ! ምን ጊዜም ከአንተ ትእዛዝ ውጪ አንድም ነገር ሰርቼ እንደማላውቅ ታውቃለህ:: የአሁኑ ግን ለየት ያለ ጉዳይ ስለሆነ ወደ ኒውዮርክ ከመሄድ ልታስቀረኝ አትችልም" አለችው ፍርጥምጥም ባለ አነጋገር::

"ለምን? እስቲ አሳማኝ ምክንያት ብቻ ንገሪኝ?"

"የተወሳሰበ ነገር ስለሆነ ማስረዳቱ ይከብደኛል:: ግን ከቤተሰብ ጉዳይ ውጪ እንደማይዘል አረጋግጥልሃለሁ::"

"እንደምትዋሺኝ ከፊትሽ ላይ ይነበባል አሌክሳንድራ!" እውነቱን ነበረ:: ግን መዋሸቷ ደግሞ ወዳ ሳይሆን አማራጭ በማጣቷ ነበረ:: እውነቱን አፍረጥርጣ ልትነግረው ወኔ ከዳት:: "እባክህ ሄነሪ እንደዚህ አትበል:: እየው የምሄደው ለጥቂት ቀናት ብቻ ነው" ስትል ልትለማመጠው ሞከረች::

"ለምን እኮ ነው የምልሽ? ለምን? ጥያቄዬ አልገባሽም?" አለና ጠረጴዛውን በቡጢ ደጋግሞ መታው::

"እባክህ ሄነሪ ልትረዳኝ ሞክር?" አለችው አሌክሳንድራ የምታደርገው ጠፍቷት:: "እናቴ ዘመዶቿን ለማየት ስለምትፈልግ አብሬአት ብሄድ ምን አለበት? ምንስ ጉዳት ያስከትላል?"

"ለአንቺ ጉዳት ሳያስከትል ይችላል:: ለእኔ ግን አትሄጂም ስልሽ ብትሄጂ የሚያጉድለኝ ነገር ይኖራል:: ስለዚህ አትሄጂም" አለ ይብሱኑ ፍርጥም ብሎ::

"እሄዳለሁስ ብል?"

"እንደዚህ ካለ ውሳኔ ላይ ለመድረስ የምትችይ አይደለሽም ቤተሳጤ እንዳልሆንሽ እወቂ!"

"እንደዚህ ካልክስ ባሪያም አይደለሁም! ያለነው በሰለጠነው በሃያኛው ክፍል ዘመን እንጂ በድንጋይ ዳቦ ዘመን አይደለም!"

"ለካስ የእኛ እመቤት ሳይታወቅብሽ ለሴቶች የእኩልነት መብት ተከራካሪ ወጥቶሻል! ይህን አስተሳሰብሽን ከእኔ ጋር አብረሽ እየኖርሽ ልትገፊበት አትችይም:: እንዳሻሽም የሽርሽር ፕሮግራም ለማውጣት መብት ያለሽ አይመስለኝም::"

"እረ እባክህ ሄነሪ እንደዚህ አትሁን! ለምን እንደ በደልኩህ አስመስለህ ታወራለህ?"

"በደልሺኝ አላልኩም! አሁን የምንነጋገረው በዚህ ቤት ውስጥ ውሳኔ ስለሚሰጠው ሰው ነው:: ልክ እንዳለፉት አስራ አራት ዓመታት ወሳኙ እኔ እሆናለሁ::"

"እኔስ በበኩሌ ውሳኔ ላይ ብደርስ?" አለችው ትዕግስቷ ወደ መሟጠጡ እየተቃረበ:: በሕይወቷም ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ነበረ ሄነሪን ልትጠላው ስትደርስ:: እርግጥ ሄነሪ ሐቀኛና ለቤተሰቡ ደህንነት ያላሰለሰ ጥረት የሚያደርግ ሰው ነው:: ግን ለሆነው ላልሆነው ቁጥጥር ያበዛ ስለነበረ፤ ለአሌክሳንድራ ደስታ ደንቃራ ሆኖባታል:: አሁንም እየሆነባት ነው::

"የግልሽ ውሳኔ ላይ የመድረስ ዕቅድ ካለሽ መጋጨታችን እንደማይቀር ለመጨረሻ ጊዜ ሳስጠነቅቅሽ እፈልጋለሁ" አላት ፊቱን እንዳኮሳተረ::

"እኔም በተቻለ ትህትና ልገልፅልህ የምፈልገው በነሐሴ ወር መጨረሻ ላይ ከእናቴ ጋር ወደ ኒውዮርክ እንደምሄድ ነው::"





"ስትሄጂ ለማየት ያብቃና! ደግሞም ልጆቼን ይዘሽ ለመሔድ እንደማትችይ ይገባሻል?"

"እነሱም እንደኔ ነፃነት የላቸውም ማለት ነው?"

"ከመሰለሽ?"

"ለምን አይመስለኝም:: እንደ ጥፋተኛ ከፓሪስ አባረህ በዚህ ቤት ውስጥ ግዞተኛ አድርገኸኝ ከረምክ:: እስቲ የፈፀምኩትን በደል ንገረኝ?"

"ለምን እነግርሻለሁ:: የሰራሺው በደል ቢኖርማ ነው ለሕሊናሽ እየተሰማሽ እንደዚህ የምትናገሪው::"

"ልክ አይደለህም! የእንተ ሙከራ በግድ በደለኛ ልታደርገኝ ነው:: እኔ ግን ምንም ጥፋት ስላላጠፋሁ እንዳችም የሕሊና ፀፀት አይሰማኝም:: ከእናቴ ጋር ለመሄድ ፍቀድልኝ ብዬም የምለማመጥህ አይምሰልህ! ይህን ለመሳሰለው ጉዳይ ራሴ ልወስን እችላለሁ::"

"የእኛ እመቤት! ለመብረር ክንፍሽን ዘርግተሻል ማለት ነው? እረ ይኼ ሁሉ ልበ ሙሉነት ከወዴት መጣ? ከሄነሪ ቤት ብወጣ በግል ሀብቴ ልተዳደር እችላለሁ ብለሽ በመኩራራት ነው?"

"እንደዚህ ያለ ሐሳብ አንድም ቀን ተሰምቶኝ አያውቅም" አለችው:: የዛሬ አነጋገሩ ከከሶ የመረረ ነበረ:: ለምንስ በቀላሉ አልተረታችልኝም ሲል ንዴቱ አያህልም::

"ቢሰማሽ ባይሰማሽም እንደማትሄጂ ወስኛለሁ" አላትና የውጪውን በር ከፍቶ ወጣ:: ከኋላ ኋላውም እያየችው ተስፋ በመቁረጥ ራሷን እያወዛወዘች:: ሄነሪ የማያዋጣ አቋም መያዙን አልተረዳውም:: አሌክሳንድራን ወደኒውዮርክ ከመሄድ ማንም ሊገታት አይችልም... የምትወደው ሄነሪ እንኳን ቢሆን::

# ምዕራፍ ሃያ አራት

ቻፕማን ከኬንታኪ አውሮፕላን ማረፊያ ሲደርስ ከሌላ ፕላኔት ላይ የደረሰ እንጂ በዚህ ዓለም ውስጥ ያለ አልመሰለውም ነበረ። ሚጋን ከላከችለት ሹፌር ጋር በዚያ ገባ ወጣ መንገድ ላይ ለሶስት ሰዓት ያህል እየነጠሩ ተጉዘው ከአንዲት አነስተኛ መንደር ደረሱ። በመንደሯ ውስጥ በምትገኝ አንዲት አነስተኛ ሆቴል መኝታ ከያዙ በኋላ ለምሳ የዕንቁላል ሳንድዊች በልተው ጉዟቸውን ቀጠሉ።

ሆስፒታሉ ከመንደሯ ውጪ ባለ አንድ ረዘም ያለ ተራራ ላይ ነበረ የተሰራው። ቅርንጫፍ ከቅርንጫፍ በተያያዘው የጥድ ጫካ ውስጥ እያቆራረጡ ከተራራው ጫፍ ሲደርሱ ቻፕማን የሚያየውን ሁሉ ማመን አቃተው። በሆስፒታሉ ዙሪያ ሰብጠርጠር ያሉ ደሳሳ ጎጆዎች ይታያሉ። በደርዘን የሚቆጠሩ ሕፃናት በባዶ እግራቸው ከጨርቅ በተሰራ ኳስ ይጫወታሉ። አጥንታቸው የሚቆጠር ውሾች በየቆሸሸ መከመሪያው አካባቢ ያነፈንፋሉ። በአጠቃላይ አካባቢው እርዛትና ርሀብ የሰፈነበት ነበረ። በእንደዚያ ያለ ውብ ተራራ ላይ ያን ሁሉ ጉስቁልና ማየቱ ቻፕማንን ከማዘንም አስገርሞታል። እንደ ኒውዮርክና ዋሽንግተን የመሳሰሉት ዘመናዊ ከተሞች አሁን ቻፕማን ከቆመበት ስፍራ የሚርቁት በመቶ በሚቆጠሩ ኪሎ ሜትሮች ብቻ ነበረ።

ከሆስፒታሉ በስተጀርባ ወደ ነበረው ክሊኒክ ሲወስዱት አሁንም ቻፕማን ሌላ አሳዛኝ ሁኔታ ገጠመው። ከሃያ እስከ ሰላሳ የሚደርሱ ነፍሰጡር ሴቶች በአግዳሚው ወንበር ላይ ተኮልኩለው ተቀምጠዋል። ከአመጋገብ ጉድለት ሆዳቸው የተቆዘረና ልብሳቸው እላያቸው ላይ የተበጫጨቀ ህፃናት በየእናቶቻቸው እግር ስር ኩርምት ብለው ተቀምጠዋል። ከነፍሰጡሮቹ ሴቶች መካከል አብዛኞዎቹ ዕድሜአቸው ከሃያ ባይበልጥም ሁሉም ከሶስትና አራት ህፃናት በላይ የወለዱ ነበሩ።

ወደ ክሊኒኩ ውስጥ እንደገባም ከፊት ለፊት ከሚታየው ዴስክ ላይ አንድ ወርቃማ ፀጉር ያላበሰው ያቀረቀረ ራስ አየ። ራመድ ብሎ ወደፊት ሲጠጋም ያ ያቀረቀረ ራስ ቀና ብሎ ዓይን ለዓይን ተጋጩ።





ወርቃማ ፀጉር... ትልልቅ አረንጓዴ ዓይኖች... ቁርጥ ሌላዋ አሌክሳንድራ ነበረች። እርግጥ ሚጋን፣ ፀጉሯን እንደ አሌክሳንደራ በውበት ሳሎን ውስጥ የምትንከባከብበት ጊዜውም ዕድሉም አልነበራትም። ስለዚህ መሐል ለመሐል ከፍላ የኋሊት ጉንጉናዋለች። በአለባበሷም ከፓሪሷ ፋሽን አማራጭ አሌክሳንድራ ልትወዳደር ቀርቶ ከአሜሪካም አቻዎቿ ያነሰ ነበረ። ሰማያዊ ጂንስ ሱሪ፣ ከደረቱ የተከፈተ ነጭ ሸሚዝ ለብሳለች። ያደረገችውም ረጅም ቦት ጫማ ነበረ። ከመቀመጫዋ ተነስታ ወደርሱ እጇን ዘርግታ ስትመጣ "ደህና ነሽ ዶክተር?" አለና በፈገግታ ጨበጣት። እርሷም ሳቅ ብላ ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ በስተጉን ወደነበረችው አነስተኛ ክፍል ይዛው ገባች።

ቻፕማን ስለ እህቶቿ ያደረገውን ጥናት የያዘውን ፋይል እንድትመለከተው ሰጣት። እርሷም ገፆቹን አንድ በአንድ ስታነብ ቆየች። እንደጨረሰችም ቀና ብላ ቻፕማንን በዝምታ አየችው።

"እንደ በፊቱ አሁንም እህቶችሽን ልትገናኚያቸው ፈቃደኛ ነሽ?" አላት የምትለውን እስከሚሰማ በመጓጓት።

"አዎን! በጣም እንጂ ማስተር ቻፕማን!" አለችው።

"ቀን ቀጠሮውም ያው ለመስከረም አንድ መሆኑ ነው።"

"ጥሩ! በበኩሌ ይስማማኛል። ግን ስለቀጠሮው ለእህቶቼስ ነግረኻቸዋል?"

"ለአሌክሳንድራ ነግሬአት እንደምትመጣም ቃል ገብታልኛለች። ለሂላሪ ግን እስከ አሁን አልነገርኳትም።"

"ለምን ሚስተር ቻፕማን? ለምን?" አለች ፊቷ እንደ ማዘን ብሎ።

"አይዞሽ! ከዚህ እንደተመለስኩ አነጋግራታለሁ። ምንም ሐሳብ አይግባሽ" አላት።

"ሳታገኛት እንዳትቀር ብዬ ነው" አለች አሁን ፈገግ ብላ።

"ፍርሃትሽ ይገባኛል። ግዴለሽም አገኛታለሁ"

"ጥሩ" አለችና ለጥቂት ጊዜ ስታስብ ቆይታ እርሷም አሌክሳንድራ አንስታበት የነበረውን ጥያቄ ጠየቀችው። "ለምንድን ነው አባታችን እናታችንን የገደላት?" አለችው። ቻፕማን ለአሌክሳንድራ እንደነገራት ሁሉ የምክንያቱን በትክክል አለማወቅ ገልጾላት. ሆኖም በመካከላቸው

ጭቅጭቅ ተፈጥሮ ነበር የሚል ወሬ በኋላ ላይ መንፈሱን አጫወታት:: ቀጠለችና ስለ ሂላሪ አንዳንድ ጥያቄዎች አቀረበችለት:: በእህቷም ታሪክ ከልብ በማዘኗ እንባዋን መቆጣጠር አቅቷት ነበረ:: ስለ አሌክሳንድራ ባጫወታት ጊዜ ግን በደስታ እየተፍነከነከች፤ "እስቲ የእኔንና የርሷን ኑሮ አወዳድረው! በኬንታኪና በፈረንሳይ መካከል ያለውን ርቀት ያህል ነው በእኔና በአሌክሳንደራ የኑሮ ደረጃ መካከል ያለው ልዩነት" አለችና ቻፕማንን አሳቀችው::

ንግግሩንም ወደ ሌላ አቅጣጫ በመቀየር "እናቴ ግን ከእህቶቼ ጋር መገናኘቴን እምብዛም አልወደደችውም" አለችው::

"ፍቅርሽ ሁሉ ለእህቶችሽ ይሆናል ብለው በመፍራታቸው ነው:: አባትሽ ግን ይህ እንደማይደርስ ሊያሳምኗቸው መሞከራቸውን አይቻለሁ"

"መፍራት አይኖርባትም:: እህቶቼን እንዳየኋቸው ወዲያውኑ ስልክ እደውልልሻለሁ ብያታለሁ:: አለመለወጤን ለማረጋገጥ ስትልም ልታየኝ ውሳ ሳታድር እንደምትመጣ እርግጠኛ ነኝ" ስትል ሁለቱም ተሳሳቁ:: የሚጋን አረንጓዴ ዓይኖቿ ሕይወትን፣ ደስተኛነትን፣ ቀናነትን ነበረ የማያንፀባርቁት::

ለጥቂት ጊዜ ያህል ተለይታው ለሕመምተኞቹ እርዳታ ስታደርግ ከቆየች በኋላ ተመልሳ መጣች:: ከዚያም በዚያው በሆስፒታሉ ግቢ ውስጥ ወደምትገኘው አነስተኛ መኖሪያ ቤቷ አብሯት እንዲሄድ ጋበዘችው::

ከክሊኒኩ በመውጣት ላይ እንዳለ አሁንም በአግዳሚ ወንበር ላይ የተደረደሩትን ሴቶች ብዛት ቻፕማን አይቶ፤"ለማመን የሚያስቸግር ነገር ነው" አላት::

"አዎን! አሜሪካንን ያህል በሰለጠነ ሀገር ውስጥ እንደዚህ በችግር የሚቆራመዱ ሰዎች መኖራቸው በጣም የሚያሳዝን ነው:: ያየኻቸው ሁሉ የትምህርት፣ የሕክምና፣ የልብስና የምግብ እርዳታ የሚያሻቸው ናቸው" አለችው::

የሚጋን ቤት እንደውጪው ሳይሆን ውስጡ ማራኪ ነበረ:: ግርግዳዎቹ በልዩ ልዩ የእጅ ስራዎች አጊጠዋል:: ወንበሮቹ የአካባቢው ሕዝብ ባህላዊ ውጤቶች ነበሩ:: ሚጋን ለእራታቸው ሾርባ ቀቅላ ከበሉ በኋላ ለስላሳ መጠጥ እየጠጡ ሲጫወቱ አመሹ::





ፈገግታዋ፣ ጨዋታዋ፣ ቀልዷ ሁሉ ልክ የኮረዳነት ጊዜዋ እንዳለፈ ልጃገረድ ነበረ:: "እህቶቼን ባላስታውሳቸውም ሳያቸው መንገቴን ታውቀዋለህ ሚስተር ቻፕማን?" አለችው ሌላ ሌላ ነገር ሲወያዩ ጣልቃ አስገብታ:: ቻፕማን እጇን ያዝ አደረገና፤ "አውቃለሁ" አላት:: እውነትም ትንሿ ሚጋን ስለ ሂላሪም ሆነ አሌክሳንድራ እንዳችም ትዝታ አልነበራትም:: መንፈሷም በሐዘን ባለመቁሰሉ ነው ዛሬ ልበ ሙሉና ቀና ሴት ለመሆን የበቃችው::

ማታ ላይ ከተራራው ሥር ወደምትገኘዋ መንደር ቻፕማንን በጂፕ መኪናዋ ሸኘችው:: ከዚያ በደማቅ ጨረቃ ባሸበረቀ ምሽት ከጎኑ ተቀምጣ ለሰዓታት እንድታወራው ፈልጉ ነበረ:: ግን ከምሽቱ አራት ሰዓት በኋላ ተረኛ ስለነበረች ወደ ሆስፒታሉ መመለስ ነበረባት::

"መቼም አንተም በኮኔክቲከቱ የመተዋወቂያ በዓላችን ላይ እንደምትገኝ አልጠራጠርም" አለችው ከመለያየታቸው በፊት::

"አዎን እገኛለሁ" አላትና ፈገግ አለ:: "ለጥቂት ጊዜም ቢሆን መገኘቴ አይቀርም:: ሚስተር ፓተርሰን እናንተን የመቀበሉንና የማስተናገዱን ኃላፊነት የተውት ለእኔ ነው::"

"እስከምንገናኝ ደህና ሁን" ብላ አንድ እጇን እወዛውዛለት በዚያ ኮረኮንች መንገድ ላይ ጉዞዋን ቀጠለች:: ቻፕማንም ከቆመበት ሳይንቀሳቀስ በዓይኑ ተከተላት:: ከተራራው ላይ የሚነፍሰው ቀዝቃዛ አየር ጉንጮቹን ዳሰስ እያደረጋቸው ያልፋል:: በየዋሻው ውስጥ የሚገኙ የእያሌ ጉጉቶች ጩኸት የምሽቱን ፀጥታ ይሰነጥቀዋል:: በተለይም የጨረቃዋ ድምቀት ልብን የሚሰልብ ነበረ:: 'ምነው ከሚጋን ጋር በዚህ ከሥልጣኔ በራቀ መንደር ለዘለዓለም በኖርኩ' ሲል ለጥቂት ጊዜም ቢሆን መመኘቱ አልቀረም::

# ምዕራፍ ሃያ አምስት

አሌክሳንድራ ለኒውዮርኩ ጉዞዋ የሚያስፈልጋትን ማናቸውንም ዝግጅት አጠናቃለች:: ልጆቹን በማለባበስ ላይ እንዳለች ነበረ ሳታስበው ሄነሪ የደረሰባት:: ክንዷንም ለቀም አድርጎ በመያዝ "የተናገርኩሽ የገባሽ መስሎኝ ነበረ! ወደ ኒውዮርክ አትሄጂም ብዬአለሁ! አትሄጅም!" ሲል ጮኸባት::

"እባክህ ሄነሪ፤ እባክህን መሄድ አለብኝ" አለችው ለዘብ ብላና ጨምድዶ የያዘውን ክንዷን ለማስለቀቅ ሳትሞክር::

"ካልሄድኩ ብለሽ ይህንን ያህል ሙዝዝ ያልሺው ለምንድነው?" ብሉ በንቀትም በጥላቻም ዓይን ያያት ጀመረ:: ጥርጣሬው ያው ሌላ ወንድ አፍቅራ ነው የሚል ነው::

"በጣም የጓጓሁለት ጉዳይ ስላለ ነው::"

"ጉጉትሽ ለምን እንደሆነ አልገለፅሽልኝም:: ከእናትሽ ጋር ወደ ኒውዮርክ መሄድ ምኑ ላይ ነው የሚያጓጓው? ይህንን ብቻ አስረጂኝ::"

እንባዋ በዓይኖቿ ግጥም እንዳለ ዝም ብላ ስታየው ቆየች:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ምን ያህል እንደ ጨከነባት ይታወሳታል:: ዛሬም ቢሆን ያ ጠባዩ አልተቀየረም ነበረ:: "ላስረዳህ ስለማልችል ነው:: ስለምን ለመሄድ የፈለግኩበት ምክንያት ከረጅም ጊዜ በፊት በተፈፀመ ድርጊት ሳቢያ በመሆኑ ነው::"

"ከወንድ ጋር የተፈፀመ ድርጊት?" አለና ወንጀል እንደፈፀመች ሁሉ በማንቋሸሽ ዓይን አያት:: እርሷም ቀና ብላ አየችው:: ከበስተ ጆርባው ያረፈበት የሪቪዬራ የበጋ ፀሐይ የፊቱን ቆዳ ያለወትሮው ያሸበሸበ አስመስሎታል:: ጣል ጣል ያለበትም ሽበት ዛሬ ያለወትሮው ደምቆ ይታያል:: 'ይህን ሁሉ ጥርጣሬ' አለች አሌክሳንድራ በሆዷ 'ድሮ ያልነበረውን ጥርጣሬ አሁን ምን አመጣው? ምናልባት ከርሱ ወጣት የሆነ ሌላ ወንድ





በላዩ ላይ ያፈቀርኩ መስሎት ይሆን?' ስትል አሰበችና በሁኔታው በጣም አዘነችለት:: በዚያን ጊዜም ነበረ በመላ ከምታካሂደው ክርክር መስመር ስታ የወጣችው::

"ከሌላ ወንድ ጋር ግንኙነት ይኖራታል ብለህ ፍፁም ጥርጣሬ አይግባህ:: ጉዳዩ ወላጆቼን የሚመለከት ነው" አሁን እውነቱን ተናገረች:: ወላጆቿ ማለቷ ግን ኮምት ዲ.ቦርንና ማርጋሬትን አልነበረም::

"ስለነርሱስ ቢሆን ከእኔ ምን የምትደብቂው ነገር ይኖርሻል?" አላት:: የሄነሪ ግምት ሌላ ነበረ:: አሌክሳንድራ ከአሁን ወዲያ ራሷን መቆጣጠር አልቻለችም:: በቅርቡ ካገኘችው ወንበር ላይ ተቀመጠችና ፊቷን በሁለት እጆቿ ሸፍና ታለቅስ ጀመረ:: ሄነሪ ሊያፅናናት አልሞከረም:: የደበቀችውን ሚስጢር እስከምትነግረው ሊያኮርፋት ቆርጧል::

"እኔ እንኳን ልደብቅህ የፈለግኩት ነገር ነበረ:: እንደ እውነቱ ከሆነም ባትሰማው ይሻላል ባይ ነኝ"

"ግዴለም! ንገሪኝ"

"እኔም ያንን ታሪክ ከሰማሁት ከሁለት ወር አይበልጥም" አለችና ቀና ብላ በማስተዛዘን አየችው:: ሄነሪ አንድ ነገር ሆድ ሆዱን በላው:: ምናልባት አሌክሳንድራን አኩርፊያት የነበረው ባላደረገችው ነገር ይሆን? ሲል መፀፀት ጀምሯል::

"ታሪኩን እናቴ ... ወይንም ቤተሰቦቼ አስቀድመው ሊነግሩህ በተገባ ነበረ:: እኔም ብሆን ስለረሳሁት ነው እንጂ ሆን ብዬ ከአንተ ለመደበቅ ያደረግኩት አይደለም ..."

"እሺ ልስማዋ" አለ ሄነሪ ለውነቱን እንደ ፍርሃት እየወረረው::

"ሄነሪ! የጉዲፈቻ ልጅ ነኝ" አለችውና በረጅሙ ተነፈሰች:: እርሱም ለጥቂት ጊዜ በድንጋጤ ፈዞ ቆየ::

"የጉዲፈቻ ልጅ?... ማነው የጉዲፈቻ ልጅ?... አንቺ!" አለ የሰማውን በመጠራጠር:: በአዎንታ ራሷን አወዛወዘች::

"አይደረግም!... ሌላው ቢቀር አባትሽ ይነግሩኝ ነበረ" አለ አሁንም ድንጋጤው ከፊቱ ላይ በግልፅ እየተነበበ:: ከእንግዲህ አሌክሳንድራ የምትደብቀው ነገር አይኖራትም::

"ከዚያም በፊት ሌላ የጉዲፈቻ አባት ነበረኝ፡፡ የማርጋሬት የቀድሞው ባሏ ..."

ከት ብሎ ሳቀና፤ "ለምን ትቀልጃለሽ አሌክሳንድራ? የኮምት ደ.ቦርገና የማርጋሬት ልጅ አይደለሁም ነው የምትይኝ?"

እምን ስትል ራሷን ዘንበል ቁማድረግ መለሰችለት፡፡

"እና ማርጋሬትም እናትሽ አይደለችም ማለት ነው?"

"አይደለችም"

"ጉድ ነው!" አለና ጣሪያው እስከሚሰነጠቅ ድረስ ሳቀ፡፡ መሐረቡንም አውጥቶ ዓይኖቹን እያባበሰ፤ "እኔ እኮ አንቺም ሆንሽ ህፃናቱ ልጆች እንዳችሁም ማርጋሬትን ባለመምሰላችሁ ሁል ጊዜ ይገርመኝ ነበረ፡፡ ለካስ ለዚህ ኖሯል? እና እነማን ናቸው የአንቺ ወላጆች?" የተራ ድሃ ልጅ ልትሆን ትችላለች... ሴት አዳሪ እናቷ ከሥርቻ ጥላት የተገኘችም የማትሆንበት ምክንያት የለም... ከቶውንም ወላጆቿን ላታውቃቸው ትችላለች፡፡ ይህንን ማሰቡ ራሱ ራስ ምታት በሽታ ለቀቀበት፡፡ ከርሱ ቀደምት የነበሩት ዝርያዎቹ ለአስር ክፍለ ዘመናት ያህል ከነገስታት ቤተሰብ ጋር ብቻ እንዳልተጋቡ ሄነሪ ግን ከአንዲት ምንነቷ ከማይታወቅ ሴት ልጆች ወለደ! ንዴቱ እንደማበድ አድርጉታል፡፡

"እኔም ይህንን ጉድ የሰማሁት በቅርቡ ነው፡፡ ብነግርህ ደግሞ እንደምትደነግጥ ስላወቅሁ ነው ምስጥር አድርጌ መቆየቱን የመረጥሁ" በዚህ አነጋገሯ ሄነሪ ሊፅናና ቀርቶ ይብሱኑ ንዴቱ ግሎ ቤቱን ለቆላት ሊወጣ ከበራፉ ሲደርስ ዘወር አለና በጥላቻ አመለካከት እያያት "ይህን ቀፋፊ ዜና ከመስማት ከሌላ ወንድ ጋር ተኝተሽ ብይዝሽ ይሻል ነበር" አላት፡፡

"ይገባኛል ምን ያህል እንደተናደድህ! ለዚህም ዱብ ዕዳ ስለዳረግኩህ በጣም ነው የማዝነው" ረጋ ብላና አንገቷን አቀርቅራ ነበር የምትናገረው፡፡ ከአሁን ወዲያ እንደ ሚስቱ እንደማይቆጥራት ታውቃለች፡፡ ሄነሪ ዘርን በተመለከተ ቀልድ አያውቅም፡፡ ሌላ ጥፋት ብታጠፋ ይሻላት እንደነበረ እርሷም የምታምንበት ነው፡፡ ግን አንዴ የሆነውን ነገር ለመለወጥ አትችልም፡፡

"ለመሆኑ ወላጆችሽ... እውነተኞቹ ወላጆችሽ ማለቴ ነው እነማን ናቸው?"





ለዚህ ጥያቄ መልስ ለመስጠት ራሷን ማደፋፈር ነበረባት፡፡ ትንፋሿንም በኃይል ሳበችና በልበ ሙሉነት እየተመለከተችው "እናቴ ፈረንሳዊት መሆኗን አውቃለሁ፡፡ ስሟም ሶላንጅ በርትራንድ ይባል ነበረ፡፡ አባቴም ፓሪስን ነፃ ካወጡት ወታደሮች አንዱ ስለነበረ በዚያን ወቅት ነው እናቴን ሊያገኛት የቻለው፡፡ በኋላ ግን ፤በጣም ዝነኛ የትያትር ተዋናይ ለመሆን በቅቶ እንደነበረ ሰምቻለሁ፡፡ ሳም ምከር ነበር የሚባለው፡፡ እናቴን በጣም ስለ ወደዳት እርሷም የዚያኑ ያህል ስላፈቀረችው ተጋብተው ሶስት ሴቶች ልጆች ወለዱ፡፡ ከሶስቱ እህትማማቾች መካከል እኔ ሁለተኛዋ ነኝ፡፡ ከዚያም..." አለች ጉሮሮዋን ሲቃ እየተናነቃትና ልትቆጣጠረው ያልቻለችው እንባዋ በጉንጮቿ ላይ እየተንከባለለ "ከዚያም በግልፅ ባልታወቀ ምክንያት አባቴ እናቴን ገደላት፡፡ የራሱንም ሕይወት አጠፋ፡፡ እኛም ያለአሳዳጊ ቀረን፡፡ ለጥቂት ወራት ያህል ከአንዲት አክስታችን ጋር እንድንቀመጥ ተደርጎ ነበረ፡፡ በኋላ ግን አንድ የአባቴ ጓደኛ የሆነ ሰው እኔን ለማርጋሬት የመጀመሪያ ባል ለጆርጅ ጉርሐም በጉዲፈቻ ልጅነት ሰጠኝ፡፡ ያን ጊዜ ገና የአራት ዓመቴን ጨርሼ አምስተኛዬን ዓመት መያዜ ነበረ፡፡ ለዚህም ነው ወላጅ አባቴንና እናቴን ልረሳቸው የቻልኩት፡፡ ጉርሐም የተባለውም ከስድስት ወራት በኋላ በመሞቱ እርሱንም እረስቸዋለሁ፡፡ እናቴም... ማለቴ ማርጋሬት ባሏ ከሞተ በኋላ በአሜሪካ ለመቆየት ባለመፈለጓ ወደ ፈረንሳይ ይዛኝ መጣች፡፡ ከዚያም ከኮምት ደ.ቦርን ጋር ለመጋባት በቃች፡፡ እኔም እውነተኛ ወላጆቼ መስለውኝ አደግሁ፡፡ ከዚያም ከአንተ ጋር ለመገናኘ ት በቃን" አለችና ፈገግ ለማለት ሞከረች፡፡

ሄነሪ በአፀፋው ፈገግታ አላሳያትም፡፡ በዚያው ንዴት በተሞላ ንግግሩ "እንዴት ያለ ጣፋጭ ታሪክ ነገርሺኝ እባክሽ? ለዚህን ያህል ዘመን እውነቱን ደብቃችሁ በነፍሴ ስትጫወቱብኝ ኖሯል! አንቺ እንኳን ስለማላስታውሰው ልነግርህ አልቻልኩም ብትይም ይቺስ እናትሽ ለምን ሳትነግረኝ ቀረች? ያስ እንደ አባትሽ ሆኖ አንቺን የዳረልኝ ኮምት ደ.ቦርን? እንዳላችሁ አታላዮች ኖራችኋል! በዚህም ክስ ልመሰርትባችሁ እንደምችል አታውቁም? ወይኔ ሄነሪ ለፍቼ መና መቅረቴ!" አለ በቁጭት፡፡

"ከምኑ ነው የቀረኸው? ልጆች ወልጄልሃለሁ፡፡ እነርሱን በማግኘ ትህም አዝነሃል ማለት ነው?" ስትል ያው የተለመደ እንባዋ በጉንጮቿ እየወረደ በለበሰችው ብጫ የሐር ቀሚስ ላይ ጠብ ጠብ ይል ጀመረ፡፡

ሄነሪ ሁኔታዋን ቢያየውም ቅንጣት ታህል አላዘነላትም፡፡ "አዋርደሽኛ ል! የሰው መሳቂያ መሳለቂያ ሆኛለሁ! የሚገርመው ደግሞ ይሄ እኩይ

አድራጐትሽ እነሰና ወደ ኒውዮርክ ካልሄድኩ ብለሽ ታታክሪኛለሽ። ኒውዮርክ የሚኬደው በወላጆችሽ መቃብር ላይ የአበባ ጉንጉን ለማስቀመጥ ነው?" እላት የጥላቻ አመለካከቱን ሳይቀይር።

"እኔ እንኳን የምሄደው ለየት ሳለ ጉዳይ ነው። እኔን በጉዲፈቻ ልጅነት ለነማርጋሬት የሰጠኝ የአባቴ ጓደኛ የሆነው ሰው ለመሞት እየተቃረበ ነው። እኔንም ሆነ እህቶቼን ለማግኘት ሲያፈላልግ ወራት አልፈዋል። ከመሞቱ በፊት እህትማማቾቹ እንደተለያየን እንዳንቀር ሲያገናኘን ዕቅድ አለው። እንድንለያይ በማድረጉ በመጨረሻ ላይ የተፀፀተ ይመስለኛል። እኔ እንኳን በጣም ዕድለኛ ነኝ ለማለት እችላለሁ። አንደኛዋ እህቴ ግን እንደኔ አልታደለችም ነበረ።"

"እና ምን ሆነች? በኒውዮርክ አውራ ጎዳናዎች ላይ ወንድ ፍለጋ የምትዟዟር ሴተኛ አዳሪ? ምን አልከሁና ነው የእኔ እምላክ! የኮምት ዲብርን ልጅ ናት የምላት ሚስቴ በደቂቃዎች ውስጥ የወታደር ልጅ ... በጦርነት ወቅት የተገኘች ሴት ልጅ ... የነፍስ ገዳይ ልጅ ... ሕይወቱን በገዛ እጁ ያሳለፈ ሰው ልጅ... ምኑ ቅጡ?... ምኑ ቅጡ! ገና ሌላም ይጨመርበት ይሆናል። ታዲያ አንቺን ለመሰልሺው ሴት ወይዘሮ ወደ ኒውዮርክ ሄደሽ ከእህቶችሽ ጋር እንድትገናኚ እንድፈቅድልሽ ትጠይቂኛለሽ?" ሲል በምፀት ተናገራትና ጥቂት እንደማሰብ ካለ በኋላ "እንዳውም ይሄ ሁሉ ተንኮል የተቀነባበረው በዚያች በእናትሽ ሳይሆን አይቀርም! ለአባታችሁ ጓደኛ ሐሳቡን ያቀረበችለት እርሷ መሆን አለባት! ምን ያህል እንደምትጠላኝ ስለማውቅ የእኔን ትዳር ለማፍረስ ጥሩውን ኑሮዬን ለማደፍረስ ያደረገችው መሆን አለበት። ለዚህ በደሏ ደግሞ አፀፋውን ባልመልስላት እኔ ሄነሪ አይደለሁም!" ሲል ደነፋ።

"አትሳሳት ሄነሪ! እናቴን በዚህ ጉዳይ ውስጥ አታስገባት። እንደ እውነቱ ከሆነ ከአንተ የበለጠ ነው እርሷም በዚህ በእውነተኛ ወላጆቼ ጉዳይ የተናደደችው። እርሷን እንጂ ሌላ እናት እንደነበረኝ እንዳውቅ አትፈልግም ነበረ። ሌላው ስህተትህ ደግሞ ሄነሪ፣ የእኔ እህት በኒውዮርክ ጐዳናዎች ላይ ወንድ ለመፈለግ የምትዟዟር ጋለሞታ አይደለችም!..."

"ታዲያ ምን ትሆን ይሆን?" ሲል በንቀት አነጋገር አቋረጣት።

"በኒውዮርክ ከተማ ውስጥ የሚገኝ የአንድ ዕውቅ ዜና አገልግሎት ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ ናት። እርግጥ በልጅነት ጊዜዋ እንደ እኔ አልተመቻትም ነበረ። ትንሿ እህቴ ደግሞ በሕክምና የዶክትሬት ዲግሪ





ያላት ናት። ወላጆቼም ቢሆኑ አንተ እንዳንቋሸሽካቸው ሳይሆን በመላ አሜሪካ የታወቁ ሰዎች ነበሩ። ስለዚህ ሄነሪ ወደድክም ጠላህም እህቶቼን ማየት አለብኝ። እንዳውቃቸው እንዲያውቁኝ እፈልጋለሁ። የአንተ ሚስት መሆን አንድ ራሱን የቻለ ነገር ነው። ከእህቶቼ ጋር መገናኘቱ ደግሞ ሌላ!" አለችው ምርር ባለ አነጋገር።

"እንደገባኝ እመቤቴ ከአሁኑ በእኔ ባልነት ያለሽ እምነት መቦርቦር ጀምሯል ማለት ነው?" ሲል በማሾፍ ተናገራትና ወዲያውኑ ኮስተርተር በማለት "ግን አሌክሳንድራ ለምንድነው ሕይወቴን ልታጨልሚው የምትፈልጊው? ይህ ታሪክ ቢሰማ ከዘመዶቼ ተቆራርጬ እንደምቀር አታውቂም? በፖለቲካው ዓለም ውስጥ ልጫወተው ያቀድኩትን ሚና እንደሚያሰናክልብኝስ ሳትረጂው ቀርተሽ ነው? ሌላ ሌላው ይቅር! እስቲ በልጆቻችን ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት እንኳን እይው! ወንድ አያታቸው ሴት አያታቸውን እንደገደለና የራሱንም ሕይወት እንዳጠፋ ሲያውቁ ምን ያህል የአሁኑን አስተሳሰባቸውን ይበክለዋል" ብሎ ፍፁም የዛለ ሰውነቱን ከአልጋው ላይ አሳርፎ ራሱን በሁለት እጆቹ ያዘና "አሁንም ቢሆን ለማመን የሚያስቸግር ታሪክ!" አለ እንዳቀረቀረ።

"እንዳልከው ለእኔም ቢሆን ለማመን ከብዶኝ ነበረ። ታሪኩ ቢሰማ ስትል ስላደረብህ ጥርጣሬ ግን እኛ ሆነ ብለን ካላወራነ ሌላ አንድም ሰው ሊያውቀው አይችልም። እኔና እህቶቼ የምንገናኘው በምስጢር ነው። ልጆቻችንም ቢሆኑ ወደ ኒውዮርክ የሚሄዱት ለሽርሽር ነው የመሰላቸው። እኔም ወደ ኮንክቲከት ስሄድ ከአያታቸው ጋር ኒውዮርክ ይጠብቁኛል።"

"ለምን ሕፃናቱን ይዘሻቸው ለመሄድ እንደ ፈለግሽ አልገባኝም። ምን ያደርጋሉ?"

"የእነርሱ ከአጠገቤ አለመለየት ብርታት ይሰጠኛል" ብላ ትንሽ አሰብ አደረገችና፣ "እሺ አትለኝም እንጂ አንተማ ፈቃድህ ሆኖ አብረን ብንሄድ ደስታውን አልችለውም ነበረ። ለሰላሳ ዓመት የተለያየኋቸውን እህቶቼን ለመጀመሪያ ጊዜ መገናኘት ማለት ቀላል ነገር አይደለም። ኦህ ድሮ በጣም እወዳቸው ነበረ" ስትል ያልተጠበቀ ጥያቄ አቀረበችለት።

"አብሬሽ ልሄድ ቀርቶ አንቺም እንድትሄጂ አልፈልግም። አሁንም ቢሆን እንዳትሄጂ አስጠነቅቅሻለሁ። እህቶቼ እህቶቼ የምትያቸው ሴቶች እንዳንቺ የተከበሩ እመቤቶች አይደሉም። ስለዚህ ልመና ጭምር አትሂጂ ነው የምልሽ።"

ከዚህ በላይ አሌክሳንድሪ ልትለማመጠው አልፈለገችም። ወደ ኒውዮርክ በመሄዷ ቆርጣለች። እነኛንም እህቶቿን አግኝታ ለማየት ብቻ ሳይሆን ልትነካቸው፣ ልታቅፋቸው፣ ልታፈቅራቸውም ትችል ይሆናል። «አዝናለሁ ሄነሪ በመሄዴ ቆርጫለሁ። ይህ ደግሞ በትዳራችን ላይ ችግር ያስከትላል ብዬ አልገምትም» አለችና ወደ ተቀመጠበት ሄደች በማለት አንገቱን ልታቅፈው ሞከረች።

አላስቀረባትም ነበረ። በሩቁ እጆቿን በእጁ ገፈተረና "ከዛሬ ጀምሮ የእኔና ያንቺ ነገር አከተመለት" አላት።

"በጣም ነው የማዝነው ሄነሪ... የእኔ እህቶቼን ማግኘት ለዚህ የሚያደርሰን ከሆነ በድጋሚ ሐዘኔታዬን እገልፅልሃለሁ ... እኔ ግን ነገ ወደ ፓሪስ ከተመለስኩ በኋላ ተነገ ወዲያ ወደ ኒውዮርክ በራሪ ነኝ" አለችው ከርሱ ጋር መቆራረጧ እየታያት ለቅሶ ጀምራ።

በመነፋረቅ ላይ ለነበረችው አሌክሳንድራ ሌላ ተጨማሪ ቃል ሳይናገራት ከተቀመጠበት ተነስቶ በሩን ከፍቶ ወጣ።





# ምዕራፍ ሃያ ስድስት

የመስከረም አንዱ ቀጠሮ ከመድረሱ ከሶስት ቀናት በፊት ነበረ ቻፕማን ሂላሪን ለማነጋገር ወደ ቢሮዋ የሄደው። እንደ በፊቱም በልዩ ዘዴ ያገኘውን መታወቂያ ደብተር ለዘብተኞች በማሳየት ያለ ችግር ወደ ሕንፃው ገባ። ከዚያም የሂላሪ ቢሮ ወደነበረበት ፎቅ ወጣ። ልክ ቀደም ሲል እንደሚተዋወቅ ሰው ለልዩ ፀሐፊዋ ማራኪ ፈገግታውን ለማሳየት የሂላሪን መኖር አለመኖር ጠየቃት።

"ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ወደ ውጪ የሚሄዱበት ጉዳይ አለ ..." ቻፕማን ማንነቱን እስከምትጠይቀው እንኳን ጊዜ አላጠፋም። በጉና አልፎ ወደ ሂላሪ ቢሮ ገባ። ልዩ ፀሐፊዋ ግራ ተጋባች። የዚያ ድርጅት ሰራተኛ ባይሆንም ሂላሪን በቅርብ የሚያውቃት ሰው መሆን አለበት ስትል ገመተች። መልኩ፣ ቁመናው፣ አለባበሱ ጭምር ያማረ ነበረ። ስለ ሂላሪ የግል ሕይወት አንድም ሰው እንደዚያ ነው ብሎ ለመናገር ባይችልም በምስጢር ሊኖሯት ከሚችሉት ወዳጆቿ መካከል አንዱ ሊሆን ይችላል ስትልም አሰበች። ቻፕማን ድምፅ ሳያሰማ የቢሮውን በር ከኋላው ከዘጋ በኋላ አቀርቅራ ትፅፍ ከነበረችው ሂላሪ ፊት ለጥቂት ጊዜ ቆመ። ቀና ብላ ስታየውም እንደ መደንገጥ አለች።

"ምን ነበር?" ስትልም ጠየቀችው። አይታው የማታውቀው ፊት ነው። ግን ወደርሷ ቢሮ ደግሞ ለተለያየ የስራ ጉዳይ የሚመላለሱ ሰዎች ብዙ ናቸው። አመጣጣቸው በቀጠሮ ሲሆን አስተያየታቸውም አሁን ክፊቷ እንደቆመው ሰው አልነበረም። ለብዙ ጊዜ እንደሚያውቃት ዓይነት በሐዘን አመለካከት ሲያያት ቆየ። ወደ ርሷም ጠጋ ሲል እርዳታ ለመጠየቅ የስልኩን መነጋገሪያ ለማንሳት እጇን ቀስ ብላ ሰደደች። ለእርሷም ቢሆን ያን ልብ የሚሰልብ ፈገግታ ሲያሳያት ወዲያውኑ ሃሳቧን ቀየረች። እንደ ፀሐፊዋም እርሷም በዓይነ ህሊናዋ ከግምት ውስጥ አስገባችው። ቆንጆ ነው። አመለካከቱ የምሁር ነው። አለባበሱም እንከን አይወጣለትም። ግን ወደርሷ ቢሮ የሚያመጣው አንድም ምክንያት አስባ ለማግኘት አልቻለችም።

“እመቤት ሂላሪ!” ስሟን ረጋ ባለ ድምፁ በቅድሚያ ጠራ:: እርሱ የሚፈልጋት ሂላሪ ስመሆኗ አሁን የሚጠራጠረው ነገር አልነበረም:: “ከከባድ ስራ ሳይ ስላቋረጥኩሽ ይቅርታ እጠይቅሻለሁ:: ለጥቂት ደቂቃዎች እንዳነጋግርሽ ብትፈቅጂልኝ?” አለና ቀረብ አላት::

ሁኔታው ስላላማራት ሌላ ነገር ቢመጣ ራሷን ለማዘጋጀት ቀስ ብላ የጠረጴዛውን ጠርዝ ተደግፋ ተነሳች:: ከዚያም በአረንጓዴ ትላልቅ ዓይኖቿ እንደ በረዶ በቀዘቀዘ አመለካከት እያየችው፤ “አሁን ከቢሮ ልወጣ ነው:: ስለዚህ ከልዩ ፀሐፊዬ ቀጠሮ ይዘህ ነገ ልታነጋግረኝ ትችላለህ:: ለመሆኑ በየትኛው መምሪያ ውስጥ ነው የምትሰራው?” ስትል ጠየቀችው::

ቻፕማን ቶሎ መለኛ መሆን ነበረበት:: እለበለዚያ ወዲያውኑ ዘበኞች እስጠርታ ከቢሮዋ እንደምታባርረው ያውቃል:: ስለዚህ በጣም አስቃቂ የሆነ አቀራረብ መረጠ:: “የመጣሁት ስለ ሚጋንና አሌክሳንድራ ላነጋግርሽ ነበረ” አለና በጭካኔ የወረወራቸው ቃላት ያሳደሩባትን ስሜት ሰማወቅ በዓይኑ ተከተላት:: በሰላ ጩቤ በጥልቀት የተወጋ ሰው፣ ወይንም በጥይት የተመታ ሰው ወዲያውኑ ደም እንደማይፈሰው ሁሉ ሂላሪም ለመጀመሪያ ጊዜ ምንም ለውጥ አልታየባትም ነበረ:: “እህቶችሽ ሊያዩሽ ይፈልጋሉ” ሲል ቻፕማን አከለበት::

“ለመሆኑ አንተ ማነህ?” አለችና አሁን በግልጽ በሚታየው በሚንቀጠቀጠው እጇ ስልኩን ለማንሳት ሞከረች:: ግን ቻፕማን ፈጠን ብሎ መነጋገሪያውን እንዳታነሳው ወደ ታች ተጭኖ ያዘባት::

“እባክሽን... አምስት ደቂቃ ብቻ ስጭኝ:: ታሪኩ ረጅም እንደሆነና በጣም እንደሚያሳዝንሽ ባውቅም በተቻለ መጠን እሳጥረዋለሁ::”

ያንጊዜም ሰውየው ከአሁን በፊት ስልክ ደውሎላት የነበረው እንደሆነ አስታወሰችና ንዴቷ ብልጭ ብሎ “ላያቸው አልፈልግም” ስትል ጮኸችበት::

“እነርሱ ግን ሊያዩሽ ይፈልጋሉ:: ሁሰቱም እህቶችሽ! አሌክሳንድራ ከፈረንሳይ ድረስ ነው ተጉዛ የምትመጣው... ሚጋን ደግሞ ከኪንታኪ...” የእህቶቿን ስም በጠራ ቁጥር የሰውነቷን መሸማቀቅ ... በዓይኖቿ ላይ የሚያንዣብበውን ጥልቅ ሐዘን አጤነ:: የእርሱም ሆድ ተንቦጫቦጨ::

“ያ ውሻ ሽማግሌ! እርሱ ነው የላከህ! አይደለም? ግን ለምን?” አለች በአረንጓዴ አይኖቿ ትኩር ብላ እያየችው::





“መሞቻው በመቃረቡ ነው::”

“ደስታውን አልችለውም::”

“ምናልባት ባደረሰባችሁ በደል ተፀፅቶ ይሆናል:: ስለዚህም ሶስታችሁንም በዚህ ሳምንት መጨረሻ ላይ ኮኒክቴክት ግዛት ውስጥ ባለው መኖሪያ ቤቱ ሊያገናኛችሁ ሐሳብ አለው :: ሶስታችሁን ለማግኘት ወራት ፈጅቶበታል...”

“እህያ በለው!” ስትል አቋረጠችውና፤ “ዳግመኛ ሊያታልለኝ አይችልም:: ከሃያ ዓመታት በፊት እህቶቼን የት እንዳደረሳቸው ጠይቄው ምንም የሚያውቀው ነገር እንደሌለ ነግሮኛል:: ይህ እንግዲህ የሚያ ሳየው ስለ አንዳችንም ደህንነት አለማሰቡን ነው:: ታዲያ ዛሬ እንዴት ተደርጐ እኛን ለማግኘት ይችላል? ምናልባት አንተ ትሆን አፈላልገህ ያገኘ ኸን?” ብላ ጠየቀችው:: ቻፕማን ራሱን ጐንበስ በማድረግ ብቻ መለሰላት:: እርሷንም ሆነ እህቶቿን ለማግኘት በመቻሉ ልትጠላው ወይም ልትወደው ትችላለች:: ግን ያለፈና የተረሳ ነገር ቀስቅሶ ስሜቷን እንደጎዳው ይታወ ቀዋል:: ፓተርሰንን ለመጨረሻ ጊዜ ካነጋገረችው በኋላ፤ እህቶቼን አገኛ ቸዋለሁ የሚለው ተስፋዋ ዕለት ከዕለት እየመነመነ ሄዷል:: ላለፉት አስር ዓመታትም ትዝታቸው ጨርሶ ከህሊናዋ ተፍቆ ነበረ:: ሂላሪ የራሴ ብላ የምታፈቅረው አንድም ሰው የላትም:: ራሷን በስራ በመጥመዷ ነበረ እነኛ ን አስከፊ የብቸኝነት ዓመታት ልታሳልፋቸው የቻለችው:: አንድ ዓላማ ብቻ ነበራት:: የዚያ የዜና አገልግሎት ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ መሆን! ከዚያም ማዕረግ ደርሳለች:: “ማን እንደሆንክ ባላውቅም፤ ለዚያ ለላከህ ሰው እጅግ ዘግይተህል ስትል ንገረው!” አለች የፓተርሰንን ስም መጥራቱ እየቀፈፋት::

“እኔ እንኳን ቻፕማን ጆን ቻፕማን ነው የምባለው::”

“ጥሩ ሚስተር ቻፕማን፣ በሃያ ዓመት ዘግይተሃል በለው! ... የለም ሰላሳ አድርገው እንጂ!” አለች ምሬቷ ሳይቀንስ:: ቻፕማን ሂላሪን ልብ ብሎ አያት:: በአንዳንድ መንገድ ለዕድሜዋ ወጣት ትመስላለች:: በሌላ በኩል ደግሞ ካለ ዕድሜዋ ሐሳብ የበዛባት ትመስል ነበረ:: በተለይም ከዓይኖቿ ውስጥ የሚነበበው የሐዘን ጥልቀት በዘመን ሊቆጠር የሚችል አልነበረም::

“ለእህቶችሽስ ምን ብዬ ልንገራቸው?” አላት ቻፕማን አስተያየቱን ሳይቀይር::

"ለእነርሱማ... ለእነርሱማ..." አለች ትንፋሿ ቁርጥ ቁርጥ እያለና ዓይኖቿን የቆየ ትዝታ እንደሚያሰላስል ሰው በቻፕማን ጭንቅላት ላይ አሻግራ ማዶ ማዶውን እያየች:: "ለእነርሱማ... እወዳቸው እንደነበረ... ከነፍሴ አስበልጬ እፈቅራቸው እንደነበረ... ንገራቸው:: አሁን ግን እንጃ... ጊዜው ረዘመ" አለችና አቀርቅራ ራሷን ደጋግማ አወዛወዘች:: ቻፕማን ለሂላሪ ቀረብ የሚለውን ወንበር ስቦ ተቀመጠ:: በእነኚህ ሁሉ ዓመታት ውስጥ በልቧ ታምቆ በቆየው ጥላቻ ምትክ፣ ቅንጣት ታህል ፍቅርን እንዴት ሊዘራባት እንደሚችል ተጨንቆ ተጠቦ አሰበ::

"አልረዘመም ሂላሪ... እስታውሺ ... ለእነኛ ህፃናት በእናትና በአባት ምትክ ያለሻቸው እለኝታ አንቺ ብቻ ነበርሽ" ሂላሪ ለእህቶቿ ስለነበራት ፍቅር ፓተርሰን በመደጋገም ለቻፕማን አንስቶበታል:: ቻፕማንም የእነኛን ህፃናት እህትማማቾች ሁኔታ በሐሳቡ እየታየው ዓይኑ እንባ አቁሮ ነበረ:: "ስለዚህ ሂላሪ እንደምንም ብለሽ እባክሽ ልታያቸው ፈቃደኛ ብትሆኚ?"

ቻፕማንን አሁንም በመገረም ትኩር ብላ አየችው:: ስለ እርሷና ስለ እህቶቿ ታሪክ ከማወቁም ያስደነቃት እንዴት ሊያገኛት እንደቻለ ነበረ:: "እየው ሚስተር ቻፕማን! እህቶቼ በአሁኑ ጊዜ ትላልቅ ሴቶች ናቸው:: ስለዚህ እኔ አላስፈልጋቸውም ማለት ነው::" አለችና ትንሽ ቆየት ብላ "በነገራችን ላይ! ለመሆኑ ስራ ይዘዋል ወይንስ ባል አግብተው ከቤት ነው የሚውሉት?" ስትል ጠየቀችው:: የሂላሪ ግምት ግፋ ቢል የቢሮ ፀሐፊነት ስራ ቢያገኙ ነው የሚል እንደነበረ ቻፕማን ተሰማውና ፈገግ አለ::

"አንዷ ከፈረንሳይ ነገስታት ዘር ተወላጅ ተጋብታ የተከበረች እመቤት ሆናለች:: ሁለት ልጆችም ወልዳለች:: ሌላዋ ደግሞ በሕክምና የዶክትሬት ዲግሪ አላት:: የሚያኮሩ እንጂ የሚያሳፍሩ እህቶች አይደሉም:: እንደምትወጂያቸውም እርግጠኛ ነኝ ..."

"የትኛዋ ናት ዶክተር የሆነችው?" ከእነኛ ሁለት ህፃናት መካከል አንዷ ለዚህ ማዕረግ ትበቃለች ብሎ መገመቱ አዳጋች ሆነባት::

"ሚጋን ናት:: ግሩም ልጅ ወጥቷታል:: አሌክሳንድራም ብትሆን በእመቤትነቷ ሳትኩራራ፣ በጣም ሩህሩህ የደስ ደስ ያላት ሴት ናት::"

"በህፃንነቷም ጊዜ እንደዚሁ ነበረች" ስትል ድምጿን ዝቅ በማድረግ ተናገረችና፤ ሳይታሰብ ፊቷን በሁለት እጆቿ ሸፍና አቀረቀረች:: ራሷንም





እያወዛወዘች "እነኛን ከሲኦል የከፋ አስር የመከራ ዓመታት ለመግፋት የቻልኩት እህቶቼን እገኛቸዋለሁ በማለው ተስፋ በመፅናናቴ ነበረ:: ከእክስቴም አስር ሺህ ብር የሰረቅሁት ወደ ኒውዮርክ መጥቼ እህቶቼን አሳድግበታለሁ ብዬ በማቀዴ ነበረ" አለችና እጆቿን ከፊቷ ላይ ሳታነሳ ለረጅም ጊዜ ከት ከት ብላ ሳቀች:: ቻፕማን ግን የሚያየው በጣቶቿ መሐል እየተንከባለሉ ከጠረጴዛው ላይ የሚንጠባጠቡትን የዕንባ ዘለላዎች ነበረ:: የሚተናነቃትን ሲቃ እንደ ምንም እየዋጠች፤ "ግን... ግን ያ ሰው... ያ አረመኔ ሰው የት እንደደረሱ አላውቅም አለኝ... እኔም አፈላልጌ አፈላልጌ አጣኋቸው" አለችና ማንባት ባላቋረጡት ዓይኖቿ ቻፕማንን ያለ ሀፍረት አየችው:: "ታዲያ ሚስተር ቻፕማን!... እኛን ዛሬ ማግኘቱ ምን ይጠቅማል? ያለፈ ትዝታ እያስታወስን ራሳችንን እንድናሰቃይ ነው?" አለችው በምሬት እነጋገር::

"ትዝታ ላልሽው ሂላሪ! ስላለፈው ልታስታውሺ የምትችይው አንቺ ብቻ ነሽ:: ሌሎቹ ስለ ወላጆቻቸው የሚያውቁት ነገር የለም:: እርግጥ አሌክሳንድራ አንቺን አልረሳችሽም:: ሚጋን ግን ገና የዓመት ልጅ በመሆኗ ምንም ልታውቅ አትችልም:: በተጨማሪም አንዴ የሆነ ነገር ስለሆነ ስለወላጆቻችሁ እያነሳችሁ የምትሳቀቁበት ምክንያት አይኖርም:: ያለፈው አልፏል፤ አሁን ያላችሁት ሶስታችሁ ብቻ ናችሁ... ስለዚህ እህቶችሽን ብትገናኛቸው::"

"ያ ውሻ ሽማግሌ! ለወላጆቻችን ሞት ምክንያት ከሆነና እንደገናም እኛን ሕፃናቱን ካለያየ በኋላ፤ አሁን ወደ መቃብር መውረጃው ሲቃረብ ጥፋቱን ለማካካስ በቤቱ መሞከሩ ይሆናል! እኔ ግን የህሊና እረፍት አግኝቶ እንዲሞት አልፈልግም! እኛን ሰላም እንደነሳን እርሱም ሰላምን እያገኛትም! ከእህቶቼ ጋር አሁን ብንገናኝም ምንም ጥቅም አይኖረውም:: ይሄ ሁሉ ድሮ ቀረ:: እንደሞቱት ወላጆቼ ሁሉ ረስቻቸዋለሁ::"

"እርግጥ ወላጆችሽ ከሞቱ ስለማይመለሱ ረስተሻቸው ሊሆን ይችላል ... እህቶችሽ ግን በሕይወት እንዳሉ ናቸው:: አነጋግሬአቸዋለሁም:: አንቺን ለማየት በጣም ነው የጓጉት:: ሂላሪ! እንደምንም ብለሽ አንቺም ልታያቸው ሞክሪ:: ወይ ትወጃቸው፣ እንደ ድሮሽም ታፈቅሪያቸው ይሆናል::"

እርሷ ግን በተቃርኖ እራሷን በሀይል አወዛውዛ ከመቀመጫዋ ተነሳችና፤ "አላደርገውም! ያውም ፓተርሰን ቤት እግሬ ሊገባ? ምን ያህል እንደምጠላው ብትነግረው! መጥላት ቢሉህ መጥላት አይምሰልህ ... በቃላት ሊገለፅ የሚችል አይደለም!"

"ግን ለምን? እህትማማቾቹን አብራችሁ እንዳትኖሩ ማድረጉን አውቃለሁ:: ለዚህም በቂ ምክንያት ነበረው:: ሌላ የተለየ በደል ፈፅሞብሽ ይሆን?" ሲል ቻፕማን ጠየቃት:: ይህን ጥያቄ ያቀረበላት ሆን ብሎ ነበረ:: ፓተርሰን ላይ የያዘችው ሌላ ቂም ለመኖሩ ከሁኔታዋ ያስታውቃል::

"ሁሉንም ዘክዝኮ መናገሩ ምን ጠቀሜታ ይኖረዋል? እርሱ ግን በእኛ ቤተሰብ ላይ የፈፀመውን ወንጀል ያውቀዋል:: የሰራውን ግፍ ባስታወሰ ቁጥር ሰላም አያገኝም:: እኔ የምፈልገው ሰላምን ሳያገኝ ወደ መቃብሩ እንዲወርድ ነው:: ስለዚህ የኔ አሁን እህቶቼን ማየት አለማየት እርሱን ከማስደሰት ባሻገር ሌላ ጠቀሜታ አይኖረውም:: እራሳቸውን ችለዋል:: እኔም ራሴን ችያለሁ::"

"ለቁሳቁሳዊ ፍላጐትሽ ማሟያ ምንም የሚቸግርሽ ነገር እንደሌለ ግልፅ ነው:: ግን ሂላሪ፣ ብቸኝነት ምን ማለት እንደሆነ ስለማውቀው የሚሰማኝን ብነግርሽ ፀጥታ በሰፈነበት ምሽት ከማን ጋር ሐሳብሽን ትካፈያለሽ? ማንስ እጅሽን እያሻሸ የሚያፅናናሽ አይዞሽ የሚልሽ ይኖራል? እኔ እንኳን ከሚስቴ ብለያይ ወላጆችና ሁለት ወንድሞች አሉኝ ..."

"ውጣልኝ! ውጣልኝ!" ስትል ሳትጨርሰው ጮኻበት በንዴት ወደ በራፏ ሄዳ በመክፈት እስኪወጣ ቆማ ጠበቀችው:: ክብሩን ካልጠበቀ ተገፍትሮ መውጣትም ሊከተል ይችላል:: ያም ሆኖ ቻፕማን አንድ የመጨረሻ ሙከራ አደረገ:: ከኪሱ ቁራጭ ወረቀት አውጥቶ ከጠረጴዛዋ ላይ አኖረ:: በወረቀቱም ላይ እህትማማቾቹ መስከረም አንድ ቀን የሚገናኙበትን የፓተርሰን የኮኔክቲከት ግዛት ቤት አድራሻና የስልክ ቁጥር ፅፎበት ነበረ::

ከበራፉ ደርሶ ከመውጣቱ በፊት በሐዘኔታ ተመለከታትና፣ "የምክርና የሶላንጅ ልጅ ሂላሪ... የአሌክሳንድራና የሚጋን እህት ሂላሪ ... በልጅነትሽ ስላሳለፍሽው ኑሮ አንድ በአንድ ለማወቅ በመቻሌ አንጀቴ ተላውሶልሻል፣ ልቤም አልቅሶልሻል:: ቻልርስተን ታወን ድረስ ሄጄ ከነ ኢሊንና ጆንስ ጋር በሕፃንነትሽ የኖርሽበትን ቤት አይቼዋለሁ:: ከሁለቱ ሰካራሞች ጋር በዚያ በጨቅላ ዕድሜሽ ያሳለፍሽው ስቃይ ይሰማኛል:: ጃክሰንቪልም ድረስ ሄጃለሁ:: እዚያም የኖራችሁበት መኖሪያ ቤት ከቻርልስተን ታውን የማይሻል እንደነበረ አይቻለሁ:: ጆንስ ምን እንዳደረገሽ... በመጠለያ ቤት ውስጥ ምን እንደደረሰብሽ... በጠባይ ማረሚያ ውስጥ ስላሳለፍሻቸው ዓመታት... ስለ ሁሉም ነገር አንድ በአንድ





ደርሼበታለሁ:: ይህን ሁሉ አውቃለሁ" እያለ ሲያናግራት እንባው በዓይኑ ግጥም ብሎ ነበረ:: "እና ሂላሪ... እባክሽን ስለ እግዚአብሔር ብለሽ... በዚያ ዕለት እንዳትቀሪ... እኔም በቦታው እገኛለሁ... የሚያስፈልገውን እገዛ ሁሉ አደርግልሻለሁ ..."

ቀና ብላ በመገረም ታየው ነበረ:: ስለርሷ ያለፈ ታሪክ ለማወቅ በመቻሉ እጅግ አድርጐ ደንቋታል:: "አደራሽን እንዳትቀሪ..." አለና እንደ ሚግባቡት ሰው ክንዷን ያዝ በማድረግ ተሰናብቷት ወጣ:: ከኋላ ኋላውም ስታየው, ቆይታ በሩን ከውስጥ ከቆለፈች በኋላ ወደ ጠረጴዛዋ ተመለሰች:: አንገቷን ዘንበል እንዳደረገችም በሐሳብ ጭልጥ ብላ ሄደች:: ብዙ ያለፉ ትዕይንቶች በዓይነ ሕሊናዋ ተራ በተራ እየታዩዋት ተጠቅልለው ነጐዱ:: በመጨረሻም ላይ ሳይታወቃት ፊቷን በእጆቿ ሸፍና ከወንበሩ ላይ ወረድረድ ብላ ተንበርክካ ነበረ:: ልክ ከሰላሳ ዓመታት በፊት ፓተርሰን እህቶቿን ቀምቶ በወሰደበት ዕለት ከመኪናው መንገድ ዳር ተንበርክካ እንደምታለቅሰው የአስር ዓመቷ ሂላሪ ነበረ የዛሬውም ለቅሶዋ:: አራሷ ሚጋንና አሌክሳንድራም ከመኪናው ውስጥ ሆነው ይጮሁ ነበረ:: ጨካኙ... አረመኔው ... ፓተርሰን ... ለወላጆቿ ሞት ምክንያት የሆነው ፓተርሰን ግን ግማሽ አካሎቿ የሆኑት እህቶቿን ነጥቋት በረረ... ለዓይን ጠፉ... የእህቶቿም ደብዛ እንደዚሁ ...

ሂላሪ እንኳንስ ከዚያ ሰው ቤት እግሯ ሊደርስ ... የዚያን ሰው ዓይን ልታይ ... ያንን ሰው ልታነጋግረው ቀርቶ ... ከነፀፀቱ ቢቻል አስር አስር ጊዜ ቢሞት ፈቃዷ ነበረ:: ስለዚህ ቻፕማን በከንቱ ለፋ!!!

## ምዕራፍ ፳ሃያ ሰባት

"ጨክነሽ መሄድሽ ነው ማለት ነው?" አለ ሄነሪ ከመኝታ ቤቱ በር ላይ ቆሞ አሻግሮ እየተመለከታት:: ያን ቀን ሄነሪ ያደረው ከሳሎን ውስጥ ሶፋ ሳይ ነው:: እንዳኮረፋት ለማሳየት መሆኑ ግልፅ ነበረ::

"አዎን" አለችው አሌክሳንድራ ያለ አንዳች ማወላወል:: ልጆቿም እንደርሷ ለባብሰው ለጉዞው ተዘጋጅተው ነበረ:: የተለያዩ ሻንጣዎች ቀደም ሲል ከመኪና ላይ ጭነዋል:: ከማርጋሬት ጋር ፓሪስ አውሮፕላን ማረፊያው እንዲገናኙ ነበረ ቀጠሮአቸው:: ከዚያም ቀጥታ ወደኒውዮርክ ይበራሉ::

"ብትቀሪ እንደሚሻል ለመጨረሻ ጊዜ እመክርሻለሁ::"

"አልቀርም" ስትል ራሷን አወዛወዘችና፤ "እንዳልከው ባለማድረጌ በጣም ነው የማዝነው" ብላ ከእቅፉ ገብታ ልትሰናበተው ስትጠጋው ወደ ኋላው አፈገፈገባት:: ወሽመጧም ቁርጥ ነበር ያለው::

"እንድትቀርቢኝ አልፈልግም! ሆኖም መልካም ጉዞ እመኝልሻለሁ" የመጨረሻዎቹ ቃላት የምፀት ጭምርም ነበሩ::

"የምቆየው ግፋ ቢል እስከ መስከረም አስር ቀን ብቻ ነው:: የማርፈውም በፒየር ሆቴል ስለሆነ ስልክ ልትደውልልኝ ትችላለህ:: እኔም ደውዬ አነጋግርሀለሁ::"

"የሚያስፈልግ አይመስለኝም:: ብትደውይም ስራ ስለሚበዛብኝ አታገኚኝም" አላትና ወደ ኋላው ዞር ብሎ ከቤት በመውጣት ጀርባውን ሰጥቷት ከበረንዳው ላይ ቆመ:: አሌክሳንድራም ወደሚጠብቃት መኪና ለመሄድ ደረጃውን መውረድ ስትጀምር ለመጨረሻ ጊዜ የታያት ያው የሄነሪ ጀርባ ነበረ:: መኪናው ተንቀሳቅሶ ከግቢው በመውጣት ላይ እንዳለ ግን፤ የሄነሪ ዓይኖች ከፊቱ በተንጣለለው ባህር ላይ ተሰክተው በእንባ ይዋኙ ነበረ:: ሆኖም ይህን አሌክሳንድራ አላየችውም:: ለይምስል ይኮሳተርባት እንጂ ሄነሪ ከልቡ ነበረ የሚያፈቅራት:: አሁን ግን ለዘለዓለም





እንዳጣት ያህል ሆዱን ባር ባር አለው:: ለብዙ ዓመታት ተሳስበው እንዳልኖሩ፣ የጠየቃትን ሁሉ በደስታ እንዳልፈፀመችለት ሁሉ በጥቂት ቀናት ውስጥ ያ የሞቀ ትዳር፣ ያ የፍቅር ቤት፣ የንትርክ ቤት ሆነ... አሌክሳንድራ የኮምት ደ.ቦርን ልጅ አልነበረችም... ሌላው ቀርቶ ማርጋሬት እንኳንስ እናቷ ልትሆን ቀርቶ የስጋ ዝምድናም አልነበራቸውም... አሌክሳንድራ ከተለየቻቸው ሰላሳ ዓመት የሆነውን... የረሳቻቸውን እህቶቿን ለማየት ከሄነሪ ትዕዛዝ ውጪ ለመጀመሪያ ጊዜ በራሷ ወሰነች... ያ በነ አክሴልና ማሪ ሳቅና ጨዋታ፣ በአሌክሳንድራ ውበትና ደግነት ሕይወት የነበረው ቤት ከበረዶ ቀዘቀዘ... በአሌክሳንድራና በሄነሪ ትዳር ላይ ጥቁር ጥላ አንዣበበበት::

በአውሮፕላን ውስጥ የተያዘላቸው መቀመጫ አንደኛ ማዕረግ ነበረ:: በዚያ ክፍል ውስጥ ሌላ ተሳፋሪ ባለመኖሩ አሌክሳንድራና ማርጋሬት እንደልብ ለመወያየት ችለው ነበረ:: ስለ ሄነሪም ሁኔታ አንስተው ብዙ ተነጋገሩ:: በመጨረሻም ላይ አሌክሳንድራ፤ "ቁርጥ አድርጐ ባይነግረኝም የሁለታችን ነገር አክትሟል:: ስመለስ መግቢያ ቤት እንደማላገኝና የፍርድ ቤት መጥሪያ እንደሚጠብቀኝ እርግጠኛ ነኝ" አለቻት ለእናቷ::

"ለምን እኔ እንዳስቸገርኩሽና ወደ ኒውዮርክም አብረሺኝ እንድትሄጂ እንዳደረግሁ አስመስለሽ ኣትነግሪውም ነበረ?" አለች ማርጋሬት::

"ሞክሬ ነበረ:: ግን የምሄደው ለሌላ ጉዳይ እንደሆነ ሊነቃብኝ ቻለ:: ውጥር አድርጎ ስለያዘኝም እውነቱን አፍረጥርጬ ነገርኩት" አሌክሳንድራ ከዚህ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ብዙ ነገሮችን አመዛዝና ነው:: በዚሁ ሳቢያ ከባሏ ልትለያይ ትችላለች:: ያም ሆኖ ትክክለኛውን ምርጫ ማድረጓ ይሰማታል:: ከህሊና ፀፀት አሁን ነፃ ናት::

"ትልቅ ስህተት ነው የፈፀምሽው" አለቻት እናቷ አፍ አውጥታ ለአሌክሳንድራ ባትነግራትም ከእንግዲህ ትዳራቸው ስለመፍረሱ እርግጠኛ ነበረች:: ልጆቹንም ይቀማታል የሚል ስጋት አድሮባታል:: ሁለቱም ቢሆኑ በዚህ አርእስት ላይ ቀጥለው ለመወያየት አልፈለጉም:: ማርጋሬት ከህፃናቱ ጋር መጫወቱን ስትመርጥ አሌክሳንድራ ግን ወደ ሐሳቡ ዓለም አመራች:: ስለወላጆቿ ... ስለ እህቶቿ ... ብዙ ነገሮች በአእምሮዋ አመላለሰች ... ሂሲን ... ሚጋንን ... ለሰላሳ ዓመታት የተለዩዋትን እህቶቿን ልታያቸው ነው ... የወደፊቱ እየታሰባት ከውስጥ የተሰማት ደስታ ፊቷን እንደ አበባ አፈካው::

ኒውዮርክ በደረሱ በማግስቱ ከዝነኛው ቪርግዶርፍ የውበት ሳሎን ሄዳ ፀጉሯን በፎቶግራፍ ላይ እንዳየችው እንደ እናቷ ሶላንጅ ከሁለት ከፍላ ተሰራችው:: ያም ወርቃማ ፀጉሯ ይበልጥ ፀዳል ተላብሶ ከትከሻዋ ላይ ዘንፈል አለ:: በውጤቱም በጣም ነበር የተደሰተችው::

ገና እግሯ ከያዙት መኝታ ክፍል ከመድረሱ ትንሿ አክሲል በእናቷ ያልተለመደ ፀጉር አበጣጠር በፈንጠዝያ እየሳቀችና እጇን እያጨበጨበች፣ "እማይ! ዛሬ ልክ እኔን ነው የምትመስይው" አለች:: ማርጋሬትም ብትሆን በአሌክሳንድራ ልዩ ውበት ከመደሰቷም የጥንቱን ትዝታ ቀስቅሶባት ሳብ አድርጋ እንደ ህፃን ልጅ ከደረቷ አስጠጋቻትና "አክሲ እወድሻለሁ" አለቻት:: አሌክሳንድራም በተመሳሳዩ ነበር ለእናቷ ያላትን ፍቅር የገለፀችው::

ምሳ ከበሉ በኋላ፤ በልዩ ልዩ ሱቆች እየተዘዋወሩ አንዳንድ የመታሰቢያ ዕቃዎችና ለህፃናቱም አሻንጉሊቶች ሲገዙ ቆዩ:: አስር ሰዓት ከመድረሱም በፊት ወደ ሆቴላቸው ተመለሱ:: አሌክሳንድራም ለኮኔክቲከቱ ጉዞዋ መዘገጃጀት ጀመረች:: ለመንገድ የሚያስፈልጋት አንድ ሻንጣ ብቻ ነበር:: ቀጠሮ የያዘችው አስር ሰዓት እንደ ሞላም እናቷንና ልጆቿን ተራ በተራ ከሳመች በኋላ ማታ ላይ ስልክ እንደምትደውልላቸው ቃል ገባች:: ከዚያም ወደ ኮኔክቲከት ሊወስዳት ከሆቴሉ ፊት ለፊት ይጠብቃት ከነበረው የፓተርሰን ካዲላክ መኪና ውስጥ ገባች:: ያን ጊዜ ብቻ ነው አሌክሳንድራ ፍርሐት ፍርሃት ያላት:: ሰላሳ ዓመት ያህል ጊዜ ወደ ኋላ ተጉዞ ከእህቶቿ ጋር መገናኘት ቀላል ነገር አልነበረም:: በተጨማሪም የዛሬው ግንኙነታቸው በወደፊት ሕይወታቸው ላይ ለውጥ ማስከተሉም አይቀርም::





# ምዕራፍ ሃያ ስምንት

በኮኔክቲከት ግዛት ከባህር ዳርቻ ይገኝ ከነበረው የፓተርሰን ቤት ለመድረስ ከሁለት ሰዓት በላይ ይፈጅ ነበረ:: አሌክሳንድራ ከአውቶሞቢሉ የኋላ መቀመጫ ላይ እንደልቧ ተዝናንታ ብትቀመጥም በሌላ በኩል ከሐሳብ ባህር ውስጥ ተዘፍቃለች:: ዓይኖቿን በመስታወቱ ውስጥ አስርጋ ውጪ ውጪውን እያየች በቅድሚያ ስለ እናቷ ስለ ማርጋሬት ታሰላስል ጀመረ:: አንድም የእናትነት ርህራሄ ሳይጉድልባት አሳድጋ ለወግ ለማዕረግ አብቅታታለች:: ለሰላሳ ዓመታት ሙሉ ገደብ የለሽ ፍቅሯን እንዳሳየቻት ነበረ:: ለማርጋሬትም ቢሆን ያለቻት አለኝታ እርሷ ብቻ ነበረች:: ማርጋሬት ግን አሁን ፈርታለች:: አሌክሳንድራ እህቶቿን ካገኘች ትቀየርብኝ ይሆናል ስትል ሰግታለች:: የሚብሰው ደግሞ የሄነሪ ጉዳይ ነበረ:: ወደኒውዮርክ እንዳትሄድ ባለ በሌለ መንገድ ሊያስፈራራት ሞክሮ አልተሳካለትም:: ለመጀመሪያ ጊዜ ከባሏ ፈቃድ ውጪ የፈፀመችው ነገር ቢኖር ይህን ብቻ ነው:: ማን ያውቃል? ከእንግዲህ አሌክሳንድራ ዲቦርን መሆኗ ቀርቶ አሌክሳንድራ ምከር ትባል ይሆናል::

ከሚስተር ፓተርሰን ግቢ ዋና በር ሲደርሱ በአካባቢው ዘበኛ አልነበረም:: በኤሌክትሮኒክ የሚሰራው ትልቁ የብረት በር ድምፅ ሳያሰማ ተከፈተ:: ራቅ ባለ መጠነኛ ኮረብታ ላይ ወደተሰራው ቤት ለመድረስ ግራና ቀኙን በተለያዩ ዛፎች ያጌጠ ረጅም ጠመዝማዛ መንገድ ማለፍ ያስፈልጋል:: ባለ አንድ ፎቁ ቤት ያለፈው ክፍለ ዘመን ቢሆንም ስፋቱ፣ የዓምዶቹ እስተናነፅና የበሮቹና የመስኮቶቹ ቅርፅ ዓይን የሚማርክ ነበረ:: በስፋት ከተንጣለለው የፎቁ ባልኮኒም ላይ ውዳውድ የሆኑ መቀመጫዎች ዙሪያውን ተደርድረውበታል:: አሌክሳንድራ ከአውቶሞቢሉ ወርዳ ምድረ ግቢውን ማድነቅ ከመጀመሯ ነበር "እንኳን ደህና መጣሽ" የሚል አንድ የማትረሳው ድምፅ የሰማችው::

ቻፐማን ፊቱን ደስታ እየወረረውና ከልብ የሆነ ፈገግታ እያሳያት ከቀረበ በኋላ አሌክሳንድራን እቅፍ አደረጋትና “ጉዞውስ እንዴት ነበረ... አደከመሽ?” ሲል ጠየቃት፡፡

“የምን ድካም? በጣም ደስ የሚል ጊዜ ነው ያሳለፍኩት” አለችው የርሷም ፊት በአፀፋው ፈገግታ እየተሳበሰ፡፡ ቀጠል አድርጋም “ግቢውና ሕንፃው እንዴት ያምራል?” አለች፡፡

“እንዳልሺውም በጣም ግሩም ነው፡፡ በተለይም ውስጡ እጅግ ውብ በመሆኑም ሚስተር ፓተርሰን ብዙ ገንዘብ አፍስሰውበታል የሚል ነው ግምቴ፡፡ ወደ ውስጥ እንግባና አስጎበኝሻለሁ” ቻፐማን የአሌክሳንድራን ፀጉር አሰራር ያየው ከኋላ ኋላዋ ሆኖ በተከተላት ጊዜ ነበረ፡፡ የተሰማውንም ባለመደበቅ “መዳፈር አይምሰልብኝና ከፓሪስም ይበልጥ ዛሬ እጅግ ውብ ሆነሻል” አላት፡፡

አሌክሳንድራ በሙገሳው አልተከፋችም ነበረ፡፡ ዘወር ብላ ፈገግ አለችለትና “እህቶቼ በቀላሉ እንዲለዩኝ ስል በተቻለ መጠን እናታችንን ለመምሰል ሙከራ አድርጌአለሁ” ብላው ወደዋናው ቁም ነገር በማምራት “የተቀሩትስ መጥተዋል?” ስትል ጠየቀችው፡፡

ቻፐማን ምን ብሎ እንደሚመልስላት ግራ ተጋባ፡፡ ግንባሩን ቋጠር አድርጎ ጥቂት አሰበና “እስከአሁን አልደረሱም፡፡ ሚጋን እንኳን ብትዘገይ እንጂ አትቀርም፡፡ ሂላሪ ግን እንጃ” አለ ድምፁን እንደ መርዶ ተናጋሪ ጎትቶ፡፡

ብርግግ እንደ ማለት ብላ “እንዴት እንጃ? አልመጣም አለችህ?” ስትል ጠየቀችው፡፡

“ቁርጥ አድርጋ አልመጣም አላለችኝም፡፡ እርግጥ ሚስተር ፓተርሰንን ለማየት እንደማትፈልግ አክራ ነው የተናገረችው፡፡ ዋናው ችግር ከዚህ ላይ ነው” አላት ነገር እያለሳለሰ፡፡

አሌክሳንድራ በሐዘን አንገቷን ሰበር አድርጋ ሂላሪን ለማየት ትበቃ ዘንድ በሆዷ ፀለየች፡፡ በሂላሪ ላይ የደረሰባትን በደል ሁሉ አሌክሳንድራ ታስታውሳለች፡፡ እንደ ሁለቱ እህትማማቾቿም ዕድለኛ አለመሆኗ ግልፅ ነው፡፡ ይህም ሆኖ ሂላሪ መቅረት አይኖርባትም ስትል አሌክሳንድራ ተመኘች፡፡ የተረሳችው ሂላሪ ብቻ ሳትሆን እርሷና ትንሿ ሚጋንም ጭምር ሶስቱም ነበሩ፡፡ አስተዳደጋቸው ከሆነ ደግሞ ያ ሌላ





ነገር ነበረ፡፡ የአምስት ዓመቷስ አሌክሳንድራ ከሂላሪ አልለይም ብላ አላለቀሰችም ነበርን? ስለሆነም ለእህቶቿ ባላት በዚያ በዱሮ ፍቅር ተጉትታ ነው አሌክሳንድራ ትዳሯንና ንብረቷን ጥላ የመጣችው፡፡ ታዲያ ሂላሪ ልትቀር? 'እባክህ አታስጨክናት! ሆዷን እራራው' ስትል በሆዷ ለአምላኳ ምልጃ አቀረበችና ወደ ቤቱ ውስጥ ገቡ፡፡

የፊት ለፊቱ አዳራሽ እጅግ ውድና ጥንታዊ በሆኑ መቀመጫዎችና በሚያማምሩ ጠረጴዛዎች ዳር እስከዳር ተገጥግጧል፡፡ የምንጣፉ ዓይነት፣ የእሳት መሞቂያው ምድጃ አሰራር ሁሉ ዓይንን የሚስብ ነው፡፡ ከበስተጉኑ ያለው ክፍል የሚስተር ፓተርሰን የጥናት ክፍል በመሆኑ እንደ አሌክሳንድራ ግምት ከዚያ የሚያገኙት መስሏት ነበረ፡፡ ሆኖም አለመኖሩን እንዳየች “እርሳቸውስ ወዴት ሄዱ?” ስትል ቻፐማንን ጠየቀችው፡፡ እጅግ ቢዘገይም እህትማማቾቹን መልሶ ለማገናኘ ት ስላደረገው ጥረት ሚስተር ፓተርሰንን ልታመሰግነው ፈልጋ ነበረ፡፡

“ፎቁ ላይ በሚገኘው መኝታ ቤታቸው ዕረፍት በማድረግ ላይ ናቸው” አላት ቻፐማን፡፡ ሚስተር ፓተርሰንን የሚረዱ ሁለት ቋሚ አስታማሚዎች ተቀጥረው ነበረ፡፡ እንደ እውነቱ ለዚህን ያህል ጊዜ በሕይወት መቆየቱ የተአምር ነው ለማለት ይቻላል፡፡ የዛሬውን ዕለት ለመጠበቅ ሲል ነፍሱን ታግሎ ያቆያት እንጂ እንደ አያያዙስ ከሆነ ገና ዱሮ አፈር ትቢያ በሆነ ነበረ፡፡

“አሁኑኑ ልታያቸው ትፈልጊያለሽ?” አላት ቻፐማን፡፡

“አዎን” አለችና ቀና ስትል ዓይን ለዓይን ተጋጩ፡፡ ፈገገላት... ፈገገችለት፡፡ የቻፐማን አለባበስ በመካከለኛው ዕድሜ እንዳለ ሰው ተጠንቅቆ ሳይሆን ካኪ ሱሪና ከደረቱ የተከፈተ ሰማያዊ ሸሚዝ ነበረ የለበሰው፡፡ ገፅታው ለምሁርነቱ ምስክር ቢሆንም መልኩና ሁኔታው ግን የጉረምሳ ነበረ የሚመስለው፡፡ አሌክሳንድራ ከፊት ለፊቷ የቆመውን የደስ ደስ ያለውን ቻፐማንንና ኮስታራውን ባሏን ሄነሪን በሐሳቧ አወዳደረቻቸው፡፡ የሄነሪ ፊት አለመፈታት... ትእዛዛዊ አነጋገሩ... በኩራት የተጠነነው አረማመዱ... አመለካከቱ... ሁለንተናው ወዲያውኑ ነበረ በሰው ላይ የዝቅተኝነት ስሜት የሚያሳድረው፡፡ ቻፐማን ግን በተቃራኒው ፍልቅልቅና ቦርቧራ የልብ ልብ የሚሰጥ ዓይነት ሰው ነበረ፡፡

ወደ ደረጃው ሲቃረቡ ሲሉ ከበስተላይ የኮቴ ድምፅ ስለሰሙ ቆም አሉ:: ወዲያውኑም ሚስተር ፓተርሰን በሁለቱ አስታማሚዎቹ ተደግፎ ደረጃውን መውረድ ሲጀምር አዩ:: እግሮቹን የሚያነሳው በግድ ነበረ:: የእርጅናው፣ የክሳቱ፣ የትከሻው መጉበጥ የዘጠና ዓመት ሽማግሌ አስመስሎታል:: ቁልቁል መልከት ሲል ዓይኖቹ በአሌክሳንድራ ላይ በማረፋቸው እንደ መደናገጥ ብሎ ባለበት ለጥቂት ጊዜ ፍዝዝ ብሎ ቆመ:: እንባውም ቆረር እያለ በጉንጮቹ ላይ ወረደ:: አሌክሳንድራ ደረጃዎቹን ፈጠን ብላ ወጣችና ግማሽ መንገድ ላይ ተገናኘችው::

የተለመደም ነውና "ደህና ነዎት ሚስተር ፓተርሰን?" ስትል ሰላምታ ለጠችው:: ፓተርሰን መልስ ሲሰጣት እንደተሳነው ስታይ ጉንበስ ብላ ጉንጩን ሳመችውና "እህቶቼን እንዳገኛቸው ስላደረጉልኝ ውለታ አመሰግንዎታለሁ" አለችው:: የፓተርሰን ሰውነት ከበፊቱም ይልቅ አሁን በኃይል ተንቀጠቀጠ:: ለመናገር ቢፈልግም አንድም ቃል ከአፉ አልወጣልህ አለው:: በድካም የዛለትን እጆቹን ግን ከአሌክሳንድራ እጆች ላይ አደረገና ባለ በሌለ አቅሙ ጭምቅ አድርጐ ይዟቸው ለጥቂት ጊዜ ቆየ:: የተቀሩትን ደረጃዎች የወረደው ከአንድ ወገን አሌክሳንድራ ደግፋው ነበረ:: ጕንና ጐኑን ደግፎ የሚይዝለት ምቹ ወንበር መርጠው ፓተርሰንን ደጋግፈው አስቀመጡት::

ትንፋሹም መለስ ሲልለት በሻከረና ጐርናና ድምፅ፤ "የአምላክ ያለህ! ከቶ ለማመን አልችልም! ቁርጥ እርሷን አይደለም እንዴ የምትመስለው? ለመሆኑ አንቺ አሌክሳንድራ ነሽ ወይንስ ሚጋን?" ሲል ጥያቄ አቀረበላት:: ሂላሪን አሁንም ቢሆን አልረሳትም:: እርሷም ትሆናለች ሲል ከጥርጣሬ ያልገባው የሂላሪ ፀጉር እንደ አባቷ ፀጉር ጥቁር መሆኑን ያውቅ ስለነበረ ነው::

"አሌክሳንድራ ነኝ ጌታዬ" ስትል መለሰችለት:: በሆዷም ማንን ነው ትመስያለሽ የሚሉኝ? ስትል አስባ ልትጠይቀው ከጅሏት ነበረ::

ፓተርሰን ግን ቀጠል አድርጎ "መልክና ቁመናሽ ብቻ አይደለም፣ የድምፅሽ ቅላፄ ቁርጥ እናትሽን ነው" አለና በመገረም ራሱን ለጥቂት ጊዜ አወዛወዘ:: አሌክሳንድራ ሶላንጅን ብትረሳም እርሷን በመምሰሏ ውስጥ ውስጡን ደስታ ተሰምቷታል::

"ከወላጆቼ ጋር በጣም ትቀራረቡ ነበረ?" ይህንን ጥያቄ ያቀረበችለት ሆን ብላ ነበረ:: ሌሎቹ እህቶቿ እስከሚመጡ ድረስ





ፓተርሰንን ማነጋገር ዘዴ ብላው ነው እንጂ ከወላጆቿ ጋር ስለነበረው ግንኙነት ሳታውቀው ቀርታ አልነበረም::

ፓተርሰን ራሱን ዘንበል አደረገና በአሌክሳንድራ ጥያቄ ላይ ጥቂት ጊዜ አሰበበት:: ከዚያም "መቀራረብ ነው ያልሺኝ አሌክሳንድራ? ሁለቱንም እንዴት እወዳቸው እንደነበረ ለመግለፅ ቃላት ያጥሩኛል:: አባትሽን የማየው ልክ እንደታናሽ ወንድሜ ነበረ:: በዚህም ሳቢያ ሶላንጅ በጣም ትወደኝና ታቀርበኝ ነበረ:: እንደ ታላቅ ወንድሟም በመቁጠር ችግሯን ሁሉ የምታካፍለው ለእኔ ነበረ:: እንዴት ያለች ቆንጆ ልጅ ነበረች ይመስልሻል! ለውበቷ ተወዳዳሪ የማይገኝላት... ክብሯን ጠባቂ ... ርህሩህና ቸር... ምን ልበልሽ? ግሩም የሆነች ልጅ ነበረች..." አለና ፊቱን የመነመነ ፈገግታ አላብሶ አባቷና ሶላንጅ እንዴት ለመገናኘት እንደበቁ ታሪኩን ከሥር አንስቶ ያወጋት ጀመረ:: "አባትሽ መሸነፍ የሚባል ነገር አያውቅም:: ታዲያ ሶላንጅ ብታስፈራራው፣ ብትስድበው ተስፋ ቆርጦ ሊመለስ መሰለሽ? ቀኑን ሙሉ ከመኖሪያ ቤቷ በር ተለጥፎ ዋለ:: ማምሻውንም እንደዚሁ:: መቼም የእርሱም መልክና ቁመና የሰጠ ነበረና መጨረሻ ላይ ልትሸነፍለት በቃች..."

ከፓተርሰን ፊት ላይ ፈገግታው ከመቅፅበት ተገፈፈ:: አንድ ሌላ ትዝታ መጥቶበት እንደነበረ ግልፅ ነው:: እንዳቀረቀረም "አባትሽ ጀግና ወታደር ነበረ:: ራሱን ለአደጋ በማጋለጥ እኔን ብቻ ከሁለት ጊዜ በላይ ከሞት አድኖኛል:: የጀርመንን ጦር በሰሜን አፍሪካ በረሃ ድል ከመታነው በኋላ ወደ ሲስሊና ከዚያም በኔፕልስ በኩል ወደ ዋናው የጣሊያን ግዛት ገባን..." ፓተርሰን ረጅሙን ታሪክ ቀጠለ... ከኔፕልስ ወደ ሮም ወሰዳት... መለስና ወደ ፓሪስ በዝርዝር ሊያጫውታት... ስለነበርሊን መያዝና የጦርነቱ ማብቃት ስለርሱም ወደ አሜሪካ መመለስ ... ስለ ሶላንጅ ወደ አሜሪካ መምጣት... ስለ ምከር ዝነኛ ተዋናይ መሆን... "ባይገርምሽ አባትሽ በአንድ ወቅት በመላ አገሪቱ ውስጥ ተወዳዳሪ የማይገኝለት ተዋናይ ለመሆን በቅቶ ነበረ:: ዝናው በመላው ዓለም ተሰራጨ:: ሀብቱም እንደዛው ተትረፈረፈ:: የሙት ወቃሽ አትበይኝና በዚያን ወቅት ነበረ እንደ ዕብደት ጐነጥ ሊያደርገው የጀመረ ..."

ያን ጊዜ የመኪና ድምፅ ከውጪ ተሰማ:: እስከ አሁን ድረስ ፊንጠር ብሎ ተቀምጦ የሁለቱን ጭውውት በጥሞና ያዳምጥ የነበረው ቻፕማን እየተቻኮለ ወጣ:: ፓተርሰንና አሌክሳንድራም ጆሯቸውን

ወደ በራፉ አቅንተው የሚሆነውን በመጠባበቅ ላይ ናቸው:: በራፉም ተከፍቶ እንደገባች ቆም እንደማለት አለች:: ዙሪያውን አየት በማድረግ ላይ እንዳለችም ከአሌክሳንድራ ጋር ዓይን ለዓይን ተጋጩ:: ፍዝዝ ብላም ቀረች::

አሌክሳንድራ ከመቀመጫዋ እጆቿን ዘርግታ ተነሳች:: ያቺም ፍፁም የርሷን ግልባጭ የምትመስለው ልጅ ሮጣ ከእቅፏ ገባች:: አሌክሳንድራም ከደረቷ ልጥፍ አድርጋት «ሚጋን... ሚጋን... ትንሿ እራሷ ሚጋን...» አለች እንባዋ በመዝረብረብ እየወረደ:: የሁለቱን ሴቶች መልክና ቁመና ለመለየት ያዳግታል:: ወርቃማ ፀጉራቸው ትላልቅ አረንጓዴ ዓይናቸው፣ ዝርጋዳና ውብ ቅርፃቸው እህትማማችም መንትዮች ያሰኛቸዋል::

እንደ ተቃቀፉም ብዙ ቆዩ:: ከዚያም አሌክሳንድራ ሚጋንን ቀና አደረገችና አየቻት:: እርሷም ታለቅስ ነበረ:: የሚጋን ለቅሶ ግን የደስታ እንጂ ከነአካቴው እህቶች እንዳሏት አታውቅም:: አሁን ግን ከፊት ለፊቷ የቆመችውን ሴት እያየች «ቁርጥ እኔን አይደለም እንዴ የምትመስይው!» አለቻት ታላቅ እህቷን::

አሌክሳንድራ በእንባዋ ውስጥ ፈገግ አለችና እንደገና ስባ በደረቷ አቅፋት «ቁርጥ አንቺን እንዳልመስል በአንድ ነገር እንለያያለን:: በአለባበስ!» አለችና እነ ቻፕማንን ጭምር አሳቀቻቸው:: አሌክሳንድራ እውነቷን ነበረ:: የእርሷ አለባበስና ጌጣጌጦች እንደ አውሮፓውያን መሳፍንት ሚስቶች ሁሉ እጅግ ያማረና በጥንቃቄ የተመረጠ ነበረ:: ሚጋን ግን የምታዘወትረውን ጂንስ ሱሪና እጅጌ ጉርድ ሸሚዝ ብቻ ነበረ የለበሰችው:: የተጫማችውም እንደ አዘቦቱ ከጉልበቷ የሚደርስ ረጅም ቦት ጫማ ነበረ:: ከእህቷ ደረት ላይ ቀና አለችና «እንዳንቺ ያለች ቆንጆ ሴት አይቼ አላውቅም» አለች እየሳቀች:: ሌሎቹም ተሳሳቁ:: ከዚያም አሌክሳንድራ አንድ እጇን ይዛ ሚስተር ፓተርሰን ወደ ተቀመጠበት ወንበር ልታስተዋውቃቸው ወሰደቻት::

«ደህና ነዎት ሚስተር ፓተርሰን?» ስትል ሚጋን ዓይኖቿን ሰበር አድርጋ በትሕትና ሰላምታ ሰጠችው:: ፓተርሰን በሚጋን አቋምና ሁኔታ ኩራት ተሰምቶት ነበረ:: እንደ እናቷ እንደ ሶላንጅ ቆንጆ ናት:: በሴት ወይዘሮነቱ በኩል የአሌክሳንድራን ያህል ባትታደልም በመልካም አያያዝ ለማደግ ከፊቷ ላይ በግልፅ ይነበባል:: ደርበብ ያለና ብልህ አመለካከቷ ስለ ጨዋነቷ አፍ አውጥቶ የመመስከር ያህል ነበረ::





«ባልሳሳት አንቺ ዶክተሯ መሆን አለብሽ!» አላት ፓተርሰን::

«አዎን እኔ ነኝ:: ግን የማገለግለው በትልቅ ከተማ በሚገኝ ዘመናዊ ሆስፒታል ሳይሆን በአንድ የገጠር መንደር ውስጥ ባለ አነስተኛ የሕክምና ጣቢያ ውስጥ ነው» አለችው በትህትና ራሷን ዝቅ ለማድረግ በመሻት::

«ይገባኛል» አለና ፓተርሰን ፈገግ እንደማለት ብሎ እህትማማቾቹን ተራ በተራ አያቸው:: ሁለቱም የመጨነቅ ስሜት አይታይባቸውም:: የጥላቻም አስተያየት አይነበብባቸውም:: ፓተርሰን ለሁለቱም የመረጠላቸው የጉዲፈቻ አባቶች በእንክብካቤ ሊያሳድጓቸው የሚችሉ ሰዎች መሆናቸውን ካረጋገጠ በኋላ ነበረ:: ምስኪኗን ሂላሪ ግን የሚያስጠጋት ጠፋ:: ቻፕማን ከቢሮዋ ድረስ ሄዶ እንዳነጋገራትና ምን እንደመለሰችለት ለፓተርሰን አጫውቶት ነበረ:: ምናልባት ብትመጣም ፓተርሰንን በነገር ግርፊያ እንደምትሸነቁጠው አያጠራጥርም:: ፓተርሰንም ይህንን ፈርቷል:: ግን ከምትቀር ብትመጣና ብትሰድበው ይመርጣል:: ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ሊያያት ይቅርታም ሊጠይቃት ምኞቱ ነው::

እስከ ምሽቱ ሁለት ሰዓት ድረስ ጠበቋት:: ግን ሂላሪ አልመጣችም:: 'ጨክና መቅረቷ ነው' ሲሉ ሁሉም ውስጥ ውስጡን መታመስ ከጀመሩ ቆይተዋል:: ላይ ላዩን ግን ለማስመሰል ያህል አንዳንድ ነገሮችን እያነሱ መጫወታቸው አልቀረም:: ፓተርሰን ስለ አለፈው የወላጆቻቸው ታሪክ የሚያስታውሰውን ያህል ሊያወጋቸው ሞከሯል:: ሚጋንና አሌክሳንድራ ስለ ግል ሕይወታቸው አልፎ አልፎ መነጋገራቸው አልቀረም:: አሌክሳንድራ የሁለቱን ልጆቿን፣ የሄነሪን፣ እናቴ የምትላትን የማርጋሬትንና በበጋ በክረምት እየቀያየረች የምትኖርባቸው ሕንፃ ቤቶች ፎቶግራፎች አምጥታ ስለነበረ ተራ በተራ አሳየቻቸው:: ሚጋንም በፊናዋ ያሳደጓትን የሬቤካንና የዴቪድን፣ የምትሰራበትን የኬንታኪውን ሆስፒታል ፎቶግራፍ በመያዟ ከአሌክሳንድራ ፎቶግራፎች ጎን ደረደረቻቸው:: የሁለቱን ሁኔታ ላጤነው ለሰላሳ ዓመት እንዳልተለያዩ ያህል አሁን በጥቂት ሰዓታት ውስጥ በማስካካት ውስጠ ሚስጥራቸውን ለመገላለፅ ዕቅድ እንዳላቸው ነበረ የሚመስለው:: የሚጋንን አትኩሮት በተለይ የሳበው የሄነሪ ፎቶግራፍ ነበረ:: ከዶሮኙ መኖሪያ ቤታቸው ሕንፃ ፊት ለፊት ለተነሳው ፎቶግራፍ በእርግጥ የነገስታት ዘር ለመሆኑ ይመስክራል:: ከሕንፃው

ውብትና ግዝፈት ሌላ የሄነሩ ግርማ ሞገስ ልዩና የሚያርድ ነበረ:: ከእንደዚህ ካለ ሰው ጋር እህቷ መጋባቷና እነኛን የመሳሰሉ ልጆች መውለዷ ሚጋንን እጅግ አድርጎ ነው ያስደነቃት::

"እስቲ የአንቺንና የእኔን ሕይወት አወዳድሪው? በጣም የተለያየ ነው:: አስተዳደግሽ በፈረንሳይና እንደ መሳፍንት ልጅ፣ የተጋባሽው ከነገስታት ዘር ያም ሆኖ የአንድ እናት የአንድ አባት ልጆች ነን:: በመልክ እንመሳሰላለን:: እንደ አየሁትም ከሆነ ባሕሪያችንም አንድ ዓይነት ነው:: እስቲ ማንስ ነው አሁን እኛን በተለያየ ቤተሰብ ውስጥ አድገዋል ብሎ የሚጠረጥረው?" አለች ሚጋን:: አባባሏ ትክክል ነበረ:: ለአሌክሳንድራም ሌላ ትዝታ ቀሰቀሰባት:: ምስኪኗ ሂላሪም የእነርሱ እህት ነበረች:: ግን አስተዳደጓ እንዴት የከፋ ነበረ? ሂላሪ እስከ አሁን ድረስ አልመጣችም:: ሰዓቱም እየገፋ በሄደ መጠን የአሌክሳንድራም ትካዜ ጨመረ:: ድንገትም የማንኮ ራፋት ድምፅ በመስማቷ ወደ ፓተርሰን አየት አደረገች:: በተቀመጠበት እንቅልፍ አሸልቦት ነበረ:: አሌክሳንድራ ወደሚቀጥለው ክፍል ገብታ በሩን ከውስጥ ቆለፈች:: ከምንጣፉም ላይ ተንበርክካ ወደ አምላኳ ፀለየች:: እንባዋን እያፈሰሰች 'እባክህ የእህቴን ልብ አራራውና እንድትመጣ አድርግልኝ' ስትል ደጋግማ ተማፀነች:: ከእንብርክኳ ተነስታ ማልቀሷ እንዳይታወቅባት ዓይኖቿን ከጠራረገች በኋላ በራፉን በመክፈት ላይ እንዳለች የመኪና ድምፅ ተሰማ:: ቻፕማንም እየከነፈ ወጣ:: አሌክሳንድራ ከቆመችበት መንቀሳቀስ ተስኗት ዓይኖቿን ብቻ በዋናው በር ላይ ተክላ ቆየች:: ከበስተ ውጪ በኩል አንዳንድ ኃይለ ቃላት ሲወረወሩ ከተሰማ በኋላ በራፉ በኃይል ተከፈተ:: ካሸለበው እንቅልፍ ፓተርሰን የነቃው በዚያን ጊዜ ነበረ::

አመጣጧ ቀጥታ ከቢሮዋ ለመሆኑ በተጨማደደው ለማያዊ ሊኖ ቀሚሷ ለመናገር ይቻላል:: ከአረንጓዴ ዓይኖቿ በስተቀር በቁመናና በመልኳ ወደ አባቷ ወሰድ የሚያደርጋት ሂላሪ ከበራፉ እንደቆመች በቅድሚያ የታያት ፓተርሰን ነበረ:: ያም የቀድሞ ጥላቻዋ ታድሶባት በነገር ልትገርፈው ስትል ዓይኖቿ ከጐኑ ከተቀመጠችው ባለወርቃማ ፀጉር ወጣት ሴት ላይ አረፉ:: ከርሷም ላይ ዓይኖቿን ነቅላ ሌላኛይቱን ለመፈለግ ዙሪያውን ማተረች:: ከበስተጐን ካለ ክፍል በር ላይ ቆማ ከነበረችው ሴት ጋር እንደተያዩ ባለችበት ፈዛ ቀረች:: አሌክሳንድራ ግን ነፍስ የዘራችው በዚያን ጊዜ ነበረ::





አሁን በምትታያት ረጅምና ሙሉ ሴት ምትክ ለአሌክሳንድራ በዓይነ ሕሊናዋ ትመላለስ የነበረችው የዱሮዋ ሂላሪ ያቺ ከአጠገቧ የማትለያት እንደ እናት የምትንለፈለፍላት ፀጉረ ጥቁር ልጅ ነበረች:: አሌክሳንድራም የለቅሶ ሳግ ጉሮሮዋን እየተናነቃት ልትቆጣጠረው ያልቻለችው እንባዋ የዓይኗን ግድብ ጥሶ በጉንጮቿ ላይ እየወረደ "ሂ... ሂሲ... ሂሲ..." በማለት ላይ እንዳለች ሂላሪም ሳይታወቃት ከእህቷ አንገት ላይ ተጠምጥማ "አክሲ... አክሲ ... የእኔ ትንሿ አክሲ ..." ስትል እንባዋን ለቀቀችው:: ፓተርሰን እህቶቿን በጉልበት ነጥቆ ካለያያት ወዲህ ዛሬ ለመጀመሪያ ጊዜ ስታቅፋት ነው:: የዚያን ጊዜዋ አሌክሳንድራ... ያቺ ፎልፏላና ስትስቅ ፣ ስትናገር እናቷን ሶላንጅን የምትመስለው አሌክሳንድራ... "እወድሻለሁ አክሲ እወድሻለሁ ..." የሚሉትን ቃላት ብቻ እየደጋገመች ሁለቱም እንደተቃቀፉ ለረጅም ጊዜ ተላቀሱ:: ከዚያች ዓይኖቿ በአሌክሳንድራ ትከሻ ላይ አልፈው በሚጋን ላይ ተንገዋለሉ:: ሚጋንም እንደ እህቶቿ አስታውሳ የምታለቅስበት ያለፈ ትዝታ ባይኖራትም ሁኔታቸው አንጀቷን ስላላወለው እርሷም አብራቸው ማንባቱን ተያይዛው ነበረ:: ሂላሪ አንዱን እጇን ከአሌክሳንድራ ላይ እንስታ ወደ ሚጋን ዘረጋች:: ሚጋንም ከመቀመጫዋ ተነስታ ከእህቶቿ ጋር ተቃቀፈች:: "... ሚጊ ... ለመጨረሻ ጊዜ ካየሁሽ እምብዛም አልተቀየርሺብኝም" ስትል ሂላሪ ሶስቱም እህትማማቾች ማልቀሳቸውን ትተው ተሳሳቁ::

እህቶቿን በግራና በቀኝ እጇ ይዛ ወደ ፓተርሰን ቀረብ አለችና "አንተን ላለማየት ስል ብቻ ላልመጣ ወስኜ ነበረ:: ይገባሃል አይደል?" አለችው ሂላሪ ድምጿን ከፍ አድርጋ:: ፓተርሰን ቀና ብሎ ሊያያት አልደፈረም:: እንዳጐነበሰ ራሱን ዝቅ ብድግ በማድረግ ብቻ የገባው ለመሆኑ አሳየ:: "እንዴት እንደምጠላህ ታውቀው የለም?" አለችው አሁንም ደገመችና::

"ለምን ሂሲ? ለምን? እኛ ደግሞ በአንቺ መምጣት ምን ያህል እንደተደሰትን አታይም:: እስካገኘሽ ድረስ በጣም ጓጉቼ ነበረ:: ሚጋንም እንደዚሁ" አለች አሌክሳንድራ ወደ ትንሿ እህቷ በፈገግታ እያየች::

"ቆይ አንድ ጥያቄ ብቻ ልጠይቀው ፍቀዱልኝ" ብላ ሂላሪ የእህቶቿን እጆች ጭብጥ እንዳደረገች በጣም ተጠጋችው:: ጐንበስ ብላም "ምን ስላደረግንህ ነው ያን ያህል በደል የፈፀምክብን? ደግሞስ ያለፈው አንሶ ከተረሳሳን ከስንት ዓመታት በኋላ ልታገናኘን የፈለግከው

ለምንድን ነው? የረሳነውን የወላጆቻችንን ትዝታ እያስታወስን እንድንሰቃይ ነው?» አለችው ሂላሪ በዚያው በመራራ አነጋገሯ፡፡

ፓተርሰን ጉሮሮው ውስጥ ተሰርንቀው በልውጣ አልወጣም የሚታገሉትን ቃላት አንድ ባንድ በምጥ ተናገራቸው፡፡ «ጥፋቴን አውቀ ዋለሁ... ምልናልባትም እህትማማቾቹን በማለያየት ለፈፀምኩት በደል... ይህ የዛሬው መገናኘታችሁ ማካካሻ ቢሆንልኝ በሚል ግምት ነው ...»

«እና በአንድ የራት ግብዣ ላይ እንገናኘንና በእኛ ቤተሰብ ላይ የዋልከው በደል ይፋቅልሃል ማለት ነው? ሰላሳ ዓመት አለያይተኸን የቆየኸው ለአንተ ቀላል ነገር መስሎህ ይሆን?»

«በእኔ ላይ የመረረ ጥላቻ እንዳለሽ አውቃለሁ ሂላሪ! ምክንያቱም ይገባኛል፡፡ እህቶችሽ ግን እንዳንቺ አይጠሉኝም፡፡»

«እኔ የማውቀውን ስለማያውቁ አይጠሉህም ይሆናል፡፡ ለእኔ ደግሞ የፈፀምክብን በደል እንዲህ በቀላሉ የሚዘነጋኝ አይሆንም» አለችው ከአረንጓዴ ዓይኖቿ የጥላቻ ጨረር እየተወረወረና እየተጠጋችው፡፡ በቤቱ ውስጥ የሚሰማው ንግግር በሁለቱ መካከል የሚካሄደው ጭቅጭቅ ብቻ ነበረ፡፡

አሌክሳንድራ ጣልቃ በመግባት ነገሩን ለማለዘብ ሞከረች፡፡ «እባክሽ ሂሊ.... ያለፈው አልፏል፡፡ ከእንግዲህም ማስታወሱ ምን ጠቀሜታ ይኖረዋል?»

«ለምን አይኖረውም አክሲ!» አለች እህቷን ዞር ብላ በትኩረት እየተመለከተቻት፡፡ «አንቺ በዚያን ጊዜ ሕፃን በመሆንሽ የምታውቂው ነገር አይኖርም፡፡ ከእኔ ከተለየሽ በኋላ ያደግሽው በምቾት ነው፡፡ ግን እኔ ያኔ ፍዳዬን በማየት ላይ ነበርኩ፡፡ አንድ ጊዜ በመጠለያ ቤት፣ በሌላ ወቅት በጠባይ ማረሚያ ውስጥ ስሰቃይ እንደነበረ ታውቂያለሽ? በአስራ ሶስት ዓመት ዕድሜዬ ክብረ ንፅሕናዬን እንዳጣሁ ስነግርሽ ምን ይመስልሻል? ያም ሆኖ ቀንም ሆነ ሌሊት እናንተን አገኛለሁ በሚል ተስፋ ስፅናና ቆየሁ፡፡ አገኛችኋለሁ ስል የሰረቅሁትን አስር ሺህ ብር ይዤ ወደ ኒውዮርክ መጣሁ፡፡ እርሱ ግን አድራሻችሁን እንኳን እንደማያውቀው ነገረኝ፡፡ ከእቅፌ መንጭቆ የወሰዳችሁ ሰው... እኔን ለዚያ ሁሉ ስቃይና መከራ የዳረገኝ ያ ሰው...» አለችና ሂላሪ እህቶቿን ተራ በተራ እያየች «ዕለት ዕለት እንዳስታወስኳችሁ ነበረ ... እንደማላገኛ





ችሁም ካወቅሁ በኋላ ተስፋ በመቁረጤ እንዳለቀስኩላችሁ ነበረ፡፡ እሺ! ይህን ሁሉ ልርሳው ልበል! ግን ያ እኛን ልጆቹን እንደ ዓይን ብሌኑ ያየን የነበረውን አባቴን... ያቺ እንደነፍሷ ትወደን የነበረችውንስ እናቴን እንዴት ልርሳቸው? ሌላ ሌላው ቢረሳ የወላጆቼ ነገር ሊረሳኝ ይችላል?» አለች በግራና በቀኝ ጉንጮቿ እንባዋ ያለማቋረጥ እየፈሰሰ፡፡

«ወላጆቻችንን ሚስተር ፓተርሰን አልገደሏቸው» አለች አሌክሳንድራ ሚጋንን ጭምር በመወከል፡፡ «እርግጥ እኛ አብረን እንዳናድግ አድርገው ይሆናል፡፡ በኋላም አድራሻችንን አለማወቃቸው ደግሞ ያን ያህል የከበደ ጥፋት አይደለም፡፡ ማን ያውቃል? ከቁጥጥራቸው ውጪ የሆነ ችግር ገጥሟቸውስ እንደሆነ?» ብላ ሽማግሌውን ፓተርሰንን በፍቅር አመለካከት እይታው ወደ ሚጋን ዞር ስትል እርሷም በእህቷ ንግግር ለመስማማቷ ራሷን ቀና ጉንበስ በማድረግ አሳየች፡፡ የሂላሪ ጥላቻ ያን ያህል የሚከርበት ምክንያት ለሁለቱም አልገባ አላቸው፡፡ ማለያየት አለያይቷቸዋል፡፡ ግን እስከ መጨረሻ ድረስ ረስቶ አልረሳቸውም፡፡

«እናንተ የምታውቁት ምንም ነገር ባለመኖሩ ነው ... ያን ጊዜ ሕፃናት ነበራችሁ ... እኔ ግን እማማ በሞተችበት ምሽት ከሳሎኑ በር አጠገብ ቆሜ ነበረ... አባባ በገደላት ምሽት... ከበሩ-ፉም ተለጥፌ የሆነውን ሁሉ አይቻለሁ... ምን እንደተባባሉም ሰምቻለሁ» እያለች ሂላሪ ተንሰቅስቃ ማልቀሷን ቀጠለች፡፡ የሰውነቷን በሲቃ መናጥ ያየው ቻፕማን የምትወድቅ መስሎት ሊያቅፋት ከጃጅሎት ነበረ፡፡ ሂላሪ ግን እጆቿን ከጆሮዎቻ ላይ አድርጋና አቀርቅራ «እማማ ስትጮህ... እርሱ እየደጋገመ ሲመታት አንድ ባንድ አይቻለሁ... ደግሞ ደጋግሞ ከደበደባት በኋላ በመጨረሻ ላይ ጉሮሮዋን አንቆ ገደላት» አለችና ወደ ፓተርሰን አንድ እርምጃ ቀረብ ብላ ከላይ እታች ስታየው ቆየች፡፡

«ለምን አባቴ እናቴን እንደገደላት ታውቃለህ ሚስተር ፓተርሰን?» ስትልም አምባረቀችበት፡፡ «ከአንተ ጋር ትወሳልት ስለነበረ ነው... ታባልጋትም እንደነበረ ለአባቴ ፊት ለፊት ነበረ የነገረችው» አለችና የዛን ምሽት ድርጊት ለዓይን ሕሊናዋ ወለል ብሎ የታያት ይመስል ፍዝዝ ብላ ቆይታ «አንተ እንዳታለልከኝ እኔም ተጫውቼብሃለሁ አለችው ... አባቴ ግን ውሸት ነው ካንቺ ሌላ ሴት አላውቅም አላት... እርሷም በቅርቡ አብራው ካሊፎርኒያ እስከ ስነበተችው ሴት ማንነት ጭምር ያፈራረቃቸውን ወዳጆቹን ስም ዘርዝር

ቆጥራ ስታበቃ እንደነርሱ እርሷም ወዳጅ ያላት መሆኑን ገለፀችለት... ከዚያም ሰው ጋር ፍቅር የያዛት መሆኑንና ሕጋዊ ፍቺ ጠይቃ ልታገባው መወሰኗን ነገረችው... ልጆቼንም በሙሉ እወስዳቸዋለሁ አለችው... እንደዚያ ብታደርጊ እገልሻለሁ ሲል ዛተባት... ስለ ዛተባትም አልፈራችውም... ይባስ ብላ እንዳበደ ሰው አስካክታ ሳቀችና የዚያን ፍቅረኛዬ ያለችውን ሰው ስም ነገረችው" አለችና ሂላሪ ሕቅ ብላ ዘለግ ላለ ጊዜ ካለቀሰች በኋላ በዚያው ብግን ያለ አነጋገሯ "የሰውየውን ስም ለአባቴ እንደነገረችው ታውቅ የለ ሚስተር ፓተርሰን? ነግራው የለም?" ስትል ተንጨረጨረች:: ከዚያም እንባ በተሞሉ ዓይኖቿ እህቶቿን ተራ በተራ አየችና ከርሷ አእምሮ ያልፋቀውን እህቶቿ ግን የማያውቁትን ታሪክ ነገረቻቸው:: "እናታችን የአባታችን የቅርብ ጓደኛ ከነበረው ከሚስተር ፓተርሰን ጋር ነበረ ፍቅር የያዛት... አባታችን እገልሻለሁ ብሎ ቢያስፈራራትም እርሷ ግን ግንቡ እስቲናጋ ሳቀችበት... በፓሪስ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ከተያዩበት ቀን ጀምሮ ፍቅሯ ለፓተርሰን እንጂ ለአባታችን እንዳልነበረ ነገረችው... በመሆኑም ወደ አሜሪካ መጥታ አባታችንን ካገባችበት ወቅት ጀምሮ ከፓተርሰን ጋር በድብቅ ትገናኝ እንደነበረ ገለፀችለት... በመጨረሻም ላይ ሚጋንን የወለደችው ከፓተርሰን አብራክ ስለሆነ ቢያንስ እርሷን ለመውሰድ የሚያዳግት ኃይል እንደማይኖር አረዳችው ... ያን ጊዜም አባታችን ዘለለና አነቃት ..."

በቤቱ ውስጥ ያልተጠበቀ ፀጥታ ሰፍኗል:: ፓተርሰን መብረቅ እንደመታው ሰው በስማው ክው ብሎ ቀርቷል:: ሂላሪ ከእንግዲህ የምትናገረው ሐሳብና ትካዜ በገባው በለሰለሰ ድምፅ ነበረ:: "ከርሱ የምንወለደው ሁለታችን ብቻ መሆናችንን በመናገሯም ገደላት፣... እኛም እንደ ዓይናቸው ብሌን ይወዱን የነበሩትን ወላጆቻችን ለማጣት በቃን... " ብላ አቅራቢያዋ ከሚገኘው ወንበር ላይ ተቀምጣ ማንባቷን ቀጠለች:: አሌክሳንድራና ሚጋንም እንገቷን አቅፈው አብረዋት አለቀሱ::

ፓተርሰን ከድካሙ የተነሳ በሻከረና በጐረነነ ድምፅ "ይህስ ውሸት ነው... ከቶም አላደረግኩትም... በአምላኬ ስም እምላለሁ... ሁላችሁም የእርሱ ልጆች ናችሁ" እያለ በግልፅ እንባውን አውጥቶ አፈሰሰ:: ከሁሉም ግን የድንጋጤ ምልክት በሚጋን ፊት ላይ ይነበብ ነበረ:: ለወላጆቿ ሞት ምክንያት ሆና መገኘቷ ቀስ በቀስ እየተሰማት





የሄደ ይመስላል:: "ነገሩ ሁሉ እንዲህ መሆኑን ባወቅኩኝ ኖሮ..." አለና ፓተርሰን የጀመረውን ተናግሮ ሳይጨርስ ማልቀሱን ቀጠለ::

"ብታውቅስ ኖሮ ምን ታደርግ ነበረ? ሚጋንን ለብቻዋ ወስደህ ታሳድጋት ነበር ማለት ነው? ለሁለታችን ግን ቅንጣት ያህል ስሜት እንደማይኖርህ የማውቀው ነው:: ከሁሉም ለወላጆቻችን ሞት ምክንያት እንደሆንክ ግልፅ ሆኖ ሳለ ለአባቴ ጥብቅና እቆምልሃለሁ ማለትህ ነው የሚያስገርመው" አለችው ሂላሪ በዛው በጥላቻ በሚተፋ አነጋገሯ::

"ሌላ ጠበቃ እንደማይፈልግ ስላስጠነቀቀኝ እንጂ እኔስ በአሜሪካ ውስጥ የታወቀ ነገረ ፈጅ ላቆምለት ነበረ:: ደግሞም ከሶላንጅ ሞት በኋላ አባታችሁ በሕይወት ለመኖር እንደማይፈልግ ተጠራጥሬም ነበረ:: ግን ባላሰብኩት ቀን..." አለና እንባውን ባለማቋረጥ ማፍሰሱን ቀጠለ::

ሂላሪ በዚያን ወቅት ነበረ ለመጀመሪያ ጊዜ ስብዕና ያለው ፍጡር መስሎ የታያት:: አርጅቷል፣ መቃብሩ የተቆፈረ ነው:: የፈፀመውን በደል ግን ማንም ቢሆን ሊሽርለት አይችልም:: በርሱ ምክንያት የሚዋደዱ ባልና ሚስት ሕይወት አልፏልና ያንን የፈሰሰ ደም ምንም ኃይል አያነፃውም:: ሂላሪ ከመቀመጫዋ ተነስታ ቁልቁል እየተመለከተችው "እመጣጤ በአንተ ላይ ያለኝን ጥላቻ ልነግርህና ልበ አስት መሆንህን ልገልፅልህ ነበረ:: ሆኖም ሳይህ ደግሞ እጅግ የምታሳዝን ምስኪን ሰው ነህ:: ግን ከልቤ እንዴት ይቅርታ እንደማደርግልህ አላውቅም:: በአንተ የተነሳ ባይሆን ኖሮ ይህን ጊዜ ምን ዓይነት ሕይወት ባሳለፍን ነበረ!" አለች::

"በቃ ያለፈ ነገር ያለፈ ነው:: እርሺው ሂላሪ! ከእንግዲህ ግን ማሰብ ያለብን ስለ ወደፊቱ ነው:: እኔ ለምሳሌ እንዳችሁንም አላስታውሳችሁም:: ወላጆቼም የሚመስሉኝ ያሳደጉኝ ሰዎች ነበሩ:: ዓመታት እንበለስ ከንቱ እንደከበለሱ መቁጠር የለብንም:: ስለዚህ ምንም እንኳን አንቺ የሥቃይ ዓመታትን ብታሳልፊም ያንን ሁሉ ችግር ተወጥተሺው ለዚህ ማዕረግ ከመብቃትሽም ትቆረቆሪልን የነበረውን እህቶችሽን ዛሬ ለማግኘት በመቻልሽ ያለፈውን እሮሮ ረስተሺው ልትደሰቺ ይገባል" ስትል ትንሿ ሚጋን ሂላሪን ልታፅናናት ሞከረች::

እሌክሳንድራም በበኩሏ ከእህቷ ቀበል በማድረግ "ሂሊ... የዛሬዋን ቀን በእንዴት ያለ ናፍቆት ስጠባበቃት ነበረ ይመስልሻል? ስለዚህ ሂሊ እባክሽ ደስ ይበልሽ" ስትል አማጠነቻት። እውነትም እሌክሳንድራ በዚያች ዕለት ከእህቶቿ ጋር መገናኘቱ እመዝኖባት የከፈለችው መሥዋዕት ቀላል አልነበረም። "ከፓሪስ ወደዚህ መምጣት ለእኔ ምን ያህል ከባድ ነገር ነበር ይመስልሻል? ባሌ ማስጠንቀቂያ ቢሰጠኝም ትዳራችን ሊፈርስ እንደሚችል ቢያስፈራራኝም ከእህቶቼ የሚበልጥ ነገር አይኖርም ስል ነው ቆርጬ የመጣሁት። እና እባክሽን ይህን ምሽት በደስታ እናሳልፈው?" ስትል እንባ ባዘሉ ዓይኖቿ ጭምር እሌክሳንድራ ተሰመማጠቻት። ሂላሪም እህቷን ከደረቷ አስጠግታ አቀፈቻትና ከትከሻዋ ላይ አሻግራ ሚስተር ፓተርሰንን ሰረጅም ጊዜ ስታየው ቆየች። 'ምናልባት ይህንን ሰው እኔ እንደ ደመኛ ባየውም ጥፋተኛ ላይሆን ይችላል። በወቅቱ ለነበረው ችግር መፍትሄ እኛን ማለያየቱ ብቻ ሆኖም አግኝቶት ይሆናል! እኔ ብሰቃይም ደግሞ በሌላ በኩል እህቶቼ መልካም አስተዳደግ አልተጓደለባቸውም...' ስትል ታሰላስል ነበረ።

በአእምሮዋ የሚመላለሰውን ሐሳብ የተረዳው ይመስል ፓተርሰን "ከእንግዲህስ ይቅርታ አታደርጊልኝም? ሶስታችሁም ይቅርታ እንድታደርጉልኝ እለምናችኋለሁ..." እለ ተራ በተራ ከተመለከታቸው በኋላ የተንጉላጁ ዓይኖቹን በሂላሪ ላይ ሰክቶ።

"ምን እንደምል አላውቅም። አሁኑኑ ይቅርታ አድርጌልሃለሁ ስማለት ያስቸግረኛል... ሰጥቂት ጊዜም ቢሆን ነገሮችን ማመዛዘን አለብኝ" አለች ሂላሪ ዓይኖቿን ሰበር አድርጋ።

"በጣም ጥሩ! ዋናው ቁም ነገር ከሶስታችሁ መገናኘት ላይ ነው። በመሆኑም እንደዛሬው ዕለት በሕይወቴ ተደስቼ አላውቅም። ከእንግዲህም ሶስታችሁን የሚለያይ ምንም ኃይል አይኖርም። ቀድሞውንም ቢሆን ቆራጥ አለመሆኔ እንጂ ከእኔ ጋር እንድትኖሩ ሚስቴን ባስገደድኳት ነበረ። መቼም ያለፈ አለፈ። እኔም ለፈፀምኩት ጥፋት በቂ ቅጣቴን የተቀበልኩ ይመስለኛል..." ፓተርሰን በረጅሙ ተነፈሰ። በጣም ተደካክሞም ስለነበረ ዓይኖቹን ከደነ። ቻፕማንና አስታማሚዋ ወደ መኝታ ቤቱ ሊወስዱት ደጋግፈው አስነሱት። ደረጃውንም ከወጣ በኋላ ዞር ብሎ ቁልቁል እየተመለከተ ቁርጥ ቁርጥ በሚል ድምፅ "ይህ ቤት ከእንግዲህ የእናንተ የእህትማማቾቹ ቤት





ይሆናል... ልጆቻችሁን፣ባሎቻችሁን ይዛችሁ መጥታችሁ መሰባሰቢያችሁ ይህ የእኔ የመጨረሻ ስጦታዬ የሆነው ቤት እንደሚሆን ተስፋ እለኝ ..." ሲል ሚጋንና እሌክሳንደራ በእንድነት "እናመሰግናለን" ሲሉ መሰሱለት። ሂላሪ ግን ከእንገቷ ጉንበስ በማለት ብቻ ምስጋናዋን በምልክት ገለፀች።

ሐኪሟ ሚጋን ለሚስተር ፓተርሰን የሚያስፈልገው የሕክምና እርዳታ ቢኖር ስመከታተል ከእህቶቿ አስፈቅዳ ተለየቻቸው። ሂላሪና እሌክሳንድራ እጅ ለእጅ ተያይዘው ወደ አሌክሳንድራ መኝታ ክፍል አመሩ። ከክፍሉም ውስጥ እንደገቡ ነበረ ሁለቱም ስመጨረሻ ጊዜ አብረው የኖሩባትን ያቺ አክስታቸው ኢሊን ከልላላቸው የነበረችውን ትንሽ መኝታ ቤት የታወሰቻቸው። ሂላሪና እሌክሳንድራ በአንድ አልጋ ላይ ተቃቅፈው ሲተኙ ትንሿ ሚጋን እንዳትወድቅ ከበስተግርግዳው በኩል ተዘርግታላት በነበረች እንካሳ የአራስ አልጋ ላይ ነበረ የምትተኛው። ኢሊንም ሕፃናቱን እንዳትመታቸው ሂላሪ ታደርገው የነበረው ጥንቃቄ ትዝ ብሏት ሌላ ሐሳብ መጣባትና "እስከ አሁን ሳልጠይቅሽ! ለመሆኑ ልጆችሽ ማንን ነው የሚመስሉት?" ስትል ከአሌክሳንድራ ጐን አልጋው ላይ ተቀመጠችና ጠየቀቻት።

እሌክሳንድራ እህቷ ባቀረበችላት ጥያቄ ፈገግ አለችና "ትልቋ ማሪ ቁርጥ አንቺን ነው የምትመስለው። እቋቋሟ ፀጉሯ... ሁሉ የአንቺ ትክክል ግልባጭ ነው። አክሴል ደግሞ በሕፃንነቴ የተነሳሁትን ፎቶግራፍ ትመስላለች። በሁለቱ መካከል የወለድኩት ወንድ ልጅ ግን በእራስነቱ ሞተብኝ" እለች በዚሁ ትዝታዋ ሰውነቷ ስቅጥጥ ብሎ። ሂላሪ ከብዙ ዓመታት በፊት ያስወረደችው ፅንስ በዚያን ወቅት ለመጀመሪያ ጊዜ ታወሳት። ከዚያን ወዲህ ከሕፃናት ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት እንዳይኖራት ትጠነቀቅ ነበረ። አሁን ግን ከምትወዳት እሌክሳንድራ የተወለዱ ሁለት የእህቷን ልጆች ልታይ ነው።

"ፈረንሳይኛ መናገሩን አልረሳሽውም?" ስትል እሌክሳንድራ ጠየቀቻት።

ሂላሪ ፈገግ አለችና "ብዙ ቢረሳኝም እንደነገሩ ከሕፃናቱ ጋር ስመግባባት ያህል የሚያቅተኝ አይመስለኝም" ስትል መለሰችላት።

“በፈረንሳይኛ መግባባት ካልቻላችሁ፣ በእንግሊዘኛም ልትነጋገሩ ትችላላችሁ:: እናቴ ለራሷ ስትል ማሪንም አክሴልንም እንግሊዘኛ አስተምራቸዋለች::”

“ልትመሰገን ይገባታል! እስቲ ስለ ባልሽ ደግሞ አጫውቺኝ” አለች ሂላሪ ለምትሰማው ሁሉ ጉጉቷ እየጨመረ::

አሌክሳንድራ እህቷን የምትደብቃት ምንም ነገር ሊኖር አይችልም:: እንዴት አድርጋ እንደምትገልፀው ቢያስጨንቃትም “በጣም አስቸጋሪ ሰው የመሆኑን ያህል በዚያው መጠን ብልህ ነው:: ከእኔ የሚጠብቃቸው ብዙ ነገሮች አሉ:: በቤታችን ውስጥ ፈላጭ ቆራጩ እርሱ ነው:: ከእርሱ ፍላጐት ውጪ ዝንፍ ብዬ ብገኝ መዓት ነው የሚያወርድብኝ” አለቻት::

“እና እንደዚህም ሆኖ አብራችሁ በሰላም ትኖራላችሁ?” ስትል ሂላሪ በመገረም ጠየቀቻት:: ይህ ለርሷ ሰምታ የማታውቀው አዲስ ነገር ነበረ::

“ስለ ለመድኩት ምንም አይመስለኝም:: ደግሞም ላይ ላዩን ፍፁም ኮስታራ ቢመስልም ልቡ የዋህ መሆኑን አውቃለሁ:: እኔንም ልጆቹንም ሲበዛ ይወደናል” አለችና ትንፋሽ እንደ ማግኘት ብላ፤ “ይወደን ነበረ ማለቱ ይመረጣል መሰለኝ? ከአሁን ወዲያ ትዳራችን ጤናማ ሆኖ መቀጠሉን እንጃ:: በተለይም ስለ ወላጆቻችን ታሪክ ሳጫውተው የደነገጠው ድንጋጤ አያድርስ ነበረ!”

“አባታችን እናታችንን መግደሉንና ሕይወቱንም በገዛ እጁ በማጥፋቱ ነው?”

“አዎን! ያ ድርጊት በእንቺ ሕይወት ላይ ያመጣውን ለውጥ ያህል በእኔም ሕይወት ላይ ይኖረዋል ብዬ እሰጋለሁ:: ሚጋን ግን ከዚህ ሁሉ ነፃ ናት” ስትል ነበር አሌክሳንድራ ትንሿ እህታቸው ወደነበሩበት ክፍል የገባችው:: ፓተርሰንን በሕመም ከመሰቃየቱም በምሽቱ የተፈራረቀበት ስሜት ተጨምሮ የሰላም እንቅልፍ ሊወስደው ባለመቻሉ የሚያደነዝዝ መርፌ ወግታው መምጣቷ ነበረ::

“ገላው በያለበት መፈነዳዳት ጀምሯል:: ስለዚህ በሕይወት ለመቆየት ብዙ ሰዓት የሚኖሩት አይመስለኝም” አለች እህቶቿ ወደ ተቀመጡበት አልጋ እየመጣች:: ሂላሪ ሚጋንን ያን ጊዜ ነበረ ልብ ብላ





ያየቻት:: በመልኳም ሆነ በቁመናዋ የአሌክሳንድራ መንትያ ነበር የምትመስለው::

“ሞት የርሱንም ደጅ በተራው ሊያንኳኳ ነው?” ስትል የፊት መታመስ እየተነበባት ተናገረች::

“አዎን! ለማንም እንደማይቀር ሁሉ!” ብላ ሚጋን መለሰችላት:: ሂላሪ ስለ ፓተርሰን የምታስታውሰውን ሁሉ ለእህቶቿ በማጫወት ላይ እንደነበረች ነው፤ ቻፕማን ሲሰናበታቸው በሩን ከፍቶ ከደፉ ላይ የቆመው:: ከእንግዲህ እህትማማቾቹ ብቻቸውን ሆነው የልባቸውን መጫዋወት አሰባቸው:: ቻፕማን ግዳጁን በሚገባ ተወጥቷል::

“ዳግመኛ እንደምንገናኝ ተስፋ አለኝ::” ስትል ቅድሚያ ምኞቷን የገለፀችው አሌክሳንድራ ናት:: ቻፕማን ግን ተስፋ እንደቆረጠ ሰው ራሱን በመደጋገም አወዛወዘ:: ከፊቱም ላይ የሚነበበው የቅሬታ ፈገግታ ነበረ::

“ለወደፊቱ እንደ እናንተ የተጠፋፋ ሰው እንዳፈላልጋችሁ እስካልጠየቃችሁኝ የምንገናኝበት ምክንያት የሚኖር አይመስለኝም:: ይህንን የመሰለ አጋጣሚ ደግሞ ተደጋግሞ የሚከሰት አይደለም” አለና ሶስቱንም ተራ በተራ ከተመለከተ በኋላ “ከእናንተ በመለየቴ የሚሰማኝ ሐዘን ከባድ ነው” ሲል ተናገረ:: በእርግጥም ባለፉት ጥቂት ወራት ቀን ከሌሊት በውኑም በእንቅልፉም የሚያስበው ስለ እነኚሁ ሶስት እህትማማቾች ነበረ:: ከፊል ሕይወቱም አድርጎ ሊቆጥራቸው በቅቷል:: በተለይም አሁን ጭንቀት የሆነበት ከሂላሪ የመለየቱ ጉዳይ ነው:: አንጀቱ ተላውሶላታል፣ መንፈሱ ቆስሎላታል በልቡም አልቅሶላታል:: ምን እንደሚያደርግላት ግራ ገብቶታል::

“ለሁላችሁም መልካም ዕድል እመኝላችኋለሁ” ብሎ በደመ ነፍሱ ከተናገረ በኋላ ሊወጣ ሲል ሚጋን ፈጠን ብላ በመራመድ ደርሳበት “በጣም ነው የማመሰግንህ ሚስተር ቻፕማን” አለችና ጉንጩን ሳም አደረገችው:: እንደታላቅ ወንድም ያህል ነበረ የወደደችው:: “እግር ጥሎህ ኬንታኪ ከመጣህ እንድትጠይቀኝ እሺ?” አለችው::

“ኬንታኪ ብዙ ጊዜ የመቆየት ዕቅድ አለሽ?” አላት ቻፕማን ከእህትማማቾቹ ጋር ሲጫወት ቢቆይ ፈቃዱ ነበረና::

"እስከነጭራሹም ከዚያ የመውጣት ምኞት የለኝም" አለችና ፈገግ አለች ::

"ቆራጥ! ሚጋን ጉበዝ!" አለና ትከሻዋን መታ መታ አድርጎ ወደ አሌክሳንድራ ሲመለከት እርሷም ሮጣ መጥታ ከእቅፉ ውስጥ ገባችና ጉንጩን ሳም አድርጋ "ላደረግክልን ውለታ ሁሉ በጣም ነው የማመሰግንህ" አለችው::

ቻፕማን አዲሱን የፀጉር አበጣጠሯን በአድናቆት እያየ "ከእንግዲህ የፈረንሳይ መሳፍንት ሚስት መሆንሽ ብቻ ሳይሆን አሜሪካዊ ሴት ወይዘሮ መሆንሽንም አስታውሺ... አዲሱ የፀጉር አሰራርሽ እንዴት ያቆነጀሽ ይመስልሻል!" አለና አሳቃት::

ሂላሪ ግን እንደ እህቶቿ ሳትቀርበው ለመሰናበት እጇን በሩቁ ዘረጋችለትና "ከቢሮዬ ድረስ መጥተህ ልታነጋግረኝ በሞከርክበት ወቅት ስላበሳጨሁህ ይቅርታ እጠይቅሃለሁ" ብላ ከንፈሯን በግድ አላቃ ፈገግ በማለት "ከእህቶቼም ጋር ለመገናኘት ስላበቃኸኝ በጣም አመሰግንሃለሁ" አለችው:: እንደ ልማዷ ዓይኖቿ እንባ እያቀረሩ:: እርሱም እጇን ጨብጦ ሳይታወቃት ስቦ ከደረቱ አስጠጋት:: ከእቅፉም ውስጥ ሳትንቀሳቀስ ለብዙ ጊዜ ቆየች:: እስከ ዘላለሙም እንደዚያ እንዳቀፋት ብትቆይ ፈቃዷ ነበረ::

"አይዞሽ ሂላሪ! በርቺ! ... ከእንግዲህ ብቸኛ አይደለሽም... የብቸኝነትሽና የሐዘንሽ ጊዜ ከእንግዲህ አብቅቷል..." ሲላት ቃላቶቹ በጆሮዋ ውስጥ እንደመረዋ ደወሉ:: ስሜት ላይጉነትለው በማህተም ታሽጉ የነበረው ልቧ ቀስ በቀስ መቅለጥ ጀመረ:: ከእቅፉም ወጥታ ዓይን ዓይኑን ስታየው ቆየች:: የሂላሪም ከንፈሮች ለመጀመሪያ ጊዜ ከትዕዛዟ ውጪ ፈገግታ አሳዩ::

"ቢሮዬ ድረስ መጥተህ ትጠይቀኝ የለም?" አለችው ሂላሪ እንደ መለማመጥም ጭምር::

"እጠይቅሻለሁ እንጂ አልፎ አልፎም አብረን ምሳ እንበላን" አላት ቻፕማን ዓይኖቹ በፈገግታ እየተሞሉ::

"በፈለግከው ሰዓት ስልክ ልትደውልልኝና ልትመጣ ትችላለህ"

"ሥራ ማስፈታት ካልሆነብኝ::"





"ግድየለም በተጨማሪም ቤቴን ላሳይህ ስለምችል ከዚያን በኋላ ቢሮም መምጣት አያስፈልግ ይሆናል" ብላም እጅ ለእጅ እንደተያያዙ ወደ በራፉ አመሩ:: ሂላሪ አለማወቋ እንጂ ቤቷን እንኳን ለቻፕማን ቀደም ሲል በውጪውም ቢሆን አይቶታል:: ከመኪናው አድርስውት በመመለስ ላይ እንዳሉ ሂላሪ ከደስታዋ ብዛት የተነሳ እንባዋ እየተናነቃት ነበረ:: በአንድ ቀን... ያውም በአንድ ምሽት በምትወዳቸው እህቶቿ ተከባለች... ሌላም የሚወዳት ሰው ስለመኖሩ እርግጠኛ ለመሆን የበቃችው ዛሬ ነው::

አሌክሳንድራ ከፍል እንደ ገቡም ሂላሪ ከመካከል ሁለቱ እህቶቿ በግራና በቀኝ ተቀምጠው ሲያወሩ አመሹ:: ለወሬው አቀንቿ ሚጋን ነበረች:: በተለይም አሌክሳንድራን የማትጠይቃት ጥያቄ አልነበረም:: ስለ ባሏ ... ስለ ቤተሰቦቹ... ስለ ፓሪስ... ስለ ሪቬዬራ... ስለ መኖሪያ ቤቶቻቸው አበዛዝ ... ስለ አሽከሮቻቸው ... ስለ ልጆቿ ... የልጅ ነገር ሲነሳም አሌክሳንድራ በተራዋ ሚጋንን ልጅ የመውሰድ ፍላጐት እንዳላትና እንደሌላት ጠየቀቻት:: ለሕክምና ሙያዋ እንቅፋት እስካልሆነ መውሰዱን እንደማትጠላ ነገረቻት:: የሚያወሩት ሁሉ አብሮ እንዳደገ እህትማማች እንጂ ለሰላሳ ዓመት ያህል የተለያየ ሕይወት እንደመሩ ሁለት የተለያዩ ሴቶች አልነበረም::

ሂላሪም በእህቶቿ ውይይት መሐል ጣልቃ ገብታ "እኔስ ልጅ የሚባል ነገር ፈልጌ አላውቅም:: ልጅም ስለሌለኝ ቅሬታ አይሰማኝም" አለች:: ሂላሪ ውሸቷን ነበረ:: ያንን ፅንስ በማስወረዷ አሁንም ሆድ ሆዷን ይበላታል:: ቀጠል አድርጋም "በወጣትነቴ እንኳን ቢሆን መቼም ሌሎቹ ሲወልዱ ሳይ ልጓጓ እችላለሁ:: በአሁኑ ወቅት ግን የመውለጃ ጊዜዬ የተላለፈ ይመስለኛል" አለች::

"ዕድሜሽ ስንት ሆነና?" ስትል ሚጋን ሐኪሟ ግንባሯን ቋጠር አድርጋ ጠየቀቻት:: ሚጋን የራሷም ሆኖ የእህቶቿ ዕድሜ ይዘነጋት ነበረ::

"ሰላሳ ዘጠኝ" አለቻት ሂላሪ::

"በአሁኑ ጊዜ በተለይም በሰለጠነው ህብረተሰብ አካባቢ በዚህ ዕድሜ መውለድ የተለመደ ነው" አለችና ሚጋን ፈገግ እንደማለት ብላ "እኔ በምሰራበት መንደር ውስጥ ገና የአስራ ሁለትና የአስራ ሶስት ዓመት ልጃገረዶች ናቸው የሚወልዱት:: በእኛ በእህትማማቾቹ መካከል

ልዩነት እንዳለ ያህል በኮኔክቲከት ተራራ ላይ በሚኖሩ እናቶችና በኒውዮርክ ሴቶች መካከል አለ። አሌክሳንድራ አንድ ጊዜ በፓሪስ በሌላ ጊዜ በሪቪዬራ የበጋ የክረምት የፀደይ ... ማሳለፊያ ሕንፃ ቤቶችና ቪላዎች ታማርጣለች። እኔ ደግሞ የምኖረው ዓመቱን ሙሉ በአንዲት ጎጆ ውስጥ ነው። ሂላሪም ብትሆኚ የትልቅ ዜና አገልግሎት ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ ነሽ። ምን ያህል ዕድለኛ እንደሆንሽ ይሰማሻል?" አለች ሚጋን።

"አይ ዕድል! እንዲህ አድርጉም ዕድል የለ! ከዛሬ ሃያ አምስት ዓመት በፊት ባየሺኝ ኖሮ እንደዚህ ባላልሽም ነበረ" አለች ረጋ ባለ አንደበት።

"እስቲ የደረሰብሽን አንድ በአንድ አጫውቺኝ። ለእኛ ስትይ የተሰቃየሽውን ሁሉ ማወቅ ይኖርብናል" ስትል ሚጋን አሌክሳንድራንም ወክላ ተናገረች። ሂላሪ ያንን ታሪኳን ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው አንድ በአንድ አጫወተቻቸው። ያንን ረጅም የከፋና የበደል ታሪክ ስታወጋቸው ከሁለት ሰዓት በላይ ፈጀባት። በሆዷ የቋጠረችውን ሁሉ ለእህቶቿ በመናገሯ እፎይታ ተሰማት። ሁለቱም እህቶቿ ከግራና ከቀኝ አቅፈው እንባቸውን አብረዋት አፈሰሱ። እርሷ በአሳለፈችበት የሕይወት ውጣ ውረድ ውስጥ በዓይነ ሕሊናቸው አብረዋት ተጓዙ፣ ተመላለሱ። ወደየመኝታ ክፍላቸውም የሄዱት ሊነጋጋ ሲል ነበረ።

እስከ እኩለ ቀን ድረስ ሁሉም በእንቅልፍ ላይ ነበሩ። ቀድማ የተነሳችው አሌክሳንድራ የእህቶቿን መኝታ ክፍል በር በመቆርቆር ከቀሰቀሰቻቸው በኋላ ስልክ ለመደወል ወደ ምድር ቤቱ ወረደች። በቅድሚያ ወደ ኒውዮርክ ደውላ ከእናቷና ከልጆቿ ጋር ስትነጋገር ከግማሽ ሰዓት በላይ ቆየች። ከሁለት ቀናት በኋላም እንደምትመለስ ለእናቷ ገልፃላት ስልኩን ዘጋች። ቀጠለችናም ወደ ሄነሪ ለመደወል የስልኩን መነጋገሪያ አነሳች። ግን ፍርሃት ፍርሃት ስላላት መናገሪያውን መልሳ አስቀምጣ ወደ መኝታ ክፍሏ ሄደች። ገላዋን ተጣጥባ ወደ ሂላሪ ክፍል ስትገባ ሚጋንን እዛው አገኘቻት። እንደ ድሮውም እንደ ሕፃንነት ጊዜያቸው ሂላሪ የሚጋንን ፀጉር አበጥራ እየጐነጐነችላት ነበረ። ሚጋን ዛሬም የለበሰችው ጂንስ ሱሪና ሸሚዝ ሲሆን በዚያ ከፀጉሯ አበጣጠር ጋር ላያት የሕክምና ዶክተር ቀርቶ ገና አፍላ ኮረዳ ነበረ የምትመስለው። አሌክሳንድራም በእህቷ ሁኔታ ከልብ ነበረ የሳቀችባት። ግን ሂላሪም ሆነች አሌክሳንድራ በዚያን ቀን ሁሉም በልጃገረድ ዕድሜ አካባቢ ያሉ





ነበረ የሚመስለው። ከሁሉም ትከሻ ላይ የእርጅና ጫና የወረደ ይመስላል። ሂላሪ እህቶቿን አግኝታለች ... ቻፕማንንም የምትረሳው አልነበረችም። አሌክሳንድራ ስለ ሄነሪ ማሰቡንም ትታዋለች። ከእንግዲህ የሚወዷት ልጆቿ፣ እህቶቿ ሂሊና ሚጋን አሏት። እናቷም ማርጋሬት ሌላዋ መፅናኛዋ ነበረች። ሚጋን በሙያዋ ለማገልገል ሚስተር ፓተርሰንን እየተመላለሰች ለማየት ከምትለያቸው በስተቀር አፍ ለአፍ ገጥመው እንዳወሩ ነበር የዋሉት።

"ዛሬም እንደትናንቱ ስናወራ ካደርን ነገ መነሳታችንንም እንጃ" ስትል ሂላሪ እህቶቿን እያየች ፈገግ አለች።

አሌክሳንድራ ግን ፊቷ ቅዝዝ እያለ "ነገ ወደኒውዮርክ ልትመለሺ ነው? አይደለም እንዴ ሂሊ?" ስትል ጠየቀቻት።

"አዎን! ሰኞ ጠዋት ስብሰባ ስለሚኖርብኝ ቢያንስ ማታ ገብቼ ማደር አለብኝ። የአንቺ ዕቅድ እንዴት ነበረ?" አለቻት።

"እኔ እንኳን እስከ ሰኞ ለመቆየት ፈልጌ ነበረ። አንቺ ነገ የምትሄጂ ከሆነ ግን አብሬሽ መሄዱን እመርጣለሁ። በተጨማሪም ልጆቼም እናቴም ሊናፍቁኝ ይችላሉ"

"በጣም ጥሩ! በእኔ መኪና ልንሄድ እንችላለን። ከተቻለም ከእናትሽና ከሕፃናቱ ጋር አብረን እራት ለመብላት ለመድረስ እንሞክራለን።"

"ምን ያህል ደስ ይለኝ መሰለሽ ሂሊ! ኒውዮርክ ውስጥ ለአንድ ሳምንት እሰነብታለሁ። ስለዚህ በየቀኑ ልንገናኝ እንችላለን" አለችና ባሏን እንደማስታወስ ብላ "ከእንግዲህ ሄነሪ ፈታኝም አልፈታኝም ጉዳዬ አይደለም። እንዳውም በቅርቡ ፓሪስ ድረስ መጥተሽ እንደምትጎበኚን እርግጠኛ ነኝ" አለች አሌክሳንድራ።

"እትጠራጠሪ" አለችና በመሳቅ ላይ እንዳለች ሚጋን ሚስተር ፓተርሰንን አይታ ወደ ክፍሉ ውስጥ ገባች።

"ከአሁኑ ምን ተንኮል እየሸረባችሁ ነው?" ስትል ሚጋን እህቶቿን ተራ በተራ በፈገግታ እያየች ጠየቀቻቸው።

"ኒውዮርክ ውስጥ ለጥቂት ቀናት ያህል ስንዘንጥ ለመክረም ዕቅድ እያወጣን ነው:: እና ትንሿ ሚጋን ከእኔ ጋር አብራ እንድትከርም በዚህ አጋጣሚ ልመናዬን አቀርብላታለሁ" አለች ሂላሪ እየሳቀች::

"ለምን? ከእኔ ጋር ነው አብራ የምትቆየው" ስትል አሌክሳንድራ ክርክር ከፈተች:: የሚጋን ውሳኔ ግን ከእህቶቿ ፍላጐት ለየት ያለ ነበረ::

"ከሁለታችሁም ጋር ተራ በተራ አድር ነበረ:: ግን የሚስተር ፓተርሰን ቁርጣቸውን እስካላየሁ ድረስ ትቻቸው ለመሄድ አልችልም:: ከሙያ ግዴታዬም ሌላ የሕሲና ዕረፍት ስለማይሰጠኝ ለጥቂት ቀናት እዚሁ መቆየት ይኖርብኛል:: ከዚያም ወደ ኒውዮርክ እመጣለሁ" አለች ሚጋን::

በዚያን ምሽት ራት በመብላት ላይ እንዳሉ ጭውውታቸው ከአንዱ አርዕስት ወደ ሌላ ሲንከባለል ቆይቶ በመጨረሻም ላይ የጆን ቻፕማን ወሬ ተነሳ::

"ከቢሮዬ ዘው ብሎ ገብቶ ከፊት ለፊቴ ሲቆም አደጋ ሲጥልብኝ የመጣ ሰው መስሎኝ ደንግጬ ነበረ" አለችና ሂላሪ እህቶቿን አሳቀቻቸው::

"እኔ ግን ለመጀመሪያ ጊዜ ሳየው በመልከ መልካም ቁመናው በመማረኬ የሚወደድ እንጂ የሚፈራ ሰው ሆኖ አላገኘሁትም" ስትል አሌክሳንድራ በእህቷ አነጋገር ተሳለቀች::

ሚጋንም ቀጠል አድርጋ "እኔም እንደ አሌክሳንድራ የሚፈቀር እንጂ የሚጠላ ሆኖ አልታየኝም" ስትል በተራዋ አሾፈች:: ሶስቱም ውስጥ ውስጡን ተነቃቅተው ነበርና እንደ አፍላ ልጃገረዶች ሲሳሳቁ ቆይተው 'ቻፕማን ሚስት ይኖረው ይሆን?' በሚለው ጥያቄ ላይ ውይይታቸውን ቀጠሉ::

"ሚስቱን ፈትቶ በወንደላጤነት እንደሚኖር የነገረኝ ይመስለኛል" አለችና አሌክሳንድራ ወደ ሂላሪ ቆረጥ አድርጋ አየች::

ሂላሪ ምንም እንደማታውቅና ግዴለሽ በመምሰል ትከሻዋን ሰበቅ በማድረግ ነገሩን እንደቀላል ለማለፍ ብትሞክርም እህቶቿ ከፊቷ ላይ ያነበቡት ስሜት ነበረ:: ስላወቁባት ደግሞ ሂላሪ ቅንጣት ያህል





አላፈረችም:: ከእንግዲህ ምስጢረኞቿ የሚሆኑት እክሲንና ሚጋንን አግኝታለች:: በማዕበል ሲታወክ በሞገድ ሲንገላታ የከረመ መርከብ ከወደብ ሲደርስ የሚለማው እፎይታ ያህል በሐዘን የደማው የሂላሪ ልብ በሥቃይ የቆሰለው የሂላሪ መንፈስ ከእንግዲህ የሚፅናናበት ምሽግ ባለቤት ሆኗል::

## ምዕራፍ ሃያ ዘጠኝ

በማግስቱ ከበረንዳ ተቀመጠው ለረጅም ሰዓታት ሲያወሩ ቆዩ:: ለወደፊቱ መቼና የት እንደሚገናኙ በየስንት ቀናት ደብዳቤ እንደሚሰዋወጡና ስልክ እንደሚደዋወሉ ተወያይተው እንደጨረሱ የሂላሪና የአሌክሳንድራ መሄጃ ጊዜ ቀረበ:: ሚጋንን ሁለቱም እህቶቿ ተራ በተራ አንገቷን አቅፈው እያሰቀሱ ከሳሟት በኋላ ወደ መኪናቸው ገቡ:: እርሷም መኪናውን ከዓይኗ እስከሰወር ድረስ እጇን ስታውለበልብ ቆይታ አንገቷን እንዳቀረቀረች ወደ ቤት ተመለሰች:: እርግጥ እህቶቿን ከጥቂት ቀናት በኋላ ኒውዮርክ ውስጥ ታገኛቸዋለች:: ያም ሆኖ ግን የትንሿ የሚጋን ልብ ከእህቶቿ ጋር አብሮ ተጓዘ::

በዚያን ጊዜ ሚስተር ፖተርሰን በከባድ እንቅልፍ ላይ ነው:: ሚጋንም የማደንዘዣ መርፌ የወጋችው ሂላሪና አሌክሳንድራ ከተሰናበቱት በኋላ ነበረ:: አንድ ዓይኑን ብቻ ገርበብ አድርጎ ከፊተና እህትማማቾቹን በእይታ ለመሰናበት ከአንዷ ወደ ሌላዋ አንገዋለለው:: ፈገግ ለማለትም ሞከረ:: ሂላሪ ለረጅም ጊዜ አቀርቅራ ስታየው ቆየችና የሚተናነቃትን እንባ በመቆጣጠር ከእህቷ ቀድማ ከቤት በመውጣት ወደ መኪናው ሄደች:: አሌክሳንድራም ወዲያውኑ ተከትላት ከመኪናው ገብታ ከአጠገቧ ተቀመጠች::

በጉዞም ላይ እንዳሉ "ውሉ የሚያድር ይመስልሻል?" ስትል አሌክሳንድራ ሂላሪን ጠየቀቻት::

"ማን ያውቃል:: ግን እንደዚህ ከሚሰቃይ ቶሎ ቢገላገል የሚሻል ይመስለኛል" አለች ሂላሪ:: በፓተርሰን ላይ ያላት ያ ሁሉ ጉሜ ከመቅፅበት ተወግዷል ባይባልም በሁኔታው አዝናለታለች:: በባዶም ቤት ብቻውን ከሚሆን ሚጋን ልታስታምመው በመቅረቷም ውሳኔዋን በሆዷ ደግፋዋለች::





ኒውዮርክ የደረሱት ከራት ሰዓት በፊት ነበረ:: መኪናዋም ከአሌክሳንድራ ሆቴል ፊት ለፊት እንደቆመ ሂላሪ እህቷን በውጪ ተሰናብታት ወደ መኖሪያ ቤቷ በሄደች ፍላጐቷ ነበረ:: የሰጠችውም ምክንያት የአሰባበሷን መጐሳቆል ይሁን እንጂ ሂላሪ ግን የፈራችው ሌላ ነገር ነው:: የአሌክሳንድራ ልጆች አክስታቸው መሆኔን ሲያውቁ ያልወደዱኝስ እንደሆን? የሚል ሥነ ልቦናዊ ጥርጣሬ አደረባት:: ማለትም በአባታቸው በኩል የመሳፍንት ዘሮች በመሆናቸው ሊንቁኝ ይችላሉ ስትል ፍርሃት ገብቷታል:: አሌክሳንድራ ግን የሂላሪን እጅ ጐትታ ካወረደቻት በኋላ እንደተያያዙ ወደ ተከራየችው ልዩ የሆቴል ክፍል አመሩ:: በሩንም ከፈት ከማድረጓ አክሴል ከመቀመጫዋ ተነስታ በመወረወር ከእናቷ አንገት ላይ ተጠመጠመች:: ሂላሪም ባየችው ክው ብላ ደንግጣ ቆመች:: እንባዋ ተሰል ብሎ ፈሰሰ::

አሌክሳንድራ የልጇን ፀጉር እያሻሸች ወደ ሂላሪ አዞረቻትና "ማንን መሰለሽ ዛሬ ይገፍልሽ የመጣሁት የእኔ ፍቅር? ይቺ የምታያት ሴት ማንስ መሰሰችሽ?" አለቻት:: በዚያን ጊዜ አክሴል በአረንጓዴ ዓይኖቿ ያቺን ረጅም ጥቁር ፀጉር ያላትንና ቁመና መልካም ሴት ስታያት ቆይታ "ማን ናት እርስዋ?" አለች::

"እህቴ ናት" ብላ አሌክሳንድራም ታሰቅስ ጀመረ:: ልጇንም ከተጠመጠመችበት አንገቷ ላይ አውርዳ በአንድ እጇ የሂላሪን እጅ ያዘችና "ከተሰያየን ብዙ ጊዜ ሆኖን ነበረ:: ዛሬ ግን ተገናኘንና እናንተን ላሳያት አመጣኋት:: ሌላም ሚጋን የምትባል ትንሽ እህት አለችኝ:: እርሷም ሰሞኑን ትመጣለች:: ይቺም አክስትሽ ሂላሪ ናት" ስትላት አክሴል መጀመሪያ እንደ ማመንታት አለች:: ሂላሪ እጆቿን እንደ ዘረጋችላት ስታይ ግን ሮጣ ከእቅፏ ገባች:: ሂላሪም ከአንገቷ ሥር አቅፋ "አክሲ ልጅ... የምወዳት የእህቴ ልጅ..." ስትል የደስታ እንባ አፈሰሰች::

ቀጥላም መጥታ የሳመቻት ማሪ ነበረች:: ማሪ ትንሽም ቢሆን ነፍስ በማወቋ ለአክስቷ ተገቢውን ክብር በመስጠት ነበረ የተዋወቀቻት:: ከሂላሪ የምትመሳሰልበት በመልክና በቁመናዋ ብቻ ሳይሆን በፀባይም ጭምር ነበረ:: ከአሌክሳንድራም ይልቅ ከሂላሪ ማሕፀን ነው የወጣችው ማለቱ ይቀላል:: ለአክስቷ ፍቅሯን የገለፀችበት መንገድ ቢኖር እጇን እንደያዘች ከጐኗ ባለመለየቷ ነው::

ከማርጋሬት ጋር ሁሉ ሲተዋወቁ ማሪና ሂላሪ እጅ ለእጅ እንደተያያዙ ነው:: ማርጋሬትም በበኩሏ ሂላሪን ያየቻት በአሌክሳንድራ ዓይን እንደ እናት ነበረ:: አቅፋ ከሳመቻት በኋላ "ደህና ነሽ ሂላሪ? እህትማማቾቹ ለመገናኘት በመብቃታችሁ ምን ያህል ደስታ የተሰማኝ ይመስልሻል?" ስትል ከልብ የመነጨውን ስሜቷን እንባዋን በማፍሰስ ጭምር አሳየች::

ከዚያም ከሶፋ ላይ አረፍ እንዳሉ ትንሿ አክሴል ከእናቷ ጭን ላይ ማሪ ደግሞ ከሂላሪ ጐን ተቀመጡ:: "ለምንድነው እስከዛሬ አክስታችንን ሳታሳይን የቆየሽው?" ስትል ጥያቄ ያቀረበችው ግዴለሿ አክሴል ነበረች::

"እይው አክሴል እንደ እናንተ ትንንሽ ልጆች በነበርንበት ወቅት ብዙ የሚያሳዝን ነገር ደርሶብን ነበረ:: በመሆኑም እህትማማቾቹ ለመለያየት በቃን:: በተለይ ሂላሪ እንደ እኔ ዕድለኛ ባለመሆኗ የሥቃይ ዓመታትን አሳልፋለች:: ያ ሁሉ ሆኖ ዛሬ ለመገናኘት በቃን" ስትል አሌክሳንድራ መለሰችላት::

"አይ" ስትል ከንፈሯን በመምጠጥ ፀፀቷን ማሪ ስትገልፅ አክሴል ግን የልጅ ነገር ነውና ወዲያውኑ ወደ ሌላ ነጥብ ዘላ "መቼም እማዬ ትናንትና እንዴት ደስ ብሎን ዋልን መሰለሽ? አያታችን ያላስጐበኘችን ቦታ የለም:: በመጨረሻም ላይ ሲኒማ ይዛን ገብታ ማታ ላይ ነው ወደ ሆቴላችን የተመለስነው" ስትል የመሰላትን ትልቅ ዜና አበሰረች:: አዋቂዎቹ ይሳሳቁበት እንጂ ታላቅ እህቷ ማሪ ግን በወሬኛነቷ ታዝባት በዓይኗ የቁጣ መልዕክት አስተላልፋላት ነበረ::

እራት ከተበላና ለማወራረጃም ሻምፖኝ ቀርቦ በመጨዋወት ላይ እንዳሉ የሕፃናቱ የመኝታ ጊዜ በመድረሱ አሌክሳንድራ ልታስተኛ ቸው ሄደች:: ሂላሪም በዚህ አጋጣሚ ማርጋሬትን ብቻዋን በማግኘቷ ገብቷት ስለነበረው ሥጋት አነሳችባት::

"በጣም እንደምትወድሽ ደጋግማ ነው የነገረችኝ:: ስለ ክምት ዲቦርንም አንስታ ብዙ አጫውታኛለች:: እንደ ወላጆቿ የምትቆጥረው እናንተን ብቻ ለመሆኑ ጥርጣሬ አይግባሽ" ስትል ሂላሪ አረጋጋቻት::





ማርጋሬት ያሂላሪን እጅ በፍቅር ጭብጥ አድርጋ ያዘችና "ስለ ባሏ ስለ ሄነሪ ያነሳችብሽ ነገር ነበር?" ስትል ጠየቀቻት:: ሂላሪ ራሷን ጐንበስ በማድረግ "አዎን" አለቻት::

"ይኸውልሽ ከመጣን ጀምሮ አንድ ጊዜ እንኳን ስልክ አልደወለም:: ቢያንስ ቢያንስ ልጆቹን ማነጋገር ነበረበት:: እና ጨክኖ ለመቁረጡ ይህ ብቻውን አሳማኝ ማስረጃ ሆኖ ነው ያገኘሁት:: አሌክሳንድራን አትንገሪው ስል መክሬአት ነበረ:: ግን እምቢ አለችኝ" አለች ማርጋሬት::

"እዚህስ ላይ ደግ አደረገች" ስትል ሂላሪ መለሰች:: ቀጠለችናም "እንደ እኔ አሌክሳንድራ የተሸፋፈነ ኑሮ ትኑር አልልም:: መወደድ ያለባት በራስነቷ ነው እንጂ በወላጆቿ ማንነት መሆን የለበትም:: ስለዚህ ሐቁን ተረድቶ ራስን ማስተካከል ይኖርበታል ነው የምለው" ስትል አስተያየቷን ሰጠች::

ማርጋሬት የቅሬታ ፈገግታ በማሳየት "አይ ሂላሪ! ሄነሪን ብታውቂው ኖሮ እንዲህ ባላልሽም ነበረ" አለቻት::

ያን ጊዜ አሌክሳንድራ በመመለሷ የተጀመረው ውይይት ሳያልቅ ተቋረጠ:: አሌክሳንድራ ሕፃናቱን እንዲተኙ ብታደርጋቸውም ከአክስታቸው ጋር ሲጫወቱ ለማምሸት ፍላጐት ነበራቸው::

"ነገ ከስብሰባ እንደወጣሽ እንደምትመጪ ነግሬ ነው ልጆቹን አባብዬ ያስተኛኋቸው" አለቻት አሌክሳንድራ ሂላሪን::

"በቀጥታ እንጂ ከዚያ በኋላ ቀኑን ሙሉ አብረን ነው የምንውለው:: እንዳውም ከሰዓት በኋላ ቢሮዬን አንድ በአንድ ሳስጐበኛ ቸው ነው ዕቅዴ" ስትል ሂላሪ መለሰችላት:: ሂላሪ ከአሁኑ አክስት በመሆኗ ውስጥ ውስጡን የተሰማት ኩራት ሌላ ነበረ::

ከዚያም በማግስቱ ስለሚጐበኟቸው ሌሎች ተጨማሪ ሥፍራዎች ከተነጋገሩ በኋላ ሂላሪ ልትሰናበታቸው ተነሳች:: ከእህቷም፣ ከማርጋሬትም ጋር ተቃቅፈው በመሳሳም ተለያዩ:: "ደስ ያለሽ ይመስለኛ ል አክሲ ትክክል አይደለሁም?" ስትል ጠየቀቻት::

"በጣም ነው ደስ ያለኝ እማማ ሁለቱንም. እህቶቼን ለማግኘት በመብቃቴ በጣም ዕድለኛ ነኝ:: ከገመትኩት በላይ ነው ደስታ የተሰማኝ" አለችና ማሪጋሬትን አቅፋ "በዚህም ደስታዬ ወቅት ከእኔ ባለመለየትሽ ደስታዬን እጥፍ እጥፍ ያደርገዋል" አለች አሌክሳንድራ:: ከዚያም ከማርጋሬት መኝታ ክፍል ገብተው ባለፉት ሁለት ቀናት ከእህቶቿ ጋር ስላሳለፈችው ሕይወት አንድ በአንድ ስታጫውታት ቆየች::





# ምዕራፍ ሰላሳ

በማግስቱ ሂላሪ ምሳ የበላችው ከአሌክሳንድራና ከሕፃናቱ ጋር ነበረ:: ማርጋሬት የሆነ ምክንያት ፈጥራ ተለይታቸዋለች:: ይኸውም ናፍቆታቸውን እንደልባቸው እንዲወጡ በማሰቧ ነበረ:: ሂላሪ አሌክሳንድራንና ሕፃናቱን የምትመራውን የዜና አገልግሎት ድርጅት ቢሮዎች አንድ በአንድ አዘዋውራ አስጐበኘቻቸው:: ከዚያም በከተማው የሚገኙትን የተለያዩ መናፈሻ ሥፍራዎች፣ ዝነኛ የትያትር ቤቶች፣ የንግድ ድርጅቶችና... ወዘተ ስታሳያቸው ቆየች:: ለሕፃናቱ የተለያዩ አሻንጉሊቶች ስትገዛ ለእህቷ ደግሞ መታሰቢያ የሚሆን በሉል የተሰራ ያንገት ጌጥ አበረከተችላት:: በመጨረሻም ላይ ያሳየቻቸው ይኖሩበት የነበረውን የዱሮ መኖሪያ ቤታቸውን ነበረ:: ሂላሪና አሌክሳንድራም ወላጆቻቸውን አስታውሰው አንገት ለአንገት ተቃቅፈው ሲያለቅሱ ምክንያቱ ያልገባቸው ሕፃናት ልጆቻቸውም ሆኑ አላፊ አግዳሚው መንገደኛ እንደጉድ ያዩዋቸው ነበረ:: ለአሌክሳንድራም ሆነ ለሂላሪ የውቧ እናታቸው የሶላንጅ ትዝታ፣ የዝነኛው አባታቸው የምክር ሰቀቀን ያንን መኖሪያ ቤት ሲያዩ ሳይታወቅ ተቀስቅሶባቸው ለተመልካች እንቆቅልሽ የሆነውን ለቅሷቸውን የገቱት "እረ ሰው ይታዘባችኋል" ብላ ትልቋ ሕፃን ማሪ በነገር ስትገጫቸው ነበረ::

ሂላሪ፣ ማሪ፣ አሌክሳንድራና አክሴል እጅ ለእጅ እንደተያያዙ መንገዱን አቋርጠው ወደ ፒየር ሆቴል አመሩ:: ራት አብረው በልተው ሲጨዋወቱ ካመሹ በኋላ ሂላሪ ወደ መኖሪያ ቤቷ ለመመለስ ተነሳች:: በበነጋታውም ሥራ ቢበዛባት እንኳን ለምሳ ሰዓት እንደማትቀር ከእህቷ ጋር ተቀጣጥረው ተለያዩ::

ገና ከመኖሪያ ቤቷ ሳሎን ከመግባቷ የስልክ ድምፅ አንቃጨለ:: ስልክ ደዋዩም ጆን ቻፕማን ነበረ:: ሚጋን ከሰዓት በኋላ ባለው ጊዜ ውስጥ ሁሉ እህቶቿን በስልክ ለማግኘት ሳይሳካላት ይቀራል:: በዚያን ጊዜም ነው ጆን ቻፕማንን ማነጋገሩን እንደ አማራጭ የተጠቀመችበት::

የሚስተር ፓተርሰን የቀብር ሥነ ሥርዓት ከሁለት ቀናት በኋላ በኮኔክቲከት እንደሚፈፀም ነግራዋለች::

"የምትሄጂ ከሆነ በእኔ መኪና አብረን እንድንሄድ ላሳስብሽ ነበረ" አላት ቻፕማን:: ሂላሪ ጥቂት እንዲታገሳት ጠይቃው ከሁለት ቀናት በኋላ ስላላት ቀጠሮ ማስታወሻ ደብተሯን አገላብጣ አየች:: የማያንቀሳቅስ ከባድ ጉዳይ ይጠብቃት ስለነበረ ምክንያቶቹን ጭምር በመግለፅ ለመሄድ እንደማትችል አስታውቃው "አሌክሳንድራ ግን በቀብሩ ላይ የማትገኝበት ምክንያት ስለማይኖር ደውዬ እነግራትና አብራችሁ እንድትሄዱ አደርጋለሁ" አለችው::

"ችግርሽ ይገባኛል:: ለምኑን ደግሞ ከማታምኚው ቢሮሽ ተለይተሽ ነው የከረምሺው:: ለመሆኑ አሌክሳንድራ እንዴት ናት? ልጆቹስ?" አላት::

"ሁሉም ደህና ናቸው:: ገና አሁን ነው ከነርሱ ተለይቼ ወደ ቤት የተመለስኩት:: ቀኑን ሙሉ አብረን ነው የዋልነው"

"ደስ የሚል ጊዜ አሳልፈሻል?"

"በጣም እንጂ ጆን በሕይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ደስታ የተሰማኝ እህቶቼን ካገኘሁበት ቀን ጀምሮ ነው:: በዚህም አጋጣሚ ስለዋልክልን ውለታ በድጋሚ አመሰግናለሁ"

"በደረቁ ምስጋና የለም እመቤት፤ አንቺ ባትጋብዥኝም ከኮኔክ ቲከት እንደ ተመለስኩ ቢያንስ እራት አብረን መብላት ይኖርብናል" አለና ሳቅ ካለ በኋላ "የቱን ያህል መሰለሽ የናፈቅኩሽ ሂሊ ..." አላት በዚያ በገርማማ ድምፁ:: ሂላሪ ልትቆጣጠረው የማትችለው ስሜት ሰውነቷን ወረራት:: ለምኑን በፈንጠዝያ በከረመው የሂላሪ ልብ ውስጥ የቻፕማን ፍቅር ሰተት ብሎ ገብቶበታል::

"አንድም ጊዜ ቢሆን ስለ አንቺ ከማሰብ አላቋረጥኩም" አለ ቻፕማን ቀጠል በማድረግ:: ፊት ለፊት ደፍሮ የማይናገራትን ቃላት ሁሉ አሁን በስልክ ውስጥ አፈሰሳቸው::

"ለምን?" አለችው ሂላሪ የልቧ ምት ትርታ እየጨመረ::

"በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ እንደ አካሌ ቁራጭ አድርጌ ነው የምቆጥርሽ:: ንክ ነህ አትበይኝ እንጂ ..."





"በመጠኑ" ስትል አቋርጣው ሳቀችና "ግን ያንተ ንክነት የሚያስጠላ ዓይነት አይደለም:: ለሥራህ ካለህ ፍቅር የተነሳ የጉሻሸመህ ይመስለኛል" አለችው::

"አዎን ለመጀመሪያ ጊዜ እንደዚያ ሲያደርገኝ ነው:: እና ሂሊ መቼ ነው ለራት የምንወጣው? የፊታችን ሐሙስ ብንገናኝ ምን ይመስልሻል?"

"ይሁና" አለች ሂላሪ የሴት ወጉ እንዳይቀርባት በመግደርደር:: እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ምንም ዓይነት ቀጠሮ ቢኖራት እንኳን ለቻፕማን ስትል ወዲያው እንደምትሰርዘው ይታወቃት ነበረ:: "ቢሮዬን ታውቀው የለም?" አለችና አሁንም ሳቀችበት::

"አስራ ሁለት ሰዓት ከሩብ ላይ ከበራፉ እጠብቅሻለሁ:: ከዚያ ንቅንቅ እንደማልል እንድታውቂው!" አለ ብዙ እንዳታስጠብቀው በመስጋት::

"ግዴለም አታስብ! ብቻ በደህና ተመለስ" ብላው ተሳሳቁ:: ቻፕማን የሚስተር ፓተርሰን ውርስ ጉዳይ ባይኖርበትና ውርሱም እነ ሂላሪን የሚመለከት ባይሆን ኖሮ ወደ ኮኔክቲከት ባልሄደም ነበረ::

## ምዕራፍ ሰላሳ አንድ

❧

የሚስተር ፓተርሰን የቀብር ሥነ ሥርዓት እንደተፈፀመ ቻፕማን አሌክሳንድራና ሚጋን አብረው ወደ ኒውዮርክ ተመለሱ:: ሶስቱም እህትማማቾችና ቻፕማን በተገኙበት ለመጨረሻ ጊዜ በአንድነት ራት ሲበሉ አመሹ:: ሚጋን በሚስተር ፓተርሰን ሕመም የተነሳ ከተሰጣት የፈቃድ ቀናት ውጪ በመዘግየቷ እኩለ ሌሊት ላይ ወደ ኬንታኪ በአውሮፕላን መብረር ነበረባት:: ከማርጋሬትና ከአሌክሳንድራ ልጆች ጋር ብዙም የመጫወት ዕድል አይግጠማት እንጂ ተዋውቃቸዋለች::

ፓተርሰን በኑዛዜው ስለተወላቸው መኖሪያ ቤትና ሌሎችም ንብረቶች አንስተው መጫወታቸው አልቀረም:: ዘላቂ ከሆነ የመፍትሔ ሐሳብ ላይ እስቲደርሱም ማናቸውም በውርስ ያገኙትን ንብረት ቻፕማን በኃላፊነት እንዲያስተዳድርላቸው ማድረጉን መረጡ:: የሚቀጥለውንም የክረምት ጊዜ ሶስቱ እህትማማቾች በኮኔክቲከቱ ቤታቸው ለማሳለፍ ተስማሙ::

"እንዳውም እኮ በየዓመቱ በክረምት ወራት የማንገናኝበት ምክንያት አይኖርም:: ስለዚህ ይህንን ቋሚ ልምድ ልናደርገው ይገባል" ስትል ሐሳቡን ያመነጨችው አሌክሳንድራ ነበረች:: ሁለቱም እህቶቿ ስምምነታቸውን በፈገግታ ገለፁላት እንጂ በዚህ ዕቅድ ላይ ቅንጣትም ያህል ቅሬታ አልነበራቸውም::

"እኔ ግን የኬንታኪን ባሕላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች ይዤ ብመጣ ቅር አይላችሁም አይደለም?" አለች ሚጋን እህቶቿን::

"ደስ ያለሽን ነገር ሁሉ ለማምጣት ትችያለሽ" አለቻትና ሂላሪ ወደ ቻፕማን አየት አደረገች:: የሙዚቃ መሣሪያ ብቻ ሳይሆን ምናልባትም የምታፈቅረው ጉልማሳ ቢኖር ይዛ ለመምጣት መቻሏን ሂላሪ መጠቆሟ ነበረ:: ሚጋን የምትሄድበት ጊዜ በመቃረቡ አውሮፕላን ማረፊያ ድረስ አብረዋት ሄዱ:: ሚጋን ሂላሪን በቅርቡ እንደምታገኛት





ስለምታውቅ ረዘም ላለ ጊዜ አቅፋ ስትስማትና ፍቅሯንም ስትገልፅ የቆየችው ለአሌክሳንድራ ነበረ:: ሚጋንን እህቶቿ በእንባ ከሸኟት በኋላ ወደ ከተማው ተመለሱ:: ሁሉም ተዳክመው ስለነበረ እንቅልፍ አምሯቸዋል:: በቻፕማን የምትነዳው መኪና በቅድሚያ የምታልፈው በአሌክሳንድራ ሆቴል በኩል ስለነበረ እርሷን አውርደው ወደ ሂላሪ ቤት አመሩ:: አሌክሳንድራም ከሆቴሉ ውስጥ እንደገባች ቀጥታ ወደ መኝታ ክፍሏ ሄደች::

የማርጋሬትና የሕፃናቱ የመኝታ ክፍሎች መብራቶች ጠፍተዋል:: የርሷ ግን ይበራ ነበረ:: 'ማን ሊያበራው ይችላል?' ስትል ግራ እንደመጋባት ብሏት ከበራፉ አጠገብ ቆማ አመነታች:: ልትከፍተው ስትሞክር ደግሞ ከውስጥ ተቆልፏል:: ወዲያውንም የጫማ ኮቴ ሰማች:: በራፉንም በከፈተላት ባሏ ላይ ዓይኖቿ እንደተሰኩ ቀሩ:: ከፓሪስ የደረሰው ከጥቂት ሰዓታት በፊት ነበረ:: ማርጋሬትም እራት ከጋበዘችውና ከአንገት በላይ ስታዋራው ከቆየች በኋላ ከአሌክሳንድራ መኝታ ክፍል አስገብታው ተኝታለች:: የሄነሪ ቆፍጣናነት አሁንም ያው የቀድሞው ነው:: የመጣበት ምክንያት ግልፅ ያልሆነላት አሌክሳንድራ በድንጋጤ ክች ብላ ስታየው ብትቆይም እርሱ ግን ስላልታሰበው ጉብኝቱ አንዳችም ማብራሪያ የሚሰጥ ዓይነት አልነበረም::

"ሄነሪ?" አለች አሌክሳንድራ የሚታያት ምትሐት እንጂ እውነተኛው ባሏ መሆኑን በመጠራጠር::

" ምነው? ሌላ የምትጠብቂው ሰው ነበረ ማለት ነው?" አላት:: እርግጥ የአሁኑ አነጋገሩ በውንጀላ መልክ ሳይሆን ፈገግታም ታክሎበት ነበረ:: "ሌላ የምትጠብቂው ሰው እንደማይኖር ተሰፋ አለኝ:: ለመሆኑ ልጆቻችንስ ደህና ናቸው?" አላት አሁንም ፈዛ የምትመለከተውን አሌክሳንድራን::

"በጣም ደህና ናቸው:: ሁላችንም ደስ ብሎን ነው የከረምነው"

"እናትሽም የነገረችኝ ይህንኑ ነበረ:: ከፓሪስ እዚህ እንደደረስኩ ተቀብላ አስተናገደችኝ"

ይህ የዳር ዳርታ አነጋገር ለአሌክሳንድራ አልጣማትም:: ለምን እንደመጣ ቁርጡን ማወቅ አለባት:: ለጥል ወይንስ ለፍቅር? ምንስ ብሎ ሊያስፈራራት ይሆን? የሚገርመው ግን የዱሮ ፍርሃቷ ሁሉ ዛሬ

ገሸሽ ብሎላት ነበረ። የፈለገውን ነገር ቢያመጣ ጉዳይዋ አልነበረም። ወደ አልጋው ተመልሶ ሲቀመጥ ሁሉ ከቆመችበት ንቅንቅ ሳትል በልበ ሙሉነት አየችው። ሄነሪ ከፊት ለፊቱ ከነበረው የሻምፓኝ ጠርሙስ ሁለት ብርጭቆዎች ሞላና አንዱን አንስቶ « የሚያስፈልግሽ ከሆነ?» ሲል ሊሰጣት እጁን ዘረጋ።

አሌክሳንድራ ግን ራሷን ቊምር በማወዛወዝ "አመሰግናለሁ ለመጠጣት አልፈልግም። ይልቅስ ለምን እንደመጣህ ብትነግረኝ?" አለችው ጠጠር ባለ አነጋገር።

"አንቺን ለማየት ነዋ... ልጆቹንም..." አለ ራሱን የበወዘውንና ፀጥታ የነሳውን ነገር አፍረጥርጦ መናገሩ እየተሳነው። "መወያየት ያለብን መስሎኝ ነበረ" ሲልም ዓይኖቹን በማስለምለም አከለበት።

" ስልክ ልትደውልልኝ ትችል ነበረ" ስትል አሌክሳንድራ የቀድሞ አስተያየቷን ባለመቀየር ተናገረች። ከፉ ነገር ከአፉ ወጥቶ ያስቀይመኛል የሚል ነው ሥጋቷ ሁሉ።

"በስልክ ባነጋግርሽ ይሻል ነበረ ማለት ነው?" አለና ሄነሪ በትካዜ አቀረቀረ። ያን ጊዜ አሌክሳንድራ ተጠግታ ልታቅፈው ልታፅናናው በልቧ ከጅላ ነበረ። ሆዷ ግን ፈራባት። አትቅረቢኝ ብሎ ቢያመናጭቃትስ? ውይይትስ ያለው መወያያ ርዕስ የትዳራቸው መፍረስ ከሆነስ? አስቀድማ ቁርጡን ማወቅ አሰባት።

"ለምን እንደመጣህ እኮ እስካሁን ግለፅ አላደረክልኝም» አለችው እንደገና ረገጥ ባለ አነጋገር።

ከተቀመጠበት ተነስቶ ብርጭቆውን ካስቀመጠ በኋላ ረጋ ብሎ በመራመድ ተጠጋት። "አንቺን ለማየት ነዋ አሌክሳንድራ የእኔ ፍቅር ... ምን ያህል እንደምወድሽ ማመኑ ያስቸግርሽ ይሆናል ... ግን የማንም ልጅ ብትሆኚ የምወድው አንቺን ብቻ ነው" አለና ጉንበስ ብሎ አዲሱን የፀጉር አሰራሯን እያየ "ከአሁኑ እንደ አሜሪካዊ መሆንም እየሞካከርሽ ነው" ብሎ ፈገግ አለ። የዛሬው አነጋገሩም ሆነ አድራጐቱ የአሌክሳንድራን ፍቅር የሚያቀጣጥለው አለበለዚያም እስከነአካቴው እንደሚያሽከረው ታውቆታልና ይጠነቀቅ ነበረ።





"እይው አሌክሳንድራ! መጀመሪያ ስለቤተሰቦችሽ ታሪክ ስትነግሪኝ... በተለይ ስለወላጆችሽ ... በጣም ነበረ የደነገጥኩት። እንደሚመስለኝ ደግሞ ያን ዓይነቱ ዜና ለጊዜውም ቢሆን ማንኛ ውንም ሰው ማስደንገጡ አይቀርም። ዛሬ ግን ኒውዮርክ ድረስ መምጣቴ ባለፈው ጥፋቴ መፀፀቴን ልገልፅልሽ ነው። ከእንግዲህ አንቺነትሽ ብቻ እንጂ የማን ልጅ መሆንሽ ለእኔ ክብደት አይኖረውም። እንደ ዱሮው በየምሽቱ እንግዶች እየጋበዝኩ አላስቸግርሽም። በየሆቴሉ በየትያትር ቤቱ ያለ ፍላጐትሽ ካልተከተልሺኝ ስል አላስገድድሽም። እኔ የአንቺን ማንነት አውቄ አሜን ብዬ በሰላም እንድትኖሪ የምመኘውን ያህል አንቺም የእኔን ማንነት በፀጋ እንድትቀበይው እለምንሻለሁ" አላት እንባው በዓኖቹ ቲፍ እያለ።

አሌክሳንድራ በመገረም ዝም ብላ ታየው ነበረ። ያ ከእንግዲህ ክልቡ አንቅሮ ጠልቶኛል ስትል ታስበው የነበረው ሰው አሁን ከፊት ለፊቷ ቆሞ የፍቅሩን ኑዛዜ እያፈሰሰላት ነው። "በጥቂት ቀናት ውስጥ ወደ ሀገራችን መመለስ አለብን። እስከዛው ድረስ ከአጠገብሽ አልለይም። የእኔ ፍቅር የእኔ አሌክሳንድራ" አለና ጐትቶ ከደረቱ ለጠፋት። በነገስታት ዝርያው ተመፃዳቂው ሄነሪ... ቆፍናናው፣ ኮስታራው ሄነሪ... አሌክሳንድራን ከደረቱ አቅፏት አለቀሰ። አሌክሳንድራ በፈገግታ የተወረረውን ባሏን ዓመሉን ሁሉ ችላ በደስታ ኖረዋል። ታፈቅረው የነበረው ባሏ ነው። ወልደዋል ከብደዋል። ከእንግዲህስ ከሄነሪ የተለየ ምን ሕይወት ሊኖራት?

በራፉን ቀስ ብሎ ዘጋና እጇን ይዞ ወደ አልጋው ወሰዳት። ቆይቶም ክንዱን ተንተርሳ እንደተኛች ቀና ብሎ አያት። አሌክሳንድራም የሰላም እንቅልፍ አሸልቧት ነበረ። ግንባሯን በክንፈሩ ዳሰስ በማድረግ ሳማትና እርሱም ተኛ። ወደ ኒውዮርክ በመምጣቱ በጣም ደስ ያሰው በዚያው ጊዜ ነበረ።

## ምዕራፍ ሰላሳ ሁለት

በኒውዮርክ ውስጥ ያሳለፉት የመጨረሻ ምሽት ድሎት ያልተጓደለውም ቢሆን በሌላ መልኩ ደግሞ ሐዘንና ትካዜ ማስከተሉ አልቀረም። እራት የበሉት በኮት ባስክ ሆቴል ሲሆን ሄነሪና አሌክሳንድራ ሕፃናቱንም ይዘዋቸው መጥተው ነበረ። ማርጋሬት ከሄነሪ ጋር ማምሸቱ ደስ ባይላትም በአሌክሳንድራ ጉትጎችነት ተገኝታለች። ሂላሪ ደግሞ ቀደም ሲል ከሌላ እንግዳ ጋር እንደምትመጣ ለእህቷ ገልፃላታለች። ስለ እንግዳው ማንነት ግን ሂላሪ አልነገረቻትም አሌክሳንድራም ለማወቅ ብትፈልግም ደፍራ አልጠየቀቻትም። ከሂላሪ ጋር የመጣው ሰው ጆን ቻፕማን መሆኑን ስታይ ግን አሌክሳንድራ ውስጥ ውስጡን ፈንጥዛ ነበረ። ቻፕማንን ወዳዋለች። አሁን ደግሞ የምታየው እንደ ታላቅ ወንድሟ ነበረ። መልከ መልካሙ ቻፕማን ለዚያ ላማረ ቁመናው የሚስማማ ጥቁር ሱፍ ለብሷል። ቁንኑ ሄነሪ እንኳን ያሳየው አክብሮት ለየት ያለ ነበረ። ረጋ ካለ አንደበቱ የሚሰነዘሩት ቃላት አእምሮ ብሩህነቱን ብቻ ሳይሆን ለመልካም አስተዳደጉም ምስክሮች ነበሩ። በዚያን ምሽት ሂላሪና ቻፕማን ይህ ጉደላቸው የማይባሉ ጥንድ ሆነው ነው የታዩት። ግብዣውም ሞቅ ያለ ነበረ። ሌላው ቀርቶ ሕፃናቱ እንኳን ሻምፓኝ እንዲጠጡ አባታቸው ፈቅዶላቸዋል። በዚሁ ሁኔታ እስከ ሌሊቱ እጋማሽ ድረስ ሲጫወቱ አምሽተው ተለያዩ። ሂላሪም ወደ ቀድሞው የብቸኝነት ዓለሟ አልተመለሰችም ዛሬም ሌሊቱን ያሳለፈችው ከቻፕማን ጋር ነበረ።

ወደ ፓሪስ ከሚበሩበት ሰዓት በፊት ሁሉም በአውሮፕላን ማረፊያው ተገናኙ። ትንሿ አክሴልና ማሪ አክስታቸው የገዛችላቸውን ትልልቅ አሻንጉሊቶች በየብብታቸው ታቅፈው ከፊት ለፊት ይሄዳሉ። ሄነሪ የሚስቱንና የማርጋሬትን ሥፍር ቁጥር የሌላቸው የልብስ ሻንጣዎች ለማሳፈር ከወዲያ ወዲህ ይላል። ሂላሪና አሌክሳንድራ ደግሞ አፍ ለአፍ ገጥመው በየደቂቃው ቆም እያሉ ያወራሉ። ሂላሪ ከትንሿ እህታቸው ከሚጋን ጋር ለገና ወደ ፓሪስ እንደሚመጡ





ለአሌክሳንድራ ቃል ገብታለች። ያም ሆኖ የአሁኑ መለያየት ለሁለቱም ጨንቋቸዋል።

ባለቤት ቆመው ሲያወሩ ማርጋሬት ሕፃናቱን ወደ አውሮፕላን ውስጥ በማስገባት ላይ መሆኗ ታያቸው። ሄነሪ ፈንጠር ብሎ ቆሞ ከነበረው ቻፕማን ጋር የመጨረሻ የስንብት ቃላት በመለዋወጥ ላይ ነበሩ። ሂላሪ እህቷን እቅፋ "አክሲ እንደ ድሮው ዛሬም ልትለይኝ ነው ..." እያለች ተንሰቅስቃ ታለቅስ ጀመረ።

"ፍርሃትና ጭንቀትሽ ይገባኛል ሂሊ.... ይገባኛል" ብላ አሌክሳንድራም ራሷን በእህቷ ትከሻ ላይ ዘንበል አድርጋ አለቀሰች። ሂላሪም ያንን ወርቃማ ፀጉሯን እያሻሸች "አክሲ ... እወድሻለሁ ... ምን ጊዜም እንደምወድሽ እንድታውቂ..." የሚሉትን እነኛን የሕፃንነት ዘመኗን መሰናበቻ ቃላት ሲቃ እየተናነቃት ተናገረች። "አይዞሽ ሂሊ ... አይዞሽ ... ብቻ ራስሽን እንደምትጠብቂ ቃል ግቢልኝ... እኔ ደግሞ በየዕለቱ ስልክ እየደወልኩ አነጋግርሻለሁ..." ሁለቱን እህትማማቾች ለማላቀቅ ከሄነሪም ይልቅ ወኔ የነበረው ቻፕማን ነበረ። ሂላሪን አቅፎ ወደኋላ ሲያስቀራት ሄነሪ ደግሞ የአሌክሳንድራን እጅ ይዞ በመንደረደር የአውሮፕላኑን መሰላል ወጣ። ገና ከመግባታቸው በሩ ተዘጋ።

የሂላሪ ዕንባ በጉንጮቿ ላይ ይወርዳል። ቻፕማን ከደረቱ እንዳቀፋት "በርቺ ሂላሪ ... አይዞሽ ከእንግዲህ ደግሞ እኔ አለሁልሽ" ሲላት ቀና ብላ በፈገግታ አየችው። የተናገረው ከልቡ መሆኑን አምናበታለች። ይበልጥም ወደ ሰውነቱ አስጠጋትና "የምትፈልጊው ሁሉ ከእንግዲህ ተሟልቶልሻል" አላት።

# እስካሁን የጭን ቁስል መፅሂፍን አላነበቡም?

**8ኛ ዕትም ላይ ደርሷል!!!**

**ሙሉ በሙሉ እውነተኛ ታሪክ**




*ስለ የጭን ቁስል መፅሀፍ ምርጥነት ያነበቡትን ሰዎች መጠየቅና 8ተኛ ዕትም መድረሱን ማየት ብቻ ይበቃዎታል!!*

*በየመፅሀፍት መደብሩ ያገኙታል*

**የጭን ቁስል መፅሀፍ እኔን አይመለከተኝም ብሎ ነገር የለም:: እርስዎንም የሚመለከት መፅሀፍ ነውና!**





# የቀን ጨለማ

**ሙሉ በሙሉ እውነተኛ ታሪክ**

## ሁሉም ሰው ሊያነበው የሚገባ ምርጥ መፅሀፍ

*ትርጉም*
*በተስፋሁን ምትኩ*
*(የዳቪንቺ ኮድ መፅሀፍ ተርጓሚ)*

*ስርትዕትና ድጎረ-ታሪክ*
*በተከሉ ጥላሁን*
*(የጭን ቁስል መፅሀፍ ፀሀፊ)*




የእውነት ስሜት የሚፈነቅል... እጅግ ልዩ መፅሀፍ የተባለለትን የቀን ጨለማ መፅሀፍ ያንብቡት:: ልብ ቀስቃሽና አስደማሚ፣ ግልፅና የሚጥም... ልብ ሰቅሎ የሚያነጉድ... በቀላሉ የማይረሳ ግሩም መፅሀፍ ተብሎ የተመሰከረለት እውነት መሆኑን ይረዱታል::

**አንዳንድ ጊዜ በህይወታችን ውስጥ ቀኑ ይጨልምብናል::**

*በየመፅሐፍት መደብሩ ያገኙታል*